እ.ኤ.አ. በ1945 ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የአማሪኛ መጽሐፍ ቅዱስ ለብዙ ዓመታት ሳይታተም መቆይቱንና ለኢትዮጵያ ሕዝብ በበቂ ሁኔታ አለመቀረቡን በመረዳታቸው የግል አዲስ ኪዳናቸው ዳግም እንዲታተም አበረከቱ።

በእጅ በብራና ላይ የተጻፈው የእርሳቸው አዲስ ኪዳን ወደ አሜሪካ ተልኮ በፎቶ ግራፍ ኮፒ ተደርጎ ታተመ። እ.ኤ.አ. በሰኔ ወር በ1946 ዓ.ም. ሕትመቱን በገንዘብ የደገፉና ያስፈጽሙት ዶ/ር ዶናልድ ባርንሃውስ የተባሉት አሜርካዊ ወደ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቤተመንግሥት በመሄድ ከታተመው 25,000 አዲስ ኪዳን ውስጥ የመጀመሪያውን አንድ ሺህ አዲስ ኪዳን ለግርማዊነታቸው አበርክተዋል።

በአሁኑ ወቅት ይህ አዲስ ኪዳን በቁጥር በጣም ጥቂት ብቻ እንደሚገኝ የሚታመን ሲሆን በዚህ ዌይብ ሳይት የሚያገኙት ይህንን አዲስ ኪዳን ነው።

በዚህ አዲስ ኪዳን ትርጉም ውስጥ አንድ ችግር ነበር። በራዕይ 22፡9 ላይ መልአኩ ለሐዋሪያው ዮሐንስ ‹‹እንድትሰግድለኝ እወቅ›› ይለዋል። ይህ ግን የአንድ ፊደል ግድፈት አለው። በ ‹‹ዳ›› ፊደል ቦታ ‹‹ድ›› ተጽፏል። መልአኩ መልዕክተኛ ብቻ በመሆኑ ለዮሐንስ እንዳይሰግድለት ነበር የነገረው። ይህ ደግሞ ከአውዱ በግልጽ ይታያል።

እ.ኤ.አ. በ1945 ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የአማሪኛ መጽሐፍ ቅዱስ ለብዙ ዓመታት ሳይታተም መቆይቱንና ለኢትዮጵያ ሕዝብ በበቂ ሁኔታ አለመቀረቡን በመረዳታቸው የግል አዲስ ኪዳናቸው ዳግም እንዲታተም አበረከቱ።

በእጅ በብራና ላይ የተጻፈው የእርሳቸው አዲስ ኪዳን ወደ አሜሪካ ተልኮ በፎቶ ግራፍ ኮፒ ተደርጎ ታተመ። እ.ኤ.አ. በሰኔ ወር በ1946 ዓ.ም. ሕትመቱን በገንዘብ የደገፉና ያስፈጸሙት ዶ/ር ዶናልድ ባርንሃውስ የተባሉት አሜርካዊ ወደ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቤተመንግሥት በመሄድ ከታተመው 25,000 አዲስ ኪዳን ውስጥ የመጀመሪያውን አንድ ሺህ አዲስ ኪዳን ለግርማዊነታቸው አበርክተዋል።

በአሁኑ ወቅት ይህ አዲስ ኪዳን በቁጥር በጣም ጥቂት ብቻ እንደሚገኝ የሚታመን ሲሆን በዚህ ዌይብ ሳይት የሚያገኙት ይህንን አዲስ ኪዳን ነው።

በዚህ አዲስ ኪዳን ትርጉም ውስጥ አንድ ችግር ነበር። በራዕይ 22፡9 ላይ መልአኩ ለሐዋሪያው ዮሐንስ ‹‹እንድትሰግድለኝ እወቅ›› ይለዋል። ይህ ግን የአንድ ፊደል ግድፈት አለው። በ ‹‹ዳ›› ፊደል ቦታ ‹‹ድ›› ተጽፏል። መልአኩ መልዕክተኛ ብቻ በመሆኑ ለዮሐንስ እንዳይሰግድለት ነበር የነገረው። ይህ ደግሞ ከአውዱ በግልጽ ይታያል።

15

አዲስ ፡ ኪዳን ።

በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡

ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡

መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ታተመ ።

፲፱፻፴፰ ዓ. ም.

MANUFACTURED IN THE UNITED STATES OF AMERICA
BY NATIONAL BIBLE PRESS, PHILADELPHIA

AMHARIC ALPHABET

ሀ	ሁ	ሂ	ሃ	ሄ	ህ	ሆ
ለ	ሉ	ሊ	ላ	ሌ	ል	ሎ
ሐ	ሑ	ሒ	ሓ	ሔ	ሕ	ሖ
መ	ሙ	ሚ	ማ	ሜ	ም	ሞ
ሠ	ሡ	ሢ	ሣ	ሤ	ሥ	ሦ
ረ	ሩ	ሪ	ራ	ሬ	ር	ሮ
ሰ	ሱ	ሲ	ሳ	ሴ	ስ	ሶ
ሸ	ሹ	ሺ	ሻ	ሼ	ሽ	ሾ
ቀ	ቁ	ቂ	ቃ	ቄ	ቅ	ቆ
በ	ቡ	ቢ	ባ	ቤ	ብ	ቦ
ተ	ቱ	ቲ	ታ	ቴ	ት	ቶ
ቸ	ቹ	ቺ	ቻ	ቼ	ች	ቾ
ኀ	ኁ	ኂ	ኃ	ኄ	ኅ	ኆ
ነ	ኑ	ኒ	ና	ኔ	ን	ኖ
ኘ	ኙ	ኚ	ኛ	ኜ	ኝ	ኞ
አ	ኡ	ኢ	ኣ	ኤ	እ	ኦ
ከ	ኩ	ኪ	ካ	ኬ	ክ	ኮ
ኸ	ኹ	ኺ	ኻ	ኼ	ኽ	ኾ
ወ	ዉ	ዊ	ዋ	ዌ	ው	ዎ
ዐ	ዑ	ዒ	ዓ	ዔ	ዕ	ዖ
ዘ	ዙ	ዚ	ዛ	ዜ	ዝ	ዞ

ዠ	ዡ	ዢ	ዣ	ዤ	ዥ	ዦ
የ	ዩ	ዪ	ያ	ዬ	ይ	ዮ
ደ	ዱ	ዲ	ዳ	ዴ	ድ	ዶ
ጀ	ጁ	ጂ	ጃ	ጄ	ጅ	ጆ
ገ	ጉ	ጊ	ጋ	ጌ	ግ	ጎ
ጠ	ጡ	ጢ	ጣ	ጤ	ጥ	ጦ
ጨ	ጩ	ጪ	ጫ	ጬ	ጭ	ጮ
ጸ	ጹ	ጺ	ጻ	ጼ	ጽ	ጾ
ጰ	ጱ	ጲ	ጳ	ጴ	ጵ	ጶ
ፀ	ፁ	ፂ	ፃ	ፄ	ፅ	ፆ
ፈ	ፉ	ፊ	ፋ	ፌ	ፍ	ፎ
ፐ	ፑ	ፒ	ፓ	ፔ	ፕ	ፖ

ቈ	ቊ	ቍ	ቋ	ቌ
ኰ	ኲ	ኵ	ኳ	ኴ
ኈ	ኊ	ኍ	ኋ	ኌ
ጐ	ጒ	ጕ	ጓ	ጔ

AMHARIC NUMERALS

፩	፪	፫	፬	፭	፮	፯	፰	፱	፲
1	2	3	4	5	6	7	8	9	10
፳	፴	፵	፶	፷	፸	፹	፺	፻	፲፻
20	30	40	50	60	70	80	90	100	1000

አዲስ፡ኪዳን።

ብስራት፡ማቴዎስ፡ሐዋርያ፡ለ
ሐዲ፡እምአሠርቱ፡ወክልኤቱ፡
ሐዋርያት፡ጸሎቱ፡ወበረከቱ፡
የሃሉ፡ምስለ፡ንጉሥነ፡መፍቀ
ሬ፡እግዚአብሔር፡ኃይለ፡ሥላ
ሴ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ስለ፡ጌታችን፡ትውልድ፡ቍጥር።
ስለ፡ፅንሰቱ። ስለ፡ዮሴፍ፡አሳ
ብ። ኢየሱስ፡ስለ፡ተባለበት፡ም
ክንያት።

፩ የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡የትውል
ዱ፡መጽሐፍ፡የዳዊት፡ልጅ፡የ
አብርሃም፡ልጅ። ሉቃ ፫፡፳፫፡፴

፪ ፳። አብርሃም፡ይስሐቅን፡ወለደ
ይስሐቅም፡ያዕቆብን፡ወለደ፡
ያዕቆብም፡ይሁዳንና፡ወንድ
ሞቹን፡ወለደ። ዘፍ ፳፭፡፳፮፡ም፳፱፡
፴፭፡ም፳፱፡፴፫፡ም፵፱፡፲።

፫ ይሁዳም፡ከትዕማር፡ፋሬስንና
ዛራን፡ወለደ፡ፋሬስም፡ኤስሮ
ምን፡ወለደ። ኤስሮምም፡አራ
ምን፡ወለደ። ዘፍ፡፴፰፡፳፱፡፴፱፡፲፰፡
ዜና፡፪፡፭፡፱።

፬ አራምም፡አሚናዳብን፡ወለ
ደ፡አሚናዳብም፡ነአሶንን፡ወለደ
ነአሶንም፡ሰልሞንን፡ወለደ። ፩ዜ

፭ ና፡፪፡፲። ሰልሞንም፡ከራኬብ፡
ቦዔዝን፡ወለደ፡ቦዔዝም፡ከሩ
ት፡ኢዮቤድን፡ወለደ፡ኢዮቤድ
ም፡እሴይን፡ወለደ። ሩት፡፬፡[illegible]

፮ እሴይም፡ንጉሥ፡ዳዊት[illegible]
ደ፡ንጉሥ፡ዳዊትም፡ከኦር[illegible]
ሚስት፡ሰሎሞንን፡ወለደ[illegible]

፯ ሙ፡፲፪፡፳፬። ሰሎሞንም፡[illegible]
ምን፡ወለደ፡ሮብዓምም፡አቢ
ያን፡ወለደ፡አቢያም፡አሳፍን፡ወ
ለደ፡፩ዜና፡፫፡፲።

፰ አሳፍም፡ኢዮሳፍጥን፡ወ[illegible]
ኢዮሳፍጥም፡ኢዮራም[illegible]
ደ፡ኢዮራምም፡ዖዝያን[illegible]
ደ። ፩ነገሥ፡፲፭፡፳፬፡፲፪፡፳፭[illegible]

፱ ና፡፫፡፲፩። ዖዝያንም፡ኢ[illegible]
ምን፡ወለደ፡ኢዮአታም[illegible]
ዝን፡ወለደ፡አካዝም፡[illegible]

፲ ስን፡ወለደ። ሕዝቅያስም፡[illegible]
ሴን፡ወለደ፡ምናሴም፡አ[illegible]
ወለደ፡አሞንም፡ኢዮስያስን፡

፲፩ ወለደ። ኢዮስያስም፡በባቢሎን
ምርኮ፡ጊዜ፡ኢኮንያንን፡[illegible]

፲፪ ድሞቹን፡ወለደ። ከባቢ[illegible]
ርኮም፡በኋላ፡ኢኮንያን፡[illegible]
ያልን፡ወለደ፡ሰላትያል[illegible]
ባቤልን፡ወለደ። ዕዝ፡፫፡[illegible]

፲፫ ዘሩባቤልም፡አብዩድ[illegible]
አብዩድም፡ኤልያቄም[illegible]
ደ፡ኤልያቄምም፡አዛር[illegible]

፲፬ አዛርም፡ሳዶቅን፡ወለደ፡ሳዶቅ ም፡አኪምን፡ወለደ፡አኪምም፡
፲፭ ኤልዩድን፡ወለደ፤ኤልዩድም፡ አልዓዛርን፡ወለደ፡አልዓዛርም፡ ማታንን፡ወለደ፡ማታንም፡ያዕ
፲፮ ቆብን፡ወለደ፤ያዕቆብም፡የማር ያምን፡እጮኛ፡ዮሴፍን፡ወለደ፡ክ ርስቶስ፡የተባለው፡ኢየሱስ፡ከእ ርስዋ፡የተወለደ፤ም፳፯፡፲፯፡፳፬
፲፯ ትውልድም፡ሁሉ፡ከአብርሃም፡ እስከ፡ዳዊት፡አሥራ፡አራት፡ትው ልድ፡ናቸው፨
፲፰ የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ልደት፡እንዲ ህ፡ነው፡እናቱ፡ማርያም፡ለዮ ሴፍ፡በታጨች፡ጊዜ፡ሳይገናኙ፡በ መንፈስ፡ቅዱስ፡ፀንሳ፡ተገኘች፤
፲፱ ሉቃ፡፩፡፴፭፨እጮኛዋ፡ዮሴፍ፡ ግን፡ጻድቅ፡ነበረ፡በሕዝብም፡ፊ
፳ ት፡ሊገልጻት፡አልወደደም፡ሰው ሮም፡ሊተዋት፡አሰበ፡እርሱ፡ግ ን፡ይህን፡ሲያስብ፡የእግዚአብሔ ር፡መልአክ፡በሕልም፡ታየውና፡እ ንዲህ፡ሲል፡የዳዊት፡ልጅ፡ዮሴፍ ሆይ፡ከእርስዋ፡የሚወለደው፡በ መንፈስ፡ቅዱስ፡ነውና፡እጮኛህ ን፡ማርያምን፡ለመውሰድ፡አትፍ
፳፩ ራ፡ሉቃ፡፲፰፨ልጅም፡ትወልዳለች ስሙንም፡ኢየሱስ፡ትለዋለህ፡ ወገኖቹን፡ከኃጢአታቸው፡ያድ ናቸዋልና፨ሉቃ፡፩፡፴፩፡፪፡፳፩፡፩
፳፪ የሐዋ፡፬፡፲፪፨ከእግዚአብሔር፡ በነቢይ፡የተባለው፡ይፈጸም፡ ዘንድ፡ይህ፡ሁሉ፡ሆነ፡እንዲህ፡ሲ ል፨ኢሳ፡፯፡፲፬፡፡
፳፫ እነሆ፡ድንግል፡ትፀንሳለች፡ልጅ ም፡ትወልዳለች፡ስሙንም፡አማ ኑኤል፡ይሉታል፡ትርጓሜውም፡ እግዚአብሔር፡ከኛ፡ጋራ፡ነው፨ ሉቃ፡፩፡፴፩፨
፳፬ ዮሴፍ፡ከእንቅልፉ፡ተነሥቶ፡ የእግዚአብሔር፡መልአክ፡እን ደዘዘው፡አደረገ፡እጮኛውንም፡
፳፭ ማርያምን፡ወሰደ፨የበኵር፡ልጅ ዋንም፡እስክትወልድ፡ድረስ፡አ ላወቃትም፡ስሙንም፡ኢየሱስ ብሎ፡አወጣለት፨ሉቃ፡፪፡፯፡ም፪

ምዕራፍ፡፪፡

ስለ፡ሰብአ፡ሰገል፡መምጣት፡ስለ፡ሄ ሮድስ፡መደንገጥ፤ስለ፡ሰብአ፡ሰገ ል፡መመለስ፨ስለ፡ጌታችን፡ወደ፡ ግብፅ፡ስደት፨ስለ፡ሕፃናት፡መ ታረድ፡፡ስለ፡ጌታችን፡ወደ፡ምድ ረ፡ገሊል፡መመለስ፨ስለ፡ጌታችን፡ ናዝራዊ፡መባል፨
፩ በንጉሡ፡በሄሮድስ፡ዘመን፡በይሁ ዳ፡ዕፃ፡በቤተልሔም፡ኢየሱስ፡በ ተወለደ፡ጊዜ፡እነሆ፡ሰብአ፡ሰገል ከምሥራቅ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም መጡ፨ሉቃ፡፩፡፯፨
፪ ኮከቡን፡በምሥራቅ፡አይተን፡እ ንሰግድለት፡ዘንድ፡መጥተናል ና፡የተወለደው፡የአይሁድ፡ንጉ

ሥ፡ወደቲ፡ነው፡እያሉ፨ዘኍ ፳

፫ ፬፡፲፯፨ንጉሡም፡ሄሮድስ፡በሰ‹
ማ፡ጊዜ፡ደነገጠ፡ኢየሩሳሌምም

፬ በመላዋ፡ከእርሱ፡ጋራ፨የካህና
ትንም፡የሕዝቡንም፡ጸሐፎች፡ሁ
ሉ፡ሰብስቦ፡ክርስቶስም፡የሚወ
ለደው፡በወዴት፡ነው፡ብሎ፡ ጠ

፭ የቃቸው፨እርሳቸውም፡አሉ
ት፡በይሁዳ፡ዕፃ፡በቤተ፡ልሔም፡
በነቢይ፡እንዲህ፡ተብሎ፡ተጽፏ
ልና፨ሚክ ፭፡፩፡ዮ ፯፡፵፪።

፮ አንቺም፡ቤተ፡ልሔም፡የይሁዳ፡
ምድር፡ካንቺ፡ሕዝቤን፡፳ ልን፡
የሚጠብቅ፡መስፍን፡ይወጣልና
ከይሁዳ፡አለቆች፡ሁሉ፡አታንስ‹
ምም፨፪ ሳሙ፡፭፡፪፡ሚክ ፭፡፩፡ዮ ፯

፯ ፵፪፨ከዚህ፡በኋላ፡ሄሮድስ፡ሰ
ብአ፡ሰገል፡በስውር፡ጠራቸው
የታያቸውንም፡የኮከቡን፡ዘመ

፰ ን፡ከእርሳቸው፡ተረዳ፨ወደ፡ቤተ
ልሔም፡ሰደዳቸው፡ሒዳችሁም
ስለ፡ተወለደው፡ሕፃን፡እጅግ፡መ
ርምሩ፡በገኛችሁትም፡ጊዜ፡ንገ
ሩኝ፡እኔም፡ደግሞ፡መጥቼ፡እሰ

፱ ግድለት፡ዘንድ፡አላቸው፨እርሳ
ቸውም፡ከንጉሡ፡ሰምተው፡ሔ
ዱ፡እነሆም፡በምሥራቅ፡ያዩት፡
ኮከብ፡ሕፃኑ፡ባለበት፡ላይ፡መጥ
ቶ፡እስኪቆም፡ድረስ፡ይመራቸው

፲ ነበር፨ኮከቡንም፡ባዩ፡ጊዜ፡ታላቅ

፲፩ ደስታ፡አደረጉ፨ወደ፡ቤተ፡ ልሔ
ምም፡በገቡ፡ጊዜ፡ሕፃኑን፡ከናቱ
ከማርያም፡ጋራ፡አገኙት፡ተደፍተ
ውም፡ሰገዱለት፡ሳጥናቸውን‹
ም፡ከፈቱ፡ወርቅና፡ዕጣን፡ከርቤ
ም፡እጅ፡መንሻ፡አገቡለት። መዝ፡
፸፪፡፲፡፲፩፡ኢሳ፡፷፡፮፨

፲፪ ወደ፡ሄሮድስም፡እንዳይመለሱ፡በ
ሕልም፡ታያቸው፡በሌላም፡መ
ንገድ፡ወደ፡አገራቸው፡ሔዱ፨

፲፫ እርሳቸውም፡ካለፉ፡በኋላ፡እነሆ
የእግዚአብሔር፡መልአክ፡ለዮሴ
ፍ፡በሕልም፡ታየው፡እንዲህ፡ሲ
ል፡ተነሣ፡ሕፃኑንና፡እናቱን፡ይዘ
ህ፡ወደ፡ምስር፡ሽሽ፡ሄሮድስ፡ሕፃ
ኑን፡ሊገድለው፡ይሻዋልና፡እስክ
ነግርህ፡ድረስ፡በዚያ፡ተቀመጥ፨

፲፬ እርሱም፡ተነሥቶ፡ሕፃኑንና፡እ
ናቱን፡ይዞ፡በሌሊት፡ወደ፡ምስር፡

፲፭ ሔደ፨ሄሮድስም፡እስኪሞት፡ድ
ረስ፡በዚያ፡ተቀመጠ፡ከእግዚአ
ብሔር፡ዘንድ፡በነቢይ፡እንዲህ፡ብ
ሎ፡የተነገረው፡ይፈጸም፡ዘንድ፡
ልጄን፡ከምስር፡ጠራሁት፨ሆሴ ፲፩

፲፮ ፩፨ከዚያም፡ወዲያ፡ሄሮድስ
ሰብአ፡ሰገል፡እንደ፡ተሣለቁበት፡
ባየ፡ጊዜ፡እጅግ፡ተቆጣ፡በቤተ፡ል
ሔም፡ባውራጃዋ፡ያሉትን፡ሕፃ
ናት፡ሁሉ፡ልኮ፡ገደለ፡ሁለት፡ዓመ
ት፡የሆነውን፡ከዚያም፡የሚያን
ሰውን፡ከሰብአ፡ሰገል፡በተጠየቀ
ዘመን፡ቍጥር፨

፲፯ የዚያን፡ጊዜ፡በነቢይ፡በኤርምያስ፡የተባለው፡ተፈጸመ፡እንዲህ ሲል፡፡ኤር፡፴፩፡፲፭፡፡

፲፰ ራሄል፡ስታለቅስ፡ዋይታም፡እጅግም፡ጩኸትም፡ድምፅም፡በራማ፡ተሰማ፡ስለ፡ልጆቿ ዋ፡ታለቅስለች ና፡መጽናናትም፡አልተቻላትም፡የሉምና። ዘፍ ፴፫፡፲፱ ኢዩኤል ስም፡በሞተ ጊዜ፡እነሆ፡የእግዚአብሔር፡መልአክ፡በምስር፡ለዮሴፍ፡በሕል

፳ ም፡ታየው፡እንዲህ፡ሲል፡የሕፃኑን፡ነፍስ፡የሚሹ፡ሙተዋልና፡[illegible]ሥተህ፡ሕፃኑንና፡እናቱን፡ይ[illegible]ህ፡ወደ፡እሥራኤል፡አገር፡ተመለስ፡ዘ

፳፩ [illegible]፡፬፡፲፱፡፡እርሱም፡ተነሥቶ፡ሕፃ[illegible]ን፡እናቱን፡ይዞ፡ወደ፡እሥራኤል፡ምድ

፳፪ [illegible]ብ፡፡አርኬላኦስም፡በአባቱ፡በ[illegible]ሮድስ፡ፈንታ፡በይሁዳ፡እንደ ነገሠ፡በሰማ፡ጊዜ፡ወደዚያ፡ለመሔድ፡ፈራ፡እግዚአብሔር፡በሕልም፡ተገለጠለት፡ወደ፡ገሊላም

፳፫ አገር፡ሔደ፡ናዝራዊ፡ይባላ፡ ዘኁ [illegible]በነቢያትም፡የተባለው፡እን[illegible]ዲፈጸም፡መጥቶ፡ናዝሬት፡በ[illegible]ምትባል፡አገር፡ተቀመጠ። ሉ[illegible]፩፡፳፮፡ኢሳ፡፲፩፡፩፡፶፡፫፡፷፡ዮ[illegible]፩፡፵፮፡ዘኍ፡፮፡፲፰ ።

ምዕራፍ፡፫ ።

[illegible]ሰ፡መጥምቁ፡ዮሐንስ፡ስብከቱ፡ስለ፡ጌታችን፡መጠመቅ ፡፡

፪ በዚያም፡ወራት፡መጥምቁ፡ዮሐንስ፡በይሁዳ፡ምድረ፡በዳ፡እየሰበከ፡መጣ፡እንዲህ፡አያለ፡፡ማር፡፩፡፩፡፲፭፡ሉቃ፡፫፡፩፡፳፡፡

፫ መንግሥተ፡ሰማያት፡ቀርባለችና፡ንስሐ፡ግቡ፡፡ም ፬፡፲፯፡፡

፬ በነቢዩ፡በኢሳይያስ፡የተባለለት፡ይህ፡ነውና፡እንዲህ፡ሲል፡ያዋጅ፡ነጋሪ፡ቃል፡በምድረ፡በዳ፡የሚጮህ፡የእግዚአብሔርን፡መንገድ፡ጥረጉ፡ጥርጊያውንም አስተካክሉ፡፡ኢሳ፡፵፡፫፡ዮሐ፡፩፡፳፫ ፡፡

፭ የዮሐንስም፡ልብስ፡የግመል፡ጸጉር፡ነበር፡በወገቡም፡ላይ የጠፍር፡መታጠቂያ፡ምግቡም፡አንበጣና፡የጣዝማ፡ማር፡ነበር፡፡፬ነገ፡፩፡፰ ፡፡

፮ በዚያም፡ጊዜ፡ኢየሩሳሌም፡ይሁዳም፡ሁሉ፡በዮርዳኖስም፡አውራጃ፡ያሉ፡አገሮች፡ሁሉ፡ወደ እርሱ፡ይመጡ፡ነበሩ፡፡ጸሩ፡ማኝ፡ከፈሪሳውያንና፡ከሰዱቃውያን፡ብዙ፡ሆነው፡ወደ፡ጥምቀቱ፡ሲመጡ፡ባየ፡ጊዜ፡እንዲህ፡አላቸው፡እናንተ፡የእፉኝት፡ልጆች፡ከሚመጣው፡ቁጣ፡እንድትሸሹ፡ማን፡አመለከታችሁ፡፡ም ፲፪፡፴፬ እንግዲህ፡ለንስሐ፡የሚገባ፡ፍሬ አድርጉ፡በራሳችሁ፡አብርሃም አባታችን፡ነው፡የምትሉ፡ አይምሰላችሁ፡ከነዚህ፡ድንጋዮች፡ለአ

ብርሃም፡ልጆች፡ሊያስነሣለት ለእግዚአብሔር፡እንዲቻለው እነግራችኋለሁ።ዮ፰፡፴፫፡፴ ፱፡ሮሜ፡፬፡፳፫፡፳፱።

፲ አሁንም፡ደግሞ፡ምሳር፡በዛፎች፡ሥር፡ሳይ፡ተቀምጦአል፡መልካም፡ፍሬ፡የማታፈራ፡ዛፍ፡ሁሉ፡ተቈረጣለች፡ወደ፡እሳትም ትጣላለች።ሉቃ ፫፡፱፡፱ ።

፲፩ እኔ፡ለንስሓ፡በውኃ፡አጠምቃችኋለሁ፡ከኔ፡በኋላ፡የሚመጣው ግን፡እርሱ፡ከእኔ፡ይልቅ፡ይበረታል፡እርሱ፡በመንፈስ፡ቅዱስና በእሳት፡ያጠምቃችኋል።ዮሐ፡ ፩፡፳፮፡፳፯።

፲፪ አውድማውን፡የሚያጠራበትን፡መንሽን፡የያዘ ስንዴውንም፡በጐተራው፡ይሰበስባል፡ገለባውን፡ግን፡በማይጠፋ፡እሳት፡ያቃጥላል።፲፫፡፫፡መዝ ፩፡፬።

፲፫ በዚያን፡ጊዜ፡ኢየሱስ፡ከዮሐንስ፡ይጠመቅ፡ዘንድ፡ከገሊላ፡ወደ፡ዮርዳኖስ፡መጣ።ማር፩ ፱፡፲፩፡ሉቃ፡፫፡፳፩፡፳፪፡ዮሐ፡፩፡፴ ፩፡፴፬።

፲፬ ዮሐንስ፡ግን፡እኔ፡ካንተ ልጠመቅ፡ያስፈልገኛል፡አንተም፡ወደ፡ኔ፡ትመጣለህን፡ብሎ፡እምቢ፡አለው።

፲፭ ኢየሱስም፡መልሶ፡ለሱ፡እንዲሁ፡ጽድቅን፡ሁሉ፡እንፈጽም፡ዘንድ፡ይገባናልና፡አሁንስ፡ተው፡አለው፡ከዚያም፡ወዲያ፡አሺ፡ብሎ፡ተወው

፲፮ ኢየሱስም፡ከተጠመቀ፡በኋላ፡ያንጊዜውን፡ከውኃ፡ወጣ፡እነሆ፡ሰማዮችም፡ተከፈቱ፡የእግዚአብሔርም፡መንፈስ፡እንደ ርግብ፡ወርዶ፡በራሱ፡ሳይ፡ሲቀመጥ፡አየ።

፲፯ እነሆም፡ይህ፡ነው፡የምወደው፡ልጄ፡በእርሱ፡ደስ ዩኝ፡የማይበት፡የሚል፡ድምፅ ከሰማይ፡መጣ።ም፲፯፡፭፡ኢሳ፡ ፵፪፡፩። ። ። ።

ምዕራፍ፡፬።

ስለ፡ጌታችን፡ጾም፡ስለ፡ዲያብሎስ፡ፈተና፡ስለ፡ጌታችን፡መጀመሪያ፡ስብከት፡ስለ፡ጴጥሮስና፡ስለ እንድርያስ፡ስለ፡ያዕቆብ፡[illegible]ስለ፡ዮሐንስ፡መጠራት።

፩ ከዚያም፡ወዲያ፡መንፈስ[illegible]ሉስን፡ወደ፡ምድረ፡በዳ፡አወ[illegible]፡ ከዲያብሎስ፡ይፈተን፡ዘ[illegible]። ማር፡፩፡፲፪፡፲፫፡ሉቃ፡፬፡፩[illegible]፩ ብ፡፬፡፲፭።

፪ አርባ፡ቀንና፡አርባ፡ሌሊትም፡ከጾመ፡በኋላ፡ተራበ፡ዘፀ፡፴፬፡፳፰።

፫ የሚፈታተነው፡ፈታኝ[illegible]መጣበት፡አለውም፡የእግዚአ[illegible]ር ልጅ፡እንደሆንህ፡እነዚህ[illegible]ን ጎች፡እንጀራ፡እንዲሆኑ[illegible]ሉ፡ ዘፀ፡፫፡፩፡፳፫።

፬ እርሱም፡መለሰ፡ተጽፎ[illegible]ው በእንጀራ፡ብቻ፡እንዳይኖር[illegible]እግዚአብሔር፡አፍ፡በሚ[illegible]ጣ

ው፡ቃል፡ሁሉ፡እንጂ፡አለው፡ዘዳ፰፡፫

፭ ከዚያም፡በኋላ፡ሰይጣን፡ወደ፡ቅድስት፡ሀገር፡ወሰደው፡በቤተ፡መቅደስ ስም፡ጫፍ፡ላይ፡አቆመው።ምሽ፪፡፶፫

፮ ልሰውም፡የእግዚአብሔር፡ልጅ እንደሆንህስ፡ወደታች፡ተወርወር፡መላእክቶቹን፡ስለአንተ፡እንዲያዝ፡ተጽፍዋልና፡በእጃቸው፡ያነሡሃል፡እግርህ፡በደንጊያ፡እንዳትሰናከል፡መዝ፡፺፩፡፲፩፡፲፪

፯ ኢየሱስም፡አምላክህ፡እግዚአብሔርን፡አትፈታተነው ተብሎ፡ደግሞ፡ተጽፏል፡አለው ዘዳ፮፡፲፮

፰ ደግሞም፡ሰይጣን፡ወደረጅም፡ተራራ፡አወጣው፡የዓለምን፡መንግሥታት፡ሁሉ፡ክብራቸውንም፡አሳየው

፱ ተደፍተህ ብትሰግድልኝ፡ይህን፡ሁሉ፡እሰጥሃለሁ፡አለው

፲ በዚያም፡ጊዜ ኢየሱስ፡ለአምላክህ፡ለእግዚአብሔር፡ስገድ፡እርሱንም፡ብቻ፡አምልክ፡ተብሎ፡ተጽፏልና፡አንተ፡ሰይጣን፡ከኔ፡ራቅ፡አለው ዘዳ፮፡፲፫

፲፩ ከዚያም፡ወዲያ፡ሰይጣን፡ተወው፡እነሆ፡መላእክት፡መጡ፡ያገለግሉትም፡ነበር፡ዮሐ፡፵፩፡ዕብ፡፩፡፲፬

፲፪ ኢየሱስም፡ዮሐንስ፡እንደ፡ተያዘ በሰማ፡ጊዜ፡ወደ፡ገሊላ፡ሔደ።ም፡፲፬፡፫

፲፫ ናዝሬትንም፡ተወ፡መጥቶም፡በባሕር፡አጠገብ፡ባለችው በቅፍርናሆም፡ተቀመጠ፡በዛብሎንና፡በንፍታሌም፡ዳርቻ

፲፬ በነቢዩ፡በኢሳይያስ፡የተባለው፡ይፈጸም፡ዘንድ፡እንዲህ ሲል፡ኢሳ፱፡፩፡፫፡፲

፲፭ የዛብሎን፡ምድርና፡የንፍታሌም፡ምድር፡በባሕር፡መንገድ፡በዮርዳኖስ፡ማዶ፡የአሕዛብ፡ገሊላ

፲፮ በጨለማ፡የሚኖር፡ሕዝብ፡ታላቅ፡ብርሃን፡አየ፡በሞት፡አገርና፡ጥላ፡ለሚኖሩ፡ብርሃን

፲፯ ወጣላቸው፡ከዚያም፡ዘመን፡ጀምሮ፡ኢየሱስ፡መንግሥተ፡ሰማያት፡ቀርባለችና፡ንስሐ፡ግቡ፡እያለ፡ይሰብክ፡ጀመረ

፲፰ ኢየሱስም፡በገሊላ፡ባሕር፡ዳር፡ሲዳርሲ፡መሳለስ፡ሁለት፡ወንድማማች፡ጴጥሮስ፡የሚሉትን፡ስምዖን፡ወንድሙንም፡እንድርያስን፡መረባቸውን፡ወደ፡ባሕር፡ሲጥሉ፡አየ፡ዓሣ፡አጥማጆች፡ነበሩና፡ማር፡፩፡፲፮፡፳፡ሉቃ፡፭፡፩፡፲፩

፲፱ ሰውንም፡እንድታጠምዱ፡አድርጋችኋለሁና፡ተከተሉኝ፡አላቸው፡ም፲፫፡፵፯፡ሕዝ፵፯፡፲

፳ እርሳቸውም፡መረባቸውን ትተው፡ያንጊዜውን፡ተከተሉት

፳፩ ከዚያም፡ጥቂት፡አልፎ፡ሌሎች ሁለት፡ወንድማማች፡የዘብዴዎስን፡ልጅ፡ያዕቆብን፡ወንድሙን

ም፡ዮሐንስን፡ካባታቸው፡ከዘብ
ዴዎስ፡ጋራ፡በታንኳ፡ሆነው፡መረ
ባቸውን፡ሲያበጁ፡አየና፡ጠራቸ
፳፪ ው። እነርሳቸውም፡ታንኳቸው
ንና፡አባታቸውን፡ትተው፡ያንጊ
፳፫ ዜውን፡ተከተሉት። ኢየሱስም፡
በምኵራባቸው፡እያስተማረ፡የ
መንግሥትንም፡ወንጌል፡እየሰ
በከ፡በሕዝብም፡ያለውን፡ሁሉ፡
ሕማም፡እየፈወሰ፡በገሊላ፡ሁሉ፡
ይዞር፡ነበር። ሉ፡፬፡፲፭፡ማ፮፡የሐዋ
፳፬ ፲፡፴፰። ወሬውም፡በሶርያ፡ሁሉ
ወጣ፡የታመሙትንም፡ሥቃያቸ
ውንና፡ደዌያቸውንም፡ልዩ፡ልዩ
የሆነውን፡አጋንንትም፡የያዛቸ
ቸውን፡በወር፡በወሩም፡የሚጥ
ላቸውን፡እኽላቸው፡የዘለባቸ
ውን፡ወደ፡እርሱ፡አመጡ፡ፈወ
፳፭ ሳቸውም፡ማር፡፫፡፯፡፯።
ከገሊላ፡ካስሩም፡አገሮች፡ከኢ
የሩሳሌምም፡ከይሁዳም፡ከዮር
ዳኖስም፡ማዶ፡ብዙ፡ሕዝብ፡ተከ
ተሉት። ሉቃ፡፯።

ምዕራፍ፡፭።

ጌታችን፡ወደ፡ተራራ፡ወጥቶ፡ስለ ደ
ቀ፡መዛሙርቱ፡እንደ፡ዕበከ፡ስለ፡ደ
ቀ፡መዛሙርቱ፡ክብር፡ኦሪትን
ነቢያትን፡ለመሻር፡ስለ፡አለመ
ምጣቱ። ጠላትን፡ስለ፡መውደድ
፩ ብዙ፡ሕዝብ፡ባየ፡ጊዜ፡ወደ፡ተራራ
ወጥቶ፡ተቀመጠ፡ደቀ፡መዛሙር
ቱም፡ወደ፡እርሱ፡ቀረቡ። ሉቃ፡፮
፪ ፳፡ማ፱። አፉንም፡ከፈተ፡እንደዚህ
ብሎም፡ያስተምራቸው፡ጀመረ፡
፫ በመንፈሳቸው፡የተቸገሩ፡ብፁ
ዓን፡ናቸው፡መንግሥተ፡ሰማያት
የርሳቸው፡ናትና። ኢሳ፡፶፯፡፲፭፡
፬ የሚያዝኑ፡ብፁዓን፡ናቸው፡መ
ጽናናትን፡ያገኛሉና። መዝ፡፻፳
፮፡፭፡ኢሳ፡፷፩፡፪፡፪፡ራእ፡፯፡፲፯።
፭ የዋሆች፡ብፁዓን፡ናቸው፡እርሳቸ
ው፡ምድርን፡ይወርሳሉና። መ
፮ ዝ፡፴፯፡፲፩። ጽድቅን፡የሚራቡ፡
የሚጠሙም፡ብፁዓን፡ናቸው፡እ
ርሳቸው፡ይጠግባሉና። መዝ፡፻፯፡
፱፡ኢሳ፡፶፭፡፲፯፡፻፫፡፩፡፪፡ም[illegible]
፯ ፳፩። የሚራሩ፡ብፁዓን፡ናቸው፡
እርሳቸው፡ምሕረትን፡ያገኛሉና
ምሳ፡፲፡፴፫፡ም፡፲፩፡፳፫፡ያዕ፡፪፡፲፫።
፰ ልባቸው፡የነፃ፡ብፁዓን፡ናቸው፡
እርሳቸው፡እግዚአብሔርን፡ያዩ
ታልና። መዝ፡፳፬፡፲፬፡፩፡ዮሐ፡፫፡፪፡
፱ ፫። ዕርቅ፡የሚያደርጉ፡እርሳቸ
ው፡የእግዚአብሔር፡ልጆች፡ይባ
ላሉና፡ብፁዓን፡ናቸው። ፩
፪፡፲፬፡መዝ፡፴፬፡፲፬።
፲ ስለ፡ጽድቅ፡የሚሰደዱ፡መንግሥ
ተ፡ሰማያት፡የእርሳቸው፡ናትና፡
ብፁዓን፡ናቸው። ፩ጴጥ፡፫፡[illegible]፡፪
፲፩ ጢሞ፡፪፡፲፪። በሰደቡዋችሁና፡በ
አሳደድዋችሁም፡ጊዜ፡ክፉንም፡
ሁሉ፡ስለኔ፡በሐሰት፡በተናገሩባች

ቹሁ፡ጊዜ፡እናንተ፡ብፁዓን፡ና
ችሁ፨ ፩ጴጥ፡፬፡፲፬፡ኢሳ፡፶፩፡፯፡
፲፪ ፳፬፨ዋጋችሁ፡በሰማይ፡ብዙ፡ነው
ና፡ከናንተ፡በፊት፡የነበሩትን፡ነ
ቢያትንም፡እንዲሁ፡አሳደዋልና
ደስ፡ይበላችሁ፡ሐሤትም፡አድር
ጉ፨ያዕ፡፫፡፲፡ዕብ፡፲፩፡፳፭፡ማ፨

፲፫ እናንተ፡የምድር፡ጨው፡ናችሁ
ጨው፡አልጫ፡ቢሆን፡ግን፡በም
ን፡ይጣፍጣል፡ወደ፡ውጭ፡ይጣላ
ል፡ሰውም፡ይረግጠዋል፡እንጂ፡
የሚረባው፡የለም፨ዮሐ፡፲፡፲፬፡

፲፬ ፊል፡፲፪፡፲፭፨እናንተ፡የዓለም፡ብ
ርሃን፡ናችሁ፡በተራራ፡ላይ፡የተ
ሠራች፡መንደር፡መሠወር፡አይ

፲፭ ቻላትም፡፡በዕንቅብ፡ውሥጥ፡ሊ
ያኖሩት፡መብራት፡አያበሩም፡
በመቅረዝ፡ላይ፡እንጂ፡በቤት፡ላ
ሉት፡ሁሉ፡እንዲያበራ፨ማር፡፬

፲፮ ፳፩፡፳፪፡፲፫፨እንዲሁ፡መልካሙ
ን፡ሥራችሁን፡አይተው፡የሰማ
ዩ፡አባታችሁን፡ያመሰግኑት፡
ዘንድ፡ብርሃናችሁ፡በሰው፡ፊት
ይብራ፨፩ጴጥ፡፪፡፲፪፡፡

፲፯ ኦሪትንና፡ነቢያትን፡ልሽር፡አል
መጣሁም፡አይምሰላችሁ፡ልፈ
ጽም፡ነው፡እንጂ፡ለመሻር፡አል
መጣሁም፨ምሮ፡፲፫፡ሮሜ፡፫፡፴

፲፰ ፩፡፲፡፬፨እውነት፡እነግራችኋለ
ሁ፡ሰማይና፡ምድር፡እስኪያል
ፍ፡ሁሉም፡እስኪሆን፡ድረስ፡አን
ዲቱ፡የውጣ፡ወይም፡አንዲቱ፡
ጽሕፈትዋ፡ከኦሪት፡አታልፍም
ም፡ሉቃ፡፲፮፡፲፯፡ኢሳ፡፵፡፰፡፲፰፡

፲፱ ከነዚህም፡ከጥቃቅኑ፡ትእዛዛት
አንዲቱን፡የሻረ፡ለሰውም፡እን
ዲሁ፡ያስተማረ፡በመንግሥተ፡
ሰማያት፡ታናሽ፡ይባላል፡እርሱ፡
አያደረገ፡የሚያስተምር፡በመ
ንግሥተ፡ሰማያት፡ታላቅ፡ይባላ
ል፨ያዕ፡፪፡፲፡ዕዝ፡፯፡፲፨

፳ ጽድቃችሁም፡ከጻፎችና፡ከፈሪ
ሳውያን፡ጽድቅ፡ካልበለጠ፡ምን
ም፡ቢሆን፡ወደ፡መንግሥተ፡ሰማ
ያት፡አትገቡም፡ብዬ፡እነግራች

፳፩ ኋለሁ፨ለቀደምት፡የተባለው
ን፡ሰምታችኋል፡አትግደል፡የገ
ደለ፡ይፈረድበታል፨ዘፀ፡፳፡፲፫፡
ዘሌዋ፡፳፬፡፲፯፡ዘዳ፡፲፯፡፳፨

፳፪ እኔ፡ግን፡እላችኋለሁ፡በወንድሙ
ላይ፡በከንቱ፡የሚቆጣ፡ሁሉ፡በፍ
ርድ፡ይፈረድበታል፡ወንድሙን
ም፡ጨርቃ፡ለባሽ፡የሚለው፡በ
ሸንጎ፡ይፈረድበታል፡ደንቆሮ፡
የሚለው፡ግን፡በገሃነመ፡እሳት፡
ይፈረድበታል፨፩ዮሐ፡፫፡፲፭፡ኢሳ

፳፫ ፷፯፡፲፬፨ቍርባንህን፡በመሠ
ዊያ፡ስታቀርብ፡ወንድምህም
የሚነቅፍብህ፡እንዳች፡እንዳለ
ው፡ትዝ፡ቢልህ፡ማር፡፲፩፡፳፭፨

፳፬ ቍርባንህን፡በዚያው፡በመሠዊ
ያው፡ፊት፡ተወው፡ሒደህም፡አ

ስቀድመህ፡ከወንድምህ፡ጋራ፡
ታረቅ፡ተመልሰህም፡ቍርባን
፳፭ ህን፡አቅርብ፨ከጠላትህ፡ጋራ፡
በመንገድ፡ሳለህ፡ፈጥነህ፡ተስ
ማማ፡ታረቅ፡ጠላትህ፡ለዳኛ፡አ
ሳልፎ፡እንዳይሰጥህ፡ዳኛውም
ለሚያስር፡ይሰጥሃል፡ወደ፡ግዞ
ትም፡ትገባለህ፨፯፡፲፬፡፴፭፡
ሉቃ፡፲፪፡፶፰፡፶፱፨
፳፮ የኋለኛውን፡ዲዋኒ፡ሮሳ፡እስክ
ትከፍል፡ድረስ፡ከዚያው፡እንዳት
ትወጣ፡በእውነት፡እነግርሃለሁ
፳፯ ለቀደምት፡የተባለውን፡ሰምታ
ችኋል፡አታመንዝሩ፨ዘፀ፡፳፡፲
፳፰ ፬፨እኔ፡ግን፡እላችኋለሁ፡ወደ፡ሴ
ት፡ያየ፡የተመኛትም፡ፈጽሞ፡በ
ልቡ፡አመነዘረባት፨ኢዮ፡፴፩፡
፩፡፪፡ኪ፡፪፡፲፬፨
፳፱ ቀኝ፡ዓይንህ፡ብታስትህ፡ከንተ፡
አውጥተህ፡ጣላት፡አካልህ፡ሁሉ
ወደ፡ገሃነም፡ከሚገባ፡ይልቅ፡አ
ንዱ፡አካልህ፡ቢጠፋ፡ይሻልሃል
ና፨ማር፡፱፡፵፯፡ቈላ፡፫፡፭፡ም፲፰
፴ ፱፨ቀኝ፡እጅህም፡ብታስትህ፡ከን
ተ፡ቈርጠህ፡ጣላት፡አካልህ፡ሁ
ሉ፡ወደ፡ገሃነም፡ከሚገባ፡ይልቅ
አንዱ፡አካልህ፡ቢጠፋ፡ይሻላሃ
፴፩ ልና፨ሚስቱንም፡የሚፈታ፡ሁ
ሉ፡የፍችዋንም፡መጽሐፍ፡ይ
ስጣት፡ተባለ፨ም፲፱፡፫፡ዘዳ፡፳፬፡
፴፪ ፩፨እኔ፡ግን፡ያለ፡ዝሙት፡ምክን

ያት፡ሚስቱን፡የሚፈታ፡ሁሉ
አመንዝራ፡አደረጋት፡የተፈታ
ችውንም፡የሚያገባ፡አመነዘረ
እላችኋለሁ፨ሉቃ፡፲፮፡፲፰፡[illegible]
፴፫ ቆሮ፡፯፡፲፨ደግሞ፡ለቀደም[illegible]
ተባለውን፡ሰምታችኋል፡መ[illegible]
ላህን፡ለእግዚአብሔር፡ስጥ፡እን
፴፬ ጂ፡በሐሰት፡አትማል፨እኔ፡ግን፡
እላችኋለሁ፡በከንቱ፡አትማሉ
በሰማይ፡ስ፡እንኳ፡የእግዚአብሔ
ር፡ዙፋን፡ናትና፨ዘፀ፡፳፡፯፡ዘሌ፡
፲፱፡፲፪፡ዘኍ፡፴፡፲፪፨
፴፭ በምድርም፡የእግሩ፡መረገጫ
ዱ፡ካ፡ናትና፡በኢየሩሳሌም፡[illegible]
የታላቁ፡ንጉሥ፡ከተማ፡ና[illegible]
፴፮ መዝ፡፵፰፡፪፡ቀ፡በራስህም፡[illegible]
ማል፡አንዲቱን፡ጸጉር፡ነጭ[illegible]
ም፡ጥቁር፡ለማድረግ፡አይ[illegible]
፴፯ ህምና፨ምዕ፡፭፡፲፪፨ነገር[illegible]
ነገራችሁ፡እንዲህ፡ይሁን፡[illegible]
አዎን፡አይደለም፡አይደለም፡ከነ
ዚህ፡የወጣ፡ከክፉ፡ነው[illegible]
፩፡፲፯፡ያዕ፡፭፡፲፪፨
፴፰ ዓይን፡በዓይን፡ጥርስም፡[illegible]
ስ፡እንደ፡ተባለ፡ሰምታችኋ[illegible]
ዘፀ፡፳፩፡፳፬፨
፴፱ እኔ፡ግን፡እላችኋለሁ፡ክፉ[illegible]
አትቃወሙ፡ነገር፡ግን፡ቀ[illegible]
ጉንጭህን፡ለጸፋህ፡ደግሞ፡[illegible]ተ
ኛውን፡አዙርለት፨ሐ፡፲፯፡[illegible]
፳፫፡ዘሌ፡፲፱፡፲፰፨

፵ ሊጣላህና፡ቀሚስህን፡ሊወስድ
ብህ፡ለወደደ፡ደግሞ፡መጐናጸፊ
፵፩ ያህን፡ተውለት። እንድ፡ምዕራ
ፍም፡ለሚጐትትህ፡ሁለተኛው
፵፪ ን፡ከርሱ፡ጋራ፡ሒድ። ለሚለም
ንህ፡ስጥ፡ካንተ፡ሊበደርም፡ለሚ
ፈልገው፡አትከልክለው። ዘዳ፡
፵፫ ፲፭፡፯፡፲፩። ባልንጀራህን፡ውደ
ድ፡ጸላትህን፡ጥላ፡እንደ፡ተባለ፡ሰ
ምታችኋል፡ዘፀ፡፳፫፡፬፭፡ዘሌ፡
፵፬ ፲፱፡፲፰። እኔ፡ግን፡እላችኋለሁ፡
ጸላቶቻችሁን፡ውደዱ፡የሚረግ
ሟችሁንም፡መርቁ፡ለሚጸል
ዋችሁም፡መልካም፡አድርጉ፡
ስለሚበድሏችሁና፡ስለሚያሳ
ድዷችሁ፡ጸልዩ። ሉቃ፡፳፫፡፴፬፡
የሐዋ፡፯፡፶፱፡ሮሜ፡፲፪፡፲፬፡፳።
፵፭ በሰማያት፡ላለው፡አባታችሁ፡ል
ጆች፡ትሆኑ፡ዘንድ፡እርሱ፡ለክ
ፉዎችና፡ለደጎችም፡ፀሐዩን፡ያወ
ጣልና፡ዝናሙንም፡በጻድቃን
ና፡በኃጥአን፡ላይ፡ያዘንማልና፡
፵፮ ሉ፡፮፡፴፪። የሚወድዋችሁን፡ማ
ብትወዱ፡ምን፡ደመወዝ፡ዋጋ፡አ
ላችሁ፡ቀራጮችስ፡እንዲህ፡ያደ
ርጉ፡የለምን። ሉቃ፡፮፡፴፪፡፴
፵፯ ፫። ከወንድሞቻችሁም፡ጋራ፡
ብቻ፡ብትገናኙ፡ምን፡ብልጫ፡
አደረጋችሁ፡አሕዛብስ፡እንዲ
፵፰ ህ፡ያደርጉ፡የለምን። ስለዚህም
የሰማዩ፡አባታችሁ፡ፍጹም፡እ
ንደ፡ሆነ፡እናንተም፡ፍጹማን፡
ሁኑ፡ዘሌ፡፲፱፡፪።

ምዕራፍ፡፮።

ስለ፡ምጽዋት፡ስለ፡ጸሎት፡ስለ፡ጾም
ስለ፡ምድራዊና፡ስለ፡ሰማያዊ፡መ
ዝገብ፡ስለ፡ምግብና፡ስለ፡መጠ
ጥ፡ስለ፡ልብስም፡በብዙ፡መ
ጨነቅ፡እንዳይገባ።

፩ ምጽዋታችሁን፡በሰው፡ፊት፡እ
ንዳታደርጉ፡ተጠንቀቁ፡ለራሳ
ችሁ፡ትታዩ፡ዘንድ፡እንዲህስ፡
ካልሆነ፡በሰማዩ፡አባታችሁ፡ዘ
ንድ፡ዋጋ፡የላችሁም። ም፳፫፡፳
፪ ፭። ምጽዋትም፡ባደረግህ፡ጊዜ
በፊትህ፡መለከት፡አታስነፋ፡ግ
ብዞች፡በመስጊድ፡በገቢያም፡
እንደሚያደርጉ፡እርሳቸው፡በሰ
ው፡ፊት፡ይመስገኑ፡ዘንድ፡ዋጋቸ
ውን፡እንዲወስዱ፡በውነት፡እነ
፫ ግራችኋለሁ። አንተ፡ግን፡ምጽ
ዋት፡ባደረግህ፡ጊዜ፡ቀኝህ፡የ
ሚሠራውን፡ግራህ፡አይወቅ።
ም፳፭፡፵፪፡ሮሜ፡፲፪፡፳።
፬ ምጽዋትህ፡በስውር፡ትሆን፡ዘ
ንድ፡በሥውር፡የሚያይ፡አባት
ህ፡እርሱ፡በግልጽ፡ይሰጥሃል።
፭ ዳን፡፬፡፳፯። በጸለይህም፡ጊዜ፡እ
ንደ፡ግብዞች፡አትሁን፡እርሳቸ
ው፡ለሰው፡ለመታየት፡በመስጊድ
ባደባባይ፡ማዕዘንም፡ቆመው፡
ይጸልዩ፡ዘንድ፡ይወዳሉና፡ዋጋቸ

ውን፡እንደ፡ወሰዱ፡በውነት፡እ
፮ ነግራችኋለሁ። አንተ፡ግን፡በጸ
ለይህ፡ጊዜ፡ወደ፡ቤትህ፡ግባ፡ደ
ጅህንም፡ዘግተህ፡በስውር፡ወደ፡
ሚያይህ፡አባትህ፡ጸልይ፡በስው
ር፡የሚያይም፡አባትህ፡በግልጽ
ይሰጥሃል፡፪ነገ፡፬፡፴፫።
፯ በጸለያችሁም፡ጊዜ፡እንደ፡አሕ
ዛብ፡ነገር፡አታብዙ፡እርሳቸው
በነገራቸው፡ብዛት፡የሚሰማ
ላቸው፡ይመስላቸዋልና። ኢሳ፡
፩፡፲፭፡ማቴ፡፳፫፡፲፬።
፰ አባታችሁ፡እርሱን፡ሳትለምኑ
ት፡የምትሹትን፡ያውቃልና፡አ
ትምሰሏቸው፡እናንተስ፡እንዲ
ህ፡እያላችሁ፡ጸልዩ። ቍ፴፪።
፱ አባታችን፡ሆይ፡በሰማይ፡የምት
ኖር፡ስምህ፡ይቀደስ። ሉቃ፡፲፩፡፪፡
፱፡ዮሐ፡፲፯፡፱፡፮።
፲ መንግሥትህ፡ትምጻ፡ፈቃድህ፡
በሰማይ፡እንደሆነ፡እንዲሁ፡በም
ድር፡ይሁን። ምዕ፡፮፡፳፭፡ሉ፡፳፱፡
ሥራ፡፳፩፡፲፬።
፲፩ የሚበቃኝን፡የዕለት፡ምግባች
፲፪ ንን፡ዛሬ፡ስጠን። በደላችንን፡ይቅ
ር፡በሉልን፡እኛም፡የበደሉንን፡ይቅ
ር፡እንደምንል፡ቍ፲፬፡፲፭፡ምዕ፲፰፡
፲፫ ፳፩፡፴፭። ወደ፡ፈተናም፡አታግባ
ን፡ከክፉ፡አድነን፡እንጂ፡መንግ
ሥት፡ያንተ፡ነውና፡ኃይልም፡ም
ስጋናም፡ለዘላለሙ፡አሜን።

ዜና፡መዋ፡፳፱፡፲፡፲፫፡፬፡ጢሞ፡
፲፬ ፩፡፲፯። ለሰዎች፡ኃጢአታቸው
ን፡ይቅር፡ብትሉ፡የሰማዩ፡አባታ
ችሁ፡ደግሞ፡ይቅር፡ይላችኋልና
ማር፡፲፩፡፳፭፡፳፮።
፲፭ ለሰዎች፡ኃጢአታቸውን፡ይቅር
ባትሉ፡ግን፡አባታችሁም፡ኃጢ
፲፮ አታችሁን፡አይላችሁም። በጾማ
ችሁም፡ጊዜ፡እንደ፡ግብዞች፡አት
ጸውልጉ፡እርሳቸው፡እንደ፡ጾሙ
ለሰዎች፡ሊታዩ፡ይጸወልጋሉና፡
ፊታቸውንም፡ይቋጥራሉና፡ዋ
ጋቸውን፡በውነት፡እንደ፡ወሰዱ፡
እነግራችኋለሁ። ኢሳ፡፶፰፡፭፡፮፡
፲፯ አንተ፡ግን፡በጾምህ፡ጊዜ፡ራስህን
ተቀባ፡ፊትህንም፡ታጠብ።
፲፰ በስውር፡ለሚያይ፡ላባትህ፡እንጂ
ለሰው፡ጾመኛ፡መስለህ፡እንዳትታ
ይ፡በስውር፡የሚያይ፡አባትህም፡
በግልጽ፡ይሰጥሃልና። ቍ፬።
፲፱ ትል፡ወደሚበላው፡ነቅዝም፡ወ
ደሚያነቅዘው፡ሌቦችም፡ነድለ
ው፡ወደሚሠርቁት፡ለእናንተ፡
በምድር፡ላይ፡መዝገብ፡አትሰብ
ስቡ። ምሳ፡፲፱፡፳፩፡፳፬።
፳ ነገር፡ግን፡ትል፡ወደማይበላው፡
ነቀዝም፡ወደ፡እማያነቅዘው፡
ሌቦችም፡ነድለው፡ወደ፡እማይ
ሠርቁት፡ለናንተ፡በሰማይ፡መ
ዝገብ፡ሰብስቡ። ሉ፡፲፪፡፴፫፡ቈ
፳፩ ላ፡፫፡፩፡፪። መዝገባችሁ፡ወደ፡አ

ለበት፡ልባችሁ፡በዚያ፡ይሆና
ልና፡መዝ፡፷፪፡፲፩ ፨
፳፪ የሰውነት፡የሥጋ፡መብራቱ፡ዓ
ይን፡ነው። ዓይንህም፡ጥሩ፡ቢ
ሆን፡ሰውነትህ፡ሁሉ፡የበራ፡ይሆ
ናል፥ሉቃ፡፲፩፡፴፬፡፴፮ ፨
፳፫ ዓይንህ፡ታማሚ፡ቢሆን፡ግን፡ሰ
ውነትህ፡ሁሉ፡የጨለመ፡ይሆና
ል፡በአንተ፡ያለው፡ብርሃን፡ጨ
ለማ፡ከሆነ፡ጨለማው፡እንዴ
ት፡ይበዛ፥መክ፡፪፡፲፫፡፲፬ ፨
፳፬ አንድ፡አገልጋይ፡ለሁለት፡ጌቶች
መገዛት፡አይቻለውም፡አንዱን
ጠልቶ፡ሁለተኛውን፡ይወዳል፡ወ
ይም፡አንዱን፡አክብሮ፡ሁለተኛ
ውን፡ይንቃል፡ለእግዚአብሔርና
ለገንዘብ፡መገዛት፡አትችሉም፡
፩፡ነገሥ፡፲፰፡፳፩፡ሉቃ፡፲፮፡፲፫፡፩፡
፳፭ ቆሮ፡፯፡፲፭ ፨ ስለዚህ፡እላችኋለሁ
ለሕይወታችሁ፡በምትበሉት፡በ
ምትጠጡት፡ለሰውነታችሁም
በምትለብሱት፡አትጨነቁ፡ሕ
ይወት፡ከመብል፡ሰውነትም፡ከ
ልብስ፡የሚበልጥ፡አይደለምን
ሉቃ፡፲፪፡፳፪፡፶፭፡፳፪፡ፊል፡፬፡፮፡ጴ
ጥ፡፭፡፯፡ዕብ፡፲፫፡፭ ፨
፳፮ ወደ፡ሰማይ፡ወፎች፡ተመልከቱ
እርሳቸውን፡የሰማይ፡አባታች
ሁ፡ይመግባቸዋል፡እንጂ፡አይ
ዘሩም፡አያጭዱም፡በጎተራ
ም፡አይከቱምና፡እናንተ፡ከርሳቸ
ው፡እጅግ፡የምትሻሉ፡አይደላ
ችሁምን፨ ፲፡፳፱፡፵፩ ፨
፳፯ ከእናንተ፡ወገን፡ተጨንቆ፡አ
ስቦ፡በቁመቱ፡ላይ፡አንድ፡ክንድ
መጨመር፡የሚችል፡ማነው፧
፳፰ ስለልብስ፡ስለምን፡ትጨነቃላች
ሁ፡የምድረ፡በዳ፡አበቦች፡እንዴ
ት፡እንደሚያድጉ፡ተመልከቱ፡
እርሳቸውን፡አይደክሙም፡አይፈ
፳፱ ትሉም። እላችኋለሁም፡ሰሎ
ሞን፡እንኳ፡በዚያ፡ሁሉ፡ክብሩ
ከነዚህ፡እንደ፡አንዲቱ፡አለበሰም
፩፡ነገ፡፲፡፲፡፳፡መክ፡፪፡፬፡፲፩ ፨
፴ እናንተ፡እምነት፡የጐደላችሁ፡የ
ምድረ፡በዳን፡ሣር፡ዛሬ፡የሚገኘ
ውን፡ነገ፡ወደ፡ዕቶን፡የሚጣለው
ን፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡የሚ
ያለብሰው፡ከሆነ፡እናንተን፡ይ
ልቅ፡አብዝቶ፡አያለብሳችሁም
፴፩ ን፨መዝ፡፺፡፱፨እንግዲህ፡ምን፡
እንበላለን፡ምን፡እንጠጣለን፡ም
ን፡እንለብሳለን፡ብላችሁ፡አት
፴፪ ጨነቁ፨ይህን፡ሁሉ፡አሕዛብ፡ይ
ሹታልና፡እናንተስ፡ይህን፡ሁሉ
እንድትሹ፡የሰማይ፡አባታችሁ
፴፫ ያውቃልና፨ነገር፡ግን፡አስቀድ
ማችሁ፡የእግዚአብሔርን፡መ
ንግሥት፡ጽድቁንም፡እሹ፡ይህ
ም፤ሁሉ፡ይጨመርላችኋል፡ሮ
ሜ፡፲፬፡፲፯፡፩፡ነገ፡፫፡፲፫፡መዝ፡፴፯
፴፬ ፳፭። ለነገም፡አትጨነቁ፡አታስቡ፡

ነገ፡ ለራሱ፡ ያስባልና፡ የቀኑስ፡ ክፋቱ፡ ይበቃዋልና። ፴፬፡ ዘፀ ፲፮ ፲፱።

ምዕራፍ ፯።

በሰው፡ ላይ፡ ስለ፡ መፍረድ፡ ማስጠንቀቂያ፡ ስለ፡ ተቀደሰው፡ ነገር። የለመኑትን፡ ስለማግኘት፡ ስለ፡ ጠባቢቱና፡ ስለ፡ ሰፊይቱ፡ ደጅ። የበግ ለምድ፡ ለብሰው፡ ስለሚመጡ፡ በአፍ፡ ብቻ፡ ጽድቅ፡ ስለ፡ አለማግኘት፡ ስለ፡ ትምህርቱ፡ መደነቅ።

፩ አትፍረዱ፡ እንዳይፈረድባችሁ፡ ሮሜ፡ ፪፡ ፩፡ ቆሮ፡ ፬፡ ፭።

፪ በፈረዳችሁት፡ ፍርድ፡ ይፈረድባችኋልና፡ በምትሰፍሩበትም፡ መስፈሪያ፡ ይሰፈርባችኋልና። ማር፡ ፬፡ ፳፬።

፫ በወንድምህ፡ ዓይን፡ ያለውን፡ ጉድፍ፡ ለምን፡ ታያለህ፡ በዓይንህ፡ ያለውን፡ ምሰሶ፡ ግን፡ አትመለከትም።

፬ እንዴትስ፡ ወንድምህን፡ ተወኝ፡ ከዓይንህ፡ ውስጥ፡ ጉድፍ፡ ላውጣልህ፡ ትለዋለህ። እነሆ፡ ባንተ፡ ዓይን፡ ምሰሶ፡ አለ።

፭ አንተ፡ ግብዝ፡ አስቀድመህ፡ ከዓይንህ፡ ውስጥ፡ ምሰሶውን፡ አውጣ፡ ከዚያ፡ በኋላ፡ ከወንድምህ፡ ዓይን፡ ጉድፍ፡ ታወጣ፡ ዘንድ፡ አጥርተህ፡ ታያለህ።

፮ የተቀደሰውን፡ ለውሾች፡ አትስጡ፡ ዕንቋችሁንም፡ በእሪያ፡ ፊት፡ አትጣሉ፡ በእግራቸው፡ እንዳይረግጡት፡ ተመልሰውም፡ እንዳይነክሱችሁ። ሐጌ፡ ፪፡ ፲፪።

፯ ለምኑ፡ ይሰጣችኋል፡ ፈልጉ፡ ታገኛላችሁ፡ ደጅ፡ ምቱ፡ መዝጊያው፡ ይከፈትላችኋልሁ፡ ማርቆ፡

፰ ፳፩። የሚለምን፡ ይወስዳልና፡ የሚፈልግም፡ ያገኛል፡ ደጅ፡ ለሚመታም፡ ይከፈትለታልና፡ ማር፡ ፲፩፡ ፳፬፡ ሉ፡ ፲፩፡ ፱፡ ፲፫፡ ኤር፡ ፳፱፡ ፲፫፡ ፲፬።

፱ በውነት፡ ወይስ፡ ከናንተ፡ ምን፡ ሰው፡ ነው፡ ልጁ፡ እንጀራ፡ ቢለምነው፡ ደንጊያ፡ ይሰጠዋልን፡

፲ ዓሣስ፡ ቢለምነው፡ እባብ፡ ይሰጠዋልን።

፲፩ እንኪያስ፡ እናንተ፡ ክፉዎች፡ ስትሆኑ፡ ለልጆቻችሁ፡ መልካም፡ ስጦታ፡ መስጠት፡ የምታውቁ፡ ከሆናችሁ፡ የሰማዩ፡ አባታችሁማ፡ ለሚለምኑት፡ መልካም፡ ነገር፡ እንዴት፡ አብልጦ፡ ይሰጣቸዋል፡ ማቴ፡ ፲፰፡ ፲፱፡ ያዕ፡ ፩፡ ፲፯።

፲፪ ሰዎችም፡ ሊያደርጉላችሁ፡ የምትወዱትን፡ ሁሉ፡ እናንተም፡ ደግሞ፡ እንዲሁ፡ አድርጉላቸው፡ ኦሪትም፡ ነቢያትም፡ ይህ፡ ነውና። ሉቃ፡ ፮፡ ፴፩፡ ሮሜ፡ ፲፫፡ ፰፡ ፲።

፲፫ በፀበበችው፡ ደጅ፡ ግቡ፡ ወደ፡ ጥፋት፡ የሚወስደው፡ ደጅ፡ የሰፋ፡ ነውና፡ መንገዱም፡ የተዘረጋ፡ ነውና፡ ወደ እርሱም፡ የሚገቡ፡ ብዙ፡ ናቸው፡ ሉቃ፡ ፲፫፡ ፳፬።

፲፬ ወደ፡ ሕይወት፡ የምትመራው፡ ግን፡ ደጂቱ፡ የጠበበች፡ መንገዱም፡ የቀጠነች፡ ናትና፡ የሚገቡባትም፡ የሚያገኙዋ

ቱ ምን፡ዋቄቶችን፡ናቸው፡ማቴ፡፲፱፡

፲፭ ፳፬፡ዮሐ፡፲፬፡፳፬ የበግ፡ለምድ፡ለብሰው፡ከሚመጡባችሁ፡ከሐሰተኞች፡ነቢያት፡ተጠንቀቁ፡በውሥጣቸው፡ግን፡ነጣቂዎች፡ተኵላዎች፡ናቸው፡ቀምጽ፬፡፬፡፫፡፳፬፡የ

፲፮ ሐዋ፡፳፡፳፱ ተበፍሬያቸው፡ታውቋቸዋላችሁ፡ከእሾህ፡ወይን፡ከአሜከላስ፡በለስ፡ይለቀማልን፡ገላ፡፫ ፲፱፡፳፮፡ያዕ፡፫፡፲፪፡

፲፯ እንዲሁ፡መልካም፡ዛፍ፡ሁሉ፡መልካም፡ፍሬ፡ያፈራል፡ክፉ፡ዛፍ፡ግን፡ክፉ፡ፍሬ፡ያፈራል፡ሉቃ፡፮፡፵፫፡

፲፰ መልካም፡ዛፍ፡ክፉ፡ፍሬ፡ማፍራት፡አይቻለውም፡ክፉም፡ዛፍ፡መልካም፡ፍሬ፡ማፍራት፡አይቻለው

፲፱ ም፡መልካም፡ፍሬ፡የማያፈራ፡ዛፍ፡ሁሉ፡ይቈረጣል፡ወደ፡እሳትም፡ይጣላል፡ማቴ፡፫፡፲፡ዮሐ፡፲፭

፳ ፮፡፪፡ስለዚህም፡ከፍሬያቸው፡ታ

፳፩ ውቋቸዋላችሁ፡አቤቱ፡አቤቱ፡የሚሉኝ፡ሁሉ፡መንግሥተ፡ሰማያት፡የሚገባ፡አይደለም፡በሰማይ፡ያለውን፡ያባቴን፡ፈቃድ፡የሚያደርግ፡ነው፡እንጂ፡ሮሜ፡፪፡፲፫፡

፳፪ በዚያች፡ቀን፡ብዙች፡ይሉኛል፡አቤቱ፡አቤቱ፡በስምህ፡ትንቢት፡የተናገርን፡አይደለንምን፡በስምህ፡አጋንንት፡ያወጣን፡አይደለንምን፡በስምህ፡ብዙ፡ኃይል፡አላደረግንምንን፡፲፫፡ሉቃ፡፳፮፡፳፯፡፩ቆሮ፡፲፫፡፩፡፪፡፡

፳፫ በዚያም፡ጊዜ፡በውነት፡አላቸዋለሁ፡እናንተ፡ኃጢአትን፡የምትሠሩ፡ከቶ፡አላወቅኋችሁም፡ከእኔም፡ራቁ፡ቀምጽ፮፡ማ፩፡፰፡ጢሞ፡፰፡፲፱፡

፳፬ ስለዚህ፡ይህን፡የኔን፡ነገር፡የሚሰማው፡ሁሉ፡የሚያደርገውም፡ቤቱን፡በድንጊያ፡ላይ፡የሠራ፡ጠቢብ፡ብልህ፡ሰውን፡ይመስላል፡ቀ፡፮፡ዮሐ፡፲፫፡፲፯፡

፳፭ ዝናብ፡ዘነበ፡ጐርፍም፡ጐረፈ፡ነፋስም፡ነፈሰ፡ያንንም፡ቤት፡ገፋት፡በድንጊያ፡ላይ፡ተመሥርቷል

፳፮ ና፡አልወደቀም፡ይህንም፡የኔን፡ነገር፡ሰምቶ፡የማያደርገው፡ሰው፡ሁሉ፡ቤቱን፡በአሸዋ፡ላይ፡የሠራ፡ሰነፍ፡ሰውን፡ይመስላልቁም፲፯፡፲

፳፯ ፲፪፡ዝናብ፡ዘነበ፡ጐርፍም፡ጐረፈ፡ነፋስም፡ነፈሰ፡ያንንም፡ቤት፡ገፋት፡ወደቀም፡አወዳደቁም፡ታላቅ፡ሆነ፡ሕዝ፲፫፡፲፡፲፩፡፡

፳፰ ኢየሱስም፡ይህን፡ተናግሮ፡በጨረሰ፡ጊዜ፡የተሰበሰቡት፡ሕዝብ፡በትምርቱ፡ተደነቁ፡ማር፩፡፳፪፡ሉቃ፡፬፡፴፪፡

፳፱ ሥልጣን፡እንዳለው፡ያስተምራቸው፡ነበርና፡እንደ፡ጸሐፎቻቸው፡አይደለም፡ዮሐ፯፡ማ፯፡ኢሳ፡፶፩፡፲፮፡፡

ምዕራፍ፡፰

ከተራራ፡ስለ፡መውረዱና፡ስለ፡ለምጻሙ፡መምጣት፡ስለ፡የመቶ፡አለቃ

ሌጅ፡መጻን፥ስለ፡ጴጥሮስ፡አማት
መዳን፥ስለድውያን፡መፈወስ፡ስለ
አንድ፡ጸሐፊ፡መከተል፥አባቱን፡
ለመቀበር፡ስለ፡ጠየቀው፥ደቀ፡
መዝሙር፡ወደ፡ታንኳ፡ስለ፡መግ
ውጣትና፡ስለ፡ማዕበል፡መነሣት
ጋኔን፡ስለ፡አደረባቸው፡ሰዎችና፡
ስለ፡እሪያ፡መንጋ፨

፩ ከተራራውም፡በወረደ፡ጊዜ፡ብዙ
ሕዝብ፡ተከተሉት፡ማር፩፡፵፡፵

፪ ፬፡ሉቃ፡፭፡፲፪፡፲፬፨እነሆ፡ለምጻ
ምም፡መጣ፡ሰግዶለትም፡እንዲህ
ሲል፡አቤቱ፡አቤቱ፡ብትፈቅድስ
አኔን፡ማንፃት፡ይቻልሃል፨

፫ ኢየሱስም፡እጁን፡ዘረጋና፡ዳሰሰ
ው፡እንዲህ፡ሲል፡እፈቅዳለሁ፡
ንጻ፡በዚያ፡ጊዜም፡ከለምጹ፡ነፃ

፬ ኢየሱስም፡ለሰው፡ተጠንቀቅ፡ለ
ማንም፡አትናገር፡ነገር፡ግን፡ሒ
ደህ፡ራስህን፡ለካህን፡አሳይ፡ሙሴ
ም፡ያዘዘውን፡ቍርባኑን፡አቅር
ብ፡ምስክር፡ይሆንባቸው፡ዘንድ
ም፩፡፵፡ማር፪፡፵፪፡ዘሌ፲፬፡፪፨

፭ ኢየሱስም፡ወደ፡ቅፍርናሆም፡
በገባ፡ጊዜ፡የመቶ፡አለቃ፡ወደ፡እ
ርሱ፡መጣ፡ከእርሱ፡ሲሻ፡እንዲህ
ሲል፥ሉቃ፡፯፡፩፡፲፨

፮ አቤቱ፡ብላቴናዬ፡በጽኑ፡ሥቃይ
ድውይ፡ሁኖ፡በቤት፡ወድቋል፨

፯ ኢየሱስም፡እኔ፡መጥቼ፡እፈው

፰ ሰዋለሁ፡አለው፨የመቶ፡አለቃ
ውም፡መልሶ፡አለው፡አቤቱ፡ወ
ደ፡ቤቴ፡ጣራ፡ትገባ፡ዘንድ፡አ
ይገባኝም፡ነገር፡ግን፡አንዲት፡
ቃል፡ብቻ፡ተናገር፡ብላቴናዬ

፱ ም፡ይድናል፨እኔም፡ደግሞ፡የም
ገዛ፡ሰው፡ነኝና፡በበታቼም፡ጭ
ፍራ፡አለኝ፡ይህንም፡ሒድ፡እለ
ዋለሁ፡ይሔዳልም፡ሌላውንም
ና፡እለዋለሁ፡ይመጣልም፡ሎሌ
ዬንም፡ይህን፡አድርግ፡ብለው፡

፲ ያደርጋል፨ኢየሱስም፡ይህን፡በ
ሰማ፡ጊዜ፡ተደነቀ፡ለሚከተሉት
ም፡አለ፡በእስራኤል፡እንኳ፡ይህን
ያህል፡እምነት፡እንዳላገኘሁ፡በ
ውነት፡እነግራችኋለሁ፨[illegible]፲፫

፲፩ ፳፱፨እላችኋለሁም፡ከምሥ
ራቅና፡ከምዕራብ፡ብዙ፡ይመ
ጣሉ፡በመንግሥት፡ሰማያትም
ከአብርሃምና፡ከይስሐቅ፡ከያዕ
ቆብም፡ጋራ፡ይቀመጣሉ[illegible]ሳ፵
፱፡፲፪፡ሉቃ፡፲፫፡፳፰፡፳፱፨

፲፪ የመንግሥት፡ልጆች፡ግን፡ወደ፡
አፍአዊ፡ጨለማ፡ሊቀቡ፡ጥርስ
ማፋጨት፡ወደ፡አለበት፡ይወድ
ቃሉ፨ም፳፪፡፲፫፡፳፬፡፶፩፡፳፭፡፴

፲፫ ኢየሱስም፡ለመቶው፡አለቃ፡ሒ
ድ፡እንደ፡እምነትህ፡ይሁንልህ፡አ
ለው፡ብላቴናውም፡በዚያች፡ሰ
ዓት፡፱ዳነ፨ም፱፡፳፱፡፲፭፡፳፰፡

፲፬ ኢየሱስም፡ወደ፡ጴጥሮስ፡ቤት፡በ
ገባ፡ጊዜ፡አማቱ፡በመኝታ፡በንዳ

ዱ፡በሽታ፡ወዱቃ፡እየማር፡፩፡፳
፱፡፴፩፡ሉቃ፡፬፡፴፰፡፴፱ቍ
፲፭ [..]ዷኝም፡ዲሰሳት፡መኛሾዋም፡
[..]ዋት፡ተነሥታም፡አገለገለቻ
፲፮ [..]ውቍበመሸም፡ጊዜ፡ሰይጣኛ
[..]ደረባቸውኝ፡ብዙ፡ሰዎች፡አ
[..]መጡለት፡መናፍስቱኝም፡በ
ቃሉ፡ያወጣ፡ነበረ፡በክፉም፡ደዌ
የተያዙትኝ፡ሁሉ፡አዳነቍ
፲፯ በነቢዩ፡በኢሳይያስ፡የተባለው
ዱፈጸም፡ዘንድ፡እኛዴ፡ህ፡ሲል
እርሱ፡ደዌያችነን፡ወሰዴ፡ሕማ
ማችነንም፡ተሸከመቍኢሳ፡፶፫
፲፰ [..]ኢየሱስም፡በዙርያው፡
[..]ሰበሰቡትኝ፡ብዙ፡ሰዎች፡ባ
የ[..]ጊዜ፡ወደ፡ማዶ፡ይሸገሩ፡ዘን
ድ፡አዘዘቍማር፡፬፡፴፭ቍ
፲፱ አ[..]ድ፡ጸሐፊም፡ወደ፡እርሱ፡መ
ጥ[..]፡መምህር፡ሆይ፡ወደምት
ሄ[..]በት፡ሁሉ፡እንድከተልህ፡
[..]ዲለሁ፡አለውቍሉ፡፱፡፶፯፡፷፩ቍ
፳ [..]የሱስም፡ለቀበሮች፡ጉድጓድ
[..]ላቸው፡ለሰማይ፡ዓሮችም፡
[..]ማረፊያ፡አላቸው፡ለሰው፡ልጅ
ግን፡ራሱን፡የሚያስጠጋበት፡
የለውም፡አለውቍ፪ቆሮ፡፰፡፱፡
፳፩ [..]ደቀ፡መዛሙርቱም፡አንዱ፡አ
ቤቱ፡አስቀድሚ፡ሔጄ፡አባቴን
እንድቀብር፡ፍቀድልኝ፡አለው
፳፪ ነገ፡፲፱፡፳ቍኢየሱስም፡ተከተለ
ኝ፡፤ሙታን፡ሙታኖቻ፡ተዋቸው፡ሙታና
ቸውኝ፡ይቀብሩ፡አለው፡፩፡ጢ፡
፳፫ ፭፡፳ቍወደ፡ታንኳም፡በወጣ፡ጊዜ
ደቀ፡መዛሙርቱ፡ተከተሉት፡
፳፬ እነሆ፡በባሕርም፡ታላቅ፡መናወ
ጥ፡ሆነ፡ከማዕበሉም፡የተነሣ፡ታ
ንኳው፡እስኪሰጥም፡ድረስ፡እር
ሱ፡ግን፡ተኝቶ፡ነበረቍማር፡፬፡፴
፳፭ ፭፡ዮና፡፩፡፬ቍደቀ፡መዛሙርቱ
ም፡ወደ፡እርሱ፡ቀርበው፡አስነ
ሡት፡እንዲህ፡ሲሉ፡አቤቱ፡አድ
ነኝ፡ልናልቅ፡ነውናቍም፲፬፡፴፡
፳፮ እናንተ፡እምነት፡የጎደላችሁ፡
ለምን፡ትፈራላችሁ፡አላቸው፡
በዚያም፡ጊዜ፡ተነሥቶ፡ነፋሳት
ንም፡ባሕሩንም፡ገሠፀ፡ታላቅ፡
ም፡ጸጥታ፡ሆነቍም፲፯፡፳፫ቍ
፳፯ ሰዎቹ፡ግን፡ይህ፡ማነው፡ነፋሳት
ና፡ባሕር፡የሚታዘዙለት፡እያሉ
አደነቁቍመዝ፡፷፭፡፯፡፹፱፡፱፡፲፭
፳፰ ፴፡ም፡፴፬ቍወደ፡ማዶ፡ወደ፡ጌርጌ
ሴኖን፡አገር፡በመጣ፡ጊዜ፡ጋኔን
ያደረባቸው፡ሁለት፡ሰዎች፡ከመ
ቃብር፡ወጥተው፡ተቀበሉት፡እ
ጅግም፡ክፉዎች፡ነበሩ፡እንድ፡ሰ
ው፡በዚያ፡መንገድ፡ማለፍ፡እ
ስኪሳነው፡ድረስቍማር፡፭፡፩፡
፳፱ እነሆ፡እርሳቸውም፡እንዲህ፡ብለ
ው፡ጮሁ፡የእግዚአብሔር፡ልጅ
ኢየሱስ፡ሆይ፡ባንተና፡በኛ፡መካ
ከል፡ምን፡ነገር፡አለ፡ጊዜው፡ሳይደ
ርስ፡ልትሣቅየን፡ወደዚህ፡መጣ

ሠ ሀንቁሉ፡ ፬፡ ሣ፮፡ ፪፡ ዴጥ፡ ፬፡ ፬ ።
በዚያም፡ ከእርሳቸው፡ እርቃ፡
ብዙ፡ የእሬያ፡ መንጋ፡ ትሰማራ፡
ነበረ ቿ። ዘሌ ፲፮፡ ፳ ።

ሠለ አጋንንትም፡ ከእርሱ፡ ለመኑ፡
እንዲህ፡ ሲሉ፡ ከነዚህስ፡ የምታ
ወጣን፡ ከሆነ፡ ወደ፡ እርያው፡ መ
ንጋ፡ እንድንገባ፡ ፍቀድልን፡ ማር

ሠሐ ፭፡ ፱፡ ፲ እርሱም፡ ሒዱ፡ አላቸው
እርሳቸውም፡ ወጥተው፡ ወደ
እርያው፡ መንጋ፡ ሔዱ፡ እነሆ፡
የእርያው፡ መንጋ፡ ሁሉ፡ እየደ
ነበሩ፡ በገደል፡ አፋፍ፡ ወደ፡ ባሕ
ር፡ ተወረወሩ፡ በውኃም፡ ውስ

ሠመ ጥ፡ ሞቱ። እረኞቹ፡ ግን፡ እየሸ
ሹ፡ ወደ፡ መንደር፡ ሔዱ፡ ነገሩን
ም፡ ጋኔን፡ ባደረባቸውም፡ የሆ

ሠሠ ነውን፡ ሁሉ፡ አወሩ፡ እነሆ፡ ኢየ
ሱስንም፡ ለመቀበል፡ መንደሩ፡ ሁ
ሉ፡ ወጣ፡ ባዩትም፡ ጊዜ፡ ከአገራ
ቸው፡ እንዲሔድ፡ ለመኑት።
ሉቃ፡ ፰፡ ፲፬፡ የሐዋ፡ ፲፮፡ ፴፱ ።

ምዕራፍ፡ ሀ ።

ስለ፡ አንዱ፡ መጻጉዕ፡ ስለ፡ ማቴዎ
ስ፡ መጠራትና፡ በማቴዎስ፡ ቤት
ም፡ ስለ፡ መብላት፡ ስለ፡ ዮሐን
ስ፡ ደቀ፡ መዛሙርት፡ በጾም፡ ነ
ገር፡ መጠየቅ፡ የአንዱ፡ መኰን
ን፡ ልጅ፡ ከሞት፡ ስለ፡ ማስነሣት
ስለ፡ ሁለት፡ ዕውራን፡ ጋኔን፡ ስለ
ማውጣት፡ ድውያን፡ ስለ፡ መፈ

ሀ ወስ። ወደ፡ ታንኳም፡ በገባ፡ ጊዜ
ወደ፡ ማዶ፡ ተሻገረ፡ ወደ፡ ከተማ
ውም፡ መጣ። ማቴ፡ ፬፡ ፲፫፡ ማር፡ ፪
፩፡ ፲፪፡ ሉ፡ ፭፡ ፲፪፡ ፳፪ ።

ለ እነሆም፡ ባልጋ፡ ላይ፡ የተኛ፡ [አን]ዱ
መፃጉዕ፡ አመጡለት፡ ኢየሱ[ስ]
ም፡ እምነታቸውን፡ ባየ፡ ጊዜ፡ ል
ጁ፡ ሆይ፡ ጽና፡ አይዞህ፡ ኃጢአት
ህ፡ ተሠረየችልህ፡ አለው። የሐ
ዋ፡ ፱፡ ፴፫፡ ሉ፡ ፲፬፡ ፬ ።

ሐ እነሆም፡ ከጻፎች፡ ወገን፡ በል[ባ]
ቸው፡ ይህስ፡ እግዚአብሔርን፡ ይ
ሳድባል፡ አሉ። ማር፡ ፪፡ ፯ ።

መ ኢየሱስም፡ አሳባቸውን፡ አው[ቆ]፡
አላቸው፡ እናንተ፡ ለምን፡ በል[ባ]
ችሁ፡ ክፉ፡ ታስባላችሁ። ምዕ፲፪
፳፭፡ ዮሐ፡ ፪፡ ፳፭ ።

ሠ ኃጢአትህ፡ ተሠረየችልህ፡ ከ
ማለትና፡ ወይስ፡ ተነሣና፡ ሂ
ድ፡ ከማለት፡ ማናቸው፡ ይ[ቀ]ላ

ረ ል፤ ነገር፡ ግን፡ በምድር፡ ላይ፡ ኃ
ጢአት፡ ለማስተሥረይ፡ ለሰው፡
ልጅ፡ ሥልጣን፡ እንዳለው፡ ታው
ቁ፡ ዘንድ፡ በዚያ፡ ጊዜ፡ መፃጉዕ
ን፡ ተነሣ፡ አልጋህንም፡ ተሸክመ
ህ፡ ወደ፡ ቤትህ፡ ሒድ፡ አለው።

ሰ ተነሥቶም፡ አልጋውን፡ ተሸክ

ሸ ሞ፡ ወደ፡ ቤቱ፡ ሔደ። የተሰበሰቡ
ትም፡ አይተው፡ አደነቁ፡ ለሰው፡
እንዲህ፡ ያለ፡ ሥልጣን፡ የሰጠ፡ እ
ግዚአብሔርንም፡ አመሰገኑ።

፱ ኢየሱስም፡ከዚህ፡ባለፈ፡ጊዜ፡ስ
ሙን፡ማቴዎስ፡የሚሉትን፡ሰው
በመቅረጫ፡ስፍራ፡ተቀምጦ
አየ፡ተከተለኝም፡አለው፡እር
ሱም፡ተነሥቶ፡ተከተለው፨ማ
ር፡፪፡፲፫፡ሉ፡፭፡፳፯፡፵፪፨
፲ በቤቱም፡ለምሳ፡ተቀምጦ፡ሳለ
ብዙ፡ቀራጮችና፡ኃጢአተኞ
ች፡መጥተው፡ከደቀ፡መዛሙ
፲፩ ርቱ፡ጋራ፡ተቀመጡ፨ፈሪሳው
ያንም፡አይተው፡ደቀ፡መዛሙር
ቱን፡መምህራችሁ፡ከቀራጮ
ችና፡ከኃጢአተኞች፡ጋራ፡ለም
ን፡ይበላል፡አሏቸው፨ሉ፡፲፭፡፪
፲፪ ፩ቆሮ፡፭፡፲፩፨ኢየሱስም፡በሰማ
ጊዜ፡አላቸው፡የታመሙ፡እንጂ
ባለጤኖች፡ባለመድኃኒት፡አ
፲፫ ይሹትም፨ነገር፡ግን፡ሒዱም፡
ዕወቁትም፡ይህ፡ምንድር፡ነው፡
ምሕረትን፡እወዳለሁ፡መሥዋዕ
ትንም፡አይደለም፡ኃጥአንን፡ወደ
ንስሐ፡እንጂ፡ጻድቃንን፡ለመጥራ
ት፡አልመጣሁምና፨፩ሳሙ፡፲፭፡
፳፪፡ሆሴ፡፮፡፮፡ምዕ፲፪፡፯፨
፲፬ በዚያ፡ጊዜ፡የዮሐንስ፡ደቀ፡መዛ
ሙርት፡ወደ፡እርሱ፡መጡ፡እንዲ
ህ፡ሲሉ፡እኛና፡ፈሪሳውያን፡ስለ
ምን፡እንጾማለን፡ደቀ፡መ
ዛሙርትህ፡ግን፡አይጾሙም፨
ማር፡፪፡፲፰፡ሉ፡፭፡፴፫፡፴፭።
፲፭ ኢየሱስም፡አላቸው፡በውኑ፡የሙ
ሽራ፡ልጆች፡ሙሽራው፡ከርሳቸ
ው፡ጋራ፡ሳለ፡ያለቅሱ፡ዘንድ፡ይች
ላሉን፡ነገር፡ግን፡ሙሽራው፡ከርሳ
ቸው፡የሚለይበት፡ወራት፡ይመ
ጣል፡በዚያ፡ጊዜ፡ይጾማሉ፨ዮ፡፫፡
፲፮ ፳፱፨ማንም፡ሰው፡ባረጀ፡ልብስ፡
ላይ፡አዲስ፡እራፊ፡የሚጥፍ፡የለ
ም፡የጣፈው፡ይቀዳዋልና፡ሁሉ፡ይቀ
ዳልና፡ቀዳዳው፡የባሰ፡የሰፋ፡ይሆ
ናል፡ዮሐ፡፩፡፲፯፨
፲፯ ባረጀ፡አቁማዳዎች፡ቀርበታ፡አ
ዲስ፡ጠጅ፡የሚያኖር፡የለም፡ይ
ህስ፡ቢሆን፡አቁማዳዎቹ፡ይፈነዳ
ሉ፡ጠጁም፡ይፈሳል፡አቁማዳዎቹ
ም፡ይበሰብሳሉ፨ነገር፡ግን፡አዲሱ
ን፡ጠጅ፡በአዲስ፡አቁማዳ፡ቀርበታ
ያደርጉታል፡ሁለቱም፡ይጠባበቃ
፲፰ ሉ፨ይህንም፡ሲነግራቸው፡እነሆ
አንድ፡መኰንን፡መጥቶ፡ሰገደለት
እንዲህ፡ሲል፡ልጄ፡አሁን፡ሞተች፡
ነገር፡ግን፡መጥተህ፡በላዩዋ፡እጅህ
ን፡አኑርባት፡ትድናለች፨ማር፡፭፡
፳፪፡፵፫፡ሉ፡፰፡፵፩፡፶፮፨
፲፱ ኢየሱስም፡ተነሥቶ፡ከደቀ፡መዛ
፳ ሙርቱ፡ጋራ፡ተከተለው፨እነሆ፡ካ
ሥራ፡ሁለት፡ዓመት፡ጀምሮ፡ደም፡
የሚፈሳት፡ሴት፡በኋላው፡መጣች
፳፩ የልብሱንም፡ጫፍ፡ነካች፨በልብዋ
የልብሱን፡ጫፍ፡ብቻ፡ብነካሁ፡እ
ድናለሁ፡ብላ፡ነበርና፨ምዕ፲፬፡፴፮፡
፳፪ ኢየሱስም፡ተመልሶ፡አያት፡ልጄ፡

ሆይ፡አይዞሽ፡ጽኚ፡እምነትሽ፡አዳ
ነሽ፡ለላት፡ሴቲቱም፡በዚያው፡ሰ
፷፫ ዓት፡ዳነች። ኢየሱስም፡ወደ፡መ
ኰንኑ፡ቤት፡በመጣ፡ጊዜ፡እምቢል
ታ፡የሚነፉ፡ትንና፡የሚጩጩሁት
፷፬ ን፡ሕዝብ፡አየ። ብላቴናይቱ፡ተኛ
ታለች፡እንጂ፡አልሞተችምና፡ከዚህ፡
ውጡ፡አላቸው፡ከነገሩም፡የተነሣ
ሳቁ። ዮሐ፡፲፩፡፲፮፡፲፬፡፳፫።
፷፭ እርሳቸውም፡በወጡ፡ጊዜ፡እርሱ፡
ገባ፡እጅዋንም፡ያዘት፡ብላቴናይ
፷፮ ቱም፡ተነሣች። ዝናው፡በዚያች፡
፷፯ አገር፡ሁሉ፡ወጣ፡ተሰማ። ኢየሱስ
ም፡ከዚያ፡ባለፈ፡ጊዜ፡ሁለት፡ዕው
ሮች፡እየጮሁና፡የዳዊት፡ልጅ፡ማ
፷፰ ረን፡እያሉ፡ተከተሉት። ወደ፡ቤት
ም፡በገባ፡ጊዜ፡ዕውሮቹ፡ወደ፡እርሱ
መጡ፡ኢየሱስም፡ይህን፡ማድረግ
እንዲቻለኝ፡ታምናላችሁን፡አላቸ
ው፡እርሳቸውም፡አዎን፡አቤቱ፡አ
፷፱ ሉት። በዚያም፡ዓይኖቻቸውን፡ዳሰ
ሰ፡እንደ፡ሀ፡ሲል፡እንደ፡እምነታችሁ
፸ ይሁንላችሁ። ምዕ፡፫። ዓይኖቻ
ቸውም፡ተከፈቱ፡ኢየሱስም፡ ማ
ንም፡ሰው፡እንዳያውቅ፡ተጠንቀቁ
ብሎ፡አዘዛቸው፡ምዕ፡፬።
፸፩ እርሳቸው፡ግን፡ከዚያ፡ወጥተው፡
በዚያች፡አገር፡ሁሉ፡አወሩት።
፸፪ እርሳቸውም፡ከወጡ፡በኋላ፡እነሆ
ጋኔን፡ያደረበት፡ዲዳ፡ሰው፡አመጡ
፸፫ ለት። ጋኔኑም፡በወጣለት፡ጊዜ፡ዲዳ
ው፡ተናገረ፡ሕዝቡም፡እንዲህ፡
ያለ፡አልታየም፡እያሉ፡አደነቁ።
፸፬ ፈሪሳውያን፡ግን፡በአጋንንት፡አለ
ቃ፡አጋንንትን፡ያወጣል፡አሉ። ም
፸፭ ዕ፡፳፬። ኢየሱስም፡በከተማው
ም፡በመንደሩም፡ዙርያ፡ሁሉ፡እየ
ሔደ፡በየመስጊዳቸው፡እያስተ
ማረ፡የመንግሥትንም፡ወንጌል፡
እየሰበከ፡በሕዝቡም፡ያለውን፡
ደዌን፡ሁሉ፡ድካምም፡ሁሉ፡እየ
ፈወሰ፡በከተማውም፡በመንደሩ
ም፡ዙርያ፡ይሔድ፡ነበር። ም፬፡፳፫
፸፮ ብዙም፡የተሰበሰቡ፡ባየ፡ጊዜ፡ደከ
መው፡ጠባቂም፡እንደሌላቸው፡በ
ጎች፡ተቅበዝብዘው፡ነበሩና፡አዘ
ነላቸው፡ለደቀ፡መዛሙርቱም፡አ
ላቸው፡መከሩ፡ብዙ፡ነው፡ሠራተ
ኞቹ፡ግን፡ጥቂቶች፡ናቸው። ሉ፡፲፡
፪፡ዮሐ፡፬፡፴፭፡፴፯። ስለዚህም፡ባ
ለመከሩ፡ለመኸር፡ሠራተኞቹን፡
ይሰድ፡ዘንድ። ምዕራፍ፡፲።
ለደቀ፡መዛሙርቱ፡በአጋንንት፡ላ
ይ፡ሥልጣን፡ስለ፡ሰጣቸውና፡ስለ፡
ሰጣቸው፡ስብከት፡ስለ፡ሰደዳቸ
ውና፡ስለ፡መከራቸው፡በምድር
ላይ፡ሰላም፡ለማድረግ፡አልመጣ
ሁም፡ስለ፡ማለቱ። ነቢዩን፡የተቀ
በለ፡የነቢዩን፡ዋጋ፡ይወስዳል፡ስ
፩ ለ፡ማለቱ። አሥራ፡ሁለቱን፡ደቀ፡
መዛሙርቱንም፡ወደ፡እርሱ፡ጠራ
በርኩሳን፡አጋንንትም፡ላይ፡ሥል

ጣናን፡ሰጣቸው፡ያወጧቸው፡ዘ
ንድ፡ደዌን፡ሁሉ፡ሕማምንም፡ሁ
ሉ፡ይፈውሱ፡ዘንድ፤ማር፡፮፡፯፡
፲፫፡ሉ፡፱፡፩፡፫፤ያሥራ፡ሁለቱ፡ሐ
ዋርያት፡ስማቸው፡ይህ፡ነው።
መጀመሪያው፡ጴጥሮስ፡የተባለ
ው፡ስምዖን፡ወንድሙ፡እንድር
ያስም፡የዘብዴዎስ፡ልጅ፡ያዕቆ
ብ፡ወንድሙ፡ዮሐንስም፤ማር፡፫
፲፬፡ሉ፡፮፡፲፬፡ዮሐ፡፩፡፵፪።
ፊልጶስ፡በርተሎሜዎስ፡ቶማስ
ቀራጩም፡ማቴዎስ፡የእልፍዮስ
ልጅ፡ያዕቆብ፡ታዴዎስ፡የተባለ
ው፡ልብድዮስም፤ቀነናዊ፡ስምዖ
ን፡የአስቆሮቱ፡ይሁዳም፡እርሱም
አሳልፎ፡የሰጠው፤ኢየሱስ፡እነ
ዚህን፡አሥራ፡ሁለቱን፡ላካቸ
ው፡አዘዛቸውም፡እንዲህ፡ብ
ሎ፡በአሕዛብ፡መንገድ፡አትሒዱ
ወደ፡ሳምራውያንም፡ከተማ፡አ
ትግቡ፤ነገር፡ግን፡ከ፳ል፡ወደ
ጠፉ፡በጎች፡ሒዱ፤ም፲፭፡፳፬፡
የሐዋ፡፲፫፡፵፮፤በሒዳችሁም
ጊዜ፡መንግሥተ፡ሰማያት፡ቀ
ርባለች፡እያላችሁ፡ስበኩ፤ም፫
፲፪፤ድውያንን፡ፈውሱ፡ለም
ጻሞችን፡አንጹ፡ሙታንን፡አን
ሡ፡አጋንንትን፡አውጡ፤በከንቱ
የወሰዳችሁትን፡በከንቱ፡ስጡ።
የሐዋ፡፳፡፴፫፤ወርቅም፡ብር
ም፡ናስም፡በመቀነታችሁ፡አት

ቋጥሩ፤ለመንገድም፡የስንቅ፡ከ
ረጢት፡ሁለት፡ልብስም፡ጫማ
ም፡በትርም፡አትያዙ፤ለሠራተ
ኛ፡ምግቡ፡ይገባዋልና፤፩ጢሞ፡
፭፡፲፰፤ወደ፡ማናቸውም፡ከተ
ማ፡ወይ፡መንደርም፡ብትገቡ፡በር
ሷ፡ያለ፡የሚገባው፡ማነው፡ጠይ
ቁ፡እስክትወጡም፡ድረስ፡በዚያ
ተቀመጡ፤የሐዋ፡፲፫፡፵፮፤
ወደ፡ቤትም፡በገባችሁ፡ጊዜ፡ሰላ
ምታ፡ስጡት፤ሉቃ፡፲፡፭፡፡ቤቱም
የሚገባው፡ቢሆን፡ሰላማችሁ፡
ይደርበት፡ባይገባው፡ግን፡ሰላማ
ችሁ፡ይመለስላችሁ፤ኢሳ፡፵፰፡፳፪
የማይቀበላችሁም፡ቃላችሁን
ም፡የማይሰማ፡ከዚያው፡ቤት፡
ወይም፡ከዚያች፡ከተማ፡ወጥታ
ችሁ፡የእግራችሁን፡ትቢያ፡አራ
ግፉ፤ሉ፡፲፡፲፩፡የሐዋ፡፲፫፡፶፩፤
በፍርድ፡ቀን፡ከዚያች፡ከተማ፡ይ
ልቅ፡ለሰዶምና፡ለገሞራ፡እንዲቀ
ልላቸው፡ዕረፍት፡እንዲሆን፡በእ
ውነት፡እነግራችኋለሁ፤ቅም፲፩
፳፬፡ሉ፡፳፬፡ማ፫፡ሐዝ፡፲፯፡ማ፳፫፡
፱፫፤እነሆ፡እኔ፡እንደ፡በጎች፡በተኩ
ላዎች፡መካከል፡እሰዳችኋለሁ
እንደ፡እባብ፡ጠቢባን፡እንደ፡ርግ
ብ፡የዋሆች፡ሁኑ፤ሉ፡፲፫፡ሮሜ፡፲፮
፲፱፡ኤፌ፡፫፡፲፭፤ነገር፡ግን፡ወደ
ሸንጎ፡ይወስዷችኋልና፡በምኩ
ራባቸውም፡ይገርፏችኋልና፡ከ

ሲዎች፡ተጠበቁ። ማቴ፡፳፬፡፱፡
ማር፲፫፡፱፡፲፫። ሉ፡፳፩፡፲፪፡፲፯።
፲፰ ስለእኔም፡ወደ፡ለሰዎች፡ወደ፡ነገ
ሥታትም፡ይወስዷችኋል፡ለር
ሳቸውም፡ለአሕዛብም፡ምስክ
ር፡ይሆኑባቸው፡ዘንድ። ምዕ፳፬፡
፱፡፲፬፡የሐዋ፡፳፭፡፳፫፡፳፯፡፳፬።
፲፱ አሳልፈውም፡በሰጧችሁ፡ጊዜ፡እ
ንዴት፡ስ፡ወይም፡ምን፡እንድትናገ
ሩ፡አትጨነቁ፡የምትናገሩት፡በ
ዚያች፡ሰዓት፡ይሰጣችኋልና።
፳ ሉ፡፲፪፡፲፩። እናንተ፡የምትናገሩ
ት፡አይደላችሁምና፡የሚናገር
ባችሁ፡የሰማዩ፡አባታችሁ፡መን
ፈስ፡ነው፡እንጂ፡፩ቆሮ፡፪፡፬።
፳፩ ወንድምም፡ወንድሙን፡አባትም
ልጁን፡ለሞት፡አሳልፎ፡ይሰጣል፡
ልጆችም፡በወላጆቻቸው፡ላይ፡ይ
ነሣሉ፡ያስገድሏቸዋልም። ቍ፡፴
፳፪ ፭። ስለ፡ስሜም፡በሰው፡ሁሉ፡ዘን
ድ፡የተጠላችሁ፡ትሆናላችሁ፡እ
ስከ፡ፍጻሜ፡የሚታገሥ፡ግን፡እር
ሱ፡ይድናል። ምዕ፳፬፡፲፫።
፳፫ ከዚህችም፡ቢያሳድዷችሁ፡ወደ
ሌላዪቱ፡ሸሹ፡የሰው፡ልጅ፡እስ
ኪመጣ፡ድረስ፡የ፳ ልኝ፡አገር፡እ
ንዲትጨርሱ፡በውነት፡እነግራ
ችኋለሁና። ምዕ፲፯፡፳፰፡የሐዋ፡፲
፳፬ ፬፡፳፡፳፩። ደቀ፡መዝሙር፡ከመ
ምህሩ፡ሎሌው፡ከጌታው፡አይበ
ልጥም። ሉ፡፮፡፵፡ዮ፡፲፫፡፲፮፡፲፭።

፳፭ ለደቀ፡መዝሙር፡እንደ፡መምህ
ሩ፡ሎሌም፡እንደ፡ጌታው፡ቢሆን፡
ይበቃዋል፡የቤቱን፡ባለቤት፡ብዔ
ልዜቡል፡ካሉት፡የቤቱን፡
ሰዎችስ፡እንዴት፡አብልጠው፡ይ
ሏቸውም። ፲፪፡፳፬፡፳፱፡ዮ፡፰፡፵፰
፳፮ የተሰወረ፡ሳይገለጥ፡የተሸሸገ
ው፡ሳይታወቅ፡አይቀርምና፡እን
ግዲህ፡አትፍሩዋቸው። ሉ፡፲፪፡፪፡
፳፯ ፫። በጨለማ፡የነገርኋችሁን፡
በብርሃን፡ንገሩት፡በጆሮዋችሁ
ም፡በቀስታ፡የሰማችሁትን፡በሰ
ገነት፡ላይ፡ሆናችሁ፡አስተምሩ።
ማር፡፬፡፳፪። ሉ፡፰፡፲፯።
፳፰ ሥጋን፡ከሚገድሉ፡አትፍሩ፡ነፍ
ስን፡ግን፡መግደል፡አይቻላቸው
ም፡ነገር፡ግን፡ሥጋንና፡ነፍስን፡በ
ገሃነም፡ማጥፋት፡ከሚቻለው፡ከእ
፳፱ ርሱ፡እጅግ፡ፍሩ። ሁለት፡ድንቢ
ጦች፡ባንድ፡ድሪም፡ጧሳ፡ይሸጡ
የለምን፡ከርሳቸው፡እንዲ[illegible]፡ይ
ስ፡አባታችሁ፡ፈቃድ፡በምድር፡
፴ ሳይ፡አትወድቅም። የእናንተስ
የራስ፡ጸጕራችሁ፡ሁሉ፡የተቈጠ
፴፩ ረ፡ነው። እንግዲህም፡አትፍሩ
ከብዙ፡ድንቢጦች፡እናንተ፡ትሻ
፴፪ ላላችሁና። በሰው፡ፊት፡የሚያ
ምንብኝ፡ሁሉ፡እኔም፡ደግሞ፡በ
ሰማይ፡ባለው፡ባባቴ፡ፊት፡አም
፴፫ ነዋለሁ። ሮሜ፡፲፱፡፲፡ በሰው፡ፊ
ት፡የካደኝን፡ግን፡እኔም፡ደግሞ፡

በሰማዩ፡አባቴ፡ፊት፡እክደዋለ
ሁ፨ሉ፡፱፡፳፮፡፪፡ጢሞ፡፪፡፲፪፨
፴፬ በምድር፡ሰላም፡ለማድረግ
የመጣሁ፡አይምሰላችሁ፡ሰይ
ፍን፡እንጂ፡ሰላም፡ለማድረግ፡አ
ልመጣሁምና፨ሉ፡፲፪፡፶፩፡፶፫፨
፴፭ ወንድ፡ልጅን፡ካባቱ፡ሴት፡ልጅን
ከናቷ፡ምራትን፡ካማቷ፡እለይ
፴፮ ዘንድ፡መጥቻለሁና፨የሰውም
ጠላቶቹ፡ቤተ፡ሰዎቹ፡ይሆኑታል
፴፯ ከእኔም፡ይልቅ፡አባቱን፡እናቱን፡
የሚወድ፡ለኔ፡ሊሆን፡አይገባው
ም፡ወንድ፡ልጁን፡ሴት፡ልጁን፡ከ
ኔ፡ይልቅ፡የሚወድ፡ለኔ፡ሊሆን፡አ
ይገባውም፨ዘዳ፡፴፫፡፱፡ሉ፡፲፬፡
፴፰ ፳፮፨መስቀሉንም፡ተሸክሞ፡
በኋላዬ፡የማይከተለኝ፡ለኔ፡ሊሆ
ን፡አይገባውም፨ም፲፮፡፳፬፡፳፭
ማር፰፡፴፬፡፴፭፡ዮሐ፡፲፪፡፳፭፨
፴፱ ነፍሱን፡የሚያገኛት፡ሁሉ፡ያጠፋ
ታል፡ነፍሱንም፡ስለ፡እኔ፡ያጠፋ፡
ያገኛታል፨ሉ፡፲፯፡፴፫፡ዮሐ፡፲፪፡
፵ ፳፭፨እናንተን፡የሚቀበላችሁ፡
እኔን፡ተቀበለኝ፡እኔንም፡የሚቀ
ባለኝ፡የላከኝን፡ተቀበለ፨ም፲፰፡
፭፡ሉ፡፲፪፡ዮሐ፡፲፡፲፫፡፳፨
፵፩ ነቢዩን፡በነቢይ፡ስም፡የተቀበለ፡
የነቢዩን፡ዋጋ፡ይወስዳል፡ጻድ
ቁንም፡ስም፡ጻድቁን፡የተቀበለ፡የ
፵፪ ጻድቁን፡ዋጋ፡ይወስዳል፨በደቀ፡
መዝሙር፡ስም፡ከነዚህ፡ከታናና
ኞቹ፡ላንዱ፡አንድ፡ጽዋ፡ቀዝቃዛ፡
ውኃ፡የሚያጠጣ፡ዋጋው፡እንዳይ
ጠፋ፡በውነት፡እነግራችኋለሁ፡
ም፳፭፡፵፨ምዕራፍ፡፲፩፡
ዮሐንስ፡በግዞት፡ሳለ፡ወደ፡ክርስቶ
ስ፡መላክተኞች፡ስለ፡መላኩ፤ዮሐን
ስ፡ከሁሉ፡እንዲበልጥ፤ስለ፡መናገ
ሩ፤በገበያ፡ስለ፡ተቀመጡ፡ልጆች
ምሳሌ፤ስለ፡ቤተ፡ሳይዳ፡ስለ፡ኰ
ራዚ፤ስለ፡ቅፍርናሆም፡ጥፋት፤
ሸክም፡ስለከበዳቸው፡ሰዎች፡ስለ
፩ ማቀለል፨ኢየሱስም፡ለአሥራሁ
ለቱ፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡ትእዛዙን፡
በፈጸመ፡ጊዜ፡በያገራቸው፡ያስተ
ምርና፡ይሰብክ፡ዘንድ፡ከዚያ፡እለ
፪ ፈ፨ሉ፡፯፡፲፰፡፴፭፨ዮሐንስም፡በግ
ዞት፡ቤት፡ሳለ፡የክርስቶስን፡ሥራ
በሰማ፡ጊዜ፡ከደቀ፡መዛሙርቱ፡ሁ
፫ ለቱ፡ላከ፨ም፲፬፡፫፨የሚመጣው፡አ
ንተ፡ነህን፡ወይስ፡ሌላውን፡እንጠብ
ቅን፡አለው፨ሚልክ፡፫፡፩፡ዮሐ፡፩፡፴
፬ ፬፨ኢየሱስም፡እንዲህ፡ብሎ፡መ
ለሰላቸው፡ሒዱ፡ያያችሁትን፡የሰ
ማችሁትንም፡ለዮሐንስ፡ንገሩት፡
፭ ዕውሮች፡ያያሉ፡አንካሶችም፡ይ
ሔዳሉ፡ለምጻሞችም፡ይነፃሉ፡ደ
ንቆሮችም፡ይሰማሉ፡የሞቱትም
ይነሣሉ፡ለድኆችም፡ወንጌል፡ይ
ሰበካል፨ኢሳ፡፴፭፡፭፡፷፩፡፩፨
፮ በእኔም፡የማይሰናከል፡ምስጉን፡
ነው፨ም፲፫፡፶፯፡፳፮፡፴፩፨

፯ እነዚያም ፡ ከሔዱ ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ
ለተሰበሰቡት ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ዮሐን
ስ ፡ ሊናገር ፡ ጀመረ ፡ ምን ፡ ልታዩ ፡ ወ
ደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወጣችሁ ፡ ነፋስ ፡ የ
ሚወዘውዘው ፡ ሸምበቆ ፡ ነውን ፧
፰ ምዕ ፡ ፫ ፡ ፭ ፡ ዮሐ ፭ ፡ ፴፭ ። ወይስ ፡ ምን
ልታዩ ፡ ወጣችሁ ፡ ቀጭን ፡ ልብስ ፡
የለበሰውን ፡ ሰውን ፡ ነውን ፡ እነሆ ፡ ቀ
ጭን ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፡ በነገሥታት ፡
፱ ቤት ፡ ይኖራሉ ። ወይስ ፡ ምን ፡ ልታ
ዩ ፡ ወጣችሁ ፡ ነቢይን ፡ ነውን ፡ አዎ
ን ፡ እላችኋለሁ ፡ እርሱ ፡ ከነቢያት
ይበልጣልና ። ሉ ፡ ፩ ፡ ፸ ፡ ፮ ።
፲ ስለ ፡ እርሱ ፡ የተጻፈለት ፡ ይህ ፡ ነው
ና ፡ እነሆ ፡ መንገድህን ፡ በፊትህ ፡ የ
ሚጸርግ ፡ መልክተኛዬን ፡ በፊት
ህ ፡ እሰጻለሁ ። ሚልክ ፡ ፫ ፡ ፩ ።
፲፩ ከሴቶች ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ ከመጥም
ቁ ፡ ዮሐንስ ፡ የሚበልጥ ፡ እንዳልተ
ነሣ ፡ እውነት ፡ እነግራችኋለሁ ፡ በ
መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ግን ፡ የሚያ
ንሰው ፡ ይበልጠዋል ። ዘካር ፡ ፲፬ ፡ ፳
፲፪ ም ፲፫ ፡ ፲፪ ። ከመጥምቁ ፡ ዮሐንስ
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ መንግ
ሥተ ፡ ሰማያት ፡ በብርቱ ፡ ትገፋለ
ች ፡ የሚገፏት ፡ በኃይል ፡ ይናጠቋ
፲፫ ታል ። ነቢያትም ፡ ሁሉ ፡ ኦሪትም ፡
እስከ ፡ ዮሐንስ ፡ ትንቢት ፡ ተናግረ
፲፬ ዋልና ። ትቀበሉትም ፡ ዘንድ ፡ ት
ወዱ ፡ እንደሆነ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ያለ
ው ፡ ኤልያስ ፡ እርሱ ፡ ነው ። ሚልክ
፬ ፡ ፭ ፡ ማቴ ፡ ፲፯ ፡ ፲ ፡ ፲፫ ።
፲፭ የሚሰማ ፡ ጆሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ።
፲፮ ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ትውልድ ፡ በምን ፡
አመስለዋለሁ ፡ በገበያ ፡ ተቀምጠ
ው ፡ ባልንጀሮቻቸውን ፡ የሚጠሩ
፲፯ ልጆችን ፡ ይመስላሉ ። የሚሉም
አምቢልታ ፡ እየነፋን ፡ ዘፈንንላች
ሁ ፡ አልዘፈናችሁም ፡ አለቀስንላ
ችሁ ፡ አላለቀሳችሁም ። ምሳሌ ፡ ፳፱
፲፰ ዮሐንስ ፡ ሳይበላ ፡ ሳይጠጣ ፡ መጥቶ
አልና ፡ ጋኔን ፡ አለበት ፡ አሉት ። ምዕ ፫
፲፱ ፬ ። የሰው ፡ ልጅ ፡ እየበላ ፡ እየጠጣ ፡
መጣ ፡ እነሆ ፡ የሚበላ ፡ ጠጅም ፡ የ
ሚጠጣ ፡ ሰው ፡ የቀራጮችና ፡ የኃ
ጢአተኞች ፡ ወዳጅ ፡ ነው ፡ አሉት ፡
ጥበብም ፡ ከልጆችዋ ፡ ጸደቀች ፡፡
ም ፡ ፱ ፡ ፲፩ ፡ ሉ ፡ ፲፭ ፡ ፴፱ ።
፳ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ ከሁሉ ፡ የ
ሚበዛ ፡ ያደረገባቸውን ፡ አገሮች
ንስሐ ፡ አልገቡምና ፡ ይነቅፍ ፡ ጀመ
፳፩ ረ ። ሉ ፡ ፲ ፡ ፲፫ ። ወዮልሽ ፡ ኮራዚ
ሆይ ፡ ወዮልሽ ፡ ቤተ ፡ ሳይዳ ፡ ሆይ ፡
በናንተ ፡ የተደረገው ፡ ኃይል ፡ በጢ
ሮስና ፡ በሲዶና ፡ ተደርጎ ፡ በሆነ ፡ ማ
ቅ ፡ ለብሰው ፡ አመድ ፡ ነስንሰው ፡ አስ
ቀድመው ፡ ንስሐ ፡ በገቡ ፡ ነበርና ።
ዮናስ ፡ ፫ ፡ ፮ ፡ ሉ ፡ ፲ ፡ ፲፫ ።
፳፪ ነገር ፡ ግን ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ከናንተ ፡
ይልቅ ፡ ለጢሮስና ፡ ለሲዶና ፡ የተሻ
ለ ፡ እንዲሆን ፡ እነግራችኋለሁ ።
፳፫ አንቺም ፡ ቅፍርናሆም ፡ ሆይ ፡ እስ

ከ፡ሰማይ፡ከፍ፡ያልሽ፡ብትሆኚ
ወደ፡ሲኦል፡ትወርጃለሽ፡ባንቺ፡
የተደረገው፡ኃይል፡በሰዶም፡ተ
ደርጎ፡ቢሆን፡እስከ፡ዛሬ፡በኖረች
ነበር፨ም፬፡፲፫፡ኢሳ፡፲፬፡፲፭፡ሕዝ
፳፬ ፲፮፡፵፱፨ነገር፡ግን፡በፍርድ፡ቀ
ን፡ካንቺ፡ይልቅ፡የሰዶም፡ምድ
ር፡ዕረፍት፡እንድታገኝ፡እነግራ
ችኋለሁ፨ም፡፲፡፲፭፨

፳፭ በዚያ፡ጊዜ፡ኢየሱስ እንዲህ፡ብሎ
ተናገረ፡አባት፡ሆይ፡የሰማይና፡
የምድር፡ጌታ፡ይህን፡ከብልሃተኞ
ችና፡ካዋቆች፡ስለ፡ሠወርህ፡ለሕ
ፃናትም፡ስለ፡ገለጽህላቸው፡አ
መሰግንሃለሁ፨ሉ፡፲፡፳፩፡፳፪፨
፳፮ አዎን፡አባት፡ሆይ፡ፈቃድህ፡በፊ
፳፯ ትህ፡እንዲህ፡ነበረችና፨ከአባቴ፡
ዘንድ፡ሁሉ፡ተሰጠኝ፡ከአብ፡በቀ
ር፡ወልድን፡የሚያውቅ፡ማንም
የለም፤አብንም፡ከወልድ፡ሊገ
ልጽለት፡ከሚወደው፡በቀር፡ማ
ንም፡አያውቀውም፨ሉ፡፲፡፳፪፡፲
፳፪፡ዮሐ፡፫፡፴፭፡ፊልጵ፡፪፡፱፨
፳፰ እናንተ፡ደካሞች፡ሸክማችሁ፡
ም፡የከበደ፡ወደእኔ፡ኑ፡እኔም፡እ
ሳርፋችኋለሁ፨ም፡፲፬፡፳፡ኢሳ፡፵፭
፳፱ ፡፳፪፡ኤር፡፴፩፡፳፭፨ቀምበሬን፡
በላያችሁ፡ተሸከሙ፡ከእኔም፡
ተማሩ፡እኔም፡የዋህ፡ነኝና፡ልቤ
ም፡ትሑት፡ነውና፡ለነፍሳችሁም
ዕረፍት፡ታገኛላችሁ፡ኤር፡፮፡፲፮
፴ ቀምበሬ፡ልዝብ፡ነውና፡ሸክሜ፡
ም፡ቀሊል፡ነው፨፩ዮሐ፡፭፡፫።

ምዕራፍ ፲፪ ።

ጌታችን፡በሰንበት፡በእርሻ፡መካከ
ል፡ስለ፡መሔዱና፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡
እሸት፡እየቀረጡ፡ስለ፡መብላታ
ቸው፡ስለ፡ቀደሚት፡ሰንበት፡ክ
ርክር፤እጁ፡ስለ፡ሰለለች፡ሰው፡ዕ
ውርና፡ድዳ፡ስለማዳኑ፤ስለ፡ብዔ
ል፡ዜቡል፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ላይ
የሚሳደብ፡ኃጢአቱ፡እንደማይ
ሠረይለት፤ስለ፡ፈሪሳውያን፡
ምልክት፡መሻት፤ስለ፡ንግሥተ፡
አዜብ፡ስለ፡መንፈስ፡ርኩስ፨

፩ በዚያ፡ወራት፡ኢየሱስ፡በሰንበት፡በ
እርሻ፡መካከል፡አለፈ፡ደቀ፡መዛሙ
ርቱ፡ተርበው፡ነበሩና፡እሸት፡እ
ያሹ፡ይበሉ፡ጀመሩ፡ማር፡፪፡፳፫፡
፪ ፳፫፡ሉ፡፮፡፩፨ፈሪሳውያንም
ባዩዋቸው፡ጊዜ፡እነሆ፡ደቀ፡መዛ
ሙርትህ፡በሰንበት፡ለማድረግ፡
የማይገባውን፡ያደርጋሉ፡አሉት
፫ ዘፀ፡፳፡፲፨እርሱ፡ግን፡አላቸው፡ዳ
ዊት፡በተራበ፡ጊዜ፡ያደረገውን፡አ
ላነበባችሁትምን፡ከርሱም፡ጋራ
የነበሩት፡በተራቡ፡ጊዜ፤፩ሳሙ
፬ ፳፩፡፮፨ወደ፡ቤተ፡እግዚአብሔ
ር፡እንዴ፡ገባ፡የመሥዋዕቱንም
ኅብስት፡እንዴ፡በላ፡ለካህናት፡ብ
ቻ፡እንጂ፡ለእርሱ፡ከእርሱም፡ጋ
ራ፡ለነበሩት፡የማይገባውን፡ዘሌ፡

፭ ኍ፰፡፱፤ በኦሪትስ፡ ያለውን፡ አላነበ ባችሁምን፡ ካህናት፡ በሰንበት፡ ቀ ን፡ በመቅደስ፡ ሰንበትን፡ ቀደሚን እንደያረክሱ፡ ኃጢአት፡ እይሆን

፮ ባቸውምን፧ ዘኍ፡ ፳፰፡ ፱፤ እኔ፡ ከ መቅደስ፡ የሚበልጥ፡ ከዚህ፡ አለ

፯ እላችኋለሁ፤ ብታውቁስ፡ ምን እንደሆነ፡ ምሕረትን፡ እወዳለሁ፡ መሥዋዕትን፡ አይደለም፡ ኃጢ አትም፡ በሌለባቸው፡ ላይ፡ ባልፈ ረዳችሁም፡ ነበር፤ ሆሴ፡ ፮፡ ፮ ሳ

፰ ሙ፡ ፲፭፡ ፳፪፤ የሰንበት፡ ጌ ታ፡ የሰው፡ ልጅ፡ ነውና፡ ማር፡ ፪፡ ፳፯

፱ ከዚያም፡ ባለፈ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ መስጊ ዳቸው፡ ሔደ፤ ማር፡ ፫፡ ፩፡ ሉ፡ ፮፡ ፯

፲ ፲፩ቀ በዚያም፡ እነሆ፡ የሰለለችው ሰው፡ ነበር፤ ይከሱትም፡ ዘንድ፡ በ ሰንበት፡ መፈወስ፡ ይገባልን፡ ብለ ው፡ ጠየቁት፡ ሉ፡ ፲፬፡ ፫።

፲፩ እርሱም፡ እላቸው፡ ከእናንተ፡ አ ንድ፡ በግ፡ ያለው፡ በሰንበት፡ ቀን፡ ወ ደ፡ ፈረፈር፡ ቢወድቅበት፡ የማይ ዘው፡ የማያወጣውስ፡ ማን፡ ሰው

፲፪ ነው፤ ከበግ፡ ይልቅ፡ ማ፡ ሰው፡ ምን ያህል፡ ይበልጥ፡ እንኪያስ፡ በሰንበ ት፡ መልካም፡ መሥራት፡ ይገባል

፲፫ ሉ፡ ፲፬፡ ፭፤ በዚያም፡ ጊዜ፡ ያንን፡ ሰው፡ እጅህን፡ ዘርጋ፡ አለው፡ እር ሱም፡ ዘረጋት፡ ፈዋናም፡ ደነች፡ እ ንደ፡ ሁለተኛይቱ፡ ሆነች።

፲፬ ፈሪሳውያን፡ ግን፡ በወጡ፡ ጊዜ፡ ሊ ያጠፉት፡ ተማከሩ፡ ዮሐ፡ ፭፡ ፲፰፤

፲፭ ኢየሱስም፡ ይህን፡ ባወቀ፡ ጊዜ፡ ከዚ ያ፡ ወጣ፡ ሔደ፡ ብዙ፡ ሕዝብም፡ ተከተሉት፡ ሁሉንም፡ ፈወሳቸ

፲፮ ው፤ ለማንም፡ እንዳያስታውቁ፡ አዘዛቸው፤ ማር፡ ፫፡ ፯፡ ፲፪፡ ምዕ፡

፲፯ ፩፤ በነቢዩ፡ በኢሳይያስ፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ የተነገረው፡ ይፈጸም፡ ዘንድ፡ ኢሳ፡ ፵፪፡ ፩፡ ፬፤

፲፰ እነሆ፡ ልጄ፡ የመረጥሁት፡ ወዳጄ፡ ነፍሴ፡ የወደደችው፡ መንፈሴን፡ በርሱ፡ ላይ፡ አኖራለሁ፡ ፍርድን ም፡ ለአሕዛብ፡ ይነግራል፤ ምዕ፡ ፫፡ ፲፯

፲፱ እርሱ፡ አይከራከርም፡ አይጮህ ም፡ ድምፁንም፡ በአደባባይ፡ የሚ

፳ ሰማው፡ የለም፤ የተቀጠቀጠ፡ ሸ ምበቆ፡ አይሰብርም፡ የሚጤስ ም፡ የመብራት፡ ፈትል፡ አያጠፋ ም፡ ፍርድን፡ በማሸነፍ፡ እስኪያ

፳፩ መጣ፡ ድረስ፤ አሕዛብም፡ በስሙ ተስፋ፡ ያደርጋሉ፤ ኢሳ፡ ፵፪፡ ፩፤

፳፪ በዚያም፡ ጊዜ፡ ጋኔን፡ ያደረበት፡ ዕ ውር፡ ድዳም፡ የሆነ፡ አመጡለት፡ ዕውሩና፡ ድዳው፡ እስኪናገር፡ እ ስኪያይም፡ ድረስ፡ ፈወሰው፤ ማር፡ ፫፡ ፳፪፡ ሉ፡ ፲፩፡ ፲፬፡ ፵፪ ፤

፳፫ ሕዝቡም፡ ሁሉ፡ የዳዊት፡ ልጅ፡ እ ይደለምን፡ እያሉ፡ ያደንቁ፡ ነበር፤

፳፬ ፈሪሳውያን፡ ግን፡ ሰምተው፡ በሰ ይጣናት፡ አለቃ፡ በብዔል፡ ዜቡል፡ ነ ው፡ እንጂ፡ ይህስ፡ አጋንንት፡ አያወ

ጣም፡ አሉ፡፡ ምዕ ፱፡፴፬፡ ፪፡ ነገ፡ ፩ ፨

፳፭ ኢየሱስም፡ አሳባቸውን፡ አውቆ፡ አላቸው፡ እርስ፡ በርሱ፡ የሚለያይ፡ መንግሥት፡ ይጠፋል፡ እርስ፡ በርሱ፡ የሚለያይ፡ ከተማም፡ ሆነ፡ ቤትም፡ ሆነ፡ አይጸናም ፨

፳፮ ሰይጣንም፡ ሰይጣንን፡ የሚያወጣው፡ ከሆነ፡ እርስ፡ በርሱ፡ ተለያየ፡ እንዴትስ፡ ከሆነ፡ መንግሥቱ፡ እንዴት፡ ይጸናል ፨

፳፯ እኔስ፡ በብዔል፡ ዜቡል፡ ሰይጣናትን፡ የማወጣ፡ ከሆነ፡ ልጆቻቸው፡ በምን፡ ያወጥዋቸዋል፡ ስለዚህም፡ እርሳቸው፡ ፈራጆች፡ ይሆኑባችኋል ፨

፳፰ እኔ፡ ግን፡ በእግዚአብሔር፡ መንፈስ፡ ሰይጣናትን፡ የማወጣ፡ ከሆንሁ፡ እነሆ፡ የእግዚአብሔር፡ መንግሥት፡ እርሷ፡ ወደ፡ እናንተ፡ ቀረበች ፨ ፩፡ ዮሐ፡ ፫፡ ፰

፳፱ ወይስ፡ ሰው፡ አስቀድሞ፡ ብርቱውን፡ ካላሰረ፡ ወደ፡ ብርቱ፡ ቤት፡ ገብቶ፡ ዕቃውን፡ ይነጥቅ፡ ዘንድ፡ እንዴት፡ ይችላል፡ ከዚያ፡ በኋላ፡ ግን፡ ቤቱን፡ ይበዘብዛል ፨ ኢሳ፡ ፵፱፡ ፳፬፡ ፳፭፡

፴ ከእኔ፡ ጋራ፡ ያይደለ፡ ጻላቴ፡ ነው፡ ከኔ፡ ጋራ፡ የማያከማች፡ እርሱ፡ ይበትናል ፨ ማር፡ ፱፡ ፵ ፨

፴፩ ስለዚህ፡ ኃጢአትና፡ ስድብም፡ ሁሉ፡ ለሰው፡ እንዲሠረይ፡ እላችኋለሁ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ላይ፡ ስድብ፡ ግን፡ ለሰው፡ አይሠረይም፡ ዕብ፡ ፮፡ ፬፡ ፮፡ ፲፡ ፳፮፡ ፩፡ ዮሐ፡ ፭፡ ፲፮ ፨

፴፪ በሰው፡ ልጅም፡ ላይ፡ አንዲት፡ ቃል፡ የሚናገር፡ ይሠረይለታል፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ላይ፡ የሚናገር፡ ግን፡ በዚህ፡ ዓለም፡ በሚመጣውም፡ ዓለም፡ ቢሆን፡ አይሠረይለትም ፨ ሉቃ፡ ፲፪፡ ፲፡ ፩፡ ጢሞ፡ ፩፡ ፲፫፡ ፩፡ ዮሐ፡ ፭፡ ፲፮ ፨ ፨

፴፫ መልካም፡ ዛፍ፡ በፍሬዋ፡ ትታወቃለች፡ ፍሬዋንም፡ መልካም፡ አድርጉ፡ ወይም፡ ክፉ፡ ዛፍ፡ ፍሬዋንም፡ ክፉ፡ አድርጉ፡፡ ምዕ ፯፡ ፲፯ ፨

፴፬ እናንተ፡ የእባብ፡ ልጆች፡ እናንተ፡ ክፉ፡ ስትሆኑ፡ እንዴት፡ መልካም፡ መናገር፡ ትችላላችሁ፡ ከልብ፡ የተረፈውን፡ አፍ፡ ይናገራልና ፨ ኢሳ፡ ፶፱፡ ፲፫ ፨

፴፭ መልካም፡ ሰው፡ ከመልካም፡ ልቡ፡ መዝገብ፡ መልካም፡ ያወጣል፡ ክፉም፡ ሰው፡ ከክፉ፡ መዝገቡ፡ ክፉ፡ ያወጣል ፨

፴፮ እኔ፡ ግን፡ እላችኋለሁ፡ ሰዎች፡ የሚናገሩት፡ ምናምን፡ ነገር፡ ሁሉ፡ በፍርድ፡ ቀን፡ መልስ፡ ይሰጡበታል ፨

፴፯ ከቃልህ፡ የተነሣ፡ ትጸድቃለህና፡ ከቃልህም፡ የተነሣ፡ ይፈረድብሃል ፨

፴፰ በዚያ፡ ጊዜ፡ ከጻፎችና፡ ከፈሪሳውያን፡ ወገን፡ ሰዎች፡ መልሰው፡ እንዲህ፡ ሲሉ፡ መምህር፡ ሆይ፡ ካንተ፡ ምልክት፡ እናይ፡ ዘንድ፡ እንወዳለን፡ ምዕ ፲፮፡ ፩ ፨

፴፱ እርሱም፡ መልሶ፡ አላቸውም፡ ክፉም፡ አመንዝራ፡ ትውልድ፡ ምልክት፡ ይሻል፡ ከነቢዩ፡ ከዮናስ፡ በቀር፡ ምልክት፡ አይሰጠውም

ሉቃ፡፲፩፡፳፱፡ኢሳ፡፶፯፡፫፡ዮ፡፫፡፴፱
፵ ነገር፡ግን፡ዮናስ፡በዓሣ፡አንበሪ፡ ሆድ፡ውስጥ፡፫ ቀን፡ሶስት፡ሌሊ ት፡እንደኖረ፡እንዲሁም፡የሰ ው፡ልጅ፡በምድር፡ሆድ፡በመቃ ብር፡ሶስት፡ሌሊት፡ሶስት፡ቀን ይኖራልና፨ዮና፡፪፡፩፡ም፡፲፯፡
፵፩ ፳፩፡ሉቃ፡፲፩፡፴፪፨የነነዌ፡ሰዎች፡ በዮናስ፡ስብከት፡ንስሐ፡ገብተዋ ልና፡ከዚህ፡ትውልድ፡ጋራ፡በፍር ድ፡ቀን፡ይነሣሉ፡ይፋረዱታ ልም፡እነሆ፡ከዮናስ፡የሚበልጥ፡በ ዚህ፡አለ፨ም፡፲፩፡፲፯፡ሮሜ፡፪፡፳
፵፪ ፯፡ዮና፡፫፡፭፨ንግሥተ፡አዜብ፡የ ሰሎሞንን፡ጥበብ፡ለመስማት፡ ከምድር፡ዳር፡መጥታለችና፡ከ ዚህ፡ትውልድ፡ጋር፡በፍርድ፡ቀ ን፡ትነሣለች፡ትፋረዳቸዋለች ም፡እነሆ፡ከሰሎሞን፡የሚበል ጥ፡ከዚህ፡አለ፨፩ነገሥ፡፲፨
፵፫ ርኩስ፡መንፈስም፡ከሰው፡በወ ጣ፡ጊዜ፡ዕረፍትን፡ሲሻ፡ውኃ፡በ ሌለበት፡ስፍራ፡ይዞራል፡አያገ
፵፬ ኘውምም፨ከዚህም፡በኋላ፡ወደ፡ ወጣሁበት፡ቤቴ፡ልመለስ፡ይላ ል፡በመጣም፡ጊዜ፡ባዶ፡ሁኖ፡ተ ጸርጎ፡ተሸልሞ፡ያገኘዋል፨
፵፭ ከዚያ፡ወዲያም፡ይሔዳል፡ከእር ሱም፡ይልቅ፡የከፉትን፡ሌሎች ሰባት፡አጋንንት፡ከእርሱ፡ጋራ፡ ይወስዳል፡ይገቡበታልም፡በዚ ያም፡ይኖራሉ፡፡የዚያም፡ሰው ከፊተኛው፡የኋለኛው፡የባሰ፡ይ ሆናል፡እንደዚህም፡በዚህ፡ክ ፉ፡ትውልድ፡ይሆንበታል፨ሉ፡
ጴጥ፡፪፡፳፨
፵፮ ይህንም፡ለሕዝቡ፡ ሲናገር፡እነሆ፡እናቱና፡ወንድሞ ቹ፡ከእርሱ፡ጋራ፡ሊነጋገሩ፡ፈ ልገው፡በውጭ፡ቆመው፡ነበሩ፨
፵፯ ከሰዎቹም፡አንዱ፡እነሆ፡እናት ህና፡ወንድሞችህ፡ሊነጋገሩህ፡ፈ ልገው፡በውጭ፡ቆመዋል፡አለ ው፨ማር፡፫፡፴፩፡፴፫፡ሉ፡፰፡፲፱፡ ፳፩፡ም፡፲፫፡፶፭፨
፵፰ እርሱ፡ግን፡መልሶ፡ለነገረው፡ሰው፡ እናቴ፡ማናት፡ወንድሞ ቼስ፡እነማን፡ናቸው፨፰፡፱፡፡
፵፱ እጁንም፡ወደ፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡ ዘረጋ፡እነሆ፡እናቴ፡ወንድሞቼ ም፡እነዚህ፡ናቸው፡አለው፨
፶ በሰማይ፡ያለውን፡ያባቴን፡ፈቃድ፡ የሚያደርግ፡ሁሉ፡እርሱ፡ወንድ ሜም፡እኅቴም፡እናቴም፡ነውና፨ ሮሜ፡፰፡፳፱፨ምዕራፍ፡፲፫፡፡

ስለ፡ምሳሌ፡ዘርዕና፡ስለ፡ትርጓሜ ው፡ስለ፡እርሾ፡ስለ፡መዝገብ፡ስለ፡ዕ ንቍ፡ስለ፡መረብ፡ምሳሌ፡ስለ፡ት ምህርቱ፡መደነቅ፨

፩ በዚያም፡ቀ ን፡ኢየሱስ፡ከቤት፡ወጥቶ፡በባሕ ር፡አጠገብ፡ተቀመጠ፨
፪ ብዙ፡ሰዎ ችም፡ወደ፡እርሱ፡ተሰበሰቡ፡ወደ፡ ታንኳም፡ወጥቶ፡ተቀመጠ፡ሰዎ

ቸ፡ሁሉ፡ግን፡በዳር፡ቁመው፡ነበ
፫ ሩ፤በምሳሌም፡እጅግ፡እድርጎ፡ነ
ገራቸው፡እንዲህ፡ሲል፡እነሆ፡ዘሪ
ሊዘራ፡ወጣ፤ማቴ፡፬፡፩፡ቶ፡ሉ፡፰፡
፬ ፭፡፲፰፤እርሱም፡ሲዘራ፡አንዱ፡አ
ንዱ፡ወደቀ፡ወፎቹም፡መጥተው
፭ በሉት። አንዱ፡አንዱም፡እጅግም፡
መሬት፡በሌለበት፡በጭንጫ፡ላይ
ወደቀ፡ጥልቅ፡መሬት፡ስላልነበረ
፮ ው፡ፈጥኖ፡በቀለ፤ፀሐይ፡በወጣ
ች፡ጊዜ፡ግን፡ጸወለገ፡ሥርም፡ስላ
፯ ልኖረው፡ደረቀ። አንዱ፡አንዱ
ም፡በእሾህ፡መካከል፡ወደቀ፡እሾ
ህም፡አደገና፡አነቀው፤ኤር፡፬፡፫፡
፰ ሌላውም፡በለስላሳ፡መሬት፡ወደቀ
ፍሬውም፡አንዱ፡መቶ፡ሌላውም
ስሳ፡ሌላውም፡ሠላሳ፡ሰጠ፡አፈራ
፱ ዘፍ፡፳፮፡፲፪፤የሚሰሙ፡ጆሮች
ያሉት፡ይስማ፤ማር፡፯፡፲፯፡ዮሐ፡ራ
፲ ዕ፡፪፡፯፤ደቀ፡መዛሙርቱም፡ወደ
እርሱ፡ቀርበው፡ስለምን፡በምሳሌ
፲፩ ትናገራቸዋለህ፡አሉት፤እርሱም
መለሰ፡አላቸውም፡ለናንተ፡የመ
ንግሥተ፡ሰማያትን፡ምሥጢር፡
ማወቅ፡ተሰጥቶዋችኋልና፤እር
፲፪ ሳቸው፡ግን፡አልተሰጣቸውም፡ላ
ለው፡ይሰጠዋልና፡ይጨመርለታ
ልም፡የሌለው፡ግን፡ያውም፡ያለው
ይወሰድበታል፤ም፳፭፡፳፱፤
፲፫ እነርሱ፡እያዩ፡አያዩምና፡እየሰ
ሙም፡አይሰሙምና፡አያስተው
ሉምና፡ስለዚህ፡በምሳሌ፡እነግ
ራቸዋለሁ፤ዘዳ፡፳፱፡፬፤
፲፬ የኢሳይያስ፡ትንቢት፡በርሳቸው
ተፈጸመ፡የሚለው፡መስማት፡
ትሰማላችሁ፡አታስተውሉም
ም፡ማየትም፡ታያላችሁ፡አታዩ
ምምም። ኢሳ፡፮፡፱፡፲፤
፲፭ የዚህ፡ሕዝብ፡ልብ፡ደንድንዋል
ና፡ጆሮዎቻቸውም፡ከመስማት፡
ደንቁርዋልና፡ዓይናቸውን
ጨፍነዋልና፡በዓይናቸውም፡
እንዳያዩ፡በጆሮዎቻቸውም፡እን
ዳይሰሙ፡በልባቸውም፡እንዳያ
ስተውሉ፡እፈውሳቸውም፡ዘንድ፡
ወደእኔ፡እንዳይመለሱ።
፲፮ የናንተ፡ግን፡ዓይኖቻችሁ፡ያያ
ሉ፡ጆሮዎቻችሁም፡ይሰማሉና፡
ብፁዓን፡ናቸው፤ሉ፡፲፡፳፫፤
፲፯ እውነት፡እላችኋለሁና፡ብዙ፡ነ
ቢያት፡ጻድቃንም፡እናንተ፡የም
ታዩትን፡ያዩ፡ዘንድ፡ተመኙ፡አላ
ዩምም፡እናንተ፡የምትሰሙት
ን፡ይሰሙ፡ዘንድ፡ተመኙ፡አልሰ
፲፰ ሙም። እንግዲህ፡እናንተ፡የዘ
፲፱ ሪውን፡ምሳሌ፡ስሙ። ሰው፡ሁ
ሉ፡የመንግሥትን፡ቃል፡ቢሰማ
ባያስተውልም፡ክፉው፡ይመጣ
ል፡በልቡም፡የተዘራውን፡ይነጥ
ቃል፡በመንገድ፡ዳር፡የተዘራው
፳ ይህ፡ነው። በጭንጫ፡መሬት፡የ
ተዘራው፡ቃልን፡የሚሰማ፡ፈጥ

ኖ ምን፡በደስታ፡የሚቀበል፡ነው፨
፳፩ ነገር፡ግን፡ለጊዜው፡ነው፡እንጂ፡
ሰርም፡በርሱ፡የለበትም፡ስለ፡ቃ
ሉም፡መከራ፡ወይም፡ስደት፡በሆ
፳፪ ነ፡ጊዜ፡ፈጥኖ፡ይክዳል፨በሾህ
ም፡መካከል፡የተዘራው፡ቃሉን፡
የሚሰማ፡ነው፡ይህንን፡ዓለም፡በ
ማሰብ፡ባለጠግነትንም፡በመው
ደድ፡ቃሉን፡ይንቃል፡ያለ፡ፍሬም፡
፳፫ ይሆናል፨፩ጢሞ፡፮፡፱፨በመልካ
ምም፡ምድር፡የተዘራው፡ቃሉን፡የ
ሚሰማ፡የሚያስተውልም፡ነው፡
እርሱም፡አንዱ፡መቶ፡ሌላው፡ም
ስሳ፡ሌላውም፡ሠላሳ፡ፍሬ፡ይሰ
፳፬ ጣል፨ሌላም፡ምሳሌ፡መሰለላቸ
ው፡እንዲህ፡ሲል፡መንግሥተ፡ሰ
ማያት፡በርሻው፡መልካም፡ዘር፡
የዘራ፡ሰውን፡ትመስላለች፡ቁ፡፴
፳፭ ፮፨ሰዎችም፡በተኙ፡ጊዜ፡ጠላቱ፡
መጣ፡በስንዴው፡መካከል፡እንክ
፳፮ ርዳድ፡ዘርቶ፡ሔደ፨ብቃያውም
ባደገና፡ባፈራ፡ጊዜ፡በዚያ፡ጊዜ፡
፳፯ ደግሞ፡እንክርዳድ፡ታየ፨ባለቤ
ቱንም፡አገልጋዮቹ፡መጥተው፡
ጌታ፡ሆይ፡መልካም፡ዘር፡በርሻህ
ዘርተህ፡አልነበርህምን፡እንክር
ዳዱ፡ከወዴት፡መጣ፡አሉት፨
፳፰ እርሱ፡ግን፡ጸላት፡ሰው፡ይህን፡አ
ደረገ፡አላቸው፡አገልጋዮቹም፡
ሔደን፡ብንነቅለው፡ትወዳለህን
፳፱ አሉት፨እርሱ፡ግን፡አላቸው፡ለ

ይሆንም፡እንክርዳዱን፡ስት[illegible]
ሉ፡ስንዴውን፡ከርሱ፡ጋራ፡ትነ
ቅሉታላችሁ፨ኢሳ፡፳፰፡፳፬፡፳፭፨
፴ ተውዋቸው፡እስከ፡መከር፡ወራ
ት፡ባንድነት፡ይደጉ፡በመከ[illegible]
ወራት፡አጫጆቹን፡እላለሁ፡እን
ክርዳዱን፡አስቀድማችሁ፡ሰብ
ስቡ፡ለማቃጠልም፡በየነዶው፡እ
ሰሩት፡ስንዴውን፡ግን፡በጐተራ
ዬ፡ክተቱ፨ምዕ፫፡፲፪፨
፴፩ ሌላም፡ምሳሌ፡መሰለላቸው፡እ
ንዲህ፡ብሎ፡መንግሥተ፡ሰማያ
ት፡ሰው፡ወስዶ፡በርሻው፡ውስጥ
የዘራትን፡የሰናፍጭ፡ቅንጣትን
ትመስላለች፨ሉቃ፡፲፫፡፲፰፡፲፱፨
፴፪ እርሷም፡ከዘሮች፡ሁሉ፡ታንሳ
ለች፡ባደገች፡ጊዜ፡ግን፡ከቡቃያ፡
ሁሉ፡ትበልጣለች፡ዛፍም፡ትሆ
ናለች፡የሰማይ፡ወፎች፡መጥተ
ው፡በጫፎቸዋ፡እስኪ፡ሰፍሩ፡
፴፫ ድረስ፨ሌላም፡ምሳሌ፡ነገራቸ
ው፡መንግሥተ፡ሰማያት፡ሴት፡
የወሰደችውን፡ሁሉም፡እስኪ
ቦካ፡በሶስት፡መስፈሪያ፡ዱቄት
ም፡የሸሸገችውን፡እርሾ፡ትመ
፴፬ ስላለች፨ሉ ፲፫፡፳፩፨ኢየሱስም
ይህን፡ሁሉ፡ለተሰበሰበ፡ሕዝ
ብ፡በምሳሌ፡ተናገረ፡ያለ፡ምሳሌ
ግን፡አልነገራቸውም፨ማር፡፬፡
፴፭ ፴፫፡፴፬፨በነቢይ፡የተባለው፡ይ
ፈጸም፡ዘንድ፡እንዲህ፡ሲል፡አ

3

ፌን፡በምሳሌ፡እከፍታለሁ፡ከጥ
ንት፡ጀምሮ፡የተሠወረውንም፡
እናገራለሁ። መዝ፸፰፡፪።

፴፮ በዚያን፡ጊዜ፡ኢየሱስ፡ሕዝቡን፡አ
ሰናብቶ፡ወደ፡ቤት፡ገባ፡ደቀ፡መዛ
ሙርቱም፡ወደ፡እርሱ፡ቀርበው፡
የእርሻውን፡እንክርዳድ፡ምሳሌ

፴፯ ተርጉምልን፡አሉት። እርሱ፡ግ
ን፡መለሰ፡አላቸውም፡መልካም
ዘር፡የዘራ፡እርሱ፡የሰው፡ልጅ፡ነ

፴፰ ው። እርሻውም፡ይህ፡ዓለም፡ነው፡
መልካሙም፡ዘር፡እነዚህ፡የመን
ግሥት፡ልጆች፡ናቸው፡እንክር
ዳዱም፡እርሳቸው፡የክፉ፡ልጆች

፴፱ ናቸው። ፩ቆሮ፡፫፡፱። የዘራው
ም፡ጠላት፡እርሱ፡ዲያብሎስ፡ነው
መከሩም፡የዓለም፡ፍጻሜ፡ነው
አጫጆቹም፡መላእክት፡ናቸው

፵ እንክርዳዱም፡ተሰብስቦ፡በእሳ
ት፡እንዲቃጠል፡በዚህ፡ዓለም፡ፍ

፵፩ ጻሜ፡እንዲሁ፡ይሆናል። የሰው፡
ልጅ፡መላእክተኞቹን፡ይልካል፡
ከመንግሥቱም፡የሚሰናከሉ
ትንና፡ዓመፃ፡የሚያደርጉትን
ሁሉ፡ይሰበስባሉ። ምዕ፲፰፡፯፡፳

፵፪ ፪። ወደ፡ዕቶነ፡እሳትም፡ልቅሶ፡ጥ
ርስ፡ማፋጨትም፡ወደ፡አለበት፡
ይጥላቸዋልም። ፲፱።

፵፫ የዚያን፡ጊዜ፡ጻድቃን፡በአባታቸ
ው፡መንግሥት፡እንደ፡ፀሐይ፡ይ
በራሉ፡የሚሰማ፡ጆሮ፡ያለው፡ይ

፵፬ ስማ፡ዳን፡፲፪፡፫። መንግ
ሥተ፡ሰማያት፡በርሻ፡ውስጥ፡የ
ተቀበረ፡ሰውም፡ያገኘው፡የሠ
ወረውም፡መዝገብን፡ትመስላለ
ች፡ከደስታውም፡የተነሣ፡ሔዶ፡ያ
ለውን፡ሸጠ፡ያንንም፡እርሻ፡ገዛው
ም። ምሳ፡፪፡፬፡ፊልጵ፡፫፡፯።

፵፭ ደግሞ፡መንግሥተ፡ሰማያት፡የ
ከበረ፡ዕንቊ፡የሚፈልግ፡ነጋዴ

፵፮ ሰውን፡ትመስላለች፡ዋጋዋም፡የ
በዛ፡አንድ፡ዕንቊ፡ባገኘ፡ጊዜ፡ሄ
ዶ፡ያለውንም፡ሁሉ፡ሸጦ፡ገዛት።

፵፯ ደግሞ፡መንግሥተ፡ሰማያት፡ወ
ደ፡ባሕር፡የተጣለች፡ከዓሣውም
ዓይነት፡ሁሉ፡የሰበሰበች፡መረብ
ን፡ትመስላለች። ሕዝ፵፯፡፱።

፵፰ በሞላችም፡ጊዜ፡ወደ፡ዳር፡አወጡ
ዋት፡ተቀምጠውም፡መልካሙ
ን፡በዕቃቸው፡አከማቹ፡ክፉ
ውን፡ግን፡ወደ፡ውጭ፡ጣሉት።

፵፱ በዓለም፡ፍጻሜ፡መላእክት፡ይ
መጣሉ፡ክፉዎችን፡ከጻድቃን፡መ
ካከል፡ይለያሉ። ምዕ፳፭፡፴፪።

፶ ወደ፡ዕቶነ፡እሳትም፡ይጥሏቸዋ
ል፡በዚያም፡ልቅሶና፡ጥርስ፡ማፋ

፶፩ ጨት፡ይሆናል። ኢየሱስም፡ይህ
ን፡ሁሉ፡አስተዋላችሁን፡አላቸ
ው፡እርሳቸውም፡አዎን፡አቤቱ፡

፶፪ አሉት። እርሱም፡አላቸው፡ስለዚ
ህ፡ለመንግሥተ፡ሰማያት፡የተ
ማረ፡ጻሐፊ፡ሁሉ፡ከመዝገቡ፡አ

ዲሱንም፡ አሮጌውንም፡ የሚ
ያወጣ፡ ባለቤት፡ ሰው፡ ይመስላ
ል። መዝ፡ ፻፵፬፡ ፲፫ ።

፶፫ ኢየሱስም፡ እነዚህን፡ ምሳሌዎ
ች፡ በፈጸመ፡ ጊዜ፡ ከዚያ፡ ሔደ።
ማር፡ ፮፡ ፩፡ ፮፡ ሉቃ፡ ፬፡ ፲፮፡ ፴ ።

፶፬ ወደ፡ አገሩ፡ መጣ፡ በምኵራባቸው
ም፡ ያስተምራቸው፡ ነበር፡ ይህ
ኃይልስ፡ ይህ፡ ጥበብስ፡ ለእርሱ
ከወዴት፡ ተሰጠው፡ እያሉ፡ እስ

፶፭ ኪደነቁ፡ ድረስ። ይህ፡ የእንጨ
ት፡ ጸራቢ፡ ልጅ፡ አይደለምን፡ እና
ቱስ፡ ማርያም፡ ትባል፡ የለምን፡ ወ
ንድሞቹስ፡ ያዕቆብ፡ ዮሳ፡ ስምዖ
ን፡ ይሁዳም፡ አይደሉምን፥ ም፡

፶፮ ፲፪፡ ፵፮፡ እኅቶቹስ፡ ሁሉ፡ ከእኛ
ጋራ፡ አይደሉምን፡ ለዚህ፡ ይህ፡ ሁ
ሉ፡ ከወዴት፡ መጣለት። ዮሐ፡ ፮

፶፯ ፵፪፡ ፶፪ ። ይሰናከሉበትም፡ ነበር
ኢየሱስ፡ ግን፡ ነቢይ፡ በሀገሩና፡ በ
ቤቱ፡ አይከበርም፡ አላቸው።

፶፰ ዮሐ፡ ፬፡ ፵፬ ። ካለማመናቸው
ም፡ የተነሣ፡ ብዙ፡ በዚያ፡ ኃይል፡
አላደረገም ። ምዕራፍ፡ ፲፬ ።

ስለ፡ ሄሮድስ፡ በዓልና፡ ስለ፡ መጥ
ምቁ፡ ዮሐንስ፡ ጌታችን፡ የዮሐን
ስን፡ ሞት፡ ስለ፡ መስማቱ፤ ባምስ
ት፡ እንጀራ፡ በሁለት፡ ዓሣ፡ ፭ ሺ፡
ሰው፡ ስለ፡ ማጥገቡ፤ በታንኳ፡ በ
ባሕር፡ ላይ፡ እንደ፡ ሔደ፤ በጌንሴሬ
ጥ፡ ድውያንን፡ ስለ፡ ፈወሰ።

፩ በዚያም፡ ዘመን፡ የገሊላ፡ ንጉሥ
ሄሮድስ፡ የኢየሱስን፡ ዝና፡ ሰማ
ማር፡ ፮፡ ፲፬፡ ፲፮፡ ፳ ፱፡ ሉ ፫፡ ፲፱፡ ፳፤

፪ ለሎሌዎቹም፡ ይህ፡ ነው፡ መጥ
ምቁ፡ ዮሐንስ፡ እርሱ፡ ከሙታ
ን፡ ተነሣ፡ ስለዚህም፡ እንደዚህ፡ ያ
ሉ፡ ኃይላት፡ ይደረጉበታል፡ አ

፫ ላቸው። ሄሮድስም፡ ስለ፡ ወን
ድሙ፡ ስለ፡ ፊልጶስ፡ ሚስት፡ ስ
ለ፡ ሄሮድያዳ፡ ዮሐንስን፡ ይዞ፡ አ
ሥሮ፡ በግዞት፡ አኑሮት፡ ነበረና።

፬ ዮሐንስም፡ ለአንተ፡ ትሆን፡ ዘን
ድ፡ አይገባም፡ ይለው፡ ነበረና
ዘሌ ፲፰፡ ፲፮።

፭ ሊገድለውም፡ ይወድ፡ ነበር፡ ነገር
ግን፡ ዮሐንስ፡ በርሳቸው፡ ዘንድ፡
እንደ፡ ነቢይ፡ ነበርና፡ ሕዝቡን፡ ፈ
ራቸው። ም ፳፩፡ ፳፮፡

፮ የሄሮድስም፡ የተወለደበት፡ ቀ
ን፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ የሄሮድያዳ፡ ልጅ
በመካከላቸው፡ ዘፈነች፡ ሄሮድ
ስም፡ ደስ፡ አሰኘች፤ ሆሴ፡ ፯፡ ፭፤

፯ ስለዚህም፡ የምትፈልገውን፡ ሁ
ሉ፡ እንዲሰጣት፡ በመሐላ፡ ተስፋ

፰ አስደረገላት። እርስዋም፡ አስ
ቀድማ፡ ከናቷ፡ ተመክራ፡ ነበር
የመጥምቁ፡ የዮሐንስን፡ ራስ፡ በ
ዚህ፡ በፃሕል፡ ስጠኝ፡ አለችው፤

፱ ንጉሡም፡ አዘነ፡ ነገር፡ ግን፡ ስለ፡
መሐላው፡ ከርሱ፡ ጋራም፡ ስለ፡ ተ
ቀመጡ፡ ሰዎች፡ እንዲሰጧት፡ አ

፲፩ ዘዘ። ልኮም፡ በማዘት፡ ሰሉ፡ የዮሐ
ንስን፡ ራስ፡ አስቈረጠ፨ ራሱንም
በፃሕል፡ አምጥተው፡ ለብላቴና
ይቱ፡ ሰጧት፡ እርሷም፡ ለናቷ፡ አ
፲፪ መጣችው፨ ደቀ፡ መዛሙርቱ፡
ም፡ መጡ፡ ሬሳውንም፡ አንስተው
ቀበሩት፡ ሔደውም፡ ለኢየሱስ፡ ነ
፲፫ ገሩት፨ ም፡ ፳፪፡ ፵፪፨ ኢየሱስ
ም፡ ይህን፡ በሰማ፡ ጊዜ፡ ከዚያ፡ ተነ
ሥቶ፡ በታንኳ፡ ሁኖ፡ ብቻውን፡
ወደ፡ ምድረ፡ በዳ፡ ሔደ፡ ተሻገረ፡ ሕ
ዝቡም፡ ሰምተው፡ ከየከተማቸ
ው፡ በእግር፡ ተከተሉት፡ ማር፡ ፮፡
፲፬ ፴፪፡ ፵፬፡ ዮሐ፡ ፮፡ ፩፡ ፲፫፨ ኢየሱስ
ም፡ በወጣ፡ ጊዜ፡ ብዙ፡ ሕዝብ፡ አየ
አዘነላቸውም፡ ድውያናቸውንም
፲፭ አዳነ፡ ም ፱፡ ፴፪፨ በመሸም፡ ጊዜ፡ ደ
ቀ፡ መዛሙርቱ፡ ወደ፡ እርሱ፡ ቀርበ
ው፡ ቦታው፡ ምድረ፡ በዳ፡ ነው፡ ጊዜ
ውም፡ አለፈ፡ ወደ፡ መንደርም፡ ሒ
ደው፡ ምግባቸውን፡ ይገዙ፡ ዘንድ
፲፮ ሕዝቡን፡ አሰናብት፡ አሉት፨ ኢየሱ
ስም፡ አላቸው፡ መሔዳቸውን፡ አ
ያስፈልጋም፡ እናንተ፡ ስ፡ የሚበሉ
፲፯ ት፡ ስጧቸው፡ አላቸው፨ እርሳቸ
ውም፡ በዚህ፡ ካምስት፡ እንጀራና
ከሁለት፡ ዓሣ፡ በቀር፡ ምንም፡ የለ
፲፰ ንም፡ አሉት፨ እርሱም፡ ወደዚህ፡ ወ
ደኔ፡ አምጧቸው፡ አላቸው፨
፲፱ ሕዝቡም፡ በመስኩ፡ በመስኩ፡ ሳ
ር፡ እንዲቀመጡ፡ አዘዘ፨ አምስቱ

ኛም፡ እንጀራና፡ ሁለቱን፡ ዓሣ፡ ወ
ደ፡ ሰማይም፡ አሻቅቦ፡ አየ፡ ባረከ
ውም፡ እንጀራውንም፡ ቈርሶ፡ ለ
ደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ሰጠ፡ ደቀ፡ መዛ
ሙርቱም፡ ለሕዝቡ፡ አቀረቡ፨
፳ ሁሉም፡ በልተው፡ ጸገቡ፡ የተረ
ፈውንም፡ ቍራሽ፡ አሥራ፡ ሁለት
መሶብ፡ መልተው፡ አነሡ፨ ፬፡ ነገ
፳፩ ሥ፡ ፬፡ ፵፬፨ የበሉትም፡ ከሴቶች
ና፡ ከሕፃናት፡ በቀር፡ አምስት፡ ሺ
፳፪ ሰዎች፡ ያህሉ፡ ነበሩ፨ በዚያ፡ ጊዜም
ፈጥኖ፡ ሕዝቡን፡ እስኪያሰናብ
ት፡ ድረስ፡ ደቀ፡ መዛሙርቱን፡ ወ
ደ፡ መርከብ፡ ወጥተው፡ ወደ፡ ማዶ
ይቀድሙት፡ ዘንድ፡ ግድ፡ አላቸው
ማር፡ ፮፡ ፵፭፡ ፶ ፡ ዮሐ፡ ፮፡ ፲፮፡ ፳፩
፳፫ ሕዝቡንም፡ አሰናብቶ፡ ይጸልይ፡ ዘ
ንድ፡ ብቻውን፡ ወደ፡ ተራራ፡ ወጣ፡
በመሸም፡ ጊዜ፡ ብቻውን፡ በዚያ፡ ነ
፳፬ በረ፨ ሉ፡ ፮፡ ፲፪፡ ም ፱፡ ፲፰፨ ታንኳይ
ቱም፡ እስቀድማ፡ በባሕር፡ መካከ
ል፡ ነበረች፡ ነፋሱም፡ በፊት፡ ለፊት
ነበርና፡ ከማዕበሉ፡ የተነሣ፡ ትጨ
፳፭ ነቅ፡ ነበረች፨ ከሌሊቱም፡ ባራተ
ኛው፡ ክፍለ፡ ሰዓት፡ ኢየሱስ፡ በባ
ሕር፡ ላይ፡ እየሔደ፡ ወደ፡ እርሳቸው
፳፮ መጣ፨ ደቀ፡ መዛሙርቱም፡ በባ
ሕር፡ ሲሔድ፡ ባዩት፡ ጊዜ፡ ምትሐ
ት፡ ነው፡ ብለው፡ ደነገጡ፡ ከፍርሃት
ም፡ የተነሣ፡ ጮሁ፡ ሉ ፳፬፡ ፴፯፨
፳፯ በዚያም፡ ጊዜ፡ ኢየሱስ፡ ፈጥኖ፡ አ

ይዟቸው፡እኔ፡ነኝ፡አትፍሩ፡ብሎ
፳፯ ተናገራቸው። ጴጥሮስም፡መ
ለሰለት፡አቤቱ፡አንተስ፡እንደ፡ሆ
ንህ፡በውኃ፡ላይ፡ወዳንተ፡እመጣ
፳፱ ዘንድ፡እዘዘኝ፡አለው። እርሱም
ና፡አለው። ጴጥሮስም፡ከታንኳ
ወርዶ፡በውኃ፡ላይ፡ወደ፡ኢየሱስ
፴ መጣ። ነገር፡ግን፡የነፋሱን፡ብር
ታት፡ባየ፡ጊዜ፡ፈራ፡ለመስጠም
ጀመረ፡አቤቱ፡አድነኝ፡እያለ፡
፴፩ ጮኸ። ም፳፰፡፲፫። በዚያም፡ጊ
ዜ፡ኢየሱስ፡ፈጥኖ፡እጁን፡ዘረ
ጋ፡ያዘውም፡እንዲህም፡አለው።
አንተ፡እምነት፡የጐደለህ፡
ስለምን፡ተጠራጠርህ፡አለው
፴፪ ም፳፪፡፴፩፤ ፮፡፳፮። ወደ፡መርከብ
ም፡በወጡ፡ጊዜ፡ነፋሱ፡ጸጥ፡አለ
፴፫ በታንኳውም፡የነበሩት፡መጥተ
ው፡ሰገዱለት፡እንዲህ፡ሲሉ፡አን
ተ፡በውነት፡የእግዚአብሔር፡ል
ጅ፡ነህ። ም፫፡፲፯፡፲፯፡፭።
፴፬ ተሻግረውም፡ወደ፡ጌንሴሬጥም
፴፭ ድር፡መጡ። የዚያም፡አገር፡ሰዎ
ች፡ባወቁት፡ጊዜ፡ባጠገባቸው።
ወዳለው፡ወደዚያ፡አገር፡ሁ
ሉ፡ላኩ። ድውያንንም፡ሁሉ፡አመ
፴፮ ጡለት። የልብሱንም፡ጫፍ፡ብ
ቻ፡ይነኩ፡ዘንድ፡ለመኑት፡የነኩ
ትም፡ሁሉ፡ዳኑ። ም፱፡፳፤ ሉ፡፲
፱።

ምዕራፍ፡፲፭።

እጅን፡ሳይታጠቡ፡ስለ፡መብላት።
ፈሪሳውያን፡እንደ፡ጠየቁት፤ [...]
ፍ፡የሚገባ፡መብል፡ሰውን፡እን
ደሚያረክሰው፤ ስለ፡ከነዓናዊቱ፡
ሴት፡ልጅ፡ዕውሮችንና፡ድውያ
ንን፡እንደ፡ፈወሰ፤ ፯ እንጀራ፡[...]
ር፡ከቶ፡አራት፡ሺ፡ሰው፡እንደ[...]

፩ በዚያ፡ጊዜ፡ጸሐፍትና፡ፈሪሳው
ያን፡ከኢየሩሳሌም፡ወደ፡ኢየ[ሱስ]
መጥተው፡እንዲህ፡አሉት፡ማር
፪ ፯፡፩፡፭፡፲። ደቀ፡መዛሙርትህ፡
የሽማግሌዎችን፡ወግ፡ለምን፡ይ
ተላለፋሉ፡እንጀራ፡ሲበሉ፡እጃ
ቸውን፡አይታጠቡምና። ዘዳግ፬
፫ ፪፡ሉ፡፲፩፡፴፰። እርሱም፡መልሶ
አላቸው፡እናንተስ፡ስለ፡ወጋችሁ
የእግዚአብሔርን፡ሥርዓት፡ስ
፬ ምን፡ትተላለፋላችሁ። እግዚአ
ብሔር፡እንዲህ፡ብሎአልና፡
አባትህንና፡እናትህን፡አክብር፡አ
ባቱንና፡እናቱን፡የሚሰድብ፡ፈ
ጽሞ፡ይሙት። ዘፀ፡፳፡፲፪፡፳፩፡፲፯
፭ እናንተ፡ግን፡ትላላችሁ፡አባቱን፡
ወይም፡እናቱን፡የሚል፡ከእኔ፡መ
ሥዋዕት፡የምትፈልገውን፡አሳረ
ጋሁልህ፡ቢል፡አባቱን፡እናቱን፡ያከ
፮ ብር፡ዘንድ፡አያስፈልገውም። ስ
ለ፡ወጋችሁም፡የእግዚአብሔር
፯ ን፡ሥርዓት፡አፈረሳችሁ። እናን
ተ፡ግብዞች፡ኢሳይያስ፡መልካም፡
ተናገረባችሁ፡እንዲህ፡ሲል።
፰ ኢሳ፳፱፡፲፫። ይህ፡ሕዝብ፡አፉ፡ወ

ደ፡እኔ፡ይቀርባል፡በከንፈሩም፡ያ
ከብረኛል፡ልቡ፡ግን፡ከእኔ፡እስረ
፱ ዝሞ፡ይርቃል፤የሰውም፡ሥርዓ
ት፡ትምህርት፡እያስተማሩ፡በከ
፲ ንቱ፡ያመልኩኛል፤ሕዝቡንም፡
ጸራ፡እንዲህ፡አላቸው፡ስሙ፡አስ
፲፩ ተውሉም፤ወደ፡አፍ፡የሚገባ፡ሰው
ን፡የሚያረክስ፡አይደለም፡ከአፍ
የሚወጣ፡ግን፡ይህ፡ሰውን፡ያረክሰ
ዋል፤፩፡ጢሞ፡፬፡፬፡ምዕ፲፬፡ሐ፲፡ሐ
፲፪ ፲፭፤በዚያን፡ጊዜ፡ደቀ፡መዛሙር
ቱ፡ቀርበው፡ፈሪሳውያን፡ይህን፡ነ
ገር፡በሰሙ፡ጊዜ፡በነገርህ፡እንደ፡
ተሰናከሉ፡ታውቃለህን፡አሉት፤
፲፫ እርሱም፡መልሶ፡እንዲህ፡አለ፡የሰ
ማዩ፡አባቴ፡ያልተከለው፡ተክል፡
፲፬ ሁሉ፡ይነቀላል፤ተዉአቸው፡ዕ
ውሮችን፡የሚመሩ፡ዕውሮች፡ና
ቸው፡ዕውርም፡ዕውርን፡ቢመራ
ው፡ሁለቱም፡ተያይዘው፡ወደ፡ጕ
ድጓድ፡ይወድቃሉ፤ሉቃ፡፮፡፴፱፡ሮ
፲፭ ሜ፡፪፡፲፱፤ጴጥሮስ፡መልሶ፡ይህን፡
፲፮ ምሳሌ፡ተርጕምልን፡አለው፤ኢየሱ
ስ፡እንዲህ፡አለ፡እናንተ፡ደግሞ፡እ
ስከ፡ዛሬ፡ድረስ፡አታስተውሉምን፤
፲፯ ወደ፡አፍ፡የሚገባ፡ሁሉ፡ወደ፡ሆድ፡
እንዲወርድ፡ወደ፡ውጭም፡እንዲ
፲፰ ወድቅ፡አታውቁምን፤ከአፍ፡የሚ
ወጣ፡ግን፡ከልብ፡ይወጣል፡ሰውን፤
ም፡የሚያረክሰው፡እርሱ፡ነው፤
፲፱ ከልብ፡ክፉ፡አሳብ፡መግደልም፡ግ
ዝር፡ዝሙት፡መስረቅ፡አሰት፡መ
መስከር፡ስድብም፡ይወጣልና፤
፳ ዘፍ፰፡፳፩፤ሰውን፡የሚያረክስ
ው፡ይህ፡ነው፡እንጂ፡እጅን፡ሳይታ
ጠቡ፡መብላት፡ሰውን፡አያረክ
፳፩ ሰውም። ኢየሱስም፡ከዚያ፡ወጥ
ቶ፡ወደ፡ጢሮስና፡ወደ፡ሲዶና፡አገር
፳፪ ሔደ፤ማር፡፯፡፳፬፡፴፤እነሆም፡የ
ከነዓን፡ሴት፡ከዚያ፡አገር፡ወጣች፡
ወደ፡እርሱም፡እየጮኸች፡እንዲ
ህም፡እያለች፡ማረኝ፡የዳዊት፡ል
ጅ፡ጌታዬ፡ሆይ፡ልጄን፡ክፉ፡ሰይጣ
ን፡ይዞ፡ይሣቀያታልና፡ማርልኝ፤
፳፫ እርሱ፡ግን፡አንዳችም፡አልመለሰ
ላትም፤እንዲህም፡አሉት፡አሰና
ብታት፡በኋላችን፡ትጮኻለችና፤
፳፬ እርሱም፡መለሰ፡ዓለም፡ከኧል፡ቤ
ት፡ወደ፡ጠፉ፡በጎች፡እንጂ፡አልተ
፳፭ ላክሁም፡አላቸው፤ም፲፡፳፤እር
ሷ፡ግን፡ቀረበችና፡ሰገደች፡ለት፡እ
ንዲህ፡ስትል፡አቤቱ፡እርዳኝ፤
፳፮ እርሱም፡መለሰ፡እንዲህ፡ሲል፡የል
ጆችን፡እንጀራ፡ወስዶ፡ለውሾች
፳፯ መስጠት፡አይገባም፡አላት፤እር
ስዋም፡አዎን፡አቤቱ፡ውሾችም
ደግሞ፡ከጌቶቻቸው፡ማዕድ፡የወደ
ቀውን፡ፍርፋሪ፡ይበላሉ፡አለች፤
፳፰ በዚያ፡ጊዜ፡ኢየሱስ፡መልሶ፡አንቺ
ሴት፡እምነትሽ፡ታላቅ፡ነው፡እን
ደ፡ወደድሽ፡ይሁንልሽ፡አላት፡ል
ጅዋ፡በዚያ፡ሰዓት፡ዳነች። ምዕ፲፡፲፡

፳፱ ፲፫ ኢየሱስም፡ ከዚያ፡ ተነሥቶ፡ ወደ፡ ገሊላ፡ ባሕር፡ አጠገብ፡ ወጣ፡ ወደ፡ ተራራም፡ ወጥቶ፡ ተቀመጠ።

፴ ማር ፯፡ ፴፩ ብዙ፡ ሕዝብም፡ ወደ፡ እርሱ፡ መጡ፡ ከእርሳቸውም፡ ጋራ፡ አንካሶች፡ ዕውሮችም፡ ድዳችም ሌሎችም፡ ብዙ፡ ነበሩ፡ በኢየሱስ፡ በእግሩ፡ በታች፡ አኖሯቸው፡ ፈወሳቸውም።

፴፩ ሕዝቡም፡ ድዳች፡ ሲናገሩ፡ ደካሞች፡ ሲፈወሱ፡ አንካሶች ሲሔዱ፡ ዕውሮችም፡ ሲያዩ፡ ባዩ፡ ጊዜ፡ አደነቁ፡ የ፲ልንም፡ አምላክ፡ አመሰገኑ።

፴፪ ኢየሱስም፡ ደቀ፡ መዛሙርቱን፡ ጠራ፡ በዚህ፡ ከእኔ፡ ጋራ፡ ከዋሉ፡ ሶስት፡ ቀናቸው፡ ነውና፡ ለዚህ፡ ሕዝብ፡ እራራለሁ፡ የሚበሉትም፡ የላቸውም፡ በመንገድም፡ እንዳ ይደክሙ፡ ጾማቸውን፡ አሰናብታቸው ዘንድ፡ አልወድም፡ አላቸው። ማር ፰፡ ፩፡ ፲

፴፫ ደቀ፡ መዛሙርቱም፡ ይህን፡ የሚያህል፡ ሰው፡ የሚያጠግብ፡ እንጀራ፡ ከወዴት፡ እናመጣለን፡ አሉት። ም፡ ፲፬፡ ፲፬፡ ፲፯

፴፬ ኢየሱስም፡ ስንት፡ እንጀራ፡ አላችሁ፡ አላቸው፡ እርሳቸውም፡ ሰባት፡ ጥቂትም፡ ዓሣ፡ አሉት።

፴፭ ሕዝቡንም፡ በምድር፡ ላይ፡ እንዲቀመጡ፡ አዘዘ።

፴፮ ፯ቱንም፡ እንጀራ፡ ዓሣውንም፡ አንስቶ፡ ያዘ፡ አመስግኖም፡ ቈረሰ፡ ለደቀ፡ መዛሙርቱም፡ ሰጠ፡ ደቀ፡ መዛሙርቱም፡ ለሕዝቡ። ፩ ጢሞ፡ ፬፡ ፬፡ ፭

፴፯ ሁሉም፡ በሉ፡ ጠገቡም፡ የተረፈውንም፡ ቍርስራሽ፡ ሰባት፡ መሶብ፡ መልተው፡ አነሡ። ም ፲፡ ፳፰

፴፰ የበሉትም፡ ሰዎች፡ ከሴቶችና፡ ከሕፃናት፡ በቀር፡ አራት፡ ሺ፡ ነበሩ።

፴፱ ሕዝቡንም፡ አሰናብቶ፡ ወደ፡ መርከብ፡ ወጣ፡ ወደ፡ መጋዳላ፡ አገርም፡ ሔደ። ም ፲፡ ፴፱

ምዕራፍ ፲፮።

ከፈሪሳውያን፡ እርሾ፡ ስለ፡ መጠንቀቅ፡ በቂሣርያ፡ ደቀ፡ መዛሙርቱን፡ እንደ፡ ጠየቃቸው፤ ጴጥሮስ፡ ብፁዕ፡ እንደ፡ ተባለና፤ (የመንግሥት፡ ሰማያት፡ መክፈቻ፡ ለመቀበል፡ ተስፋ፡ እንዳገኘ)፤ በኢየሩሳሌም፡ ስለሚቀበለው፡ መከራ፡ ሞትን፡ ስለማይቀምሱት፡ ሰዎች

፩ ፈሪሳውያንና፡ ሰዱቃውያንም፡ ሊፈትኑት፡ መጡ፡ ከሰማይም፡ ምልክት፡ ያሳያቸው፡ ዘንድ፡ ጠየቁት። ማቴ፡ ፲፪፡ ፴፰፡ ማር፡ ፰፡ ፲፩፡

፪ ፳፬ እርሱም፡ መልሶ፡ አላቸው፡ ምሽት፡ በመሸም፡ ጊዜ፡ ሰማዩ፡ ቀልቶ ዋልና፡ ብራ፡ ይሆናል፡ ትላላችሁ።

፫ ሉ፡ ፲፪፡ ፶፬፡ ፶፯ በነጋም፡ ጊዜ፡ ሰማዩ፡ በደመና፡ ገጥሞ፡ ይፈልቃልና፡ ዛሬ፡ ይዘንማል፡ ትላላችሁ፡ እናንት፡ ግብዞች፡ የሰማዩን፡ ፊት፡ (መለየት፡ ታውቃላችሁን፡ የዘመኑን፡ ምልክት፡ መለየት፡ አትችሉምን። ም፡ ፩፡ ፲።

ከፉና፡ለመንዝራ፡ት፡ውልድ፡ምልክት፡ይሻል፡ምልክት፡ግን ከነቢዩ፡ከዮናስ፡ምልክት፡በቀር አይሰጠውም፡ከዚያም፡እነርሱን፡ትቶ፡ሔደ፤ም፲፮፡፩፡፬፡ማር ደቀ፡መዛሙርቱም፡ወደ፡ማዶ፡በደረሱ፡ጊዜ፡እንጀራ፡እለመያዛቸው፡ትዝ፡ብሏቸው፡ነበር። ኢየሱስም፡ከፈሪሳውያንና፡ከሰዱቃውያን፡እርሾ፡ተጠንቀቁ፡ተቀመጡ፡አላቸው፤ሉ፡፲፪፡፩፡እርሳቸውም፡ግን፡በልባቸው፡አሰቡ፡እንጀራም፡ባንይዝ፡ነው፡ተባባሉ። ኢየሱስም፡አውቆ፡አላቸው፡እናንተ፡እምነት፡የጐደላችሁ፡እርስበርሳችሁ፡ምን፡ተባባላችሁ፡እንጀራ፡ባትይዙ፡ነውን፤ም፲፮፡፯ እስከ፡ዛሬ፡ገና፡አታስተውሉምን፡ወይስ፡አታስቡምን፡አምስት እንጀራ፡ለአምስት፡ሺህ፡ሰዎች፡ሰጥቼ፡መሶብ፡አነሣችሁ፤ም፲፬፡፲፯ ወይስ፡፯እንጀራ፡ላራት፡ሺ፡ሰዎች፡ሰጥቼ፡መሶብ፡አነሣችሁ፡ም፲፭፡፴፬፡፴፰፤እንዴት፡ከፈሪሳውያንና፡ከሰዱቃውያን፡እርሾ፡ተጠበቁ፡ዘንድ፡ስለ፡እንጀራ፡እንዳላኋችሁ፡አታስተውሉምን፤ ኢየሱስም፡ወደ፡ፊልጶስ፡አገር፡ወደ፡ቂሣርያ፡በመጣ፡ጊዜ፡ደቀ፡መዛሙርቱን፡ጠየቀ፡እንዲህ፡ብሎ፡እኔን፡የሰው፡ልጅ፡ሰዎች፡ማ

ነው፡ይሉኛል፡ማር፰፡፳፯፡ሉ፱፡፲፰፡፳፩፤ከዚያ፡ወዲያ፡ከፈሪሳውያንና፡ከሰዱቃውያን፡ትምህርት፡እንጂ፡ከእንጀራ፡እርሾ፡ይጠበቁ፡ዘንድ፡እንዳላላቸው፡አወቁ፤እርሳቸውም፡አንዳንዱ፡መጥምቁ፡ዮሐንስ፡ነው፡የሚሉህ፡አሉ ሌሎቹም፡ኤልያስ፡ሌሎቹም፡ኤርምያስ፡ወይም፡ከነቢያት፡አንዱ፡ነው፡ይላሉ፡አሉ፤ም፲፬፡፱፡፲፪፡፲፤ እናንተ፡ስ፡ማን፡እንደሆንሁ ትላላችሁ፡አላቸው፤ስምዖን፡ጴጥሮስም፡መለሰ፡አንተ፡የሕያው፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ክርስቶስ፡ነህ፡አለ፤ዮሐ፮፡፷፱፤ ኢየሱስም፡እንዲህ፡ብሎ፡መለሰ የዮና፡ልጅ፡ስምዖን፡ሆይ፡አንተ፡ብፁዕ፡ነህ፡ይህን፡የሰማዩ፡አባቴ፡ነው፡እንጂ፡ሥጋና፡ደም፡አልገለጠልህም፤ገላ፩፡፲፡፲፪፤ እኔም፡አንተ፡ጴጥሮስ፡አለት፡ነህ፡አልሃለሁ፡በዚህችም፡ዴንጊያ፡አለት ላይ፡ቤተ፡ክርስቲያኔን፡እሠራለሁ የገሃነምም፡ደጆች፡አያቸንፏዋትም፤ዮሐ፩፡፵፪፡ኤፌ፪፡፳፤ የመንግሥተ፡ሰማያትንም፡መክፈቻ፡እሰጥሃለሁ፡በምድር፡ያሠርኸው፡በሰማይ፡የታሠረ፡ይሆናል፡በምድርም፡የፈታኸው፡በሰማያት፡የተፈታ፡ይሆናል፤ም፲፰፡፲፰ ከዚያም፡ወዲያ፡ኢየሱስ፡እርሱ

ክርስቶስ፡እንዲሆነ፡ለማንም፡እ
ንዳይናገሩ፡ደቀ፡መዛሙርቱን
፳፩ አዘዛቸው፡ምዕ፲፯፡፱። ከዚያም
ጊዜ፡ጀምሮ፡ኢየሱስ፡ወደ፡ኢየ
ሩሳሌም፡ይሔድ፡ዘንድ፡እንዲገ
ባው፡ከሽማግሌዎችና፡ከካህናት
አለቆች፡ከጻፎችም፡ብዙ፡መከ
ራ፡እንዲቀበል፡እንዲገድሉት
ም፡በሶስተኛውም፡ቀን፡ከሙታ
ን፡እንዲነሣ፡ለደቀ፡መዛሙርቱ
ይገልጥላቸው፡ጀመረ። ማር፰፡
፳፪ ፴፩፡ሉ፡፱፡፳፪። ጴጥሮስም
ለብቻው፡ወሰደው፡ይገሥፀው
ም፡ጀመረ፡እንዲህ፡ሲል፡አቤቱ፡
ይህ፡ይሆንብህ፡ዘንድ፡አይድርስ
፳፫ ብህ፡ምዕ፲፮፡ማ፡ዮሐ፡፬፡፲፱። እርሱ
ም፡ዘወር፡ብሎ፡ጴጥሮስን፡ለሰው
አንተ፡ሰይጣን፡ከኋላዬ፡ሒድ፡ዕ
ንቅፋት፡ሆነህብኛልና፡ለእግዚ
አብሔር፡አታስብምና፡የሚሆነ
ውን፡ለሰው፡የሚሆነውን፡ነው፡እ
፳፬ ንጂ። የዚያን፡ጊዜ፡ኢየሱስ፡ለደ
ቀ፡መዛሙርቱ፡አለ፡እኔን፡መከተ
ል፡የሚወድ፡ቢኖር፡ነፍሱን፡ይካ
ድ፡መስቀሉንም፡ተሸክሞ፡ይከ
፳፭ ተለኝ፡ምዕ፲፡፴፰። ማዳን፡የሚወ
ድ፡ያጠፋታል፡ስለእኔም፡ያጠፋ፡
፳፮ ያገኛታል። ሰው፡ምን፡ይጠቀ
መዋል፡ዓለሙን፡ሁሉ፡ቢያተር
ፍ፡ነፍሱን፡ግን፡ቢያጎድል፡ወይ
ስ፡ምን፡ይጠቀመዋል፡ሰው፡ለነፍ

፳፯ ሱ፡ቤዛ፡ምን፡ይሰጣል። የሰው
ልጅ፡ባባቱ፡ክብር፡ከመላእክቱ
ጋራ፡ይመጣ፡ዘንድ፡ጊዜ፡አለ
ውና፡በዚያም፡ጊዜ፡ለሁሉም፡እ
ንደ፡ሥራው፡ዋጋውን፡ይሰጣ
፳፰ ል፡ሮሜ፡፪፡፯። እውነት፡እነግራ
ችኋለሁ፡የሰው፡ልጅ፡በመንግ
ሥቱ፡ሲመጣ፡እስኪያዩ፡ድረስ
በዚህ፡ከቆሙት፡ሰዎች፡ሞትን፡
የማይቀምሱት፡አሉ።

ምዕራፍ፡፲፯።

በተራራ፡ላይ፡መልኩ፡እንደ፡ተለ
ወጠና፡ሙሴና፡ኤልያስ፡እንደ፡መ
ጡ፡ከደመናም፡ድምፅ፡እንደ፡መ
ጣ። ጻድቃን፡ኤልያስ፡አስቀድሞ፡
ይመጣል፡ስለ፡ማለታቸው፡ጋኔን
የሚሣቀየውን፡እንደ፡አዳነ። ስለ
መከራው፡ነገር። ጴጥሮስ፡በቅፍ
ርናሆም፡ከዓሣ፡ሆድ፡አራት፡ድ
ሬም፡አግኝቶ፡ግብር፡እንደ፡ሰጠ
፩ ከስድስት፡ቀንም፡በኋላ፡ኢየሱስ
ጴጥሮስንና፡ያዕቆብን፡ወንድሙ
ን፡ዮሐንስንም፡ለብቻቸው
ይዞ፡ወደ፡ረጅም፡ተራራ፡ወጣ።
ማር፱፡፪፡ሉ፡፱፡፳፰።
፪ በፊታቸውም፡መልኩ፡ተለወጠ፡
ፊቱም፡እንደ፡ፀሐይ፡አበራ፡ልብ
ሱም፡እንደ፡ብርሃን፡ነጭ፡ሆነ፡፪
፫ ጴጥ፡፩፡፲፮፡፲፯። እነሆ፡ሙሴና፡ኤ
ልያስም፡ከእርሱ፡ጋራ፡ሲነጋገሩ
ለእርሳቸው፡ታዩ፡ሚል፡፬፡፭።

፬ ጴጥሮስም፡መለሰ፡ኢየሱስንም
አለው፡አቤቱ፡በዚህ፡ብንቀመጥ
ለእኛ፡መልካም፡ነው፡ይመቸና
ል፡ብትፈቅድስ፡ሦስት፡ዳስ፡አንዱ
ላንተ፡አንዱም፡ለሙሴ፡አንዱን
ም፡ለኤልያስ፡በዚህ፡እንሥራ፨
፭ እርሱም፡ይህን፡ሲናገር፡እነሆ፡
ብሩህ፡ደመና፡መጥቶ፡ሠወራቸ
ው፡ከደመናም፡ድምፅ፡መጣ፡እ
ንዲህ፡ሲል፡ይህ፡ነው፡የምወደው
ልጄ፡በርሱ፡ደስ፡የሚለኝ፡እርሱ
ን፡ስሙ፡ተቀም ፫፡፲፫፡ዘዳግ፡፲፰፡
፮ ፲፭፡፲፱፨ደቀ፡መዛሙርቱም፡በሰ
ሙ፡ጊዜ፡በግምባራቸው፡ወደቁ
፯ እጅግም፡ፈሩ፨ኢየሱስም፡ወደ
እርሳቸው፡መጣ፡ዳሰሳቸውም፡
አለም፡ተነሡ፡አትፍሩ፨ዳን፡፲፡
፰ ፲፰፨ዓይናቸውንም፡አነሡ፡ማን
ንንም፡አላዩም፡ኢየሱስን፡ብቻ፡
፱ እንጂ፨ከተራራም፡በወረዱ፡ጊዜ
ኢየሱስ፡ይህን፡ያያችሁትን፡የሰ
ው፡ልጅ፡ከሙታን፡እስኪነሣ፡ድ
ረስ፡ለማንም፡አትናገሩ፡ብሎ፡
፲ አዘዛቸው፨ም ፲፯፡፭፨ደቀ፡መዛ
ሙርቱም፡ጠየቁት፡እንዲህ፡ሲ
ሉ፡ጻፎች፡ኤልያስ፡አስቀድሞ፡
ይመጣል፡ለምን፡ይላሉ፨ምል፡፬፡
፲፩ ፲፭፡ሚል፡፬፡፫፨ኢየሱስም፡መ
ለሰ፡አላቸው፡ኤልያስ፡በውነት፡
አስቀድሞ፡ይመጣል፡ሁሉንም፡
ያቀናል፡ያከናውናል፡የሐዋ፫፡፳፩

፲፪ እላችኋለሁ፡ኤልያስ፡ፈጽሞ፡እ
ንዲመጣ፡እርሳቸው፡ግን፡አላወ
ቁትም፡የወደዱትን፡ሁሉ፡አደረ
ጉበት፡እንዲሁ፡እንዲሁም፡የሰው
ልጅ፡ደግሞ፡ከእርሳቸው፡መከ
ራ፡ይቀበል፡ዘንድ፡ጊዜ፡አለው፨
፲፫ ም ፲፬፡፱፡፲፪፨ከዚያ፡ወዲያም፡ደ
ቀ፡መዛሙርቱ፡ስለ፡መጥምቁ፡
ዮሐንስ፡እንዲ፡ተናገረ፡አወቁ፨ሉ
፲፬ ፩፡፲፯፨ወደ፡ሕዝቡም፡በደረሱ፡ጊዜ
አንድ፡ሰው፡በጉልበቱ፡እየሰገደ
ና፡እንዲህ፡እያለ፡ወደ፡እርሱ፡መ
ጣ፨ማር ፱፡፲፬፡፲፱፡ሉ፡፱፡፴፯፡፵፪፨
፲፭ አቤቱ፡ልጄን፡ማረው፡በየወሩ፡
መጀመሪያ፡በክፉ፡ጋኔን፡ይሠቃያ
ልና፡ብዙ፡ጊዜም፡በእሳት፡ብዙ፡
፲፮ ጊዜም፡በውሀ፡ይወድቃልና፨ወደ፡
ደቀ፡መዛሙርትህም፡አመጣሁ
፲፯ ት፡ሊፈውሱት፡አልቻሉም፨ኢየ
ሱስም፡መለሰ፡እንዲህ፡አለ፡እናን
ተ፡ያላመነ፡ጠማማ፡ትውልድ፡እ
ስከ፡መቼ፡ከእናንተ፡ጋራ፡እኖራለሁ
እስከ፡መቼ፡እታገሣችኋለሁ፡
፲፰ ወዲህ፡ወደ፡እኔ፡አምጣው፨ኢየ
ሱስምጋኔኑን፡ገሠፀው፡ከእርሱም
ወጣ፡ብላቴናውም፡በዚያች፡ሰዓ
፲፱ ት፡ዳነ፨በዚያ፡ጊዜ፡ደቀ፡መዛሙ
ርቱ፡ለብቻቸው፡ወደ፡ኢየሱስ፡መ
ጥተው፡ስለምን፡እኛ፡ልናወጣው
፳ አልቻልንም፡አሉት፨ም ፲፡፩፡ኢ
የሱስ፡ም፡አላቸው፡ከእምነታ

ችሁ፡መጕደል፡የተነሣ፡ነው። እው
ነት፡እላችኋለሁ ፡የሰናፍጭ፡ቅ
ንጣት፡የሚያህል፡ሃይማኖት፡ቢ
ኖራችሁ፡ይህን፡ተራራ፡ከዚህ፡
ወዲያ፡ተነሣ፡ብትሉት፡ይነሣል፡
የሚሳናችሁ፡የለም፨ማቴ፳፩፡፳፩፡
፳፩ ዘካ፡፬፡፯፡ሉ፡፲፯፡፲፮፨እንዲህ፡ያለ፡
ዓይነት፡ግን፡አይወጣም፡በጾም፡
በጸሎት፡እንጂ፨ማር፱፡፳፱፡ሉ፡፱፡
፳፪ ፵፫፨በገሊላም፡ሲመላለሱ፡ኢየሱ
ስ፡አላቸው፡የሰው፡ልጅ፡በሰው፡እ
ጅ፡አልፎ፡ይሰጥ፡ዘንድ፡ጊዜ፡አለ
ው፨ም፲፮፡፳፩፨ይገድሉታልም፡በ
፳፫ ሶስተኛውም፡ቀን፡ይነሣል፡አርሳ
፳፬ ችውም፡እጅግ፡አዘኑ፨ወደ፡ቅፍ
ርናሆምም፡በደረሱ፡ጊዜ፡ግብር
የሚቀበሉ፡ሰዎች፡ወደ፡ጴጥሮስ፡
መጡ፡ አሉትም፡መምህራችሁ፡
ግብር፡አይሰጥምን፨ዘፀ፡፴፡፲፫፨
፳፭ አርሱም፡አዎን፡አለ፡ወደ፡ቤትም
በገባ፡ጊዜ፡አስቀድሞ፡ኢየሱስ፡ሲ
ሞን፡ሆይ፡አለው፡ምን፡ይመስል
ሃል፡የምድር፡ነገሥታት፡ግብር፡
ቀረጥም፡ከማን፡ይወስዳሉ፡ከል
ጆቻቸው፡ወይስ፡ከእንግዶች፡ሰዎ
፳፮ ች፡ከሌሎች፨ጴጥሮስም፡ከሌሎ
ች፡ነው፡አለው፡ኢየሱስም፡እንኪያስ
ልጆቻቸው፡ነፃ፡ናቸው፡አለው፨
፳፯ ነገር፡ግን፡እንዳናሰናክላቸው፡
ወደ፡ባሕር፡ሒድ፡መቃጥንም፡ጣ
ል፡በፊትም፡የወጣውን፡ዓሣ፡ያ
ዘህ፡አፉን፡ክፈተው፡በእርሱም
አራት፡ድሪም፡ታገኛለህምወስ
ደህም፡ስለእኔና፡ስለ፡አንተ፡ስጣቸ
ው፨፩፡ቆሮ፡፲፡፴፪፡ሮሜ፡፲፫፡፯፡ሉ፡፳
፫፡፱፨

ምዕራፍ፡፲፰።

በመንግሥተ፡ሰማይ፡የሚበል
ጠው፡እንደ፡ጠየቁት፡ስለ፡ዓላ
ም፡መሰናክል፡ስለ፡መቶ፡በጎች
ም፡ምሳሌ፤ስለ፡ወንድም፡በደል፡
ይቅርታ፤ ስለ፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡
ሥልጣን፡ስለ፡አንድ፡ንጉሥ፡ምሳ
፩ ሌ፨በዚያች፡ሰዓት፡ደቀ፡መዛሙ
ርቱ፡ወደ፡ኢየሱስ፡ቀርበው፡በመ
ንግሥተ፡ሰማያት፡የሚበልጠው
ማነው፡አሉት፨ማር፱፡፴፫፡፴፯፡
፪ ሉ፡፱፡፵፮፡፵፯፨ኢየሱስም፡ሕፃን፡
ጠርቶ፡በመካከላቸው፡አቆመው፡
፫ አለም፡እውነት፡እላችኋለሁ፡ካል
ተመለሳችሁና፡እንደ፡ሕፃናት፡ካ
ልሆናችሁ፡ወደ፡መንግሥተ፡ ሰ
ማያት፡አትገቡም፨ም፱፡፲፬፨
፬ እንደዚህም፡ሕፃን፡ራሱን፡የሚያ
ዋርድ፡በመንግሥተ፡ሰማይ፡የሚ
፭ በልጥ፡እርሱ፡ነው፨እንደዚህም፡
ያለውን፡ሕፃን፡በስሜ፡የሚቀበል
እኔን፡ይቀበላል፨ም፲፡፵፨
፮ በእኔም፡ከሚያምኑት፡ከነዚህ፡
ከታናናሾቹ፡አንዱን፡ያሰናከለ፡የ
ወፍጮ፡መጅ፡በአንገቱ፡ታሥሮ፡ወ
ደ፡ጥልቅ፡ባሕር፡መስጠም፡ይሻለ
ዋል፨ኤር፡፶፩፡፷፫፡ሉ፡፲፯፡፩፡፪፡፲፬፡፲፫

ሰሉ፡መሰናክያ፡ሰዓለም፡ወዮለ
ት፡መሰናክያ፡በሚያመጣ፡ዘ
ንድ፡ግዚ፡አላትና፡ነገር፡ግን፡በር
ሱ፡ጠንቅ፡መሰናክያ፡ለምትመ
ጣበት፡ለዚያ፡ሰው፡ወዮለት።
፰ እጅህም፡እግርህም፡ብታስትህ
ቊርጠህ፡ካንተ፡ጣላት፡ሁለት፡እ
ጅ፡ሁለት፡እግር፡ኖርህ፡ወደ፡ዘለ
ዓለም፡እሳት፡ከምትጣል፡ይልቅ
አንካሳ፡ወይም፡ጒንድሽ፡ሁነህ፡
ወደ፡ሕይወት፡ብትገባ፡ይሻልሃል
ና። ም ፭፡፳፱፡፴። ዓይንህም፡ብ
ታስትህ፡አውጥተህ፡ጣላት፡ሁለት
ዓይን፡ኖርህ፡ወደ፡ገሃነመ፡እሳት፡ከ
ምትጣል፡ባንድ፡ዓይን፡ወደ፡ሕ
ይወት፡ብትገባ፡ይሻልሃልና።
፲ ከዚህ፡ከታናናሾቹ፡አንዱን፡እንዳ
ትንቁ፡ተጠንቀቁ፡መላእክቶቻቸ
ው፡በሰማያት፡ሁልጊዜ፡የሰማዩ
ን፡ያባቴን፡ፊት፡እንዲያዩ፡እላች
፲፩ ኋለሁና። ዕብ፡፩፡፲፬። የሰው፡ልጅ
የጠፋውን፡ለማዳን፡መጥቷልና
ም ፱፡፲፫፡ሉ፡፲፱፡፲፡፩ጢሞ ፩፡፲፭።
፲፪ ምን፡ይመስላችኋል፡ላንድ፡ሰው፡
መቶ፡በጎች፡ቢኖሩት፡ከነርሳቸ
ውም፡አንዱ፡ቢጠፋ፡ዘጠና፡ዘጠኙ
ን፡በተራራ፡ትቶ፡የጠፋውን፡ለ
መሻት፡አይሄድምን፧ኤር፡፬፡፯፡ሕ
ዝ፡፴፬፡፮፡፲፩፡፲፪፡ሉ፡፲፭፡፬፡፯።
፲፫ ባገኘውም፡ጊዜ፡ካልጠፉት፡ከዘ
ጠና፡ዘጠኙ፡ይልቅ፡በእርሱ፡ደስ፡
እንዲለው፡እውነት፡እላችኋለሁ
፲፬ እንዲሁም፡ከእነዚህ፡ከታናናሾ
ቹ፡አንዱ፡ይጠፋ፡ዘንድ፡የሰማዩ፡
አባታችሁ፡ፈቃድ፡አይደለም።
፲፭ ወንድምህ፡ቢበድልህ፡አንተ፡ሂደህ
ለብቻው፡ንገረው፡ቢሰማህ፡ወን
ድምህን፡ጠቀምኸው። ዘሌ፡፲፱፡፲
፲፮ ፯፡ገላ፡፮፡፩። ባይሰማህም፡በሁለ
ትና፡በሶስት፡ምስክር፡አፍ፡ነገር፡
ሁሉ፡ተጸና፡ዘንድ፡ደግመኸ፡አንዱ
ወይም፡ሁለት፡ካንተ፡ጋራ፡ውሰድ
፲፯ እርሳቸውንም፡ባይሰማ፡ለቤተ፡
ክርስቲያን፡ንገራት፡ደግሞ፡ቤተ
ክርስቲያንን፡ባይሰማት፡እንደ፡አ
ረሚና፡እንደ፡ቀራጭ፡ቊጠረው
፲፰ ፩ቆሮ፡፭፡፲፩። እውነት፡እላችኋለ
ው፡በምድር፡ያሠራችሁት፡በሰማ
ይ፡የታሠረ፡ይሆናል፡በምድርም
የፈታችሁት፡በሰማይ፡የተፈታ
ይሆናልና። ም ፲፮፡፲፱፡ዮሐ፡፳፡፳፫።
፲፱ ደግሞ፡እላችኋለሁ፡ከእናንተ፡ሁ
ለቱ፡በምድር፡ተስማምተው፡ቢ
ለምኑ፡የለመኑት፡ሁሉ፡ከሰማዩ
አባቴ፡ዘንድ፡ይደረግላቸዋል፡ማ
፳ ር፡፩፡፳፬። ሁለት፡ወይም፡ሶስት፡
ሆነው፡በስሜ፡ወደ፡እሜሰበሰቡ
በት፡ከዚያ፡በመካከላቸው፡እሆና
፳፩ ለሁና። ም ፳፰፡፳። በዚያ፡ጊዜ፡ጴ
ጥሮስ፡ወደ፡እርሱ፡ቀርቦ፡አቤቱ፡ወንድ
ሜ፡ስንት፡ጊዜ፡ቢበድለኝ፡ይቀር፡ልበለ
፳፪ ው፡እስከ፡፯ት፡ጊዜ፡ነው፡የሚለው፡ሉ፡፲፯፡፬፡ኢየሱ

ሰም፡ አለው፡ ፯ት፡ ጊዜ፡ ፯ት፡ ነው፡ እንጂ፡ ሰባት፡ ጊዜ፡
፳፫ ስለዚህም፡ ዘፍ፡ ፬፡ ፳፬። ስለዚህ
መንግሥተ፡ ሰማያት፡ አገልጋዮ
ቹን፡ ሊቈጣጠራቸው፡ ዘንድ፡
የወደደ፡ ንጉሥን፡ ትመስላ
፳፬ ለች፡ ከእርሳቸውም፡ ጋራ፡ መቈ
ጣጠርን፡ በጀመረ፡ ጊዜ፡ እልፍ፡
መክሊት፡ እዳ፡ ያለበትን፡ አንዱን
፳፭ ወደ፡ እርሱ፡ አመጡት፤ የሚከፍለ
ውም፡ ባይኖረው፡ ጌታው፡ እርሱ
ሚስቱም፡ ልጆቹም፡ ያለውን፡
ሁሉ፡ ተሸጦ፡ እዳው፡ ይከፈል፡
፳፮ ዘንድ፡ አዘዘ፤ ፬፡ ነገ፡ ፬፡ ፩፤ ያም፡ አገ
ልጋይ፡ ተደፍቶ፡ ሰገደለት፡ እንደ
ህ፡ ሲል፡ አቤቱ፡ ጥቂት፡ ታገሠኝ፡
ገንዘብህንም፡ ሁሉ፡ እከፍልሃለ
፳፯ ሁ፤ የዚያም፡ ያገልጋዩ፡ ጌታ፡ አ
ዘነለት፡ ተወው፡ እዳውንም፡ ማ
፳፰ ረው፡ ሉ፡ ፯፡ ፵፪፤ ያም፡ አገልጋይ፡
ወጥቶ፡ ከአገልጋዮቹ፡ ባልንጀሮ
ቹ፡ መቶ፡ ወቄት፡ እዳ፡ ያለበት፡ አን
ዱ፡ አገልጋይ፡ አገኘ፡ በሳይሁም፡ ያ
ለብህን፡ ገንዘቤን፡ ክፈለኝ፡ ብሎ፡
፳፱ አንቆ፡ ያዘው፤ እንዴ፡ እርሱም፡ ያ
ለው፡ አገልጋይ፡ ባልንጀራው፡ ከእ
ግሩ፡ በታች፡ ተደፍቶ፡ ጥቂት፡ ታ
ገሠኝ፡ እኔም፡ ገንዘብህን፡ ሁሉ፡
እከፍልሃለሁ፡ ብሎ፡ ለመነው።
፴ እርሱ፡ ግን፡ እምቢ፡ አለው፡ እዳው
ንም፡ ሁሉ፡ እስኪ፡ ከፍል፡ ድረስ፡
ወስዶ፡ በግዞት፡ ቤት፡ አገባው።

፴፩ ባልንጀሮቹም፡ አገልጋዮቹ፡ ያ[illegible]
ረገውን፡ ሁሉ፡ አይተው፡ እጅግ፡ አ
ዘኑ፡ መጥተውም፡ የሆነውን፡ ሁ
፴፪ ሉ፡ ለጌታቸው፡ ነገሩት። ከዚ[illegible]
ም፡ ወዲያ፡ ጌታው፡ ጠርቶ፡ አለ[illegible]
አንተ፡ ክፉ፡ አገልጋይ፡ ስለ፡ ለመን
ኸኝ፡ እኔ፡ ያንን፡ ሁሉ፡ እዳ፡ ማርሁ[ህ]
፴፫ እኔ፡ አንተን፡ እንደ፡ ማርሁህ፡ አንተ[illegible]
ደግሞ፡ ይህን፡ አገልጋይ፡ ባልንጀራህ[illegible]
ትምር፡ ዘንድ፡ አይገባህም፡ ነበር፤ ቆላ፡ ፫፡ ፲፫፤
፴፬ ጌታውም፡ ተቈጣና፡ እዳውን፡ ሁሉ፡ እስኪ
ከፍለው፡ ድረስ፡ ለሚሣቀዩት፡ አ
ሳልፎ፡ ሰጠው። ምሳ፡ ፳፩፡ ፲፫፤ ያዕ፡ ፪፡
፴፭ ፲፫። ከእናንተም፡ ወንድሙን፡ ሁሉ፡ እያ
ንዳንዱ፡ ከልቡ፡ ይቅ
ር፡ ባያደርግለት፡ እንዲሁ፡ ደግሞ፡ የ
ሰማዩ፡ አባቴ፡ ያደርግባችኋል፤
ም፮፡ ፲፬፡ ፲፭። ምዕራፍ፡ ፲፱።

በይሁዳ፡ አገር፡ ብዙ፡ ድውያን፡ እን
ደ፡ ፈወሰ፡ ፈሪሳውያን፡ ስለ፡ ሚስቱ
መፋታት፡ እንደ፡ ጠየቁት፡ ሕፃና
ት፡ ወደ፡ እርሱ፡ እንደ፡ መጡ፡ አን[ድ፡]
ሰው፡ የዘለዓለም፡ ሕይወትን፡ [illegible]
ማግኘት፡ ምን፡ ላድርግ፡ ብሎ፡ [illegible]
ደ፡ ጠየቀው፡ ጴጥሮስ፡ እኛ፡ ምን፡ [illegible]
ናገኝ፡ ይሆን፡ ብሎ፡ እንደ፡ ጠየቀው።

፩ ኢየሱስ፡ ይህን፡ ነገር፡ በፈጸመ፡ ጊ
ዜ፡ ከገሊላ፡ ተነሥቶ፡ የዮርዳኖስ
ማዶ፡ ወደ፡ እሚሆን፡ ወደ፡ ይሁዳ፡ አ
ገር፡ መጣ፤ ማር፡ ፲፡ ፩።
፪ ብዙ፡ ሕዝብም፡ ተከተሉት፡ በዚ

፫ ያም፡ ሊወሳቸው፥ ሊረሳው፡ ያኘ
ም፡ ሊፈትኑት፡ ወደ፡ እርሱ፡ መጡ፡
በማናቸውም፡ ምክንያት፡ ሁሉ፡
ሚስቱን፡ ይፈታ፡ ዘንድ፡ ለሰው፡ ይ
ገባዋልን፡ አሉት። ዘዳግ፡ ፳፬፡ ፩፡
፬ እርሱ፡ ግን፡ መለሰ፡ አላቸውም፡ አ
ላነበባችሁምን፡ አስቀድሞ፡ የፈ
ጠረ፡ ወንድና፡ ሴትን፡ ፈጥሯቸዋ
፭ ልና፡ ዘፍ፡ ፩፡ ፳፯። አለም፡ ስለዚህ፡
ሰው፡ አባቱንና፡ እናቱን፡ ይተዋል፡
ሚስቱንም፡ ይከተላል፡ ሁለቱ
ም፡ አንድ፡ ሥጋ፡ ይሆናሉ። ዘፍ፡ ፪፡
፮ ፳፬። ስለዚህም፡ አንድ፡ ሥጋ፡ ናቸ
ው፡ እንጂ፡ ሁለት፡ አይደሉም፡ እግዚ
አብሔር፡ አንድ፡ ያደረገውን፡ ሰው፡
አይለየውም፥ ሮሜ፡ ፯፡ ፪።
፯ እርሳቸውም፡ እንኪያስ፡ የፍቾዋ
ን፡ መጽሐፍ፡ ሰጥቶ፡ ይፈታት፡ ዘ
ንድ፡ ሙሴ፡ ለምን፡ አዘዘ፡ አሉት።
፰ ማ፡ ፭፡ ፴፩፡ ፴፪። እርሱም፡ አላቸ
ው፡ ሙሴ፡ ስለ፡ ልባችሁ፡ ክፋት፡
ሚስቶቻችሁን፡ ትፈቱ፡ ዘንድ፡ ፈ
ቀደላችሁ፡ ከጥንቱ፡ ግን፡ አይደለ
፱ ም። እኔም፡ እላችኋለሁ፡ ያለ፡ ዝሙ
ት፡ ምክንያት፡ ሚስቱን፡ ፈት
ቶ፡ ሌላዪቱን፡ የሚያገባ፡ ሁሉ፡ ፈ
ጽሞ፡ አመነዘረ፡ የተፈታችውን
ም፡ ያገባ፡ ፈጽሞ፡ አመነዘረ።
ሚል፡ ፪፡ ፲፬፡ ፲፮፡ ዘዳግ፡ ፳፬፡ ፪።
፲ ደቀ፡ መዛሙርቱም፡ ሰውስ፡ ከሚ
ስቱ፡ ጋራ፡ እንዲህ፡ ከሆነ፡ ማግባት

መልካም፡ አይደለም፡ አሉት። ፩ቆ
፲፩ ሮ፡ ፯፡ ፩። እርሱ፡ ግን፡ አላቸው፡ ይ
ህ፡ ነገር፡ ለተሰጣቸው፡ ነው፡ እንጂ፡
ለሁሉ፡ መፈጸም፡ አይቻላቸው
፲፪ ም። ፩ቆሮ፡ ፯፡ ፯፡ ፲፯። ከእናቶቻቸ
ቸው፡ ማሕፀን፡ ጀምረው፡ ጃንደ
ረባ፡ ሁነው፡ የተወለዱ፡ አሉና፡ ሌ
ሎችም፡ ሰዎች፡ ሰልበው፡ ጃንደረ
ባ፡ ያደረጉዋቸው፡ አሉና፡ ደግሞ
ም፡ ስለ፡ መንግሥተ፡ ሰማያት፡ ሰ
ውነታቸውን፡ ጃንደረባ፡ ያደረ
ጉ፡ አሉና፡ መፈጸም፡ የሚቻል፡ ግ
ን፡ ይፈጽም። ፩ቆሮ፡ ፯፡ ፴፪።
፲፫ በዚያ፡ ጊዜ፡ እጁን፡ ይጭንባቸው
ና፡ ይጸልይላቸው፡ ዘንድ፡ ሕፃና
ትን፡ ወደ፡ እርሱ፡ አመጡ፡ ደቀ፡ መዛ
ሙርቱም፡ ተቈጧቸው፡ ማር፡
፲፡ ፲፫፡ ሉቃ፡ ፲፰፡ ፲፭፡ ፲፯።
፲፬ ኢየሱስም፡ አለ፡ ሕፃናትን፡ ተዉዋ
ቸው፡ መንግሥተ፡ ሰማያትም፡ እ
ንደነዚህ፡ ላሉት፡ ናትና፡ ወደ፡ እኔ፡
ይመጡ፡ ዘንድ፡ አትከልክሉ
፲፭ ም። ፲፰፡ ፫። እጁንም፡ ጫነባቸውና፡
፲፮ ከዚያ፡ ሔደ። እነሆም፡ አንድ፡ ሰው፡
ወደ፡ እርሱ፡ መጥቶ፡ አንተ፡ ቸሩ፡
መምህር፡ የዘለዓለም፡ ሕይወትን
አገኝ፡ ዘንድ፡ ምን፡ መልካም፡ ነገር
ላድርግ፡ አለው። ሉቃ፡ ፲፰፡ ፲፰።
፲፯ እርሱም፡ ለምን፡ ቸር፡ ትለኛለህ
ካንዱ፡ ከእግዚአብሔር፡ በቀር፡ ሌ
ላ፡ ማንም፡ ቸር፡ የለም፡ ወደ፡ ሕይወ

ት፡ትገባ፡ዘንድ፡ብትወድ፡ትእዛ
ዙን፡ጠብቅ፡አለው። ሉቃ፡፲፡፳፭፡፳፰።
፲፰ እርሱም፡ማናቸውን፡አለው።
ኢየሱስም፡አትግደል፡አትስረቅ
አታመንዝር፡ሐሰት፡አትመስክ
፲፱ ር፡አለው። አባትህንና፡እናትህን
አክብር፡አለው፡ባልንጀራህን፡እን
ደ፡ራስህ፡ውደድ። ዘሌ፡፲፱፡፲፰።
፳ ያም፡ጐበዝ፡ይህን፡ሁሉ፡ከሕፃን
ነቴ፡ጀምሬ፡ጠብቄያለሁ፡ደግሞ
ሌላ፡ምን፡ይጐድልብኛል፡አለው።
፳፩ ኢየሱስም፡ፍጹም፡ትሆን፡ዘንድ
ብትወድስ፡ሒደህ፡ያለህንም፡ሸ
ጠህ፡ለድሆች፡ስጥ፡መዝገብህ
ም፡በሰማይ፡ተከማችቶ፡ይቆይ
ሃል፡መጥተህም፡ተከተለኝ፡አለ
፳፪ ው። ማር፡፲፡፳፪። ሉቃ፡፲፰፡፳፫። ጐበዙ
ም፡ይህንን፡ነገር፡በሰማ፡ጊዜ፡ብዙ
ገንዘብ፡ነበረውና፡አዝኖ፡ሒደ።
፳፫ መዝ፡፷፪፡፲፩። ኢየሱስም፡ለደቀ
መዛሙርቱ፡እንዲህ፡አላቸው፡እውነት፡እላች
ኋለሁ፡ባለጸጋ፡ወደ፡መንግሥተ፡
ሰማያት፡ይገባ፡ዘንድ፡ጭንቅ፡ነ
ው። ፩ጢሞ፡፮፡፱፡፲፯።
፳፬ ደግመኛም፡እላችኋለሁ፡ባለጸጋ
ወደ፡እግዚአብሔር፡መንግሥት
ከሚገባ፡ይልቅ፡ግመል፡በመርፌ
፳፭ ቀዳዳ፡ማለፍ፡ይቀላል። ደቀ
መዛሙርቱም፡ሰምተው፡እጅግ፡አ
ደነቁ፡እንግዲህ፡ሲሉ፡እንኪያ፡ማ
፳፮ ን፡ለመዳን፡ይቻላል፤ ኢየሱስም

አይቶ፡ይህ፡በሰው፡ዘንድ፡አይቻ
ልም፡በእግዚአብሔር፡ዘንድ፡
፳፯ ግን፡ሁሉ፡ይቻላል፡አላቸው። በዚ
ያም፡ጊዜ፡ጴጥሮስ፡እንዲህ፡ብሎ
መለሰ፡እነሆ፡እኛ፡ሁሉን፡ትተን፡ተ
ከተልንህ፡ምን፡እናገኝ፡ይሆን።
፳፰ ኢየሱስም፡አላቸው፡እውነት፡እ
ላችኋለሁ፡የተከተላችሁኝ፡እና
ንተ፡ስ፡የሰው፡ልጅ፡በሐዲስ፡ል
ደት፡በምድር፡አት፡በምሥጋና
ዙፋን፡በተቀመጠ፡ጊዜ፡እናንተ
ደግሞ፡በአሥራ፡ሁለቱ፡ዙፋን፡ተ
ቀምጣችሁ፡በአሥራ፡ሁለቱ፡በ
እሌ፡ነገድ፡ትፈርዳላችሁ፡መዝ
፻፳፪፡፭፡ምዕ፡፲፮፡፲፰። ሉቃ፡፳፪፡፴።
፳፱ ቤቶችንም፡ወንድሞችንም፡እኅቶ
ችንም፡አባትንና፡እናትንም፡ልጆ
ችንም፡እርሻንም፡ስለ፡ስሜ፡የ
ተወ፡ሁሉ፡መቶ፡እጥፍ፡ይወስዳ
ል፡የዘላለሙንም፡ሕይወት፡ይ
፴ ወርሳል። ነገር፡ግን፡ብዙ፡የፊተኞ
ችም፡የኋለኞች፡ይሆና
ሉ፡ደግሞ፡የኋለኞችም፡የፊተኞ
ች፡ይሆናሉ። ምዕ፡፳፡፲፮። ሉ
ቃ፡፲፫፡፴። ምዕራፍ፡፳።

ስለ፡ወይን፡ባለቤት፡ምሳሌ፡የመከ
ራው፡ነገር፡ለደቀ፡መዛሙርቱ
እንደ፡ነገራቸው፤ የዘብዴዎስ፡ል
ጆችና፡እናታቸው፡እንደ፡መጡ።
ከኢያሪኮ፡ሲወጣ፡ሁለት፡ዕው
ራን፡እንደ፡አዳነ፤

መንግሥተ፡ሰማያት፡ለወይኑ፡ስ
ራ፡ሠራተኞችን፡ሊስማማ፡ማ
ለደ፡የወጣ፡ባለቤት፡ሰውን፡ተመ
ስላለች፨ም፳፩፡፴፪፨ሠራተኞ
ችንም፡በቀን፡አንድ፡ዲናርም፡ሊ
ሰጣቸው፡ተስማማቸ፡ወደ፡ወ
ይኑ፡ስፍራ፡ሰደዳቸው። በሦስት
ሰዓትም፡ጊዜ፡ወጣ፡ሌሎችንም
ባደባባይ፡ቆመው፡ሥራ፡ፈትተ
ው፡አየ፨እነዚያንም፡እናንተም
ወደ፡ወይኔ፡ስፍራ፡ሒዱ፡የሚገ
ባውን፡እሰጣችኋለው፡አላቸው
እርሳቸውም፡ሔዱ፨ደግሞም፡
በ፮ተኛ፡በዘጠኛም፡ሰዓት፡ወ
ጣ፡እንዲሁም፡አደረገ፨በአሥራ
አንደኛውም፡ሰዓት፡ጊዜ፡ወጣ፡ሌ
ሎችንም፡ቆመው፡ስራ፡ፈትተው
አገኘ፡ቀኑን፡ሁሉ፡ሥራ፡ፈትታች
ሁ፡ከዚህ፡ለምን፡ቆማችኋል፡አ
ላቸው፨እርሳቸውም፡የሚከራ
የን፡ባይኖረን፡ነው፡አሉት፡እርሱ
ም፡አላቸው፡እናንተ፡ደግሞ፡ወ
ደ፡ወይኔ፡ስፍራ፡ሒዱ፡የሚገባች
ሁን፡ተቀበላላችሁ፡አላቸው፨
በመሸም፡ጊዜ፡የወይኑ፡ባለቤት
መጋቢውን፡ሠራተኞችን፡ጥራ፡
ከኋለኞቹም፡ጀምረህ፡እስከ፡
ፊተኞቹ ፡ዲናር፡ዋጋቸውን፡
ስጣቸው፡አለው፨በአሥራ፡አን
ደኛው፡ሰዓት፡የተከራያቸ
ው፡መጥተው፡አንዳንድ፡አን

ድ፡ዲናርም፡ተቀበሉ፨የፊተኞቹ
ም፡በመጡ፡ጊዜ፡ብዙ፡የሚወስዱ
መስሏቸው፡ነበር፡ነገር፡ግን፡እር
ሳቸው፡ደግሞ፡አንዳንድ፡አን
ዳንዚያው፡አንድ፡ዲናርም፡ተቀበ
ሉ፨ከተቀበሉም፡በኋላ፡በባለቤ
ቱ፡አንጐራጐሩበት፨ሉቃ፡፲፭፡፳፱
እንዲህ፡አያሉ፡እነዚህ፡የኋለኞቹ
አንዲት፡ሰዓት፡ብቻ፡ሰሩ፡አንተ
ም፡የቀኑን፡ድካም፡የተኩሳቱን
ም፡ድናት፡ከተሸከምነ፡ከእኛ፡
ጋራ፡አስተካከልሃቸው፨ዘፍ፴፩
፴፱፨እርሱ፡ግን፡መለሰ፡ከእርሳቸ
ውም፡ለአንዱ፡አለ፡ወዳጄ፡ሆይ፡አ
ልበደልሁህም፡ባንድ፡ዲናርም፡አ
ልተስማማሁህም፨የሚገባህ
ን፡ይዘህ፡ሒድ፡እኔም፡ለዚህ፡ለኋ
ለኛው፡እንዳንተ፡እሰጠው፡ዘ
ንድ፡እወዳለሁ፨ወይስ፡በገንዘቤ
የወደድሁትን፡አደርግ፡ዘንድ፡አ
ይገባኝምን፡ወይስ፡እኔ፡ቸር፡ስለ
ሆንሁ፡ዓይንህ፡ምቀኛ፡ናት፨ቀ
ርሜ፡፱፡፲፮፡፳፩፨እንደዚህ፡የኋለ
ኞች፡ፊተኞች፡ይሆናሉ፡የፊተኞ
ችም፡የኋለኞች፡ይሆናሉ፡የተጠ
ሩ፡ብዙዎች፡ናቸውና፡የተመረጡ
ግን፡ጥቂቶች፡ናቸው፨ም፲፱፡፴፡
ኢየሱስም፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ሲወ
ጣ፡አስራ፡ሁለቱን፡ደቀ፡መዛሙር
ቱን፡በመንገድ፡ለብቻቸው፡ወሰ
ደቸው፡አላቸውም፨ማር፡፲፡፴፪፡፴

፲፰ ፬፡ ሉ፡ ፲፰፡ ፴፩፡ ፴፫◆እነሆ፡ ወደ፡
ኢየሩሳሌም፡ እንወጣለን፡ የሰው
ልጅም፡ ለካህናት፡ አለቆችና፡ ለጻ
ፎች፡ ይሰጣል፡ የሞትም፡ ፍርድ፡
ይፈርዱበታል፡ ፲፯፡ ፳፮፡ ፲፯፡ ፳፪
፲፱ ለአሕዛብም፡ አሳልፈው፡ ይሰጡ
ታል፡ ይዘባበቱበታልም፡ ይገርፉ ታ
ልም፡ ይሰቅሉታልም፡ በሦስተኛ
፳ ውም፡ ቀን፡ ይነሣል◆በዚያም፡ ጊ
ዜ፡ የዘብዴዎስ፡ የልጆቹ፡ እናት፡ ከ
ልጆቿ፡ ጋራ፡ ወደ፡ እርሱ፡ መጣች፡ ከ
እርሱም፡ አንዳች፡ እየለመነች፡ ሰ
ገደች ለትንማር ፲፡ ፴፭፡ ፴፯፡ ምዕ፲፡ ፪
፳፩ እርሱም፡ ምን፡ ትሻለሽ፡ አላት፡ እ
ርሷም፡ በመንግሥትህ፡ እነዚህ፡ ሁለ
ቱ፡ ልጆቼ፡ አንዱ፡ በቀኝህ፡ አንዱ፡ በግራህ
እንዲቀመጡ፡ አድርግልኝ፡ አለች
፳፪ ው◆፲፱፡ ፲፰◆ኢየሱስም፡ መለ
ሰ፡ አለም፡ የምትለምኑትን፡ አታው
ቁም፡ እኔ፡ የምጠጣውን፡ ጽዋ፡ ት
ጠጡ፡ ዘንድ፡ ትችላላችሁን፡ እኔስ
የምጠመቀውን፡ ጥምቀት፡ ትጠ
መቃላችሁን፡ አላቸው፡ እርሳቸው
ም፡ እንችላለን፡ አሉት◆፳፯፡ ፴፱
፳፫ ፱፡ ዮሐ፡ ፲፰፡ ፲፩፡ ሉ፲፪፡ ፶◆ጽዋዬን፡
ትጠጣላችሁ፡ እኔ፡ የምጠመቀው
ንም፡ ጥምቀት፡ ትጠመቃላችሁ
በቀኜና፡ በግራዬ፡ መቀመጥ፡ ግን
ከአባቴ፡ ዘንድ፡ ለተዘጋጀላቸው፡ ይ
ሰጣቸዋል፡ እንጂ፡ እኔ፡ የምሰጥ፡ አ
ይደለሁም፡ አላቸው◆ሮሜ፡ ፰፡ ፲፯◆

፳፬ አሥሩም፡ ሰምተው፡ በሁለቱ፡ ወን
ድማማች፡ አዘኑ◆ሉ፳፪፡ ፳፭፡ ፳፯
፳፭ ኢየሱስም፡ ወደ፡ እርሱ፡ ጠራቸው
አለም፡ የአሕዛብ፡ አለቆች፡ እን
ገዟቸው፡ ታላላቆቻቸውም፡
ላያቸው፡ ሥልጣን፡ እንዳላቸው፡
ታውቃላችሁ◆፳፱፡ ፳፮◆
፳፮ በእናንተስ፡ እንዲህ፡ አይሆንም
ገር፡ ግን፡ በእናንተ፡ ታላቅ፡ ሊሆ
የሚወድ፡ አገልጋይ፡ ይሁናችሁ፡
፳፯ በእናንተም፡ አለቃ፡ ሊሆን፡ የሚ
ወድ፡ ሎሌ፡ ይሁናችሁ◆
፳፰ እንዲሁ፡ የሰው፡ ልጅ፡ ሊያገለግ
እንጂ፡ ሊያገለግሉት፡ እንዳልመ
ጣ፡ ነፍሱንም፡ ለብዙ፡ ቤዛ፡ ሊሰጥ
ዮሐ፲፫፡ ፬፡ ፲፡ ፊል፡ ፪፡ ፯፡ ፩፡ጢሞ፡
፳፱ ፮◆ከኢያሪኮም፡ በመጡ፡ ጊዜ፡ ብ
ዙ፡ ሕዝብ፡ ተከተሉት፡ ማር፲፡ ፵፮
፴ ፶፪፡ ሉ፡ ፲፰፡ ፴፭፡ ፵፫◆እነሆም፡ ሁ
ለት፡ ዕውሮች፡ በመንገድ፡ አጠገ
ብ፡ ተቀምጠው፡ ነበሩ፡ ኢየሱስም
በዚያ፡ እንዲያልፍ፡ በሰሙ፡ ጊ
አቤቱ፡ የዳዊት፡ ልጅ፡ ማረን፡ እ
፴፩ ጮሁ◆ሕዝቡም፡ ዝም፡ እንዲ
ገሠጿቸው፡ እርሳቸው፡ ግን፡ አ
ብዝተው፡ ጮሁ፡ እንዲህ፡ ሲሉ፡ አ
፴፪ ቤቱ፡ የዳዊት፡ ልጅ፡ ማረን፡ ኢየሱ
ስም፡ ቆሞ፡ ጠራቸውና፡ ምን፡ ትሻ
ኙ፡ አደርግላችሁ፡ ዘንድም፡ አላ
ቸው◆ዓይኖቻችን፡ ይከፈቱ፡ ዘ
፴፫ ንድ፡ አሉት◆ኢየሱስም፡ ራራላቸ

ው፡ ባደሮቻቸውንም፡ ደስ ሰ፡ በዚ
ያም፡ ጊዜ፡ ባደሮቻቸው፡ ለዩ፡ አር
ሳቸውም፡ ተከተሉት፡

ምዕራፍ፡ ፳፩፡፡

ከቤተ፡ ፋጌ፡ ሁለቱን፡ ደቀ፡ መዛሙር
ቱን፡ ላከ፡ ሁለት፡ አህዮች፡ እንደ ስመ
ጣ፡ ሕዝቡ፡ ልብሳቸውን፡ በመንገ
ዱ፡ ሳይ፡ እንደነፀፉ፡ ቅጠል፡ እንደ
ጐዝጐዙ፤ ሆሣዕና፡ በአርያም፡
ም፡ እንደሉ፡ በመቅደስ፡ የሚገበያ
ዩት፡ እንደ ሰወጣ፤ በመቅደስ፡ ዕው
ሮችንና፡ አንካሶችን፡ እንደ፡ ፈወሰ
በመንገድም፡ አጠገብ፡ በለሲቱን፡
እንደረገመ፤ የካህናት፡ አለቆች፡
በማን፡ ሥልጣን፡ ይህን፡ ታደርጋለ
ህ፡ ብለው፡ እንደ፡ ጠየቁት፤ ስለ፡ ወይ
ን፡ ተክል፡ ባለቤት፡ ምሳሌ።

ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡ ቀርበው፡ በደብ
ረ፡ ዘይት፡ አጠገብ፡ ወደ፡ ቤተ፡ ፋጌ፡
በደረሱ፡ ጊዜ፡ ኢየሱስ፡ በዚያ፡ ጊዜ
ከደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ሁለቱን፡ እንደ
ዚ፡ ብሎ፡ ላከ፡ ማር፡ ፲፩፡ ፲፡ ፴፡ ፫፡ ሉ፡ ፲፱
፳፱፡ ፴፰፡ ዮሐ ፲፪፡ ፲፪፡ ፲፰።
በፊታችሁ፡ ወዳለችው፡ መንደር፡
ሒዱ፡ ያን ጊዜም፡ የታሠረች፡ አህ
ያ፡ ታገኛላችሁ፡ ውርጫዋንም፡
ከእርሷ፡ ጋራ፡ እርሳቸውንም፡ ፈት
ታችሁ፡ አምጡልኝ። ማንም፡ አ
ንዳች፡ ቢላችሁ፡ ለጌታ፡ ያስፈልጉ
ታል፡ በሉ፡ እርሱም፡ በዚያ፡ ጊዜ፡
ፈጥኖ፡ ይሰዳቸዋል፤ ም፳፪፡ ፲፰

ይህም፡ ሁሉ፡ የሆነ፡ በነቢይ፡ የተ
ባለው፡ ይፈጸም፡ ዘንድ፡ ነው፡ እን
ደ፡ ህ፡ ሲል፡ ለፅዮን፡ ልጅ፡ ንገሯት
እነሆ፡ ንጉሥሽ፡ ገር፡ ሁኖ፡ በአህያ
ና፡ በአህያይቱም፡ ግልገል፡ ከው
ርጫይቱ፡ ላይ፡ ተቀምጦ፡ ወደንች
ይመጣልሻል። ዘካ ፱፡ ፱፡ ፲፪።
ደቀ፡ መዛሙርቱም፡ ኢየሱስ፡ እን
ደ፡ አዘዛቸው፡ አደረጉ። አህያይቱ
ንና፡ ውርጫዋን፡ አመጡ፡ ልብሳ
ቸውንም፡ በላያቸው፡ ጫኑ፡ አስቀ
መጡትም። እጅግም፡ ብዙ፡ ሰዎች
ልብሳቸውን፡ በመንገድ፡ አነፀፉ፡
ሌሎችም፡ ከዛፍ፡ ጫፍ፡ ጫፉን፡
ቈርጠው፡ በመንገድ፡ ጐዝጐዙ፡
፪ ነገ፡ ፱፡ ፲፫። በፊቱም፡ የሚሔዱ
የተከተሉትም፡ ሰዎች፡ ሆሣዕና፡
ለዳዊት፡ ልጅ፡ በእግዚአብሔር፡ ስ
ም፡ የሚመጣ፡ የተባረከ፡ ነው፡ ሆ
ሣዕና፡ በአርያም፡ እያሉ፡ ይጮሁ
ነበር። መዝ፡ ፻፲፰፡ ፳፭፡ ፳፮። እርሱ
ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡ በገባ፡ ጊዜ፡ ከተ
ማዪቱ፡ በመላዋ፡ ይህ፡ ማነው፡ እያ
ለች፡ ተሸበረች፡ ታወከች።
ሕዝቡም፡ ይህ፡ የገሊላ፡ ወገን፡ የም
ትሆን፡ የናዝሬት፡ ነቢይ፡ ኢየሱስ
ነው፡ አሉ። ኢየሱስም፡ ወደ፡ እግዚ
አብሔር፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ ገባ፡ በቤ
ተ፡ መቅደስም፡ የሚሸጡትንና፡ የ
ሚገዙትን፡ ሁሉ፡ አወጣ፡ የሰራፎ
ችንም፡ ማዕድ፡ ገበታ፡ የርግብ፡ ሻ

ጮችንም፡ወንበር፡ገለበጠ፥ዮሐ
፲፫ ፪፡፲፬፥እላቸውም፡ቤቴ፡የጸሎት
ቤት፡ይባላል፡ተብሎ፡የተጸፈው፡
ነው፡እናንተ፡ግን፡የሌቦች፡ዋሻ፡አ
ደረጋችሁት፥ኢሳ፡፶፮፡፯፤ኤር፡፯፡፲፩
፲፬ በቤተ፡መቅደስም፡ዕውሮችና፡አ
ንካሶች፡ወደ፡እርሱ፡መጡ፡ፈወሳ
፲፭ ቸውም፥የካህናት፡አለቆችና፡ጸ
ፎችም፡የሠራውን፡ታምራት፡ሕፃ
ናትም፡በቤተ፡መቅደስ፡ሲጮ
ሁና፡ሆሣዕና፡ለዳዊት፡ልጅ፡ሲሉ
፲፮ ባዩ፡ጊዜ፡ተቈጡ፥እነዚህ፡የሚሉ
ትን፡አትሰማምን፡አሉት፡ኢየሱስ
ም፡አላቸው፡አዎን፡ከሕፃናትና፡ከሕ
ፃናት፡አፍ፡ምስጋና፡አዘጋጀህ፡የተባ
ለውን፡ከቶ፡አላነበባችሁምን፥መዝ
፲፯ ፰፡፪፥ትተዋቸውም፡ከከተማ፡ውጭ
ም፡ወደ፡ቢታንያ፡ወጣ፡በዚያም፡አደ
፲፰ ረ፥በነገውም፡ወደ፡ከተማ፡ሲመለ
፲፱ ስ፡ተራበ፥በመንገድም፡አጠገብ፡በ
ለስ፡አየ፡ወደ፡እርሷም፡ሄደ፡ከቅጠል፡በቀር
አንዳች፡ስላላገኘባትም፡ለዘላለም፡ፍሬ
አይሁንብሽ፡አላት፡በዚያም፡ጊዜ፡በለ
ሲቱ፡ደረቀች፡፡ኤር፡፰፡፲፫፤ሕዝ፡፲፯፡፳፬፡
፳ ዕብ፡፮፡፰፡፡ደቀ፡መዛሙርቱም፡አይተው፡
ተደነቁ፡እንዴት፡ሲሉ፡በለሲቱ፡አሁን፡ባሁን
፳፩ እንዴት፡ደረቀች፡፡ኢየሱስም፡መልሶ፡አላቸው፡
ም፡እውነት፡እላችኋለሁ፡እምነት፡ቢኖራችሁ
ባትጠራጠሩም፡በበለሲቱ፡ብቻ፡እንዲህ፡የተደረገው
አታደርጉም፡ነገር፡ግን፡ይህን፡ተራራ፡ተነቅለህ፡ወደባሕ
ር፡ተወርወር፡ብትሉት፡ይደረጋል፡ማ፲፩፡፳፫፡
፳፪ በጸሎትና

በእምነትም፡የምትለምኑትን፡ሁ
፳፫ ሉ፡ትወስዳላችሁ፥ወደ፡ቤተ፡መቅ
ደስም፡መጥቶ፡ሲያስተምር፡የካ
ህናት፡አለቆችና፡የሕዝብ፡ሽማ
ግሌዎች፡ወደ፡እርሱ፡መጥተው፡በ
ማን፡ሥልጣን፡ይህን፡ታደርጋለህ
ይህንንስ፡ሥልጣን፡የሰጠህ፡ማነ
፳፬ ው፡አሉት፡ዮሐ፡፪፡፲፰፥ኢየሱስም
መልሶ፡አላቸውም፡እኔም፡ደግሞ፡
አንዲት፡ነገር፡እጠይቃችኋለሁ፡
እናንተ፡ብትነግሩኝ፡እኔም፡ደግ
ሞ፡ይህን፡በማን፡ሥልጣን፡እንዳደ
፳፭ ርግ፡እነግራችኋለሁ፥የዮሐንስ
ጥምቀት፡ከወዴት፡ነበረች፡ከሰማ
ይን፡ወይስ፡ከሰው፡እርሳቸውም፡ግን
በልባቸው፡አሰቡ፡እንዲህ፡ሲሉ፡
ከሰማይ፡ብንለው፡እንኪያ፡ምነው
፳፮ አላመናችሁትም፡ይለናል፥ከሰው
ም፡ብንል፡ሕዝቡን፡እንፈራለን፡ሁ
ሉ፡ዮሐንስን፡እንደ፡ነቢይ፡ያዩት፡ነ
፳፯ በርና፥ም፲፬፡፭፥ለኢየሱስም፡እና
ውቅም፡ብለው፡መለሱለት፡እርሱ
ም፡እኔም፡በምን፡ሥልጣን፡እንዳደ
ርግ፡አልነግራችሁም፡አላቸው፡
፳፰ ምን፡ይመስላችኋል፡ሁለት፡ል
ጆች፡የነበሩት፡ሰው፡ነበር፡ወደ፡ፊ
ተኛውም፡መጥቶ፡ልጄ፡ሆይ፡ዛሬ
ወደ፡ወይኔ፡ስፍራ፡ሒድና፡ሥራ፡አ
፳፱ ለው፡እርሱም፡እምቢ፡አለ፡ከዚያ
፴ ወዲያ፡ተጠጠተና፡ሔደ፥ወደ፡ሁለ
ተኛውም፡መጣ፡እንዲሁም፡አለው

እርሱም፡መለሰ፡እሺ፡ጌታዬ፡እሄ
ዳለሁ፡አለ፡ነገር፡ግን፡አልሄደም፡
ም፯፡፳፰፤ከሁለቱ፡ያባቱን፡ፈቃ
ድ፡ያደረገ፡ማናቸው፡ነው፡እርሱ
ቸው፡ም፡የፊተኛው፡አሉት፡ኢየ
ሱስም፡እውነት፡እላችኋለሁ፡ቀራ
ጮችና፡አመንዝሮች፡ወደ፡እግዚ
አብሔር፡መንግሥት፡በመግባት
ይቀድሟችኋል፡አላቸው፤ሉ
ቃ፡፲፰፡፲፬፤ዮሐንስ፡በጽድቅ፡መን
ገድ፡መጥቶላችሁ፡ነበርና፡አላመ
ናችሁትምም፡ቀራጮችና፡አመ
ንዝሮች፡ግን፡አመኑበት፡እናንተ
ም፡ይህን፡አይታችሁ፡በኋላ፡እን
ኳ፡ታምኑበት፡ዘንድ፡አልተጠጠ
ታችሁም፡ሉቃ፡፯፡፳፱፡ሌላ፡ምሳ
ሌ፡ስሙ፡የወይን፡ተክል፡የተከለ
ባለቤት፡ሰው፡ነበር፡አጥርም፡አ
ዞረለት፡መጥመቂያም፡ማሰለ
ት፡ጠረበለት፡ግምብም፡ሠራ፡
ለወይን፡ጠባቆችም፡ሰጣቸውና፡
ወደ፡ሩቅ፡አገር፡ሔደ፤ማር፡፲፪፡፩
፲፪፡ሉቃ፡፳፡፱፡፲፱፤የፍሬውም፡
ዘመን፡በደረሰ፡ጊዜ፡ፍሬውን፡ያ
መጡለት፡ዘንድ፡አገልጋዮችን
ወደ፡ወይኑ፡ጠባቆች፡ላከ፤ኢሳ፭
፩፡፲፤ወይኑን፡ጠባቆችም፡አገልጋ
ዮቹን፡ያዝዋቸው፡አንዱንም
መቱት፡ሌላውንም፡ገደሉት፡ሌ
ላውንም፡ወገሩት፤ም፳፫፡፴፬፡መ
ጊ፡ደግሞ፡ከፊተኞቹ፡የሚበዙ
ሌሎች፡አገልጋዮችን፡ላከ፡እነደ
ሁም፡አደረጉባቸው፤ም፡፳፪፡፴፡
በመጨረሻው፡ግን፡እስኪ፡ልጄ
ን፡ያፍሩት፡እንደሆነ፡ብሎ፡ልጁን
ላከባቸው፤የወይን፡ጠባቆችም፡
ልጁን፡ባዩት፡ጊዜ፡እነሆ፡ወራሹ
ይህ፡ነው፡ኑ፡እንግደለው፡ርስቱ
ን፡እኛ፡እናድርግ፡ተባባሉ፤ም፳፯
፲፰፤ይዘውትም፡ከወይኑም፡ስፍራ
ወደ፡ውጭ፡አወጡና፡ገደሉት። ዕ
ብ፲፫፡፲፪፤የወይኑም፡ባለቤት፡በ
መጣ፡ጊዜ፡የወይኑን፡ጠባቆች፡
ምን፡ያደርጋቸዋል፤ሉቃ፡፳፡፲፭
ክፎችን፡በክፉ፡ያጠፋቸዋል፡የ
ወይኑንም፡ተክል፡ለሌሎች፡ጠ
ባቆች፡አሳልፎ፡ይሰጣል፡አሉት፡
ኢየሱስም፡ከቶ፡በመጽሐፍ፡አላ
ነበባችሁምን፡ግንቢዎች፡የናቁት
ድንጊያ፡እርሱ፡የማዕዘን፡ራስ፡ሆነ
ይህም፡ከእግዚአብሔር፡ዘንድ
ሆነ፡ለዓይናችንም፡ድንቅ፡ነው፡አ
ላቸው፤መዝ፡፻፲፰፡፳፪፡የሐዋ፡፬
፲፩፡ሮሜ፡፱፡፴፫፡፩፡ጴጥ፡፪፡፯፤
ስለዚህ፡እላችኋለሁ፡የእግዚአብ
ሔር፡መንግሥት፡ከእናንተ፡እንድ
ትወጣ፡ፍሬዋንም፡ለሚያደርጉ፡
ሕዝብ፡ትሰጣለች፤በዚህም፡ደን
ጊያ፡ላይ፡የሚወድቅ፡ይቀጠቀጣ
ል፡ደንጊያውም፡የሚወድቅበት
ን፡ይፈጨዋል፡ዳን፡፪፡፴፬፡፴፭፡፵
፬። የካህናት፡አለቆችና፡ፈሪሳውያ

ኛም፡ምሳሌውን፡በሰሙ፡ጊዜ፡ስ
ለ፡እርሳቸው፡እንደ፡ተናገረ፡አወ
፵፮ ቁ፤ሊይዙትም፡አሰበው፡ሕዝቡ
ን፡ፈሩ፡በእርሳቸው፡ዘንድ፡እርሱ
እንደ፡ነቢይ፡ነበርና፤

ምዕራፍ፡፳፪።

ስለ፡ንጉሥ፡ሠርግ፡ምሳሌ፡ፈሪሳው
ያን፡ስለ፡ቄሣር፡ግብር፡እንደ፡ጠየቁ
ት፡ለሰዱቃውያን፡ትንሣኤ፡ሙታ
ንን፡እንደ፡ሰረደ፤እንደ፡ኦሪታዊ፡የ
ምትበልጠውን፡ትእዛዝ፡እንደ፡ጠ
የቀው፤ፈሪሳውያን፡የዳዊት፡ልጅ
ነቱን፡እንደ፡ጠየቁት፤

፩ ኢየሱስም፡መልሶ፡ደግሞ፡እን
ደ፡ሀ፡ብሎ፡በምሳሌ፡ነገራቸው፡፡ሉ
፪ ቃ፡፲፬፡፲፮፡፳፩፤መንግሥተ፡ሰማያ
ት፡ለልጁ፡ሠርግ፡ያደረገ፡ንጉሥ፡
ሰውን፡ትመስላለች፤ዮሐ፡፫፡፳፱፤
፫ የታደሙትንም፡ወደ፡ሠርጉ፡ይጠ
ሩ፡ዘንድ፡አገልጋዮቹን፡ላከ፡ነገር፡
፬ ግን፡አምቢ፡አሉ፤ደግሞ፡እንደ፡ህ
ብሎ፡ሌሎች፡አገልጋዮቹን፡ላከ፡
የታደሙትን፡በሏቸው፡እነሆ፡መ
ብሉን፡አዘጋጀሁ፡ሰንጎቼም፡መሰ
ናዎቹም፡ታርደዋል፡—ሁሉም፡
ተዘጋጅቷል፡ለ፡ወደ፡ሠርጉ፡ኑ፤
፭ ም፡፳፭፡፴፫፤እነርሳቸው፡ግን፡ቸል
ስሉ፡እንዱ፡ም፡ወደ፡እርሻው፡ሌላ
፮ ውም፡ወደ፡ንግዱ፡ሔደ፤የቀሩ ት
ም፡አገልጋዮቹን፡ያዙቸው፡ሰደ
ቡዋቸውም፡ገደሉዋቸውም፤

፯ ንጉሡም፡ይህን፡በሰማ፡ጊዜ፡ተ
ቆጣ፡ጭፍሮቹንም፡ላከ፡እነዚያ
ንም፡ገዳዮች፡አጠፋ፡ከተማቸው
ንም፡አቃጠለ፤ም፡፳፩፡፴፡ኢሳ፡፳፩፡
፰ ደኒ፡፱፡፳፯፤ከዚያ፡ወዲያም፡
ልጋዮቹን፡አለ፡ሠርጉስ፡ተዘጋጅ
ቶ፡ነበር፡ነገር፡ግን፡የታደሙት፡
ሚገባቸው፡አልሆኑም፤ሐዋ፡፲፫፡፵፮፤
፱ እንግዲህ፡ወደ፡መንገዱ፡መተላለ
ፊያ፡ሒዱቸሁ፡ያገኛቸሁትን፡ሁ
ሉ፡ወደ፡ሠርጉ፡ጥሩ፡ተቀሉ፡፲፬፡ማ
፲ ፳፡፳፩፡፲፮፤እነዚያም፡አገልጋዮ
ች፡ወደ፡መንገድ፡መንገድ፡ወጥተ
ው፡ያገኙትን፡ሁሉ፡ክፉዎችንም
በጎቹንም፡ሰበሰቡ፡የሠርጉን፡
ቤት፡ተቀማጮች፡መሉት፤ማ
፲፩ ፳፡፵፱፤ንጉሡም፡የተቀመ
ጡትን፡ለማየት፡በገባ፡ጊዜ፡በ
ዚያ፡የሠርግ፡ልብስ፡ያለበሰ፡
፲፪ ንድ፡ሰው፡አየ፤ወዳጄ፡ሆይ፡የሠር
ግ፡ልብስ፡ሳትለብስ፡እንዴት፡
ዚህ፡ገባህ፡አለው፡እርሱ፡ግን፡
ሳሽ፡አጣ፤ኢሳ፡፷፩፡፲፡፪፡ቆሮ፡
፲፫ በዚያም፡ጊዜ፡ንጉሡ፡ሎሌዎቹ
እሳቸውን፡እጆቹንና፡እግሮቹን፡
ሥሩት፡ወደ፡ጨለማ፡ወደ፡ውጭ
ም፡ጣሉት፡በዚያም፡ልቅሶና፡ጥር
ስ፡ማፋጨት፡ይሆናል፤ም፡፲፫፡ማ
፲፬ ፪፡፳፭፡፴፤የተጠሩ፡ብዙዎች፡
ናቸውና፡የተመረጡ፡ግን፡ጥቂቶ
ች፡ናቸው፡፡ም፡፳፡፲፮፡፡

፲፭ በዚያም፡ጊዜ፡ፈሪሳውያን፡ሔዱ
ባነጋገርም፡ያስቱት፡ዘንድ፡ተማ
ከሩ÷ማር፡፲፪፡፲፫፡ሉ፡፳፡፳፡
፲፮ ደቀ፡መዛሙርቶቻቸውንም፡ከ
ሄሮድስ፡ሰዎች፡ጋራ፡ላኩበት፡እን
ዲህ፡ሲሉ፡መምህር፡ሆይ፡አንተ፡
እውነተኛ፡እንደ፡ሆንህ፡በውነት
ም፡የእግዚአብሔርን፡መንገድ፡
እንድታስተምር፡ማንንም፡ማን፡
እንደ፡ተፈራ፡የሰውን፡ፊት፡አይተ
ህ፡እንደ፡ታደላ፡እናውቃለን÷ማ
፲፯ ር፡፫፡፯÷እንኪያ፡የሚገባውን፡
ንገረን፡ምን፡ይመስልሃል፡ለቄሳ
ሣር፡ግብር፡መስጠት፡ይገባልን፡
፲፰ ወይስ፡አይገባም÷ኢየሱስም፡ክ
ፋታቸውን፡አውቆ፡እናንተ፡ግብ
ዞች፡ለምን፡ትፈታተኑኛላችሁ
፲፱ አሳቻችሁ÷የግብሩን፡ወርቅ፡አሳዩ
ኝ፡አርሳቸውም፡ወርቁን፡አመጡ÷
፳ ይህች፡መልክ፡ጽሕፈቲቱስ፡የማ
፳፩ ን፡ናት፡አሉት÷እርሳቸውም፡
የቄሣር፡ነው፡አሉት፡እንኪያስ፡የ
ቄሣርን፡ለቄሣር፡የእግዚአብሔ
ርንም፡ለእግዚአብሔር፡ስጡ፡፡
፳፪ አላቸው÷ሮሜ፡፲፫፡፯÷ሰምተው
ም፡ተደነቁ፡ትተውትም፡ሔዱ፡፡
፳፫ በዚያውም፡ቀን፡ትንሣኤ፡ሙታ
ን፡የለም፡የሚሉ፡ሰዱቃውያን፡
፳፬ ወደ፡እርሱ፡መጡ÷እንዲህም፡
ብለው፡ጠየቁት፡መምህር፡ሆይ
ሙሴ፡አንድ፡ሰው፡ልጅ፡ሳይኖረ
ው፡ቢሞት፡ወንድሙ፡ሚስቱን፡
ወርሶ፡ለአባቱ፡ለወንድሙ፡ዘር፡
ያቁም፡ይተካ፡ብሏል÷ዘዳግ፡፳፭፡
፳፭ ፭÷በእኛም፡ዘንድ፡ሰባት፡ወንድ
ማማች፡ነበሩ፡ታላቃቸው፡ሚስ
ት፡አግብቶ፡ሞተ፡ዘርም፡ስለሌለ
ው፡ሚስቱን፡ለወንድሙ፡ተወው፡
፳፮ እንደዚሁም፡ደግሞ፡ሁለተኛው፡ሦ
ስተኛውም፡እስከ፡ሰባተኛው፡ድ
፳፯ ረስ÷ከሁሉም፡በኋላ፡ደግሞ፡ሴ
፳፰ ቲቱ፡ሞተች÷እንግዲህ፡ሁሉም፡
አግብተዋታልና፡ሙታን፡በሚነ
ሡበት፡ቀን፡ከሰባቱ፡ለማናቸው
፳፱ ሚስት፡ትሆናለች÷ኢየሱስም፡
መለሰ፡አላቸውም፡መጻሕፍትን
ና፡የእግዚአብሔርን፡ኃይል፡ባለማ
፴ ወቅ፡ትስታላችሁ÷ሙታንስ፡ሲነ
ሡ፡እንደ፡እግዚአብሔር፡መላእ
ክቶች፡በሰማይ፡ይኖራሉ፡እንጂ፡
፴፩ አያገቡም፡አይጋቡም÷ራእ፡፳፩፡፲፪
ስለ፡ትንሣኤ፡ሙታን፡ግን፡ከእግዚ
፴፪ አብሔር፡ዘንድ፡የተባለውን፡አላ
ነበባችሁምን÷እኔ፡እግዚአብሔር
የአብርሃም፡አምላክ፡የይስሐቅ
ም፡አምላክ፡የያዕቆብም፡አምላ
ክ፡ነኝ፡እግዚአብሔርየሕያዋን፡እ
ምላክ፡ነው፡እንጂ፡የሙታን፡አም
ላክ፡አይደለም፡የሚል፡ዘፀ፡፫፡፮፡
፴፫ ፲፯፡ዕብ፡፲፩፡፲፮÷ሕዝቡም፡ይህን
ሰምተው፡ትምህርቱን፡አደነቁ÷
፴፬ ፈሪሳውያንም፡ሰዱቃውያንም፡

ምላሽ፡እንዳሳጣቸው፡በሰሙ፡ጊዜ
፴፭ ወደ፡እርሱ፡ተሰበሰቡ፤ከእርሳቸ
ውም፡ወገን፡አንዱ፡የሕግ፡አዋቂ፡ሊ
ፈትነው፡ጠየቀው፡እንዲህም፡አለ
፴፮ ው፤ማር፡፲፪፡፳፰፡፳፭፤መምህር፡
ሆይ፡ከኦሪት፡ትእዛዝ፡ማናቸቱ፡ት
፴፯ በልጣለች፡ሉቃ፡፲፡፳፯፤ኢየሱስም
አለው፡እግዚአብሔር፡አምላክህን
በፍጹም፡ልብህ፡በፍጹም፡ነፍስህ
ም፡በፍጹም፡አሳብህም፡ውደድ።
፴፰ ዘዳግ፡፮፡፭፡፲፤መጀመሪያይቱና፡
የምትበልጠው፡ትእዛዝ፡ይህቺ፡ና
፴፱ ት፡ሁለተኛይቱም፡የምትመስላት
ባልንጀራህ፡እንደ፡ራስህ፡ውደድ፡ና
፵ ት፤ዘሌ፡፲፱፡፲፰፤በእነዚህ፡በሁለቱ
ትእዛዛት፡ኦሪትም፡ሁሉ፡ነቢያት
ም፡ተሰቅለዋል፡ጸንተዋልና፡ሮሜ
፵፩ ፲፫፡፲፡ገላ፡፭፡፲፬፤ፈሪሳውያንም፡ተሰ
ብስበው፡ሳሉ፡ኢየሱስ፡ጠየቃቸው፡
እንዲህ፡ሲል፤ማር፡፲፪፡፴፭፡፴፯፡ሉ
፵፪ ቃ፡፳፡፵፩፤ስለ፡ክርስቶስ፡ምን፡ይ
መስላችኋል፡የማን፡ልጅ፡ነው፡እር
ሳቸውም፡የዳዊት፡ልጅ፡ነው፡አሉት
፵፫ ኢየሱስም፡አላቸው፡እንኪያ፡እንዴ
ት፡ዳዊት፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ለሱ፤
፵፬ ጌታ፡ጌታዬን፡ጠላቶችህን፡ከእግርህ
ጫማ፡በታች፡እስክ፡አደርግልህ፡ዱ
ረስ፡በቀኜ፡ተቀመጥ፡አለው፤መዝ፡
፵፭ ፻፲፡፩፤ዳዊት፡ጌታ፡ብሎ፡ከጠራው፡
እንዴት፡ልጁ፡ይሆናል፡፩፡ዜና፡፲፯፡፲
፵፮ ፩፤ማንም፡በነገር፡ይመልስለት፡

ዘንድ፡አልቻለም፡ከዚያ፡ቀን፡ጀም
ሮ፡ማንም፡ከቶ፡ይጠይቀው፡ዘንድ
አልደፈረምና፨ ምዕራፍ፡፳፫።
ጻፎችንና፡ፈሪሳውያንን፡እንደ፡ገሠ
ፀ፡ስለ፡አቤልና፡ስለ፡ዘካርያስ፡ደም፡
መፍሰስ፡ስለ፡ኢየሩሳሌም፡ከተማ
፩ ማ፡መፍረስ፨ከዚያም፡ወደ፡ኢ
የሱስ፡ለሕዝቡና፡ለደቀ፡መዛሙ
ርቱ፡እንዲህ፡ብሎ፡ነገራቸው፡፡ማ
፪ ር፡፲፪፡፴፰፡፵፤ጻፎችና፡ፈሪሳው
ያን፡በሙሴ፡ወንበር፡ተቀምጠዋል
ሉቃ፡፲፩፡፵፮፡፵፯፡ዘፀ፡፲፰፡፲፫።
፫ ስለዚህም፡ተጠበቁ፡ዘንድ፡ያዘዙ
ዋችሁን፡ሁሉ፡ጠብቁት፡አድርጉት
ም፡እንደ፡ሥራቸው፡ግን፡አትሥሩ፤
የሚያስተምሩትን፡አያደርጉትም
፬ ና፡ሚል፡፯፡፪፤ታላቅ፡ሸክም፡የከ
በደም፡ተብትበው፡በሰው፡ጫንቃ፡ይ
ጭኑታልና፡እርሳቸው፡ግን፡በጣታ
ቸውስ፡እንኳ፡አይነኩትም፡ሉቃ፡
፭ ፲፩፡፵፮፤ሥራቸውንም፡ሁሉ፡ለሰ
ው፡ሊታዩ፡ይሠራሉ፡የቀሚሳቸ
ውንም፡እጅጌ፡ያሰፋሉ፡የልብሳ
ቸውንም፡ዘርፍ፡ያስረዝማሉ፤
ም፤ዘ፡፮፡፰፡ዘፀ፡፲፫፡፱፡ዘኍ፡፲፭፡፴፰፤
፮ በምሳም፡ጊዜ፡በላይ፡በምኵራብም
በፊተኛው፡ወንበር፡መቀመጥ፡ይ
ወዳሉ፤ሉቃ፡፲፬፡፯፡፲፩፡፵፫፡ገበያም
፯ ለገበያም፡ሰላምታ፡መስጠት፡ሰው
ም፡መምህራን፡ይሉአቸው፡ዘንድ።
፰ እናንተ፡ግን፡መምህራችሁ፡እንዱ

እርሱ፡ክርስቶስ፡ነውና፡መምህ
ራን፡ተብላችሁ፡አትጠሩ፡እናንተ
ም፡ሁላችሁ፡ወንድማማቾች፡ናችሁ
አባታችሁም፡በሰማይ፡ያለው፡አ
ንዱ፡ነውና፡በምድር፡ላይ፡ማንንም
አባት፡ብላችሁ፡አትጥሩ፡ሚል፡፩
፯፡፱፡፲፡ፊሊ፡፫፡፲፬፡፲፭፨ጌታችሁም
አንድ፡እርሱ፡ክርስቶስ፡ነውና፡ጌቶ
ችም፡ተብላችሁ፡አትጥሩ፨ከእናን
ተም፡የሚበልጥ፡አገልጋይ፡ይሁና
ችሁ፡፡ም፳፪፡፳፡፳፪፨ራሱን፡ከፍ፡
ከፍ፡የሚያደርግ፡ይዋረዳልና፡ራ
ሱንም፡የሚያዋርድ፡ከፍ፡ይላል
ና፨ምሳ፡፳፱፡፳፫፡ሐዝ፡፳፩፡፳፯፡፩
ጴጥ፡፭፡፭፨ወዮላችሁ፡እናንተ፡ጻ
ፎችና፡ፈሪሳውያንም፡ግብዞች፡
መንግሥተ፡ሰማያት፡በሰው፡ፊት
ትዘጋላችሁና፡እናንተም፡አትገ
ቡም፡የሚገቡትንም፡እንዳይገቡ
ትከለክሏቸሁ፨ሉቃ፡፲፩፡፶፪፨
ወዮላችሁ፡እናንተ፡ጻፎች፡ፈሪሳ
ውያንም፡ግብዞች፡በጸሎታችሁ
ርዝመት፡ምክንያት፡የመበለቶ
ችን፡ድሆች፡ቤት፡ትበላላችሁና፡
ስለዚህ፡ታላቅ፡ፍርድ፡ትቀበላላ
ችሁ፨ሐዝ፡፳፱፡፳፭፡ሚክ፡፪፡፱፨
ወዮላችሁ፡እናንተ፡ጻፎች፡ፈሪሳ
ውያንም፡ግብዞች፡አንድ፡ሰው፡እ
ስራኤላዊ፡ለማድረግ፡ባሕሩንም
ደረቁንም፡ትዞራላችሁና፡በሆነ
ጊዜም፡ከናንተ፡ሁለት፡እጥፍ፡የ
ገሃነምም፡ልጅ፡ታደርጉታላችሁ፨
ወዮላችሁ፡እናንተ፡የዕውሮች፡
መሪዎች፡በቤተ፡መቅደስ፡የማለ፡
መሐላው፡አይደርስበትም፡በቤ
ተ፡መቅደስ፡ወርቅ፡የማለ፡ግን፡እር
ሱ፡መሐላው፡ይደርስበታል፡የምት
ሉ፨ም፲፭፡፲፬፡እናንተ፡ሰነፎች፡
ዕውሮችም፡የሚበልጠው፡ማና
ቸው፡ነው፡ወርቁን፡ወይስ፡ወርቁ
ን፡የሚቀድሰው፡ቤተ፡መቅደስ፡
ደግማችሁም፡በመሠዊያው፡የ
ማለ፡መሐላው፡አይደርስበትም፡
በቍርባኑ፡የማለ፡ግን፡መሐላው፡
ይደርስበታል፡ትላላችሁ፨እናን
ተ፡ሰነፎች፡ዕውሮችም፡የሚበ
ልጠው፡ማናቸው፡ነው፡ቍርባኑን
ነው፡ወይስ፡ቍርባኑን፡የሚቀድሰ
ው፡መሠዊያው፨ዘፀ፡፳፱፡፴፯፨
እንኪያስ፡በመሠዊያው፡የሚም
ል፡ፈጽሞ፡በእርሱ፡በላዩም፡ባለ
ው፡ሁሉ፡ይምልበታል፨በቤተ፡መ
ቅደስም፡የሚምል፡በእርሱና፡በሚ
ያድርበትም፡ይምልበታል፨በሰማይ
ም፡የሚምል፡እርሱ፡በእግዚአብሔ
ር፡ ዙፋን፡በላዩም፡በተቀመጠው
ይምላል፨ም፭፡፴፬፨ወዮላችሁ፡
እናንተ፡ጻፎች፡ፈሪሳውያንም፡ግ
ብዞች፡ከሙን፡ዝርን፡ጤና፡አዳምን
አንሰላልናም፡ካሥር፡አንድ፡ታወጣ
ላችሁና፡ታላቁንም፡የኦሪት፡ትእዛ
ዝ፡ትዋችሁ፡ፍርድን፡ምሕረትን፡

ሃይማኖትን፡ለታደርጉ፡ይገባች
ኋል፡ያንንም፡አትተዉ፡ሉቃ፡፲፩፡
፵፪፡ዘሌ፡፳፯፡፴፡ሚክ፡፮፡፰።
፳፬ እናንተ፡የዕውሮች፡መሪዎች፡ተ
ንኙን፡የምታጠሩ፡ግመልንም፡የ
፳፭ ምትውጡ፥ወዮላችሁ፡እናንተ
ጻፎች፡ፈሪሳውያንም፡ግብዞች፡
ጽዋውንና፡ወጭቱን፡ላይ፡ላዩን፡ታ
ጸራላችሁና፡በውስጣቸው፡ግን፡
ቀሚያን፡ስስትንም፡ተመልተዋ
፳፮ ልና፥ሉቃ፡፲፩፡፴፱፡ማር፡፯፡፬፥አንተ
ዕውር፡ፈሪሳዊ፡አስቀድመህ፡ጽ
ዋውንና፡ወጭቱን፡ውስጡን፡አጽ
ራ፡ላይኛው፡ደግሞ፡ንጹሕ፡ይሆን
፳፯ ዘንድ፥ቁጥር፡፩፡፲፫፥ወዮላችሁ፡እ
ናንተ፡ጻፎች፡ፈሪሳውያንም፡ግ
ብዞች፡በውጭ፡መልካም፡ሆኖ፡የ
ሚታይ፡የተለሰነ፡መቃብርን፡ትመ
ስላላችሁና፡በውስጡ፡ግን፡የሙ
ታን፡አፅንት፡ርኩስትም፡ሁሉ፡መ
ልቶበታልና፥ሉቃ፡፲፩፡፵፬፡የሐዋ፡፳፫
፳፰ ፫፥እንዲሁ፡ደግሞ፡እናንተም፡በ
ውጭ፡ለሰው፡ጻድቃን፡መስላችሁ
ትታያላችሁ፡በውስጣችሁ፡ግን
ግብዝነትና፡ዓመፃ፡ነት፡መልቶ
፳፱ ባችኋልና፥ወዮላችሁ፡እናንተ፡ጻ
ፎች፡ፈሪሳውያንም፡ግብዞች፡የ
ነቢያትን፡መቃብር፡ትሠራላችሁ
የጻድቃንን፡መቃብር፡ታስጌጣላች
፴ ሁና፥ሉቃ፡፲፩፡፵፯፡፵፩፥በአባቶቻች
ን፡ዘመን፡ኖረን፡በሆነ፡በነቢያት፡
ደም፡ባልተባበርናቸውም፡ነበር፡
፴፩ ትላላችሁ፥እነሆ፡የነቢያት፡ገዳ
ዮች፡ልጆች፡እንደሆናችሁ፡ራሳች
ሁ፡ትመሰክራላችሁ፥የሐዋ፡[...]
፴፪ ፶፪፡እናንተ፡ያባቶቻችሁን፡መ[...]
፴፫ ርያ፡ፈጽሙ፥ምሉ፥እናንተ፡የጉ[...]
ና፡ልጆች፡እባቦች፡ከገሃነም፡ፍር[...]
እንዴት፡ታመልጣላችሁ፥ም፫፡[...]
፴፬ ስለዚህ፡እነሆ፡ነቢያትን፡ጠቢባን[...]
ጻፎችንም፡ወደ፡እናንተ፡እልካለ
ሁ፡ከነርሳቸውም፡ትገድላላችሁ
ትሰቅሉማላችሁ፡ከነርሳቸውም
በመስጊዳቸሁ፡ትገርፋላችሁ፡ከ
አገርም፡ወደ፡አገር፡ታሳድዳላች[...]
፴፭ ሁ፥ም፲፡፶፪፥ከጻድቁ፡ከአቤ[...]
ደም፡ጀምሮ፡በቤተ፡መቅደስና፡
በመሠዊያው፡መካከል፡እስከ፡ገ
ደላችሁት፡እስከ፡በራክዩ፡ልጅ፡እ
ስከ፡ዘካርያስ፡ደም፡ድረስ፡በምድ[...]
ር፡ላይ፡የፈሰሰው፡የጻድቃን፡ደም
ሁሉ፡ይደርስባችሁ፡ዘንድ፥
ኦሪ፡፳፬፡፲፰፡፩፡ዮሐ፡፫፡፲፪፡፪፡ዜ[...]
፴፮ ፳፬፡፳፡፳፩፥ይህም፡ሁሉ፡በዚ[...]
ት፡ውልድ፡ላይ፡እንዲደርስ፡በእው[...]
፴፯ ት፡እላችኋለሁ፥ኢየሩሳሌም፡ኢ
የሩሳሌም፡ሆይ፡ነቢያትን፡የምት
ገድዪ፡ወደአንቺ፡የተላኩትንም፡
የምትወግሪ፡ዶሮ፡ጫጩቶቿን
ን፡በክንፍዋ፡በታች፡እንደምትሰበ
ስብ፡ልጆችሽን፡እሰበስብ፡ዘንድ፡
ስንት፡ጊዜ፡ፈቀድሁ፡እናንተ፡ግን

ን፡ እምቢ፡ አላችሁ፡ ሉቃ፡ ፲፫፡ ፴፬፡
፴፰ የሐዋ፡ ፯፡ ፶፩። እነሆ፡ ቤታችሁ፡
የፈረሰና፡ የተፈታ፡ ሆኖ፡ ይቀር
ላችኋል፡ ፩፡ ነገ፡ ፱፡ ፯፡ ኤር፡ ፳፪፡ ፭
፴፱ ፲፡ በእግዚአብሔር፡ ስም፡ የሚ
መጣ፡ የተባረከ፡ ነው፡ እስክትሉ፡
ድረስ፡ እንግዲህ፡ አታዩኝም፡ ብዬ
በውነት፡ እነግራችኋለሁ፡ ም፡ ፻፲
፰።

ምዕራፍ ፳፬።

ስለ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ መፍረስ፡ ስለ፡ ሐ
ሳዊ፡ መሲሕ፡ ስለ፡ ዓለም፡ ጦርነትና፡
መከራ፤ ወንጌል፡ በዓለሙ፡ ሁሉ፡
ስለ፡ መሰበኩ፤ ስለ፡ ምጽአት፡ ምል
ክት፤ ስለ፡ ሴባ፡ አመጣጥና፡ ስለ፡
ታመኑ፡ መጋቢ።

፩ ኢየሱስም፡ ከቤተ፡ መቅደስ፡ ወጥ
ቶ፡ ሲሄድ፡ ደቀ፡ መዛሙርቱም፡ የቤ
ተ፡ መቅደስን፡ ሥራ፡ ሊያሳዩት፡ ወ
ደ፡ እርሱ፡ ቀረቡ። ማር፡ ፲፫፡ ሉቃ፡ ፳
፪ ፩። ኢየሱስም፡ ይህን፡ ሁሉ፡ ታያ
ላችሁን፧ እውነት፡ እላችኋለሁ፡ ከ
ዚህ፡ ድንጊያ፡ በድንጊያ፡ ላይ፡ ሳይፈ
ርስ፡ አይቀርም፡ አላቸው። ሉ፡ ፲፱፡ ፵
፫ ፬። እርሱም፡ በደብረ፡ ዘይት፡ ተቀ
ምጦ፡ ሳለ፡ ደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ለብ
ቻቸው፡ ወደ፡ እርሱ፡ ቀርበው፡ ይ
ህ፡ መቼ፡ ይሆናል፡ የመምጣትህስ
የዓለሙ፡ ፍጻሜ፡ ምልክት፡ ምን
ድር፡ ነው፡ እስኪ፡ ንገረን፡ አሉት።
፬ ኢየሱስም፡ መልሶ፡ ማንም፡ እንዳ
ያስታችሁ፡ ተጠንቀቁ፡ አላቸው።

፭ ብዙ፡ ሰዎች፡ እኔ፡ ክርስቶስ፡ ነኝ፡ እ
ያሉ፡ በስሜ፡ ይመጣሉና፡ ብዙ፡ ሰ
ዎችንም፡ ያስታሉ። ቍ፡ ፳፬፡ የሐዋ
፮ ፭፡ ፴፯፡ ፩፡ ዮሐ፡ ፪፡ ፲፰። ጦርነትን
የጦርነትንም፡ ወሬ፡ ትሰማላችሁ
ይህ፡ ሁሉ፡ ይሆን፡ ዘንድ፡ አለውና፡ እ
ንዳትደነግጡ፡ ዕወቁ፡ ነገር፡ ግን፡ ያ
ን፡ ጊዜ፡ የሚፈጸም፡ አይደለም።
፯ ሕዝብም፡ በሕዝብ፡ ላይ፡ መንግሥ
ትም፡ በመንግሥት፡ ላይ፡ ይነሣሉ
ና፡ በያገሩም፡ ራብ፡ ቸነፈርም፡ የ
ምድር፡ መናወጥም፡ ይሆናል።
፰ ይህም፡ ሁሉ፡ የምጥ፡ ጣር፡ መጀ
፱ መሪያ፡ ነው። በዚያን፡ ጊዜ፡ ለመከ
ራ፡ አሳልፈው፡ ይሰጧችኋል፡ ይገ
ድሏችኋልም፡ ስለ፡ ስሜም፡ በሕ
ዝብ፡ ሁሉ፡ የተጠላችሁ፡ ትሆናላች
፲ ሁ። ም፡ ፲፡ ፳፪፡ ዮሐ፡ ፲፮፡ ፪። በዚያም
ጊዜ፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ ይሰናከላሉ፡ እን
ዱ፡ እንዱን፡ አሳልፎ፡ ይሰጣል፡ እ
ርስ፡ በርሳቸውም፡ ይጣላሉ።
፲፩ ብዙ፡ ሐሰተኞች፡ ነቢያትም፡ ይነሣ
ሉ፡ ብዙዎችንም፡ ያስታሉ። ም፡ ፯፡
፲፪ ፲፭፡ ፩፡ ዮሐ፡ ፬፡ ፩። ከዓመፃ፡ ብዛት
ም፡ የተነሣ፡ ፍቅር፡ ከብዙ፡ ሰዎች
ትበርዳለች። ፪፡ ተሰ፡ ፪፡ ፲፡ ፩፡ ጢሞ
፲፫ ፫፡ ፩። እስከ፡ መጨረሻ፡ የሚታገ
ሥ፡ ግን፡ እርሱ፡ ይድናል። ሉቃ፡ ፲፡ ፲
፲፬ ይህም፡ የመንግሥት፡ ወንጌል፡ በዓ
ለሙ፡ ሁሉ፡ ይሰበካል፡ ለአሕዛብ፡
ሁሉ፡ ምስክር፡ ይሆናቸው፡ ዘንድ

ያንጊዜም፡ፍጹሚ፡ይመጣሉ፡ም
፳ ፭፹፡፲፱ ም፡፲፡፲፹፣በነቢዩ፡በዳን
ኤል፡የተባለውንም፡የመፍረሱ
ን፡ርኩሰት፡በተቀደሰ፡ስፍራ፡ቁ
ሞ፡ባያችሁ፡ጊዜ፡አንባቢም፡ያ
ስተውል፥ዳን፡፱፡፳፯፡፳፯፡፲፪፡፲፩
፲፮ በዚያን፡ጊዜ፡በይሁዳ፡ያሉ፡ሰዎ
፲፯ ች፡ወደተራራ፡ይሽሹ። በሰገነ
ት፡ያለም፡ከቤቱ፡ዕንዳች፡ይወ
ስድ፡ዘንድ፡አይውረድ፥ሉ፡፲፯፡
፲፰ ፴፩፡በውድማ፡በዱር፡ያለም፡ል
ብሱን፡ ይውሰድ፡ወደ፡ኋላው
፲፱ አይመለስ፥በዚያም፡ወራት፡ለ
ርጉዞችና፡ለሚያጠቡ፡ወዮ፡ላ
፳ ቸው፥መሸሻችሁም፡ስደቱ
ችሁም፡በክረምትና፡በሰንበት
፳፩ እንዳይሆን፡ጸልዩ፥በዚያን፡ጊዜ
ዓለም፡ከተፈጠረ፡ጀምሮ፡እስከ
ዛሬ፡ድረስ፡እንዳርሱ፡ያልሆነ፡እ
ንግዲህም፡የማይሆን፡ታላቅ፡መ
፳፪ ከራ፡ይሆናልና፥ዳን፡፲፪፡፩፡እነዚ
ያ፡ወራቶችንሸ፡ባያጥሩ፡ሥጋ፡የ
ለበሰ፡ሁሉ፡ባልዳነም፡ነበር፡ነገር
ግን፡እነዚያ፡ቀኖች፡ስለ፡ተመረ
፳፫ ጡት፡ያጥራሉ፥በዚያን፡ጊዜ፡(
ማንም፡እነሆ፡ክርስቶስ፡በዚህ፡
ነው፡ወይም፡በዚያ፡ነው፡ቢሏች
፳፬ ሁ፡አትመኑ፥ሐሰተኞች፡መሲሆ
ች፡መምህራን፡ሐሰተኞች፡ነቢ
ያቶችም፡ይነሣሉና፡ለማሳት፡(
ም፡ታላላቅ፡ምልክትና፡ታምራ

ት፡ያደርጋሉ፡ቢቻላቸውስ፡የተ
መረጡትን፡ስንኳ፡ያስታሉ፥ሞ
፳፭ ሮ፡፲፩፡፳፡ተሰ፡፪፡፫፡፱፥እነሆ፡አስቀ
፳፮ ድሜ፡ነገርኋችሁ፥እነሆ፡በም
ድረ፡በዳ፡ነው፡ቢሏችሁ፡አትውጡ
ጡ፡እነሆ፡በቤትም፡ነው፡ቢሏች
፳፯ ሁ፡አትመኑ፥መብረቅ፡ከምሥራ
ቅ፡ተወርውሮ፡እስከ፡ምዕራብ
ም፡እንደሚበራ፡የሰው፡ልጅ፡መ
ምጣቱ፡እንዲሁ፡ይሆና
፳፰ ልናሉ፡ቃ፡፲፯፡፳፬፥ጥንብም፡ወ
ደአለበት፡ከዚያ፡አሞሮች፡ይሰበ
ሰባሉ፥ኢዮ፡፴፱፡፴፡ ፡ዕንባ፡፩
፳፱ ፲፭፡ሉ፡፲፯፡፴፯፥ከዚያም፡ዘመኑ
መከራ፡በኋላ፡ፀሐይ፡ጨለማ፡ት
ሆናለች፡ጨረቃም፡ብርሃኗን
አትሰጥም፡ከዋክብትም፡ከሰማ
ይ፡ይወድቃሉ፡የሰማይም፡ኃይ
ላት፡ይናወጣሉ፥ኢሳ፡፲፫፡፲፪፡፬፡ጴ
፴ ጥ፡፫፡፲፥በዚያን፡ጊዜ፡የሰው፡ልጅ
ምልክት፡በሰማይ፡ይገለጻል፡በዚ
ያን፡ጊዜ፡የምድር፡ሕዝቦች፡ሁ
ሉ፡ያለቅሳሉ፡የሰው፡ልጅንም፡
ከኃይልና፡ከብዙ፡ግርማ፡ጋራ፡በ
ሰማይ፡ደመና፡ሲመጣ፡ያዩታል
፴፩ መላእክቶቹንም፡ከታላቅ፡መለ
ከት፡ድምፅ፡ጋራ፡ይልካቸዋል
ለእርሱ፡የተመረጡትንም፡ከሰ
ማይ፡ዳር፡ጀምሮ፡እስከ፡ዳርቻው
ረስ፡ከአራቱ፡ነፋሳት፡ማዕዘን፡ይ
ሰበስባሉ፥፩፡ቆሮ፡፲፭፡፶፪፡፩፡ተሰ፡፬

፲፯፡ራዕ፡፰፡፩፡፲፥ምሳሌዋንም፡ከ
በለስ፡ዕወቁ፡ጫፍዋ፡ያቈጠቈጠ
ቅጠሏዋም፡የለመለመ፡እንደሆነ፡
መከር፡እንደ፡ቀረበ፡ታውቃላችሁ
እንዲሁ፡ደግሞ፡እናንተም፡ይህን
ሁሉ፡ባያችሁ፡ጊዜ፡በደጅ፡እንደ፡
ቀረበ፡ዕወቁ፥ይህ፡ሁሉ፡እስኪሆ
ን፡ድረስ፡ይህች፡ትውልድ፡አንዳ
ታልፍ፡እውነት፡እላችኋለሁ፥
ሰማይና፡ምድር፡ያልፋሉ፡ቃሌ፡ግ
ን፡አያልፍም፡ም፳፬፡፲፰፥ስለዚያች
ቀን፡ስለዚያችም፡ሰዓት፡ግን፡ከን
ጂ፡ከአብ፡በቀር፡የሰማይ፡መላእ
ክት፡ወልድም፡ቢሆን፡የሚያው
ቃት፡የለም፥፩ተሰ፡፭፡፩፡፲፪፥
በኖህ፡ዘመንም፡እንደሆነ፡የሰው
ልጅ፡መምጣት፡ደግሞ፡እንዲሁ፡
ይሆናል፥ዘፍ፡፮፡፲፩፡፳፪፡ሉቃ፡፲፯
፳፮፡፳፯፥ ከጥፋት፡ውሀ፡ዘመን፡
በፊት፡ኖኅ፡ወደ፡መርከብ፡እስከ
ሚገባበት፡ቀን ═══ ሲበሉም
ሲጠጡም፡ሲያገቡም፡ሲጋቡ
ም፡እንደ፡ነበሩ፥፩፡ጴጥ፡፫፡፳፡፪፡
የጥፋት፡ውሀ፡መጥቶ፡ሁሉን፡እ
ስኪያጠፋ፡ድረስ፡እንዳላወቁ፡የ
ሰው፡ልጅ፡መምጣት፡ደግሞ፡እ
ንዲሁ፡ይሆናል፥በዚያን፡ጊዜ፡ሁ
ለቱ፡በእርሻ፡ይሆናሉ፡አንዱ፡ይ
ወሰዳታል፡ሁለተኛው፡ግን፡ይተ
ዋታል፡ሉ፡፲፯፡፴፭፡፴፮፥ሁለት
ሴቶች፡በወፍጮ፡ይፈጫሉ፡

ሉ፡አንደኛዪቱ፡ትወሰዳለች፡ሁ
ለተኛዪቱም፡ትተዋለች፥
እንግዲህ፡ጌታችሁ፡በምን
ኛ፡ሰዓት፡እንዲመጣ፡አታውቁ
ምና፥ም፳፬፡፲፫፥ይህንን፡ግን፡ዕ
ወቁ፡ባለቤት፡በምን፡ጊዜ፡ሌባ፡እ
ንዲመጣ፡ቢያውቅ፡ተግቶ፡በጠ
በቀ፡ነበር፡ቤቱንም፡ሲቆፍር፡ዝ
ም፡ባላለም፡ነበር፥ሉ፡፲፪፡፴፱፡፵
ስለዚህ፡እናንተም፡ደግሞ፡ተዘጋ
ጅታችሁ፡ተቀመጡ፡የሰው፡ልጅ
ባላሰባችሁት፡ሰዓት፡ይመጣልና፥
ምግባቸውን፡በየጊዜው፡ይሰጣቸ
ው፡ዘንድ፡ጌታው፡በቤቱ፡ሰዎች፡
ላይ፡የሚሾመው፡የታመነውና፡
ብልሃተኛው፡አገልጋይ፡እስኪ
ማነው፥ጌታው፡መጥቶ፡እንዲህ
ሲያደርግ፡የሚያገኘው፡ያ፡አገ
ልጋይ፡ብፁዕ፡ነው፡ም፳፭፡፳፩፡፳
፫፥ዕውነት፡እላችኋለሁ፡በገን
ዘቡ፡ላይ፡ሁሉ፡እንዲሾመው፥
ያ፡ክፉ፡አገልጋይ፡ግን፡በልቡ፡ጌታ
ዬ፡እስኪመጣ፡ይዘገያል፡ቢል፥
መክ፡፰፡፲፩፥ባልንጀሮቹንም፡አ
ገልጋዮች፡ሊመታ፡ይጀምራል፡ከ
ሰካሮችም፡ጋራ፡ይበላል፡ይጠጣ
ልም፡፡የዚያም፡አገልጋይ፡ጌታ፡
ባላሰበው፡ቀን፡ባላወቃትም፡ሰዓ
ት፡ይመጣል፥ከመካከሉም፡ይ
ሰነጥቀዋል፡ይሸረዋል፡እድሉ
ንም፡ከግብዞች፡ጋራ፡ያደርገዋል

በዚያም፡ ልቅሶ፡ ጥርስ፡ ማፋጨት፡ ይሆናል፡ ማቴ፡ ፰፡ ፲፪።

ምዕራፍ፡ ፳፭።

ስለ፡ አሥሩ፡ ደናግል፡ ምሳሌ፡ ስለ፡ አምስቱ፡ ስለ፡ ሁለቱ፡ ስለ፡ አንድም፡ መክሊት፡ ምሳሌ፤ ስለ፡ ምጽአት፡ ስለ፡ ጻድቃንና፡ ስለ፡ ኃጥአን፡ ፍርድ።

፩ በዚያ፡ ጊዜ፡ መንግሥተ፡ ሰማያት፡ መብራታቸውን፡ ይዘው፡ ሙሽራውን፡ ለመቀበል፡ የወጡ፡ አሥር፡ ደናግልን፡ ትመስላለች። ሉቃ፡ ፲፪፡ ፴፭፡ ራዕ፡ ፲፱፡ ፯። ፪ ከነርሳቸውም፡ አምስቱ፡ ብልሃተኞች፡ አምስቱ፡ ሰነፎች፡ ነበሩ። ፫ ሰነፎች፡ ግን፡ መብራታቸውን፡ ይዘው፡ ከነርሳቸው፡ ጋራ፡ ዘይት፡ አልያዙም። ፬ ብልሃተኞች፡ ግን፡ ከመብራቸው፡ ጋራ፡ በማሰሮዎቻቸው፡ ዘይት፡ ይዘዋል። ፭ ሙሽራውም፡ በዘገየ፡ ጊዜ፡ ሁሉም፡ እንቅላፋ፡ ተኙም። ፮ እኩል፡ ሌሊትም፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ ጩኸት፡ ሆነ፡ እነሆም፡ ሙሽራ፡ ደረሰ፡ ትቀበሉት፡ ዘንድ፡ ውጡ። ፩፡ ተሰ፡ ፬፡ ፲፯። ፯ በዚያ፡ ጊዜ፡ እነዚያ፡ ደናግል፡ ሁሉ፡ ተነሡ፡ መብራታቸውንም፡ አዘጋጁ። ፰ ሰነፎችም፡ ብልሃተኞቹን፡ መብራታችን፡ ሊጠፋብን፡ ነውና፡ ከዘይታችሁ፡ ስጡን፡ አሏቸው። ማቴ፡ ፭፡ ፲፭። ፱ ብልሃተኞቹም፡ ለእኛና፡ ለእናንተ፡ አይበቃንም፡ ወደሚሸጡት፡ ሒዱና፡ ለእናንተ፡ ግዙ፡ እንጂ፡ ብለው፡ መለሱላቸው። ፲ ሊገዙም፡ በሄዱ፡ ጊዜ፡ ሙሽራው፡ መጣ፡ የተዘጋጁትም፡ ከእርሱ፡ ጋራ፡ ወደ፡ ሠርግ፡ ገቡ፡ ደጁም፡ ተዘጋ። ሉ፡ ፲፫፡ ፳፭። ፲፩ ከዚያም፡ በኋላ፡ የቀሩት፡ ደናግል፡ መጥተው፡ አቤቱ፡ ክፈትልን፡ ሉ፡ ፲፫፡ ፳፭። ፲፪ እርሱ፡ ግን፡ መልሶ፡ እውነት፡ እላችኋለሁ፡ እንዳላውቃችሁ፡ አላቸው። ማቴ፡ ፯፡ ፳፫። ፲፫ እንግዲህ፡ የሰው፡ ልጅ፡ የሚመጣበትን፡ ቀኒቱን፡ ሰዓቲቱንም፡ አታውቁትምና፡ ትጉ። ማቴ፡ ፳፬፡ ፵፪። ፲፬ ወደ፡ ሩቅ፡ አገር፡ ለመሔድ፡ እንደ፡ ሰበና፡ አገልጋዮቹንም፡ ጸርቶ፡ ገንዘቡን፡ እንደ፡ ሰጣቸው፡ ሰው፡ ነውና። ሉ፡ ፲፱፡ ፲፪፡ ፳፪። ፲፭ ለሁሉም፡ እንደ፡ ችሎቱ፡ ላንዱ፡ አምስት፡ መክሊት፡ ሰጠው፡ ለሁለተኛው፡ ሁለት፡ መክሊት፡ ለሦስተኛው፡ አንድ፡ መክሊት፡ ሰጣቸው፡ ከዚያም፡ ወዲያ፡ መንገዱን፡ ሔደ። ሮሜ፡ ፲፪፡ ፮። ፩ቆሮ፡ ፲፪፡ ፬። ፲፮ አምስት፡ መክሊት፡ የወሰደውም፡ ሔደና፡ ነግዶበት፡ ሌላም፡ አምስት፡ መክሊት፡ አተረፈበት። ፲፯ እንዲሁም፡ ደግሞ፡ ሁለት፡ መክሊት፡ የወሰደው፡ እርሱም፡ ደግሞ፡ ሌላ፡ ሁለት፡ መክሊት፡ አተረፈበት። ፲፰ አንድ፡ መክሊት፡ የወሰደው፡ ግን፡ ሔዶ፡ ምድርም፡ ቆፈረና፡ የጌታውን፡ ወርቅ፡ ቀበረ። ፲፱ ከብዙ፡ ዘመንም፡ በኋላ፡ የነዚያ፡ አገልጋዮች፡ ጌታ፡

መጣና፡ተቈጣጠራቸው፡ም፲፰፡ ፳፫፡ እምስት፡መክሊትም፡የወሰደው፡መጥቶ፡አቢቱ፡አምስት፡መክሊት፡ሰጥተኸኝ፡ነበር፡እነሆ ሌላ፡አምስት፡መክሊት፡አተረፍሁበት፡ብሎ፡ሌላ፡አምስት፡መክሊት ሰጠ፡ጌታው፡ም፡አዎን፡አንተ፡መልካምና፡የታመንህ፡አገልጋይ፡ በጥቂት፡ታምነሃልና፡በብዙ፡ላይ፡እሾምሃለሁ፡ወደ፡ጌታህ፡ደስታ፡ግባ፡አለው፡ም፳፭፡ሟ፳፡ሉ፡፲፪፡ ፲፡ዕብ፡፲፪፡፪ ሁለት፡መክሊትም የወሰደው፡መጣ፡አለም፡ጌታዬ፡ሆይ፡ሁለት፡መክሊት፡ሰጥተኸኝ፡ነበር፡እነሆ፡ሌላ፡ሁለት፡መክሊት፡አተረፍሁ ጌታው፡ም፡አዎን፡አንተ መልካምና፡የታመንህ፡አገልጋይ በጥቂት፡ታምነሃልና፡በብዙ፡ላይ እሾምሃለሁ፡ወደ፡ጌታህ፡ደስታ፡ግባ፡አለው ፳፭ አንድ፡መክሊትም፡የወሰደው፡መጣና፡አለ፡ጌታዬ፡ሆይ፡ያልዘራኸውን፡የምታጭድ፡ ያልበተንኸውን፡የምትሰበስብ፡ ጨካኝ፡ሰው፡እንደሆንህ፡አወቅሁ እሬም፡ፈራሁና፡ሔጄ፡ወርቅህን፡ ቀበርሁ፡እነሆ፡ገንዘብህን፥ምዕ፡፳ ፬፡፲፫፡ጌታው፡ም፡መለሰ፡አለው፡ም፡ አንተ፡ክፉ፡ሥራ፡ፈትም፡አገልጋይ ያልዘራሁትን፡እንደማጭድ፡ያልበተንሁትንም፡እንድሰበስብ፡ታውቃለህ፡ስለዚህ፡ወርቄን፡ለለዋጮች፡ለሰጥጮች፡መስጠት፡ይገባህ፡ነበር፡እኔም፡መጥቼ፡ገንዘቤን፡ ከትርፉ፡ጋራ፡እወስድ፡ነበርሁ፡ ስለዚህም፡ያንን፡አንዱን፡መክሊት፡ከእርሱ፡ነጥቃችሁ፡አሥር፡መክሊት፡ላለው፡ስጡት፡፡ላለው፡ሁሉ፡ይሰጡታል፡ይጨምሩለታልም፡ለሌለው፡ግን፡ያንኑ፡ያለውን፡ ይወስዱበታልና፡ም፲፫፡፲፪፡ሉ፡ር፳፡ ፲፫፡ያንኑም፡ሰነፍ፡አገልጋይ፡ወደ ውጭ፡ጨለማ፡ወደ ለበት፡ጣሉት በዚያም፡ልቅሶና፡ጥርስ፡ማፋጨት፡ይሆናልና፡ም፳፬፡፶፩፡ቀዱሳን፡ መላእክት፡ሁሉ፡ከእርሱ፡ጋራ፡ሁነው፡የሰው፡ልጅ፡በግርማው፡በመጣ፡ጊዜ፡በዚያን፡ጊዜ፡በጌትነቱ፡ ዙፋን፡ይቀመጣል፤፩ተሰ፡፬፡፲፯፡ ፬፡ተሰ፡፩፡፯፡ሕዝብም፡ሁሉ፡በፊቱ፡ይሰበሰባሉ፡እርስ፡በርሳቸውም ም፡ይለያቸዋል፡ጠባቂ፡በጎችን፡ ከፍየሎች፡እንደሚለይ፤ሮሜ፡፲፬፡ ፲፡ራዕ፡፳፡፲፪፡ሕዝ፡፴፬፡፲፯፡ በጎችንም፡በቀኙ፡ፍየሎችንም፡ በግራው፡ያቆማል፤በዚያን፡ጊዜ ንጉሡ፡በቀኙ፡ያሉትን፡እናንተ፡ ያባቴ፡ብሩካን፡ኑ፡ዓለሙ፡ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን፡መንግሥት፡ ተወርሱ፡ዘንድ፡ኑ፡ይላቸዋል፤ ኢሳ፡ ፫፡፳፫፡ ዮሐ፡፲፪፡፳፮፡ ተርቤ፡አብልታችሁኛልና፡ተጠምቼ፡አጠጥታችሁኛልና፡እንግ

ጸ፡ሁኚ፡ተቀብላችሁኛልና፡ኢሳ፡
ሣ፯ ፶፱፡፪፡ቃርዝ፡አልብላችሁኛል
ና፡ታምሚ፡ጕብኛታችሁኛልና፡
ሣ፰ ታስሬ፡ወደኔ፡መዋታችኋልና፡በ
ዚያኛ፡ጊዜ፡ጸድቃኛ፡እኝዱህ፡ብለ
ው፡ይመልሱለታል፡አቤቱ፡መቼ፡
ተርበህ፡አየኝህ፡አበላኝ፡ወይስ፡ተ
ጸምተህ፡አጠጣኝህ፡፡ም፡፬፡፫፥
ሣ፱ መቸስ፡እኝግዷ፡ሁነህ፡አየኝህ፡ተቀ
በልኝህ፡ወይስ፡ታርዘህ፡አለበስኝ
ሥ ህ፥መቼ፡ታመምክና፡አየኝህ፡ወ(
ይስ፡መቼ፡ታሠርክና፡ጠየቅኝህ፡
ሥ፩ ኛጉሡም፡መልሶ፡እውነት፡እላች
ኋለሁ፡ከነዚህ፡ከታናናሾቹ፡ወኝ
ድሞቼ፡ላኝዱ፡ያደረጋችሁት፡ለኔ
አደረጋችሁ፡ይላቸዋል፥ም፡፲፡፵
ሥ፪ ፩ጴጥ፡፬፡፲፡ያዕ፡፪፡፲፫፥ከዚያ፡ወደ
ያ፡ደግሞ፡በግራው፡ያሉትኝ፡እናኝ
ተ፡ርጉማኝ፡ከኔ፡ራቁ፡ለሰይጣኝና
ለመላእክቱም፡ወደ፡ተዘጋጀው፡ወ
ደ፡ዘለዓለም፡እሳት፡ሒዱ፡ይላቸዋ
ል፥ኢሳ፡፴፡፴፫፡ራእ፡፳፡፲፡፲፫፥
ሥ፫ ተርቤ፡አላበላችሁኝምና፡ተጠም
ቼ፡አላጠጣችሁኝምና፡ኢዮ፳፱፡፯
ሥ፬ ፯፡ያዕ፡፬፡፲፯፥እኝግዷ፡ሁኚ፡አልተቀ
በላችሁኝምና፡ታርዝ፡አላለበሳ
ችሁኝምና፡ታምሚ፡ታስሬም፡እ
ሥ፭ ላያችሁኝምና፥በዚያኝ፡ጊዜም፡
እርሳቸው፡ደግሞ፡እኝዱህ፡ሲሉ፡
ይመልሱለታል፡አቤቱ፡ተርበህወ
ይስ፡ተ(ጸምተህ፡ወይስ፡እኝግዷሁ

ነህ፡ወይስ፡ታርዘህ፡ወይስ፡ታመ
ህ፡ወይስ፡ታሥረህ፡መቸ፡አይተኝ
ሥ፮ ህ፡አላገለገልኝህም፥በዚያኛ፡ኛጉ
ሡ፡እውነት፡እላችኋለሁ፡ከነዚህ
ከታናናሾቹ፡ላኝዱ፡ያላደረጋችሁ
ት፡ለኔ፡አላደረጋችሁትም፡ብሎ፡
ሥ፯ ይመልስላቸዋል፥እነዚያም፡ወ
ደ፡ዘለዓለም፡ኵነኔ፡ይሔደሉ፥ጻድ
ቃኝ፡ወደ፡ዘለዓለም፡ሕይወት፥ዮ
ሐ፡፭፡፳፱፥ምዕራፍ፡፳፮፡፡
ስለ፡ፋሲካ፡በዓል፡እኝዲት፡ሴት፡ሽቱ፡
እኝደ፡ቀባቸው፡ይሁዳ፡ከካህናት፡አ
ለቆች፡ጋራ፡እኝደ፡ተነጋገረ፤ስለ፡
ሥጋና፡ደሙ፡ምሥጢር፤ሁላችሁ
ም፡ተክዱኛ ላችሁ፡ብሎ፡እኝዴ፡ተ
ናገረ፤በጌቴሴማኔ፡እኝዴ፡ጸለየና
ተጨኝቀ፡እኝደዘነ፤የካህናቱ፡አለ
ቃ፡አገልጋይ፡ጆሮው፡እኝደ፡ተቆረ
ጠ፤ጌታችኝ፡እኝዴ፡ተያዘና፡በካህና
ት፡አለቆች፡ፊት፡እኝዴ፡ቀመ፤ጴጥ(
ሮስ፡እኝደ፡ካደና፡ኝስሐ፡እኝዴ፡ገባ፥
፩ ሆነም፡ኢየሱስ፡ይህኝ፡ነገር፡ሁሉ፡
በፈጸመ፡ጊዜ፡ለደቀ፡መዛሙርቱ
፪ አሉቃማር፲፬፡ሉ፡፳፪፥ከሁለት፡ቀ
ኝ፡በኋላ፡ፋሲካ፡እኝዴሆኚ፡ታውቃ
ላችሁ፡የሰው ― ልጅኝም፡ሊሰቀ
ል፡አሳልፈው፡ይሰጡታል፥
፫ በዚያኝ፡ጊዜ፡የካህናት፡አለቆችና
ጸሮች፡የሕዝቡኝም፡ሽማግሌች
ቀያፋ፡በሚባለው፡በሊቀ፡ካህና
፬ ቱ፡ቤት፡ተሰበሰቡ፥ኢየሱስኝም፡

በተንኰል፡ሊይዙትና፡ሊገድሉ
ት፡ባገኙነት፡ተማከሩ፤ነገር፡ግን
በሕዝቡ፡ሁከት፡እንዳይሆን፡በበዓ
ል፡አይሆንም፡ኢየሱስ፡ግን፡በቢታ
ንያ፡በለምጻሙ፡ስምዖን፡ቤት፡ሳ
ለ፡ዮሐ፡፲፪፡፩፥አንዲት፡ሴት፡ዋጋው
የበዛ፡ሽቱ፡ብርሌ፡ይዛ፡ወደ፡እርሱ
መጣች፡እርሱም፡ተቀምጦ፡ሳለ
በራሱ፡ላይ፡አፈሰሰችው፡ሉ፡፯፡መ
፯፥ደቀ፡መዛሙርቱም፡ያንን፡በ
ዩ፡ጊዜ፡ይህን፡ያህል፡ጥፋት፡ለም
ንድር፡ነው፥በብዙ፡ዋጋ፡ተሸጦ፡
ለድሆች፡ይሰጥ፡ነበር፡ብለው፡ተ
ቈጡ፤ኢየሱስም፡ይህን፡ባወቀ፡
ጊዜ፡ይህች፡ሴት፡ለኔ፡መልካም፡አ
ደረገችልኝ፡ለምን፡ታሳዝኗታላ
ችሁ፡ለላቸው፥ድሆች፡ሁልጊዜ፡
ከናንተ፡ጋራ፡ናቸው፡እኔ፡ግን፡ከ
ናንተ፡ጋራ፡ሁልጊዜ፡አልኖርም፤
ዘዳ፡፲፭፡፲፩፥ይህም፡በራሴ፡ላይ
ያፈሰሰችው፡ሽቱ፡ለመቃብሬ፡አ
ደረገችው፥እውነት፡እላችኋለሁ፡ይ
ህ፡ወንጌል፡በሚሰበክበት፡ስፍራ
በዓለሙ፡ሁሉ፡ይህች፡ሴት፡ያደረ
ገችው፡ለእርስዋ፡መታሰቢያ፡ሆ
ኖ፡ይነገራል፥በዚያ፡ጊዜ፡ከሥራ
ሁለቱ፡አንዱ፡ስሙ፡ይሁዳ፡የሚ
ሉት፡የአስቆሮቱ፡ወደ፡ካህናቱ፡
አለቆች፡ሔዶ፥እኔ፡ባስይዛችሁ
ምን፡ትሰጡኛላችሁም፡አላቸው
እርሳቸውም፡በ፴፡ብር፡ከእርሱ፡
ጋራ፡ተስማሙ፡ዮሐ፡፲፩፡፵፯፡ዘካ፡
፲፩፡፲፪፥ከዚያ፡ቀን፡ጀምሮ፡አ
ሳልፎ፡ሊሰጣቸው፡ምቹ፡ጊዜ፡ይ
ሻ፡ነበር፡፩፡ጢሞ፡፮፡፱፡፲፥ከፋሲካ
ም፡አስቀድሞ፡በነበረው፡የቂጣ፡በ
ዓል፡በዓለ፡ናዕት፡ደቀ፡መዛሙርቱ
ወደ፡ኢየሱስ፡መጥተው፡ፋሲካውን
ትበላ፡ዘንድ፡ወዴት፡ልናዘጋጅልህ
ትወዳለህ፡አሉት፡ዘፀ፡፲፪፡፲፰፡፳፥
እርሱም፡በከተማ፡ወደ፡እገሌ፡ዘንድ
ሒዳችሁ፡መምህር፡ጊዜዬ፡ደርሶአ
ል፡በአንተ፡ቤት፡ከደቀ፡መዛሙርቴ
ጋራ፡ፋሲካን፡አከብራለሁ፡ይልሃል
በሉት፡አላቸው፥ምሳ፡፳፮፡፫፥ደቀ፡
መዛሙርቱም፡ኢየሱስ፡እንዳዘዛ
ቸው፥አደረጉ፡ፋሲካውንም፡አዘጋ
ጁ፥በመሸም፡ጊዜ፡ከሥራ፡ሁለቱ
ደቀ፡መዛሙርቱ፡ጋራ፡ለመብላ፡
ተቀመጠ፥ሲበሉም፡እውነት፡እላ
ችኋለሁ፡ከእናንተ፡አንዱ፡አሳልፎ
ይሰጠኛል፡አላቸው፥ዮሐ፡፲፫፡፳፩፡
፳፪፥እጅግም፡አዘኑ፡ከእርሳቸው
ም፡እያንዳንዱ፡እቤቱ፡ከቶ፡እኔ፡እሆ
ንን፡ይሉ፡ጀመር፥እርሱም፡መልሶ
ከኔ፡ጋራ፡እጁን፡ወደ፡ወጭቱ፡
የሚጠልቅ፡እርሱ፡አሳልፎ፡ይሰጠ
ኛል፡አለ፥ዮሐ፡፲፫፡፲፰፥የሰው፡ልጅ፡
ግን፡ስለ፡እርሱ፡እንደ፡ተጻፈ፡ይሄዳል
ነገር፡ግን፡በእርሱ፡ምክንያት፡የሰው
ልጅ፡አልፎ፡ለሚሰጥበት፡ለዚያ፡ሰ
ው፡ወዮለት፡ያ፡ሰውስ፡ባይወለድ፡ይ

፳፭ ሽ ሰው፡ ነበር። አሳልፎ፡ የሚሰጠ
ው፡ ይሁዳም፡ መልሶ፡ መምህር፡ ሆ
ይ፡ ከቶ፡ እኔ፡ እሆን፧ አለ፡ አንተ፡ ት
፳፮ ላለህ፡ አለው። እነ፡ እርሳቸው፡ ሲ
በሉ፡ ኢየሱስም፡ ኅብስቱን፡ አንስቶ፡
ያዘ፡ ባረከውም፡ ቈርሶም፡ ለደቀ
መዛሙርቱ፡ እንኩ፡ ብሉ፡ ይህ፡ ሥ
ጋዬ፡ ነው፡ ብሎ፡ ሰጠ። ፩ቈሮ፡ ፲፩፡ ፳፫
፳፯ ፳፬። ጽዋንም፡ ተቀብሎ፡ አመሰ
ግኖ፡ ሁላችሁ፡ ከዚህ፡ ጠጡ፡ ብሎ
፳፰ ም፡ ሰጣቸው። ይህ፡ የሐዲስ፡ ሥ
ርዓት፡ ኃጢአትን፡ ለማስተሥተ
ሥረይ፡ ስለ፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ የሚፈስ
ስ ደሜ፡ ነው። ዘፀ፡ ፳፬፡ ፰። ኤር፡ ፴
፳፱ ፩፡ ፴፩፡ ዘካ፡ ፱፡ ፲፩። በአባቴ፡ መን
ግሥት፡ ከእናንተ፡ ጋራ፡ አዲሱን፡
እስከ፡ እምጠጣበት፡ እስከ ዚያ፡ ቀን
ድረስ፡ ከዛሬ፡ ጀምሮ፡ ከዚህ፡ ከወ
ይኑ፡ ፍሬ፡ አልጠጣም፡ እላችኋለ
፴ ሁ። የምስጋናም፡ መዝሙር፡ ከ
ዘመሩ፡ በኋላ፡ ወደ፡ ደብረ፡ ዘይት
፴፩ ወጡ። መዝ፡ ፻፲፫፡ ፻፲፰። ከዚህ፡
በኋላ፡ ኢየሱስ፡ በዚች፡ ሌሊት፡ ሁ
ላችሁ፡ ትክዱኛላችሁ፡ አላቸው።
ጠባቂውን፡ እገድላለሁ፡ የመንጋ
ውንም፡ በጎች፡ ይበተናሉ፡ ተብ
ሎ፡ ተጽፎአልና። ዘካ፡ ፲፫፡ ፯። ዮ
፴፪ ሐ፡ ፲፮፡ ፴፪። ነገር፡ ግን፡ በተነሣሁ
ጊዜ፡ ወደ፡ ገሊላ፡ እቀድማችኋለ
፴፫ ሁ። ጴጥሮስም፡ መልሶ፡ ሁሉ፡ ቢ
ክዱህ፡ እኔ፡ ከቶ፡ አልክድህም፡ አ

፴፬ ለው። ኢየሱስም፡ መልሶ፡ በዚ
ች፡ ሌሊት፡ ዶሮ፡ ሳይጮህ፡ አስቀ
ድመህ፡ ሶስት፡ ጊዜ፡ እንደምትክደኛ
እውነት፡ እልሃለሁ፡ አለው። ዮሐ
፴፭ ፲፫፡ ፴፰። ጴጥሮስም፡ ከአንተ፡ ጋራ
እሞታለሁ፡ እንጂ፡ አልክድህም
አለው። ደቀ፡ መዛሙርቱም፡ ሁሉ
፴፮ እንዲሁ፡ አሉ። [illegible] ከዚህ፡ በ
ኋላ፡ ኢየሱስ፡ ከእር[illegible] ጋራ ጌ
ቴሴማኒ፡ ወደምትባል፡ ስፍራ፡
መጣ፡ ደቀ፡ መዛሙርቱንም፡ ወደ
ዚያ፡ ሒጄ፡ እስክጸልይ፡ ድረስ፡ ከዚ
፴፯ ህ፡ ቆዩ፡ አላቸው። ከእርሱም፡ ጋ
ራ፡ ጴጥሮስንና፡ ሁለቱን፡ የዘብዴ
ዎስን፡ ልጆች፡ ወሰደ፡ ያዝንም፡ ይ
ተክዝም፡ ጀመር። ዕብ፡ ፭፡ ፯።
፴፰ በዚያን፡ ጊዜ፡ ነፍሴ፡ እስከ፡ ሞት፡
ድረስ፡ አዝነች፡ በዚህ፡ ተቀመጡ፡
ከኔ፡ ጋራም፡ ትጉ፡ አላቸው። ዮሐ፡
፴፱ ፲፪፡ ፳፯። ከዚያም፡ ጥቂት፡ ፈቀ
ቀ፡ ብሎ፡ እየጸለየ፡ በግምባሩ፡ ሰገ
ደ፡ እንዲህም፡ አለ፡ አባቴ፡ ሆይ፡ ይ
ቻል፡ እንደሆንስ፡ ይህቺ፡ ጽዋ፡ ከኔ
ትለፍ፡ ነገር፡ ግን፡ [illegible]፡ ፈቃድ፡ ይ
ሁን፡ እንጂ፡ የኔ፡ [illegible]፡ አይደለም
ዮሐ፡ ፲፰፡ ፲፩። ዕብ፡ ፭፡ ፯።
፵ ወደ፡ ደቀ፡ መዛሙ[illegible]ም፡ መጣ፡
ኛተውም፡ አገኛቸው፡ ጴጥሮስንም
ከኔ፡ ጋራ፡ አንዲት፡ [illegible]ት፡ ትተጉ
እንዴት፡ አልቻላችሁም፡ አለው።
፵፩ ወደ፡ ፈተናም፡ እንዳትገቡ፡ ትጉ፡

ጸልዩም፡ መንፈስ፡ ይወዳልና፡ ሥ
ጋ፡ ግን፡ ደካማ፡ ነውና፥ ም፡ ፬፡ ፲፭፡ ዕ
፵፪ ብ፡ ፭፡ ፲፬፥ ደግሞ፡ ሁለተኛ፡ ሔደ
ና፡ አባቴ፡ ሆይ፡ ይህችን፡ ጽዋ፡ ሳል
ጠጣት፡ ከኔ፡ ታልፍ፡ ዘንድ፡ የማ፥
ይቻል፡ እንደሆነ፡ ፈቃድህ፡ ትሁን
፵፫ ብሎ፡ ጸለየ፥ ሁለተኛም፡ በተመ
ለሰ፡ ጊዜ፡ ዓይኖቻቸው፡ በእንቅ
ልፍ፡ ከብደው፡ ነበሩና፡ ተኝተው
፵፬ አገኛቸው፥ ደግሞም፡ ትቷቸ
ው፡ ሄደ፥ ሶስተኛም፡ ያንኑ፡ የፊተ
ኛውን፡ ቃል፡ ጸለየ፥ ፪፡ ቆሮ፡ ፲፪፡ ፰
፵፭ ከዚያ፡ ወደ፡ ደቀ፡ መዛሙ
ርቱ፡ መጥቶ፡ እሳቸው፡ እንግዲህ፡
ተኙ፡ እረፉም፡ እነሆ፡ ሰዓቱ፡ ደረሰ
የሰው፡ ልጅም፡ በኃጢአተኞች፡
፵፮ እጅ፡ ይሰጣል፥ ተነሡ፡ እንሂድ፡ እ
ነሆ፡ አሳልፎ፡ የሚሰጠኝ፡ አሁን፡ ደ
፵፯ ረሰ፥ እርሱም፡ ይህን፡ ሲናገር፡ እ
ነሆ፡ ከአሥራ፡ ሁለቱ፡ አንዱ፡ ይሁዳ
መጣ፡ ከእርሱም፡ ጋራ፡ ከካህናት፡
አለቆችና፡ ከሕዝብ፡ ሽማግሌዎች
ዘንድ፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ ሰይፍና፡ ጐመ
፵፰ ድ፡ ይዘው፡ መጡ፥ አሳልፎ፡ የሚሰ
ጠውም፡ የምስመው፡ እርሱ፡ ነው
ና፡ ያዙት፡ ብሎ፡ ምልክት፡ ሰጣቸ
፵፱ ው፥ ወዲያውም፡ ወደ፡ ኢየሱስ፡ ቀ
ርቦ፡ መምህር፡ ሆይ፡ ደኅና፡ ነህን፡ ብ
፶ ሎ፡ ሳመው፥ ኢየሱስም፡ ወዳጄ፡
ሆይ፡ መጣህን፡ አለው፡ በዚያን፡ ጊ
ዜ፡ ቀርበው፡ እጃቸውንም፡ በኢየሱ
ስ፡ ላይ፡ ጫኑ፡ ያዙትም፡ መዝ፡ ፵፩፡
፶፩ ፲፩፥ እነሆም፡ ከኢየሱስ፡ ጋራ፡ ከነበ
ሩት፡ አንዱ፡ እጁን፡ ዘርግቶ፡ ሰይፉ
ን፡ መዘዘ፡ የካህናቱንም፡ አለቃ፡ እ
ገልጋይ፡ መታው፡ ጆሮውንም፡ ቆረ
ጠው፥ ዘፍ፡ ፱፡ ፮፡ ራእ፡ ፲፫፡ ፲፥
፶፪ በዚያን፡ ጊዜ፡ ኢየሱስ፡ አለው፡ ሰይፍ
የሚያነሡ፡ ሁሉ፡ በሰይፍ፡ ይጠፋ
ሉና፡ ሰይፍህን፡ ወደ፡ አፎቱ፡ መልስ፡
፶፫ ወይስ፡ ከመላእክት፡ ወገን፡ ከአሥራ
ሁለቱ፡ አለቆች፡ የሚበልጡ፡ ይሰ
ዱልኝ፡ ዘንድ፡ አሁን፡ ወደ፡ አባቴ፡ ለ
መለመን፡ የማልችል፡ ይመስልሃ
፶፬ ልን፥ ዳን፡ ፯፡ ፲፥ ነገር፡ ግን፡ እንዲህ፡
ይሆን፡ ዘንድ፡ እንዲገባ፡ መጽሐፍ
፶፭ ት፡ እንዴት፡ ይፈጸማል፥ በዚያን
ጊዜ፡ ኢየሱስ፡ ሕዝቡን፡ አላቸው፡
እንደ፡ ሌባ፡ በሰይፍና፡ በጎመድ፡ ል
ትይዙኝ፡ መጣችኋልን፡ በቤተ
መቅደስ፡ ተቀምጬ፡ እያስተማር
ሁ፡ ሁልጊዜ፡ ከናንተ፡ ጋራ፡ እኖር፡ ነ
በርሁ፡ ለምን፡ አልያዛችሁኝም፥
፶፮ ዮሐ፡ ፲፰፡ ፳፥ ነገር፡ ግን፡ ይህ፡ ሁሉ፡ የ
ሆነ፥ የነቢያት፡ መጽሐፍት፡ ይፈጸ
ሙ፡ ዘንድ፡ ነው፡ ከዚህ፡ በኋላ፡ ደቀ
መዛሙርቱ፡ ሁሉ፡ ጥለውት፡ ሸሹ
፶፯ ዮሐ፡ ፲፰፡ ፳፪፥ ኢየሱስን፡ የያዙ
ት፡ ግን፡ ጻፎችና፡ ሽማግሌዎች፡ ወ
ደ፡ ተሰበሰቡበት፡ ወደ፡ ሊቀ፡ ካህናቱ
ወደ፡ ቀያፋ፡ ቤት፡ ወሰዱት፥ ዮሐ፡ ፲፰
፶፰ ፲፫፡ ፳፬፥ ጴጥሮስ፡ ግን፡ የነገሩን፡

ፍጻሜ፡ ያይ፡ ዘንድ፡ በሩቅ፡ ሆኖ፡ እ
ስከ፡ ሊቀ፡ ካህናቱ፡ ቤት፡ ድረስ፡ ተ
ከተለው፡ ወደ፡ ውሥጥም፡ ገብቶ
፶፱ ከሎሌዎች፡ ጋራ፡ ተቀመጠ። የካ
ህናት፡ አለቆችና፡ ሽማግሌዎች፡
ጻፎችም፡ በሸንጎም፡ ያሉት፡ ሁ
ሉ፡ ይገድሉት፡ ዘንድ፡ በኢየሱስ
ላይ፡ የሐሰት፡ ምስክር፡ ይሹ፡ ነበ
ር፡ ነገር፡ ግን፡ አላገኙበትም።
፷ ብዙም፡ የሐሰት፡ ምስክሮች፡ መ
ጡና፡ አላገኙበትም፡ በኋላም፡
ሁለት፡ የሐሰት፡ ምስክሮች፡ መ
፷፩ ጥተው፡ እንደዚህ፡ አሉ። ይህ፡ ቤተ
እግዚአብሔርን፡ አፍርሼ፡ በሦስ
ት፡ ቀን፡ እሠራው፡ ዘንድ፡ እችላለሁ
፷፪ አለ። ዮሐ፡ ፪፡ ፲፱፡ ፳፩። የካህናት፡
አለቃም፡ ተነሥቶ፡ እነዚህ፡ የሚ
መሰክሩብህ፡ አትሰማምን፡ አ
፷፫ ለው። ኢየሱስ ግን፡ ዝም፡ አለ፡ የካ
ህናት፡ አለቃም፡ አንተ፡ የእግዚአ
ብሔር፡ ልጅ፡ ክርስቶስ፡ እንደ፡ ሆን
ህ፡ እንድትነግረኝ፡ በሕያው፡ እግ
ዚአብሔር፡ አምልሃለሁ፡ አለው።
፷፬ ም ፭፯፡ ፲፪። ኢየሱስም፡ አንተ፡
አልህ፡ አለው፡፡ ከእንግዲህ፡ ወዲህ
ግን፡ እላችኋለሁ፡ የሰው፡ ልጅ፡ በ
ኃይል፡ ቀኝ፡ ሲቀመጥ፡ በሰማይም
ደመና፡ ሲመጣ፡ እንድታዩ። ምዕ፡ ፲፮
፳፯፡ መዝ፡ ፻፲፡ ፩፡ ዳን፡ ፯፡ ፲፫፡ ፲፬።
፷፭ በዚያን፡ ጊዜ፡ የካህናት፡ አለቃ፡ ል
ብሱን፡ ቀደደ፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ እነሆ፡
እርሱ፡ እግዚአብሔርን፡ ተሳደ
በ፡ ስድቡንም፡ ሰማችሁ፡ እንግዲ
ህ፡ ወዲህ፡ ምስክር፡ ምን፡ ያስፈል
፷፮ ገናል፡ ዮሐ፡ ፲፡ ፴፫። እንግዲህ፡ ምን፣
ን፡ ይመስላችኋል፡ እርሳቸው፡ ግን፡
መልሰው፡ ይህ፡ ሞት፡ ይገባዋል፡ አ
፷፯ ሉ። ዮሐ፡ ፲፱፡ ፯። በዚያን፡ ጊዜ፡ በፊ
ቱ፡ ተፉበት፡ ራሱንም፡ መቱት፡ ሌ
ሎችም፡ በጥፊ፡ መቱት። ኢሳ፡ ፶፡ ፮።
፷፰ ክርስቶስ፡ ሆይ፡ ትንቢት፡ ንገረን፡
ማነው፡ በጥፊ፡ የመታህ፡ እያሉት
፷፱ ጴጥሮስ፡ ግን፡ ከቤት፡ በስተ ውጭ
ተቀምጦ፡ ነበር፡ አንዲት፡ ገረድ፡
መጣችና፡ አንተ፡ ደግሞ፡ ከገሊላ
ው፡ ከኢየሱስ፡ ጋራ፡ ነበርህ፡ አላች
፸ ው። ዮሐ፡ ፲፰፡ ፲፮፡ ፳፭። እርሱ፡ ግ
ን፡ የምትናገሪውን፡ አላውቅም፡ ብ
፸፩ ሎ፡ በሁሉ፡ ፊት፡ ካደ። ወደ፡ ውጭ፡
ም፡ ወጣና ጊዜ፡ ሌላዪቱ፡ አየችው
በዚያም፡ ለነበሩት፡ ይህም፡ ደግሞ
ከናዝሬቱ፡ ከኢየሱስ፡ ጋራ፡ ነበረ፡
፸፪ አለቻቸው። ዮሐ፡ ፲፰፡ ፳፭። ደግመ
ኛም፡ ያንን፡ ሰው፡ እንዳያውቀው
፸፫ በመሐላ፡ ካደ። ጥቂትም፡ ቆይተ
ው፡ ቁመው፡ የነበሩት፡ ቀርበው፡
ጴጥሮስን፡ አነጋገርህ፡ ያስታው
ቅብሃልና፡ በውነት፡ አንተም፡ ደ
ግሞ፡ ከእርሳቸው፡ ወገን፡ ነህ፡ አ
፸፬ ሉት። ከዚያ፡ በኋላ፡ ይህን፡ ሰው፡
አላውቀውም፡ እያለ፡ ይረግምም፡ ይ
ምልም፡ ጀመረ፡ በዚያን፡ ጊዜም፡ ዶ

፸፭ ጴጥሮስም፡ ዶሮ፡ ሳይ
ጮኽ፡ ሦስት፡ ጊዜ፡ ትክደኛለህ፡ ያ
ለውን፡ የኢየሱስን፡ ቃል፡ አሰበ።
ወደ፡ ውጭም፡ ወጥቶ፡ መራራ፡
አልቅሶ፡ አለቀሰ፡ ሉቃ ፳፪ ፷፪ ።

ምዕራፍ፡ ፳፯።

ኢየሱስን፡ ሊገድሉት፡ እንደ፡ መከ
ሩ፤ ይሁዳ፡ ታንቆ፡ እንደ፡ ሞተ፡ በተ
[illegible] ር፡ የመቃብር፡ ቦታ፡
እንደ፡ [illegible] በት፤ በጲላጦስ፡ ፊት
እንደ [illegible] ጲላጦስ፡ እጁን፡ እንደ
ታጠበ፤ እንደ፡ ተገረፈ፡ እንደ፡ ተ
ሰቀለ፤ ሁለት፡ ወንበዴች፡ ከእርሱ
ጋራ፡ እንደ፡ ተሰቀሉ፤ የቤተ፡ መቅ
ደሱ፡ መጋረጃ፡ እንደ፡ ተቀደደ፤ የአ
ርማትያሱ፡ ዮሴፍ፡ ሥጋውን፡ ከ
መስቀል፡ አውርዶ፡ እንደ፡ ቀበረው፡
የካህናት፡ አለቆች፡ መቃብሩን
በዘበኞች፡ እንዳስጠበቁት።

፩ በነጋም፡ ጊዜ፡ የካህናት፡ አለቆች
ሁሉ፡ የሕዝቡም፡ ሽማግሌዎች፡ ይ
ገድሉት፡ ዘንድ፡ በኢየሱስ፡ ላይ፡ ተ
ማከሩ፡ ማር፡ ፲፭፡ ፩፡ ሉቃ፡ ፳፪ ፡ ፷፮፡ ፳፫
ዮሐ፡ ፲፰፡ ፳፰። አሥረውም፡ ወሰዱ
ት፡ ለሀገረ ገዢው፡ ለጴንጤናዊው፡ ጲ
ላጦስ፡ አሳልፈው፡ ሰጡት።

፫ በዚያን፡ ጊዜ፡ አሳልፎ፡ የሰጠው፡
ይሁዳ፡ እንደ፡ ተፈረደበት፡ ባየ፡ ጊ
ዜ፡ [illegible] ት፡ ፴ ሰውን፡ ብር፡ ወ
ደ [illegible] ት፡ አለቆችና፡ ወደ፡ ሽማ
[illegible] ው፡ አንዲህ፡ ሲል፡

፬ ምሕ፡ ፲፩፡ ፲፫ ንጹሕ፡ ደምም፡ አሳል
ፌ፡ በመስጠቴ፡ በደልሁ፡ አርሳቸ
ው፡ ግን፡ እኛን፡ ምን፡ አግዶን፡ አንተ
ስህ፡ አንተ፡ ዕወቅ፡ አሉት።

፭ ብሩንም፡ በቤተ፡ መቅደስ፡ በትኖ
ና፡ ሄዶ፡ ታንቆ፡ ሞተ። የሐዋ፡ ፩
፲፰፡ ፲፱፡ ሳሙ፡ ፲፯፡ ፳፫።

፮ የካህናት፡ አለቆች፡ ብሩን፡ ወስደው፡ የደም
ዋጋ፡ ነውና፡ በእግዚአብሔር፡ ቍ
ርባን፡ ሣጥን፡ እናኖረው፡ ዘንድ፡
አይገባንም፡ አሉ፡ ማር፡ ፲፪፡ ፵፩

፯ ተማክረውም፡ ለእንግዶች፡ መቃ
ብር፡ የሸክላ፡ ሠሪ፡ መሬት፡ ገዙበት

፰ የሐዋ፡ ፩፡ ፲፱፡ ስለዚህ፡ ያ መሬት፡ እ
ስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡ የደም፡ ምድር፡ ተ

፱ ብሎ፡ ተጠራ። በዚያን፡ ጊዜ፡ በነቢ
ዩ፡ በኤርምያስ፡ የተባለው፡ ተፈ
ጸመ፡ የእስራኤል፡ ልጆች፡ የገመገሙ
ትን፡ የከብሩን፡ ዋጋ፡ ፴ውን፡ ብር
ወሰዱ። ዘካ፡ ፲፩፡ ፲፪፡ ፲፫፡ ኤር፡ ፴፪፡ ፱

፲ ለሸክላ፡ ሠሪም፡ መሬት፡ ሰጡት፡
እግዚአብሔር፡ እንዳዘዘኝ።

፲፩ ኢየሱስም፡ በገዢው፡ ፊት፡ ቆመ፡
ገዢውም፡ የአይሁድ፡ ንጉሥ፡ አን
ተ፡ ነህ፡ ብሎ፡ ጠየቀው። ኢየሱስም
አንተ፡ ትላለህ፡ አለው። ማር፡ ፲፭፡
፪፡ ሉቃ፡ ፳፫፡ ፫፡ ዮሐ፡ ፲፰፡ ፴፫።

፲፪ የካህናት፡ አለቆችና፡ ሽማግሌ
ዎችም፡ ሲከሱት፡ አልመለሰ
ውም። ኢሳ፡ ፶፫፡ ፯።

፲፫ በዚያን፡ ጊዜ፡
ጲላጦስ፡ ይህን፡ ያህል፡ ሲከሱህ

፲፬ አትሰማምን፡ አለው። እርሱም እንዲት፡ ቃል፡ ሰንኳ፡ አልመለሰ ለትም፡ ሹሙ፡ እጅግ፡ እስኪያደን
፲፭ ቅ፡ ድረስ። በየበዓሉም፡ ለሕዝቡ ከእስረኞቹ፡ ውስጥ፡ የወደዱትን አንድ፡ እስር፡ ይፈታላቸው፡ ዘንድ
፲፮ ለሹሙ፡ ልማድ፡ ነበረው። በዚያ ን፡ ጊዜ፡ በርባን፡ የሚባል፡ የታወቀ
፲፯ አንድ፡ እስር፡ ነበረ። እርሳቸውም፡ ተሰብስበው፡ ሳሉ፡ ጲላጦስ፡ ማንን እፈታላችሁ፡ ዘንድ፡ ትወዳላችሁ በርባንን፡ ወይስ፡ ክርስቶስ፡ የሚ ባለው፡ ኢየሱስን፡ አላቸው።
፲፰ በቅናት፡ አሳልፈው፡ እንደ፡ ሰጡ
፲፱ ት፡ ያውቅ፡ ነበርና። እርሱም፡ በፍ ርድ፡ ወንበር፡ ተቀምጦ፡ ሳለ፡ ሚስ ቱ፡ በዚያ፡ ጻድቅ፡ ሰው፡ በደል፡ እን ዳትውል፡ ተጠንቀቅ፡ ስለ፡ እርሱ፡ ዛሬ፡ በሕልም፡ እጅግ፡ መከራ፡ ተ ቀብያለሁና፡ ብላ፡ ላከችበት።
፳ የካህናት፡ አለቆችና፡ ሽማግሌዎ ች፡ በርባንን፡ ለማዳን፡ ኢየሱስ ን፡ ለመግደል፡ ይለምኑ፡ ዘንድ ሕዝቡን፡ አባበሉ። አሺ፡ ለሰኛ ዋ
፳፩ ቸው። ሹሙ፡ ግን፡ መልሶ፡ ከሁለ ቱ፡ ማናቸውን፡ እፈታላችሁ፡ ዘን ድ፡ ትወዳላችሁ፡ አላቸው። እርሳቸ
፳፪ ውም፡ በርባንን፡ አሉ። ጲላጦስም ክርስቶስ፡ የሚባለውን፡ ኢየሱስ ን፡ ምን፡ ላድርግበት፡ አላቸው። ሁሉ
፳፫ ም፡ ይሰቀል፡ አሉ። ሹሙም፡ ምን፡ ምን

ክፉ፡ አደረገ፡ አላቸው። እርሳቸ ው፡ ግን፡ ይሰቀል፡ እያሉ፡ ጩኸት፡
፳፬ አበዙ። ጲላጦስም፡ ሁከት፡ ከመ ብዛት፡ በቀር፡ አንዳች፡ እንዳይረባ ባየ፡ ጊዜ፡ ውሀ፡ አስ[illegible]ቶ፡ እኔ፡ ከ ዚህ፡ ጻድቅ፡ ደም፡ ንጹሕ፡ ነኝ፡ እና ንተ፡ ዕወቁ፡ ብሎ፡ በሕዝቡ፡ ፊት፡
፳፭ እጁን፡ ታጠበ። ዘዳ፡ ፳፩፡ ፮-፯። ሕዝ ቡም፡ ሁሉ፡ ደሙ፡ [illegible]ና፡ በልጆቻ ችንም፡ ላይ፡ ይሁን፡ [illegible] መለሱ። የሐዋ፡ ፭፡ ፳፰፡ ዘዳ[illegible] ፲፱፡ ፲
፳፮ በዚያን፡ ጊዜ፡ በርባንን፡ ፈታላቸ ው፡ ኢየሱስንም፡ ገርፎ፡ እንዲ
፳፯ ሰቀል፡ አሳልፎ፡ ሰጣቸው። ከዚያ፡ ወዲያም፡ የሹሙ፡ ጭፍሮች፡ ኢ የሱስን፡ ወደ፡ ፍርድ፡ ሸንጎ፡ ወሰዱ ት፡ ጭፍራውንም፡ ሁሉ፡ ሰበሰቡ
፳፰ ት። ዮሐ፡ ፲፱፡ ፪። ልብሱንም፡ ገፈፉ፡ ቀ
፳፱ ዩ፡ ልብስ፡ አለበሱት። የእሾህ፡ አክሊ ልም፡ ጎንጉነው፡ በራሱ፡ ላይ፡ ጫ ኑበት፡ በቀኙ፡ እጁም፡ ዘንግ፡ አስያ ዙት፡ በፊቱም፡ በጉልበታቸው፡ ተንበርክከው፡ ሰላም፡ ይድረስህ፡ የአይሁድ፡ ንጉሥ፡ ሆይ፡ እያሉ፡ ተ
፴ ሣለቁበት። ተ[illegible]ቱም፡ ነበር። ዘንጉንም፡ ነጥቀው፡ ራሱን፡ መቱ
፴፩ ት። ኢሳ፡ ፶፡ ፮። ካ[illegible]በትም፡ በኋ ላ፡ ቀዩን፡ ልብስ፡ ገፈፉት፡ ልብሱን አልብሰው፡ ሊሰቅሉት፡ ወሰዱት።
፴፪ ሲወጡም፡ ስሙ፡ ስምዖን፡ የሚ ባለውን፡ የቀሬና፡ ሰው፡ አገኙ፡ እርሱ

ኛም፡ መስቀሉን፡ ይሸከም፡ ዘንድ፡
፴፫ ጉተቀቀቀ፨ ዕብ፡ ፲፫፡ ፲፪፡ ፲፫፨ ትር
ጓሜው፡ የራስ፡ አጽንት፡ ቦታ፡ የ
ተባለ፡ ጎልጎታ፡ ወደሚሉት፡ ሥ
፴፬ ፍራም፡ በደረሱ፡ ጊዜ። በሐሞት
የተደባለቀ፡ መፃፃ፡ ኽምጣጣ፡ ሰ
ጡት፡ ቀምሶም፡ ሊጠጣው፡ አልወ
፴፭ ደደም፨ መዝ፡ ፳፪፡ ፲፰፡ ፳፪፨ በሰቀሉት
ም፡ ጊዜ፡ ዕጣ፡ ተጣጥለው፡ ልብሱ
ን፡ ተካፈሉ፡ በነቢዩ፡ ልብሶቼን፡ አ
ርስ፡ በርሳቸው፡ ተካፈሉ፡ በቀሚ
ሴም፡ ላይ፡ ዕጣ፡ ተጣጣሉ፡ የተባለ
ው፡ ይፈጸም፡ ዘንድ፨ መዝ፡ ፳፪፡
፴፮ ፲፰፡ በዚያም፡ ተቀምጠው፡ ይጠብ
፴፯ ቁት፡ ነበር፨ ከራሱም፡ በላይ፡ ይ
ህ፡ ኢየሱስ፡ የአይሁድ፡ ንጉሥ፡ ነ
ው፡ ተብሎ፡ የተጻፈውን፡ ወንጀ
፴፰ ሉን፡ ለጠፉ፡ አጣበቁ፨ በዚያን፡ ጊ
ዜ፡ ሁለት፡ ወንበዴዎች፡ አንዱን፡ በቀ
ኙ፡ አንዱንም፡ በግራው፡ ከእርሱ
፴፱ ጋራ፡ ሰቀሉ፨ ኢሳ፡ ፶፫፡ ፲፪፨ የሚያ
ልፉትም፡ እራሳቸውን፡ እየነቀነ
ቁ፡ እንዲህ፡ ሲሉ፡ ይሰድቡት፡ ነበሩ
፵ ቤተ፡ መቅደስን፡ አፍርሰህ፡ በሦስት
ቀን፡ የምሠራ፡ ሆይ፡ ራስህን፡ አድ
ን፡ የእግዚአብሔርም፡ ልጅም፡
እንደሆንህ፡ ከመስቀል፡ ውረድ፡
፵፩ ዮሐ፡ ፪፡ ፲፱፨ እንዲሁም፡ ደግሞ፡ የ
ካህናት፡ አለቆች፡ ከጻፎችና፡ ከሽ
ማግሌዎች፡ ጋራ፡ ያፌዙበት፡ ነበር
፵፪ እንዲህ፡ እያሉ፨ ሌሎችን፡ ያድና
ል፡ ራሱን፡ ግን፡ ማዳን፡ አልቻለም
እርሱ፡ የእስራኤል፡ ንጉሥ፡ ከሆነ፡ አሁ
ን፡ ከመስቀል፡ ይውረድ፡ እኛም፡
፵፫ አይተን፡ እንመንበት፨ በእግዚ
አብሔር፡ ታመነ፡ ከወደደው፡
ም፡ አሁን፡ ያድነው፡ እኔ፡ የእግ
ዚአብሔር፡ ልጅ፡ ነኝ፡ ብሏልና፨
፵፬ መዝ፡ ፳፪፡ ፰፨ እንደዚሁም፡ ደግሞ
ከእርሱ፡ ጋራ፡ የተሰቀሉት፡ ወንበ
፵፭ ዴዎች፡ ይሰድቡት፡ ነበር፨ ከ፮ት፡ ሰ
ዓት፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ ዘጠኝ፡ ሰዓ
ት፡ በምድር፡ ላይ፡ ሁሉ፡ ጨለማ፡
፵፮ ሆነ፨ በዘጠኝ፡ ሰዓት፡ ጊዜም፡ ኢየሱ
ስ፡ ኤሎሄ፡ ኤሎሄ፡ ላማ፡ ሰበቅታ
ኒ፡ ብሎ፡ በታላቅ፡ ቃል፡ ጮኸ፡ ይህ
ም፡ አምላኬ፡ አምላኬ፡ ለምን
ተውኸኝ፡ ማለት፡ ነው፨ መዝ፡ ፳፪፡
፵፯ ፩፨ ከዚያ፡ የቆሙትም፡ ሐዝብ፡
በሰሙ፡ ጊዜ፡ ይህስ፡ ኤልያስን፡ ይ
፵፰ ጠራል፡ አሉ፨ ከእርሳቸውም፡ አንዱ
ሩጦ፡ ሰፍነግ፡ ወሰደ፡ መፃፃም፡ መ
ላበትና፡ በዘንግ፡ ላይ፡ አሥሮ፡ አጠ
ጣው፨ ዮሐ፡ ፲፱፡ ፳፱፡ መዝ፡ ፷፱፡ ፳፩፨
፵፱ ሌሎቹ፡ ግን፡ ተዉት፡ ኤልያስ፡ መጥ
ቶ፡ ያድነው፡ እንደሆነ፡ እንይ፡ አሉ
፶ ኢየሱስም፡ ደግሞ፡ በታላቅ፡ ቃል፡
፶፩ ጮኸ፡ ነፍሱንም፡ ሰጠ፨ እነሆም፡ የ
ቤተ፡ መቅደስ፡ መጋረጃ፡ ከላይ፡ እስ
ከ፡ ታች፡ ከሁለት፡ ተቀደደ፡ ምድርም
ተናወጠች፡ ደንጊያዎችም፡ ተሰነጠቁ
ዘፀ፡ ፳፮፡ ፴፩፡ ዕብ፡ ፲፡ ፲፱፡ ፳፨

፶፪ መቃብሮችም፡ተከፈቱ፡ከተኙ
ትም፡የቅዱሳን፡በድኖች፡ብዙዎ
፶፫ ች፡ተነሡ። ከመቃብራቸውም፡ወ
ጡ፡ከትንሣኤውም፡በኋላ፡ወደ፡ቅ
ድስት፡ከተማ፡ገብተው፡ለብዙዎ
፶፬ ች፡ታዩ። የሐዋ፡፳፮፡፳፫። የመቶው
አለቃ፡ግን፡ከእርሱም፡ጋራ፡ኢየሱ
ስን፡ሲጠብቁ፡የነበሩ፡መናወጡ
ን፡የሆነውንም፡ሁሉ፡ባዩ፡ጊዜ፡እ
ጅግ፡ፈሩ፡በውነትም፡ይህ፡የእግ
፶፭ ዚአብሔር፡ልጅ፡ነው፡አሉ። በዚ
ያም፡ብዙ፡ሴቶች፡በሩቅ፡ያዩ፡ነበር
እርሳቸውም፡ኢየሱስን፡ከገሊላ፡
የተከተሉትና፡ያገለገሉትም፡ና
፶፮ ቸው። ሉ፡፰፡፪፡፫። እነዚያውም፡
ማርያም፡መግደላዊት፡ማርያም
ም፡የያዕቆብና፡የዮሳ፡እናት፡የዘ
ብዴዎስም፡የልጆቹ፡እናት፡ናቸው
፶፯ በመሸም፡ጊዜ፡ስሙ፡ዮሴፍ፡የ
ሚባል፡ባለጸጋ፡ሰው፡ከአርማቴ
ያስ፡መጣ፡እርሱም፡ደግሞ፡የኢየሱ
ስ፡ደቀ፡መዝሙር፡ነበር። ዮሐ፲፱፡፴፰
፶፰ ፴፱፡፵፪፡ዘፀ፡፴፩፡፳፭። እርሱም፡ወ
ደ፡ጲላጦስ፡ሒዶ፡የኢየሱስን፡ሬ
ሳ፡ለመነ፡ጲላጦስም፡ሬሳውን፡ይሰ
፶፱ ጡት፡ዘንድ፡አዘዘ። ዮሴፍም፡ሬሳ
ውን፡ወስዶ፡በነጭ፡በፍታ፡ከፈነው
፷ ለራሱም፡በደንጊያ፡ባሳነፀው፡በአ
ዲሱ፡መቃብር፡ቀበረው፡የመቃብ
ሩንም፡ደጃፍ፡ታላቅ፡ደንጊያ፡አንከባ
ብሎ፡ገጥሞት፡ሔደ። ኢሳ፡፶፫፡፱፡

፷፩ በዚያም፡ማርያም፡መግደላዊ
ት፡ሁለተኛይቱ፡ማርያም፡በመቃ
ብሩ፡አንፃር፡ቁመው፡ነበሩ።
፷፪ በነገውም፡ከዓርብ፡በኋላ፡በሚ
ሆን፡ቀን፡የካህናት፡አለቆች፡ፈሪ
ሳውያን፡ወደ፡ጲላጦስ፡ተሰበሰቡ።
፷፫ አሉትም፡ጌታዬ፡ሆይ፡ያ፡መስሐ
ቲ፡በሕይወቱ፡ሳለ፡ከሦስት፡ቀን፡በ
ኋላ፡እነሣለሁ፡ያለውን፡አሰብን፡
፷፬ ቀኑ፡፫። ስለዚህም፡ደቀ፡መዝሙር
ቹ፡በሌሊት፡መጥተው፡እንዳይሰ
ርቁት፡ለሕዝቡም፡ከሙታን፡ተነሣ
እንዳይሉ፡መቃብሩ፡እስከ፡ሦስት
ቀን፡እንዲጠበቅ፡እዘዝ፡የኋለኛ
ው፡ቱም፡ስሕተቱ፡ከፊተኛይቱ፡የ
፷፭ ከፋች፡ትሆናለችና። ጲላጦስም፡
ጠባቆች፡አሏችሁ፡ሒዱችሁ፡እ
ንደምታውቁ፡መቃብሩን፡አፅኑ።
፷፮ አላቸው። እርሳቸውም፡ሒደው፡
መቃብሩን፡አፅኑ፡ደንጊያውንም
አትመው፡ጠባቆችን፡አስቀመጡ
ዳን፡፮፡፲፯። ምዕራፍ፡፳፰።
ለእሑድ፡አጥቢያ፡ሴቶች፡ወደ፡መቃ
ብሩ፡እንደ፡መጡ፡ጌታችን፡ከሙታ
ን፡እንደ፡ተነሣ፡የካህናት፡አለቆ
ች፡ለዘበኞች፡ገንዘብ፡እንደ፡ሰጡ፡
የጥምቀትን፡ሥርዓት፡እንዳስተማ
ረ፡እስከ፡ዓለምም፡ፍጻሜ፡ከናንተ፡ጋ
፩ ራ፡ነኝ፡እንዳላቸው። በሰንበት፡ማ
ታ፡ለእሑድ፡አጥቢያ፡ማርያም፡መ
ግደላዊት፡ሁለተኛይቱም፡ማርያ

ም[illegible]ብሩን፡ሊያዩ፡መጡ፤ማ
ር፡፲፮፡ሉቃ፡፳፬፡፩፡ዮሐ፡፳፡፩፡ቈር፡፲፭፡
፪ ፩፡፫። እነሆ፡ታላቅ፡መናወጥ፡ሆኖ፡ነ
በረ፡የእግዚአብሔር፡መልአክ፡ከሰማ
ይ፡ወርዷልና፡መጥቶም፡ድንጊያውን፡
ከመቃብሩ፡ደጃፍ፡ፈንቀለው፡በላዩም፡
፫ ተቀመጠ[illegible]መልኩም፡እንደ፡መብረቅ፡ል
ብሱም፡እ[illegible]በረዶ፡ነጭ፡ነበረ፤ምዕ፲፯፡፪፡
፬ የሐለው[illegible]ግርማውም፡የተነሣ፡ጠባ
ቂዎች፡ደንግ[illegible]ው፡እንደ፡በድን፡ሆኑ።
፭ መልአ[illegible]ለሴቶቹም፡አላቸው
እናንተስ፡አትፍሩ፡የተሰቀለውን፡ኢየሱ
፮ ስን፡እንድትፈልጉ፡አውቃለሁና፤እርሱም
እንደ፡ተናገረ፡ተነሥቶአል፡ከዚህ፡የለ
ም፡ተ[illegible]ርበት፡የነበረውን፡ስፍራ፡ዘን
ድ፡ኑና፡እዩ፤ምዕ፲፮፡፳፩፡ዮሐ፡፲፡፲፮።
፯ ፈጥናችሁም፡ሒዱ፡ለደቀ፡መዛሙርቱ
ም፡ከሙታን፡እንደ፡ተነሣ፡ንገሩአቸው፤
እነሆም፡ወደ፡ገሊላ፡ይቀድማችኋል፡በ
ዚያም፡ታዩታላችሁ፤እነሆም፡ነገርኋ
፰ ችሁ። ምዕ፳፮፡፴፪። ፈጥነውም፡ከመቃ
ብሩ፡ወጡ፡በፍርሃት፡በታላቅ፡ደስታም፡
ለደቀ፡መዛሙርቱ፡ይነግሩ፡ዘንድ፡ሔ
፱ ዱ። እነሆ፡ኢየሱስ፡ አገኛቸውና፡ደ
ስ፡ይበላ[illegible]፡አላቸው፤እርሳቸውም
ቀርበው፡እግሩን፡ይዘው፡ሰገዱለት።
፲ በዚያም፡ጊዜ፡ ኢየሱስ፡አትፍሩ፡ሒዱ
ችሁ፡ወደ፡ገሊላ፡እንዲሔዱ፡ለወንድሞ
ቼ፡ንገሩ፡በዚያም፡ያዩኛል፡አላቸው።
፲፩ ሰብ፡፮[illegible]ሔዱም፡ጊዜ፡ከጠባቂዎች፡
ወገን፡[illegible]ወደ፡ከተማ፡መጥተው፡

የሆነውን፡ሁሉ፡ለካህናት፡አለቆች፡ነገ
፲፪ ሩ። እርሳቸውም፡ከሽማግሌዎቹ፡ጋራ
ተሰብስበው፡ተማከሩ፡ለጭፍሮችም፡ብዙ
፲፫ ገንዘብ፡ሰጧቸው። እንዲህ፡ሲሉ፡እኛ፡
ተኝተን፡ሳለን፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡በሌ
ሊት፡መጥተው፡ሠረቁት፡በሉ፤ምዕ፳፯፡
፲፬ ፷፬። ይህም፡ወሬ፡በሹሙ፡ዘንድ፡የተ
ሰማ፡እንደ፡ሆነ፡እንዲያምኑ፡እናደርግ
ዋለን፡እናንተም፡ያለ፡ሥጋት፡እንድት
፲፭ ሆኑ፡እናደርጋለን። እነርሳቸውም፡ገ
ንዘቡን፡ተቀብለው፡እንደ፡ተማርዋ
ቸው፡አደረጉ፤ይህም፡ነገር፡እስከ፡ዛሬ
በአይሁድ፡ዘንድ፡ሲነገር፡ይኖራል።
፲፮ አሥራ፡አንዱ፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡ግን፡
ኢየሱስ፡ እንዳዘዛቸው፡ወደ፡ገሊላ፡ተ
፲፯ ራራ፡ሔዱ። ባዩትም፡ጊዜ፡ሰገዱለት፤
አንዳንዶቹ፡ግን፡ተጠራጠሩ።
፲፰ ኢየሱስ ም፡ቀርቦ፡የሰማይና፡የ
ምድር፡ሥልጣን፡ተሰጠኝ፡ብሎ፡ነገ
ራቸው። ምዕ፲፩፡፳፯፡ኤፌ፡፩፡፳፩።
፲፱ እንግዲህ፡ሒዱና፡አሕዛብን፡ሁሉ፡አ
ስተምሩ፡በአብና፡በወልድ፡በመንፈ
ስ፡ቅዱስ፡ስም፡አጥምቁአቸው።
ማር፲፮፡፲፭፡፲፮።
፳ ያዘዝኋችሁንም፡ሁሉ፡እንዲጠብቁ
አስተምሩአቸው፤እነሆም፡እኔ፡እስከ
ዓለም፡ፍጻሜ፡በዘመኑ፡ሁሉ፡ከእና
ንተ፡ጋራ፡ነኝ፡አሜን።
ም፲፰፡፳፡ዘሌዋ፡፲፡፲፮።

የማቴዎስ፡ወንጌል፡ተፈጸመ።

ብሥራተ፡ማርቆስ፡ወንጌላዊ፡፩፡
አም፫ወ፱ቱ፡አርድእት፡ጸሎቱ፡
ወበረከቱ፡የሀሉ፡ምስለ፡ንጉሥነ
መፍቀሬ፡እግዚአብሔር፡ኃይ
ለ፡ሥላሴ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።
ስለ፡መጥምቁ፡ዮሐንስ፡ስብከት፡
ስለ፡ጌታችን፡መጠመቅ፡ከዲያብ
ሎስ፡እንደ፡ተፈተነ፤በገሊላ፡እንደ
ስተማረና፡አራት፡ደቀ፡መዛሙር
ቱ፤እንደ፡ተከተሉት፤በቅፍርናሆ
ም፡እንደ፡ሰበከና፤ርኩስ፡መንፈስ
ያደረበትን፤እንዳዳነ፤የጴጥሮስን
አማት፡እንደ፡ፈወሰ፤ድውያንን፡እ
ንደዳነና፤ለምጻም፡እንደ፡ነጻ።

፩ የእግዚአብሔር፡ልጅ፡የጌታችን
የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወንጌል፡መ
ጀመሪያ፡ይህ፡ነው፡ማቴ፡፫፡ሉ፡፫
፪ ዮሐ፡፩፡፲፱፡በነቢያት፡እንደ፡ተጻፈ
ው፡እነሆ፡መንገድህን፡የሚጠርግ
መልክተኛዬን፡በፊትህ፡እልካለሁ
ሚል፡፫፡፩፡፬፡ማቴ፡፲፩፡፲።
፫ የእግዚአብሔርንም፡መንገድ፡ጥ
ረጉ፡ጥርጊያውንም፡አስተካክሉ
ብሎ፡በምድረ፡በዳ፡የሚጮህ፡ያ
፬ ቃል፡ነገረ፡ቃል፤ኢሳ፡፵፡፫። ዮሐንስ
በምድረ፡በዳ፡እያጠመቀ፡ኃጢአት
ን፡ለማስተሥረይ፡የንስሐ፡ጥምቀ
፭ ቀት፡ይሰብክ፡ነበረ፤የይሁዳና፡የ
ኢየሩሳሌም፡ሰዎች፡[illegible]ሉ፡ወደ፡እ
ርሱ፡ይመጡ፡ነበር፡በኃጢአታቸ
ውም፡እየተናዘዙ፡[illegible]ርዳኖስ፡
ወንዝ፡ያጠምቃቸው፡ነበር።
፮ የዮሐንስም፡ልብሱ፡[illegible]የግመል፡ጸ
ጉር፡ነበር፡ወገቡንም፡በጠፍር፡
መታጠቂያ፡ይታጠቅ፡ነበረ፡መ
ብሉም፡አንበጣ[illegible]ዝማ፡ማ
፯ ር፡ነበረ። እንደ[illegible]ሰብ
ክ፡ነበረ፡ከእኔ፡ይ[illegible]የሚበረታ
ተጉ፡ብሼም፡የ[illegible]ን፡ጠፍር
አፈታ፡ዘንድ፡የ[illegible]ገባኝ፡እርሱ
ከኔ፡በኋላ፡ይመጣል።
፰ እኔ፡በውሀ፡አጠምቃችኋለሁ፡እር
ሱ፡ግን፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ያጠም
፱ ቃችኋል። በዚያ፡ወራትም፡ኢየ
ሱስ፡ከናዝሬት፡ከገሊላ፡አገር፡መ
ጣ፡ከዮሐንስም፡በዮርዳኖስ፡ተ
ጠመቀ። ዮሐ፩፡ማ፲፫፡ማ፲፬፡ሉ፡፫፡፳፩
፲ ከውሀም፡ሲወጣ፡ሰማዮች፡ሲከ
ፈቱ፡መንፈስ፡ቅዱስም፡እንደ፡ር
፲፩ ግብ፡ሲወርድ፡አየ፤ከሰማይም፡
የምወድህ፡ደስታዬም፡የማይ
ብህ፡ልጄ፡አንተ፡ነህ፡የሚል፡ድም
፲፪ ፅ፡መጣ፡ማ፬፡፲፯፡[illegible]ም፡መን
ፈስ፡ወዲያውም፡ወደ፡ምድረ፡በዳ፡[illegible]ሉ
፲፫ ቃ፡፬፡፩፡፲፫፡በዚያ[illegible]በምድረ፡በደ
አርባ፡ቀን፡ኖረ፡ከሰይጣንም፡ይፈ

ቀን፡ነበረ፤ከአራዊትም፡ጋራ፡ነበ
ረ፤መላእክትም፡ያገለግሉት፡ነበ
፲፬ ር፨ዮሐንስም፡ከታሰረ፡በኋላ፡ኢየ
ሱስ፡የእግዚአብሔር፡መንግሥት
ወንጌልን፡እየሰበከ፡ወደ፡ገሊላ፡መ
፲፭ ጣ፨ጊዜው፡ደረሰ፡መንግሥተ፡ሰ
ማያትም፡ቀረበች፡ንስሑ፡ግቡ፡በ
ወንጌልም፡እመኑ፡አለ፡ገላ፡፬፡፬
፲፮ በገሊላ፡ባሕርም፡አጠገብ፡ሲያል
ፍ፡ስምዖንና፡ወንድሙ፡እንድርያ
ስን፡መረባቸውን፡ወደ፡ባሕር፡ሲ
ጥሉ፡አየ፡ዓሣ፡አጥማጆች፡ነበሩ
ና፤ማቴ፡፬፡፲፰፡፳፪፡ሉ፡፭፡፩፡፲፩፨
፲፯ ኢየሱስም፡በኋላዬ፡ተከተሉ
ኝ፡ሰዎችንም፡እንድታጠምዱ፡አደ
፲፰ ርጋችኋለሁ፡አላቸው፨ያንጊ
ዜም፡መረባቸውን፡ትተው፡ተከተ
፲፱ ሉት፨ከዚያም፡ጥቂት፡ፈቀቅ፡ብ
ሎ፡የዘብዴዎስን፡ልጆች፡ያዕቆብ
ንና፡ወንድሙ፡ዮሐንስን፡በታንኳ
ሁነው፡መረባቸውን፡ሲያበጁ፡አ
ገኛቸው፡እርሱም፡ከእርሳቸው፡
፳ ጋራ፡ነበረ፨ያንጊዜም፡ጠራቸው፡
አባታቸውን፡ዘብዴዎስንም፡ከሙ
ንደኞች፡ጋራ፡በታንኳ፡ላይ፡ትተ
፳፩ ው፡ተከተሉት፨ወደ፡ቅፍርናሆ
ም፡ሔዱ፤በቅዳሚም፡ቀን፡ወደ፡መ
ስጊድ፡ገብቶ፡ያስተምራቸው፡
፳፪ ጀመር፨ሉቃ፡፬፡፴፩፡፴፪፡ትምህ
ርቱም፡አደነቁ፡እንደ፡ጻፎች፡ሳይ
ሆን፡ሥልጣን፡እንዳለው፡ያስተም

ራቸው፡ነበርና፤ማቴ፡፯፡፳፰፡፳፱
፳፫ በምኩራባቸውም፡ርኩስ፡መንፈ
ስ፡ያደረበት፡ሰው፡ነበረ፡እንዲህ
፳፬ ም፡እያለ፡ጮኸ፤የናዝሬቱ፡ኢየ
ሱስ፡ሆይ፡አንተንና፡እኛን፡ምን፡
አገናኘን፡ልታጠፋን፡መጣህን
የእግዚአብሔር፡ቅዱስ፡ሆይ፡አንተ
ማን፡እንደሆንህ፡አውቃለሁ፡ማር፡
፭፡፯፡መዝ፡፲፯፡፲፡፶፯፡፲፯፨
፳፭ ኢየሱስም፡ዝም፡በለህ፡ከእርሱ
፳፮ ውጣ፡ብሎ፡ገሠጸው፨ርኩስ፡መን
ፈስም፡አንዘፈዘፈው፡በታላቅ፡
ቃልም፡እየጮኸ፡ከእርሱ፡ወጣ፨
፳፯ ም፬፡፴፯፨ሁሉም፡አደነቁ፡እርስ፡
በርሳቸውም፡ይህ፡አዲስ፡ትምህር
ት፡ምንድር፡ነው፡ርኩሳን፡መናፍስ
ትን፡በሥልጣን፡ያዝቸዋል፡እርሳ
ቸውም፡ይታዘዙታልና፡ተባባሉ፤
፳፰ በዚያን፡ጊዜም፡ዝናው፡በገሊላ፡አ
ጠገብ፡ባለው፡አገር፡ሁሉ፡ወጣ፨
፳፱ ያንጊዜም፡ከምስጊድ፡ወጥቶ፡ወ
ደ፡ስምዖን፡ቤት፡ገባ፡ከእርሱም፡ጋ
ራ፡እንድርያስና፡ያዕቆብ፡ዮሐንስ፤
ማቴ፡፰፡፲፬፡፲፮፡ሉ፡፬፡፴፰፡፴፱፨
፴ የስምዖንም፡አማት፡በንዳድ፡መ
ኝታ፡ተኝታ፡ነበረች፡የዚያን፡ጊዜ፡
፴፩ ስለ፡እርሷ፡ነገሩት፨እርሱም፡ቀረ
በና፡እጇን፡ይዞ፡አስነሣት፡ያንጊዜ
ውንም፡የንዳዱ፡መንሾ፡ተዋት፡ተ
፴፪ ነሥታም፡አገለገለቻቸው፨በመሸ
ም፡ጊዜ፡ፀሐይ፡ሲገባ፡ልዩ፡ልዩ፡ደዌ

ያለባቸውን፡ጋኔኛም፡ያደረባቸው
፴፫ ን፡አመጡ ለትቀየ አገሩም፡ሰዎች
ሁሉ፡በደጅ፡ተሰብስበው፡ነበሩ፨
፴፬ በልዩ፡ልዩ፡ደዌ፡ከታመሙትም፡
እጅግ፡ፈወሰ፡እጅግም፡ሰይጣና
ትን፡አወጣ፡ሰይጣናትም፡ይናገሩ
ዘንድ፡አልፈቀደላቸውም፡እርሱ
ክርስቶስ፡እንደሆነ፡አውቀውታ
ልና፨ሉቃ፡፬፡፵፩፡ዮሐ፡፲፯፡፲፯፡፲፰፤
፴፭ እጅግም፡ማልደ፡በሌሊት፡ተነሣ
ወጥቶም፡ወደ፡ምድረ፡በዳ፡ሔደ፡
በዚያም፡ይጸልይ፡ነበረ፨ሉ፡፬፡፵
፴፮ ፪፡፵፫፨ስምዖንና፡ከእርሱም፡ጋ
፴፯ ራ፡የነበሩት፡ተከተሉት፨ባገኙ
ትም፡ጊዜ፡ሁሉ፡ይፈልግሃል፡አሉት
፴፰ እርሱም፡ተነሡ፡ወደ፡ሌላው፡መ
ንደር፡እንሒድ፡አላቸው፡በዚያ
ም፡እሰብክ፡ዘንድ፡ስለዚህ፡መጥ
፴፱ ቻለሁና፨ሉቃ፡፬፡፵፫፨በየመስጊ
ዳቸውም፡ሔደ፡እስተ ማረ፡በገሊ
ላም፡ሁሉ፡ሰይጣናትን፡አወጣ፨
፵ ለምጽም፡ወደ፡እርሱ፡መጥቶ፡በ
ጕልበቱም፡ተንበርክኮ፡ብትፈ
ቅድስ፡ታነጻኘ፡ዘንድ፡ትችላለህ
ብሎ፡ለመነው፨ማቴ፡፰፡፩፡ሉ፡፭
፵፩ ፲፪፡፲፯ ፨ኢየሱስ፡ም፡ራራለት፡
እጁንም፡ዘርግቶ፡ዳሰሰውና፡ፈ
፵፪ ቅደለሁ፡ንፃ፡አለው፨በተናገረም
ጊዜ፡ለምጹ፡ፈጥኖ፡ከእርሱ፡ለ
፵፫ ቀቀ፡ነፃም፨የዚያን፡ጊዜም፡ሰደ
ደው፡አዘዘውም፨ም፫፡፲፬፡፯፡፵፯

፵፬ ለማንም፡እንዳትናገር፡ተጠን
ቀቅ፡ነገር፡ግን፡ራስህን፡ለካህን፡
አስመርምር፡ስለ፡ነፃሕም፡ሙሴ
እንደ ዘዘ፡መባሕን፡አቅርብ፡ም
ስክር፡ይሆንባቸው፡ዘንድ፡አለ
፵፭ ው፨እርሱ፡ግን፡በመጣ፡ጊዜ፡እጅ
ግ፡ይሰብክ፡ጀመር፡ዝናውም፡ወ
ጣና፡ተገለጠ፡ወደሀገር፡መግባት
እስኪሳነው፡ድረስ፡ነገር፡ግን፡በ
ውጭ፡በምድረ፡በዳ፡ነበረ፡ከየቦታ
ውም፡ሁሉ፡ወደ፡እርሱ፡ይመጡ፡
ነበሩ፨ ምዕራፍ፡፪፨

በቅፍርናሆም፡መፃጕዕን፡እንደ፡
አዳነ፡የአልፍዮስን፡ልጅ፡ሌዊን፡እ
ንደ፡ጠራ፤ከቀራጮችና፡ከኃጢ
አተኞች፡ጋራ፤አብሮ፡እንደ፡በላ፤
ፈሪሳውያን፡ስለ፡ጾም፡ነገር፤እ
ንደ፡ጠየቁት፤የሰንበት፡ጌታ፡እን
፩ ደሆነ፨ ደግሞ፡ከጥቂት፡ቀን፡በኋ
ላ፡ወደ፡ቅፍርናሆም፡ገባ፡በቤት
ም፡መኖሩ፡በተሰማ፡ጊዜ፨ማቴ፡
፱፡፩፡፲፰፡ሉ፡፭፡፲፯፡፳፰፨
፪ በደጅ፡ያለው፡ስፍራ፡እስኪጠባቸ
ው፡ድረስ፡ብዙ፡ሰዎች፡ወደ፡እርሱ
ተሰበሰቡ፡ቃሉንም፡ይነግራቸው
፫ ነበረ፨አራት፡ሰዎችም፡በአልጋ፡ተ
ሸክመው፡መፃጕዕ፡ሽባ፡አመጡ
፬ ለትቀሰሉ፡ሕዝቡም፡ብዛት፡ወደ፡እ
ርሱ፡ማቅረብ፡ቢሳናቸው፡እርሱ
ያለበትን፡የቤቱን፡ጣራ፡ነድለው
መፃጕዕን፡ከነአልጋው፡አወረዱት

፭ ኢየ[illegible]እምነታቸውን፡ባዩ፡
ጊዜ፡ወ[illegible]ጕሡን፡ልጄ፡ሆይ፡ኃጢ
፮ አት[illegible]ሠረየችልህ፡አለው፡ቀበ
ዚያም፡ከጸሐፍት፡ወገን፡ሰዎች፡ተቀ
ምጠው፡[illegible]፡በልባቸውም፡አሰ
፯ ቡ፡ይህ፡ለምን፡እግዚአብሔርን
እየተሳ[illegible]ይናገራል፡ካንዱ፡ከእ
ግዚአ[illegible]ር፡በቀር፡ኃጢአት፡ማ
ስተ[illegible]ማን፡ይችላል፡አሉ፡ኢሳ
[illegible]ዝ፡ዘፀ፡፴፬፡፯ ቀ
፰ ኢየሱ[illegible]ልባቸው፡እንዲህ፡እን
ዲያስቡ፡በ[illegible]ንፈሱ፡አውቆ፡ይህን
ለባችሁ፡ለምን፡ታስባላችሁ፡አላቸ
፱ ው፡ዮሐ፡፪፡፳፬፡፳፭ ቀ መፃጉዑን፡
ኃጢአት[illegible]ሠረየልህ፡ከማለት
ና፡ወይ[illegible]ነሣ፡አልጋህን፡ተሸክ
መህ፡[illegible]ማለት፡ማናቸው፡ይ
፲ ቀላል[illegible]ድር፡ላይ፡ኃጢአትን፡
ያስተሠርይ፡ዘንድ፡ለሰው፡ልጅ፡ስ
ልጣን፡እንዳለው፡ታውቁ፡ዘንድ፡
፲፩ ጻጉመኛ፡ድውዩን፡ተነሣና፡አልጋህ
ን፡ተሸክመህ፡ወደ፡ቤትህ፡ግባ፡እል
፲፪ ሃለሁ፡አለው፡ቀ በዚያም፡ጊዜም፡
ተነሣና፡አልጋውን፡ተሸክሞ፡በሰ
ዉ፡ሁሉ[illegible]ት፡ወጣ፡ሰው፡ሁሉ፡እ
ስኪደ[illegible]፡ድረስ፡እግዚአብሔ
ርንም፡[illegible]ሰገኑ፡እንዲህ፡ያለ፡ከቶ
አላየንም፡እያሉ፡ሉቃ፡፭፡፳፮፡ደግ
፲፫ ሞም፡ወደ፡ባሕር፡ዳር፡ወጣ፡ሰውም፡
ሁሉ፡ወ[illegible]ርሱ፡ይመጣ፡ነበር።
፲፬ እርሱ[illegible]ያልፍ፡የእልፍዮስን

ልጅ፡ሌዊን፡ተቀምጦ፡ሲቀርጥ፡
አየው፡ተከተለኝም፡አለው፡እርሱ
፲፭ ም፡ተነሥቶ፡ተከተለው፡በቤቱ
ም፡ለምሳ፡ተቀምጦ፡ሳለ፡ብዙ፡ቀ
ራጮችና፡ኃጢአተኞች፡ከኢየሱ
ስና፡ከደቀ፡መዛሙርቱ፡ጋራ፡ተቀ
ምጠው፡ነበር፡የተከተሉትም፡እ
፲፮ ጅግም፡ነበሩና፡ቀ፪፡፲፯ ። ጸፎች
ና፡ፈሪሳውያንም፡ከቀራጮችና፡
ከኃጢአተኞች፡ጋራ፡ሲበላ፡ባዩ፡ጊ
ዜ፡ደቀ፡መዛሙርቱን፡መምራችሁ
ከቀራጮችና፡ከኃጢአተኞች፡ጋራ
ለምን፡ይበላል፡ይጠጣልም፡አሏቸ
፲፯ ው፡ኢየሱስም፡ሰምቶ፡ሐኪም፡የሚ
እንጂ፡ባለጤኖች፡ባለመድኃኒተኛ
አይሹትም፡ጻድቃንን፡ያይደለ፡ኃ
ጥኣንን፡ወደ፡ንስሐ፡ልጠራ፡መጥቻ
፲፰ ለሁ፡ጢሞ፡፩፡፲፭ ቀ የዮሐንስም፡ደ
ቀ፡መዛሙርት፡የፈሪሳውያንም፡ወ
ገን፡ይጾሙ፡ነበርና፡መጥተው፡የዮ
ሐንስና፡የፈሪሳውያን፡ደቀ፡መዛ
ሙርት፡ለምን፡ይጾማሉ፡ደቀ፡መ
ዛሙርትህ፡ግን፡አይጾሙም፡አሉ
፲፱ ት፡ኢየሱስም፡አላቸው፡የሠርግ፡
ልጆች፡ሚዜዎች፡ሙሽራው፡ከእ
ርሳቸው፡ጋራ፡ሳለ፡ይጾሙ፡ዘንድ፡
፳ ይቻላቸዋልን፡ግን፡ሙሽራው፡
ከእርሳቸው፡የሚለይበት፡ዘመን
ይመጣልና፡በዚያን፡ጊዜ፡ይጾማሉ።
፳፩ ማንም፡ባረጌ፡ልብስ፡ላይ፡አዲስ፡
እራፊ፡የሚጥፍ፡የሚጠቅም፡የ

ለጥፍም፡ ያለዚያ፡ግን፡አዲሱ፡እራፊ፡አ
ሮጌውን፡ይቀድዋል፡መቀደዱም፡
፳፪ ታላቅ፡ይሆናል፡አዲስ፡ጠጅም፡በ
ርጌ፡አቁማዳ፡ቀርበታ፡የሚያኖር
የለም፡ያለዚያም፡አዲሱ፡ጠጅ፡አሮ
ጌውን፡አቁማዳ፡ያፈነዳል፡ጠጁም
ይፈሳል፡አቁማዳውም፡ይበላሻል
አዲሱ፡ጠጅ፡ግን፡በአዲሱ፡አቁማዳ
፳፫ ይገለበጣል፡፡ ከዚህ፡በኋላ፡ኢየሱ
ሱ፡በሰንበት፡በእርሻ፡መካከል፡ሲሄ
ድ፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡በመንገድ፡ሲ
ያልፉ፡እሸት፡ይነቅሉ፡ነበር፡መን
ገዱንም፡ያቃኑለት፡ጀመርቀሉ፡፪
፳፬ ፩፡፭ ማቴ፡፲፪፡፩፡፰ ፈሪሳውያን
ም፡እነሆ፡ደቀ፡መዛሙርትህ፡በሰ
ንበት፡ማድረግ፡የማይገባውን፡ሲ
፳፭ ያደርጉ፡አስተውል፡አሉት፡እርሱ
ም፡አላቸው፡ዳዊት፡በተራበ፡ጊዜ
ከእርሱም፡ጋራ፡ያሉት፡ያደረገው
፳፮ ን፡አላነበባችሁምን፧ አብያታር፡
የካህናት፡አለቃ፡በነበረበት፡ወራ
ት፡ወደ፡ቤተ፡እግዚአብሔር፡ገብ
ቶ፡መብላት፡ለካህናት፡ብቻ፡እንጂ
ለእርሱ፡የማይገባውን፡የመሥ
ዋዕቱን፡ኅብስት፡እንዴት፡በላ፡ደግ
ሞ፡ከእርሱ፡ጋራ፡ለነበሩት፡እንዴ
ሰጣቸው፡፩፡ሳሙ፡፳፩፡፩፡፳፭፡፳
፳፯ ዘሌ፡፳፬፡፱፡፡ ሰንበት፡ስለ፡ሰው፡ተ
ፈጠረ፡እንጂ፡ሰው፡ለሰንበ
፳፰ ት፡አልተፈጠረም፡አላቸው፡የ
ሰንበት፡ጌታ፡የሰው፡ልጅ፡ነው፡፡

ምዕራፍ፡[illegible]

በመስጊድ፡እጁ፡የሰ[illegible]ው፡እንደ
አደነ፡ብዙ፡ሰዎች፡[illegible]ደ፡ፈወሰ፡
አሥራ፡ሁለቱን፡[illegible]ርያት፡እን
ዲ፡መረጠ፡ከሥ[illegible]ና፡መን
ፈስ፡ዊ፡ዝምድና፡[illegible]ጅ፡በልጥ።
፩ ደግሞም፡ወደ፡መ[illegible]ድ፡ገባ፡በዚ
ያም፡እጁ፡የሰለ[illegible]ነበረ።
ማቴ፡፲፪፡፱፡፲፬[illegible]
፪ በሰንበት፡ያድነ[illegible]ንደሆነ፡ብ
ለው፡ሊያሳጡ[illegible]ቀቀቱ፡ነበ
፫ ሩ። እጁ፡የሰለለ[illegible]ሰው፡በመ
፬ ካከል፡ቁም፡አለ[illegible]በሰንበት፡መ
ልካም፡ሥራ፡መ[illegible]ራት፡ይገባልን
ወይስ፡ክፉ፡ማ[illegible]ነፍስ፡ማዳ
ን፡ነው፡ወይስ፡[illegible]ል፡አላቸው
እርሳቸው፡ግ[illegible]አሉ።
፭ ስለ፡ልባቸው፡[illegible]ዚ፡አዝኖ፡ወደ
እርሳቸው፡ዞር፡በቍጣ፡ቃኘና፡ሰ
ዩ፡ያነኘም፡ሰው፡እጅህን፡ዘርጋ፡አ
ለው፡ዘረጋትም፡እጁም፡ደኅና፡ሆ
፮ ነች። የሐ፲፩፡፴፫። በዚያ፡ጊዜም፡
ፈሪሳውያንም፡[illegible]ወጥተው፡ሊገድ
ሉት፡ከሄሮድስ፡[illegible]ዎች፡ጋራ፡ተማ
፯ ከሩበት። ማቴ፡[illegible]፲፪፡ኢየሱስ፡ግ
ን፡ከደቀ፡መዛሙ[illegible]ጋራ፡ወደ፡ባ
ሕር፡ሔደ፡እንጂ[illegible]ሰዎች፡ከገሊ
፰ ላና፡ከይሁዳ፡ተ[illegible]ሉት፡ያደረገ
ውንም፡ሁሉ፡በ[illegible]ው፡ጊዜ፡ከኢየ
ሩሳሌምም፡ከኤ[illegible]ያስም፡ከዮ
ርዳኖስ፡ማዶ[illegible]ጢሮስና፡ከሲ

ደናምም፡ለመንግብ፡እጅግ፡ሰዎች፡ወደ
፱ እርሱ፡መጡ፡ስለ፡ሰዎቹም፡ብዛ
ት፡እንዳያስጨንቁት፡ታንኳ፡እ
ንዲያዘጋጁለት፡ደቀ፡መዛሙር
፲ ቱን፡አዘዛቸው፡ብዙ፡ሰዎችን፡ስ
ለፈወሰ፡ሕመም፡ያለባቸው፡ሁሉ፡
እርሱን፡ለመዳሰስ፡በላዩ፡እስከ፡
መጋፋት፡ድርሰው፡ነበርና።
፲፩ ርኩሳን፡መናፍስት፡ያደሩባቸው፡ሰ
ዎች፡ባዩት፡ጊዜ፡ይሰግዱለት፡ነበር፡
የእግዚአብሔር፡ልጅ፡አንተ፡ነ
ህ፡እያሉ፡ይጮኹ፡ነበርና፡ሉ፡፬፡፵፩
፲፪ እንዳይገልጡትም፡እጅግ፡ገሠፃ
፲፫ ቸው፡፩፡፴፬፡ወደ፡ተራራም፡ወጣ
ና፡የወደዳቸውን፡ጸራ፡ወደ፡እርሱ፡
ም፡መጡ፡ማቴ፡፲፡፩፡ሉ፡፮፡፲፪፡
፲፬ አሥራ፡ሁለቱን፡መርጦ፡ሐዋርያ
ት፡አላቸው፡ሊያስተምሩም፡ይ
ልካቸው፡ዘንድ፡ከእርሱም፡ጋራ፡
፲፭ እንዲኖሩ፡አደረጋቸው፡ደውያ
ንንም፡ለመፈወስ፡ሰይጣናትንም
ለማውጣት፡ሥልጣን፡ሰጣቸው።
፲፮ በየስማቸውም፡ጸራቸው፡ስም
፲፯ ዖንን፡ጴጥሮስ፡አለው፡የዘብዴ
ዎስን፡ልጅ፡ያዕቆብንም፡ያዕቆብ
ወንድሙ፡ዮሐንስንም፡ሰማቸው
ንም፡ቦአኔርጌስ፡አላቸው፡የነጐ
ድጓድ፡ልጆች፡ማለት፡ነው፡ሉ፡፱፡
፲፰ ፶፬፡እንድርያስንም፡ፊልጶስን፡
ም፡በርተሎሜዎስንም፡ማቴዎ
ስንም፡ቶማስንም፡የእልፍዮስ
ን፡ልጅ፡ያዕቆብንም፡ታዴዎስንም
፲፱ የቃናውን፡ስምዖንንም፡የአስቆሮ
ቱ፡ይሁዳንም፡እርሱም፡አሳልፎ፡
፳ የሰጠው፡ወደ፡ቤትም፡በገባ፡ጊዜ
እንጀራ፡ለመብላት፡ስንኳ፡እስኪ
ሳነው፡ድረስ፡ብዙ፡ሰዎች፡ተሰበሰ
፳፩ ቡ፡ዘመዶቹም፡በሰሙ፡ጊዜ፡ልቡ
ዞነጋ፡ብለዋልና፡ሊይዙት፡መጡ።
፳፪ ከኢየሩሳሌም፡የወረዱ፡ጻፎቹ
ም፡ብዔል፡ዜቡል፡አለበት፡በሰይ
ጣናትም፡አለቃ፡ሰይጣናትን፡ያ
ወጣል፡አሉ፡ማቴ፡፱፡፴፬፡፲፪፡፳፬፡ሉ፡
፳፫ ፲፩፡፲፭፡ኢየሱስም፡ጠርቶ፡ሰ
ይጣን፡ሰይጣንን፡ያወጣው፡ዘንድ
እንዴት፡ይችላል፡ብሎ፡በምሳሌ፡
፳፬ ነገራቸው፡መንግሥትም፡እርስ
በርሷ፡ብትለያይ፡ያቺ፡መንግሥት
፳፭ ትጸና፡ዘንድ፡አትችልምና፡ቤትም
እርስ፡በርሱ፡ብትለያይ፡ያቺ፡ቤት
፳፮ ትጸና፡ዘንድ፡አትችልምና፡ሰይጣ
ንም፡እርስ፡በርሱ፡ቢጻላ፡ቢለያይ
ም፡በዚሁ፡ይፈጸማል፡እንጂ፡ሊጸ
፳፯ ና፡አይችልምና፡ማንም፡አስቀድ
ሞ፡ብርቱውን፡ካላሠረ፡ወደ፡ብር
ቱ፡ቤት፡ገብቶ፡ዕቃውን፡ይዘርፍ፡
ዘንድ፡አይችልም፡ከዚያ፡ወዲያ
ም፡በቤቱ፡ያለውን፡ሁሉ፡ይዘርፋ
፳፰ ልና፡በሰው፡ልጆች፡የሚሰደቡት፡
ስድብና፡ኃጢአት፡ሁሉ፡እንዲሠ
፳፱ ረይ፡እውነት፡እላችኋለሁ፡በመ
ንፈስ፡ቅዱስ፡ላይ፡የሚሳደብ፡ግን

የዘለዓለም፡ፍርድ፡ይፈረድበታል
እንጂ፡ሥርየት፡የለውም።
፴ ርኩስ፡መንፈስ፡አድሮበታል፡ይሉ።
፴፩ ነበሩና። ቍ፭፬፡እናቱና፡ወንድሞ
ቹም፡መጥተው፡በውጭ፡ቆመው፡
ይጠሩት፡ዘንድ፡ላኩበት። ማቴ፡፲
፴፪ ፪፡፵፮፡፶፡ሉ፡፰፡ ፲፱፡፳፩፡በዙርያ
ውም፡ተቀምጠው፡የነበሩ፡ሰዎ
ች፡እናትህና፡ወንድሞችህ፡እነሆ
በውጭ፡ቆመው፡ይፈልጉሃል፡አሉት፤
፴፫ እርሱም፡እናቴ፡ማናት፡ወንድ
ሞቼስ፡እነማን፡ናቸው፡ብሎ፡መ
፴፬ ለሰላቸው፡በዙርያውም፡ተቀም
ጠው፡ወደነበሩት፡አይቶ፡እነሆ
እናቴም፡ወንድሞቼም፡እሉ፤
፴፭ የእግዚአብሔርን፡ፈቃድ፡የሚያ
ደርግ፡ሁሉ፡እርሱ፡ወንድሜ፡እኅቴ
ም፡እናቴም፡ነውና ፷ ም

ምዕራፍ፡፬።

በመርከብ፡ሁኖ፡ለሕዝቡ፡ሁሉ፡በ
ምሳሌ፡እንዳስተማረ፡ዘር፡ተዘርቶ
ሳይታወቅ፡እንዲያድግ፤ስለ፡ሰና
ፍጭ፡ምሳሌ፤በመርከብ፡ሳለ፡አ
ውሎ፡ነፋስ፡እንደ፡ተነሣ።

፩ ደግሞም፡በባሕር፡ዳር፡ያስተም
ር፡ጀመረ፡ወደ፡መርከብም፡ገብ
ቶ፡በባሕር፡እስኪቀመጥ፡ድረስ፡እ
ጅግ፡ሰዎች፡ወደ፡እርሱ፡ተሰበሰቡ
ሰውም፡ሁሉ፡በባሕሩ፡ዳር፡በምድ
ር፡ላይ፡ነበረ። ማቴ፡፲፫፡፩፡፳፫፡ሉ፡፰
፪ ፬፡፲፩፡ብዙ፡ምሳሌም፡መስሎ፡ያ
ስተምራቸው፡ነበረ፡ሲያስተ
ምራቸውም፡እንዲህ፡አላቸው።
፫ ስሙ፡እነሆ፡ዘሪ፡ይዘራ፡ዘንድ፡ወ
፬ ጣ፡እርሱም፡ሲዘራ፡ከዘሩ፡አንዳ
ንድ፡በመንገድ፡ዳር፡የወደቀ፡አለ፡የሰ
ማይ፡ወፎችም፡መጥተው፡በሉት።
፭ አንዳንዱም፡መሬት፡በሌለበት፡በጭ
ንጫ፡ላይ፡የወደቀ፡አለ፡ፈጥኖም
በቀለ፡ለመሬቱ፡ጥልቀት፡የለ
፮ ውምና፡ፀሐይ፡በወጣች፡ጊዜ
ተቃጠለ፡ሥርም፡ስለ፡ሌለው፡ደ
ረቀ፡መሬቱ፡ጥልቅ፡አይደለምና
፯ በእሾህም፡ላይ፡የወደቀ፡አለ፡እሾ
ሁ፡ወጥቶ፡አነቀውና፡አላፈራም
፰ በመልካምም፡መሬት፡የወደቀ፡
አለ፡በቀለ፡አደገ፡እንዲያም፡፴
ሌላውም፡ስልሳ፡ሌላውም፡መቶ
፱ ፍሬ፡ሰጠ፡የሚሰማ፡ጆሮ፡ያለው
፲ ይስማ፡አላቸው። ብቻውንም፡በ
ሆነ፡ጊዜ፡በዙርያው፡የነበሩት፡ከአ
ሥራ፡ሁለቱ፡ጋራ፡ምሳሌውን፡ጠየ
፲፩ ቁ፡አላቸውም፡ለእናንተ፡የእግ
ዚአብሔርን፡መንግሥት፡ምሥ
ጢር፡ማወቅ፡ተሰጥቶአችኋል፡
በውጭ፡ላሉት፡ግን፡ነገር፡ሁሉ፡በ
ምሳሌ፡ይሆንባቸዋል። ቍ፩ቆር፡፲፪
፲፪ ማየትን፡እያዩ፡እንዳይመለከቱ፡
መስማትንም፡እየሰሙ፡እንዳያ
ስተውሉ፡እንዳይመለሱም፡ይቅ
ርም፡እንዳይላቸው፡ኃጢአታቸ
ውም፡እንዳይሰረይላቸው። ኢሳ፡፮

፲፫ ፬፡ ፲[...]ውም፡ ይህን፡ ምሳሌ፡ አ
ላወቃ[...]ምን፡ እንዴትስ፡ ምሳሌ
ዎችን፡[...]ታ ውቃላችሁ፡ ዘሪው፡
፲፬ ቃሉን፡[...]ዘራ፡ ነው። ቃሉም፡ በ
፲፭ ተዘራ[...]መንገድ፡ ዳር፡ እነዚህ
ናቸው፡[...]ሉን፡ ከሰሙ፡ በኋላ፡ ሰይ
ጣን፡ ፈጥኖ፡ ይመጣል፡ በልባቸው
ም፡ የ[...]ውን፡ ቃል፡ ይወስዳል።
፲፮ እንዲሁ[...]በጭንጫ፡ ላይ፡ የተዘ
ሩት፡[...]ሰምተው፡ ለጊዜው።
በደስ[...]ይቀበሉት፡ ናቸው።
፲፯ ግንድ[...]ናቸው፡ እንጂ፡ ሥር፡
የላቸው[...]፡ ስለዚህም፡ ቃል፡ መከ
ራ፡ ወይም፡ ስደት፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ ያን፡
ጊዜው[...]ሰነካከላሉ።
፲፰ በእሾ[...]ይ፡ የተዘሩ፡ እነዚህ፡ ና
ቸው፡[...]የሚሰሙ።
፲፱ የዚህም፡[...]ም፡ አሳብና፡ ባለጠግ
ነት፡ መ[...]ሌሎቹም፡ ነገር፡
መመኘት፡ ገብተው፡ ቃሉን፡ ያንቁ
ታል፡ ያለ፡ ፍሬም፡ ይቀራል። ም፲፰
፳ በመልካም፡ ምድር፡ የተዘሩ፡ እነ
ዚህ፡ ናቸው፡ ቃሉን፡ የሚሰሙ፡ የ
ሚቀበሉትም፡ ፍሬም፡ ያደርጋሉ
እንዱ፡ መ[...]ሌላው፡ ስድሳ፡ ሌላ
፳፩ ውም፡[...]ይላቸው፡ ነበር፡ በወ
ኑ፡ ከእን[...]ወይም፡ ከአልጋ፡ በታ
ች፡ ሊያኖ[...]መብራት፡ ያበራልን፡
በመቅረ[...]ላይ፡ እንዲያስቀምጡ
ት፡ አይደ[...]ምን። ማቴ፡ ፭፡ ፲፭፡ ሉ፡ ፰፡
፳፪ ፲፮፡ ፲፯[...]ገለጥ፡ ተሰውሮ፡ የሚ
ኑር፡ የለምና፡ ሳይገለጥም፡ ተሸፍ
ኖ፡ የሚኖር፡ የለምና። ማቴ፡ ፲፡ ፳
፳፫ ፮፡ ሉ፡ ፲፪፡ ፪። የሚሰማ፡ ጆሮ፡ ያ
፳፬ ለው፡ ይስማ። አላቸውም፡ የምት
ሰሙትን፡ አስተውሉ፡ በምትሰፍ
ሩበት፡ መስፈሪያ፡ ይሰፍሩላችኋ
ል፡ ይጨምሩላችኋልም፡ ማቴ፡ ፯፡
፳፭ ፪። ላለው፡ ይጨምሩለታልና፡ የ
ሌለውን፡ ግን፡ ያንኑ፡ ያለውን፡ ቅሉ
ይወስዱበታል። ማቴ፡ ፲፫፡ ፲፪።
፳፮ አላቸውም፡ የእግዚአብሔር፡ መ
ንግሥት፡ በምድር፡ ላይ፡ ዘርን፡ እን
፳፯ ዲዘራ፡ ሰው፡ እንዲሁ፡ ናት፤ ሌሊትና፡ ቀ
ን፡ ይተኛልም፡ ይነሣልም፡ ዘሩ
ም፡ ይበቅላል፡ እርሱም፡ ሳያውቅ
፳፰ ው፡ ያድጋል፡ ያዕ፡ ፭፡ ፯፡ ምድር፡ ፍሬ፡
ም፡ ከእርስዋ፡ ፍሬ፡ ታመጣለች፡ በ
መጀመሪያ፡ ቡቃያ፡ ኋላም፡ ዛላ፡
ኋላም፡ በዛላው፡ ላይ፡ ፍጹም፡ ስንዴ
፳፱ ደግሞም፡ ከፈራ፡ በኋላ፡ መከር፡ ደ
ርሷልና፡ ያንጊዜ፡ ማጭድ፡ ይሰዳል
፴ አለም፡ የእግዚአብሔር፡ መንግሥ
ት፡ ማንን፡ ትመስላለች፡ ወይስ፡ በ
ና፡ ጥቂት፡ ጊዜ፡ ታዩኛላችሁ፥
፲፯ ም፡ ፲፬፡ ፲፱፥ ደቀ፡ መዛሙርቱም
እርስ፡ በእርሳቸው፡ እርሱ፡ ወደ
አብ፡ እሔዳለሁና፡ ጥቂት፡ ጊዜ፡
አታዩኝም፡ ደግሞም፡ እንደ፡ ገና
ጥቂት፡ ጊዜ፡ ታዩኛላችሁ፡ ማለ
ቱ፡ ይህ፡ ምንድር፡ ነው፡ ተባባሉ፡
፲፰ ይህስ፡ ጥቂት፡ የሚለው፡ ምንድ

ር፡ነው፡ይህን፡የሚናገረውን
፲፱ አላወቅነውም፡አሉ። ኢየሱስ
ም፡ይጠይቁት፡ዘንድ፡እንደ
ወደዱ፡አውቆ፡አላቸው፡ጥቂት
ጊዜ፡አታዩኝም፡ደግሞም፡እን
ደ፡ገና፡ጥቂት፡ጊዜ፡ታዩኛላች
ሁ፡ስለ፡አልሁት፡እርስ፡በርሳ
፳ ችሁ፡ትመራመራላችሁን፨እ
ውነት፡እውነት፡እላችኋለሁ፡እ
ናንተ፡እንድታለቅሱና፡እንድ
ታዝኑ፡ዓለም፡ግን፡ደስ፡ይለዋ
ል፨እናንተም፡ታዝናላችሁ፡ነገ
ር፡ኅዘናችሁ፡ወደ፡ደስታ፡ይ
ለወጣል፨ መዝ፡፻፳፭፡፭። ኤር፡፴፩፡
፳፩ ፲፫፨ሴት፡ቀንዋ፡ደርሶ፡በምጥ፡
ወልድበት፡ጊዜ፡እንድታዝን፡
ልጅ፡ከወለደች፡በኋላ፡ግን፡ስለ
ደስታዋ፡መከራዋን፡አታስበው
ም፡ወንድ፡ልጅ፡በዓለም፡ወሊ
ዶልናልና፨ዘፍ፡፫፡፲፮፡ኢሳ፡፳፮፡፲፯
፳፪ እናንተም፡ዛሬ፡አዘነተኞች፡ና
ችሁ፡ነገር፡ግን፡እንደ፡ገና፡አያች
ኋለሁ፡ልባችሁም፡ደስ፡ይለዋ
ል፡ደስታችሁንም፡ከእናንተ፡የ
ሚወስድባችሁ፡የለም፨ኢሳ፡
፳፫ ፷፭፡፲፡፳፯፡፲፱፨በዚያም፡ጊዜ
እኔን፡አንዳች፡አትጠይቁኝም፡
እውነት፡እውነት፡እላችኋለሁ
አብ፡በእኔ፡ስም፡የምትለምኑት
ን፡ሁሉ፡እንዲሰጣችሁ፨ማር፡፲፩
፳፬ ፳፬፨እስከ፡ዛሬም፡አንዳች፡ስን
ኳ፡በስሜ፡አለመናችሁትም፡
ደስታችሁም፡ይፈጸም፡ዘንድ
ለምኑና፡ትቀበላላችሁም፨
፳፭ ፲፫፡፲፬፨ይህን፡በምሳሌ፡ነገር
ኋችሁ፡ነገር፡ግን፡ስለ፡አብ፡በግ
ልጥ፡እነግራችኋለሁ፡እንጂ፡
በምሳሌ፡የማልነግራችሁ፡ጊ
፳፮ ዜ፡ይመጣል፨በዚያም፡ቀን፡በ
ስሜ፡ትለምናላችሁ፡ስለ፡እና
ንተም፡እኔ፡አብን፡እንድለም
ነው፡የምላችሁ፡አይደለሁም፨
፳፯ እናንተ፡ስለ፡ወደዳችሁኝና፡ከ
እግዚአብሔርም፡እንደ፡ወጣሁ፡
ስለ፡አመናችሁብኝ፡እርሱ፡አ
ብ፡ይወዳችኋልና፨ ፲፬፡፳፩
፳፰ ም፡፲፯፡፰፨ከአብ፡ወጣሁ፡(
ወደ፡ዓለም፡መጣሁ፡ደግሞ፡ዓ
ለምን፡እተዋለሁ፡ወደ፡አብ፡(
፳፱ ም፡እሄዳለሁም፡፲፫፡፫፨ደቀ
መዛሙርቱም፡አሉት፡እነሆ
አሁን፡በግልጥ፡ትናገራለ
ህ፡አንድ፡ስንኳ፡በምሳሌ፡አል
፴ ትናገርህም፨ ቍ፳፭፨ሁሉ
ን፡ታውቃለህ፡እንጂ፡ማንም
ይጠይቅህ፡ዘንድ፡እንዳትሻ፡አ
ወቅን፡ከእግዚአብሔርም፡እን
ደ፡ወጣህ፡በዚህ፡እናምናለን
፴፩ ም፨ ፲፮፡፲፯፨ኢየሱስም፡መለ
ሶ፡አላቸው፡አሁን፡ታምናላች
፴፪ ሁን፨እነሆ፡እናንተ፡ብቻዬን
ተታችሁኝ፡እያንዳንዱ፡በየስ

ፍራው፡የምትበተኑበት፡ጊ
ዜ ። ይደርሳል፡ደርሶዋልም
ነገር፡ግን፡ብቻዬን ። አይደለ
ሁም፡አብ፡ከእኔ፡ጋራ፡ነውና።
፴፫ ዘካ፡፲፫፡፯፡ምዕ፡፲፯፡፳፱ ። በእ
ኔም፡ሰላምን፡ታገኙ፡ዘንድ፡
ይህን፡ነገርኋችሁ፡በዓለም
ም፡መከራ፡ያገኛችኋል፡ነገ
ር፡ግን፡እኔ፡ዓለምን፡አሸንፌ
ዋለሁና፡በርቱ ። ምዕ፡፲፬፡፳፯
ሮሜ፡፰፡፭ቈሮ፡፩፡፳፡፩፡ዮሐ፡፬
፬ ። ምዕራፍ፡፲፯።

ስለ፡አመኑበት፡ሁሉ፡ወደ፡አብ፡እ
ንደ፡ጸለየ፡ስለ፡ሐብና፡ወልድ፡አ
፩ ንድነቱ። ኢየሱስም፡ይህን፡
ነገር፡ተናገሮ፡ዓይኑን፡ወደ
ሰማይ፡አቅንቶ፡አለ፡አባቴ፡ሆ
ይ፡ጊዜው፡ደርሶዋልና፡ልጅ
ህ፡ያከብርህ፡ዘንድ፡ልጅህን፡
አክብረው ። ምዕ፡፲፭፡፴፩ ።
፪ ሥጋ፡በለበሰው፡ሁሉ፡ሳይ፡እን
ደ፡አሰገዛኸው፡ለሰጠኸው፡ሁ
ሉ፡የዘላለም፡ሕይወትን፡ይ
ሰጣቸው፡ዘንድ ። መዝ፡፰፡፮ ።
፫ ማቴ፡፲፩፡፳፯ ። ምዕ፡፯፡፴፯ ። የዘ
ለዓለም፡ሕይወትም፡ይህቺ
ናት፡አንተ፡ብቻ፡እውነተኛ፡አ
ምላክ፡እንደሆንህና፡የላክኸ
ውንም፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ያ
ውቁ፡ዘንድ ። ኤር፡፱፡፳፬፡፩፡ዮ
፬ ሐ፡፫፡፳ ። እኔንም፡አደርገው

ዘንድ፡የሰጠኸኝን፡ሥራ፡ፈጸ(ምሁ)
ሜ፡በምድር፡ሳይ፡አከበርሁህ
፭ ም፡፱፡፴፩ ። አሁንም፡አባቴ ፡
ሆይ፡ዓለም፡ሳይፈጠር፡በአን
ተ፡ዘንድ፡በነበረኝ፡ክብር፡አ(ከ)
ብረኝ ። ሚክ፡፭፡፩፡ፊል፡፪፡፯፡
፮ ከዓለምም፡ለሰጠኸኝ፡ሰዎች፡
ስምህን፡ገለጽሁ፡የአንተ፡ም(ነ)
ስለሆኑ፡ለእኔ፡ሰጠሃቸው(ም)
ቃልህንም፡ጠበቁ ። ም፡፲፫፡፲(...)
፯ የሰጠኸኝም፡ሁሉ፡ከአንተ፡(ዘ)
ንድ፡እንደሆነ፡አሁን፡አወቁ
፰ የሰጠኸኝን፡ቃል፡ሰጥቻቸዋ(ለ)
ሁና፡እነርሳቸውም፡ተቀብለ(ው)
ው፡እኔ፡ካንተ፡ዘንድ፡እንደ፡(መ)
፱ ጣሁ፡በእውነት፡አወቁ። አን(ተ)
ም፡እንዲ፡ላክኸኝ፡አመኑ። እ(ኔ)
ም፡ስለ፡እነርሱ፡እለምናለሁ
ስለ፡ዓለምም፡አልለምንህ(ም)
ም፡ስለ፡እነዚያ፡ስለ፡ሰጠኸኝ
ነው፡እንዲ፡የአንተ፡ናቸውና
፲ ም፡፯፡፴፯፡፴፰ ። የእኔ፡የሆነ
ሁሉ፡የአንተ፡ነው፡የአንተ፡ም
ሁሉ፡የእኔ፡ነው፡እኔም፡በእነ
ርሳቸው፡ከብሬያለሁ። ምዕ፡፲(...)
፲፩ ፲፭ ። እኔም፡ደግሞ፡በዓለም፡
አልኖርም፡እነርሳቸው፡ግን፡
በዓለም፡ናቸው፡እኔም፡ወደ፡
አንተ፡እመጣለሁ፡ቅዱስ፡አባ
ት፡ሆይ፡እነዚህን፡የሰጠኸኝን
እንደኛ፡አንድ፡ይሆኑ፡ዘንድ፡

በስምህ፡ጠብቃቸው፡፲፡፴

፲፪ እኔ፡በዓለም፡ከእነርሳቸው፡ጋራ፡ሳለሁ፡በስምህ፡አጠብቃቸው፡ነበርሁ፡እነዚህን፡የሰጠኸኝን፡ፈጽሜ፡ጠበቅኋቸው፡ከእነርሳቸውም፡ከአንዱ፡ከጥፋት፡ልጅ፡በቀር፡አንዱ፡ስንኳ፡የጠፋ፡የለም፡የተጻፈው፡ይፈጸም፡ዘንድ።

፲፫ አሁን፡ግን፡ወደ፡አንተ፡እመጣለሁ፡ደስታዬም፡በእነርሳቸው፡ይፈጸም፡ዘንድ፡ይህን፡በዓለም፡እናገራለሁ። ም፡፲፭፡፲፩

፲፬ እኔም፡ቃልህን፡ሰጠኋቸው፡እኔም፡ከዓለም፡እንደ፡አይደለሁ፡እርሳቸውም፡ከዓለም፡አይደሉምና፡ዓለም፡ጸላቸው።

፲፭ ደግሞ፡ከክፉ፡እንድትጠብቃቸው፡እንጂ፡ከዓለም፡ታወጣቸው፡ዘንድ፡አልለምንህም። ፪፡ተሰ፡፫፡፫

፲፮ እኔም፡ከዓለም፡እንደ፡አይደለሁ፡ከዓለም፡አይደሉም።

፲፯ በእውነትህ፡ቀድሳቸው፡ቃልህ፡እውነት፡ነውና፡ም፡፰፡፴፪

፲፰ አንተ፡እኔን፡ወደ፡ዓለም፡እንደ፡ላክኸኝ፡እኔም፡ደግሞ፡ወደ፡ዓለም፡ላክኋቸው፡ም

፲፱ ፳፡፳፩ በእውነት፡ም፡የተቀደሱ፡ይሆኑ፡ዘንድ፡ስለ፡እነርሳቸው፡ራሴን፡እቀድሳለሁ። ዕብ፡፲

፳ ፲ ደግሞ፡በቃላቸው፡ስለሚያምኑብኝ፡ሁሉ፡እንጂ፡ስለ፡እነዚህ፡ብቻ፡የምለምን፡

፳፩ አይደለሁም። ሁሉም፡አንድ፡እንዲሆኑ፡አንተ፡አባት፡በእኔ፡እንዳለህ፡እኔም፡እንደ፡ሁሉ፡በአንተ፡እነርሳቸውም፡በእኛ፡አንድ፡ይሆኑ፡ዘንድ፡አንተ፡ም፡እንደ፡ላክኸኝ፡ዓለም፡ያምን፡ዘንድ፡ነው።

፳፪ ገላ፡፫፡፳፰ እኛም፡አንድ፡እንደ፡ሆንን፡እነርሳቸው፡አንድ፡ይሆኑ፡ዘንድ፡እኔ፡የሰጠኸኝን፡ክብር፡ሰጠኋቸው። የሐዋ፡፬፡፴፪

፳፫ እኔ፡በእርሳቸው፡አንተም፡በእኔ፡እነርሳቸውም፡በአንድ፡ፍጹሞችን፡ይሆኑ፡ዘንድ፡አንተም፡እኔን፡እንደ፡ላክኸኝና፡እኔን፡እንደ፡ወደድኸኝ፡እነርሳቸውን፡እንደ፡ወደድኻቸው፡ዓለም፡ያውቅ፡ዘንድ።

፳፬ ፩፡ቆሮ፡፲፭፡፲፯ አባት፡ሆይ፡እነዚህ፡የሰጠኸኝ፡እኔ፡ወደ፡አለሁበት፡ስፍራ፡እርሳቸው፡ደግሞ፡ከእኔ፡ጋራ፡ይኖሩ፡ዘንድ፡የሰጠኸኝን፡ክብር፡ያዩ፡ዘንድ፡እፈቅዳለሁ፡ዓለም፡ሳይፈጠር፡ወደድኸኛልና፡ም፡፲፪፡፳፮

፳፭ ጻድቅ፡አባት፡ሆይ፡ዓለም፡አላወቀህም፡እኔ፡ግን፡አወቅሁህ፡እነዚህም፡አንተ፡እንደ፡ላክኸኝ

፳፮ አውቀዋል። ስምህንም፡አስታወቅኋቸው፡ደግሞም፡አስታውቃቸዋለሁ፡የወደድኸኝ፡ፍቅር፡በእነርሳቸው፡ይሆን፡ዘን

ድ፡ እኔም፡ በእነርሳቸው።

ምዕራፍ ፲፰።

ኢየሱስ፡ ወደ፡ አትክልት፡ ቦታ፡ ይሁዳ፡ እንደ፡ አስያዘው፡ ጴጥሮስ፡ የሊቀ፡ ካህናቱን፡ አገልጋይ፡ በሰይፍ፡ እንደ፡ መታው፡ ጌታን፡ እንደ፡ ካደው፡ ጲላጦስ፡ ኢየሱስን፡ እንደ፡ መረመረው።

፩ ኢየሱስም፡ ይህንን፡ ነገር፡ ተናግሮ፡ አትክልት፡ ወደ፡ አለበት፡ ስፍራ ወደ፡ ቄድሮስ፡ ወንዝ፡ ማዶ፡ ወጣ ወደ፡ እርስዋም፡ ከደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ጋራ፡ ገባ፤ ማቴ፡ ፳፮፡ ፴፮፡ ፪ሳሙ፡ ፲፭፡ ፳፫፡ ማቴ፡ ፳፮፡ ፴፮፡ ፵፯፡ ማር፡ ፲፬፡ ፴፪፡ ፵፫፡ ሉቃ፡ ፳፪፡ ፴፱፡ ፵፯፤

፪ አሳልፎ፡ የሰጠው፡ ይሁዳም፡ ያንን፡ ስፍራ፡ ያውቀው፡ ነበር፤ ኢየሱስ፡ ከደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ጋራ፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ ወደዚያ፡ ይሔድ፡ ነበርና፤ ሉቃ፡ ፳፩፡ ፴፯፤

፫ ይሁዳም፡ ከካህናት፡ አለቆችና ከፈሪሳውያን፡ ጭፍራም፡ ሎሌዎችም፡ ተቀብሎ፡ ፋኖስና፡ ችቦ፡ ፋና - ጋሻና፡ ጦርም፡ ይዞ፡ ወደዚያ = መጣ፤

፬ ኢየሱስም፡ የሚመጣበትን፡ ሁሉ፡ ባወቀ፡ ጊዜ፡ ወጥቶ፡ ማንን፡ ትሻላችሁ፡

፭ አላቸው። ምሥ፡ ፲፱፡ ፳፭፤ እነርሱም፡ መልሰው፡ የናዝሬቱ፡ ኢየሱስን፡ አሉት፡ ኢየሱስም፡ እኔ፡ ነኝ፡ አላቸው፡ ያስያዘው፡ ይሁዳም ከእነርሳቸው፡ ጋራ፡ ቆሞ፡ ነበር፤ ፲፫፡ ፲፩፤

፮ እኔ፡ ነኝ፡ ባላቸውም፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ኋላቸው፡ አፈገፈጉ፡ በምድር፡ ላይም፡ ወደቁ።

፯ ደግሞም፡ ማንን፡ ትሻላችሁ፡ ብሎ፡ ጠየቃቸው፡ እነርሳቸውም፡ የናዝሬቱን፡ ኢየሱስን፡ አሉት፤

፰ ኢየሱስም፡ መልሶ፡ እኔ፡ ነኝ፡ አልኋችሁ፡ እኔንም፡ ትሹ፡ እንደ ሆነ፡ እነዚያን፡ ተዉዋቸው፡ ይሂዱ፤

፱ ይኸውም፡ ከእነርሳቸው፡ አንድ፡ ስንኳ፡ አልጠፋም፡ ያለው፡ ቃሉ፡ ይፈጸም፡ ዘንድ፡ ነው፤ ፲፯፡ ፲፪፤

፲ ስምዖን፡ ጴጥሮስም፡ ሰይፍ፡ ነበረውና፡ ሰይፉን፡ መዞ፡ የካህናቱን፡ አለቃ፡ ሎሌ፡ መታው፡ ቀኝ፡ ጆሮውንም፡ ቈረጠው፡ የሎሌውም፡ ስም፡ ማልኮስ፡ ነበር።

፲፩ ኢየሱስም፡ ጴጥሮስን፡ ሰይፍህን፡ ወደ፡ አፎቱ፡ ክተተው፡ አባቴ፡ የሰጠኝን፡ ጽዋ፡ ሳልጠጣው፡ ነውን፡ አለው፤ ማቴ፡ ፳፡ ፳፪፡ ማቴ፡ ፳፮፡ ፴፱፡ ፵፪፡ ማር፡ ፲፬፡ ፴፮፡ ሉቃ፡ ፳፪፡ ፵፪፤

፲፪ ያን፡ ጊዜም፡ ጭፍሮችና፡ የሻለቃው፡ የአይሁድም፡ ሎሌዎች፡ ኢየሱስን፡ ይዘው፡ አሰሩትና

፲፫ አስቀድመው፡ ወደ፡ ሐና፡ አመጡት፡ በዚያ፡ ዓመት፡ የካህናት፡ አለቃ፡ ለነበረው፡ ለቀያፋ፡

፲፬ አማት፡ ነበርና፤ ቀያፋም፡ ስለ

ሕዝቡ፡ሁሉ፡አንድ፡ሰው፡ቢሞት፡ይሻል፡ብሎ፡አይሁድን፡የመከራቸው፡ነው። ስምዖን፡ጴጥሮስም፡ከሌላው፡ደቀ፡መዝሙር፡ጋራ፡ኢየሱስን፡ተከተለው፤ ያም፡ደቀ፡መዝሙር፡በካህናት፡አለቃ፡ዘንድ፡የታወቀ፡ስለ ነበረ፡ከኢየሱስ፡ጋራ፡ወደ፡ካህናት፡አለቃ፡ቤት፡ገባ። ጴጥሮስ ግን፡በውጭ፡በበር፡ቆሞ፡ነበረ፤ በካህናቱም፡አለቃ፡ዘንድ፡የታወቀ፡የነበረው፡ሌላው፡ደቀ፡መዝሙር፡ወጥቶ፡ለበረኛይቱ፡ነገራትና፡ጴጥሮስን፡አስገባው። በረኛዪቱም፡ሴት፡ጴጥሮስን፡አንተም፡ደግሞ፡የዚያ፡ሰውዬ፡ደቀ፡መዛሙርት ወገን፡ነህን፡አለችው፡እርሱም፡አይደለሁም፡አላት። ሎሌዎችና፡ጭፍሮችም፡ብዙ፡ብርድ፡ስለ፡ነበረ፡እሳት፡አንድደው፡እየሞቁ፡ቆመው፡ይሞቁ፡ነበሩ፡ጴጥሮስም፡ከእነርሳቸው፡ጋራ፡ቆሞ፡ይሞቅ፡ነበር። የካህናቱ፡አለቃ ግን፡ኢየሱስን፡ስለ ደቀ፡መዛሙርቱና፡ስለ፡ትምህርቱ፡ጠየቀው። ኢየሱስም፡መለሰ፡አለው፡እኔ ለዓለም፡በግልጥ፡ተናገርሁ፤ አይሁድም፡ሁሉ፡በሚሰበሰቡበት፡በመስጊድና፡በመቅደስና፡ዘወትር፡አስተማርሁ፡በሥውርም፡የተናገርሁት፡አንድ ስንኳ፡የለም። ፯፡፳፯፡፯፡ኢሳ፡፵፭፡፲፱።

፳፩ ስለምን፡እኔን፡ትጠይቀኛለህ፡ነገሬን፡የሰሙትን እነዚያን፡ጠይቃቸው፡እነሆ፡እርሱ፡የነገርኋቸውን፡ያውቃሉ።

፳፪ ይህንንም፡በተናገረ፡ጊዜ፡በዚያ፡ቆሞ፡የነበረው፡ከሎሌዎቹ፡አንዱ፡ለካህናት፡አለቃ፡እንዲህ፡ትመልሳለህን፡ብሎ፡ኢየሱስን፡በጥፊ፡መታው። ኢሳ፡፶፡፮፡ሚክ፡፭፡፩።

፳፫ ኢየሱስም፡መለሰ፡ክፉ፡ተናግሬ፡እንደ ሆንሁ፡ስለ፡ክፉው፡መስክርብኝ፡መልካም፡ተናግሬ፡እንደ ሆንሁ፡ግን፡ስለ ምን፡ትመታኛለህ፡አለው። ፩፡ጴጥ፡፪፡፲፰፡፲፱።

፳፬ ሐናም፡እንደ፡ታሠረ፡ወደ፡ካህናት፡አለቃ፡ወደ፡ቀያፋ፡ሰደደው።

፳፭ ስምዖን፡ጴጥሮስም፡ቆሞ፡እሳት፡ሲሞቅ፡አንተ ስ፡ደግሞ፡ከደቀ፡መዛሙርቱ፡ወገን፡አይደለህምን፡አሉት፡እርሱም፡እኔ፡አይደለሁም፡ብሎ፡ካደ። ቍ፡፲፰።

፳፮ ጴጥሮስም፡ጆሮውን፡የቈረጠውን፡ዘመድ፡ከካህናት፡አለቃ፡ሎሌዎች፡አንዱ፡በአትክልት፡ከእርሱ፡ጋራ፡ሳለህ፡እኔ፡አላየሁህምን፤

፳፯ አለው። ጴጥሮስም፡እንደ፡ገና፡ካደ፡በዚያ፡ጊዜ፡ዶሮ፡ጮኸ። ማቴ፡፳፮፡፸፬፡፸፭፡ማር፡፲፬

፳፰ ፳፡፳፮፡ ሉ፡ ፳፫ ፩፡ ፳፡ ፳ ፳፰፥
ም፡ ከቀያፋ፡ ወደ፡ ፍርድ፡ ሸንጎ
ወሰዱት፡ አይሁድ፡ ግን፡ ማለዳ፡ ስ
ለ፡ ነበረ፡ ፋሲካን፡ ሳይበሉ፡ እን
ዳይረክሱ፡ ወደ፡ ፍርድ፡ ሸንጎ፡
፳፱ አልገቡም። ጲላጦስም፡ ወደ፡
ውጭ፡ ወደ፡ እነርሱ፡ ወጥ
ቶ፡ ወደ፡ እኔ፡ ባመጣችሁት፡ በ
ዚህ፡ ሰው፡ ምን፡ የክስ፡ ነገር፡ ት
ናገራላችሁ፡ አላቸው። እነር
፴ ሱም፡ መልሰው፡ ክፉ፡ አድ
ራጊ፡ ባይሆን፡ ወደ፡ አንተ፡ አ
ሳልፈን፡ ባልሰጠነውም፡ ነበር
፴፩ አሉት። ጲላጦስም፡ እናንተ፡
ወስዳችሁ፡ እንደ፡ ሕጋችሁ፡ ፍ
ረዱበት፡ አላቸው፡ አይሁድም
እኛስ፡ ማንንም፡ እንገድል፡ ዘን
ድ፡ አይገባንም፡ አሉት። ፲፱
፴፪ ፳፡ ፳፡ ኢየሱስ፡ በማናቸው፡ ሞ
ት፡ እንዲሞት፡ ሲያመለክት፡ የ
ተናገረው፡ ቃል፡ ይፈጸም፡ ዘን
ድ፦ም፡ ፲፪፡ ፴፪ ፴፫፡ ማቴ፡ ፳፯፡
፴፫ ፲፱፦ ዳግመኛም፡ ጲላጦስ፡ ወደ
ፍርድ፡ ሸንጎ፡ ገባና፡ ኢየሱስን፡
ጠርቶ፡ የአይሁድ፡ ንጉሥ፡ አንተ
፴፬ ነህን፡ አለው። ኢየሱስም፡ መ
ልሶ፡ አንተ፡ ይህንን፡ የምትናገ
ረው፡ ከራስህ፡ ነውን፡ ወይስ፡ ስለ
እኔ፡ የነገረህ፡ ሌላ፡ ሰው፡ አለን፡
፴፭ አለው። ጲላጦስም፡ መልሶ፡ እ
ኔ፡ አይሁዳዊ፡ ነኝን፡ ለእኔ፡ አ
ሳልፈው፡ የሰጡህ፡ ወገኖችህና
የካህናት፡ አለቆች፡ አይደሉም
ን፡ ኧረ፡ ምን፡ አድርገሃል፡ አለው።
፴፮ ኢየሱስም፡ መለሰ፡ መንግሥቴ፡
ከዚህ፡ ዓለም፡ አይደለችም፡ መ
ንግሥቴስ፡ ከዚህ፡ ዓለም፡ ብት
ሆን፡ ወደ፡ አይሁድ፡ እንዳልሰ
ጥ፡ ሎሌዎቼ፡ ይዋጉልኝ፡ ነበር፡
አሁን፡ ግን፡ መንግሥቴ፡ ከዚህ፡
፴፯ አይደለችም፡ አለው። ጲላጦስ
ም፡ መሆኑን፡ አንተ፡ ንጉሥ፡ ነህ፡
አለው፡ ኢየሱስም፡ መለሰ፡ እኔ፡ ን
ጉሥ፡ እንደ፡ ሆንሁ፡ አንተ፡ ትላለ
ህ፡ እኔስ፡ በእውነት፡ አመሰክር፡
ዘንድ፡ ስለዚህ፡ ተወለድሁ፡ ስለ
ዚህም፡ ወደ፡ ዓለም፡ መጣሁ፡ ከ
እውነትም፡ የሆነ፡ ሁሉ፡ ቃሌን፡
ይሰማል፡ አለው። ፩፡ ጢሞ፡ ፮፡ ፲፫
፴፰ ም፡ ፳፡ ፴፯፡ ፴፮ ጲላጦስም፡ እ
ውነት፡ ምንድር፡ ነው፡ አለው፡ ይ
ህንንም፡ ብሎ፡ ደግሞ፡ ወደ፡ አ
ይሁድ፡ መጣና፡ አላቸው፡ እኔ፡ አ
ንድ፡ ስንኳ፡ በደል፡ አላገኘሁበ
፴፱ ትም። ሉ፡ ፳፫፡ ፬፡ ፲፬ ነገር፡ ግን፡
በየፋሲካው፡ ለእናንተ፡ አንድ፡
እሥር፡ እፈታላችሁ፡ ዘንድ፡ ል
ማድ፡ አላችሁ፡ እንግዲህ፡ የአይ
ሁድን፡ ንጉሥ፡ እፈታላችሁ፡
ዘንድ፡ ትወዳላችሁን። ማቴ፡ ፳
፵ ፯፡ ፲፰ በዚያም፡ ጊዜ፡ በርባንን
ነው፡ እንጂ፡ ይህንን፡ አይደለም፡

እያሉ፡ጮሁ፡በርባንም፡ወን በዴ፡የነበረው፡ነው።የሐዋ፡፫ ፲፬።

ምዕራፍ፡፲፱።

ጲላጦስ፡እንደ፡ገረፈውና፡የእ ሾህ፡ዘውድ፡እንደ፡ደፋበት፡እንደ ሰቀሉት፡ልብሱን፡እንደ፡ተካፈ ሉ፤እናቱን፡ለሚወደው፡ደቀ፡ መዝሙር፡አደራ፡እንደ፡አለ፤መ ጻጻ፡እንደ፡አጠጡትና፤እንደ፡ሞ ተ፤አብረዉ፡ተ፤የተሰቀሉትን ጭናቸውን፤እንደ፡ሰበሩ፤ጐድ ኑ፡በጦር፤እንደ፡ተወጋ፤ዮሴፍና ኒቆዲሞስ፡እንደ፡ቀበሩት፤

፩ ከዚህም፡በኋላ፡ጲላጦስ፡ኢየሱ ፪ ን፡ወስዶ፡ገረፈው፤ጭፍሮችም የእሾህ፡አክሊል፡ጐንጉኑ፡ በራሱ፡ላይ፡ደፉበት፡ቀይ፡ልብ ፫ ስም፡አለበሱት፥እየመጡም የአይሁድ፡ንጉሥ፡ሆይ፡ሰላም ይሁንልህ፡አሉት፡በጥፊም፡ይ ፬ መቱት፡ነበሩ፥ጲላጦስም፡እን ደ፡ገና፡ወደ፡ውጭ፡ወጥቶ፡እንዲ ተ፡በደል፡ስንኳ፡እንዳላገኘሁ በት፡ታውቁ፡ዘንድ፡እነሆ፡ይህን ሰው፡ወደ፡ውጭ፡አወጣላችኋ ፭ ለሁ፡አላቸው፥ኢየሱስም፡የእ ሾህ፡አክሊል፡እንደ፡ደፉና፡ቀ ይ፡ልብስም፡እንደ፡ለበሰ፡ወደ፡ ውጭ፡ወጣ፡ጲላጦስም፡ያ፡ሰው፡ እነሆ፡አላቸው፥መዝ፡፳፪፡፮፡ኢ ፮ ሳ፡፶፫፡፫፥የካህናት፡አለቆችና ሎሌዎቹም፡ባዩ፡ጊዜ፡ስቀለ ው፡ስቀለው፡እያሉ፡ጮሁ፡ጲላ ጦስም፡እናንተው፡ራሳችሁ፡ ወስዳችሁ፡ስቀሉት፡እንጂ፡እ ኔስ፡በደል፡አላገኘሁበትም፡አላ ፯ ቸው፥አይሁድም፡መልሰው፡ ለእኛ፡ሕግ፡አለን፡እንደ፡ሕጋች ንም፡ሞት፡ይገባዋል፡እርሱ ራሱን፡የእግዚአብሔር፡ልጅ አድርጎዋልና፡አሉት፥ዘሌዋ፡ ፰ ፳፬፡፲፭፡፲፮፥ጲላጦስም፡ይህን ነገር፡በሰማ፡ጊዜ፡እጅግ፡ፈራ፡ ፱ እንደ፡ገናም፡ወደ፡ፍርድ፡ሸንጎ ግቢቱ፡ኢየሱስን፡አንተ፡ከወዴ ት፡ነህ፡አለው፡ኢየሱስ፡ግን፡አ ንድች፡ስንኳ፡አልመለሰለትም ፲ ማቴ፡፳፯፡፲፬፥ጲላጦስም፡አት ነጋገረኝምን፡አሰቀልህና፡አት ውህ፡ዘንድ፡እንዲቻለኝ፡አታው ፲፩ ቅምን፡አለው፥ኢየሱስም፡መል ሶ፡ከላይ፡ባይሰጥህ፡በእኔ፡ላይ ምንም፡ባልቻልህም፡ነበር፡ስ ለዚህም፡ለአንተ፡አሳልፎ፡የሰ ጠኝ፡በደሉ፡እጅግ፡ነው፡አለው። ፲፪ ከዚህም፡በኋላ፡ጲላጦስ፡ይተ ወው፡ዘንድ፡ፈለገ፡አይሁድ፡ግ ን፡ይህንስ፡ብትተው፡የቄሣር ወዳጅ፡አይደለህም፡ራሱን፡ንጉ ሥ፡የሚያደርግ፡ሁሉ፡እርሱ፡የ ቄሣር፡ጠላት፡ነውና፡እያሉ፡ጮ ፲፫ ሁ፥ጲላጦስም፡ይህን፡ነገር፡በ

ሰማ፡ ጊዜ፡ ኢየሱስን፡ ወደ፡ ው
ጭ፡ አወጣው፡ እርሱም፡ በአብ
ራይስጥ፡ ገበታ፡ በሚሉት፡ በ
ጸፍጸፍ፡ ስፍራ፡ በወንበር፡ ተ
፲፬ ቀመጠ። ጊዜውም፡ የፋሲካ፡
ዋዜማ፡ የመሰናዶት፡ ቀን፡ ስድ
ስት፡ ሰዓት፡ ያህል፡ ነበረ፤ አይሁ
ድም፡ እነሆ፡ ንጉሣችሁ፡ አላቸ
፲፭ ው። እነርሱ ግን፡ አስወ
ግደው፡ ስቀለው፡ እያሉ፡ ጮ
ሁ፡ ጲላጦስም፡ ንጉሣችሁን
ልሰቀለውን፡ አላቸው፡ የካህ
ናቱ፡ አለቆችም፡ መልሰው፡ ከ
ቄሣር፡ በቀር፡ ንጉሥ፡ የለንም
፲፮ አሉት። በዚያም፡ ጊዜ፡ ይሰቀ
ል ዘንድ፡ አሳልፎ፡ ሰጣቸው፡
ኢየሱስንም፡ ተቀብለው፡ ይዘ
ውት፡ ሔዱ። ማቴ፡ ፳፯፡ ፴፩፡ ፴
ማር፲፭፡ ፳፡ ፳፪፤ ሉ፡ ፳፫፡ ፳፮፡ ፴
፲፯ ፫። መስቀሉንም፡ ተሸክሞ፡ የ
ራስ፡ ቅል፡ ወደሚሉት፡ በዕብ
ራይስጥም፡ ጎልጎታ፡ ወደሚ
ባል፡ ስፍራ፡ ወጣ። ዘፍ፡ ፳፪፡ ፮።
፲፰ በዚያም፡ ሰቀሉት፡ ከእርሱም
ጋራ፡ ሌሎችን፡ ሁለት፡ አንዱን፡
በዚህ፡ አንዱን፡ በዚያ፡ ሰቀሉ፤
ኢየሱስን፡ በመካከላቸው።
፲፱ ማር፡ ፲፭፡ ፳፮። ጲላጦስም፡ ጽ
ሕፈቱን፡ ጽፎ፡ በመስቀሉ፡ ላይ
ለጠፈ፡ ጽሕፈቱም፡ የአይሁ
ድ፡ ንጉሥ፡ የናዝሬቱ ኢየሱስ

፳ ይህ፡ ነው፡ የሚል፡ ነበር። ኢየሱ
ስም፡ የተሰቀለበት፡ ስፍራ፡ ለ
ከተማ፡ ቅርብ፡ ነበረ፤ ይህን፡ ጽ
ሕፈት፡ ከአይሁድ፡ ብዙዎች፡ አ
ነበቡት፡ የተጻፈውም፡ በዕብራ
ይስጥና፡ በሮማይስጥ፡ በፅርዕ
፳፩ ም፡ ቋንቋ፡ ነበረ። የአይ
ሁድም፡ የካህናት፡ አለቆች፡ ጲ
ላጦስን፡ እርሱ፡ ራሱ፡ የአይሁ
ድ፡ ንጉሥ፡ ነኝ፡ እንዳለ፡ እንጂ፡
የአይሁድ፡ ንጉሥ፡ እንደሆነ፡ አ
፳፪ ትጻፍ፡ አሉት። ጲላጦስም፡ መ
ልሶ፡ የጻፍሁትን፡ ጻፍሁ፡ አላ
፳፫ ቸው። ጭፍሮች፡ ኢየሱስ
ን፡ በሰቀሉት፡ ጊዜ፡ ልብሶቹን፡
ወስደው፡ ለእያንዳንዱ፡ አራት
ክፍል፡ አደረጉት፡ ቀሚሱን፡
ም፡ እንዲሁ፡ ቀሚሱም፡ ከላይ
ጀምሮ፡ የተሠራ፡ ሥረ፡ ወፁ፡
ነበረ፡ እንጂ፡ የተሰፋ፡ አልነበ
፳፬ ረም። መዝ፡ ፳፪፡ ፲፰። እርስ፡ በ
ርሳቸውም፡ ለደረሰው፡ እንዲ
ደርስ፡ ዕጣ፡ እንጣጣልበት፡ እን
ጂ፡ አንቀደደው፡ ተባባሉ፡ ል
ብሶቼን፡ እርስ፡ በርሳቸው፡ ተ
ካፈሉ፡ በቀሚሴም፡ ላይ፡ ዕጣ
ተጣጣሉ፡ ተብሎ፡ የተጻፈው
ቃል፡ ይፈጸም፡ ዘንድ፡ ጭፍሮ
፳፭ ችም፡ እንዲህ፡ አደረጉ። ከኢየ
ሱስም፡ መስቀል፡ አጠገብ፡ እና
ቱ፡ የእናቱም፡ እኅት፡ የቀለዮ

ጳም፡ ሚስት፡ ማርያም፡ የመግ
ደላይቱም፡ ማርያም፡ ቆመው
፳፮ ነበሩ፡፡ ኢየሱስም፡ እናቱንና፡ ይ
ወደው፡ የነበረውን፡ ደቀ፡ መዝ
ሙሩን፡ በአጠገቡ፡ ቆመው፡
ባየ፡ ጊዜ፡ እናቱን፡ አንቺ፡ ሴት፡፡
እነሆ፡ ልጅሽ፡ አላት። ም፡ ፲፫፡ ፳፫
፳፯ ደቀ፡ መዝሙሩንም፡ እናት፡ እ
ነኋት፡ አለው፡ ከዚያችም፡ ሰዓት
ጀምሮ፡ ደቀ፡ መዝሙሩ፡ ወደ፡ ቤ
፳፰ ቱ፡ ወሰደት። ከዚህም፡ በኋላ፡ ኢ
የሱስ፡ ሁሉ፡ እንደ፡ ተፈጸመ፡ አው
ቆ፡ መጽሐፍ፡ ያለው፡ ይፈጸም፡
፳፱ ዘንድ፡ ተጸማሁ፡ አለ። በዚያም
መፃፃ፡ የመላበት፡ ዕቃ፡ ማስሮ፡
ተቀምጦ፡ ነበር፡ እነርሳቸውም
መፃፃውን፡ በሰፍነግ፡ መልተው፡
በስምዕዛ፡ ሰንሰል፡ ዘንግ፡ አኖ
ሩት፡ ወደ፡ አፉም፡ አቀረቡለት
፴ መዝ፡ ፷፰፡ ፳፩። ኢየሱስም፡ መፃ
ፃውን፡ በቀመሰ፡ ጊዜ፡ ተፈጸመ
አለ፡ ራሱንም፡ አዘንበሎ፡ ነፍሱ
፴፩ ን፡ ሰጠ። ዕብ፡ ፭፡ ፱። አይሁድ፡ ግ
ን፡ ዓርብ፡ ማታ፡ ነበረና፡ ሰንበ
ት፡ ስለሆነ፡ እነዚያ፡ ሥጋዎች፡
በመስቀል፡ እንዳያድሩ፡ ጭን፡
ጭናቸውን፡ ሰብረው፡ ያወርድ
ዋቸው፡ ዘንድ፡ ጲላጦስን፡ ለመ
ኑት። ዘፀ፡ ፴፬፡ ፳፭። ዘዳግ፡ ፳፩፡ ፳
፴፪ ፫። ጭፍሮችም፡ መጥተው፡
የፊተኛውን፡ የሁለተኛውን
ም፡ ከእርሱ፡ ጋራ፡ የተሰቀሉት
፴፫ ን፡ ጭንጭናቸውን፡ ሰበሩ። ወ
ደ፡ ኢየሱስ፡ በመጡ፡ ጊዜ፡ ግን፡ እ
ርሱ፡ ፈጽሞ፡ እንደ፡ ሞተ፡ አይተ
፴፬ ው፡ ጭኑን፡ አልሰበሩም። ነገር
ግን፡ ከጭፍሮች፡ አንዱ፡ ጐድኑ
ን፡ በጦር፡ ወጋውና፡ በዚያም፡ ጊ
ዜ፡ ፈጥኖ፡ ደምና፡ ውሀ፡ ወጣ።
፴፭ ያየውም፡ መስከረ፡ ምስክር
ነቱም፡ እውነት፡ ነው፡ እርሱም፡ እ
ናንተ፡ ታምኑ፡ ዘንድ፡ እውነት፡
፴፮ እንደ፡ ተናገረ፡ ያውቃል። ይህ
ም፡ የሆነ፡ መጽሐፍ፡ አፅንቱን፡
ከእርሱ፡ አትሰበሩ፡ ያለው፡ ቃል
ይፈጸም፡ ዘንድ፡ ነውና፡ ዘፀ፡ ፲፪፡
፴፯ ፵፮። ዳግመኛም፡ ሌላው፡ መጽ
ሐፍ፡ የወጉትን፡ ያዩታል፡ ይላል
፴፰ ዘካ፡ ፲፪፡ ፲፡ ራእ፡ ፩፡ ፯። ከዚህም
በኋላ፡ አይሁድን፡ ስለ፡ ፈሩ፡ በ
ሥውር፡ የኢየሱስ፡ ደቀ፡ መዝሙ
ር፡ የነበረው፡ የአርማትያሱ፡
ዮሴፍ፡ የኢየሱስን፡ ሥጋ፡ ይወ
ስድ፡ ዘንድ፡ መጥቶ፡ ጲላጦስን
ለመነው፡ ጲላጦስም፡ ፈቀደለ
ትና፡ ያን፡ ጊዜ፡ ሔዶ፡ የኢየሱስን
ሥጋ፡ ወሰደ፡ ማቴ፡ ፳፯፡ ፶፯፡ ፷
፩፡ ማር፡ ፲፭፡ ፵፪፡ ፵፯፡ ሉ፡ ፳፫፡
፴፱ ፶፡ ፶፮። አስቀድሞ፡ በሌሊት፡
ወደ፡ ኢየሱስ፡ መጥቶ፡ የነበረው
ኒቆዲሞስ፡ መጥቶ፡ የሚቀበ
ርበቶን፡ መቶ፡ ነጥር፡ የሚያህ

ል፡የከርቤና፡የሬት፡ቅልቅል፡ሽቱ፡አመጣ፥ም፡፻፡ ሚቴ ፎ፡፲፰፥ ፵ የኢየሱስንም፡ሥጋ፡ወሰደው፡እንደ፡አይሁድ፡አገናዝ፡ልማድ፡ከሽቱ፡ጋራ፡በበፍታ፡ከፈኑት፥ ፵፩ በተሰቀለበትም ስፍራ፡አጠገብ፡አትክልት፡ነበረ፡በአትክልቱም፡ውስጥ፡ማንም፡ያልተቀበረበት፡አዲስ፡መቃብር፡ነበረ፥ ኢሳ፡፶፫፡፱፡ ፵፪ የአይሁድም፡የመሰናዶት፡ቀን፡የሰንበት፡ዋዜማ፡ነበረና፡መቃብሩ፡ቅርብ፡ስለሆነ፡ኢየሱስን በዚያ፡ቀበሩት።

ምዕራፍ፡፳።

የመግደላዊቱ፡ማርያም፡ወደ፡መቃብሩ፡እንደ፡ሔደችና፡መላእክት፡እንደ፡ተገለጡላት፤ ጌታ፡እንደ፡ታየችና፡መነሣቱን ለሐዋርያት፡እንደ፡ነገረች፤ እጁንና፡እግሩን፡እንዳሳያቸው፡ቶማስ፡እንደ፡ተጠራጠረ።

፩ ከሳምንቱም፡በመጀመሪያው ቀን፡ማለዳ፡ገና፡ጨለማ፡ሳለ፡የመግደላዊቱ፡ማርያም፡ወደ፡መቃብር፡መጣች፡ድንጊያውንም፡ከመቃብር፡ተፈንቅሎ አየችው፥ማቴ፡፳፰፡፩፡፲፩፡ ማር፡ ፲፮፡፩፡ ሉቃ፡፳፬፡፩፡ ፲፪፥ ፪ እርስዋም፡ፈጥና፡ወደ፡ስምዖን፡ጴጥሮስና፡ኢየሱስ፡ ይወደው፡ወደ፡ነበረው፡ወደ፡ሁለተኛው፡ደቀ፡መዝሙር፡መጥታ ጌታችንን፡ከመቃብር፡ወስደውታል፡ወዴትም፡እንደ፡አኖሩት፡አላውቅም፡አለቻቸው። ዮሐ፡፲፫፡፳፫፥ ፫ ጴጥሮስና፡ሁለተኛው ደቀ፡መዝሙር፡ወጥተው፡ወደ መቃብር፡ሔዱ። ፬ ሁለቱ፡በአንድነት፡ሲሮጡ፡ሁለተኛው፡ደቀ፡መዝሙር፡ጴጥሮስን፡ቀድሞት፡ወደ፡መቃብር፡ደረሰ። ፭ አዘቅዝቆም፡ቢመለከት፡ከፈኑን፡አየ፡ነገር፡ግን፡አልገባም። ፮ ስምዖን፡ጴጥሮስም፡ተከትሎት፡መጥቶ፡ወደ፡መቃብር፡ገባና፡ከፈኑን፡በዚያው፡ተቀምጦ፡አየ፤ ፯ በራሱም፡ላይ፡የነበረው፡መጠምጠሚያ፡ለይቶ፡ለብቻው፡ተጠቅልሎ፡ነበረ፡እንጂ፡ከከፈኑ ጋራ፡አልነበረም። ፲፩፡፵፬። ፰ ያን ጊዜም፡አስቀድሞ፡ወደ፡መቃብር፡የመጣው፡ሁለተኛው፡ደቀ፡መዝሙር፡ገባና፡አይቶ፡አመነ። ፱ ከሙታን፡ይነሣ፡ዘንድ፡እንዲገባው፡በመጽሐፍ፡ያለውን፡ገና፡አላወቁምና። መዝ፡፲፮፡፲ ፩ቆሮ፡፲፭፡፬። ፲ ደቀ፡መዝሙርቱም፡ወደ፡ቤታቸው፡ሔዱ። ፲፩ ማርያም፡ግን፡ከመቃብሩ፡በስተውጭ፡ቆማ፡ታለቅስ፡ነበረች

እያለቀሰች ም፡ ወደ፡ መቃብሩ ዝቅ፡ ብላ፡ በጐበኘች፡ ጊዜ።

፲፪ ሁለት፡ መላእክት ም፡ ነጭ፡ ልብስ፡ ለብሰው፡ የኢየሱስ፡ ሥጋ፡ ተቀብሮበት፡ በነበረው፡ እግድ በራስጌ፡ ሁለተኛው፡ በግርጌ፡

፲፫ ተቀምጠው፡ አየቻቸው። እነዚያም መላእክት፡ አንቺ፡ ሴት፡ ምን፡ ያስለቅስሻል፡ አሏዋት። እርስዋም፡ ጌታዬን፡ ወስደውታል፡ ወዴትም፡ እንደ፡ አኖሩት፡ አላውቅ

፲፬ ም፡ አለቻቸው። ይህንም፡ ብላ ወደ፡ ኋላዋ፡ ዘወር፡ ብትል፡ ኢየሱስ፡ እንደ ሆነ፡ አላወቀችም፡ ነ

፲፭ በር። ማቴ፡ ፳፰፡ ፱ ኢየሱስም አንቺ፡ ሴት፡ ለምን፡ ታለቅሻለሽ፡ ማንንስ፡ ትሻለሽ፡ አላት፡ እርስዋም፡ አትክልት፡ ጠባቂ፡ መስሎዋት፣ ነበርና፡ ጌታዬ፡ ሆይ፡ አንተ፡ ወስደኸው፡ እንደ ሆነ፡ ወዴት፡ እንደ፡ አኖርኸው፡ ንገረኝ እኔም፡ ሽቱ፡ እቀባው፡ ዘንድ፡ እወስደዋለሁ፡ አለችው።

፲፮ ኢየሱስም፡ ማርያም፡ አላት፡ እርስዋም፡ ዘወር፡ ብላ፡ በዕብራይስ፡ ቋንቋ፡ ረቡኒ፡ አለችው ትርጓሜውም፡ መምህር፡ ሆይ፡ ማለት፡ ነው። ማር፡ ፲፡ ፶፩፡

፲፯ ኢየሱስም፡ ንና፡ ወደ፡ አባቴ፡ አልወጣሁምና፡ አትንኪኝ፡ ነገር ግን፡ ወደ፡ ወንድሞቼ፡ ሒደሽ፡ ወደ፡ አባቴ፡ አባታችሁም፡ ወደ፡ አምላኬ፡ አምላካችሁም፡ ዓርጋለሁ፡ ብለሽ፡ ንገሪያቸው አላት። ማቴ፡ ፳፰፡ ፱፡ ፲፡ ም፡ ፲፯ ፳፰፡ ዕብ፡ ፬፡ ፲፭፡ ፲፬።

፲፰ የመግደላዊት፡ ማርያምም፡ መጥታ፡ ጌታን፡ እንደ፡ አየችው ና፡ ይህንንም፡ እንደ፡ አላት፡ ለደ

፲፱ ቀ፡ መዛሙርቱ፡ ነገረች። በስምንተኛውም፡ የመጀመሪያ፡ ቀን፡ በመሸ፡ ጊዜ፡ ደቀ፡ መዛሙርቱ፡ አይሁድን፡ ስለ፡ ፈሩ፡ የተሰበሰቡበት፡ ቤት፡ ደጁ፡ ተቈልፎ ሳለ፡ ኢየሱስ፡ መጥና፡ በመካከላቸው፡ ቁሞ፡ ሰላም፡ ለእናንተ ይሁን፡ አላቸው። ማር፡ ፲፮፡ ፲፬፡ ፲፰፡ ሉ፡ ፳፬፡ ፴፮፡ ፩ቆሮ፡ ፲፭፡ ፭፡ ኢሳ፡ ፶፯፡ ፲፱፡ ፶፯፡ ፲፱።

፳ ይህንንም፡ ብሎ፡ እጁንና፡ ጐኑን፡ አሳያቸው። ደቀ፡ መዛሙርቱም፡ ጌታን፡ ባዩት፡ ጊዜ፡ ደስ፡ አላቸው።

፳፩ ዳግመኛም፡ ኢየሱስ፡ ሰላም፡ ለእናንተ፡ ይሁን፡ አብም፡ እንደ ላከኝ፡ እንዲሁ፡ እኔ፡ እልካችኋ

፳፪ ለሁ፡ አላቸው። ይህንንም፡ ብሎ እፍ፡ አለባቸው፡ አላቸውም መንፈስ፡ ቅዱስን፡ ተቀበሉ።

፳፫ ኃጢአታቸውንም፡ ይቅር፡ ያላችኋቸው፡ ይቀርላቸዋል፡ የያዛችሁባቸው፡ ግን፡ ይያዝባ

ቸዋል፤ ፳፬ ከአሥራ፡ሁለቱ፡አንዱ፡ዲዲሞስ፡የሚሉት፡ቶማስ፡ኢየሱስ፡በመጣ፡ጊዜ፡ከእነርሳቸው፡ጋራ፡አልነበረም፨ ማቴ፡፲፡፫ቃ ፳፭ ሌሎቹም፡ደቀ፡መዛሙርት፡ጌታን፡አየነው፡አሉት፡እርሱ፡ግን፡የችንካሩን፡ምልክት፡በእጁ፡ካላየሁ፡ጣቴንም፡ወደ፡ችንካሩ፡ካላገባሁ፡እጄንም፡በጐድኑ፡ካላኖርሁ፡አላምን፤ ፳፮ ም፡አላቸው፨ ም፡፲፬፡፴፬ቃ ከስምንተኛውም፡ቀን፡በኋላ፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡በውሥጥ፡ሳሉ፡ቶማስም፡ከእነርሳቸው፡ጋራ፡ነበር፡ደጁም፡እንደ፡ተቈለፈ፡ኢየሱስ፡መጣና፡በመካከላቸው፡ቁሞ፡ሰላም፡ለእናንተ፡ይሁን፡አ ፳፯ ላቸው፨ ቀ፡፲፱ቃ ከዚህም፡በኋላ፡ቶማስን፡ጣትህን፡ወዲህ፡አምጣና፡እጆቼን፡እይ፡እጅህንም፡አምጣና፡ወደ፡ጐድኔ፡አግባ፡ዳግመኛም፡አመን፡እንጂ፡ተጠራ ፳፰ ጣሪ፡አትሁን፡አለው፨ ቶማስም፡መልሶ፡ጌታዬ፡አምላኬም፡ ፳፱ አለ፤ ም፡፩፡፩ቃ ኢየሱስም፡አለው፡ስለ፡አየኸኝ፡አመንህ፡ብፁዓን፡ናቸው፡ሳያዩ፡የሚያምኑ፡ ፴ ናቸው፨ አለው፨ ፩፡ጴጥ፡፩፡፰ቃ ኢየሱስም፡በደቀ፡መዛሙርቱ፡ፊት፡በዚህ፡መጽሐፍ፡ያልተጻፉ፡ሌሎችን፡ብዙ፡ተአምራቶችን፡አ ፴፩ ደረገ፤ ይህ፡ግን፡የተጻፈው፡እርሱ፡ኢየሱስ፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ክርስቶስ፡እንደ፡ሆነ፡ታምኑ፡ዘንድ፡አምናችሁም፡በስሙ፡የዘለዓለም፡ሕይወትን፡ታገኙ፡ዘንድ፡ነው፨ ፩፡ዮሐ፡፭፡፲፫ቃ

ምዕራፍ፡፳፩፨

በጥብርያዶስ፡ባሕር፡ዳር፡ሲያጠምዱ፡እንደ፡ታያቸውና፡አብሮአቸው፡እንዲበላ፤ ጴጥሮስን፡ሦስት፡ጊዜ፤ መላልሶ፡ተወደኛለህ፤ እያለ፡እንደ፡ጠየቀው፤ በጎቼን፡ጠብቅ፤ እንዲል፤ ስለ፡ጴጥሮስ፡ሞቱ፤ ስለ፡ሚወደው፡ደቀ፡መዝሙር፡ሞቱና፡ሕይወቱ፨

፩ ከዚህም፡በኋላ፡ኢየሱስ፡በጥብርያዶስ፡ባሕር፡አጠገብ፡ለደቀ፡መዛሙርቱ፡እንደ፡ገና፡ተገለጠላቸው፡በእንደዚህም፡ታ ፪ ያቸው፨ ስምዖን፡ጴጥሮስ፡ዲዲሞስ፡የተባለው፡ቶማስ፡የቃና፡ዘገሊላውም፡ናትናኤል፡የዘብዴዎስም፡ልጆች፡ከደቀ፡መዛሙርቱም፡ሁለቱ፡ሌሎች ፫ በአንድነት፡ነበሩ፨ ስምዖን፡ጴጥሮስም፡እኔ፡ዓሣ፡ላጠምድ፡እሄዳለሁ፡አላቸው፡እርሱም፡እኛም፡ከአንተ፡ጋራ፡እንሄዳለን፡አሉት፡ወጥተውም፡ወደ፡ታንኳ፡ገቡ፡በዚያችም፡ሌሊት፡

ምንም፡ አልያዙም። በጸባም
ጊዜ፡ ኢየሱስ፡ በባሕር፡ ዳር፡ ቆ
ሞ፡ ደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ግን፡ ኢ
የሱስ፡ እንደሆነ፡ አላወቁም፤
ም፡ ፳፡ ፲፬፡ ሉ፡ ፳፬፡ ፲፮። ኢየሱ
ስም፡ ልጆቼ፡ አንዳች፡ የሚበላ
አላችሁን፡ አላቸው፡ እነሱም
የለንም፡ አሉት። ሉ፡ ፳፬፡ ፵፩፡
እርሱም፡ በታንኳው፡ በስተቀ
ኝ፡ በኩል፡ መረባችሁን፡ ጣሉ
ና፡ ታገኛላችሁ፡ አላቸው፡ መ
ረባቸውንም፡ በጣሉ፡ ጊዜ፡ ከዓ
ሣው፡ ብዛት፡ የተነሣ፡ ሊስቡ
ት፡ አልቻሉም። ሉ፡ ፭፡ ፮።
ያም፡ ኢየሱስ፡ ይወደው፡ የነበ
ረው፡ ደቀ፡ መዝሙር፡ ጴጥሮ
ስን፡ ጌታችን፡ ነው፡ እኮ፡ አለው፡
ስምዖን፡ ጴጥሮስም፡ ጌታ፡ እን
ደሆነ፡ በሰማ፡ ጊዜ፡ ዕራቁቱን፡
ነበረና፡ ልብሱን፡ ታጥቆ፡ ወደ፡
ባሕር፡ ተወረወረ። ም፡ ፲፫፡ ፳፫
ሌሎቹ፡ ደቀ፡ መዛሙርት፡ ግ
ን፡ ከምድሩ፡ ሁለት፡ መቶ፡ ክን
ድ፡ ያህል፡ ነው፡ እንጂ፡ እጅግ
ም፡ አልራቁም፡ ነበረና፡ ዓሣ፡
የመላበት፡ መረብ፡ እየሳቡ፡ በ
ታንኳ፡ መጡ። ወደ፡ ምድር
ም፡ በወረዱ፡ ጊዜ፡ የተጫረ፡
ፍም፡ ዓሣም፡ በላዩ፡ ሁኖ፡ እን
ጀራም፡ ተሠርቶ፡ አገኙ። ኢየ
ሱስም፡ አሁን፡ ከጸመደችሁት

፲፩ ዓሣ፡ አምጡ፡ አላቸው። ስም
ዖን፡ ጴጥሮስ፡ ወደ፡ ታንኳው፡
ገብቶ፡ መቶ፡ አምሳ፡ ሦስት፡ ታላ
ላቁ፡ ዓሦች፡ መሉቶ፡ የነበረውን
መረብ፡ ወደ፡ ምድር፡ ጐተተው፡
ይህንም፡ ያህል፡ ብዙ፡ ሲሆን፡ መ
፲፪ ረቡ፡ አልተቀደደም። ኢየሱስም
ኑ፡ ምሳችሁን፡ ብሉ፡ አላቸው፡ ከ
ደቀ፡ መዛሙርቱም፡ አንድ፡ ስ
ንኳ፡ አንተ፡ ማነህ፡ ብሎ፡ ይጠይ
ቀው፡ ዘንድ፡ የደፈረ፡ የለም፡ ጌ
ታ፡ መሆኑን፡ አውቀው፡ ነበርና
፲፫ ኢየሱስም፡ መጣና፡ እንጀራው
ን፡ አንሥቶ፡ ሰጣቸው፡ ዓሣው
፲፬ ንም፡ እንዲሁ። ም፡ ፳፡ ፲። ኢየሱ
ስ፡ ከሙታን፡ ከተነሣ፡ በኋላ
ለደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ሲገለጥ፡ ላ
ቸው፡ ይህ፡ ሦስተኛው፡ ነው።
፲፭ ምሳቸውንም፡ ከበሉ፡ በኋላ፡
ኢየሱስ፡ ስምዖን፡ ጴጥሮስን፡
የዮና፡ ልጅ፡ ስምዖን፡ ሆይ፡ ከእ
ነዚህ፡ ይልቅ፡ ትወደኛለህን፡
አለው፡ ኢየሱስም፡ የበግ፡ ግላ
ግልቶቼን፡ ጠብቅ፡ አለው።ም
፲፮ ፩፡ ጴ፡ ፪። ደግሞ፡ ሁለተኛ፡ የዮና
ልጅ፡ ስምዖን፡ ሆይ፡ ትወደኛለ
ህን፡ አለው፡ አዎን፡ አቤቱ፡ እንድ
ወድህም፡ አንተ፡ ታውቃለህ፡ አ
ለው፡ በጎቼንም፡ ጠብቅ፡ አለ
ው። ፩፡ ጴ፡ ፭፡ ፪፡ ፬።
፲፯ ሦስተኛም፡ የዮና፡ ልጅ፡ ስምዖ

ን፡ሆይ፡ትወደኛለህን፡አለው፡
ጴጥሮስም፡ሶስተኛ፡ትወደ
ኛለህን፡ስላለው፡አዘነ፡
አቤቱ፡አንተ፡ሁሉን፡ታውቃለ
ህ፡እንድወድህም፡አንተ፡ታው
ቃለህ፡አለው፡ኢየሱስም፡በጎ
ቼን፡ጠብቅ፡አለው፨ም፡፲፫፡፵
፲፰ ፲፰፨እውነት፡እውነት፡እልሃለሁ
አንተ፡ጕልማሳ፡ሳለህ፡በገዛ፡እ
ጅህ፡ወገብህን፡ታጥቀህ፡ወደ፡እ
ምትወደው፡ትሔድ፡ነበር፡በሸ
መገልህ፡ጊዜ፡ግን፡እጅህን፡ታነ
ሣለህ፡ሌላም፡ያስታጥቅሃል፡
ወደማትወደውም፡ይወስድሃ
፲፱ ል፨በምን፡ሞት፡እግዚአብሔር
ን፡ያመሰግን፡ዘንድ፡እንዲ፡አለ
ው፡ሲያመለክተው፡ይህን፡አለ
ይህነንም፡ተናግሮ፡ተከተለኝ፡
፳ አለው፨ጴጥሮስም፡ዘወር፡ብ
ሎ፡ኢየሱስ፡ይወደው፡የነበረው
ን፡ደቀ፡መዝሙር፡ሲከተለው፡
አየ፨እርሱም፡በራት፡ጊዜ፡በአ
ጠገቡ፡የተቀመጠና፡ጌታዬ፡ሆ
ይ፡አሳልፎ፡የሚሰጥህ፡ማነው፡
ያለው፡ነው፨ም፡፲፫፡፳፫፨
፳፩ ያንጊዜም፡ጴጥሮስ፡እርሱን፡
አይቶ፡ኢየሱስን፡አቤቱ፡ይህስ፡
እንዴት፡ይሆናል፡አለው፨
፳፪ ኢየሱስም፡እስከመጣ፡ድረስ፡
ይቀመጥ፡ዘንድ፡ብወድስ፡ምን
አግዶህ፡አንተ፡ግን፡ተከተለኝ፡
፳፫ አለው፤ስለዚህም፡ያደቀ፡መ
ዝሙር፡እንዳይሞት፡ይህ፡ነገ
ር፡በወንድሞቹ፡ዘንድ፡ወጣ፨ኢ
የሱስግን፡እስከመጣ፡ድረስ፡ይ
ቀመጥ፡ዘንድ፡ብወድ፡ምን፡አግ
ዶህ፡አለ፡እንጂ፡አይሞትም፡አ
፳፬ ላለውም፨
ስለዚህም፡ሥራ፡የመሰከረና
የጻፈውም፡ይህ፡ደቀ፡መዝሙ
ር፡ምስክርነቱም፡እውነት፡
እንደሆነ፡እኛ፡እናውቃለን፨
ም፡፲፱፡፴፭፡ራእ፡፩፡፪፨
፳፭ ኢየሱስም፡ያደረገው፡ሌላ፡እጅ
ግ፡ነገር፡አለ፡ሁሉም፡እያንዳን
ዱ፡ተጽፎ፡ቢሆን፡የተጻፉትን፡
መጻሕፍት፡ዓለም፡ስንኳ፡ባል
ቻላቸውም፡ነበር፡አሜን።

የዮሐንስ፡ወንጌል፡ተፈጸመ
ወስመ፤ጸሐፊሁ፤ሣህሌ፤ሀብ
ተ፡ወልድ፤ዘሀገረ፡ቡልጋ፨

ከኢየሩሳሌም፡ አትውጡ፡ እንደ፡ አላቸው፡ ስለ፡ እስራኤል፡ መንግሥት፡ መመለስ፡ እንደ፡ ጠየቁት፡ ስለ፡ ጌታችን፡ ዕርገት፡ ለጸሎት፡ እንደ፡ ተሰበሰቡ፡ ስለ፡ ማቲያስ፡ መመረጥ።

ምዕራፍ፡ ፩።

፩ ቴዎፍሎስ፡ ሆይ፡ ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ያስተምርና፡ ያደርግ፡ ዘንድ፡ በጀመረው፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ መጀመሪያውን፡ መጽሐፍ፡ ጻፍሁልህ፨ ሉ፡ ፩፡ ፫

፪ የመረጣቸውን፡ ሐዋርያቱን፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ካዘዛቸው፡ በኋላ፡ ወደ፡ ሰማይ፡ እስከ፡ ዓረገበት፡ ቀን፡ ድረስ፨

፫ ሕማማቱንም፡ ከተቀበለ፡ በኋላ፡ ሕያው፡ ሁኖ፡ በብዙ፡ መገለጥ፡ ራሱን፡ ያሳያቸው፡ አርባ፡ ቀንም፡ ሲታያቸው፡ ስለ፡ እግዚአብሔር መንግሥት፡ ነገር፡ የነገራቸው፨ ሉ፡ ፲፮፡ ፳፡ ፳፬ ሮሜ፡ ፲፩፡ ፲፪፨

፬ ከእነርሳቸውም፡ ጋራ፡ አብሮ፡ ሳለ፡ ከእኔ፡ የሰማችሁትን፡ የአብን፡ ተስፋ፡ ደጅ፡ ጽኑ ብሉ፡ ከኢየሩሳሌም፡ እንዳይወጡ፡ አዘዛቸው። ዮሐ፡ ፲፬፡ ፳፮፡ ሉቃ

፭ ፳፬፡ ፵፱፨ ዮሐንስ፡ በውሀ፡ ያጠምቅ፡ ነበርና፡ እናንተ፡ ግን፡ ከጥቂት፡ ቀን፡ በኋላ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ትጠመቃላችሁ፡ ምን፡ ፬፡ ፲፪፡ ፲፫ ፳፩፡ ማቴ፡ ፫፡ ፲፩።

፮ በተሰበሰቡም፡ ጊዜ፡ አቤቱ፡ በዚህ፡ ወራት፡ ለእስራኤል፡ መንግሥትን፡ ትመልሳለህን፡ ብለው፡ ጠየቁት፨ ሉ፡ ፳፬፡ ፳፩።

፯ አላቸውም፡ አብ፡ በሥልጣኑ፡ ያደረገውን፡ ዘመኑንና፡ ጊዜውን፡ ታውቁ፡ ዘንድ፡ ለእናንተ፡ አልተሰጣችሁም፨

፰ ነገር፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ወደ፡ እናንተ፡ በወረደ፡ ጊዜ፡ ኃይልን፡ ትቀበላላችሁ፡ በኢየሩሳሌምና፡ በይሁዳም፡ ሁሉ፡ በሰማርያም፡ እስከ፡ ምድር፡ ዳርም፡ ድረስ፡ ለእኔ፡ ትመሰክራላችሁ፨

፱ ይህንንም፡ በተናገረ፡ ጊዜ፡ እርሳቸው፡ እያዩት፡ ከፍ፡ ከፍ፡ አለ፡ ደመናም፡ ተቀበላቸው፡ ከዓይናቸውም፡ ተሠወረ፨ ማር፡ ፲፮፡ ፲፱

፲ ሉ፡ ፳፬፡ ፶፩፨ እነርሳቸውም፡ ወደ፡ ሰማይ፡ ሲመለከቱ፡ እነሆ፡ ነጫጭ፡ ልብስ፡ የለበሱ፡ ሁለት፡ ሰዎች፡ ባጠገባቸው፡ ቆመው፡ አዩ፨

፲፩ ሉ፡ ፳፬፡ ፬፨ እነዚያም፡ እናንተ፡ የገሊላ፡ ሰዎች፡ ወደ፡ ሰማይ፡ እያያችሁ፡ ለምን፡ ቆማችኋል፡ ይህ፡ ከእናንተ፡ ወደ፡ ሰማይ፡ የወጣው፡ ኢየሱስ፡ ወደ፡ ሲወጣ፡ እንደ፡ አያችሁት፡ እንዲሁ፡ ይመጣል፡ አሉ

ን፡ ሆይ፡ ትወደኛለህን፡ አለው፡ ጴጥሮስም፡ ለሶስተኛ፡ ትወደኛለህን፡ ስላለው፡ አዘነ፡ አቤቱ፡ አንተ፡ ሁሉን፡ ታውቃለህ፡ እንድወድህም፡ አንተ፡ ታውቃለህ፡ አለው፡ ኢየሱስም፡ በጎቼን፡ ጠብቅ፡ አለው። ም፡ ፲፫፡ ፴፰

፲፰ እውነት፡ እውነት፡ እልሃለሁ፡ አንተ፡ ጕልማሳ፡ ሳለህ፡ በገዛ፡ እጅህ፡ ወገብህን፡ ታጥቅ ህ፡ ወደ፡ እምትወደው፡ ትሔድ፡ ነበር፡ በሸመገልህ፡ ጊዜ፡ ግን፡ እጅህን፡ ታንሣለህ፡ ሌላም፡ ያስታጥቅሃል፡ ወደማትወደውም፡ ይወስድሃል።

፲፱ በምን፡ ሞት፡ እግዚአብሔርን፡ ያመስግን፡ ዘንድ፡ እንደ፡ አለው፡ ሲያመለክተው፡ ይህን፡ አለ ይህንንም፡ ተናግሮ፡ ተከተለኝ፡ አለው።

፳ ጴጥሮስም፡ ዘወር፡ ብሎ፡ ኢየሱስ፡ ይወደው፡ የነበረውን፡ ደቀ፡ መዝሙር፡ ሲከተለው፡ አየ። እርሱም፡ በራት፡ ጊዜ፡ በአጠገቡ፡ የተቀመጠና፡ ጌታ ዬ፡ ሆይ፡ አሳልፎ፡ የሚሰጥህ፡ ማነው፡ ያለው፡ ነው። ም፡ ፲፫፡ ፳፫።

፳፩ ያን፡ ጊዜም፡ ጴጥሮስ፡ እርሱን፡ አይቶ፡ ኢየሱስን፡ አቤቱ፡ ይህስ፡ እንዴት፡ ይሆናል፡ አለው።

፳፪ ኢየሱስም፡ እስከመጣ፡ ድረስ፡ ይቀመጥ፡ ዘንድ፡ ብወድስ፡ ምን፡ አግዶህ፡ አንተ፡ ግን፡ አትከተለኝ፡

፳፫ አለው፤ ስለዚህም፡ ያ ደቀ፡ መዝሙር፡ እንዳይሞት፡ ይህ፡ ነገር፡ በወንድሞቹ፡ ዘንድ፡ ወጣ። ኢየሱስግን፡ እስከመጣ፡ ድረስ፡ ይቀመጥ፡ ዘንድ፡ ብወድ፡ ምን፡ አግዶህ፡ አለ፡ እንጂ፡ አይሞትም፡ አላለውም።

፳፬ ስለዚህም፡ ሥራ፡ የመሰከረና የጻፈውም፡ ይህ፡ ደቀ፡ መዝሙር፡ ምስክር ነቱም፡ እውነት፡ እንደሆነ፡ እኛ፡ እናውቃለን። ም፡ ፲፱፡ ፴፭፡ ራእ፡ ፩፡ ፪።

፳፭ ኢየሱስም ያደረገው፡ ሌላ፡ እጅግ፡ ነገር፡ አለ፡ ሁሉም፡ እያንዳንዱ፡ ተጽፎ፡ ቢሆን፡ የተጻፉትን፡ መጻሕፍት፡ ዓለም፡ ስንኳ፡ ባልቻላቸውም፡ ነበር፡ አሚን።

የዮሐንስ፡ ወንጌል፡ ተፈጸመ

ወስመ፤ ጸሐፊሁ፤ ሣህሌ፤ ሀብተ፡ ወልድ፤ ዘሀገረ፡ ቡልጋ።

ከኢየሩሳሌም፡አትውጡ፡እን
ደ፡አላቸው፡ስለ፡እስራኤል፡መን
ግሥት፡መመለስ፡እንደ፡ጠየቁ
ት፡ስለ፡ጌታችን፡ዕርገት፡ለጸ
ሎት፡እንደ፡ተሰበሰቡ፡ስለ፡ማት
ያስ፡መመረጥ። ምዕራፍ፡፩።
፩ ቴዎፍሎስ፡ሆይ፡ጌታችን፡ኢ
የሱስ፡ክርስቶስ፡ያስተምር
ና፡ያደርግ፡ዘንድ፡በጀመረው፡
ሥራ፡ሁሉ፡መጀመሪያውን፡
መጽሐፍ፡ጻፍሁልህ። ሉ፡፩፡፫
፪ የመረጣቸውን፡ሐዋርያቱን፡በ
መንፈስ፡ቅዱስ፡ካዘዛቸው፡በኋ
ላ፡ወደ፡ሰማይ፡እስከ፡ዓረገባት
፫ ቀን፡ድረስ። ሕማማትንም፡ከ
ተቀበለ፡በኋላ፡ሕያው፡ሁኖ፡በ
ብዙ፡መገለጥ፡ራሱን፡ያሳያቸ
ው፡አርባ፡ቀንም፡ሲታያቸው፡
ስለ፡እግዚአብሔርመንግሥት፡ነ
ግር፡የነገራቸው። ሉ፡፳፬፡፴፮
፬ ሮሜ፡፲፬፡፲፯። ከእነርሳቸውም
ጋራ፡አብሮ፡ሳለ፡ከእኔ፡የሰማች
ሁትን፡የአብን፡ተስፋ፡ደጅ፡ጽኑ
ብሉ፡ከኢየሩሳሌም፡እንደይወ
ጡ፡አዘዛቸው። ዮሐ፡፲፭፡፳፮፡ሉቃ
፭ ፳፬፡፵፱። ዮሐንስ፡በውሀ፡ያጠ
ምቅ፡ነበርና፡እናንተ፡ግን፡ከጥ
ቂት፡ቀን፡በኋላ፡በመንፈስ፡ቅዱ
ስ፡ትጠመቃላችሁ። ም፡፩፡፲፯፡፲፰
፮ ፳፬፡ማቴ፡፫፡፲፩። በተሰበሰቡም፡ጊ
ዜ፡አቤቱ፡በዚህ፡ወራት፡ለእስራ
ኤል፡መንግሥትን፡ትመልሳለህ
ን፡ብለው፡ጠየቁት። ሉ፡፳፬፡፳፩።
፯ አላቸውም፡አብ፡በሥልጣኑ፡ያደ
ረገውን፡ዘመኑንና፡ጊዜውን፡ታ
ውቁ፡ዘንድ፡ለእናንተ፡አልተሰ
፰ ጣችሁም። ነገር፡መንፈስ፡ቅዱ
ስ፡ወደ፡እናንተ፡በወረደ፡ጊዜ፡ኃ
ይልን፡ትቀበላላችሁ፡በኢየሩሳ
ሌምና፡በይሁዳም፡ሁሉ፡በሰማር
ያም፡እስከ፡ምድር፡ዳርም፡ድረ
ስ፡ለእኔ፡ትመሰክራላችሁ።
፱ ይህንንም፡በተናገረ፡ጊዜ፡እርሳ
ቸው፡እያዩት፡ከፍ፡ከፍ፡አለ፡ደ
መናም፡ተቀበላቸው፡ከዓይና
ቸውም፡ተሠወረ። ማር፡፲፮፡፲፱
፲ ሉ፡፳፬፡፶፩። እነርሳቸውም፡ወደ
ሰማይ፡ሲመለከቱ፡እነሆ፡ነጫ
ጭ፡ልብስ፡የለበሱ፡ሁለት፡ሰዎ
ች፡ባጠገባቸው፡ቁመው፡አዩ።
፲፩ ሉ፡፳፬፡፬። እነዚያም፡እናንተ፡የ
ገሊላ፡ሰዎች፡ወደ፡ሰማይ፡እያያ
ችሁ፡ለምን፡ቆማችኋል፡ይህ፡ከ
እናንተ፡ወደ፡ሰማይ፡የወጣው፡
ኢየሱስ፡ወደ፡ሰማይ፡ሲወጣ፡እንደ፡አያ
ችሁት፡እንደሁ፡ይመጣል፡እሱ

አቸው፤ ሉ፡ ፳፬፡ ፶፪፤

፲፪ በዚያም፡ ጊዜ፡ ደብረ፡ ዘይት፡ ከ
ሚባለው፡ ተራራ፡ ወደ፡ ኢየሩሳ
ሌም፡ ተመለሱ፡ እርሱም፡ ለኢ
የሩሳሌም፡ የሰንበት፡ መንገድ
ያህል፡ የራቀ፡ ነው፤ ሉ፡ ፳፬፡ ፶፪፤

፲፫ በደረሱም፡ ጊዜ፡ ይኖሩበት፡ ወ
ደ፡ ነበረ፡ ሰገነት፡ ወጡ፤ ጴጥሮስ
ና፡ ያዕቆብም፡ ዮሐንስም፡ እንድ
ርያስም፡ ፊልጶስም፡ በርተሎ
ሚዎስም፡ ቶማስም፡ ማቴዎስ
ም፡ የእልፍዮስ፡ ልጅ፡ ያዕቆብ
ም፡ ቀናኢው፡ ስምዖንም፡ ይሁ
ዳም፡ የያዕቆብ፡ ልጅ፤ ማቴ፡ ፲፡ ፪

፲፬ ሉ፡ ፮፡ ፲፫፡ ፲፮፤ እነዚህ፡ ሁሉ፡ ከሴ
ቶችና፡ ከኢየሱስ፡ እናት፡ ከማ
ርያም፡ ከወንድሞቹ፡ ጋራ፡ ሳያ
ስታጕሉ፡ በአንድነት፡ ይጸልዩ

፲፭ ነበሩ፤ ም፡ ፪፡ ፩፡ ዮሐ፡ ፲፯፡ ፳፩፤ በዚ
ያም፡ ቀን፡ ጴጥሮስ፡ መቶ፡ ሀያ፡ የ
ሚሆኑ፡ ሰዎች፡ ተሰብስበው፡ ሳ
ሉ፡ በወንድሞች፡ መካከል፡ ተነሥ

፲፮ ቶ፡ አለ፤ እናንት፡ ሰዎች፡ ወንድሞ
ቻችን፡ ኢየሱስን፡ ለያዙት፡ መሪ
ስለ፡ ሆናቸው፡ ስለ፡ ይሁዳ፡ መን
ፈስ፡ ቅዱስ፡ አስቀድሞ፡ በዳዊ
ት፡ አፍ፡ የተናገረው፡ የመጽሐ
ፍ፡ ቃል፡ ይፈጸም፡ ዘንድ፡ ይገባ

፲፯ ሏ፤ መዝ፡ ፵፩፡ ፱፤ ከእኛ፡ ጋራ፡ ተ
ቈጥሮ፡ ነበርና፡ ለዚህም፡ አገል

፲፰ ግል፡ ታድሎ፡ ነበርና፤ በዓመፃ፡ ዋ
ጋው፡ መሬት፡ ገዛ፡ በግምባሩ
ም፡ ወድቆ፡ ከመካከሉ፡ ተሰነ
ጠቀ፡ አንጀቱም፡ ሁሉ፡ ተዘረገ

፲፱ ፈ፤ ማቴ፡ ፳፯፡ ፫፡ ፲፤ ወሬውም፡
በኢየሩሳሌም፡ በሚኖሩ፡ ሁሉ
ዘንድ፡ ታወቀ፡ ያ፡ መሬትም፡ በቋ
ንቋቸው፡ አኬልዳማ፡ ተብሎ፡
ተጸራ፡ እርሱም፡ የደም፡ መሬት

፳ ማለት፡ ነው፤ በመዝሙር፡ መጽ
ሐፍ፡ መኖርያው፡ ምድረ፡ በዳ፡
ትሁን፡ የሚኖርባትም፡ አይኑ
ር፡ ሹመቱንም፡ ሌላ፡ ይውሰደ
ቶ፡ ተብሎ፡ ተጽፎአልና፤ መዝ

፳፩ ፷፱፡ ፳፭፡ ፻፱፡ ፰፤ ስለዚህ፡ ጌታ፡
ችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ወደ፡ እኛ፡
በገባበትና፡ በወጣበት፡ ዘመን፡
ሁሉ፡ ከእኛ፡ ጋራ፡ ከነበሩት፡ ከእ
ነዚህ፡ ሰዎች፡ ለአንዱ፡ ይገባል፡

፳፪ ዮሐ፡ ፲፭፡ ፳፯፤ ከዮሐንስ፡ ጥም
ቀት፡ ጀምሮ፡ ከእኛ፡ እስከ፡ ዓረገ
በት፡ ቀን፡ ድረስ፡ እርሱ፡ ከእኛ፡ ጋ
ራ፡ ስለ፡ ትንሣኤው፡ ምስክር፡

፳፫ ይሆን፡ ዘንድ፤ ኢዮስጦስም፡ የ
ሚሉት፡ በርናባስ፡ ተብሎ፡ የተ
ጸራ፡ ዮሴፍንና፡ ማትያስን፡ ሁ

፳፬ ለቱን፡ አቀረቡ፤ እንዲህም፡ ብለ
ው፡ ጸለዩ፡ የሁሉን፡ ልብ፡ የምታ
ውቅ፡ አንተ፡ ጌታ፡ ሆይ፡ ከእነዚ
ህ፡ ከሁለቱ፡ የመረጥኸውን፡ አ
ንዱን፡ ግለጥ፤ መዝ፡ ፯፡ ፲፤

፳፭ ይሁዳ፡ ወደ፡ ስፍራው፡ ይሄድ፡

ዘንድ፡ የተዋቱን፡ ይህችን፡ የሐ
ዋርያት፡ የማገልገል፡ ቦታ፡ የሚ
፳፮ ቀበላትን። ዕጣም፡ አጣጣልዋ
ቸው፡ ዕጣውም፡ ለማትያስ፡ ደ
ረሰ፤ ከአሥራ፡ አንዱ፡ ሐዋር
ያት፡ ጋራ፡ ተቈጠረ። ም፲፮፡፴፫

ምዕራፍ፡ ፪።

ሐዋርያት፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ እ
ንደ፡ ተቀበሉና፡ በብዙ፡ ቋንቋ፡ እ
ንደ፡ ተናገሩ፤ ስክረዋል፡ እንደ
አሏቸው፤ ስለ፡ ጴጥሮስ፡ ስብ
ከት፤ ሶስት፡ መቶ፡ ሰዎች፡ እንዴ
አመኑ፤ ገንዘባቸውን፡ እንድነ
ት፡ እንዳደረጉ።

፩ በአምሳኛውም፡ ቀን፡ በጰንጠቈ
ስጤ፡ በዓል፡ ሁሉም፡ በሥፍራቸ
ው፡ በአንድነት፡ ስለ፡ ዘሌ፡፳፫፡
፪ ፲፭፡ ፳፩፡ ም፡ ፩፡ ፲፬። ድንገት፡ እን
ደ፡ አውሎ፡ ነፋስ፡ ከሰማይ፡ ድ
ምፅ፡ መጣ፡ ተቀምጠውበት፡ የ
ነበሩትንም፡ ቤት፡ ሁሉ፡ መላው
፫ የተከፋፈሉም፡ የእሳት፡ ላንቃ
ዎች፡ የመሰሉ፡ ታዩዋቸው፡
በእርሳቸውም፡ በእያንዳንዱ፡
ተቀመጡባቸው። ማቴ፡፫፡፲፩፡
፬ በሁሉም፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ መላ
ባቸውና፡ ይናገሩ፡ ዘንድ፡ መን
ፈስ፡ ቅዱስ፡ እንደ፡ ሰጣቸው፡ በ
ሌላ፡ ቋንቋ፡ ይናገሩ፡ ጀመር።
፭ ም፲፡ ፵፮። እግዚአብሔርንም፡
የሚፈሩ፡ ከሰማይ፡ በታች፡ ካሉ
አሕዛብ፡ ሁሉ፡ ደጋጎች፡ የአይ
ሁድ፡ ሰዎች፡ በኢየሩሳሌም፡
፮ ነበሩ። ም፭፡ ፳፫። ይህም፡ ድ
ምፅ፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ ሕዝቡ፡ ሁሉ፡
እየደነገጡ፡ በአንድነት፡ ተሰበ
ሰቡ፡ በየቋንቋቸውም፡ ሲናገ
ሩ፡ ይሰሙዋቸው፡ ነበሩና፡ የሚ
፯ ሉትን፡ አጡ። ሁሉም፡ በድንጋጤ
አድንቀው፡ እርስ፡ በርሳቸው፡
እንዲህ፡ አሉ፡ እነሆ፡ እነዚህ፡ የ
ሚናገሩት፡ ሁሉ፡ የገሊላ፡ ሰዎ
፰ ች፡ አይደሉምን። በሀገራችን፡
ቋንቋ፡ ሲናገሩ፡ እንዴት፡ እንሰ
፱ ማቸዋለን። እኛ፡ በተወለድን
በት፡ ጳርቴም፡ ሜዶንም፡ ኤላ
ሜጤም፡ በሁለት፡ ወንዝ፡ መ
ካከል፡ የሚኖሩትም፡ በይሁዳ
ም፡ በቀጰዶቅያም፡ በጳንጦስ
፲ ም፡ በእስያም። በፍርጊያም
ም፡ በጵንፍልያም፡ በምስርም
ወዳ፡ ቀርኔን፡ ከቀረበች፡ ከሊብ
ያም፡ አውራጃ፡ ከሮምም፡ የመ
ጡ፡ ሰዎች፡ አይሁድም፡ ከአረ
ማዊነትም፡ ወደ፡ አይሁዳዊነት
፲፩ የገቡ፡ ሰዎች። የቀርጤስም፡ የ
ዓረብም፡ ሰዎች፡ እነሆ፡ የእግዚ
አብሔርን፡ ታላቅነት፡ በቋንቋ
ችን፡ ሲናገሩ፡ እንሰማቸዋለን
፲፪ ሁሉም፡ ተደንቀው፡ የሚሉት
ን፡ አጡ፡ እርስ፡ በርሳቸውም፡ እ
ንዲህ፡ አሉ፡ እንጃ፡ ይህ፡ ምን፡ ይ

፲፫ ሆኖ። እኩሌቶቹ፡ግን፡እነዚ
ህ፡ጕሾ፡መጆ፡ጸጋብው፡ሰክረ
፲፬ ዋሌ፡እያሉ፡ሰቁባቸው፤ያንጊ
ዜም፡ጴጥሮስ፡ከአሥራ፡አንዱ
ጋራ፡ቆመ፡ድምፁም፡ከፍ፡አድ
ርጎ፡እንዲህ፡ብሎ፡ተናገራቸው
እናንተ፣የይሁዳ፡ሰዎች፡በኢየ
ሩሳሌምም፡የምትኖሩ፡ሁላች
ሁ፡ይህ፡በእናንተ፡ዘንድ፡የታ
ወቀ፡ይሁን፡ቃሎቼንም፡አድም
፲፭ ጡ፤ሰእናንተ፡እንደ፡መሰላች
ሁ፡እነዚህ፡የሰከሩ፡አይደሉም፡
ከቀኑ፡ገና፡ሦስተኛ፡ሰዓት፡ነው
፲፮ ና፤ነገር፡ግን፡ይህ፡በነቢዩ፡በኢ
ዩኤል፡የተባለው፡ነው፤ኢዩ፡
፲፯ ፪፡፳፰፤እግዚአብሔር፡ይላል
በኋለኛይቱ፡ቀን፡ይሆናል፡ሰ
ጋ፡በለበሰ፡ሁሉ፡ላይ፡ከመንፈ
ሴ፡አፈሳለሁ፤ወንዶችና፡ሴቶ
ች፡ልጆቻችሁም፡ትንቢት፡ይ
ናገራሉ፡ጕበዞቻችሁም፡ራእ
ይ፡ያያሉ፡ሽማግሌዎቻችሁም፡
ሕልም፡ያልማሉ፤ም፡፳፩፡፲፩።
፲፰ ደግሞም፡በዚያች፡ወራት፡በወ
ንዶችና፡በሴቶች፡አገልጋዮች
ላይ፡ከመንፈሴ፡አፈሳለሁ፡
፲፱ ትንቢትም፡ይናገራሉ፤በላ
ይ፡ም፡በሰማይ፣ተአምራትን
እሰጣለሁ፡በታችም፡በምድር
ምልክትን፡ደም፡እሳትም፡ጭ
፳ ጋማም፤የታወቀችዋም፡ታላ
ቅዋ፡የእግዚአብሔር፡ቀን፡
ሳትመጣ፣ፀሐይ፡ወደ፡ጨለ
ማ፡ጨረቃም፡ወደ፡ደም፡ይለ
፳፩ ዋወጣል፤የእግዚአብሔርን፡ስ
ም፡የጠራ፡ሁሉም፡ይድናል፡ሮ
፳፪ ሜ፡፲፡፲፫፤እናንተ፡የእስራኤል፡ሰዎ
ች፡ይህን፡ቃል፡ስሙ፤ራሳችሁ፣
እንደምታውቁ፡በመካከላችሁ
እግዚአብሔር፡በእርሱ፡ባደረገ
ው፡ኃይልና፡ተአምራት፡ምልክ
ት፡ም፡የገለጸው፡ሰው፡የናዝሬ
፳፫ ቱ፡ኢየሱስን፤ም፡፲፡፴፰፤ይህን
በተወሰነው፡በእግዚአብሔር
ምክርና፡በቀደመው፡ዕውቀ
ቱ፡እናንተ፡ወስዳችሁ፡በኃጢ
አተኞች፡እጅ፣አሳልፋችሁ፡ሰ
ጣችሁት፡ሰቀላችሁትም፡ገደላች
፳፬ ሁት፡ም፡፬፡፳፰፤እግዚአብሔር
ግን፡የሞትን፡ማሠሪያ፡ፈትቶ፡
አስነሣው፡ሞት፡ይይዘው፡ዘን
ድ፡አይቻልምና፤ም፡፫፡፲፭።
፳፭ ዳዊትም፡ስለ፡እርሱ፡ይላል፡እግ
ዚአብሔርን፡ሁልጊዜ፡በፊቴ፡አየ
ዋለሁ፡እንዳልታወክ፡በቀኜ፡ነው
፳፮ ና፣መዝ፡፲፮፡፰፤ስለዚህ፡ልቤ፡
ደስ፡አለው፡ልሳኔም፡ሐሤት፡አ
ደረገ፡ሥጋዬም፡ደግሞ፡በተስፋ
፳፯ ው፡አደረ፤ነፍሴን፡በሲኦል፡አት
ተዋትምና፡ጻድቅህንም፡ጥፋት
ን፡ያይ፡ዘንድ፡አትሰጠውምና፤
፳፰ የሕይወትም፡መንገድ፡አሳየኸ

ኛ፡ በፊትህም፡ አጠግብ፡ ደስታ
፳፱ ን፡ አጸገብኸኝ። እናንተ፡ ወንድ
ሞች፡ ሰዎች፡ ስለ፡ አባቶች፡ አለቃ
ስለ፡ ዳዊት፡ ለእናንተ፡ በግልጽ፡
እነግር፡ ዘንድ፡ ይገባል፡ እንደ፡ ሞ
ተ፡ እንደ፡ ተቀበረም፡ መቃብሩ
ም፡ እስከ፡ ዛሬ፡ በእኛ፡ ዘንድ፡ ነው
፴ ም፡ ፲፫፡ ፴፯፡ ፩፡ ነገ፡ ፪፡ ፲። ነቢይ፡ ነ
በርና፡ ከሆዱ፡ ፍሬ፡ በዙፋኑ፡ እን(
ዲቀመጥ፡ እግዚአብሔር፡ መሐለ
እንደ፡ ማለለት፡ ስላ፡ አወቀ። መዝ
፻፴፪፡ ፲፩፡ ፲፪፡ ፪ሳሙ፡ ፯፡ ፲፪፡ ፲፫። እር
፴፩ ሱ፡ ነፍሱ፡ በሲኦል፡ እንዳትቀር፡ ሥ
ጋውም፡ መፍረሱን፡ እንዳያይ፡ ስለ፡
ክርስቶስ፡ ትንሣኤ፡ አስቀድሞ፡ አ
፴፪ ይቶ፡ ተናገረ። ይህንም፡ ኢየሱ
ስን፡ እግዚአብሔር፡ አስነሣው፡ እ
፴፫ ኛም፡ ሁላችን፡ ምስክሮች፡ ነን። እ
ሁን፡ ግን፡ በእግዚአብሔር፡ ቀኝ፡
ከፍ፡ ከፍ፡ ብሎና፡ የመንፈስ፡ ቅዱ
ስን፡ ተስፋ፡ ከአብ፡ በተቀበለ፡
ጊዜ፡ እርሱ፡ ይህን፡ ዛሬ፡ የምታዩ
ትንና፡ የምትሰሙትን፡ አፈሰሰ(
፴፬ ው። ዳዊት፡ ወደ፡ ሰማይ፡ አልወጣ
ም፡ ነገር፡ ግን፡ እርሱ፡ አለ፡ ጌታ፡ ጌ
ታዬን፡ አለው፡ በቀኜ፡ ተቀመጥ።
፴፭ መዝ፡ ፻፲፩፤ ጸላቶችህን፡ ከእግር
ህ፡ ጫማ፡ በታች፡ እስከ፡ አደርግል
፴፮ ህ፡ ድረስ። እንግዲህ፡ ይህን፡ እናን
ተ፡ የሰቀላችሁትን፡ ኢየሱስን፡ እግ
ዚአብሔር፡ ጌታና፡ መሢሕ፡ እንደ

አደረገው፡ የእ̄ል፡ ወገን፡ ሁሉ፡ በ
እነውነት፡ ይወቁ። ፭፡ ፴፩።
፴፯ ይህንንም፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ ልባቸ(
ው፡ ተነካ፡ ጴጥሮስንና፡ ሌሎችን
ም፡ ሐዋርያትን፡ እናንተ፡ ወን
ድሞቻችን፡ ምን፡ እናድርግ፡ አ
ሉዋቸው። ም፡ ፲፮፡ ፴።
፴፰ ጴጥሮስም፡ አላቸው፡ ንስሐ፡ ግ(
ቡ፡ ኃጢአታችሁም፡ ይሠረይላ
ችሁ፡ ዘንድ፡ እያንዳንዳችሁ፡ በ
ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስም፡ ተጠመ
ቁ፡ የመንፈስ፡ ቅዱስንም፡ ጸጋ፡ ት
ቀበላላችሁ። ም፡ ፫፡ ፲፱፡ ሉ፡ ፳፬፡ ፵፯፡
፴፱ ይህ፡ ተስፋ፡ ለእናንተ፡ ለልጆ(
ቻችሁ፡ እግዚአብሔር፡ አምላ
ካችንም፡ ለሚጠራቸው፡ በሩቅ
ላሉ፡ ሁሉ፡ ነውና። ኢዩ፡ ፪፡ ፳፰።
፵ በሌላም፡ ቃል፡ እጅግ፡ አስረዳ
ከዚህ፡ ጠመፀኛ፡ ትውልድ፡ ዳኑ፡ ብ
፵፩ ሎ፡ ገሠጻቸው። ከእነርሳቸውም
ነገሩን፡ ደስ፡ ብሎአቸው፡ የተቀበ
ሉ፡ ተጠመቁ፡ በዚያም፡ ቀን፡ ሦስ
ት፡ ሺህ፡ የሚያህል፡ ነፍስ፡ ወደም
፵፪ እመናኑ፡ ተጨመሩ። በሐዋርያ
ትም፡ ትምህርትና፡ በአንድነት፡ እ
ንጀራም፡ በመባረክና፡ በጸሎት፡
፵፫ ፀንተው፡ ኖሩ። ም፡ ፩፡ ፲፬። በሰው(
ም፡ ሁሉ፡ ፍርሃት፡ ሆነ፡ በሐዋር
ያትም፡ እጅ፡ ብዙ፡ ተአምራትና
፵፬ ምልክት፡ ተደረገ። ያመኑትም
ሁሉ፡ በአንድነት፡ ነበሩ፡ ያላቸው

ኖም፡ ገንዘብ፡ ሁሉ፡ አንድነቱ፡ አ
፵፭ ደረጉ፡፡ ም፡ ፬፡ ፴፪ ፬ ቀመሬታቸው
ንና፡ ጥሪታቸውንም፡ እየሸጡ፡
ለእያንዳንዱ፡ እንደ፡ፈቃዱ፡ እን
፵፮ ዲፈቃዱ፡ ያካፍሉት፡ ነበርቀበየ
ቀኑም፡ በመቅደስ፡ እየተሰበሰ
ቡ፡ በአንድነት፡ ፀንተው፡ ይኖሩ
ነበሩ፡ በየቤቱም፡ እንጀራ፡ እየ
ቈረሱ፡ በደስታና፡ በጥሩ፡ ልቡና
ም፡ እግዚአብሔርን፡ እያመሰገ
ኑ፡ ምግባቸውን፡ ይመገቡ፡ ነበሩ
፵፯ ቀ ፵፯ ፬ ቀበሕዝቡም፡ ሁሉ፡ ፊት
ዕድል፡ ነበራቸው፡ እግዚአብሔ
ርም፡ የሚድኑትን፡ ዕለት፡ ዕለ
ት፡ ወደ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ይጨ
ምር፡ ነበርቀም፡ ፬፡ ፬፡ ፳፡ ፲፬፡ ፲፭፡
፳፭፡ ፲፬፡ ፭ ፡፡ ምዕራፍ፡ ፫፡፡

ጴጥሮስና፡ ዮሐንስ፡ ድውይ፡ እንደ
አገኙ፡ አዳኑ፡ ስለ፡ ጴጥሮስ፡ ስብከት
፩ ጴጥሮስና፡ ዮሐንስም፡ በጸሎት
ጊዜ፡ በዘጠኝ፡ ሰዓት፡ በአንድነት
፪ ወደ፡ መቅደስ፡ ወጡቀከእናቱም
ማኅፀን፡ ጀምሮ፡ ሽባ፡ ሁኖ፡ የተ
ወለደ፡ አንድ፡ ሰው፡ ነበረ፡ ወደ፡
መቅደስም፡ ከሚገቡ፡ ምጽዋ
ት፡ ይለምን፡ ዘንድ፡ ሁል ጊዜ፡ እየ
ተሸከሙ፡ መልካም፡ በሚባል
ው፡ በመቅደስ፡ ደጅ፡ ያስቀምጡ
፫ ት፡ ነበርቀይህም፡ ጴጥሮስና፡ ዮ
ሐንስ፡ ወደ፡ መቅደስ፡ ሲገቡ፡ ባየ
ጊዜ፡ ምጽዋት፡ ይሰጡት፡ ዘንድ
፬ ለመናቸውቀጴጥሮስም፡ ከዮ
ሐንስ፡ ጋራ፡ ተኩር፡ ብሎ፡ ተመ
ለከተው፡ ወደ እኛም፡ ተመልከ
፭ ት፡ አለውቀእርሱም፡ ምጽዋት
ለመቀበል፡ተስፋ፡ እድርጎ፡ ወደ፡
፮ እነርሳቸው፡ ተመለከተቀጴጥሮ
ስም፡ ወርቅና፡ ብር፡ የለኝም፡ ያለ
ኝን፡ ግን፡ እሰጥሃለሁ፡ እነሆ፡ በና
ዝሬቱ፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስም
ተነሣና፡ ሒድ፡ አለውቀም፡ ፲፬፡ ፱
፯ ፲ ቀበቀኝ፡ እጁም፡ ይዞ፡ አስነሣው
በዚያ፡ ጊዜም፡ እግሩና፡ ቍርጭ
ምጭሚቱ፡ ፀናቀማቴ፡ ፳፡ ፲፭ ቀ
፰ ተነሥቶም፡ ቆመ፡ እየሮጠና፡ እየ
ተራመደ፡ ሔደ፡ እግዚአብሔርን
ም፡ እያመሰገነ፡ ከእነርሳቸው፡ ጋ
ራ፡ ወደ፡ መቅደስ፡ ገባቀኢሳ፡ ፴፭፡
፱ ፯ ቀሕዝቡም፡ ሁሉ፡ እግዚአብ
ሔርን፡ እያመሰገነ፡ ሲሔድ፡ አዩት
፲ መልካም፡ በሚባለው፡ ምመቅደ
ስ፡ ደጅ፡ ተቀምጦ፡ ምጽዋት፡ ይለ
ምን፡ የነበረው፡ እርሱ፡ እንደሆነ
አወቁ ተቀበእርሱም፡ ከሆነው፡
የተነሣ፡ ፍርሃትና፡ መደነቅ፡ መ
፲፩ ላባቸውቀእንካሰውም፡ ከጴጥ
ሮስና፡ ከዮሐንስ፡ ጋራ፡ አብሮ፡ ሳ
ለ፡ ሕዝቡ፡ ሁሉ፡ እየተደነቁ፡ የሰ
ሎሞን፡ ወሰል፡ በሚባለው፡ ወደ
እነርሳቸው፡ሮጡ፤ም፡ ፭፡ ፲፪ ቀ ጴ
፲፪ ጥሮስም፡ ባያቸው፡ ጊዜ፡ ሕዝቡ
ን፡ አላቸው፡ እናንተ፡ የ፳ል፡ ሰዎ

ቸ፡ በዚህ፡ ለምን፡ ትደነቃላችሁ
ወይስ፡ በኃይላችን፡ በጽድቃ
ችን፡ ይህ፡ ይሔድ፡ ዘንድ፡ እንደ፡
አደረግነው፡ ለምን፡ ታዩናላ
፲፫ ችሁ። የአብርሃም፡ የይስሐቅ
የያዕቆብ፡ የአባቶቻችን፡ አም
ላክ፡ እናንተ፡ አሳልፋችሁ፡ የሰ
ጣችሁትን፡ እርሱም፡ ሊተወው፡
ወዶ፡ ሳለ፡ በጲላጦስ፡ ፊት፡ የካዳ
ችሁትን፡ ልጁን፡ ኢየሱስን፡ አ
ከበረው። ም፡ ፳፡ ፴፡ ዘፀ፡ ፫፡ ፮፡ ፲፭
10 ፲፯፡ ዮሐ፡ ፬፡ ፳፫። እናንተ፡ ግን፡ ቅ
ዱሱን፡ ጻድቁንም፡ ክዳችሁ፡ ነ
ፍስ፡ ገዳዩን፡ ሰው፡ ይተውላችሁ
ዘንድ፡ ለመናችሁ። ማቴ፡ ፳፯፡ ፳፡
፲፭ ፳፡ ፳፩፡ እግዚአብሔር፡ ከሙታ
ን፡ ያስነሣውን፡ እኛም፡ ምስክሮች
የሆንለትን፡ የሕይወትን፡ ራስ
ግን፡ ገደላችሁት። ም፡ ፬፡ ፳፡ ፴፡
፪፡ ፬፡ ፩ ሮሜ፡ ፬፡ ፳፬፡ ፳፭፡ ፩፡ ፮፡ ፮ ቆ
ሮ፡ ፪፡ ፲፬፡ ፲፭፡ ፬፡ ፲፭፡ ፱፡ ቆ፡ ፬፡ ፲፬፡
፲፮ በስሙ፡ በማመን፡ ይህን፡ የምታ
ዩትንና፡ የምታውቁትን፡ ሰው፡
ስሙን፡ አጸናው፡ በእርሱም፡ የ
ሆነች፡ እምነት፡ በሁላችሁ፡ ፊት
፲፯ ለዚህ፡ ፍጹም፡ ጤና፡ ሰጠችው።
አሁንም፡ ወንድሞቼ፡ ሆይ፡ ያደ
ረጋችሁትን፡ እንደ፡ አለቆቻች
ሁ፡ ባለማወቅ፡ እንደ፡ አደረጋች
ሁት፡ አውቃለሁ። ፳፫፡ ፴፬፡
፲፰ እግዚአብሔር፡ ግን፡ በነቢያት፡
ሁሉ፡ አፍ፡ ስለ፡ ክርስቶስ፡ ሕማ
ማት፡ የተናገረውን፡ እንደዚሁ
፲፱ ፈጸመው። ፳፬፡ ፩፡ ፳፯። አሁ
ንም፡ ኃጢአታችሁ፡ ይሠረይ
ላችሁ፡ ዘንድ፡ ንስሓ፡ ግቡ፡ ተመ
ለሱም። ኢሳ፡ ፵፫፡ ፳፭፡ ፲፡ ም፡ ፬፡ ፴፰፡
፳ ከእግዚአብሔርም፡ ፊት፡ የዕረ
ፍት፡ ዘመን፡ እንዲመጣላች
ሁ፡ አስቀድሞ፡ ለእናንተ፡ የመ
ረጠውን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ ይ
ልክላችሁ፡ ዘንድ። ዳን፡ ፪፡ ፳፬፡
፳፪፡ ሮሜ፡ ፲፫፡ ፳፬፡ ራእ፡ ፳፡ ፪።
፳፩ እግዚአብሔርም፡ ከጥንት፡ ጀ
ምሮ፡ በቅዱሳን፡ ነቢያቱ፡ አፍ፡
እስከ፡ ተናገረው፡ የመደራጀት
ዘመን፡ ደረስ፡ ሰማይ፡ ይቀበለው
፳፪ ዘንድ፡ ይገባልና። ሙሴም፡ ለአ
ባቶች፡ አለ፡ እግዚአብሔር፡ አ
ምላካችሁ፡ ከወንድሞቻችሁ
እንደ እኔ፡ ያለ፡ ነቢይ፡ ያስነሣላ
ችኋል፡ እርሱ፡ የሚነግራችሁ
ን፡ ሁሉ፡ ስሙ። ዘዳግ፡ ፲፰፡ ፲፭
፳፫ ፲፰። ያን፡ ነቢይ፡ የማይሰማ
ው፡ ነፍስ፡ ሁሉ፡ ግን፡ ከሕዝብ፡ ተ
፳፬ ለይታ፡ ትጠፋለች። ከሳሙኤል
ም፡ ጀምሮ፡ ከእርሱም፡ በኋላ፡
የነበሩ፡ ነቢያት፡ ሁሉ፡ ስለዚች
፳፭ ቀን፡ ተናገሩ፡ ሰበኩም። እናን
ተም፡ የነቢያትና፡ እግዚአብሔር
ከአባቶቻችን፡ ጋራ፡ ያደረገው
የኪዳን፡ ልጆች፡ ናችሁ፡ ለአብ

ርሃም፡ በዘርህ፡ የምድር፡ አሕ
ዛብ፡ ሁሉ፡ ይባረካሉ። ብሎ፡ ቃ
፳፮ ልና፡(ዘፍ፡ ፲፪፡ ፫፡ ፳፪፡ ፲፰)፡ አስ
ቀድሞ፡ እግዚአብሔር፡ ለእና
ንተ፡ ልጁን፡ ኢየሱስን፡ አስነሣ
ላችሁ፡ ከክፋታችሁም፡ ብት
መለሱ፡ እያንዳንዳችሁን፡ ይባ
ርካችሁ፡ ዘንድ፡ ሰደደው፤ ም፡
፲፫፡ ፵፮፤ ምዕራፍ፡ ፬።

ስለ፡ ሐዋርያት፡ መታሠር፡ ፭ቱ፡ ሺ
ሰዎች፡ እንደ፡ አመኑ፡ ሐዋርያትን፡
በማን፡ ስም፡ ይህን፡ ታደርጋላች
ሁ፡ ብለው፡ እንደ፡ መረመሯቸ
ው፤ ጴጥሮስ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡
እንደ፡ ተናገረ፤ በኢየሱስ፡ ስም፡
እንዲድኑ ሰብኩ፡ እንደ፡ ከለከሏቸ
ው፡ ከሰው፡ ይልቅ፡ እግዚአብሔ
ርን፡ መስማት፡ እንዲገባ፡ ሐዋር
ያት፡ ሲጸልዩ፡ ምድር፡ እንደ፡ ተና
ወጠ፡ ስለ፡ የገንዘብ፡ እንድነት፡
ማኅበር፨

፩ እነርሳቸውም፡ ለሕዝቡ፡ ሲነግሩ
ካህናቱና፡ የመቅደስ፡ አለቃ፡ ሰዱ
ቃውያንም፡ ተነሡባቸውም፤
፪ ሉቃ፡ ፳፪፡ ፬፡ ፳፪፡ ፶፪፤ ሕዝብን፡ ስለ
አስተማሩና፡ በኢየሱስም፡ የ
ሙታን፡ ትንሣኤ፡ ስለሰበኩ፡
ተናደው፡ ቀንዓት፡ መሳባቸው
፫ እጃቸውንም፡ ጣሉባቸው፤ ጊዜ
ው፡ ፈጽሞ፡ መሽቶ፡ ነበረና፡ እ
ስከ፡ ማግሥቱ፡ ድረስ፡ በግዞት
፬ ቤት፡ አገብዋቸው፤ ነገር፡ ግን
ነገራቸውን፡ ከሰሙት፡ አጅግ፡
ሰዎች፡ አመኑ፡ ያመኑትም፡ ሰዎ
ች፡ ቍጥራቸው፡ ፭ቱ፡ ሺህ፡ ያህ
፭ ል፡ ነበር፨ ም፡ ፬፡ ፴፮፨ በነጋው
ም፡ አለቆችና፡ ሽማግሌዎች፡ ጻፎ
ችም፡ በኢየሩሳሌም፡ ተሰበሰቡ
፮ ከእነርሳቸውም፡ ጋራ፡ የካህና
ቱ፡ አለቃ፡ ሐና፡ ቀያፋም፡ ዮሐን
ስም፡ እስክንድሮስም፡ ከካ
ህናትም፡ አለቅነትም፡ ወገን፡ የነበ
፯ ሩ፡ ሁሉ፨ ም፡ ፭፡ ፲፯፡ ሉ፡ ፫፡ ፪፨ በመ
ካከልም፡ አቁመው፡ በምን፡ ኃይ
ል፡ በማንስ፡ ስም፡ እናንተ፡ ይህ
አደረጋችሁ፡ ብለው፡ መረመር
፰ ዋቸው፨ ማቴ፡ ፳፩፡ ፳፫፨ በዚያ
ም፡ ጊዜ፡ ጴጥሮስ፡ መንፈስ፡ ቅዱ
ስን፡ ተመልቶ፡ አላቸውም፡ እናንተ
የሕዝብ፡ አለቆች፡ የ፳ልም፡ ሽማ
፱ ግሌዎች፨ ፲፪፡ ፲፩፨ ዛሬ፡ በአንዳ
ድ ውይ፡ ሰው፡ በተደረገው፡ መል
ካም፡ ሥራና፡ በምን፡ እንደ፡ ተ
ፈወሰ፡ በእኛ፡ ከተፈረደብን፡ የ
፲ ሐ፡ ፲፡ ፴፪፨ እናንተ፡ በሰቀላችሁ
ት፡ እግዚአብሔር፡ ከሙታን፡ በ
አስነሣው፡ በናዝሬቱ፡ በኢየሱ
ስ፡ ክርስቶስ፡ ስም፡ ይህ፡ ደኅና፡
ሆኖ፡ በፊታችሁ፡ እንደ፡ ቆመ፡ በ
እናንተ፡ በሁላችሁ፡ በ፳ል፡ ሕዝ
ብ፡ ሁሉ፡ ዘንድ፡ የታወቀ፡ ይሁን፤
፲፩ ም፡ ፫፡ ፲፮፡ ይህ፡ እናንተ፡ እናፃ

ች፡የናቃችሁት፡ደንጊያ፡ነው
ና፡እርሱም፡የማዕዘን፡ራስ፡ሆ
ነ፡ማቴ፡፳፩፡፵፪፡መዝ፡፻፲፰
፲፪ ፳፪።ከሰማይ፡በታች፡ሰው፡ይ
ድንበት፡ዘንድ፡በሚገባ፡የተ
ሰጠ፡ከቶ፡ሌላ፡ስም፡የለምና
፲፫ ማቴ፡፩፡፳፩።የጴጥሮስንና፡
የዮሐንስንም፡ድፍረት፡ባዩ
ጊዜ፡መጽሐፍን፡የማያውቁ
የዋሃንም፡ሰዎች፡እንደ፡ሆኑ
አውቀው፡አደነቁ፡ከኢየሱስ
ም፡ጋራ፡እንደ፡ነበሩ፡አወቅዋ
፲፬ ቸው።የተፈወሰውንም፡ሰው
ከእነርሳቸው፡ጋራ፡ቁሞ፡ባ
ዩ፡ጊዜ፡የሚናገሩትን፡አጡ
፲፭ ም፡፫፡፰፡፱።ከአደባባይም፡ወ
ደ፡ውጭ፡ይወጡ፡ዘንድ፡አዘ
ዙ፡እርስ፡በርሳቸውም፡ተማ
፲፮ ከሩ።እንዲህ፡ሲሉ፡በእነዚህ
ሰዎች፡ምን፡እንስራ፡እነሆ፡
በኢየሩሳሌም፡በሚኖሩ፡ሁ
ሉ፡ፊት፡የታወቀ፡ተአምራት
ያደርጋሉ፡ይኸውም፡የተገለ
ጸ፡ስለ፡ሆነ፡እንሸሽገው፡ዘን
ድ፡አንችልም።ዮሐ፡፲፩፡፵፯
፲፯ ነገር፡ግን፡በሕዝቡ፡እጅግ፡
እንዳይወራ፡ለማገንም፡በኢ
የሱስ፡ስም፡እንዳይናገሩ፡አ
ጠንክረን፡እንገሥፃቸው፡ም
፲፰ ፭፡፳፰።ጠርተውም፡በኢየሱስ
ስም፡ፈጽመው፡እንዳይናገ
ሩ፡እንዳያስተምሩ፡አዘዝዋ
፲፱ ቸው።ጴጥሮስና፡ዮሐንስም
መልሰው፡አሉዋቸው፡እግዚአ
ብሔርን፡ከመስማት፡ይልቅ፡እ
ናንተን፡እንስማ፡ዘንድ፡በእግዚ
አብሔር፡ፊት፡ይገባልን፡እስቲ
እናንተው፡ፍረዱ።ም፡፭፡፳፱፡
፳ እኛስ፡ባየነውና፡በሰማነው፡ሁ
ሉ፡ዝምም፡እንል፡ዘንድ፡አይቻለ
፳፩ ንም።እነርሳቸው፡ግን፡እንደ፡
ምን፡ይሣቀይዋቸው፡ዘንድ፡
ምክንያት፡ባላገኙባቸው፡ጊዜ
አስፈራርተው፡ተዉዋቸው፡
ሕዝቡ፡በተደረገው፡ሥራ፡ሁሉ
እግዚአብሔርን፡አመስግነዋል
፳፪ ና።ይህም፡የሕይወት፡ተአም
ራት፡የተደረገለት፡ሰው፡ከአ
ርባ፡ዓመት፡ይበልጠው፡ነበረና።
፳፫ በተለቀቁም፡ጊዜ፡ወደ፡ባልንጀ
ሮቻቸው፡ሒደው፡የካህናት፡
አለቆችና፡ሽማግሌች፡ያሉ
ዋቸውን፡ሁሉ፡ነገርዋቸው።
፳፬ እነርሳቸውም፡ይህን፡በሰሙ፡ጊ
ዜ፡ቃላቸውን፡ወደ፡እግዚአብ
ሔር፡በአንድነት፡ከፍ፡ከፍ፡አደ
ረጉ፡አሉም፡ጌታ፡ሆይ፡አንተ፡
ሰማዩና፡ምድሩን፡ባሕሩንም
በእነርሳቸውም፡የሚኖረው
ን፡ሁሉ፡የፈጠርህ፡አምላክ፡ሆ
፳፭ ይ።በአገልጋይህ፡በአባታችን
በዳዊት፡አፍ፡በመንፈስ፡ቅዱ

ስ፡እንዲህ፡ብለህ፡የተናገርህ፡ አሕዛብ፡ለምን፡ተሰበሰቡ። ሕዝብም፡በከንቱ፡ተናገሩ፡መዝ ፪፡፩፡፪።

፳፮ የምድር፡ነገሥታት፡ተነሡ፡አለቆችም፡በእግዚአብሔርና፡በቀባው፡ላይ፡በአንድ፡ተከማቹ።

፳፯ በቀባኸውም በቅዱሱ፡ልጅህ፡በኢየሱስ፡ላይ፡ሄሮድስና፡የጳንጤናዊው፡ጲላጦስ ከአሕዛብና፡ከ፳ልም፡ወገን፡ጋራ፡በዚህ፡ከተማ፡በእውነት፡ተሰበሰቡ፤ ሉ፳፫፡፲፪።

፳፰ እጅህና፡ምክርህ፡ይደረግ፡ዘንድ፡የወሰነውን፡ሊፈጽሙ፤ ማ፪፡፳፫።

፳፱ አሁንም፡አቤቱ፡ወደ፡ቍጣቸው ተመልከት፡አገልጋዮችህም፡ቃልህን፡አከናውነው፡በድፍረት፡ይናገሩ፡ዘንድ፡ስጣቸው

፴ ኢሳ፡፯፡፲፬። በቅዱሱ፡ልጅህም በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስም፡ሕሙማንን፡ትፈውስና፡ተአምራትና፡ምልክትንም፡ታደርግ

፴፩ ዘንድ፡እጅህን፡ዘርጋ። ከጸለዩም፡በኋላ፡ተሰብስበው፡የነበሩበት፡ስፍራ፡ተናወጠ፡በሁሉም፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ሞላባቸው፡የእግዚአብሔርንም፡ቃል

፴፪ ገልጸው፡ተናገሩ። ያመኑትም ሁሉ፡አንድ፡ልብ፡አንዲትም፡ነፍስ፡ነበሩ፡ገንዘባቸውም፡በአንድነት፡ነበረ፡እንጂ፡ይህ፡የእኔ ገንዘብ፡ነው፡የሚል፡አንድ፡ስንኳ፡አልነበረም። ምዕ፪፡፵

፴፫ ፬። ሐዋርያትም፡የጌታችን የኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ትንሣኤ፡በታላቅ፡ኃይል፡ይመሰክሩ፡ነበሩ፡በሁሉም፡ዘንድ፡ታላቅ፡ጸጋ፡ነበራቸው። ም፡፪፡

፴፬ ፵፯። ከእነርሳቸውም፡አንድ፡ስንኳ፡ችግረኛ፡የለም፡ነበር ቤትም፡ርስትም፡ያላቸው፡ሁሉ፡እየሸጡ፡ዋጋውን፡ያመጡ

፴፭ ነበር። ም፡፪፡፵፭። በሐዋርያትም፡እግር፡አጠገብ፡ያስቀምጡ፡ነበር፡እርሳቸውም፡ለያንዳንዱ፡እንደ፡ፈቃዱ፡እንደ፡ፈቃዱ፡ይሰጡ፡ነበሩ። ዘዳግ፡፲፭

፴፮ ፲፬፡ኢሳ፡፶፰፡፯። በሐዋርያትም፡ዘንድ፡ትርጓሜው፡የመጽናናት፡ልጅ፡የሚሆን፡በርናባስ፡የተባለ፡ከሌዋዊ፡ወገን የሚሆን፡ስሙን፡ዮሴፍ፡የሚሉት፡አንድ፡የቆጵሮስ፡ሰው፡ነ

፴፯ በር። እርሻም፡ነበረውና፡ሸጠ ገንዘቡን፡አምጥቶ፡ከሐዋርያት፡እግር፡አጠገብ፡አኖረው።

ምዕራፍ፡፭።

ስለ፡ሐናንያና፡ስለ፡ሰጲራ፡ሞት፡በጴጥሮስ፡ጥላ፡ብዙ፡በሽተኞች፡እንደ፡ተፈወሱ፡ስለ፡ሐዋርያት፡መታሠር፡መልአክ፡ከግዞት፡ቤት፡እንዳወጣቸው፡በ

ቤተ፡መቅደስ፡ሲያስተምሩ፡
እንዳ፡ያዝዋቸው፡ከሰው፡ይል
ቅ፡ለእግዚአብሔር፡ማድላት፡
እንዲገባ፡ስለ፡ገማልያል፡ም
ክር፡ሐዋርያት፡ተገርፈው፡ደ
ስ፡እንዳ፡አላቸው።
፩ ስሙ፡ሐናንያ፡የሚሉት፡አን
ድ፡ሰው፡ነበረ፡የሚስቱም፡ስም፡
፪ ሰጲራ፡መሬቱንም፡ሸጠ። ከሚ
ስቱም፡ጋራ፡ተማክሮ፡ከዋጋው
ከፍሎ፡ሸሸገ፤እኩሌታውንም
አምጥቶ፡ከሐዋርያት፡እግር፡
በታች፡አኖረው። ፬፡፴፯፨
፫ ጴጥሮስም፡አለው፡ሐናንያ፡ሆ
ይ፡የመሬትህን፡ሸያጭ፡ዋጋ፡በ
መስረቅ፡መንፈስ፡ቅዱስን፡ታሳ
ብል፡ዘንድ፡እንዴት፡ሰይጣን፡በ
፬ ልብህ፡መላቀው፡ሐ፡፲፫፡፪፨ቀዋኘቱ
ን፡ሳትሸጠው፡የአንተ፡አልነበረ
ምን፡ይህን፡ነገር፡ስለምን፡በልብ
ህ፡አሰብህ፡እግዚአብሔርን፡እንጂ
፭ ሰውን፡አላታለልህም፨ሐናን
ያም፡ይህን፡ቃል፡በሰማ፡ጊዜ፡ወ
ደቀ፡ሞተም፡ይህንንም፡በሰሙ፡
፮ ሁሉ፡ታላቅ፡ፍርሃት፡ሆነ፨ጐበዛ
ዝትም፡ተነሥተው፡ከፈኑት፡አ
ውጥተውም፡ቀበሩት፨ዘሌ፡፲፬፡
፯ ፬፨ከዚህም፡በኋላ፡ሦስት፡ሰዓ
ት፡ያህል፡ሚስቱ፡የሆነችው፡ሳ
፰ ታውቅ፡ገባች፨ጴጥሮስም፡መ
ልሶ፡እስቲ፡ንገሪኝ፡መሬታችሁ
ን፡ይህን፡ለሚያህል፡ሸጣች
ሁን፡አላት፡እርስዋም፡አዎን
፱ እንዲሁ፡ነው፡አለች፨ጴጥሮ
ስም፡የእግዚአብሔርን፡መንፈ
ስ፡ትፈታተኑ፡ዘንድ፡በዚህ፡ሥ
ራ፡እንደምን፡ተባበራችሁ፡እ
ነሆ፡ባልሽን፡የቀበሩት፡ሰዎች
እግር፡በደጅ፡ነው፡አንችንም
፲ ያወጡሻል፡አላት፨ያንጊዜው
ንም፡ከእግሩ፡በታች፡ወደቀች
ሞተችም፡ጐበዛዝቱም፡በገቡ፡
ጊዜ፡ሙታ፡አገኛዋት፡ወሰደው
ም፡በባልዋ፡አጠገብ፡ቀበርዋት፨
፲፩ በቤተ፡ክርስቲያን፡ሁሉና፡ይህ
ንም፡በሰሙ፡ሁሉ፡ላይ፡ታላቅ
፲፪ ፍርሃት፡ሆነ፨በሐዋርያትም
እጅ፡ምልክት፡ተአምራትም፡
በሕዝብ፡መካከል፡እጅግ፡ይደ
ረግ፡ነበር፡ሁሉም፡በሰሎሞን፡
መሰል፡በአንድ፡ነበሩ፨፫፡፲፩
፲፫ ሕዝቡ፡እጅግ፡ያከብርዋቸው
ነበረ፡ከሌሎችም፡ይቀርባቸ
ው፡ዘንድ፡አንድ፡ስንኳ፡የሚደ
፲፬ ፍር፡አልነበረም፨በጌታም፡
የሚያምኑ፡ብዙ፡ወንዶችና፡ሴ
ቶች፡እጅግ፡ይበዙና፡ይጨም
ሩ፡ነበሩ፨ ፴፪፡፬፡፬
፲፭ ፮፡፯፨ጴጥሮስም፡ባለፈ፡ጊዜ፡
ከእርሳቸው፡በአንዱ፡ጥላው፡
ያርፍበት፡ዘንድ፡ድውያኑን፡በ
አልጋ፡በቃሬዛም፡እያመጡ፡በ

አደባባይ፡ያኖሩዋቸው፡ነበሩ
፲፮ ም፡፲፱፡፲፮፡፲፪፨በኢየሩሳሌም፡
ም፡ዙሪያ፡ካሉቸው፡ከተማ፡እጅ
ግ፡ሰዎች፡ይመጡ፡ነበሩ፡ድውያ
ኖችን፡ርኩስ፡ጋኔን፡የሚሠቃያ
ቸውን፡ያመጡ፡ነበሩ፡ሁሉም፡
፲፯ ይፈወሱ፡ነበሩ፨የካህናት፡አለ
ቃም፡ከእርሱ፡ጋራ፡ከነበሩት፡ከሰ
ዱቃውያን፡ወገን፡ጋራ፡ተነሣ፡ቅ
ንዓትም፡መሳባቸው፨ም፡፬፡፩
፲፰ ፲፪፨በሐዋርያትም፡ላይ፡እጃቸው
ን፡ዘርግተው፡ያዙዋቸው፡በሕ
ዝብም፡ግዞት፡ቤት፡አኖርዋቸ
፲፱ ው።የእግዚአብሔር፡መልአክ፡
ግን፡በሌሊት፡የግዞቱን፡ደጆች፡ከ
ፍቶ፡ከዚያ፡አወጣቸው፡አላቸ
፳ ውም፨ም፡፲፪፡፲፪፨ሒዱ፡በመቅ
ደስም፡ቁማችሁ፡ይህን፡የሕይወ
ቱን፡ቃል፡ለሕዝቡ፡ሁሉ፡ንገሩ፨
፳፩ ዮሐ፡፲፪፡፶፨በሰሙም፡ጊዜ፡እጅ
ግ፡ማልደው፡ወደ፡መቅደስ፡ገብተ
ው፡አስተማሩ፡የካህናት፡አለቃ
ና፡ከእርሱ፡ጋራ፡የነበሩት፡ግን፡ጉ
ባኤውንና፡ከ፳ልም፡ልጆች፡ወገ
ን፡ሽማግሌችን፡ሁሉ፡ሰበሰቡ
ያመጡዋቸውም፡ዘንድ፡ወደግ
፳፪ ዞት፡ቤት፡ላኩ፨ም፡፬፡፫፨ሎሌ፡ሎ
ቹም፡መጥተው፡በግዞት፡ቤት፡
አላገኙዋቸውም፡ወደ፡እነርሳቸ
ውም፡ተመልሰው፡እንዲህ፡ብለ
፳፫ ው፡ነገርዋቸው።የግዞቱ፡ቤት

በሁሉ፡በኩል፡ተዘግቶ፡በቍል
ፍም፡ተቈልፎ፡ጠባቂዎችም፡በ
ደጆ፡ፊት፡በስተውጭ፡ቆመው፡
አገኘነ፡በከፈትነውም፡ጊዜ፡
ውስጡ፡አንድ፡ሰንኳ፡አላገኘ[illegible]
፳፬ ም፨የመቅደሱ፡አለቃና፡የካ[illegible]
ናቱ፡አለቆችም፡ይህን፡ነገር፡[illegible]
ሙ፡ጊዜ፡እንጃ፡ምን፡ይሆን፡እ[illegible]
ሉ፡ሰለ፡እነርሱ፡የሚያደርጉ[illegible]
፳፭ ን፡አጡ፨አንድ፡ሰውም፡መጥ[illegible]
እነሆ፡እነዚያ፡በግዞት፡ቤት፡ያገ[illegible]
ችኋቸው፡ሰዎች፡እነርሳቸው[illegible]
መቅደስ፡ቆመው፡ሕዝቡን፡ያ[illegible]
፳፮ ተምራሉ፡ብሎ፡ነገራቸው፨በ[illegible]
ያ፡ጊዜም፡የመስጊዱ፡አለቃ፡ከ[illegible]
ሳሌቱ፡ጋራ፡ሔዶ፡አባብሎ፡አመ
ጣቸው፡በግድም፡አይደለም፡ሕ
ዝቡ፡እንዳይወግርዋቸው፡ይፈ
፳፯ ሩ፡ነበሩና፨ባመጧዋቸውም፡
ጊዜ፡በሸንጎው፡አቆሙዋቸው፡
የካህናቱም፡አለቃ፡ጠየቃቸው፡
፳፰ እንዲህ፡ሲል፡በዚህ፡ስም፡እንዳ
ታስተምሩ፡ቍርጥ፡አድርገን፡[illegible]
ልከለከልናችሁምን፤እነሆ፡ኢየ
ሩሳሌምን፡ፈጽማችሁ፡በትም[illegible]
ህርታችሁ፡መላችኋት፡የዚያ[illegible]
ም፡ሰው፡ደም፡በእኛ፡ታመጡ፡ብ[illegible]
ዘንድ፡ትሻላችሁ፨ም፡፬፡፲፰፡ማቴ
፳፱ ፳፯፡፳፭፨ጴጥሮስና፡ሐዋርያት
ም፡መለሰው፡አሉ፡ከሰው፡ይልቅ፡
እግዚአብሔርን፡እንሰማ፡ዘንድ፡

ይገባል፤ ም፡፩፡፲፱፡ ደግ፡፯፡፲ቀ
፴ እናንተ፡በእንጨት፡ላይ፡ሰቀ
ላችሁ፡የገደላችሁትን፡ኢየሱ
ስን፡የአባቶቻችን፡አምላክ፡አ
ስነሣው። ም፡፫፡፲፭ቃ ይህን፡እግ
ዚአብሔር፡ለ፳ሌ፡ንስሐን፡የኃ
ጢአትንም፡ሥርየት፡ይሰጥ፡ዘ
ንድ፡ራስም፡መድኃኒትም፡አድ
ርጎ፡በቀኙ፡አስቀመጠው፥ም፡፪፡
፴፪ ፴፫ እኛም፡በዚህ፡ነገር፡ለእርሱ
ምስክሮች፡ነን፡ደግሞም፡እግዚ
አብሔር፡ለሚታዘዙት፡የሚሰ
ጠው፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ምስክር
ነው። ሉ፡፳፬፡፵፰፡ዮሐ፡፲፭፡፳፮
፴፫ ፳፯ቀ ይህንን፡በሰሙ፡ጊዜ፡በ
ልባቸው፡ተቈጡ፡ሊገድሉዋቸ
፴፬ ውም፡አሰቡ ም፡፯፡፶፬ቀ በሸንጎ
ውም፡በሕዝቡ፡ሁሉ፡ዘንድ፡የከ
በረ፡የኦሪት፡መምህር፡ስሙን
ገማልያል፡የሚሉት፡አንድ፡ፈ
ሪሳዊ፡ተነሣ፡ሐዋርያትንም፡ጥ
ቂት፡ያስወጣዋቸው፡ዘንድ፡
፴፭ አዘዘ። ም፡፳፪፡፫ቀ አላቸውም
እናንተ፡የ፳ሌ፡ወገን፡ሰዎች፡በ
እነዚህ፡ሰዎች፡በምታደርጉት
ነገር፡ለራሳችሁ፡ተጠንቀቁ።
፴፮ ከዚህም፡ወራት፡አስቀድሞ፡ቴ
ዎዳስ፡ሰው፡ራሱ፡እኔ፡ታላቅ፡ነኝ
ብሎ፡ተነሥቶ፡ነበር፡አራት፡መ
ቶ፡የሚሆኑ፡ሰዎችም፡ተከተ
ሉት፡እርሱም፡ጠፋ፡የተከተ
ሉትም፡ሁሉ፡ተበተኑ፡እንደ፡ም
፴፯ ናምንም፡ሆኑ፥ ከዚያም፡በኋላ
ሰዎች፡ስለ፡ግብር፡በተጻፉበት
ዘመን፡የገሊላው፡ይሁዳ፡ተነሣ
እጅግ፡ሰዎችንም፡አስከትሎ፡ሳበ
እርሱም፡ጠፋ፡የታዘዙትም፡ሁ
፴፰ ሉ፡ተበተኑ፥ አሁንም፡እላችኋለ
ሁ፡ከእነዚህ፡ሰዎች፡ራቁ፡ተዉ
ዋቸውም፡ይህ፡ምክር፡ይህ፡ሥ
ራ፡ከሰው፡እንደ ሆነ፡ይጠፋል፤
፴፱ ማቴ፡፲፭፡፲፫ቀ ከእግዚአብሔር፡
እንደሆነ፡ግን፡ታፈርሱት፡ዘንድ
አይቻላችሁም፡ደግሞም፡ከ
እግዚአብሔር፡ጋራ፡ስትጣሉ
፵ እንዳትገኙ፥ም፡፱፡፭ቀ ምክሩ
ንም፡ሰሙት፡ሐዋርያትንም፡ጸ
ርተው፡ገረፉዋቸው፡በኢየሱስ
ም፡ስም፡እንዳያስተምሩ፡ነግረ
ው፡ለቀቁዋቸው፥ም፡፳፪፡፲፱፡
፵፩ እነርሳቸው፡ግን፡ስለ፡ስሙ፡ይና
ቁ፡ዘንድ፡ተገብቶዋቸዋልና፡ከ
ሸንጎው፡ፊት፡ደስ፡እያላቸው፡
ወጡ፥ማቴ፡፭፡፲፡፲፪፡፩፡ጴጥ፡፬፡፲፡
፵፪ ፲፫ቀ ሁልጊዜም፡በመቅደስና፡
በቤት፡ስለ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ
የምስራች፡ሲያስተምሩና፡ሲ
ሰብኩ፡አይለያዩም፡ነበረ።

ምዕራፍ፡፮።

ስለ፡ፅርዓውያን፡ስለ፡አይሁድ
መጣላት፤ ስለ፡፯ት፡ዲያቆናት፡
ስለ፡ሥራ፡መመረጥ፡በእስጢፋ

ኖስ፡እንጁ፡ተኒሡበቱ ፲

፩ በዚያቸም፡ወራት፡ደቀ፡መዛሙ
ርቱ፡በበዙ፡ጊዜ፡የዕርዕ፡ሰዎች
በአይሁድ፡እንጕርጕሩባቸው
የዕለት፡የዕለቱን፡ምጋብ፡ሲያ
ካፍሉ፡ባልቴቶቻቸውን፡ቸላ
ይሉባቸው፡ነበሩና፨ም፡፬፡፴፭

፪ አሥራ፡ሁለቱም፡ደቀ፡መዛሙር
ት፡ሁሉ፡ጸርተው፡አልዋቸው
የእግዚአብሔርን፡ቃል፡ትተን
ማዕድን፡እናገለግል፡ዘንድ፡የ

፫ ሚገባ፡ነገር፡አይደለም፨ወንድ
ሞቻችን፡ሆይ፡ከእናንተ፡ወገን
በመልካም፡የተመሰከረላቸውን፡መንፈስ፡ቅዱስና፡ጥበብም
የሞላባቸውን፡፯ት፡ሰዎች፡መ
ርጡቸሁ፡ለዚህ፡ስራ፡እንሹም

፬ ፩ጢሞ፡፩፡፫፡፯፡፲፫፨እኛ፡ግን፡ጸ
ሎትንና፡ቃሉን፡ማስተማርን

፭ እናስታጕልም፨ይህም፡ነገር፡
በማኅበሩ፡ሁሉ፡ፊት፡ተወደደ
ሃይማኖትና፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ሰ
ም፡የመላበትን፡ሰው፡እስጢፋ
ኖስን፡ፊልጶስንም፡ጵርኮሮ
ስንም፡ኒቃሮናንም፡ጢሞንን
ም፡ጳርሜናንም፡ከአረማዊነ
ት፡ወደ፡አይሁዳዊነት፡የተመ
ለሰው፡የአንፆኪያውን፡ኒቆላ

፮ ዎስንም፡መረጡ፨በሐዋርያ
ትም፡ፊት፡አቆምዋቸው፡በጸ
ሰዩም፡ጊዜ፡እጃቸውን፡ጫኑ

፯ ባቸው፨ም፡፩፡፳፬፨የእግዚአ
ብሔርም፡ቃል፡እየሰፋ፡ሔደ፡በኢ
የሩሳሌምም፡የደቀ፡መዛሙ
ርት፡ቍጥር፡እጅግ፡በዛ፡ከካህ
ናትም፡ወገን፡እጅግ፡ሰዎች፡ለ
ሃይማኖት፡የታዘዙ፡ሆኑ፨ም፡

፰ ፲፱፡፳፨እስጢፋኖስ፡ግን፡ሃይ
ማኖትንና፡ኀይልን፡ተመልቶ
ነበርና፡በሕዝቡ፡ፊት፡ተአምራ
ትንና፡ታላቅ፡ምልክትን፡ያደር

፱ ግ፡ነበረ፨ሊቤርጢኖንም፡ከ
ምትባል፡መስጊድ፡ከቂሬኔዎ
ንም፡ከእስክንድርያም፡ከቂሊ
ቂያም፡ወገን፡ከእስያም፡ሰዎ
ች፡ተነሥተው፡እስጢፋኖስን

፲ ይከራከሩት፡ነበሩ፨ጥበብና፡
መንፈስንም፡ተመልቶ፡ይናገ
ራቸው፡ነበርና፡ይቋቋሙት፡
ዘንድ፡አልቻሉም፨ሉ፡፳፩፡፲፭

፲፩ በዚያ፡ጊዜም፡በሙሴ፡ላይ፡በእ
ግዚአብሔርም፡ላይ፡የስድብን
ነገር፡ሲናገር፡እኛ፡ሰማነው፡
የሚሉ፡የሐሰት፡ምስክሮችን፡

፲፪ አባበሉ፨ማቴ፡፳፮፡፶፱፨ሕዝበ
ንና፡ሽማግሌዎችን፡ጻፎችንም
አስነሥተው፡ይዘው፡እየጐተቱ

፲፫ ወደ፡ሸንጎ፡አቀረቡት፨የሐሰት
ምስክሮችም፡አስነሡበት፡እ
ንዲህ፡የሚሉ፡ይህ፡ሰው፡በዚህ
በተቀደሰው፡ስፍራ፡በአሪት
ም፡የስድብን፡ነገር፡ለመናገር

፲፬ አያርፍም፤ ኤር፡ ፳፮፡ ፲፩። የና
ዝሬቱም፡ ኢየሱስ፡ ይህን፡ ቤተ
መቅደስ፡ ያፈርሰዋል፡ ሙሴ
ም፡ የሰጠንን፡ ሕግ፡ ይለውጣል፡
ሲል፡ ሰምተነዋል። በሸንጎር
ም፡ የተቀመጡት፡ ሁሉ፡ ትኩ
ር፡ ብለው፡ ተመለከቱት፡ ፊቱ
ም፡ እንደ፡ መልአክ፡ ፊት፡ ሆኖ፡
ታያቸው። ምዕራፍ፡ ፯።

እስጢፋኖስን፡ ሊቀ፡ ካህናቱ፡ እን
ደ፡ ጠየቀው፡ ስለ፡ እስጢፋኖስ፡
ስብከት፡ ሕዝቡ፡ እንዴ፡ ተቈጡ
ት፡ የእግዚአብሔርን፡ ክብር
እንደ፡ አየ፥ እንዴ፡ ገደሉት።

፩ የካህናቱ፡ አለቃም፡ በውኑ፡ ይህ፡
ነገር፡ እንዲህ፡ ነውን፡ አለው።
፪ እርሱም፡ አለ፡ እናንተ፡ ሰዎች፡
አባቶቻችን፡ ወንድሞቻችን
ም፡ ስሙ። የምስጋና፡ አምላክ፥
ለአባታችን፡ ለአብርሃም፡ ገና፥
ወደ፡ ካራን፡ ሳይመጣ፡ በሜስጶታ
ሚያ፡ ምድር፡ ሳለ፡ ተገለጠለት
፫ ዘፍ፡ ፲፩፡ ፴፩፡ ፲፪፡ ፩። ከሀገርህ፡
ከዘመዶችህም፡ ወጥተህ፡ እኔ፡
ወደ፡ እማሳይህ፡ ምድር፡ ና፡ አለ
፬ ው። ዘፍ፡ ፲፩፡ ፭፡ ፲፪፡ በዚያ፡ ጊዜ፡ ከከ
ለዳውያን፡ አገር፡ ወጥቶ፡ በካራ
ን፡ ተቀመጠ፡ በዚያም፡ አባቱ፡ ከ
ሞተ፡ በኋላ፡ እናንተ፡ ዛሬ፡ ወደ፡
አላችሁባት፡ ወደዚች፡ አገር፡ አ
፭ ወጣው። ከዚችም፡ የእግር፡ ጫ
ማ፡ ስንኳ፡ የምታህል፡ ርስት፡
አልሰጠውም፥ ነገር፡ ግን፡ ያን፡
ጊዜ፡ ልጅ፡ ሳይኖረው፡ ለእርሱ
ከእርሱም፡ በኋላ፡ ለዘሩ፡ ይህ
ችን፡ ምድር፡ ያወርሰው፡ ዘንድ
ተስፋ፡ ሰጠው። ዘፍ፡ ፲፪፡ ፯። እ
፮ ግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፡ ዘ
ሮችህ፡ በሌላ፡ አገር፡ ስደተኞች
ይሆናሉ፡ አራት፡ መቶ፡ ዓመት
ም፡ ባሮች፡ ያደርጓቸዋል፡ ያ
ስጨንቋቸዋልም። ዘፍ፡ ፲፭፡
፯ ፲፫። ዘፀ፡ ፲፪፡ ፵። ባሮችም፡ የሚ
ያደርጓቸውን፡ ሕዝብ፡ እኔ፡ እ
ፈርድባቸዋለሁ፡ ከዚህ፡ በኋላ
ይወጣሉ፡ በዚህም፡ ስፍራ፡ ይገ
፰ ዙልኛል። የግዝረትንም፡ ኪዳ
ን፡ ሰጠው፡ እንዲሁም፡ አብርሃ
ም፡ ይስሐቅን፡ ወለደ፡ በስምንተ
ኛውም፡ ቀን፡ ገዘረው፡ ይስሐቅ
ም፡ ያዕቆብን፡ ያዕቆብም፡ አስ
ራ፡ ሁለቱን፡ የአባቶች፡ አለቆ
ች። ዘፍ፡ ፲፯፡ ፱፡ ፳፩፡ ፳፫፡ ዘፍ፡ ፳፭፡ ዘፍ፡ ፲፱፡ ፲፡
ዘፍ፡ ፴፭፡ ፪፡ ዘፍ፡ ፴፭፡ ፳፬።
፱ የአባቶች፡ አለቆች፡ በዮሴፍ
ቀንተው፡ ወደ፡ ምስር፡ ሰጡት፤
እግዚአብሔርም፡ ከእርሱ፡ ጋራ
፲ ነበረ፡ ዘፍ፡ ፴፯፡ ፳፰፡ ከመከራ
ውም፡ ሁሉ፡ አዳነው፡ በምስር፡
ንጉሥ፡ በፈርዖንም፡ ፊት፡ ባለ
ሞገስነትንና፡ ጥበብን፡ ሰጠው
እርሱም፡ በምስርና፡ በቤቱ፡ ሁ

ሎ፡ ሳይ፡ ቢቱ ወደዱ፡ አደረገው።
፲፩ ዘፍ፡ ፵፩፡ ፶፬፡ ፶፯ ❖ በምስር፡ አ
ገርና፡ በከነዓን፡ ምድር፡ ሁሉ፡ ራብ
ና፡ ብዙ፡ ጭንቅ፡ ሆነ፡ አባቶቻች
ንም፡ የሚመገቡትን፡ አጡ ❖
፲፪ ያዕቆብም፡ በምስር፡ እህል፡ መ
ኖሩን፡ በሰማ፡ ጊዜ፡ በመጀመሪ
ያ፡ አባቶቻችንን፡ ሰደዳቸው ❖
፲፫ ዘፍ፡ ፵፪፡ ፩ ❖ በሁለተኛውም፡ ዮ
ሴፍን፡ ወንድሞቹ፡ አወቁት፡ የ
ዮሴፍም፡ ትውልዱ፡ በፈርዖን
ዘንድ፡ የታወቀ፡ ሆነ ❖ ዘፍ፡ ፵፭፡
፲፬ ፬ ❖ ዮሴፍም፡ አባቱን፡ ዘመዶ
ቹን፡ ሁሉ፡ ልኮ፡ ጠራቸው፡ ቁጥ
ራቸውም፡ ፸፭ ት፡ ነፍስ፡ ነበረ።
፲፭ ዘፍ፡ ፵፯፡ ፪፡ ፲ ❖ ያዕቆብም፡ ወ
ደ፡ ምስር፡ ወረደ፡ እርሱም፡ ሞተ
አባቶቻችንም ❖ ዘፍ፡ ፵፯፡ ፩፡ ፵
፲፮ ፱፡ ፵፫። ወደ፡ ሴኬምም፡ አፍል
ሰው፡ አብርሃም፡ ከሴኬም፡ አባ
ት፡ ከኤሞር፡ ልጆች፡ በገንዘቡ፡
በገዛው፡ መቃብር፡ ቀበርዋቸ
ው ❖ ዘፍ፡ ፳፫፡ ፲፯፡ ፲፯፡ ኢያሱ፡ ፳፬
፲፯ ፴፪ ❖ እግዚአብሔርም፡ ለአብር
ሃም፡ የማለለት፡ የተስፋው፡
ዘመን፡ በቀረበ፡ ጊዜ፡ ሕዝቡ፡ በ
ዝተው፡ ምስርን፡ ሞሉ ❖ ዘፀ፡ ፩
፲፰ ፯ ❖ በምስር፡ ዮሴፍን፡ የማያው
ቀው፡ ሌላ፡ ንጉሥ፡ እስኪነሣ፡ ድ
፲፱ ረስ ❖ ይህም፡ በዘመዶቻችን፡ ተ
ተናኰሎ፡ ወንዶች፡ ልጆቻቸው
እንዳያድጉ፡ በወንዝ፡ ይጣሉ፡
ዘንድ፡ አዘዘ፡ በአባቶቻችንም
ላይ፡ ክፉ፡ ሠራ ❖ ዘፀ፡ ፩፡ ፳፪፡
፳ በዚያም፡ ጊዜ፡ ሙሴ፡ ተወለደ
በእግዚአብሔርም፡ ዘንድ፡ የ
ወደደ፡ ሆነ፡ በአባቱ፡ ቤትም፡ ሶ
ት፡ ወር፡ ኖረ። ዘፀ፡ ፪፡ ፪፡ ዕብ፡ ፲
፳፩ ፳፫ ❖ በተጣለም፡ ጊዜ፡ የፈርዖ
ልጅ፡ አንሥታው፡ ልጅም፡ ይሆ
ዘንድ፡ አሳደገችው ❖ ዘፀ፡ ፪፡
፳፪ ሙሴም፡ የግብፃችን፡ ሁሉ፡ ጥ
ብ፡ ተማረ፡ በነገሩና፡ በሥራው
ም፡ የበረታ፡ ሆነ ❖ አርባ፡ ዓ
ትም፡ ሲሞላው፡ ወንድሞቹ
የ፳ልን፡ ልጆች፡ ይጐበኝ፡ ዘንድ
በልቡ፡ አሰበ ❖ ዘፀ፡ ፪፡ ፲፩ ❖
፳፫ ግፍ፡ የተደረገበትንም፡ አንድ
ሰው፡ ባየ፡ ጊዜ፡ ለተገፋው፡ ረ
ው፡ ግብፃዊውን፡ ገደለው፡ በአ
፳፬ ሸዋም፡ ውሥጥ፡ ደፈነው። እ
ሱም፡ እግዚአብሔር፡ በእጁ፡ መ
ኃኒትን፡ እንዲሰጣቸው፡ ወን
ድሞቹ፡ የሚያውቁ፡ ይመስለ
ው፡ ነበረ፡ እነርሱ፡ ግን፡ አላ
፳፭ ስተዋሉትም ❖ በማግሥቱ
ም፡ ከእነርሱ፡ ሁለቱ፡ እርስ፡ በእ
ርሳቸው፡ ሲጣሉ፡ አገኛቸው፡
ሊያስታርቃቸውም፡ ወዶ፡ እና
ንተ፡ ሰዎች፡ እናንተስ፡ ወንድሞ
ማች፡ ናችሁ፡ ለምን፡ እርስ፡ በእ
ርሳችሁ፡ ትጣላላችሁ፡ አላቸ

ዘነው ። ያም ፡ ባልንጀራውን ፡ የሚ
በድል ፡ ገፋው ፡ እንዲሁ ፡ ሲል ፡ አ
ግቶቹ ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ አለቃና ፡ ፈራ
ጅ ፡ አድርጎ ፡ የሾመህ ፡ ማነው ፧
፳፰ ወይስ ፡ ትናንትና ፡ ግብጻዊውን
ን ፡ እንደ ፡ ገደልኸው ፡ ልትገድለ
፳፱ ኝ ፡ ትወዳለህን ፧ ፡ ሙሴ
ም ፡ ከዚህ ፡ ነገር ፡ የተነሣ ፡ ሸሽቶ
በምድያም ፡ አገር ፡ ስደተኛ ፡ ሁ
ኖ ፡ ኖረ ፡ በዚያም ፡ ሁለት ፡ ልጆች
፴ ን ወለደ ፨ ዘፀ ፡ ፪ ፡ ፲፭ ፨ አርብዓ ፡ ዓ
መትም ፡ ሲፈጸም ፡ የእግዚአብ
ሔር ፡ መልአክ ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ም
ድረ ፡ በዳ ፡ በእሾኁም ፡ ቍጥቋጦ
መካከል ፡ በእሳት ፡ ነበልባል ፡ ተ
ገለጠለት ፨ ዘፀ ፡ ፫ ፡ ፪ ፡ ዘዳግ ፡ ፴፫
፴፩ ፲፮ ፨ ሙሴም ፡ ይህን ፡ ድንቅ ፡ አይ
ቶ ፡ ተገረመ ፡ ቀርቦም ፡ ሲመለ
ከት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ
፴፪ እርሱ ፡ መጣ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ እኔ
የአባቶችህ ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፡ የአብ
ርሃም ፡ አምላክ ፡ ይስሐቅም
አምላክ ፡ የያዕቆብም ፡ አምላክ
ሙሴም ፡ ተንቀጠቀጠ ፡ ሲመለ
ከትም ፡ አልደፈረም ። ዘፀ ፡ ፫ ፡ ፮
፴፫ እግዚአብሔርም ፡ አለው ፡ እንተ
የቆምህባት ፡ ስፍራ ፡ የተቀደ
ሰች ፡ ምድር ፡ ናትና ፡ የእግርህ
፴፬ ን ፡ ጫማ ፡ አውልቅ ፨ በግብፅ ፡
ያሉትን ፡ የወገኖቼን ፡ መከራ ፡ ፈ
ጽሜ ፡ አየሁ ፡ ኃዘናቸውንም ፡
ሰምቼ ፡ ላድናቸው ፡ ወረድሁ ፡
አሁንም ፡ ና ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ እልክሃ
፴፭ ለሁ ፨ አለቃና ፡ ፈራጅ ፡ አድርጎ
በእኛ ፡ ላይ ፡ የሾመህ ፡ ማነው ፧ ብ
ለው ፡ የካዱትን ፡ ይህነን ፡ ሙሴ
ን ፡ በቍጥቋጦ ፡ በታየው ፡ በመ
ልአኩ ፡ እጅ ፡ እግዚአብሔር ፡ አለ
ቃም ፡ መድኃኒትም ፡ አድርጎ ፡ ሰ
፴፮ ደደው ፡፡ ዘፀ ፡ ፬ ፡ ፲፬ ፨ እርሱም ፡ በ
ግብፅ ፡ ምድር ፡ በኤርትራ ፡ ባሕ
ርም ፡ በምድረ ፡ በዳም ፡ አርብዓ
ዓመት ፡ ተአምራትና ፡ ምልክት
እያደረገ ፡ አወጣቸው ፨ ዘፀ ፡ ፯ ፡ ፲
፴፯ ፲፬ ፡ ፳፩ ፨ ለ፳ልም ፡ ልጆች ፡ እግዚ
አብሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ከወንድ
ሞቻችሁ ፡ እንደኔ ፡ ያለ ፡ ነቢይ ፡ ያ
ስነሣላችኋል ፡ እነርሱም ፡ ሰሙ
ት ፡ ያላቸው ፡ ይህ ፡ ሙሴ ፡ ነው ፨
፴፰ በደብረ ፡ ሲና ፡ ከተናገረው ፡ መ
ልአክና ፡(ከአባቶ)፡ ከአባቶቻች
ን ፡ ጋራ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በማኅበ
ሩ ፡ ውሥጥ ፡ የነበረ ፡ ይሰጠንም
ዘንድ ፡ ሕያው ፡ የሆነውን ፡ ቃል ፡
የተቀበለ ፡ ይህ ፡ ነው ፨ ዘፀ ፡ ፲፱ ፡ ፫
፴፱ አባቶቻችን ፡ ይሰሙት ፡ ዘን
ድ ፡ አልወደዱም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እ
ንቢ ፡ አሉት ፡ በልባቸውም ፡ ወ
፵ ደ ፡ ግብፅ ፡ ተመለሱ ፨ አሮንንም
በፊታችን ፡ የሚሔዱ ፡ አማልክ
ት ፡ ሥራልን ፡ ይህ ፡ ከግብፅ ፡ ም
ድር ፡ ያወጣን ፡ ሙሴ ፡ የሆነውን

እናውቅምና፡አሉት፡ዘፀ፡፴፪፡
፵፩ ፩፡፬። በዚያም፡ወራት፡ጥጃ፡አ
ደረጉ፡ለጣዖቱም፡መሥዋዕት
አቀረቡ፡በእጃቸውም፡ሥራ፡ደ
፵፪ ስ፡አላቸው፤እግዚአብሔርም፡ከ
ነርሳቸው፡ራቀ፡የሰማይንም፡
ሠራዊት፡ያመልኩ፡ዘንድ፡አሳል
ፎ፡ሰጣቸው፡በነቢያት፡መጽሐ
ፍ፡እንደ፡ተጻፈ፡እናንተ፡የ፳ል፡
ቤት፡በውኑ፡አርባ፡ዓመት፡ሙ
ሉ፡በምድረ፡በዳ፡መሥዋዕት፡ወ
ይም፡ቍርባን፡አቀረባችሁልኝ
ን፤ኤር፡፲፱፡፲፫፡ ም፡፭፡፳፭፡፳፮።
፵፫ ተሰግዳችሁለትም፡ዘንድ፡የሠራችሁ
ትን፡የሞሎክን፡ድንኳንና፡ሬ
ምፋን፡የሚሉትን፡የአምላካችሁ
ን፡ኮከብ፡ምስል፡ወሰዳችሁ፡እኔ
ም፡ከባቢሎን፡ወዲያ፡አሰዳችኋ
፵፬ ለሁ። ሙሴንም፡የተናገረው፡
ያየውን፡አስመስሎ፡ይሠራት፡
ዘንድ፡ያዘዘው፡የምስክር፡ድን
ኳን፡ከአባቶቻችን፡ጋራ፡በምድ
ረ፡በዳ፡ነበረች። ዘፀ፡፳፭፡፵፡ዕብ፡፰፡
፵፭ ፭። አባቶቻችንም፡ተቀብለው
ከኢያሱ፡ጋራ፡ከአባቶቻችን፡ፊ
ት፡ወደ፡አወጣቸው፡አሕዛብ፡አገ
ር፡ይዞዋት፡ገቡ፡እስከ፡ዳዊት፡
፵፮ ዘመን፡ድረስ። ኢያ፡፫፡፲፬። ዳዊት
ም፡በእግዚአብሔር፡ፊት፡ሞ
ገስ፡አገኘ፤የያዕቆብ፡አም
ላክ፡ማደርያ፡ያገኝ፡ዘንድ፡ለመ
ነ። ፪፡ሳሙ፡፯፡፪፡መዝ፡፻፴፪፡፭።
፵፯ ነገር፡ግን፡ሰሎሞን፡ቤት፡ሠራለ
፵፰ ት። ፩ነገ፡፮፡፩። ነገር፡ግን፡ልዑ
ል፡በሰው፡እጅ፡በሠራው፡ቤት፡አይ
፵፱ ኖርም፡ነቢዩ፡እንዳለ፡ሰማ
ይ፡ዙፋኔ፡ነው፡ምድርም፡የእግ
ሬ፡መርገጫ፡ናት፡የምትሠሩልኝ፡ቤት
እንዴት፡ያለ፡ነው፡ይላል፡እግዚአ
ብሔር፡የማርፍበትስ፡ስፍራ፡
፶ ወይ። ኢሳ፡፷፮፡፩። ይህን፡ሁ
ሉ፡እጄ፡የሠራው፡አይደለምን፡
፶፩ እናንተ፡አንገተ፡ደንዳኖች፡ል
ባችሁና፡ጆሮዋችሁም፡ያል
ገዘረ፡እናንተም፡ደግሞ፡እ
አባቶቻችሁ ሁልጊዜ፡መ
ፈስ፡ቅዱስን፡ትቃወሙታላ
፶፪ ሁ። ዘፀ፡፴፪፡፱። ከነቢያት፡ስ
ቶቻችሁ፡ያላሳደዱት፡ማን፡ነ
ዘሬም፡እናንተ፡አሳልፋችሁ፡
የሰጣችሁትን፡የገደላችሁት
ንም፡የጻድቁን፡መምጣት፡አስ
ቀድመው፡የተናገሩትን፡ገደሉ
ዋቸው። ፪ዜና፡፴፮፡፲፮፡ማቴ፡፳
፶፫ ፫፡፴፩። በመላእክትም፡ሥርዓት
ሕግን፡ተቀብላችሁ፡አልጠበቃ
ችሁትም። ዘፀ፡፳፡፩፡ገላ፡፫፡፲፱፡ዕብ
፶፬ ፪፡፪። ይህንንም፡በሰሙ፡ጊዜ፡በ
ልባቸው፡ተናደዱ፡ጥርሳቸውን
፶፭ ም፡አፋጩበት። ምዕ፡፭፡፴፫። በእ
ስጢፋኖስ፡ሳይ፡መንፈስ፡ቅዱስ
መላ፡ወደ፡ሰማይም፡ሲመለከት

የእግዚአብሔርን፡ክብር፡ኢ
የሱስንም፡በእግዚአብሔር፡ቀ
ኝ፡ቁሞ፡አየ፨እነሆም፡ሰማዮች
[ን]፡ከፍተው፡የሰው፡ልጅም፡በእ
[ግ]ዚአብሔር፡ቀኝ፡ቁሞ፡አያለ[ሁ]
[አለ]፡እሉ፨እነርሳቸውም፡በታላቅ
ቃል፡ጮሁ፡ጆሮዋቸውንም፡ያፈ
ኑ፡በአንድነትም፡ተነሥተው፡ከ
በቡት፨ምን፡፳፬፡፶፨ከከተማም
[ወ]ደ፡ውጭ፡ጐትተው፡አውግ ተ
ው፡ወገሩት፡ምስክሮችም፡ል
ብሳቸውን፡ስሙ፡ሳውል፡በሚ
ባሉት፡በአንድ፡ጐበዝ፡እግር፡አጠ
ገብ፡አኖሩ፨እስጢፋኖስንም፡ኢ
የሱስ፡ሆይ፡ነፍሴን፡ተቀበል፡እ
ያለ፡ሲጸልይ፡ወገሩት፨ሉ፡፳፫
፵፮፡መዝ፡፴፩፡፭፨በጕልበቱ
ም፡ተበርክኮ፡አቤቱ፡ይህችን፡
ኃጢአት፡አትቍጠርባቸው፡ብ
ሎ፡በታላቅ፡ቃል፡ጮኸ፡ይህን
ም፡ብሎ፡አንቀላፋ፡ሳውልም
እርሱን፡ለመግደል፡ከእነርሳቸ
ው፡ጋራ፡አብሮ፡ነበረ፨ሉ፡፳፫፡
፴፬፡፡ም፡፳፪፡፳፨

ምዕራፍ፡፰።

ስለ፡ምእመናን፡ስደት፡ስለ፡እስ
ጢፋኖስ፡መቀበር፡ስለ፡ፊልጶስ
ስብከት፤በሰማርያ፡ስለ፡ሲሞ
ን፡መሠርይ፤ስለ፡ሰማርያ፡ሰዎ
ች፤መንፈስ፡ቅዱስን፡መቀበል፤
ሲሞን፡መንፈስ፡ቅዱስን፤በገ
ንዘብ፡ለመግዛት፡እንደ፡አሰበ
ስለ፡ፊልጶስና፡ስለ፡አንድ፡ኢ
ትዮጵያዊ፨

፩ በዚያችም፡ወራት፡በኢየሩሳ
ሌም፡ባለች፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ላ
ይ፡ታላቅ፡ስደት፡ሆነ፡ከሐዋር
ያትም፡በቀር፡ሁሉ፡ወደ፡ይሁ
ዳ፡አገርና፡ወደ፡ሰማርያ፡ተበ
፪ ተኑ፨ምን፡፲፩፡፲፱፡እስጢፋኖስን
ም፡እግዚአብሔርን፡የሚፈሩ
ሰዎች፡አንስተው፡ቀበሩት፡ታ
ላቅ፡ልቅሶም፡አለቀሱለት፨
፫ ማቴ፡፲፬፡፲፪፨ሳውል፡ግን፡ቤተ
ክርስቲያንን፡ያፈርስ፡ነበር፡
ወደ፡ሁሉም፡ቤት፡እየገባ፡ወን
ዶችንም፡ሴቶችንም፡እየጐተ
ተ፡ወደ፡ግዞት፡ይጨምራቸው
ነበር፨ምን፡፱፡፩፡፳፪፡፬፨
፬ የተበተኑት፡ግን፡እየዞሩ፡የወ
ንጌልን፡የምስራች፡ቃል፡ይሰ
፭ ብኩ፡ነበር፨ፊልጶስም፡ከሰማ
ርያ፡አገሮች፡ወደ፡አንዲቱ፡ወ
ርዶ፡ክርስቶስን፡ሰበካላቸው
፮ ም፡፳፪፡፳፫፨ሕዝቡም፡ሁሉ፡ያደ
ርጋት፡የነበረውን፡ተአምራት
በሰሙና፡ባዩ፡ጊዜ፡በአንድ፡ል
ብ፡የፊልጶስን፡ነገር፡ተቀበሉ፤
፯ በብዙ፡ሰዎች፡ላይም፡የነበሩ
ርኩሳን፡አጋንንት፡በታላቅ፡ቃ
ል፡እየጮሁ፡ከእነርሳቸው፡ወ
ጡ፡ብዙ፡ሽባዎችና፡አንካሶች

፰ ተፈወሱ። ማቴ፡፲፪፡፲፪ቀበዚያ
ችም፡ አገር፡ ታላቅ፡ ደስታ፡ ሆነ፡
፱ ዮሐ፡ ፬፡ ፵፯ቀስሙንም፡ ሲሞን፡ የ
ሚሉት፡ አንድ፡ ጠንቋይ፡ ሰው።
በዚያች፡ አገር፡ ነበረ፡ እኔ፡ ታላ
ቅ፡ ነኝ፡ በማለቱም፡ የሰማርያን
፲ ሕዝብ፡ ያታልላቸው፡ ነበረቀከ
ታናናሾቹም፡ ጀምሮ፡ እስከ ታ
ላላቆቹ፡ ድረስ፡ ታላቁ፡ የእግዚ
አብሔር፡ ኃይል፡ ይህ፡ ነው፡ እያ
፲፩ ሉ፡ ይታዘዙለት፡ ነበሩቀከብዙ
ዘመንም፡ ጀምሮ፡ በአስማቱ፡
ያታልላቸው፡ ስለ፡ ነበረ፡ እጅግ
፲፪ ይከተሉት፡ ነበሩቀነገር፡ ግን፡
ፊልጶስ፡ ስለ፡ እግዚአብሔር፡
መንግሥትና፡ ስለ፡ ኢየሱስ፡ ክር
ስቶስ፡ ሲሰብክላቸው፡ ባመኑ፡ ጊ
ዜ፡ ሴቶቹም፡ ወንዶቹም፡ ተጠ
፲፫ መቁ። ማቴ፡ ፳፰፡ ፲፱ቀሲሞንም
ደግሞ፡ ራሱ፡ አመነ፡ ተጠመቀ፡
ፊልጶስንም፡ አይለየውም፡ ነበ
ርና፡ በእጁ፡ የሚደረገውን፡ ም
ልክቶችና፡ ታላቅ፡ ኃይል፡ ባየ፡ ጊ
፲፬ ዜ፡ ተደነቁቀበኢየሩሳሌም፡ የ
ነበሩ፡ ሐዋርያት፡ የሰማርያ፡
ሰዎች፡ የእግዚአብሔርን፡ ቃል
እንደ፡ ተቀበሉ፡ ሰምተው፡ ጴጥ
ሮስንና፡ ዮሐንስን፡ ሰደዱላቸው።
፲፭ እነርሱም፡ በገቡ፡ ጊዜ፡ መ
ንፈስ፡ ቅዱስን፡ ይቀበሉ፡ ዘንድ፡
፲፮ ጸለዩላቸውቀበጌታችን፡ በኢ
የሱስ፡ ስም፡ ብቻ፡ ተጠምቀ
ነበሩ፡ እንጂ፡ ከእነርሳቸው
አንዱ፡ ስንኳ፡ ገና፡ አልወረደ
፲፯ ነበረናቀበዚያ፡ ጊዜም፡ እጃ
ውን፡ ጫኑባቸው፡ መንፈስ፡ ቅ
፲፰ ዱስንም፡ ተቀበሉቀሲሞንም
በሐዋርያት፡ እጅ፡ መጫን፡
ንፈስ፡ ቅዱስ፡ እንዲሰጥ፡ ባየ፡ ጊ
ዜ፡ ገንዘብ፡ አመጣላቸው፡ እ
፲፱ ዲህ፡ ሲል፡ እጄን፡ የምጭ
ኑት፡ ሁሉ፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡
በል፡ ዘንድ፡ ለእኔም፡ ደግሞ፡
፳ ህኝ፡ ሥልጣን፡ ስጡኝ፤ ጴጥ
ም፡ አለው፡ የእግዚአብሔር
ጸጋ፡ በገንዘብ፡ ልትገዛው፡
ብሃልና፡ ገንዘብህ፡ ከአንተ፡
፳፩ ይጥፋልብህም፡ በእግዚአ
ሔር፡ ፊት፡ የቀና፡ አይደለም
ከዚህ፡ ነገር፡ ክፍል፡ ወይም፡
፳፪ ጣ፡ የለህምቀስለዚህም፡ ከ
ህ፡ ከክፋትህ፡ ተመለስ፡ ምናል
ባትም፡ የልብህን፡ አሳብ፡ ይቅ
ር፡ ይልህ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ወደ፡ እግዚ
፳፫ አብሔር፡ ለምንቀበመራራ፡ መ
ርዝና፡ በዓፍ፡ መታሠር፡ እንደ
፳፬ አለህ፡ አይሃለሁናቀሲሞንም
መልሶ፡ እናንተ፡ ካላችሁት፡ ሁ
ሉ፡ አንዳች፡ እንዳይደርስብኝ
እናንተው፡ ወደ፡ እግዚአብሔር
፳፭ ለምኑልኝ፡ አላቸውቀእነርሳ
ውም፡ እየመሰከሩ፡ የእግዚአብ

ብሔርን፡ ቃል፡ ነግሬው፡ ወደ ኢየሩሳሌም፡ ተመለሱ፡ በሰማርያም፡ በብዙ፡ መንደሮች ወንጌልን፡ አስተማሩ። የእግዚአብሔርም፡ መልአክ፡ ፊልጶስን፡ በደቡብ፡ በኩል፡ ከኢየሩሳሌም፡ ወደ፡ ጋዛ፡ በምታወርደው፡ መንገድ፡ ምድረ፡ በዳ፡ ወደሆነች፡ ተነሣና፡ ሒድ፡ አለው። ተነሥቶም፡ ሔደ፡ እነሆም፡ የህንደኬ፡ የኢትዮጵያ፡ ንግሥተ ጃንደረባ፡ ከሹማምቶቹዋ፡ የበለጠ፡ በንዘብዋም፡ ሁሉ፡ የሰለጠነ፡ አንድ፡ የኢትዮጵያ ሰው፡ ነበረ፡ ይህም፡ ሊሰግድ፡ ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡ መጥቶ ሲመለስም፡ በሠረገላ፡ ተቀምጦ፡ የነቢዩ፡ የኢሳይያስ፡ መጽ

፳፱ ሐፍ፡ ያነብ፡ ነበር። መንፈስ፡ ቅዱስም፡ ፊልጶስን፡ ሒደህ፡ ወደዚህ፡ ሠረገላ፡ ቅረብና፡ ተ

፴ ገናኘው፡ አለው። ፊልጶስም በደረሰ፡ ጊዜ፡ የነቢዩን፡ የኢሳይያስን፡ መጽሐፍ፡ ሲያነብ፡ ሰምቶ፡ የምታነበውን፡ መጽሐፍ፡ ታውቀዋለህን፡ አለው።

፴፩ እርሱም፡ የሚያስተምረኝ፡ ሳይኖር፡ እንዴት፡ ይቻለኛል አለው፡ ወደ፡ ሠረገላውም፡ ወጥቶ፡ ከእርሱ፡ ጋራ፡ ይቀመጥ

፴፪ ዘንድ፡ ለመነው። ያነበው፡ የነበረ፡ የመጽሐፉ፡ ስፍራ፡ ሓኘ፡ ይህ፡ ነበር፡ እንደ፡ በግ፡ ወደ፡ መታረድ፡ ተነዳ፡ የበግ፡ ጠቦትም፡ በሸላቹ፡ ፊት፡ ዝም፡ እንዲል፡ እንዲሁ፡ አፉን፡ አልከፈተም። ኢ

፴፫ ሳ፡ ፶፫፡ ፯። በውርደቱ፡ ፍርዱ፡ ተወገደ፡ ሕይወቱ፡ ከምድር፡ ተቈርጣለችና፡ ትውልዱን፡ ማን፡

፴፬ ይነግራል። ስለዚህ ጃንደረባውም፡ ለፊልጶስ፡ መልሶ፡ ነቢዩ፡ ይህን፡ ስለ፡ ማን፡ ይናገራል፡ ስለራሱ፡ ነውን፡ ወይስ፡ ስለ፡ ሌላ፡ ተናግሮ፡ ዘንድ፡ እለምንሃለሁ።

፴፭ አለው፡ ፊልጶስም፡ አፉን፡ ከፈተ፡ ከዚህም፡ መጽሐፍ፡ ጀምሮ፡ ስለ፡ ኢየሱስ፡ ያስተምረው፡ ነበ

፴፮ ር። እነርሱም፡ በመንገድ፡ ሲሔዱ፡ ወደ፡ ውሀ፡ ደረሱ፡ ጃንደረባውም፡ እነሆ፡ ውሀ፡ እንዳልጠመቅ፡ የሚከለክለኝ፡ ማነው

፴፯ አለው። ፊልጶስም፡ በፍጹም፡ ልብህ፡ ብታምን፡ ይገባሃል፡ አለው፡ መልሶም፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር፡ ልጅ፡ እንደሆነ፡ እኔ፡ አምናለሁ፡ አለ። ማቴ

፴፰ ፲፮፡ ፲፮፡ ማር፡ ፲፮፡ ፲፮። ሠረገላውም፡ ይቆም፡ ዘንድ፡ አዘዘ፡ ፊልጶስና፡ ጃንደረባውም፡ ወደ፡ ውሀ፡ ወረዱ፡ አጠመቀውም።

፴፱ ከውኃውም፡ ከወጡ፡ በኋላ፡ የእግዚአብሔር፡ መንፈስ፡ ፊል

ጶስን፡ነጥቆ፡ወሰደው፡ጃንደረባ
ውም፡ሁለተኛ፡አላየውም፡ነገ
ር፡ግን፡ደስ፡ብሎት፡መንገዱን
፵ ሔደ፨ ፩፡ነገ፡፲፰፡፲፪፨ ፊልጶስ፡
ግን፡በአዛጦን፡ተገኘ፡ወደቂሣ
ርያም፡እስኪመጣ፡ድረስ፡እየ
ዞረ፡በአገሩ፡ሁሉ፡ወንጌልን፡
ይሰብክ፡ነበረ፤ ም፡፳፩፡፰፡፱፨

ምዕራፍ፡፱፨

ጳውሎስ፡ምዕመናን፡ለመግደ
ል፡እንደ፡ፈለገ፡መብረቅ፡እንደ
አስደነገጠው፤ዓይኑ፡እንደ፡ታ
ወረ፥እንደ፡አመነና፡ወንጌልን፡
እንደ፡አስተማረ፡ሊገድሉት፡እ
ንደ፡መከሩና፤ደቀ፡መዛሙርቱ
እንደ፡ሸሸጉት፤ጴሮስ፡ኤንያን፡
እንደ፡አዳነው፤ዶርቃስን፡ከሞ
ት፡እንደ፡አስነሣት፨

፩ ሳውል፡ግን፡የጌታን፡ደቀ፡መዛ
ሙርት፡ለመግደልና፡ለማስፈራ
ራት፡ገና፡ይቈጣ፡ነበር፡ወደ፡ካ
ህናት፡አለቃም፡ሔደ፨ ፳፪፡፬፡
፪ ፳፮፡፲፡፲፩፨ በዚህ፡መንገድ፡ያ
ሉትንም፡ሰዎች፡ሁሉ፡ወንዶ
ችንም፡ሴቶችንም፡ቢያገኝ፡
እያሰረ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡
ያመጣቸው፡ዘንድ፡በደማስ
ቆ፡ላሉት፡መስጊዶች፡ለመነ፡ደ
፫ ብዳቤ፨ ሲሔድም፡ወደ፡ደማ
ስቆ፡በቀረበ፡ጊዜ፡ድንገት፡በ
እርሱ፡ላይ፡ከሰማይ፡ብርሃን፡ፀ
ደለ፡አንጸባረቀ፨ ፩፡ቆሮ፡፲፭፡
፬ ፰፨ በምድር፡ላይም፡ወደቀ፡
ሳውል፡ሳውል፡ለምን፡ታሳ
ደኛለህ፡የሚልም፡ድም
፭ ሰማ፨ እርሱም፡አቤቱ፡አን
ማነህ፡አለው፡ጌታም፡አን
የምታሳድደኝ፡እኔ፡የናዝሬ
ቱ፡ኢየሱስ፡ነኝ፡የሾለውን፡ብ
ረት፡ብትረግጥ፡ለአንተ፡ይ
ብስብሃል፡አለውም፡፳፮፡
፮ ፲፬፨ እየፈራና፡እየተንቀጠ
ጠም፡አቤቱ፡ምን፡አደርግ፡ዘ
ንድ፡ትሻለህ፡አለው፡ጌታም
ተነሥተህ፡ወደ፡ከተማ፡ሒ
ና፡ታደርገው፡ዘንድ፡የሚገ
ህን፡በዚያ፡ይነግሩሃል፡አለ
፯ ው፨ ከእርሱም፡ጋራ፡የነበሩ
ሰዎች፡ድምፅ፡እየሰሙ፡ማ
ንም፡ሳያዩ፡ተደንቀው፡ቆሙ
፰ ሳውልም፡ከምድር፡ተነሣ፡ዓ
ይኖቹም፡በተከፈቱ፡ጊዜ፡ማ
ንንም፡አላየም፡በእጁም፡እየ
መሩ፡ወደ፡ደማስቆ፡አገቡት
፱ ሳያይም፡ሳይበላም፡ሳይጠጣ
ም፡ሶስት፡ቀን፡ተቀመጠ፨
፲ በደማስቆም፡ስሙ፡ሐናን
ያ፡የሚሉት፡አንድ፡ደቀ፡መ
ሙር፡ነበረ፡ጌታም፡በራእይ
ሐናንያ፡ሆይ፡አለው፡እርሱ
፲፩ ም፡አቤቱ፡እነሆኝ፡አለ፨ ጌታ
ም፡ተነሥተህ፡ቀን፡መንገድ፡

የሐዋርያት፡
፳፩/፲፩

ሰምትባለው፡መተሳሰሪያ፡
ሔድ፡በዪሁዲ፡ቤትም፡እግሩ፡
ጠርሴስ፡ስሙኝም፡ሰውሌ፡የ
ሚሉትኝ፡ሰው፡ፈልጓ፡እነሆ
እርሱ፡ይጸልያልና፡አለው፨
ም፡፰፩፡፴፱፨በራእይም፡ሐና
ንያ፡የሚሉት፡ሰው፡ወደ፡እር
ሱ፡ገብቶ፡እጁን፡በላዩ፡ሲጭን
በት፡አየ፨ሐናንያም፡መልሶ፡
ጌታ፡እቤቱ፡የዚህን፡ሰው፡ነገር
በኢየሩሳሌም፡በቅዱሳንህ፡ላ
ይ፡ስንት፡ክፉ፡እንደ፡አደረገ፡ከ
ብዙ፡ሰዎች፡ሰምቻለሁ፨በዚ
ህም፡ስምህን፡የሚጸሩትን፡
ሁሉ፡ሰማሠር፡ከካህናት፡አ
ለቆች፡ሥልጣን፡አለው፨፩ቆ
ሮ፡፩፡፴፱፨ጌታም፡አለው፡ይህ፡
በአሕዛብም፡በነገሥታትም
በእ[ስ]ራኤልም፡ልጆች፡ፊት፡ስሜን
ይሸከም፡ዘንድ፡ለእኔ፡የተመ
ጠ፡ዕቃ፡ነውና፡ሒድ፨ም፡፰፫
፲፫፡ሮሜ፡፩፡፫፨ስለ፡ስሜ፡ም፡
ብዙ፡መከራ፡ይቀበል፡ዘንድ፡
እንዲገባው፡እስታውቀዋለሁ
ቍ፰፲፫፡፪ቆሮ፡፲፩፡፰፲፫፨
ሐናንያም፡ሔዶ፡ወደ፡ቤቱም፡
ገብቶ፡እጁን፡ጫነበት፡አለ
ውም፡ወንድሜ፡ሰውል፡ሆይ፡
ስትመጣ፡በመንገድ፡የታየህ፡
ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ታይ፡ዘንድና፡መንፈስ፡ቅዱ
ስም፡ይመላብህ፡ዘንድ፡ወደ
፲፰ እንተ፡ላከኝ፨በዚያ፡ጊዜም፡
ፊጥጥ፡እንደ፡ቅርፍት፡ያለ፡
ከዓይኑ፡ወደቀ፡ዓይኖቹም፡ተ
ገለጡና፡አየ፡ተነሥቶም፡ተ
፲፱ ጠመቀ፨መብልም፡በበላ፡ጊ
ዜ፡በረታ፡በደማስቆም፡ካሉ፡
ት፡ደቀ፡መዛሙርት፡ጋራ፡እጅ
፳ ጓ፡ቀን፡ኖረ፨ያን፡ጊዜውንም
ፊጥኖ፡ስለ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ
እርሱ፡የእግዚአብሔር፡ልጅ
እንደሆነ፡በመስጊዶቹ፡አ
፳፩ ስተማረ፨የሰሙትም፡ሁሉ፡
ይህ፡በኢየሩሳሌም፡ይህነን፡
ስም፡የሚጸሩትን፡ሁሉ፡ያጠ
ፋ፡የነበረ፡አይደለምን፡ስለ፡
ዚህ፡እያሠረ፡ወደ፡ካህናት፡
አለቆች፡ይወስዳቸው፡ዘንድ
ወደዚህ፡መጣ፡አልነበረም
ን፡እያሉ፡አደነቁ፨፩፡፲፬፡ም
፳፪ ፳፡፩፡፰፪፡፲፨ሳውልም፡እየበ
ረታ፡ሔደ፡በደማስቆም፡ለተ
ቀመጡት፡አይሁድ፡ይህ፡ክር
ስቶስ፡እንደሆነ፡ሲገልጽላቸ
ው፡ምላሽ፡ያሳጣቸው፡ነበር
፳፫ ም፡፲፳፡፰፳፨ብዙ፡ቀንም፡ከ
ሆነ፡በኋላ፡አይሁድ፡ይገድሉ
ት፡ዘንድ፡እንድነት፡ሁነው፡ተ
፳፬ ማከሩ፨ሰውልም፡እንደ፡ተ
ማከሩበት፡አወቀ፡ይገድሉት
ም፡ዘንድ፡በሌሊቱ፡በቀን፡የከ

ተማውን፡ በር፡ ይጠብቁ፡ ነበ
፳፭ ሩ፥ ደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ግን፡ በ
ሌሊት፡ ወስደው፡ በቅጥር፡ ላይ
በቁንቅብ፡ አወረዱት፥ ፪ ቆሮ
፳፮ ፲፩፡ ፴፫፡ ፴፪፥ ሳውልም፡ ወደ
ኢየሩሳሌም፡ በመጣ፡ ጊዜ፡ ከ
ደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ጋራ፡ በአን
ድ፡ ይሆን፡ ዘንድ፡ ወደደ፡ ነገር፡
ግን፡ ደቀ፡ መዝሙር፡ እንደ ሆነ
ስለ፡ አላመኑት፡ ሁሉም፡ ፈሩ
፳፯ ት፥ በርናባስም፡ ወስዶ፡ ወደ፡
ሐዋርያት፡ አገባው፡ ጌታች
ን፡ በመንገድ፡ እንዴት፡ እንደ፡ ታ
የው፡ እንደ፡ ተናገረው፡ በደማ
ስቆም፡ በኢየሱስ፡ ስም፡ ደፍሮ፡
እንደ፡ አስተማረ፡ አጫወታቸ
፳፰ ው፥ ቀ ፰፥ በኢየሩሳሌምም
በጌታችን፡ በኢየሱስ፡ ስም፡ በግ
ልጥ፡ እየተናገረ፡ ከእነርሳቸው
፳፱ ጋራ፡ ሲወጣ፡ ሲገባ፡ ኖረ፥ ከፅ
ርዕ፡ አገርም፡ ከሚሆኑት፡ ሰዎ
ች፡ ጋራ፡ ይከራከርና፡ ይነጋገ
ር፡ ነበረ፡ እነርሳቸውም፡ ሊ
፴ ገድሉት፡ ፈለጉ፥ ወንድሞች
ም፡ ይህን፡ ባወቁ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ቂ
ሣርያ፡ ወሰዱት፡ ወደ፡ ጠርሴስ
፴፩ ም፡ ሰደዱት፥ ም፡ ፲፭፡ ፳፪ ፳፭፥ እን
ደዚህም፡ በይሁዳና፡ በገሊላ
በሰማርያ፡ የነበሩት፡ አብያተ
ክርስቲያናት፡ ሁሉ፡ በደኅና፡
ኖሩ፡ በእግዚአብሔርም፡ ፍ

ርሃትና፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ረ
ትነት፡ እየተሠራና፡ እየፀኑ፡
፴፪ ዱ፥ ጴጥሮስም፡ በየስፍራ
ሲዞር፡ በልዳ፡ ወደሚኖሩ፡ ቅ
፴፫ ሳን፡ ወረደ፥ በዚያም፡ ከስም
ዓመት፡ ጀምሮ፡ የታመመ፡ ስ
ኝም፡ ኤንያ፡ የሚሉት፡ አንድ፡
ው፡ በአልጋ፡ ላይ፡ ተኝቶ፡ አገ
፴፬ መፃጉዕም፡ ነበር፥ ጴጥሮስም
አለው፡ ኤንያ፡ ሆይ፡ ኢየሱስ
ርስቶስ፡ ይፈውስህ፡ ተነሣ፡
ስህም፡ አንጥፍ፡ የዚያን፡ ጊ
፴፭ ውም፡ ፈጥኖ፡ ተነሣ፥ በልዳ
በሳሮናም፡ የሚኖሩ፡ ሁሉ፡
ይተዉት፡ ወደ፡ እግዚአብሔ
፴፮ ተመለሱ፥ በኢዮጴም፡ ስ
ዋን፡ ጣቢታ፡ የሚሉዋት፡ አ
ዲት፡ ረድእ፡ ነበረች፡ ትርጓ
ውም፡ ዶርቃ፡ ማለት፡ ነው፡
ህችም፡ መልካም፡ ነገር፡ የ
ላባት፡ ምጽዋትም፡ የምት
ጸውት፡ ነበረች፥ መዝ፡ ፵፩፡
፴፯ በዚያም፡ ወራት፡ ታመመች
ና፡ ሞተች፡ አጥበውም፡ በ
፴፰ ገነት፡ አስተኝዋት፥ ልዳም
ለኢዮጴ፡ ቅርብ፡ ናትና፡ ደቀ፡
መዛሙርት፡ ጴጥሮስ፡ በዚያ፡ እ
ዳለ፡ ሰምተው፡ ወደ፡ እነርሳ
ከመምጣት፡ እንዳይዘገይ፡ ይ
ምኑት፡ ዘንድ፡ ሁለት፡ ሰዎች፡
፴፱ ዷርሱ፡ ላኩ፥ ጴጥሮስም፡ ተነ

ቸ፡ ከእነርሳቸው፡ ጋራ፡ መጣ፡ በደረሰም፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ሰገነት፡ አወጡት፡ ባልቴቶችም፡ ሁሉ፡ እያለቀሱ፡ ጣቢታ፡ ከእነርሳቸው፡ ጋራ፡ ሳለች፡ ያደረገቻቸውን፡ ቀሚሶችና፡ ልብሶችንም፡ እያሳዩት፡ በፊቱ፡ ቆሙ። ጴጥሮስም፡ ሁሉ፡ ወደ፡ ውጭ፡ አስወጥቶ፡ ተንበርክኮ፡ ጸለየ፡ ወደ፡ ሬሳውም፡ ተመልሶ፡ ጣቢታ፡ ሆይ፡ ተነሽ፡ አላት፡ እርስዋም፡ ዐይኖችዋን፡ ከፈተች፡ ጴጥሮስንም፡ ባየች፡ ጊዜ፡ ተቀመጠች፡ ማር፡ ፭፡ ፵፩፡ ሉቃ፡ ፯፡ ፲፬። እጁንም፡ ዘርግቶ፡ አስነሣት፡ ቅዱሳኑንና፡ ባልቴቶቹንም፡ ጠርቶ፡ ሕያው፡ አድርጎ፡ በፊታቸው፡ አቆማት። ይህም፡ ወሬ፡ በኢዮጴ፡ ሁሉ፡ የታወቀ፡ ሆነ፡ ብዙ፡ ሰዎችም፡ በጌታ፡ አመኑ። ዮሐ፡ ፲፩፡ ፵፭፡ ፲፪፡ ፵፪። በኢዮጴም፡ ስምዖን፡ ከሚሉት፡ ከአንድ፡ ቍርበት፡ ፋቂ፡ ጋራ፡ አያሌ፡ ቀን፡ ተቀመጠ። ም፡ ፲፡ ፮።

ምዕራፍ፡ ፲።

ስለ፡ ቆርኔሌዎስ፡ ጸሎትና፡ ምጽዋት፡ መልአክ፡ እንደ፡ ተገለጸለትና፤ እንደ፡ ተናገረው፤ ስለ፡ ጴጥሮስ፡ ራእይ፤ ወደ፡ ቆርኔሌዎስ፡ ቤት፡ ገብቶ፤ እንደ፡ አስተማረ፤ ቆርኔሌዎስ፡ ከቤቱ፡ ሰዎቹ፡ ጋራ፡ እንደ፡ አመኑ።

፩ በቂሣርያም፡ ኢጣሊቄ፡ ለሚልዋት፡ ጭፍራ፡ የመቶ፡ አለቃ፡ የሆነ፡ ቆርኔሌዎስ፡ የሚሉት፡ አንድ፡ ሰው፡ ነበረ። ማቴ፡ ፰፡ ፭።

፪ እርሱም፡ ጻድቅና፡ ከቤቱ፡ ሰዎቹም፡ ሁሉ፡ ጋራ፡ እግዚአብሔርን፡ የሚፈራ፡ ለሕዝብም፡ እጅግ፡ ምጽዋት፡ የሚመጸውት፡ ወደ፡ እግዚአብሔርም፡ ሁልጊዜ፡ የሚጸልይ፡ ነበረ። ዳን፡ ፬፡ ፳፯።

፫ ከቀኑም፡ በዘጠኝ፡ ሰዓት፡ የእግዚአብሔር፡ መልአክ፡ ወደ፡ እርሱ፡ ገብቶ፡ በግልጽ፡ ቆ

፬ ርኔሌዎስ፡ ሲለው፡ አየ። ወደ፡ እርሱም፡ በተመለከተ፡ ጊዜ፡ ደንግጦ፡ ምንድር፡ ነው፡ ጌታዬ፡ ሆይ፡ አለ፡ መልአኩም፡ አለው፡ ጸሎትህና፡ ምጽዋትህ፡ ለመታሰቢያ፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት

፭ ዐረገ። አሁንም፡ ወደ፡ ኢዮጴ፡ ሰዎችን፡ ልከህ፡ ጴጥሮስ፡ የሚባለውን፡ ስምዖን፡ አስመጣ።

፮ እርሱም፡ ቤቱ፡ በባሕር፡ አጠገብ፡ ባለው፡ በቍርበት፡ ፋቂው፡ ስምዖን፡ ቤት፡ እንግድነት፡ ተቀምጦዋል፡ ታደርገውም፡ ዘንድ፡ የሚገባህን፡ እርሱ፡ ይነግ

፯ ርሃል። ም፡ ፱፡ ፵፫። ም፡ ፲፩፡ ፲፬። ይናገረውም፡ የነበረው፡ መልአክ፡ በሔደ፡ ጊዜ፡ ከሎሳልቱ

ሁለቱን፤— ከማይለዩትም፡ ‹
ጭፍሮቹ፡ እግዚአብሔርን፡ የ
ሚፈራ፡ አንዱን፡ ወታደር፡ ጠራ
፰ ነገሩንም፡ ሁሉ፡ አጫወታቸ‹
ው፡ ወደ፡ ኢዮጴም፡ ላካቸው፡
፱ በነጋውም፡ ሲሔዱ፡ ወደ፡ ከተ‹
ማ፡ በቀረቡ፡ ጊዜ፡ ጴጥሮስ፡ በ፮
ት፡ ሰዓት፡ ይጸልይ፡ ዘንድ፡ ወደ
፲ ሰገነት፡ ወጥቶ፡ ነበር። ያንጊዜ
ም፡ ርበቶ፡ ሊበላ፡ ወደደ፡ ሰዎች
ም፡ መብል፡ ሲያዘጋጁ፡ ራእይ፡
፲፩ ተገለጸለት። ሰማይም፡ ተከፍ
ቶ፡ እንደ፡ ታላቅ፡ ልብስ፡ በአራት
መዓዝን፡ የተያዘ፡ ዕቃ፡ ወደ፡
ምድር፡ ሲወርድ፡ አየ። ም፡ ፲፩ዘ፲፫
፲፪ ሉ፡ ፫፡ ፳፱። በዚያውም፡ አራት
እግር፡ ያለው፡ የምድር፡ እንስሳ
ሁሉ፡ አራዊትም፡ የሚንቀሳ
ቀስም፡ የሰማይ፡ ወፎችም፡ ነ
፲፫ በሩበት። ጴጥሮስ፡ ሆይ፡ አርደ
ህ፡ ብላ፡ የሚል፡ ድምፅ፡ ወደ
፲፬ እርሱ፡ መጣ። ጴጥሮስ፡ አቤቱ፡
አይሆንም፡ ርኩስ፡ የሚያስጸ
ይፍም፡ ከቶ፡ በልቼ፡ አላውቅ
ም፡ አለ። ሕዝ፡ ፬፡ ፲፬፤ ዘሌ፡ ፲፩።
፲፭ ፯፡ ፲፫፡ ፳፫። ደግሞም፡ ሁለተኛ
እግዚአብሔር፡ ያነፃውን፡ አን
ተ፡ አታርክሰው፡ የሚል፡ ድም
ፅ፡ ወደ፡ እርሱ፡ መጣ። ማቴ፡ ፲፭
፲፮ ፲፩። ይህንንም፡ ፫ት፡ ጊዜ፡ አለ
ው፡ በዚያም፡ ጊዜ፡ ዕቃው፡ ወ

፲፯ ደ፡ ሰማይ፡ ተመለሰ። ጴጥሮ
ስም፡ ስለ፡ አየው፡ ራእይ፡ ምን፡
ይሆን፡ ብሎ፡ በልቡ፡ ሲያስ
እነሆ፡ ቆርኔሌዎስ፡ የላካቸው
ሰዎች፡ የስምዖንን፡ ቤት፡ እየ‹
ጠየቁ፡ በደጅ፡ ቆመው፡ ነበሩ
፲፰ ጸርተውም፡ ጴጥሮስ፡ የተባለ
ው፡ ስምዖን፡ ወደዚህ፡ እንግዳ
ነት፡ መጥቶ፡ እንደሆነ፡ ብለው
፲፱ ጠየቁ። ጴጥሮስም፡ ስለ፡ አየ‹
ው፡ ራእይ፡ ሲያወጣ፡ ሲያወር
ድ፡ መንፈስ፡ አለው፡ እነሆ፡ ሦስ
፳ ት፡ ሰዎች፡ ይፈልጉሃል። ስለዚ
ህም፡ ተነሥተህ፡ ውረድ፡ እነ
ም፡ ልኬያቸዋለሁና፡ ሳትጠ
ራጠር፡ ከእነርሳቸው፡ ጋራ፡ ሒ
፳፩ ድ። ጴጥሮስም፡ ወደ፡ ሰዎቹ፡
ወርዶ፡ እነሆ፡ የምትፈልጉኝ
እኔ፡ ነኝ፡ የመጣችሁበት፡ ም
ክንያት፡ ምንድር፡ ነው፡ አላቸ
፳፪ ው። እነርሳቸውም፡ እግዚአ
ብሔርን፡ የሚፈራ፡ ጻድቅ፡ ሰው፡
በአይሁድም፡ ሁሉ፡ የተመሰ‹
ከረለት፡ የመቶ፡ አለቃው፡ ቆ
ርኔሌዎስ፡ ወደ፡ ቤቱ፡ ያጸራሕ፡
ዘንድ፡ ከአንተም፡ ቃልህን፡ ይ
ሰማ፡ ዘንድ፡ ቅዱስ፡ መልአክ፡
፳፫ አዘዘው። ተቀብሎም፡ በቤቱ
አሳደራቸው፡ በነጋውም፡ ጴጥ
ሮስ፡ ከእነርሳቸው፡ ጋራ፡ ሔደ፡
ከኢዮጴም፡ ብዙ፡ ወንድሞች

፳፬ ከእነርሱ፡ጋራ፡ሒዱ። በነጋው
ም፡ወደ፡ቂሣርያ፡ገቡ፡ቆርኔሌ
ዎስም፡ዘመዶቹንና፡የቅርብ፡
ወዳጆቹን፡ሁሉ፡ጸርቶ፡ይጠብ
፳፭ ቃቸው፡ነበረ። ጴጥሮስም፡በገ
ባ፡ጊዜ፡ቆርኔሌዎስ፡ሊቀበለው
ወጣ፡ከእግሩም፡በታች፡ወድቆ
፳፮ ሰገደለት። ጴጥሮስ፡ግን፡እኔም
እንደ፡አንተ፡ሰው፡ነኝና፡ተነሣ
ብሎ፡አስነሣው። ፲፬፡፲፭፡ራ
እ፡፲፱፡፲። ከእርሱም፡ጋራ፡እየ
ተናገረ፡ገባ፡በዚያውም፡እጅግ
ሰዎች፡ተከማችተው፡አገኘ።
፳፰ እላቸውም፡አይሁዳዊ፡ሰው፡
ወደ፡ሌላ፡ወገን፡ይገናኝና፡ይገ
ባ፡ዘንድ፡እንዳይገባ፡እናንተ
ም፡ታውቃላችሁ፡ነገር፡ግን፡እ
ግዚአብሔር፡ከሰው፡ማንንም፡
እንዳልነቅፍና፡ርኩስም፡ነው
፳፱ እንዳልል፡ለእኔ፡አሳየኝ። ስለ
ዚህም፡ብትጸሩኝ፡ሳልጠራጠ
ር፡መጣሁ፡አሁንም፡በምን፡ም
ክንያት፡እንደ፡ጸራችሁኝ፡እጠይ
፴ ቃችኋለሁ። ቆርኔሌዎስም፡
አለ፡ው፡የዛሬ፡አራት፡ቀን፡እስ
ከዚች፡ሰዓት፡ድረስ፡ጾመኛ፡ነ
በርሁ፡በዘጠኝ፡ሰዓትም፡በቤ
ቴ፡ም፡ስጸልይ፡እነሆ፡የብርሃን
ልብስ፡የለበሰ፡አንድ፡ሰው፡በ
፴፩ ፊቴ፡ቆመ። አለኝም፡ቆርኔሌ
ዎስ፡ሆይ፡በእግዚአብሔር፡ፊ
ት፡ጸሎትህ፡ተሰማልህ፡ምጽ
፴፪ ዋትህም፡ታሰበልህ። አሁንም
ወደ፡ኢዮጴ፡ልከህ፡በቁርበት፡
ፋቂው፡በስምዖን፡ቤት፡በባሕ
ር፡አጠገብ፡እንግዳነት፡ተቀ
ምጥዋልና፡ጴጥሮስ፡የተባለ
ውን፡ስምዖንን፡አስጸሩ፡እርሱ
ም፡መጥቶ፡የምትድንበትን፡
፴፫ ይነግርሃል። ያንጊዜውንም፡
ወደ፡አንተ፡ላክሁ፡አንተም፡
መምጣትህ፡መልካም፡አደረ
ግህ፡አሁንም፡አንተ፡ከእግዚአ
ብሔር፡ዘንድ፡የታዘዝኸውን፡
ሁሉ፡እንሰማ፡ዘንድ፡እነሆ፡እኛ
ሁላችን፡በእግዚአብሔር፡ፊት
፴፬ በዚህ፡አለን። ጴጥሮስም፡አፉ
ን፡ገልጾ፡አለ፡እግዚአብሔር፡ለ
ሰው፡ፊት፡እንዳያደላ፡በእውነ
ት፡አስተዋልሁ። ፩፡ሳሙ፡፲፮፡
፴፭ ፯፡ሮሜ፡፪፡፲፩። ነገር፡ግን፡በሕ
ዝብ፡ሁሉ፡እርሱን፡የሚፈራና
ቅን፡ነገርም፡የሚያደርግ፡ቢኖ
ር፡በእርሱ፡ዘንድ፡የተወደደ፡ነ
፴፮ ው። ዮሐ፡፩፡፲፯። ወደ፡፳፩ል፡ልጆ
ች፡የተላከው፡ቃል፡የሁሉ፡ጌ
ታ፡በሚሆን፡በኢየሱስ፡ክርስቶ
ስ፡ሰላምን፡የሚሰብክ፡ነው።
፴፯ ማቴ፡፫፡፲፯፡፲፯። ዮሐንስ፡ከሰበ
ከው፡ጥምቀት፡በኋላ፡ከገሊላ
ጀምሮ፡በይሁዳ፡ሁሉ፡የሆነው
ን፡ነገር፡እናንተ፡ታውቃላችሁ

፴፰ [ማቴ፡፬፡፳፫።] ስለ፡ናዝሬቱ፡ስለ፡ኢየሱስ፡እግዚአብሔር፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡በኀይልም፡እንደ፡ቀባው፡እየዞረም፡መልካም፡እንደ፡አደረገ፡ሰይጣን፡ያሸነፋቸውንም፡ሁሉ፡እንደ፡ፈወሰ፡እግዚአብሔር፡ከእርሱ፡ጋራ፡ነ
፴፱ በረና[ሉቃ፡፳፬፡፵፰።] እኛም፡በይሁዳ፡አገርና፡በኢየሩሳሌም፡ባደረገው፡ነገር፡ሁሉ፡ምስክሮች፡ነን፡ይህንንም፡በእንጨት፡
፵ ላይ፡ሰቅለው፡ገደሉት። እግዚአብሔርም፡በሦስተኛው፡ቀን፡አስነሣው፡ይገለጥም፡ዘንድ፡
፵፩ ሰጠው። ነገር፡ግን፡እግዚአብሔር፡ምስክር፡ይሆኑ፡ዘንድ፡አስቀድሞ፡ለመረጣቸው፡ነው፡እንጂ፡ለሕዝብ፡ሁሉ፡አይደለም፡ከሙታንም፡ከተነሣ፡በኋላ፡ከእርሱ፡ጋራ፡የበላን፡የጠጣንም፡እኛ፡ነን።[ሐ፡፲፫፡፴፩።]
፵፪ [፬፡፲፫፡፳ ፲፯።] በሕያዋንና፡በሙታንም፡ይፈርድ፡ዘንድ፡እግዚአብሔር፡የመረጠው፡እርሱን፡እንደ፡ሆነ፡ለሕዝቡ፡ሁሉ፡እንድንሰብክና፡እንመሰክር፡ዘን
፵፫ ድ፡አዘዘን።[፲፯፡፴፩።] በእርሱም፡የሚያምን፡ሁሉ፡በስሙ፡የኀጢአቱን፡ሥርየት፡እንዲቀበል፡ነቢያት፡ሁሉ፡ይመሰክሩለታል።[ኢሳ፶፫፡፭፡ኤር፴፩፡፴፬፡ሕዝ፡፴፬፡]
[፲፯፡ዳን፡፱፡፳፬፡ሆሴ፡፲፫፡፲፬፡ሚክ፡፯፡፲፰፡]
፵፬ ጴጥሮስም፡ይህንን፡ነገር፡ሲናገር፡ነገሩን፡በሰሙት፡ሁሉ፡ላይ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ወረደ።
ከጴጥሮስም፡ጋራ፡የመጡ፡ከግዝረት፡ወገን፡የሆኑ፡ምእመናን፡በአሕዛብ፡ላይ፡የመንፈስ፡ቅዱስ፡ጸጋ፡ስለ፡ፈሰሰ፡ደነገጡ።
በልሳኖች፡ሲናገሩ፡እግዚአብሔርንም፡ሲያከብሩ፡ሰምተዋቸዋልና።[ሐ፡፪፡፬፡ማር፡፲፮፡፲፯።]
፵፯ በዚያን፡ጊዜም፡ጴጥሮስ፡መል[ሶ] እነዚህ፡እንደኛ፡መንፈስ፡ቅዱ[ስ]ን፡ከተቀበሉ፡እንዳይጠመ[ቁ] ውኃን፡ይከለክላቸው፡ዘንድ [የ]ሚችል፡ማነው፡አለ። በጌታ[ም]፡ስም፡ይጠመቁ፡ዘንድ፡አዘ[ዛ]ቸው፡ከዚህም፡በኋላ፡በእነ[ር]ሳቸው፡ዘንድ፡አያሌ፡ቀን፡[እ]ንዲቀመጥ፡ለመኑት።[ሐ፡፬፡]

ምዕራፍ፡፲፩።

ጴጥሮስን፡ካልተገዘሩ፡ሰዎች፡ጋራ፡በላህ፡እንደ፡አሉት፡ራእዩን፡እንደ፡ነገራቸው። በአስጢፋኖስ፡ሞት፡የተሰደዱት፡እንደ፡ስተማሩና፡በርናባስ፡አይቶ፡ደስ፡እንደ፡አለው፤ስለ፡አንፆስ፡ትን ቤት።

ሐዋርያትና፡በይሁዳ፡ያሉ፡ወንድሞች፡አሕዛብ፡ደግሞ፡የእግዚአብሔርን፡ቃል፡እንደ፡ተቀበሉ

፪ ሰሙ ፡፡ ጴጥሮስም፡ ወደ፡ ኢ
የሩሳሌም፡ በወጣ፡ ጊዜ፡ የ
ግዝረት፡ ሰዎች፡ ወቀሱት፡
እንዲህ፡ ሲሉ፡ ም፡ ፩፡ ፴፡ ፫፤
ወደ፡ አልተገዘሩ፡ ሰዎች፡ ገ
ብተህ፡ ከእነርሳቸው፡ ጋራ፡
በላህ፤ ገላ፡ ፪፡ ፲፪፤ ጴጥሮስ
ም፡ ከመጀመሪያው፡ ጀምሮ
ሁሉን፡ ይነግራቸው፡ ጀመረ
፭ እንዲህ፡ እያሉም፡ ፲፡ ፲፤ እኔ፡
በኢዮጴ፡ አገር፡ ስጸልይ፡ ሳለ
ሁ፡ በራዕይ፡ ተመሰጥሁ፡ በ
አራት፡ መአዘንም፡ የተያዘ
ታላቅ፡ መጐናጸፊያን፡ የመ
ሰለ፡ ዕቃ፡ ከሰማይ፡ ሲወርድ፡
፮ አየሁ፡ ወደ፡ እኔም፡ መጣ፤ ወደ
እርሱም፡ በተመለከትሁ፡ ጊ
ዜ፡ የምድር፡ እንስሳን፡ አራዊ
ትንም፡ ተንቀሳቃሽንም፡ የሰ
ማይ፡ ወፎችንም፡ አየሁ።
፯ ጴጥሮስ፡ ሆይ፡ ተነሥተህ፡ አ
ርደህ፡ ብላ፡ የሚለኝንም፡ ድ
፰ ምፅ፡ ሰማሁ፤ እኔም፡ አቤቱ፡
አይሆንም፡ ከቶ፡ አንዳች፡ ር
ኩስ፡ የሚያስጸይፍም፡ ወደ
አፌ፡ ገብቶ፡ አያውቅም፡ አል
፱ ሁ፤ ደግመኛም፡ ሁለተኛ፡ እግዚ
አብሔር፡ ያነጻውን፡ አንተ፡ አታ
ርክሰው፡ የሚል፡ ድምፅ ።
፲ ከሰማይ፡ መለሰልኝ፤ ይህ
ም፡ ሶስት፡ ጊዜ፡ ሆነም፡ እንደ
ገናም፡ ሁሉ፡ ወደ፡ ሰማይ፡ ተሳ
፲፩ በ፤ እነሆም፡ በዚያች፡ ሰዓት፡ ሶ
ስት፡ ሰዎች፡ ከቂሳርያ፡ ወደ፡ እ
ኔ፡ ተልከው፡ እኔ፡ ባለሁበት፡ ቤ
ት፡ ቆሙ፡ መንፈስ፡ ቅዱስንም
፲፪ ሳልጠራጠር፤ ከእነርሳቸው፡
ጋራ፡ እሔድ፡ ዘንድ፡ አዘዘኝ፡ እ
ነዚህም፡ ፮ቱ፡ ወንድሞች፡ ከእ
ኔ፡ ጋራ፡ መጡ፡ ወደዚያ፡ ሰውም
፲፫ ቤት፡ ገባን፤ እርሱም፡ ነገረን፡ የ
እግዚአብሔር፡ መልአክ፡ በቤቱ
ቆሞ፡ እንደ፡ አየና፡ እንደ፡ አለው
ም፡ ወደ፡ ኢዮጴ፡ ሰዎች፡ ልከህ፡
ጴጥሮስ፡ የተባለውን፡ ስምዖ
፲፬ ን፡ አስመጣ፤ አንተና፡ የቤትህ፡
ሰዎች፡ ሁሉ፡ የምትድኑበትን፡
ነገር፡ እርሱ፡ ይነግርሃል፤ም፡ ፲
፲፭ ፯፤ ለመናገርም፡ በጀመርሁ፡
ጊዜ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ አስቀድ
ሞ፡ ለእኛ፡ እንደ፡ ወረደ፡ ለእነር
ሱም፡ ወረደ፡ ላቸው፤ም፡ ፪፡ ፬።
፲፮ ዮሐንስ፡ በውኃ፡ አጠመቀ፡ እናን
ተ፡ ግን፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ት ጠ
መቃላችሁ፡ ያለውንም፡ የጌታ
ችንን፡ ቃል፡ አሰብሁ፤ም ፩፡ ፭።
፲፯ ማቴ፡ ፫፡ ፲፩፤ እንግዲህ፡ እግዚአ
ብሔር፡ በጌታችን፡ በኢየሱስ፡ ክር
ስቶስ፡ ላመነው፡ ለእኛ፡ እንደ፡ ሰ
ጠ፡ እንደ፡ እኛ፡ አድርጎ፡ ጸጋውን
ሲሰጣቸው፡ እግዚአብሔርን፡
ለመከልከል፡ እችል፡ ዘንድ፡ ዘንድ

እኔ፡ማን፡ነኝ፡፡ ፲፰ ይህንንም፡በሰሙ፡ጊዜ፡ዝምም፡አሉ፡እግዚአብሔር፡ለአሕዛብ፡ደግሞ፡ለሕይወት፡የሚሆን፡ንስሐን፡ሰጣቸው፡እያሉም፡እግዚአብሔርን፡

፲፱ አመሰግኑ፡፡ በእስጢፋኖስ፡ሳይ በተደረገው፡መከራ፡የተበተኑት፡ግን፡ወደ፡ፊንቄ፡ወደ፡ቆጵሮስም፡ወደ፡አንጾኪያም፡መጡ፡ቃሉንም፡ለአይሁድ፡ብቻ፡እንጂ ለአንድ፡ስንኳ፡አይናገሩም፡ነበር። ም፡፰፡፩፡፬።

፳ ከእነርሳቸውም ግን፡ሌሎች፡ሰዎች፡ከቆጵሮስ፡ወገን፡ከቄሬናም፡ነበሩ፡፡ እነርሳቸውም፡ወደ፡አንጾኪያ፡በገቡ ጊዜ፡ስለ፡ጌታችን፡ስለ፡ኢየሱስ፡የምሥራች፡እየነገሩ፡አረማውያንን፡አስተማሩ።

፳፩ የእግዚአብሔርም፡እጅ፡ከእነርሳቸው፡ጋራ፡ነበረ፡ቍጥራቸውም፡እጅግ፡የሚሆን፡ሰዎች፡ወደ፡ጌታ፡ተመለሱ። ም፡፪፡፵፯።

፳፪ ይህም፡ወሬ፡በኢየሩሳሌም፡በአለው፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ስለ፡እነርሱ፡ተሰማ በርናባስንም፡ወደ፡አንጾኪያ፡

፳፫ ላኩት፡፡እርሱም፡መጥቶ፡የእግዚአብሔርን፡ጸጋ፡ባየ፡ጊዜ፡ደስ፡አለው፡በሙሉ፡ልባቸውም በጌታ፡ጸንተው፡ይኖሩ፡ዘንድ፡መከራቸውም፡፲፫፡፵፫፡፲፬፡፳፪፡

፳፬ እርሱ፡ጻድቅ፡ሰውና፡መንፈስ ቅዱስም፡ሃይማኖትም፡የመላበት፡ነበርና፡እጅግ፡ሰዎችም፡ወደ፡ጌታ፡ተጨመሩ። ም፡፪፡፵፩፤ም፡፭፡፲፬።

፳፭ በርናባስም፡ከዚያ፡ሳውልን፡ሊፈልግ ወደ፡ጠርሴስ፡ሔደ፡ባገኘውም፡ጊዜ፡ወደ፡አንጾኪያ፡ይዞት፡መጣ። ም፡፱፡፴።

፳፮ በቤተ፡ክርስቲያንም፡አንድ፡ዓመት፡ሙሉ፡በአንድነት፡ኖሩ፡እጅግ፡ሰዎችንም፡አስተማሩ፡ደቀ፡መዛሙርትም፡መጀመሪያ፡በአንጾኪያ፡ክርስቲያን፡ተባሉ። ገላ፡፬፡፲፮።

፳፯ በዚያም፡ወራት፡ነቢያት፡ከኢየሩሳሌም፡ወደ፡አንጾኪያ፡ወረዱ። ም፡፲፫፡፩፡፲፭፡፴፪።

፳፰ ከእነርሳቸውም፡አንዱ፡ስሙ፡አጋቦስ፡የሚሉት፡ተነሣቶ፡በዓለም፡ሁሉ፡ታላቅ፡ራብ፡እንዲሆን፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ተናገረ፡ይህም፡የሆነ፡በቀላውዴዎስ፡ቄሣር፡ዘመን፡ነው። ም፡፳፩፡፲

፳፱ ደቀ፡መዛሙርትም፡በይሁድ ላሉት፡ወንድሞች፡ከእነርሳቸው፡እያንዳንዱ፡እንደ፡ተቻለው፡መጠን፡አቋጥተው፡ይልኩ፡ዘንድ፡ወደዱ። ገላ፡፪፡፲

፴ እንዲህም፡አደረገው፡በበርናባስና፡በሳውል፡እጅ፡ወደ፡ሽማግሌዎች፡ሰደዱት። ም፡፲፪፡፳፭

ምዕራፍ፡ ፲፪።

ስለ፡ ዮሐንስ፡ ወንድም፡ ስለ፡ ያዕቆ
ብ፡ ሞት፡ ስለ፡ ጴጥሮስ፡ መታሠር፡
መልአኩ፡ ከግዞት፡ ቤት፡ እንደ
አወጣው፡ ደቀ፡ መዛሙርት፡ ወ
ደ፡ አሉበት፤ ቤት፡ ሔደ፡ ደጁ፤ እን
ደ፡ መታና፤ ሮዴ፤ እንደ፡ ሰማች
ው፤ ከግዞት፡ ቤት፡ ፈልገው፡ እን
ደ፡ አጡትና፡ ዘበኞች፡ እንደ፡ ተገ
ደሉ። ስለ፡ ሄሮድስ፡ ሞት።

፩ በዚያም፡ ዘመን፡ ንጉሡ፡ ሄሮድስ
መከራ፡ ያፀናባቸው፡ ዘንድ፡ በአያ
ሌ፡ ክርስቲያኖች፡ ላይ፡ እጁን፡
፪ ዘረጋ። ም፡ ፬፡ ፲። የዮሐንስን፡ ወ
ንድም፡ ያዕቆብንም፡ በሰይፍ
፫ ገደለው። አይሁድንም፡ ደስ፡ እ
ንደ፡ አሰኛቸው፡ አየ፡ ጴጥሮ
ስን፡ ደግሞ፡ ያዘው፡ የፋሲካ፡ በ
ዓልም፡ ወራት፡ ነበረ። በያዘው
ም፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ግዞት፡ ቤት፡ አገባ
ው፡ ከፋሲካም፡ በኋላ፡ ወደ፡ ሕዝ
ብ፡ ያወጣው፡ ዘንድ፡ ፈቀደ፡ በየ
ተራቸው፡ ይጠብቁት፡ ዘንድ፡ ለ
አራት፡ ክፍል፡ ወታደሮች፡ አሳል
፭ ፎ፡ ሰጠው። ም፡ ፲፪፡ ፳፩፡ ፬። ጴጥሮ
ስም፡ እንዲሁ፡ ሁኖ፡ በግዞት፡ ይጠ
በቅ፡ ነበረ፡ ነገር፡ ግን፡ በቤተ፡ ክር
ስቲያን፡ ስለ፡ እርሱ፡ ሁሉ፡ ጊዜ፡ ወ
ደ፡ እግዚአብሔር፡ ጸሎት፡ ያደር
፮ ግ፡ ነበረ። ሄሮድስም፡ ያቀርበው
ዘንድ፡ ባሰበ፡ ጊዜ፡ በዚያች፡ ሌሊ
ት፡ ጴጥሮስ፡ በሁለት፡ ሰንሰለ
ት፡ ታሥሮ፡ ከሁለት፡ ወታደሮች
መካከል፡ ተኝቶ፡ ነበረ፡ ጠባቂ
ቹም፡ በግዞት፡ ቤት፡ ደጅ፡ ሁነው
፯ ይጠብቁ፡ ነበሩ። እነሆም፡ የእግ
ዚአብሔር፡ መልአክ፡ መጥቶ፡
ባጠገቡ፡ ቆመ፡ በግዞቱ፡ ቤትም
ብርሃን፡ በራ፡ ጴጥሮስንም፡ ጎ
ድኑን፡ ነካ፡ አደረገና፡ ፈጥነህ፡ ተ
ነሣ፡ ብሎ፡ አስነሣው፡ ሰንሰለ
ቶቹም፡ ከእጁ፡ ወደቁ። ም፡ ፭፡ ፲፱
፰ መልአኩም፡ ፈጥነህ፡ ታጠቅና
ጫማህን፡ አግባ፡ አለው፡ እን
ዲሁም፡ አደረገ፡ ልብስህን፡ ል
በስና፡ ተከተለኝ፡ አለው።
፱ ጴጥሮስም፡ ተከትሎት፡ ወጣ
ራእይም፡ የሚያይ፡ ይመስለው
ነበረ፡ እንጂ፡ በመልአኩም፡ የ
ሚደረገው፡ ነገር፡ እውነት፡ እ
፲ ንደ ሆነ፡ አላወቀም። የመጀመ
ሪያውንና፡ የሁለተኛውን፡ ዘብ
ኰሉ፡ በኋላ፡ ወደ፡ ከተማ፡ ወደ
ሚያስገባው፡ ወደ፡ ብረቱ፡ መ
ዝጊያ፡ ደረሱ፡ እርሱም፡ እውቆ
ት፡ ከፈተላቸው፡ ወጥተውም
አንደኛውን፡ አደባባይ፡ ባለፉ፡
ጊዜ፡ ያን፡ ጊዜ፡ መልአኩ፡ ከእር
፲፩ ሱ፡ ተለየ። ጴጥሮስም፡ ወደ፡ ል
ቡ፡ ተመልሶ፡ እግዚአብሔር፡ መ
ልአኩን፡ ልኮ፡ ከሄሮድስ፡ እጅና
አይሁድ፡ ይጠብቁት፡ ከነበረው

ሁሉ፡፡ እንደ፡ አደነቁ፡ ለሁን፡ በ
፲፪ እውነት፡ አወቀሁ፡ አለቃባስት
ዋሉም፡ ጊዜ፡ እጅግ፡ ሰዎች፡ ተ
ከማቸተው፡ ይጸልዩበት፡ ወደ
ነበረ፡ ማርቆስ፡ ወደ፡ ተባለው፡
ወደ፡ ዮሐንስ፡ እናት፡ ወደ፡ ማርያ
፲፫ ም፡ ቤት፡ መጣ፤ ም፡ ፲፪፡ ፴፫፡ ጴ
ጥሮስም፡ የደጀን፡ መዝጊያ፡ በ
መታ፡ ጊዜ፡ ሰምዋን፡ ሮዴ፡ የሚ
ሏት፡ አንዲት፡ ብላቴና፡ ትሰማ
፲፬ ዘንድ፡ መጣች፤ የጴጥሮስ፡ ድ
ምፅ፡ መሆኑን፡ ም፡ ባወቀች፡ ጊዜ
ከደስታዋ፡ የተነሣ፡ አልከፈተ
ችም፡ ነገር፡ ግን፡ ስትሮጥ፡ ሔዳ፡
ጴጥሮስ፡ በደጅ፡ ቆሞ፡ እንደለ፡
፲፭ የምስራች፡ ነገረቻቸው፤ እርሳቸ
ው፡ ግን፡ አብደሻል፡ አሏት፡ እ
ርሷም፡ እንደሁ፡ እንደሆነ፡ አ
ስረገጠች፡ እነርሳቸውም፡ መ
ልአኩ፡ ይሆናል፡ አሉ፤ ሉ፡ ፳፬
፲፮ ፲፯፤ ጴጥሮስ፡ ግን፡ ደጁን፡ ሲ
መታ፡ ቈየ፡ ከፍተውም፡ ባዩ
፲፯ ት፡ ጊዜ፡ ደነገጡ፤ እርሱ፡ ግን፡
ዝም፡ እንዲሉ፡ በእጁ፡ አመለ
ከታቸው፡ እግዚአብሔርም፡ ከ
ግዞት፡ ቤት፡ እንዴት፡ እንደ፡ አ
ወጣው፡ ነገራቸው፡ ይህንንም
ለያዕቆብና፡ ለወንድሞች፡ ን
ገሩ፡ አላቸው፡ ከዚያም፡ ወጥ፡
፲፰ ቶ፡ ወደ፡ ሌላ፡ ስፍራ፡ ሔደ፡፡ በነ
ጋም፡ ጊዜ፡ ጭፍሮች፡ ጴጥሮስ

ኝ፡ ምን፡ አግኝቶት፡ ይሆን፡ ብለ
ው፡ ተጨነቁ፤ ም፡ ፭፡ ፳፩፡ ፳፱
፲፱ ሄሮድስም፡ አስፈልጎ፡ ባጣ
ጊዜ፡ ጠባቂዎችን፡ መረመረ፡
ገድሉዋቸውም፡ ዘንድ፡ አዘዘ
ከይሁዳ፡ አገርም፡ ወደ፡ ቂሣ
ያ፡ ወርዶ፡ በዚያ፡ ተቀመጠ፡
፳ ሮድስም፡ በጢሮስና፡ በሲዶ
ሰዎች፡ ተቈጥቶ፡ ነበረ፡ በአንድ
ነትም፡ ሁነው፡ ወደ፡ እርሱ፡ መ
ጥተው፡ የንጉሡን፡ ቤት፡ ወደ
ብላስጦስን፡ አማላጅ፡ ልከ
ዕርቅ፡ ፈለጉ፡ የአገራቸው፡ ም
ግብ፡ ከንጉሡ፡ ግዛት፡ ነበረና፤
፩፡ ነገ፡ ፭፡ ፱፡ ፲፩፡ ሕዝ፡ ፳፯፡ ፲፯
፳፩ አንድ፡ ቀንም፡ ሄሮድስ፡ ልብሰ
መንግሥቱን፡ ለብሶ፡ በዙፋን፡
ተቀመጠ፡ እነርሳቸውንም፡
፳፪ ናገራቸው፡፡ ሕዝቡም፡ የእግ
ዚአብሔር፡ ቃል፡ ነው፡ የሰው፡
ም፡ አይደለም፡ ብለው፡ ጮሁ፡
፳፫ ሕዝ፡ ፳፰፡ ፪፡ ለእግዚአብሔር፡
ምስጋና፡ ስላልሰጠ፡ በዚያ፡
ጊዜ፡ የእግዚአብሔር፡ መልአ
ክ፡ ቀሠፈው፡ ትልም፡ ፈሳበት
፳፬ ና፡ ሞተ፤ ዳን፡ ፫፡ ፳፡፡ የእግዚአ
ብሔርም፡ ቃል፡ እያደገና፡ እየሰ
ፋ፡ ሔደ፤ ም፡ ፮፡ ፯፡ ኢሳ፡ ፶፭፡ ፲፩፡
፳፭ በርናባስና፡ ሳውልም፡ አገልግ
ሎታቸውን፡ አድርሰው፡ ከኢየ
ሩሳሌም፡ ተመለሱ፡ ማርቆስ፡

የተባለውን፡ ዮሐንስንም፡ ከ
እነርሳቸው፡ ጋራ፡ ይዘዉት፡ ሄ
ዱ፨ ም፡ ፩፡ ፳፱፡ ቍ፡ ፲፪፡ ም፡ ፲፭፡ ፴
፯ ቍ

ምዕራፍ ፲፫።

ስለ፡ ሳውልና፡ ስለ፡ በርናባስ፡ በ
መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ሥራ፡ መመረ
ጥ፡ በያገሩ፡ ዞረው፡ እንዲያስተ
ማሩ፤ ስለ፡ አስማተኛው፡ በ
ርያሱስ፤ ዕውር፡ መሆን፤ ጳው
ሎስ፡ በመስጊድ፡ ገብቶ፡ እንደ
ሰበከ፤ አይሁድ፡ ከከተማ፡ እን
ደ፡ አስወጥዋቸው።

፩ በአንጾኪያም፡ ባለችው፡ ቤተ፡
ክርስቲያን፡ ነቢያትና፡ መምህ
ራን፡ ነበሩ፡ ከእነርሳቸውም፡ በ
ርናባስ፡ ኔጌር፡ የተባለው፡ ስም
ዖንም፡ የቄሬኑ፡ ሉክዮስም፡
ከአራተኛው፡ ገዢ፡ ከሄሮድስ
ም፡ ጋራ፡ ያደገ፡ ምናሔ፡ ሳው
፪ ልም፨ ም፡ ፲፩፡ ፳፪ ፳፫፡ ፩፡ ፲፬፨ እነ
ዚህም፡ እግዚአብሔርን፡ ሲያ
ገለግሉና፡ ሲጾሙ፡ መንፈስ
ቅዱስ፡ በርናባስንና፡ ሳውልን፡
ለጠራኋቸው፡ ሥራ፡ ለዩልኝ፡
፫ አሉም፡ ፱፡ ፲፭ ቍ በዚያ፡ ጊዜም፡
ጾሙ፡ ጸለዩም፡ እጃቸውንም
ጭነው፡ ባርከው፡ ሰደድዋቸ
፬ ው፨ ም፡ ፲፬፡ ፳፮ ቍ ም፡ ፯፡ ፯ ቍ እነር
ሱም፡ እንደዚሁ፡ በመንፈስ፡
ቅዱስ፡ ተልከው፡ ወደ፡ ሴሌው
ቅያ፡ ወረዱ፡ ከዚያም፡ በመር
ከብ፡ ወደ፡ ቆጵሮስ፡ ሔዱ፨ ወደ
፭ ሰላሚስም፡ በደረሱ፡ ጊዜ፡ በአ
ይሁድ፡ መስጊዶች፡ የእግዚአብ
ሔርን፡ ቃል፡ ሰበኩ፡ ዮሐንስም
አያገለግላቸው፡ ከእነርሳቸው
ጋራ፡ ነበረ፨ ም፡ ፲፪፡ ፲፪፡ ፳፭ ቍ
፮ ደሴቲቱንም፡ ሁሉ፡ እስከ፡ ጳፎስ
በዞሩ፡ ጊዜ፡ በዚያ፡ ከአይሁድ፡
ወገን፡ ስሙን፡ በርያሱስ፡ የሚ
ሉትን፡ አስማተኛ፡ ሰው፡ ሐሰተ
፯ ኛም፡ ነቢይ፡ አገኙ፨ ይህም፡ አስ
ተዋይ፡ ከሆነው፡ ሰው፡ ሰርግዮ
ስ፡ ጳውሎስ፡ ከሚባለው፡ ሹም
ጋራ፡ ይኖር፡ ነበረ፡ ይህም፡ የእ
ግዚአብሔርን፡ ቃል፡ ሊሰማ፡ ወ
ዶ፡ በርናባስንና፡ ሳውልን፡ ጠር
፰ ቶ፡ ወደ፡ እርሱ፡ አስመጣ፨ አስማ
ተኛው፡ ኤሊማስ፡ ስሙ፡ እ
ንዲሁ፡ ይተረጐማልና፡ ሹሙ
ን፡ ከማመን፡ ሊከለክል፡ ፈልጎ
ተቃወማቸው፨ ፪፡ ጢሞ፡ ፫፡ ፰
፱ ጳውሎስ፡ የተባለው፡ ሳውል፡
ግን፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ ተመል
ቶ፡ ዓይኑን፡ አተኵሮ፡ ተመለከ
፲ ተው፨ አለውም፡ አንተ፡ ሽንገ
ላና፡ ተንኰልም፡ የመላብህ፡ የ
ሰይጣን፡ ልጅ፡ የጽድቅም፡ ሁሉ
ጸላት፡ የቀናችውን፡ የእግዚአ
ብሔርን፡ መንገድ፡ ከማጣመ
፲፩ ም፡ አታርፍምን፨ አሁንም፡ እ
ነሆ፡ የእግዚአብሔር፡ እጅ፡ በ

ለንቱ፡ሳይ፡ናት፡ዕውርም፡ቱሆናለህ፡እስከ፡ጊዜውም፡ፀሐይን፡አታይም፡ያንጊዜ፡ውንም፡ጭጋግና፡ጨለማ፡ወደቀበት፡በእጁም፡የሚመራ

፲፪ ውን፡እየዞረ፡ፈለገ። ከዚያ፡ጊዜ፡ሹመው፡የተደረገውን፡ተአምራት፡ባየ፡ጊዜ፡ከእግዚአብሔር፡ትምህርት፡የተነሣ፡ተ

፲፫ ደንቆ፡አመነ። ከዚህም፡በኋላ፡ጳውሎስ፡ከጓደኞቹ፡ጋራ፡ከጳፎስ፡የጴምፊልያ፡ወደ፡እምትሆን፡ወደ፡ጵርጊያ፡መጡ፡ዮሐንስ፡ግን፡ከእነርሳቸው፡ተለይቶ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡

፲፬ ተመለሰ፥ም፡፲፭፡፴፰። እነርሳቸውም፡ከጴርጊያ፡አልፈው፡የጲስድያ፡ወደምትሆን፡ወደ፡አንጾኪያ፡መጡ፡በሰንበትም፡ቀን፡ወደ፡ምስጊድ፡ገብተው፡

፲፭ ተቀመጡ። ኦሪትና፡ነቢያትም፡ከተነበቡ፡በኋላ፡የምስጊዱ፡አለቆች፡እናንተ፡ሰዎች፡ወንድሞች፡ለሕዝብ፡ሊነገር፡የሚገባ፡የምክር፡ቃል፡እንደ፡አላችሁ፡ተናገሩ፡ብለው፡ላኩባቸው። ጳውሎስም፡ተነሥቶ፡እጁን፡ዘርግቶ፡አለ፡እናንተ፡የ፳ል፡ሰዎችና፡እግዚአብሔርንም

፲፮ የምትፈሩ፡ስሙ። የዚህ፡የ፳ል፡አምላክ፡አባቶቻችንን፡መረጠ፡ሕዝቡንም፡በተሰደዱበት፡በግብፅ፡አገር፡ከፍ፡ከፍ፡አደረጋቸው፡ከፍ፡ባለችውም፡ክንዱ፡ከዚያ፡አወጣቸው፡ኢሳ፡፩፡፪። ዘፀ፡፲፪፡፴፯፡፶፩።

፲፰ በበረሓም፡አርባ፡ዓመት፡ሙሉ፡መገባቸው። ዘፀ፡፲፮፡፴፭፡ዘኁ፡፲፬፡፴፬። ዘዳግ፡፩፡፴፩።

፲፱ ከከነዓንም፡አገር፡ሰባቱን፡አሕዛብ፡አጥፍቶ፡ምድራቸውን፡በዕጣ፡አካፈላቸው። ዘዳግ

፳ ፯፡፩። ኢያ፡፲፬፡፪። ከዚህም፡በኋላ፡እስከ፡ነቢዩ፡እስከ፡ሳሙኤል፡ዘመን፡ድረስ፡አራት፡መቶ፡ከአምሳ፡ዓመት፡ያህል፡መሳፍንቶችን፡ሾመላቸው። ዘመሳ

፳፩ ፪፡፲፮፡፫፡፲። ከዚያም፡በኋላ፡ንጉሥን፡ያነግሥላቸው፡ዘንድ፡ለመኑ፡እግዚአብሔርም፡ከብንያም፡ወገን፡የሚሆን፡ሳውል፡የቂስን፡ልጅ፡ሳኦልን፡አርባ፡ዓመት፡አነገሣቸው።

፳፪ ፩ሳሙ፡፲፡፳፩። እርሱንም፡ከሻረው፡በኋላ፡ዳዊትን፡አነገሠላቸው፡እንደ፡ልቤም፡የሆነው፡ሰው፡ፈቃዴንም፡ሁሉ፡የሚያደርግ፡የዕሤይን፡ልጅ፡ዳዊትን፡አገኘሁ፡ብሎ፡መሰከረለ

፳፫ ት። ፩ሳሙ፡፲፮፡፲፪፡፲፫። እግዚአብሔርም፡እንደ፡ተስፋው፡ከዘሩ፡ለ፳ል፡መድኃኒት፡አዳርጎ፡

ኢየሱስን፡ አስነሣ፤ ኢሳ፡፲፩፡፩። ፳፬ ከመምጣቱም፡ በፊት፡ ዮሐንስ አስቀድሞ፡ ለእስራኤል፡ ወገን፡ ሁሉ የንስሐን፡ ጥምቀት፡ ሰበከ፤ ማቴ፡፫፡፩። ፳፭ ዮሐንስም፡ ማገልገሉን፡ በፈጸመ፡ ጊዜ፡ እኔ፡ ማን፡ እንደሆንሁ፡ ታስባላችሁ፧ እኔ፡ እርሱን፡ አይደለሁም፡ ነገር፡ ግን፡ እነሆ፡ ጫማውን፡ ከእግሩ፡ አወልቅ፡ ዘንድ፡ የማይገባኝ፡ ከእኔ፡ በኋላ፡ ይመጣል፤ ዮሐ፡፩፡፳፯፡ ማር፡፩፡፯፡ ሉ፡፫፡፲፮። ፳፮ እናንተ፡ ሰዎች፡ ወንድሞቻችን፡ የአብርሃምም፡ ዘር፡ ልጆች፡ አባቶቻችሁ እግዚአብሔርን፡ የምትፈሩ፡ ይህ፡ የሕይወት፡ ቃል፡ ለእናንተ፡ ተላከ። ሉቃ፡፵፯። ፳፯ በኢየሩሳሌም፡ የሚኖሩ፡ ሰዎችና፡ አለቆቻቸው፡ ግን፡ እርሱንና፡ በየሰንበቱ፡ የሚነበበውን፡ የነቢያትን፡ ቃል ባያውቁት፡ በፍርዳቸው፡ ፈጸሙት። ዮሐ፡፲፯፡፫። ፳፰ ለሞትም፡ የሚያደርስ፡ ምክንያት፡ አንድ፡ ስንኳ ባያገኙበት፡ ይገድሉት፡ ዘንድ፡ ጲላጦስን፡ ለመኑት። ማቴ፡፳፯፡ ፳፱ ፳፬፡፳፫። ስለ፡ እርሱ፡ የተጻፈውን ሁሉ፡ በፈጸሙ፡ ጊዜ፡ ከእንጨት አውርደው፡ በመቃብር፡ አኖሩት። ፴ ማቴ፡፳፯፡፶፱። እግዚአብሔር ግን፡ ከሙታን፡ አስነሣው። ም፡፫፡ ፴፩ ፲፭። ከእርሱም፡ ጋራ፡ ገሊላ፡ ወደ

ኢየሩሳሌም፡ አወጡትና፡ አሁንም፡ በሕዝቡ፡ ዘንድ፡ ምስክሮች፡ ለሆኑት፡ ብዙ፡ ቀን፡ ተገለጸ ፴፪ ላቸው። ም፡፬፡፫። እኛም፡ ለአባቶቻችን፡ የተሰጠውን፡ ተስፋ የምስራች፡ እንሳችኋለን፡ ቀ ፴፫ ፳፫። እግዚአብሔር፡ ኢየሱስን፡ በስነሣው፡ ጊዜ፡ ይህን፡ ለእኛ፡ ለልጆቻቸው፡ ፈጸመው፡ በሁለተኛው፡ መዝሙር፡ አንተ፡ ልጄ፡ ነህ፡ እኔም፡ ዛሬ፡ ወለድሁህ፡ የሚል ጽሑፍ፡ እንዲ፡ አለ። መዝ፡፪፡፯። ፴፬ ከሙታን፡ አስነሥቶታልና፡ እንደገናም፡ ወደ፡ ጥፋት፡ እንዳይመለስ፡ የተቀደሰውንና፡ የታመነውን፡ በረከት፡ አሰጣችኋለሁ፡ አለ ፴፭ ኢሳ፡፶፭፡፫። ስለዚህ፡ ደግሞ፡ በሌላው፡ ስፍራ፡ ጻድቅህን፡ ጥፋትን ያይ፡ ዘንድ፡ አትሰጠውም፡ ይላል ፴፮ መዝ፡፲፮፡፲። ዳዊትም፡ በዘመኑ የእግዚአብሔርን፡ ፈቃድ፡ ካገለገለ፡ በኋላ፡ አንቀላፋ፡ ከአባቶቹም፡ ጋራ፡ ተቀላቀለ፡ ጥፋትንም ፴፯ አየ። ይህ፡ እግዚአብሔር፡ ያስነሣው፡ ግን፡ ጥፋትን፡ አላየም። ፴፰ እሁንም፡ እናንተ፡ ሰዎች፡ ወንድሞች፡ በእርሱ፡ የኃጢአት፡ ሥርየት፡ እንዲነገርላችሁ፡ በእናንተ፡ ዘንድ፡ የታወቀ፡ ይሁን። ፴፱ በሙሴም፡ ሕግ፡ ትጸድቁበት፡ ዘንድ ከማይቻላችሁ፡ ሁሉ፡ ያመነ፡ ሁ

ሉ፡በእርሱ፡ይጸድቃል፤ሮሜ፡፲
፵ ፬፨ስለዚህ፡በነቢያት፡የተባለ
ው፡እንዳይደርስባችሁ፡ተጠን
፵፩ ቀቁ፤ዕንባ፡፩፡፭፨እናንተ፡ቸል
ቸኞች፡እዩ፡ተደነቁም፡ጥፉ
ም፡አንድ፡ስንኳ፡ቢነግራችሁ
የማታምኑትን፡ሥራ፡በዘመ
፵፪ ናችሁ፡እሠራለሁና፨ከአይሁ
ድም፡መስጊድ፡በወጡ፡ጊዜ፡አ
ሕዛብ፡ይህነን፡ነገር፡በሚመ
ጣው፡ሰንበት፡ይነግሯቸው
፵፫ ዘንድ፡ለመኗቸው፨ጉባዔ
ውም፡ከተፈታ፡በኋላ፡ከአይሁ
ሁና፡ከአረማዊነት፡ወደ፡አይ
ሁደዊነት፡ከተመለሱት፡ከደ
ጋጉ፡ብዙ፡ሰዎች፡ጳውሎስን
ና፡በርናባስን፡ተከተሏቸው
በእግዚአብሔር፡ጸጋ፡ያጸኑ፡ዘን
ድ፡እያስረዱ፡ነገሯቸው፤ም
፵፬ ፲፬፡፳፪፨በሁለተኛውም፡ሰንበ
ት፡የከተማው፡ሰው፡ሁሉ፡የ
እግዚአብሔርን፡ቃል፡ይሰሙ፥
፵፭ ዘንድ፡ተሰበሰቡ፨አይሁድም
የተሰበሰበውን፡ሕዝብ፡ባዩ፡
ጊዜ፡ቅንዓት፡መላባቸው፡እ
የተቃወሙና፡እየተሳደቡም
ጳውሎስ፡በተናገረው፡ቃል፡ተ
ከራከሩ፨ቀኁ፡፱፡ም፡፲፬፡፪፨
፵፮ ጳውሎስና፡በርናባስም፡ደፍረ
ው፡እንዲህ፡አሉ፡የእግዚአብሔርቃል፡አ
ስቀድሞ፡ለእናንተ፡ይነገር፡ዘ
ንድ፡ይገባል፡ከገፋችሁት፡የ
ዘላለም፡ሕይወትም፡እንዲ
ይገባችሁ፡ራሳችሁ፡ከፈረዳ
ችሁ፡ግን፡እነሆ፡ወደ፡አሕዛብ፡
እንሄዳለንና፤ም፡፫፡፳፮፤ማቴ፡፲
፵፯ እግዚአብሔር፡እስከ፡ምድር፡ዳ
ርቻ፡ድረስ፡መድኃኒት፡ት
ን፡ዘንድ፡ለአሕዛብ፡ብርሃን፡አ
ደረግሁህ፡ብሎ፡አዘናልና፤ኢ
፵፰ ሳ፡፵፱፡፮፨አሕዛብም፡ይህን፡
በሰሙ፡ጊዜ፡ደስ፡አላቸው፡የ
እግዚአብሔርንም፡ቃል፡አመ
ሰገኑ፡ለዘላለም፡ሕይወትም
የተዘጋጁ፡ሁሉ፡አመኑ፨ሮሜ
፵፱ ፰፡፳፱፨የእግዚአብሔርም፡ቃ
፶ ል፡በያገሩ፡ሁሉ፡ደረሰ፨አይሁ
ድ፡ግን፡እግዚአብሔርን፡የሚ
ፈሩ፡የከበሩትን፡ሴቶችና፡ያገ
ሩን፡ሽማግሎች፡አወኩ፨
በጳውሎስና፡በበርናባስም፡ላ
ይ፡ስደትን፡አስነሡተው፡ከአገ
፶፩ ራቸው፡አባረሯቸው፨እነርሳ
ቸውም፡የእግራቸውን፡ትቢ
ያ፡አራግፈውባቸው፡ወደ፡ኢ
ቆንዮም፡ሔዱ፨ም፡፲፰፡፮፤ማቴ
፲፡፲፬፨ደቀ፡መዛሙርትም፡ደስ
ታና፡መንፈስ፡ቅዱስ፡መላባቸ
ው፨

ምዕራፍ፡፲፬።

ጳውሎስ፡ሽባ፡ሁኖ፡የተወለደው
ን፡እንዳዳነ፡ጳውሎስንና፡በር
ናባስን፡አማልክት፡ብለው፡መ

ሥዋዕት፡እንደ፡አቀረቡላ
ቸው፤ጳውሎስን፤እንደ፡ደበ
ደቡትና፤እንደ፡ጐተቱት፤በ
ደርቤና፤በሊሳም፤በኅበዙ፡አ
ገር፡እንደ፡አስተማሩ።

፩ በኢቆንዮም፡ደጋሞ፡ሆነ፡ከአይ
ሁድና፡ከአረማውያንም፡ብዙ
ሰዎች፡አስኪያምኑ፡ድረስ፡
ወደ፡አይሁድ፡መስጊድ፡በአ
ንድነት፡ገብተው፡ተናገሩ።

፪ ያላመኑት፡አይሁድ፡ግን፡የአ
ሕዛብን፡ልብ፡በወንድሞች፡ላ
ይ፡አነሳሡ፡እስከፉምቅም፡፲፫
፫ ፶፩፡፶፪።በዚያም፡ረጅም፡ወራት
ተቀመጡ፡ተአምራትና፡ም
ልክትም፡በእጃቸው፡ይደረግ
ዘንድ፡ለጸጋው፡ቃል፡ምስክ
ር፡በሰጠ፡በጌታ፡ስም፡በርትተ
ው፡ይናገሩ፡ነበሩ።ም፡፲፬፡፫

፬ ዕብ፡፬፡፬።የከተማውም፡ሰ
ዎች፡ተከፍለው፡አኩሌቶቹ
ከአይሁድ፡አኩሌቶቹም፡ከሐ
፭ ዋርያት፡ጋራ፡ሆኑ።አሕዛብ
ና፡አይሁድም፡ከአለቆቻቸ
ው፡ጋራ፡ይሣቀይዋቸውና፡ይ
ደወግርዋቸውም፡ዘንድ፡ሁ
ከት፡ባነሡ፡ጊዜ።ቍ፡፲፬፡፭
፮ ጢሞ፡፫፡፲፩።እነሱ፡ይህነን፡አ
ውቀው፡ወደ፡ሊቃኦንያ፡ከተ
ማ፡ወደ፡ልስጥራን፡ወደ፡ደርቤ
ንም፡በእነርሱም፡አውራጃ፡
ወደ፡አለው፡አገር፡ሸሹ።

፯ በዚያም፡ወንጌልን፡ሰበኩ፡ም
፰ ም፡፲፬፡፮፡፯።በልስጥራንም፥
እግሩ፡የሰለለ፡ከእናቱም፡ማ
ኅፀን፡ጀምሮ፡ሽባ፡የሆነ፡ከቶ
ም፡ሒዶ፡የማያውቅ፡ሰው፡ተ
፱ ቀምጦ፡ነበረ።ም፡፲፬፡፰።ይህ
ም፡ጳውሎስን፡ሲናገር፡ሰማ
ው፡ጳውሎስም፡ዓይኑን፡አተ
ኩሮ፡ተመለከተውና፡ይድን፡
ዘንድ፡እምነት፡እንደ፡አለው፡
፲ ባየ፡ጊዜ።ማቴ፡፱፡፳፰፡፳፱፤በታላ
ቅ፡ቃል፡ቀጥ፡ብለህ፡በእግርህ
ቁም፡አለው፡ተነሥቶም፡ተረ
፲፩ ማመደ።አሕዛብም፡ጳውሎስ፡
የደረገውን፡ባዩ፡ጊዜ፡ድምፃ
ቸውን፡አድርገው፡በሊቃኦን
ያ፡ቋንቋ፡አማልክት፡ሰዎችን
መስለው፡ወረዱ፡አሉ
፲፪ ም፡፰፡፳፰፡፳፱።በርናባስንም፡ድያ
አሉት፡ጳውሎስንም፡ነገሩን፡
የሚናገር፡እርሱ፡ስለ፡ነበረ፡
፲፫ ሄርሜን፡አሉት።በከተማው
ም፡ፊት፡ለፊት፡የነበረ፡የድያ፡
ካህን፡ግን፡በሬችንና፡አክሊ
ሎችን፡ወደ፡ደጅ፡አፍ፡አመጣ
ከሰዎችም፡ጋራ፡ሊሠዋቸው፡
፲፬ ወደደ።ጳውሎስና፡በርናባስ
ሐዋርያትም፡ይህን፡በሰሙ፡ጊ
ዜ፡ልብሳቸውን፡ቀደዱ፡ፈጥነ
ውም፡ወደ፡ሕዝቡ፡እየጮሁ፡

፲፭ ሮጡ። እንዲህ፡ እያሉ፡ እናንተ ሰዎች፡ ይህን፡ ለምን፡ ታደርጋላችሁ፡ እኛም፡ እንደ፡ እናንተ፡ የምንሞት፡ ሰዎች፡ ነን፡ ከዚህም፡ ከንቱ፡ ነገር፡ ሰማይና፡ ምድርን፡ ባሕርንም፡ በእነርሳቸውም፡ ያለውን፡ ሁሉ፡ ወደ፡ ፈጠረ፡ ወደ፡ ሕያው፡ እግዚአብሔር፡ ትመለሱ፡ ዘንድ፡ የምስራች፡ እንላችኋለንም፡ ፲፡ ፳፪።

፲፮ እርሱ፡ ባለፈው፡ ትውልድ፡ አሕዛብን፡ ሁሉ፡ በሐሳባቸው፡ ይሔዱ፡ ዘንድ፡ ተዋቸው፡ ም፡

፲፯ ፲፬፡ ፴፮። ከዚህም፡ ሁሉ፡ ጋራ፡ መልካም፡ ሥራ፡ እየሠራ፡ ከሰማይ፡ ዝናምን፡ ፍሬ፡ የሚሆንበትንም፡ ወራት፡ ሲሰጠን፡ ልባችንንም፡ በመብልና፡ በደስታ፡ ሲሞላው፡ ራሱን፡ ያለ፡ ምስክር፡ አልተወውም፡ መዝ፡ ፻፵፯፡

፲፰ ፳፫። ኤር፡ ፭፡ ፳፬። ይህንም፡ ብለው፡ እንዳይሠዉላቸው፡ ሕዝቡን፡ በግድ፡ አስተዉዋቸው።

፲፱ አይሁድ፡ ግን፡ ከአንጾኪያና፡ ከኢቆንዮንም፡ መጥተው፡ አሕዛብን፡ አባብለው፡ እሺ፡ አሰኙዋቸው፡ ጳውሎስንም፡ ወግረው፡ የሞተ፡ መስሎዋቸው፡ ከከተማ፡ ወደ፡ ውጭ፡ ጐተቱት። ፪ቆሮ፡ ፲፩፡ ፳፭፡ ፪ጢሞ፡

፳ ፫፡ ፲፩። ደቀ፡ መዛሙርት፡ ከበዉት፡ ሳለ፡ ተነሥቶ፡ ወደ፡ ከተማ፡ ገባ፡ በነጋውም፡ ከበርናባስ፡ ጋ

፳፩ ራ፡ ወደ፡ ደርቤን፡ ሔዱ። በዚያችም፡ ከተማ፡ ወንጌልን፡ እያስተማሩ፡ እጅግ፡ ደቀ፡ መዛሙርትን፡ ካደረጉ፡ በኋላ፡ ወደ፡ ልስጥራ፡ ወደ፡ ኢቆንዮንም፡ ወደ፡ እንጾኪያም፡ ተመለሱ።

፳፪ ደቀ፡ መዛሙርትንም፡ ልብ፡ ያፀናኑ፡ ነበር፡ በሃይማኖት፡ ያፀኑ፡ ዘንድ፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ መንግሥት፡ በብዙ፡ መከራ፡ እንገባ፡ ዘንድ፡ ይገባልና፡ እያሉ፡ ይመክሩዋቸው፡ ነበሩ

፳፫ ም፡ ፲፮፡ ፴፫፡ ፩ተሰ፡ ፫፡ ፫። በየማኅበሩም፡ ሁሉ፡ ሽማግሌዎችን፡ ከመረጡላቸው፡ በኋላ፡ በጸሎትና፡ በጾም፡ ላመኑበት፡ ለእግዚአብሔር፡ አደራ፡ ሰጡ

፳፬ ዋቸው። ፲፫፡ ፫። በጲስድያም፡ በኩል፡ አልፈው፡ ወደ፡ ጵም

፳፭ ፍልያ፡ መጡ፡ ፲ በጴርጌያም፡ የእግዚአብሔርንም፡ ነገር፡ ከተናገሩ፡ በኋላ፡ ወደ፡ አታልያ፡

፳፮ ወረዱ። ከዚያም፡ ስለ፡ ፈጸሙት፡ ሥራ፡ ለእግዚአብሔር፡ ጸጋ፡ አደራ፡ ወደ፡ ተሰጡበት፡ ስፍራ፡ ወደ፡ አንጾኪያ፡ በመርከብ፡

፳፯ ሔዱም፡ ፲፫፡ ፩፡ ፲፭፡ ፵። በደረሱም፡ ጊዜ፡ ማኅበሩን፡ ሁሉ፡ ሰብስበው፡ እግዚአብሔር፡ ያደረገ

ሳቸውን፡ሁሉና፡ለአሕዛብ-
ም፡ሃይማኖትን፡ደጅ፡እንደ፡
ከፈተላቸው፡ተናገሩ❖፩ቆሮ
፲፮፡፱❖ከደቀ፡መዛሙርትም፡
ጋራ፡አያሌ፡ቀን፡ተቀመጡ❖

ምዕራፍ፡፲፭፡

ካልተገዘራችሁ፡አትድኑም፡ብ
ለው፡ስለ፡ተናገሩ፡ሰዎች፡ስለ፡ጴ
ጥሮስና፡ስለ፡ያዕቆብ፡ስብከት
ለጣዖት፡የታረደና፡የታነቀም
ደምም፡መብላት፤ዝሙትም
ማድረግ፡እንደ፡ይገባ፡ስለ፡ጳው
ሎስና፡በርናባስ፡መቀያየም፡
ከይሁዳም፡የወረዱ፡ብዙዎች
እንደ፡ሙሴ፡ሥርዓት፡ካልተገ
ዘራችሁ፡ትድኑ፡ዘንድ፡አትች
ሉም፡ብለው፡ወንድሞችን፡አ
ስተማሩ፡ገላ፡፭፡፪❖በሕዝቡ
ና፡በጳውሎስ፡በበርናባስም፡
መካከል፡ብዙ፡መለያየትና፡ክ
ርክር፡በሆነ፡ጊዜ፡ስለዚህ፡ክር
ክር፡ጳውሎስና፡በርናባስ፡ከእ
ነርሳቸውም፡ሌሎች፡ብዙዎች
ወደ፡ሐዋርያት፡ወደ፡ሽማግሌ
ዎችም፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ይሔ
ዱ፡ዘንድ፡መከረው፡ጨረሱ❖
ም፡፲፭፡፴፡ገላ፡፪፡፩❖እነርሳቸው
ም፡ከቤተ፡ክርስቲያን፡ተሰነባ
ብተው፡በወጡ፡ጊዜ፡በፊንቄና
በሰማርያ፡በኩል፡ሔደው፡የአ
ሕዛብን፡መመለስ፡ነገረው

ወንድሞችን፡ሁሉ፡ደስ፡አሰኙ
፬ ዋቸው❖ወደ፡ኢየሩሳሌም-
ም፡በደረሱ፡ጊዜ፡ምዕመናን
ና፡ሐዋርያት፡ሽማግሌዎች-
ም፡ተቀበሉዋቸው፡እነርሳቸ
ውም፡እግዚአብሔር፡ያደረ
ገላቸውን፡ሁሉ፡አጫወቱዋ
፭ ቸው❖ም፡፲፬፡፳፯❖ካመኑት
ም፡ከፈሪሳውያን፡ወገን፡ብዙ
ዎች፡ተነሥተው፡ትገዝርዋ-
ቸው፡ዘንድና፡የሙሴን፡ሕግ
እንዲጠብቁ፡ታዝዋቸው፡ዘ
፮ ንድ፡ይገባል፡አሉ❖ሐዋርያት
ና፡ሽማግሌዎችም፡ስለዚህ፡ነ
ገር፡የሚያደርጉትን፡ለመማ
፯ ከር፡ተሰበሰቡ❖ከብዙ፡ክርክ
ርም፡በኋላ፡ጴጥሮስ፡ተነሥቶ
አለ፡እናንተ፡ሰዎች፡ወንድሞ
ች፡አሕዛብ፡ከአፌ፡የወንጌልን
ቃል፡ሰምተው፡ያምኑ፡ዘንድ፡
እግዚአብሔር፡ከጥንት፡ጀም
ሮ፡ከእናንተ፡እኔን፡እንደ፡መረ
ጸኝ፡እናንተ፡ታውቃላችሁ፡
፰ ም፡፲፩፡፲፰❖ልብን፡የሚያ
ውቅ፡አምላክ፡ለእኛ፡እንደ፡ሰ
ጠን፡መንፈስ፡ቅዱስን፡በመስ
፱ ጠቱ፡መሰከረላቸው❖ልባቸ-
ውን፡በእምነት፡ባነፃ፡ጊዜ
በእኛና፡በእነርሳቸው፡መካከ
ል፡አንዳች፡አላየም❖ም፡፲፡፴፬
፲ አሁንስ፡እግዚአብሔርን፡ለምን

ትፈታተናላችሁ፡ አባቶቻችን
ንና፡ እኛ፡ ልንሸከመው፡ የ
ማንችለውን፡ ቀምበር፡ በደ
ቀ፡ መዛሙርት፡ ጫንቃ፡ ላይ፡
ለምን፡ ትጭናላችሁ፧ ገላ፡ ፫
፲፩ ፲፡ ፫፡ ፩ቆ ነገር፡ ግን፡ እንደ፡ እነር
ሱ፡ በጌታችን፡ በእግዚአብሔ
ር፡ ጸጋ፡ እንድንድን፡ እናምና
፲፪ ለንቆ ሐሥ፡ ፲፡ ፬፡ ፲ቆ የተሰበሰቡ
ትም፡ ሕዝብ፡ ሁሉ፡ ዝም፡ አሉ፡
ጳውሎስና፡ በርናባስም፡ እግ
ዚአብሔር፡ በእነርሱ፡ እጅ
በአሕዛብ፡ ላይ፡ ያደረገውን፡ ታ
ላላቅ፡ ምልክትና፡ ተአምራት፡ ሲ
ነግሩዋቸው፡ ያዳምጡ፡ ነበሩ፤
፲፫ እነርሱም፡ ዝም፡ ካሉ፡ በኋ
ላ፡ ያዕቆብ፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ መለ
ሰ፡ እናንተ፡ ሰዎች፡ ወንድሞቻ
፲፬ ችን፡ ስሙኝቆም፡ ፲፭፡ ፲፬ቆ እግዚ
አብሔር፡ ከአሕዛብ፡ ወገን፡ ለስሙ
ሕዝብን፡ ይወስድ፡ ዘንድ፡ አስቀ
ድሞ፡ እንዴት፡ እንደ፡ ጐበኘ፡ ስ
፲፭ ምዖን፡ ተናግሮአልቆ ይህም
ከነቢያት፡ ቃል፡ ጋራ፡ ይስማማ
፲፮ ል፡ እንደ፡ ተጻፈቆ ከዚህ፡ በኋላ፡
ተመልሼ፡ የወደቀችውን፡ የዳ
ዊትን፡ ቤት፡ እንደ ገና፡ እሠራታ
ለሁ፡ ፍራሿንም፡ እደ ስዋለሁ
አቀናውም፡ አለሁቆ አሞ፡ ፱፡ ፲፩፡
፲፯ ፲፪ቆ የቀሩት፡ ሰዎችና፡ ስሜ፡ በ
እነርሱ፡ ላይ፡ የተጠራው

አሕዛብም፡ ሁሉ፡ እግዚአብሔ
ርን፡ ዘንድ፡ ይላል፡ ይህን፡ የሚ
፲፰ ያደርግ፡ እምላክ፡ ዓለም፡ ከተ
ፈጠረ፡ ጀምሮ፡ ሥራው፡ ሁሉ፡ በ
እግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ የታወ
፲፱ ቀ፡ ነው፤ ስለዚህም፡ ከአሕዛብ
ነት፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ የሚ
መለሱትን፡ እንዳናስቸግራቸ
፳ ው፡ ይታየኛልቆ ነገር፡ ግን፡ ከጣ
ዖት፡ ርኩሰትና፡ ከዝሙት፡ ከ
ታንቀም፡ ከደምም፡ ይከለከሉ
ዘንድ፡ እንልክባቸው፡ ዘፍ፡ ፱፡
፳፩ ዘሌ፡ ፫፡ ፲፯ቆ ሙሴስ፡ ከቀደሙ
ት፡ ትውልድ፡ ጀምሮ፡ በየመስጊ
ዱና፡ በየከተማው፡ አሁንም፡ አሁ
ንም፡ እያነበቡ፡ የሚሰብኩት፡ አ
፳፪ ሉትቆም፡ ፲፫፡ ፲፭ቆ ያንጊዜ፡ ሐዋ
ርያትና፡ ሽማግሌዎች፡ ማኅበሩ
ሁሉ፡ ከጳውሎስና፡ ከበርናባስ
ጋራ፡ ወደ፡ አንጾኪያ፡ የሚልክ
ዋቸውን፡ ሰዎች፡ ይመርጡ፡ ዘን
ድ፡ መከሩ፡ በወንድሞችም፡ መ
ካከል፡ ዋኖች፡ የነበሩትን፡ በር
ሰባ፡ የተባለውን፡ ይሁዳንና፡ ሲላ
፳፫ ስንም፡ ላኩቆ ይህንም፡ በእጃቸ
ው፡ ጽፈው፡ ላኩ፡ ከሐዋርያትና
ከሽማግሌዎች፡ ከወንድሞችም
ከአሕዛብ፡ ወገን፡ በአንጾኪያና
በሶርያ፡ በኪልቅያም፡ ላላችሁ
ወንድሞች፡ ሰላም፡ ለእናንተ፡
፳፬ ይሁንቆ ሰዎች፡ ከእኛ፡ ወጥተው

ተገዘሩ፡ዘንድና፡እሬተኛም፡
ተጠብቁ፡ዘንድ፡ይገባቸኋል
ብለው፡ባላዘዝናቸው፡ቃል፡እ
ኛደ፡አወክዋችሁና፡ልባችሁ
ኝም፡እንደ፡አናወጡት፡ሰለ፡ማ
፳፭ ኝ፨ም፡፳፡፴፡ገላ፡፭፡፲፨ከእነዚ
ህ፡ከምትወድዋቸው፡ከጳው
ሎስና፡ከበርናባስ፡ጋራ፡በአን
ድነት፡ወደ፡እናንተ፡የምንልክ
ቸውን፡ሰዎች፡እንመርጽ፡ዘን
፳፮ ድ፡መከርን፨ስለ፡ጌታችን፡ስለ
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስም፡ነፍሳቸ
፳፯ ውን፡የሰጡ፡፡ በቃላቸውም፡
ይነግርዋቸው፡ዘንድ፡ይሁዳን
፳፰ ና፡ሲላስን፡ላክንላችሁ፨ከዚህ፡
ከሚገባው፡ሐሳ፡በቀር፡ሌላ፡
ተርፍ፡ነገር፡እንደ፡ንጭንባችሁ
ለእኛ፡ለመንፈስ፡ቅዱስ፡ታ ይ
፳፱ ቶዋልና፨ለጣዖት፡ከተሠዋ፡ከ
ደምም፡ከታነቀም፡ከዝሙት
ም፡ትርቁ፡ዘንድ፡ከዚህም፡ሁሉ
ራሳችሁን፡ብትጠብቁ፡በመል
ካም፡ትኖራላችሁ፡ጤና፡ይ ስ
፴ ጣችሁ፨እነርሳቸውም፡ተሰና
ብተው፡ወደ፡እንጾኪያ፡መጡ
ሕዝቡንም፡ሁሉ፡ሰብስበው፡
፴፩ ደብዳቤውን፡ሰጥዋቸው፡፡ በ
ነበቡትም፡ጊዜ፡ደስ፡አሳቸው
በመልክቱም፡ልባቸው፡ፀና
፴፪ ም፲፫፡፴፪፨ይሁዳና፡ሲላስ፡
ደግሞ፡ነቢያት፡ነበሩና፡ወን
ድሞችን፡በብዙ፡ነገር፡ደስ፡አ
ሰኛቸው፡አፀናንዋቸው፨ም፡
፴፫ ፲፩፡፳፯፡፲፫፡፩፨በእነርሳቸውም
ዘንድ፡አያሌ፡ቀን፡ከተቀመጡ
በኋላ፡ከወንድሞች፡በደኅና፡
ተሰናብተው፡ወደ፡ሐዋርያት
፴፬ ሔዱ፨ሲላስ፡ግን፡በዚያ፡ይቀ
፴፭ መጥ፡ዘንድ፡ወደደ። ጳውሎስ
ና፡በርናባስም፡በአንጾኪያ፡
ተቀመጡ፡ደግሞም፡ከሌሎች
ከብዙ ሰዎች፡ጋራ፡የእግዚአ
ብሔርን፡ቃል፡ያስተምሩና፡የ
ምስራችም፡ይነግሩ፡ነበሩ፨
፴፮ ከብዙ፡ቀንም፡በኋላ፡ጳውሎስ
በርናባስን፡የእግዚአብሔርን
ቃል፡ወደ፡አስተማርንበት፡አገ
ር፡እየተመለስን፡ወንድሞችን
እንጐብኛቸው፡እንዴት፡እንደ
አሉም፡እንወቅ፡አለው፨፩ተሰ
፴፯ ፫፡፭፨በርናባስም፡ማርቆስ፡የ
ተባለውን፡ዮሐንስን፡ከእነርሳ
ቸው፡ጋራ፡ይወስድ፡ዘንድ፡ወደ
፴፰ ደ፨ም፡፲፪፡፲፪፡፳፭፨ጳውሎስ፡
ግን፡ይህን፡ከእነርሳቸው፡ጋራ፡
ሊወስዱ፡አልወደደም፡በጵም
ፊልያ፡ሳሉ፡ከእነርሳቸው፡ተለ
ይቶ፡ነበርና፡ወደ፡ሥራም፡ከእ
ነርሳቸው፡ጋራ፡አልመጣም፡ነ
፴፱ በርና፡፲፫፡፲፫፨ስለዚህም፡እ
ርስ፡በርሳቸው፡እስኪለያዩ፡
ድረስ፡በመካከላቸው፡መቀያ

የም፡ ሆነ፡ በርናባስም፡ ማርቆ
ስን፡ ይዞ፡ ወደ፡ ቆጵሮስ፡ በመርከ
፵ ብ፡ ሔደ፨ ጳውሎስ፡ ግን፡ ሲላስን
መረጠ፡ ወንድሞችም፡ ለእግዚአ
ብሔር፡ ጸጋ፡ አደራ፡ ሰጥተውት
፵፩ ሔደ፨ በሶርያና፡ በኪልቅያም፡
እየዞረ፡ አብያተ፡ ክርስቲያናት
ን፡ አፀና፨ ምዕራፍ፡ ፲፮።

ስለ፡ ጢሞቴዎስ፡ እምነት፡ ስለ፡ ጳ
ውሎስ፡ በያገሩ፡ ዞሮ፡ ማስተማር
አንድ፡ መቄዶንያ፡ በሕልም፡ እን
ደ፡ ጠየቀው፨ ስለ፡ ልድያ፡ መመለስ
ጳውሎስ፡ ከአንዲት፡ ሴት፡ ጋኔን
እንደ፡ አወጣ፡ ስለ፡ ጳውሎስና፡ ስ
ለ፡ ሲላስ፡ መገረፍና፤ መታሠር፤
እንደ፡ ጸለዩና፤ ሰንሰለቱ፤ እንደ፡
ወለቀላቸው፨

የወህኒ፡ ቤቱ፡ ሹም፡ እንደ፡ አመነ፡
በሠውር፡ እንፈታም፡ እንደ፡ አሉ።

፩ ወደ፡ ደርቤንና፡ ወደ፡ ልስጥራም
ደረሰ፡ እነሆም፡ በዚያ፡ የአንዲ
ት፡ ያመነች፡ አይሁዳዊት፡ ልጅ
ጢሞቴዎስ፡ የሚባል፡ አንድ፡ ደ
ቀ፡ መዝሙር፡ ነበረ፡ አባቱ፡ ግን፡
አረማዊ፡ ነበረ፨ ም፡ ፲፯፡ ፲፬፡ ፲፱፡ ፳
፪ ፪፨ በልስጥራና፡ በኢቆንዮም
በሚኖሩ፡ ወንድሞች፡ በደግነ
ት፡ የተመሰከረለት፡ ነበረ፡ ም፡
፫ ፯፡ ፫፨ ጳውሎስም፡ ከእርሱ፡ ጋ
ራ፡ ይዞት፡ ይሔድ፡ ዘንድ፡ ወደ
ደ፡ በዚያም፡ ስፍራ፡ ስለ፡ ነበሩ፡
አይሁድ፡ ወስዶ፡ ገዘረው፡ አባ
ቱ፡ አረማዊ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ሁሉ፡
፬ ያውቁ፡ ነበሩና፨ ፪፡ ጢሞ፡ ፩፡ ፭
አገሩን፡ ሁሉ፡ ሲዞሩ፡ ሐዋ
ርያትና፡ ሽማግሌዎች፡ በኢየሩ
ሳሌም፡ የወሰኑትን፡ ሕግ፡ ይጠ
ብቁ፡ ዘንድ፡ አዘዝዋቸው፡ ም፡
፭ ፲፭፡ ፳፰፡ ፳፱፨ አብያተ፡ ክርስቲ
ያናትም፡ በሃይማኖት፡ ፀንተ
ው፡ ይኖሩ፡ ነበሩ፡ ቍጥራቸው
ም፡ ዕለት፡ ዕለት፡ ይበዛ፡ ነበረ፤
፮ ወደ፡ ፍርግያና፡ ወደ፡ ገላትያም
ካለፉ፡ በኋላ፡ በእስያ፡ የእግዚ
አብሔርን፡ ቃል፡ እንዳይናገሩ፡
መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ከለከላቸው፤
፯ ም፡ ፲፰፡ ፳፫፨ ወደ፡ ሚስያም፡
በመጡ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ቢታንያ፡ ይሄ
ዱ፡ ዘንድ፡ ወደዱ፡ የኢየሱስ፡ መ
ንፈስ፡ ግን፡ አልፈቀደላቸው
፰ ም፨ ከሚስያም፡ ባለፉ፡ ጊዜ፡
፱ ወደ፡ ጥሮአስ፡ ወረዱ፨ ለጳውሎ
ስም፡ በሌሊት፡ አንድ፡ የመቄዶ
ንያ፡ ሰው፡ ቆሞ፡ ወደ፡ መቄዶን
ያ፡ እለፍና፡ እርዳን፡ እያለ፡ ሲለ
ምነው፡ ራእይ፡ ተገለጸለት፨
፲ ራእዩንም፡ ካየ፡ በኋላ፡ ያን፡ ጊዜ
ውን፡ ፈጥነን፡ ወደ፡ መቄዶንያ፡
እንሔድ፡ ዘንድ፡ ፈለግን፡ ወንጌ
ልን፡ እንሰብካቸው፡ ዘንድ፡
እግዚአብሔር፡ እንደ፡ ጠራን፡ ፈ
፲፩ ጽመን፡ አውቀናልና፨ ከጥሮአ

ስም፡ በወጣን፡ጊዜ፡መንገዳች
ንን፡ወደ፡ሳሞትራቄ፡አቀናን፡
በነጋውም፡ወደ፡ኔያጶሊስ፡ሔ
ድን፤ ከዚያም፡ወደ፡ፊልጵስዩ
ስ፡እርሱም፡የመቄዶንያ፡መጀ
መሪያ፡ከተማና፡የሮማውያን
ቅኝ፡አገር፡ናት፡በዚያችም፡አ
ገር፡አሌ፡ቀን፡ተቀመጥን። ፲፫ በሰን
በት፡ቀንም፡ከከተማው፡በር፡ጸ
ሎት፡ወደሚደረግበት፡ስፍራ
ወደ፡ወንዝ፡አጠገብ፡ወጣን፡ተቀ
ምጠንም፡ለተሰበሰቡት፡ሴቶ
ች፡ተናገርነው። ፲፬ ከቲያጥራም፡ከ
ተማ፡ስምዋን፡ልድያ፡የሚልዋ
ት፡እግዚአብሔርን፡የምትፈራ
አንዲት፡ቀይ፡ሐር፡ሻጭ፡ሴት
ትሰማ፡ነበረች፡ጳውሎስም፡የ
ሚናገረውን፡ታደምጥ፡ዘንድ
እግዚአብሔር፡ልብዋን፡ከፈተ
፲፭ ሳትቆዮ ሐ፡፯፡፵፬። እርስዋም፡
ከቤተ፡ሰዎችዋ፡ጋራ፡በተጠመ
ቀች፡ጊዜ፡በጌታ፡የማምን፡አ
ድርጋችሁኝ፡እንደ፡ሆነ፡ ወ
ደ፡ቤቴ፡ገብታችሁ፡እደሩ፡ብ
ላ፡ለመነችን፡የግድም፡አለችን።
፲፮ እንዲህም፡ሆነ፡እኛ፡ወደ፡ጸሎ
ት፡ስንሔድ፡የምዋርተኛነት፡
መንፈስ፡የነበረባት፡በጥንቈ
ልነትዋም፡ጌቶችዋን፡እጅግ
ትጠቅም፡የነበረች፡አንዲት፡
ብላቴና፡አገኘችን፤ ፲፱፡፳፬።

፲፯ ይህችም፡እነዚህ፡ሰዎች፡የ
ልዑል፡አምላክ፡አገልጋዮች፡ና
ቸው፡እነርሳቸውም፡የሕይወ
ትን፡መንገድ፡ይገልጹላችኋል
ብላ፡እየጮኸች፡ጳውሎስንና
እኛን፡ተከተለችን፤ማር፡፩፡፳፬።
፲፰ እንዲህም፡ስትል፡እጅግ፡ቀን፡
አደረገች፡ጳውሎስ፡ግን፡አሰዘ
ነቸውና፡ዘወር፡ብሎ፡ያንን፡ጋ
ኔን፡ከእርስዋ፡ትወጣ፡ዘንድ፡በ
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስም፡አዝዛ
ለሁ፡አለው፡በዚያም፡ጊዜ፡ወ
፲፱ ጣ። ማቴ፡፲፯፡፲፯። በጌቶችዋም
የመጠቀማቸው፡ተስፋ፡እን
ደ፡ተቈረጠ፡ባዩ፡ጊዜ፡ጳውሎስ
ንና፡ሲላስን፡ያዙዋቸው፡ወደ፡
ገበያና፡ወደ፡ሹማምንቶም፡ጕ
፳ ተቱዋቸው፤ወደ፡ሹማምን
ቶም፡ባቀረቡዋቸው፡ጊዜ፡እ
ንዲህ፡አሉ፡እነዚህ፡ሰዎች፡ከተ
ማችንን፡እጅግ፡አወኩ፡እነርሳ
ቸውም፡አይሁድ፡ናቸው፤ም፡
፳፩ ፲፮፡፳፩፤ እኛ፡የሮም፡ሰዎች፡እን
ቀበለውና፡እናደርገውም፡ዘንድ
የማይገባን፡ሕግ፡ይሰብካሉ።
፳፪ ሕዝቡም፡ተነሡባቸው፡ሹማ
ምንቶም፡ልብሳቸውን፡ገፈው
በበትር፡ይመቱዋቸው፡ዘንድ፡
፳፫ አዘዙ፤በብዙም፡ከገረፉዋቸ
ውም፡በኋላ፡ወደ፡ግዞት፡ቤት
አገቡዋቸው፡የግዞት፡ቤት፡ጠ

ባቂውንም፡ተመንቀቅ፡ይጠ ብቃቸው፡ዘንድ፡አዘዙት።፬፡ቆሮ፡፲፩፡፳፫፡ፊልጵ፡፩፡፴፡፩፡ተሰ፡፪፡፪።

፳፬ እርሱም፡ይህንን፡ትእዛዝ፡ተቀብሎ፡ወደ፡ውስጠኛው፡የማዘቱ፡ቤት፡አገባቸው፡እግራቸውንም፡በግንድ፡አጣብቆ፡ጠረቃቸው።

፳፭ በመንፈቀ ሌሊትም፡ጊዜ፡ጳውሎስና፡ሲላስ፡ወደ፡እግዚአብሔር፡እየጸለዩ፡በዜማ፡ያመሰግኑ፡ነበሩ፡እሥሮችም፡ይሰሙዋቸው፡ነበሩ።ም፡፬፡፴፩፡ ፳፡፴፯።

፳፮ ድንገትም፡የማዘቱ፡ቤቱ፡መሠረት፡እስኪናወጥ፡ድረስ፡ታላቅ፡የምድር፡መንቀጥቀጥ፡ሆነ፡በዚያ፡ጊዜም፡ፈጥነው፡ደጆቹ፡ሁሉ፡ተከፈቱ፡የሁሉም፡ሰንሰሎቹ፡ወለቁላቸው።

፳፯ የማዘት፡ቤት፡ጠባቂውም፡ደንግጾ፡ከእንቅልፉ፡ተነሣ፡የማዘቱ፡ቤቱ፡ደጆችም፡ሁሉ፡ተከፍቶ፡ባየ፡ጊዜ፡እሥረኞቹ፡ያመለጡ፡(መሰሎት፡ራሱን፡ይገድል፡ዘንድ፡ሰይፉን፡መዘዘ።

፳፰ ጳውሎስ፡ግን፡በታላቅ፡ቃል፡ጮኾ፡እኛ፡ሁላችን፡ከዚህ፡አለንና፡በራስህ፡ክፉ፡ነገር፡አታድርግ፡አለው።

፳፱ መብራትም፡አስመጥቶ ወደ፡ውስጥ፡ገባ፡እየተንቀጠቀጠም፡ለጳውሎስና፡ለሲላስ ሰገደ።

፴ ወደ፡ውጭ፡አውጥቶ ጌቶቼ፡ሆይ፡እድን፡ዘንድ፡ምን፡ማድረግ፡ይገባኛል፡አላቸው።ም፡፪፡፴፯፡ሉ፡፫፡፲።

፴፩ እነርሱ[illegible] ቸውም፡በጌታችን፡በኢየሱስ፡[illegible] ክርስቶስ፡እመን፡አንተና፡ቤ[illegible] ሰዎችህ፡ሁሉ፡ትድናላችሁ[illegible]

፴፪ አሉት።ዮሐ፡፫፡፲፮።ለእርሱና[illegible] በቤቱም፡ላሉ፡ሰዎች፡ሁሉ፡የ[illegible] እግዚአብሔርን፡ቃል፡ነገር[illegible] ቸው።

፴፫ በዚያም፡ጊዜም፡በሌ[illegible] ት፡ወስዱ፡ቍስላቸውን፡አጠ[illegible] ቸው፡ያንጊዜውን፡እርሱ፡ከቤ[illegible] ተ፡ሰዎቹ፡ሁሉ፡ገራ፡ተጠመቁ[illegible]

፴፬ ወደ፡ቤቱም፡አግብቶ፡ማዕድ[illegible] አቀረበላቸው፡በእግዚአብሔ[illegible] ርም፡ስለ፡አመነ፡ከቤቱ፡ሰዎች[illegible] ሁሉ፡ጋራ፡ደስ፡አለው።

፴፭ በነጋ[illegible] ም፡ጊዜ፡ሹማምንቱ፡እነዚያን[illegible] ሰዎች፡ፈትተህ፡ልቀቃቸው፡ብለው፡ሎሌዎቻቸውን፡ላኩ[illegible]

፴፮ የማዘቱ፡ቤት፡ጠባቂውም፡ተወጡ፡ዘንድ፡ሹማምንቱ፡ልከዋልና፡አሁንም፡ውጡ፡በደኅናም፡ሒዱ፡ብሎ፡ለጳውሎስ፡የምስራቹን፡ነገረው።

፴፯ ጳውሎስ፡ግን፡አላቸው፡እኛ፡የሮም፡ሰዎች፡ስንሆን፡ያለ፡ፍርድ፡በግልጽ፡ገርፈው፡በማዘቱ፡ቤት፡አገቡን፡አሁን፡ደግሞ፡በሥውር፡ያወጡናልን፡እነርሳቸው፡መጥተው

ያውጡኝ፡እንጂ፡አይሆን፤
ም፡አላቸው፤ም፡፳፪፡፳፭፡፳፪፡፳፰፡
፴፰ ሎሳሌትም፡ይህን፡ነገር፡ለ
ሹማምንቱ፡ነገሩ፡የሮም፡ሰ
ዎችም፡እንደሆኑ፡በሰሙ፡ጊ
ዜ፡ፈሩ፤ወደ፡እነርሳቸውም
መጥተው፡በመለማመጥ፡አ
ወጡዋቸው፡ከከተማም፡ይ
ወጡ፡ዘንድ፡ለመኑዋቸው፤
፵ ማቴ፡፲፡፲፬፤ከግዛትም፡ቤተ
ወጥተው፡ወደ፡ልድያ፡ቤት፡ገ
ቡ፡ወንድሞችም፡ባዩ፡ጊዜ፡አ
ፅናንዋቸው፡ከዚያም፡ወጥ
ተው፡ሔዱ።ምዕራፍ፡፲፯።
ስለ፡ደጋጎች፡አረማውያን፡እምነ
ት፡ስለ፡ኢያሶን፡መያዝ፡ስለ፡የቤ
ርያ፡ሰዎች፡ትምህርት፡መፈ
ቀበል፤ስለ፡ጳውሎስ፡ስብከት
በአቴና፡ስለ፡ድዮናስዮስ፡አ
፩ ምነት፤ወደ፡አምፊጶሊስና፡ወ
ደ፡አጶሎንያም፡በሔዱ፡ጊዜ፡የአ
ይሁድ፡መስጊድ፡ወዳለበ
ት፡ወደ፡ተሰሎንቄ፡መጡ፤፩፡
፪ ተሰ፡፪፡፪፤ጳውሎስም፡እንደ
ልማዱ፡ወደ፡እነርሳቸው፡ገብ
ቶ፡ሶስት፡ሰንበት፡ከመጽሐፍ
፫ ት፡ይነጋገራቸው፡ነበር፤ክርስ
ቶስ፡እንዲሞትና፡ከሙታንም
እንዲነሣ፡ይህም፡እኔ፡የምሰ
ብከላችሁ፡ኢየሱስ፡እርሱ፡
ክርስቶስ፡ነው፡እያለ፡ተርጉ
ሞ፡ያስረዳቸው፡ነበረ፤ሉ፡፳፬፡
፬ ፳፮፡፵፮፤ከእነርሳቸውና፡ከ
ደጋጎች፡አረማውያንም፡ብ
ዙ፡ሰዎች፡ከታላላቆች፡ሴቶች
ም፡ጥቂቶች፡ያይደሉ፡አምነ
ው፡ከጳውሎስና፡ከሲላስ፡ጋራ
፭ ሆኑ፤የማያምኑ፡አይሁድ፡ግ
ን፡ቀንተው፡ክፉ፡ሰዎችን፡ከገ
በያ፡አመጡ፡ሰዎችንም፡ሰብ
ስበው፡ከተማውን፡አወኩ፡ወ
ደ፡ሐዝብም፡ይወስዱዋቸው፡
ዘንድ፡ፈልገው፡በኢያሶን፡ቤት
፮ አድብተው፡ቆሙ፤ባላገኙዋ
ቸውም፡ጊዜ፡ኢያሶንና፡ከዚያ
የነበሩትንም፡ወንድሞች፡ወደ
ከተማው፡አለቆች፡ጐተቱዋ
ቸው፡እንዲህ፡ብለው፡እየጮሁ
ዓለምን፡ያወኩ፡እነዚህ፡ደግሞ
ወደዚህ፡መጡ፤ም፡፲፮፡፳፡፩፡ነገ
፯ ፲፰፡፲፯፤ይህም፡ኢያሶን፡ተቀ
በላቸው፡እነርሱም፡የቄሣርን
ትእዛዝ፡የሚቃወም፡ነገር፡ያ
ደርጋሉ፡ኢየሱስ፡የሚሉትም
ሌላ፡ንጉሠ፡አለ፡እያሉ፡ይሰብ
፰ ካሉ፤ሉቃ፡፳፫፡፪፤ሕዝቡና፡የ
ከተማውም፡አለቆች፡ይህን፡ነ
፱ ገር፡በሰሙ፡ጊዜ፡ታወኩ፤ከኢ
ያሶንና፡ከሌሎችም፡ዋስ፡ተቀ
፲ ብለው፡ለቀቁዋቸው፤ወንድሞ
ችም፡በዚያ፡ጊዜ፡ጳውሎስን፡ና
ሲላስን፡በሌሊት፡ወደ፡ቤርያ፡አ

ግር፡ሰደድዋቸው። ከዚያም፥
በደረሱ፡ጊዜ፡ወደ፡አይሁድ፡መ
፲፭ ስጊድ፡ገቡ። እነርሳቸውም፡በ
ተሰሎንቄ፡ከሚኖሩት፡ይልቅ
የሚሻሉ፡ነበሩ፡ቃሉንም፡በ
ፍጹም፡ደስታ፡ተቀብለው፡ነገ
ሩ፡እንደዚሁ፡እንደሆነ፡ብለው
ዘወትር፡መጻሕፍትን፡ይመረ
ምሩ፡ነበሩ። ሉቃ፡፲፮፡፲፯፡ሉ፡፲
፲፮ ፯፡፳፱፡ዮሐ፡፭፡፴፱። ከእነርሳቸ
ውና፡ከግሪኮችም፡ሴቶች፡ተል
ልቆች፡ወንዶችም፡ጥቂቶ፡
፲፯ ደይደሉ፡ብዙዎች፡አመኑ። በተ
ሰሎንቄም፡ያሉት፡አይሁድ፡ጳው
ሎስ፡በቤርያም፡ደግሞ፡የእግዚ
አብሔርን፡ቃል፡እንደ፡ሰበከ፡በሰ
ሙ፡ጊዜ፡ሕዝቡን፡ያውኩና፡ያሰ
ነሡ፡ዘንድ፡ወደዚያው፡መጡ።
፲፰ ፩፡ተሰ፡፪፡፲፬። በዚያ፡ጊዜም፡ወን
ድሞች፡ጳውሎስን፡በፍጥነት
ወደ፡ባሕር፡ይሔድ፡ዘንድ፡ሰደዱ
ት፡ሲላስና፡ጢሞቴዎስ፡ግን፡በ
፲፱ ዚያው፡ቀሩ። ምዕ፡፲፯፡፩። ጳውሎ
ስን፡የሸኙት፡ግን፡ከእርሱ፡ጋራ
አቴና፡ደረሱ፡ፈጥነውም፡ወደ፡እ
ርሱ፡ይመጡ፡ዘንድ፡ሲላስና፡ወ
ደ፡ጢሞቴዎስ፡ልኮ፡ሰደዳቸው።
፳ ጳውሎስ፡ግን፡በአቴና፡ሲጠብ
ቃቸው፡ከተማው፡ሁሉ፡ብዙ፡
ጣዖት፡ሲያመልኩ፡ባየ፡ጊዜ፡ሰ
፳፩ ውነቱ፡ተበሳጨበት። ስለዚህ፡

ም፡በመስጊድ፡ከአይሁድ፡ጋራ
እግዚአብሔርንም፡ከሚፈሩ፡
ዎች፡ጋራ፡ሁልጊዜም፡በገበያ
ከሚያገኛቸው፡ሁሉ፡ጋራ፡ይ
፳፪ ጋገር፡ነበረ። ከኤጲቆሮስና፡
እስጦኢኮችም፡ወገን፡አያሌ
ሳፎች፡ይቃወሙት፡ነበሩ፡እ
ሌቶቹም፡ይህ፡ለፍላፊ፡ምን፡
ናገር፡ይፈልጋል፡አሉ፡ሌሎ
ም፡የኢየሱስን፡የትንሣኤው
ነገር፡ሰለ፡ሰበከላቸው፡አዲ
ች፡አማልክትን፡የሚያስተ
ር፡ይመስላል፡አሉ። ፩፡ቆር፡፩፡፲
፳፫ ይዘውም፡አርዮስፋጎስ፡ወደ፡ተ
ባለው፡የፍርድ፡ቤት፡ወሰዱት፡እ
ንዲህ፡ሲሉ፡ይህን፡የምታስተ
ምረውን፡አዲስ፡ትምርት፡እና
፳፬ ውቅ፡ዘንድ፡ይቻለናልን፡ቀበጃ
ሮዋችን፡አዲስ፡ነገር፡ታሰማና
ለህና፡እኛም፡ይህ፡ነገር፡ምን፡እ
ንደሆነ፡እናውቅ፡ዘንድ፡እንወደ
፳፭ ለን። የአቴና፡ሰዎችና፡በዚያ፡
ም፡የነበሩ፡እንግዶች፡ሁሉ፡አ
ዲስ፡ነገርን፡ከመናገርና፡ከመ
ስማት፡በቀር፡ሌላ፡ሐሳብ፡የላ
፳፮ ቸውም፡ነበርና። ጳውሎስም፡በ
አርዮስፋጎስ፡መካከል፡ቆሞ
አለ፡እናንተ፡የአቴና፡ሰዎች፡በ
ሥራችሁ፡ሁሉ፡ጣዖታትን፡ጣ
ምለክ፡እንድታበዙ፡አያችኋለ
፳፯ ሁ። እኔ፡በዚህ፡ሳልፍ፡ለማይታ

10

ወቅ፡አምላክ፡የሚል፡ጽሕፈ
ት፡ያለበት፡የምታመልኩበት
ን፡እኔ፡መሠዊያችሁን፡አገኘሁ
ይህንንም፡ሳታውቁ፡የምታመ
ልኩትን፡እኔ፡እገልጽላችኋለሁ
፳፬ ዓለሙንና፡በእርሱም፡ያለውን
ሁሉ፡የፈጠረ፡አምላክ፡እርሱ፡
የሰማይና፡የምድር፡ጌታ፡ነውና
እጅ፡በሠራው፡መቅደስ፡አይኖር
ምቅም፡፯፡፵፰ቀእርሱም፡ሕይ
ወትንና፡እስትንፋስን፡ሌላውን
ም፡ነገር፡ሁሉ፡ይሰጣልና፡እንደ፡
ችግረኛ፡የሰው፡እጅ፡አያገለግለ
፳፮ ውምቅመዝ፡፵፡፰ቀእርሱም፡በ
ምድር፡ሁሉ፡ላይ፡ይኖሩ፡ዘንድ
አህዛብን፡ ሁሉ፡ከአንድ፡ደም
ፈጠረ፡ይኖሩበትም፡ዘንድ፡ዘ
መንና፡ዓመታትን፡ወሰነ፡ሠራ
፳፯ ሳቸውቅዘዳ፡፴፪፡፰ቀምናል
ባት፡እግዚአብሔርን፡ፈልገው፡
ያገኙት፡እንደሆነ፡እርሱ፡ግን፡ከ
እኛ፡ከሁላችን፡የራቀ፡አይደለም
፳፰ እኛ፡በእርሱ፡ሕያዋን፡ነንና፡እን
ቀሳቀሳለን፡እንኖራለንም፡ከ
እናንተ፡ቀኔ፡የሚቀኙ፡ብልሆች
እኛ፡ዘመዶቹ፡ነን፡ብለው፡እንደ
፳፱ ተናገሩቅእንኪያስ፡የእግዚአብ
ሔር፡ዘመዶች፡ከሆን፡በሰው ፡
አሳብና፡ብልሐት፡የተቀረጸ፡
ወርቅም፡ብርም፡ድንጊያም፡ሆ
ኖ፡ይህ፡አምላክን፡ይመስላል፡አ
ል፡ዘንድ፡አይገባም፨ዘፍ፡፩፡፳፮
፴ ኢሳ፡፵፡፲፰ቀያንንም፡የድንቁር
ናውን፡ወራት፡እግዚአብሔር፡እ
ሳለፈው፡አሁን፡ግን፡በየቦታቸ
ው፡ንስሐ፡ይገቡ፡ዘንድ፡ሰውን፡
ሁሉ፡አዘዘቅም፡፲፬፡፲፮፤ሉ፡፳፬፡
፴፩ ፵፯ቀበዚያ፡ባዘጋጀው፡ሰው፡እ
ጅ፡በዓለሙ፡ቅን፡ፍርድ፡የሚፈ
ርድባትን፡ወስኖዋልና፡ስለዚህ
እነርሱን፡ከሙታን፡ማስነሣቱ
፡ሁሉን፡ወደ፡ሃይማኖት፡መለሳ
ቸውቅሮሜ፡፲፡፲፬
፴፪ ከሙታንም፡መነሣትንም፡በሰ
ሙ፡ጊዜ፡እኩሌቶቹ፡አፌዙበት
እኩሌቶቹም፡ይህንስ፡በሌላ፡ጊ
ዜ፡እንሰማሃለን፡አሉትቅ፩፡ቆሮ
፴፫ ፩፡፲፭፡፲፪ቀጳውሎስም፡እንዲሁ፡ከ
፴፬ መካከላቸው፡ወጣ፤ከእነርሱ
ም፡ብዙ፡ሰዎች፡አምነው፡ተከ
ተሉት፡ከእነርሳቸውም፡አንዱ
የአርዮስፋጎስ፡ፈራጅ፡ዲዮና
ስዮስ፡ነበረ፡ስምዋንም፡ደማሪ
ስ፡የሚሉዋት፡አንዲስ፡ሴት፡ሌሎ
ችም፡ከእነርሳቸው፡ጋራ፨

ምዕራፍ፡፲፰።

ስለ፡ጳውሎስ፡ስብከት፡በቆሮን
ቶስ፡ስለ፡ጵርስቅላ፡አቂላ፡ስለ
ሶስቴንስ፡መደብደብ፤ስለ፡ጳ
ውሎስ፤እራሱን፡መላጨት፤ስ
ለ፡አጵሎስ፡ወደ፡አርድእት፡መ
ጨመር፨

፩ ከዚህ፡ በኋላ፡ ጳውሎስ፡ አቴናን፡ ለቆ፡ ወደ፡ ቆሮንቶስ፡ መጣ።
፪ በዚያም፡ አገሩ፡ ጳንጦስ፡ የሚሆን፡ ስሙን፡ አቂላስ፡ የሚሉት አንድ፡ አይሁዳዊ፡ አገኘ፡ እርሱም፡ ከጥቂት፡ ወራት፡ በፊት፡ ከሚስቱ፡ ከጵርስቅላ፡ ጋራ፡ ከኢጣልያ፡ መጣ፡ አይሁድ፡ ከሮሚ፡ ይወጡ፡ ዘንድ፡ ቀላውዴዎስ፡ አዞ፡ ነበርና። ሮሜ፡ ፲፮፡ ፫።
፫ ሥራቸውም፡ አንድ፡ ስለ፡ ነበረ፡ ወደ፡ እነርሳቸው፡ መጥቶ፡ ከእነርሳቸው፡ ጋራ፡ ተቀመጠ፡ ሥራቸው፡ ድንኳን፡ መስፋት፡ ነበረ። ፩ቆሮ፡ ፬፡ ፲፪።
፬ ጳውሎስም፡ በየሰንበቱ፡ ሁሉ፡ በመስጊድ፡ እየሰበከ፡ አይሁድንና፡ አረማውያንን፡ ያሳምን፡ ነበረ።
፭ ሲላስና፡ ጢሞቴዎስም፡ ከመቄዶንያ፡ በመጡ፡ ጊዜ፡ ጳውሎስ፡ ኢየሱስ፡ እርሱ፡ ክርስቶስ፡ እንደ ሆነ፡ ለአይሁድ፡ እስረድቶ፡ እየመሰከረ፡ ቃሉን በማስተማር፡ ይበረታ፡ ነበር፤ ም፡ ፲፯፡ ፲፬፡ ፲፭።
፮ እነርሳቸውም፡ በተቃቃወሙትና፡ በተሳደቡ፡ ጊዜ፡ ልብሱን፡ እያራገፈ፡ ደማቸሁ፡ በራሳቸሁ፡ ነው፡ እኔ፡ ንጹሕ ነኝ፡ ከእንግዲህም፡ ወዲህ፡ ወደ፡ አሕዛብ፡ እሔዳለሁ፡ አላቸው። ም፡ ፲፫፡ ፶፩፡ ፳፡ ፳፮።
፯ ከዚያም ወጥቶ፡ ስሙን፡ ዮስጦስ፡ ወደ ሚባል፡ እግዚአብሔርን፡ ወደ አሚፈራ፡ ሰው፡ ቤት፡ ገባ፡ ቤ
፰ ለመስጊድ፡ የቀረበ፡ ነበረ። የመ ስጊዱ፡ አለቃ፡ ቀርስጶስም፡ ከ ቤቱ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ጋራ፡ በጌታ አመነ፡ ከቆሮንቶስም፡ ወገ ብዙ፡ ሰዎች፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ አ
፱ ነው፡ ተጠመቁ። ጌታም፡ ሌሊ በራእይ፡ ጳውሎስን፡ አለው፡ ትፍራ፡ ነገር፡ ግን፡ ተናገር፡ ዝ
፲ ም፡ አትበል። በዚህ፡ ከተማ ብዙ፡ ሕዝብ፡ ስላለኝ፡ እኔ እንተ፡ ጋራ፡ ነኝና፡ ማንም፡ ክፉ ሊያደርግብህ፡ የሚችል፡ የለም። ኤር፡ ፩፡ ፰፤ ሆሴ፡ ፪፡ ፳፫፤ ዮሐ፡ ፲፡ ፲፮፡
፲፩ በቆሮንቶስም፡ የእግዚአብሔርን፡ ቃል፡ እያስተማረ፡ ዓመት፡ ከ፮ት፡ ወር፡ በመካከላቸው፡ ተቀመጠ።
፲፪ ጋልዮስም በአካይያ፡ በተሾመ፡ ጊዜ፡ አይሁድ፡ ተባብረው፡ በጳውሎስ ላይ፡ ተነሡ፡ ወደ፡ ሸንጎም፡ አመጡት፡
፲፫ እንደዚህ፡ ሲሉ፡ ይህ፡ ሰው፡ ያለ፡ ሕግ፡ እግዚአብሔርን፡ ያመልኩ፡ ዘንድ፡ ሰዎችን፡ ያባብላል።
፲፬ ጳውሎስም፡ አፉን፡ ገልጾ፡ ሊናገር፡ በወደደ፡ ጊዜ ጋሊዮስ፡ አይሁድን፡ አላቸው እናንተ፡ አይሁድ፡ ተበድላችሁ ብትሆኑና፡ ወይም፡ ሊላ፡ ክፉ፡ ነገር፡ ቢኖር፡ በጽሞታ፡ እከራከ

ራቸሁና፡ አሰማቸሁ፡ ዘንድ ይገባ፡ ነበረ፨ ም፡ ፳፫፡ ፲፩፡ ፲፰። ስለ፡ ትምህርትና፡ ስለ፡ ስም፡ ስለ፡ ሕጋቸሁም፡ የምትከራከሩ፡ ከሆነ፡ ግን፡ እናንተው ወቁ፡ እኔም፡ በዚህ፡ ነገር፡ ፈራጅ፡ እሆን፡ ዘንድ፡ አልወድም፨ ማቴ፡ ፳፯፡ ፳፬፡ ዮሐ፡ ፲፰፡ ፴፩፨ ከዚያ፡ ወደያም፡ ከጉባዔው፡ ፊት፡ አስወገዳቸው፨ ሕዝቡም፡ ሁሉ፡ የመስጊዱን፡ አለቃ፡ ሶስቴንስን፡ ይዘው፡ በጉባዔው፡ ፊት፡ መቱት፡ ጋልዮስም፡ በዚሁ፡ ነገር፡ ግድ፡ የለውም፡ ነበር፨ ፩ ቆሮ፡ ፩፡ ፩፨

፲፰ ጳውሎስ፡ ግን፡ እጅግ፡ ቀን፡ ተቀመጠ፡ ከዚያም፡ በኋላ፡ ወንድሞቹን፡ ተሰናብቶ፡ ከጵርስቂላና፡ ከአቂላ፡ ጋራ፡ በመርከብ፡ ወደ፡ ሶርያ፡ ሔደ፡ ስለትም፡ ነበረበትና፡ ራሱን፡ በክንክሬያ፡ ተላጭቶም፡ ፳፩፡ ፳፬፡

፲፱ ዘኍ፡ ፮፡ ፱፡ ፲፰፨ ወደ፡ ኤፌሶንም፡ በደረሰ፡ ጊዜ፡ እነዚያን፡ ከዚያ፡ ተዋቸው፡ እርሱ፡ ግን፡ ወደ፡ መስጊድ፡ ገብቶ፡ ለአይሁድ፡ ይነጋገራቸው፡ ነበረ፨

፳ እነርሱቸውም፡ ብዙ፡ ቀን፡ እንዲቀመጥ ሳቸው፡ ለመኑት ነገር፡ ግን፡ ፈቃዱ፡ አልሆነም፡

፳፩ ሲሰናበታቸውም፡ የሚመጣው፡ በዓል፡ በኢየሩሳሌም አውል፡ ዘንድ፡ ይገባኛል፡ የእግዚአብሔር፡ ፈቃዱ፡ የሆነ፡ እንደሆነ፡ ግን፡ ወደ፡ እናንተ፡ እመለሳለሁ፡ አላቸው፡ ከኤፌሶንም፡ በመርከብ፡ ሔደ፨ ፩ ቆሮ፡ ፬፡ ፲፱፡ ዕብ፡ ፮፡ ፫፡ ያዕ፡ ፬፡ ፲፭፨

፳፪ ወደ፡ ቂሣርያም፡ በመጣ፡ ጊዜ፡ ከዚያ፡ ወጥቶ፡ ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡ ለማኅበሩ፡ ሰላምታ፡ ሰጠ

፳፫ ና፡ ወደ፡ አንጾኪያ፡ ወረደ፨ በዚያም፡ ጥቂት፡ ቀን፡ ከተቀመጠ በኋላ፡ ከዚያ፡ ወጥቶ፡ ሔደ፡ በገላትያና፡ በፍርግያም፡ አገር፡ ሁሉ፡ በተራ፡ እየዞረ፡ ደቀ፡ መዛ

፳፬ ሙርትን፡ አፀናና፨ ከእስክንድርያም፡ አገር፡ ነገር፡ አዋቂና፡ መጽሐፍ፡ በመተርጐም፡ ብርቱ፡ የሆነ፡ ስሙን፡ አጵሎስ፡ የሚሉት፡ አንድ፡ አይሁዳዊ፡ ሰው፡ ነበር፡ ወደ፡ ኤፌሶንም፡ መ

፳፭ ጣ፨ ፩ ቆሮ፡ ፫፡ ፮፨ ይህም፡ የእግዚአብሔርን፡ መንገድ፡ የተማረ፡ ነበረ፡ በዮሐንስም፡ ጥምቀት፡ ብቻ፡ የተቀመጠ፡ ሲሆን፡ ስለ፡ ኢየሱስ፡ ለመናገርና፡ ለማስተማር፡ የሚቃጠል፡ የትጋት

፳፮ መንፈስ፡ ነበረበት፨ እርሱም በመስጊድ፡ በግልጽ፡ ይሰብክ ጀመረ፡ ጵርስቅላና፡ አቂላስም፡ በሰሙት፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ቤታ

ቸው፡ወስደው፡የእግዚአብ
ሔርን፡መንገድ፡በትክክል፡
፳፯ አስረዱት፨ እርሱም፡ወደ፡አ
ካይያ፡መሔድ፡በወደደ፡ጊዜ፡
ወንድሞች፡አፅናኑት፡ይቀበ
ሉትም፡ዘንድ፡ወደ፡ደቀ፡መዛ
ሙርት፡ጻፉለት፡ወደ፡እነርሳ
ቸውም፡በደረሰ፡ጊዜ፡ምእመ
ናን፡በእግዚአብሔር፡ጸጋ፡እጅ
፳፰ ግ፡ጠቀማቸው፨ ኢየሱስም፡
እርሱ፡ክርስቶስ፡እንደሆነ፡ከ
መጻሕፍት፡እየገለጸ፡አይሁ
ድን፡በሁሉ፡ፊት፡በፅኑ፡ተሟግ
ፅ፡ይገሥፅ፡ነበረ፨ ም፡፱፡፳፮፡
፲፯፡፩፨

ምዕራፍ፡፲፱፨

ስለ፡ጳውሎስ፡ስብከት፡በኤፌ
ሶን፤ በጳውሎስ፡መጠምጠሚ
ያ፡ቍራጭ፡ብዙ፡ድውያን፡እን
ደ፡ተፈወሱ፤ ስለ፡አስቂዋ፡ል
ጆች፤ ስለ፡ጠንቋዮች፡መጽሐ
ፋቸውን፤ በእሳት፡ማቃጠል፤
ስለ፡ድሚጥሮስና፡ስለ፡አርጤ
ሚስ፨

፩ አጵሎስም፡በቆሮንቶስ፡ሳለ፡
ጳውሎስ፡በላይኛው፡አገር፡ዞር
ወደ፡ኤፌሶን፡መጣ፡በዚያም
ብዙ፡ደቀ፡መዛሙርትን፡አገኘ
፪ ም፡፲፰፡፲፱፡፳፬፨ እነርሱንም፡
በአመናችሁ፡ጊዜ፡መንፈስ፡
ቅዱስን፡ተቀበላችሁን፡አላቸ
ው፡እነርሳቸውም፡መንፈስ፡ቅ
ዱስ፡እንዳለ፡ስንኳ፡አል
ነም፡አሉት፨ ም፡፲፡፵፯፡ዮሐ
፫ ፯፡፴፱፨ እርሱም፡እንኪያ፡በ
ን፡ተጠመቃችሁ፡አላቸ
ነርሳቸውም፡በዮሐንስ፡ጥ
፬ ቀት፡አሉት፨ ጳውሎስም
ዮሐንስ፡ከእርሱ፡በኋላ
ሚመጣው፡በኢየሱስ፡ክ
ቶስ፡ያምኑ፡ዘንድ፡ለሕዝ
እየሰበከ፡በንስሐ፡ጥም
አጠመቀ፡አላቸው፨ ማቴ
፭ ፫፡፲፩፨ ይህንንም፡በሰሙ፡ጊ
በጌታችን፡በኢየሱስ፡ክርስ
፮ ስ፡ስም፡ተጠመቁ፨ ጳውሎ
ስም፡እጁን፡በጫነባቸው፡ጊ
ዜ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ወረደላቸው፡ያን
ጊዜም፡አዲስ፡ቋንቋ፡ተገለጸላቸው፡ት
፯ ቢትም፡ተናገሩ፤ ም፡፰፡፲፯፡፲፡፵፬፡፵፮፡ ሰዎ
ም፡ሁሉ፡፲፪፡ት፡ያህል፡ነበሩ፨
፰ ፱፨ ወደ፡መስጊድም፡እየገ
በግልጽ፡ይናገር፡ነበረ፡ስለ፡እ
ግዚአብሔር፡መንግሥት፡
ነገር፡እያስተማራቸውና፡እ
ያስረዳቸው፡ሦስት፡ወር፡ያ
፱ ህል፡ተቀመጠ፨ በተሰበሰበ
ውም፡ሕዝብ፡ፊት፡እጅግ፡
ሰዎች፡ትምህርቱን፡እየተቃ
ወሙና፡መንገዱንም፡እየነቀ
ፉ፡ባሳመኑ፡ጊዜ፡ከእነርሳቸ
ው፡ራቀ፡ደቀ፡መዛሙርትን
ም፡ከእነርሳቸው፡ለይቶ፡ስ

ሙን፡ጢራኑስ፡የሚሉት፡በአ
ንድ፡መምህር፡ቤት፡ዕለት፡ዕ
ለት፡ይነጋራቸው፡ነበረ፨፪ጢ
ሞ፡፩፡፲፫፡ም፡፱፡፯፨እንዲሁም
በእስያ፡ያሉት፡አይሁድና፡አ
ረማውያንም፡ሁሉ፡የጌታች
ን፡ቃል፡እስኪሰሙ፡ድረስ፡
ሁለት፡ዓመት፡ኖረ፨ እግዚአ
ብሔርም፡በጳውሎስ፡እጅ፡ታ
ላቅ፡ኃይል፡አደረገ፨ም፡፲፩
፡፡ከልብሱም፡ሜፍና፡ከመ
ከምጠሚያው፡እየወሰዱ፡በ
ድውያን፡ላይ፡ያኖሩ፡ነበር፡ደ
ዌያቸውም፡ይለቃቸው፡ነበረ፡
ዲያሞም፡ከክፉዎች፡አጋንንት
ከእነርሳቸው፡ይወጡ፡ነበሩ፨
ም፡፫፡፲፫፨ከአይሁድም፡አስማ
ት፡እያደረጉ፡የሚዞሩ፡ሰዎች፡
ክፉዎች፡አጋንንት፡ባሉባቸው
ላይ፡ጳውሎስ፡በሚያስተምር
በት፡በኢየሱስ፡እናምላቸኋለ
ን፡እያሉ፡የጌታችን፡የኢየሱስ
ን፡ስም፡ይጸሩባቸው፡ጀመሩ።
፲፬ ሉቃ፡፱፡፵፱፨እንዲህም፡ያደረጉ
ሰዎች፡የካህናቱ፡አለቃ፡የአይ
ሁዳዊው፡የአስቄዋ፡ልጆች፡ና
ቸው፡ቍጥራቸውም፡ሰባት፡ነበ
፲፭ ር። ክፉውም፡ጋኔን፡መልሶ፡ኢየ
ሱስን፡አውቀዋለሁ፡ጳውሎስ
ንም፡ተረድቼዋለሁ፡እናንተስ
፲፮ እነማን፡ናችሁ፡አላቸው፨ያም

ክፉ፡ጋኔን፡ያለበት፡ሰው፡አሳ
ደዳቸው፡በረታባቸው፡አቸነ
ፋቸውም፡ቈስለው፡ከዚያ፡ቤ
ት፡ዕራቍታቸውን፡እስኪሸሹ
፲፯ ድረስ፨ይህም፡በኤፌሶን፡በ
ሚኖሩት፡በአይሁድና፡በአረ
ማውያን፡ሁሉ፡ዘንድ፡ታወቀ፡
በሁሉም፡ዘንድ፡ፍርሃት፡ወደ
ቀባቸው፡የጌታም፡የኢየሱስ፡
ስም፡ታላቅ፡ሆነ፨ም፡፫፡፫፡፲፭፡
፲፰ ካመኑትም፡እጅግ፡ሰዎች፡ኃ
ጢአታቸውን፡እያስታወቁ፡ያ
ደረጉትንም፡እየተናገሩ፡ይ
፲፱ መጡ፡ነበሩ፨ብዙዎችም፡አስማ
ተኞችም፡መጽሐፋቸውን፡ሰብ
ስበው፡በሰዉ፡ሁሉ፡ፊት፡አቃጠሉ
ት፡ዋጋውም፡ቢታሰብ፡አምሳ፡ሺ
፳ ብር፡ሆኖ፡ተገኘ፨እንዲህም፡እያ
ለ፡የእግዚአብሔር፡ቃል፡በኃይል
ያድግና፡ይበረታ፡ነበር፨ም፡፯፡፯
፳፩ ይህም፡ነገር፡በተፈጸመ፡ጊዜ፡ጳ
ውሎስ፡በመቄዶንያና፡በአካይ
ያ፡በኩል፡አልፎ፡ወደ፡ኢየሩሳሌ
ም፡ይሄድ፡ዘንድ፡በመንፈስ፡አሰ
በ፡ወደዚያም፡ደርሼ፡ሮሜን፡አይ
ዘንድ፡ይገባኛል፡አለ፨ም፡፳፫፡፲፩፡
፳፪ ከሚያገለግሉትም፡ጢሞቴዎ
ስንና፡ኤራስጦስን፡ሁለቱን፡
ወደ፡መቄዶንያ፡ላከ፡እርሱ፡ግን፡
በእስያ፡እያሌ፡ቀን፡ተቀመጠ
ም፡፲፰፡፲፱፡ሮሜ፡፲፮፡፳፫።

፳፫ በዚያም፡ ወራት፡ ስለዚህ፡ ትም
ህርት፡ ብዙ፡ ሁከት፡ ሆነ። ፱፡ ፪
፳፬ ቆሮ፡ ፩፡ ፲፫፥ ብር፡ ሠሪም፡ የሆነ፡ ስ
ሙን፡ ድሜጥሮስ፡ የሚሉት፡ አን
ድ፡ ሰው፡ ነበረ፡ እርሱም፡ ለአርጤ
ምስ፡ የብር፡ መቅደስ፡ እየሠራ፡
አንጥረኞችን፡ እጅግ፡ ይጠቅም
፳፭ ነበረ። ፲፮፡ ፲፱፥ እርሱም፡ ይህ
ን፡ ሥራ፡ የሚሠሩትን፡ና፡ የሥራ
ጓደኞቻቸውን፡ ሁሉ፡ ሰብስቦ
አላቸው፡ እናንተ፡ ሰዎች፡ ጥቅ
ማችን፡ በዚህ፡ ሥራ፡ እንደ፡ ሆነ፡
፳፮ ታውቃላችሁ። እነሆም፡ ይህ፡ ጳ
ውሎስ፡ በእስያም፡ ሁሉ፡ ነው፡ እ
ንጂ፡ በኤፌሶን፡ ብቻ፡ ያይደለ፡ እ
ነዚህ፡ በእጅ፡ የተሠሩት፡ አማል
ክት፡ አይደሉም፡ ብሎ፡ እጅግ፡ ሰ
ዎችን፡ እንደ፡ አስካደና፡ እንደ፡ አ
ሳቶ፡ አይታችኋል፡ ሰምታችኋ
፳፯ ል። የምንግድ፡ ሥራችን፡
ስን፡ ተናቀ፡ ብቻ፡ አይደለም፡ እ
ስያ፡ ና፡ ዓለሙም፡ ሁሉ፡ የሚያ
ወልካት፡ የታላቂቱ፡ አርጤም
ስ፡ መቅደስ፡ ምናምን፡ ሁኖ፡ ይቆ
ጠራል፡ እንጂ፡ ታላቅነትዋም፡ ይሻ
፳፰ ራል። ይህንም፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ ቍጣ
ሞላባቸው፡ የኤፌሶን፡ አርጤ
ምስ፡ ታላቅ፡ ናት፡ እያሉ፡ ጮሁ።
፳፱ ከተማውም፡ ሁሉ፡ ተሸበረ፡ ሁ
ሉም፡ በአንድነት፡ ወደ፡ ጨዋታ
ስፍራ፡ ሮጡ፡ የመቄዶንያንም፡
ሰዎች፡ የጳውሎስን፡ ባልንጀሮ
ጋይዮስንና፡ አርሰርኮስን፡ እየ
ተቱ፡ ከእነርሱ፡ ጋራ፡ ወሰ
፴ ዋቸው። ፲፬፡ ቆሮ፡ ፩፡ ፲፭። ጳው
ሉ፡ ግን፡ ወደ፡ ሕዝቡ፡ ይገባ፡ ዘን
በወደደ፡ ጊዜ፡ ደቀ፡ መዛሙ
፴፩ ከለከሉት። ከእስያም፡ ሹሞ
ወዳጆቹ፡ የሆኑ፡ ወደ፡ ጨዋታ
ፍራ፡ እንዳይሔድ፡ ልከው፡ ለ
፴፪ ኑት። ወዲያና፡ ወዲህም፡ አ
ይጮሁ፡ ነበሩ፡ በጉባዔው፡
ድብልቅ፡ ሁኖ፡ ነበር፡ የሚበ
ጡት፡ ስንኳ፡ ስለምን፡ እንደ፡ ተ
፴፫ በሰቡ፡ አላወቁም፡ ነበር። በዚያ
የተሰበሰቡትም፡ አይሁድ፡ ከመ
ካከላቸው፡ አይሁዳዊው፡ እስክ
ንድሮስን፡ አስነሡ፡ እርሱም፡ ለ
ሕዝቡ፡ ይናገር፡ ዘንድ፡ በእጁ፡ ጠ
፴፬ ቀሰ። አይሁዳዊም፡ እንደ፡ ሆነ፡
ባወቁ፡ ጊዜ፡ ሁለት፡ ሰዓት፡ የሚ
ሆን፡ የኤፌሶኒቱ፡ አርጤምስ
ታላቅ፡ ናት፡ እያሉ፡ ሁሉም፡ በአ
፴፭ ንድነት፡ ጮሁ። የከተማው፡ ጸ
ሐፊ፡ ግን፡ ሰዎችን፡ ዝም፡ አሰኝቶ
እንዲህ፡ አለ፡ እናንተ፡ የኤፌሶ
ን፡ ሰዎች፡ የኤፌሶን፡ ከተማ፡ ታ
ላቂቱ፡ አርጤምስንና፡ ከሰማ
ይ፡ የወረደውን፡ ጣዖትዋን፡ እን
ድትጠብቅ፡ የማያውቅ፡ ሰው፡
፴፮ ማነው። በዚህም፡ የሚከራ
ከር፡ ያለ፡ አይመስለኝም፡ ስለሆነ

…ን፡በቾኩሳና፡በክርክር፡
…ደሆን፡በቀስቃ፡ቃደርጉት
…ንዱ፡ይገባል፨እነዚህንም
…መቀደሳቸሁን፡ዕቃ፡ያልሰ
…ቁ፡አምላካችሁንም፡ያል
…ደቡ፡ሰዎቸ፡አመጣኋቸው
…ሚጥሮስና፡ከእርሱ፡ጋራ
…ሉት፡አንጥረኞች፡ግን፡ሌ
…ነገር፡እንደ፡አላቸው፡አ
…፡መጋብያም፡ሹማምንት
…ም፡አሉ፡እርስ፡በርሳቸው፡
…ይከራከሩ፨ይህ፡የምትካሰ
ሱበት፡ነገር፡ሌላ፡እንደሆነ፡(
ግን፡በሐጋ፡ሸንጎ፡ይለያል፤
ዛሬም፡በማይገባ፡በሆነው፡
ሽብር፡እንደንካሰስ፡እንፈራ
ለኚና፡ስለዚህ፡የምንመልሰ
ውን፡ምክንያት፡አናገኘም
ይህንም፡ብሎ፡ጉባዔውን፡
ፈታው፨ምዕራፍ።፳፡

ስለ፡ጳውሎስ፡ወደ፡መቄደንያ
መሔድ፡ስለ፡አውጤክስ፡ከመ
ስኮት፡መውደቁ፤ስለ፡ጳውሎ
ስ፡መጽናናት፤ወደ፡ኢየሩሳ
ሌም፡እንደወጣ፨

፩ ሁከቱም፡ጸጥ፡ካለ፡በኋላ፡ጳ
ውሎስ፡ደቀ፡መዛሙርቱን፡
ጸርቶ፡መከራቸው፡ተሰናብ
ቶዋቸውም፡ወደ፡መቄዶን
ያ፡ይሔድ፡ዘንድ፡ወጣ፤፩፡ጢ
፪ ሞ፡፩፡፫፨ያንንም፡አገር፡አየ
ዞረ፡በብዙ፡ነገር፡ባጽናናቸ
ው፡ጊዜ፡ወደ፡ጽርዕ፡መጣ፨
፫ በዚያም፡ሶስት፡ወር፡ተቀመጠ
ወደ፡ሶርያም፡ለመሔድ፡አሰ
ቦ፡ሳለ፡አይሁድ፡ክፉ፡ሳለ፡መከ
ሩበት፡ወደ፡መቄዶንያ፡ይመለ
፬ ስ፡ዘንድ፡ወደደ፨ከእርሱም፡ጋራ
የቤርያው፡የጲሮስ፡ልጅ፡ሶጳ
ጥሮስ፡ከተሰሎንቄም፡አርስጠ
ርኮስና፡ሲኮንዶስ፡የደርቤው
ም፡ጋይዮስ፡ከእስያም፡ጢሞቴ
ዎስና፡ቲኪቆስ፡ጥሮፊሞስም
እስከ፡እስያ፡ድረስ፡ተከተሉት፤
፭ ም፡፲፪፡፲፤ም፡፲፱፡፳፱፨እነዚህ
ም፡ወደ፡ፊታችን፡አልፈው፡በ
ጥሮአስ፡ቆዩን፨ም፡፲፯፡፳፨
፮ እኛ፡ግን፡ከፋሲካ፡በኋላ፡ከፊ
ልጶስዩስ፡ተነሥተን፡ባሕር
ሔድን፡ባምስት፡ቀን፡ወደ፡ጥ
ሮአስ፡ደረስንና፡በእርሳቸው
ዘንድ፡በዚያ፡ሰባት፡ቀን፡ተቀ
፯ መጥን፨ከሳምንቱም፡በመጀ
መሪያው፡ቀን፡እንጀራ፡መ
ቍረስ፡ተሰብስበን፡ሳለን፡ጳው
ሎስ፡ይሰብካቸው፡ነበረ፤በ
ነጋውም፡ለመሔድ፡አስቦበ
ረና፡እስከ፡መንፈቀ፡ሌሊት፡ነ
ገሩን፡አረዘመ፨፩፡ቆር፡፲፮፡፪
፰ ም፡፪፡ም፡፪፡ም፡፳፨ተሰብስ
ንም፡በነበርንባት፡ሰገነትእ
ጅግ፡መብራት፡ይበራ፡ነበ

፱ ስሙንም፡ አውጣኪስ፡ የሚሉ
ት፡ አንድ፡ ጐበዝ፡ በመስኮት፡ ተ
ቀምጦ፡ ሳለ፡ ታላቅ፡ እንቅልፍ፡
አንቀላፍቶ፡ ጳውሎስ፡ ነገርን፡
ባስረዘመ፡ ጊዜ፡ ከእንቅልፉ
ብዛት፡ የተነሣ፡ አንቀላፍቶ በ
ት፡ ከነበረ፡ ከሦስተኛው፡ ደርብ
ወደ፡ ታች፡ ወደቀ፡ ሙቶም፡ ሬሳ
፲ ውን፡ አነሡት። ጳውሎስም፡ ወ
ርዶ፡ በላዩ፡ ወድቆ፡ አቀፎም፡ ነፍ
ሱ፡ አለችና፡ አይዝዋችሁ፡ አት
ደንግጹ፡ አላቸው። ፩፡ ነገ፡ ፲፯
፲፩ ፳፩፥ ደግሞም፡ ተመልሶ፡ መጥ
ቶ፡ እንጀራ፡ ቈርሶ፡ በላ፡ እስኪነጋ
ም፡ ድረስ፡ እጅግ፡ ነገር፡ ነገራቸ
ውና፡ ከዚያ፡ በኋላ፡ ተነሥቶ፡
፲፪ ሔደ። ብላቴናውንም፡ ደኅና፡
ሁኖ፡ ወሰዱት፡ እጅግም፡ ደስ፡ አ
፲፫ ላቸው። እኛ፡ ግን፡ ጳውሎስን፡
ከዚያ፡ እንቀበለው፡ ዘንድ፡ ስለ
አሰብን፡ በመርከብ፡ ተጭነን፡
ወደ፡ አሶስ፡ ቀድመን፡ አለፍን፡ እ
ርሱ፡ በእግር፡ ይሔድ፡ ዘንድ፡ ማ
ሰቡን፡ ነግሮን፡ ነበረና።
፲፬ አሶስም፡ ደርሰን፡ ባገኘነው፡ ጊ
ዜ፡ ተቀብለነው፡ ወደ፡ ሚጢሌ
፲፭ ኔ፡ መጣን። በማግሥቱም፡ ከዚ
ያ፡ በባሕር፡ ሔደን፡ በኪዩስ፡ ፊ
ት፡ ለፊት፡ አለፍን፡ በነጋውም
በሳሞስ፡ በኩል፡ አልፈን፡ በት
ሮጊልዮም፡ ተቀመጥን፡ ከዚያ

ም፡ በኋላ፡ ወደ፡ ሚሌጦን፡
፲፮ ነ። ጳውሎስ፡ በእስያ፡ እጅ
እንዳይቀመጥ፡ በኤፌሶ
በኩል፡ ያልፍ፡ ዘንድ፡ ወደ
ርና፡ ቢቻለው፡ ለጴንጠቆ
በዓል፡ ኢየሩሳሌም፡ ይደ
ዘንድ፡ ይቸኵል፡ ነበረና።
፳፡ ፳፩፡ ፳፩፡ ፬፡ ፲፬።
፲፯ ከሚሌጦንም፡ ወደ፡ ኤፌ
ልኮ፡ የቤተ፡ ክርስቲያንን
ማግሌዎች፡ ይጠርዋቸው፡ ወ
፲፰ ንድ፡ አዘዘ። ወደ፡ እርሱም
በመጡ፡ ጊዜ፡ አላቸው፡ ወ
እስያ፡ ከገባሁበት፡ ቀን፡ ጀም
ሮ፡ ዘመኑን፡ ሁሉ፡ ከእናንተ
ጋራ፡ እንዴት፡ እንደ፡ ነበርሁ
እናንተ፡ ታውቃላችሁ። ም
፲፱ ፲፫፡ ፲፱፡ ፲፱፡ ፲፬። በትሕትና፡ ሁ
ሉና፡ በብዙም፡ ዕንባ፡ ከአይ
ሁድም፡ በደረሰብኝ፡ ፈተና
እግዚአብሔርን፡ እገለግል፡ እ
፳ ንደ፡ ነበርሁ። ቍ፫። በጉባዔ
ም፡ ሆነ፡ በቤትም፡ ሰስተም
ራችሁ፡ ከሚጠቅማችሁ፡ ነገ
ር፡ አንዳች፡ ስንኳ፡ አላስቀረ
፳፩ ሁባችሁም። ወደ፡ እግዚአብ
ሔር፡ መመለስን፡ በጌታች
ን፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ማመ
ን፡ ለአይሁድና፡ ለአረማው
፳፪ ያን፡ ስመሰክር። አሁንም፡ እ
ኔ፡ በመንፈስ፡ ታሥሬ፡ ወደ፡ ኢ

ሩሳሌም፡ አሔጻለሁ፡ ከዚ
ውም፡ የሚያገኙኝ፡ ምኙ፡ አ
ደሆነ፡ አላውቅምም፡ ፲፰፡፳
፳፫ ፩፡ ፲፱፡ ፳፩፤ ነገር፡ ግን፡ በመንፈስ
ቅዱስ፡ እስራትና፡ መከራ፡ ይቈ
ሃል፡ ብሎ፡ በገሩ፡ ሁሉ፡ ይመ
ክርልኛልና፡ ፱፡ ፲፯፡ ፳፩፡
፳፬ ፡ ፲፩፤ እኔም፡ ሩጫዬንና፡ ከጌ
ቸን፡ ከኢየሱስ፡ የተቀበል
ትን፡ መልእክቴን፡ እፈጽም
ንድ፡ የእግዚአብሔር፡ ጸጋ፡
ወንጌልን፡ እየመሰከርሁ፡ ሰው
ነቴ፡ በእኔ፡ ዘንድ፡ እንድትከብር
ምንም፡ አላስብም፡ ፳፩፡ ፲
፫፤ አሁንም፡ እነሆ፡ እየዞርሁ፡
የእግዚአብሔርን፡ መንግሥ
ት፡ እየሰበክሁላችሁ፡ አናንተ
ሁሉ፡ ከእንግዲህ፡ ወዲህ፡ ፊቴ
ን፡ እንዳታዩ፡ እኔ፡ አውቃለሁ፤
፳፮ ስለዚህም፡ ከሁላችሁ፡ ደምን
ጹሕ፡ እንደ ሆንሁ፡ እኔ፡ በዚህች
፳፯ ቀን፡ እመሰክርላችኋለሁ። የ
እግዚአብሔርን፡ ምክር፡ ሁሉ
እስተማርኋችሁ፡ እንጂ፡ አላ
፳፰ ስቀረሁባችሁምና፤ አሁንም፡
ራሳችሁንና፡ ተጠብቀዋት፡ ዘ
ንድ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ጳጳሳት
አድርጎ፡ የሾማችሁን፡ በደሙ
የዋጃትን፡ የእግዚአብሔርን
ቤተ፡ ክርስቲያን፡ መንጋዋን፡
ም፡ ሁሉ፡ ጠብቁ፤ ፩፡ ጴጥ፡ ፭፡ ፲፪፡
፳፱ ፩ ጴጥ፡ ፭፡ ፱፤ ከሔድሁም፡
በኋላ፡ ለመንጋው፡ የማያዝ
ኑ፡ የሚናጠቁ፡ ተኩላዎች፡ እ
ንዲገቡባችሁ፡ እኔ፡ አውቃ
፴ ለሁ። ማቴ፡ ፯፡ ፲፭፤ ከእናንተ
ም፡ ደቀ፡ መዛሙርትን፡ ወደ፡
ኋላቸው፡ ይስቡ፡ ዘንድ፡ ጠማ
ማ፡ ነገርን፡ የሚናገሩ፡ ሰዎች
፴፩ ይነሣሉ። ስለዚህም፡ ሦስት
ዓመት፡ ሙሉ፡ ሌሊትና፡ ቀን፡
በእንባ፡ እያንዳንዳችሁን፡ ከ
ማስተማር፡ እንዳላቋረጥሁ
፴፪ አስባችሁ፡ ትጉ፤ አሁንም፡ ለእ
ግዚአብሔርና፡ ይሠራችሁ
ም፡ ዘንድ፡ ከቅዱሳንም፡ ጋራ፡ ር
ስትን፡ ይሰጣችሁ፡ ዘንድ፡ ለሚ
ችል፡ ለጸጋው፡ ቃል፡ አደራ፡ ሰ
፴፫ ጥቻችኋለሁ፤ ወርቅና፡ ብር
ልብስም፡ ሆነ፡ ከእናንተ፡ ስንኳ
አልሻሁም፤ ማቴ፡ ፲፡ ፰፡ ፩ ቆሮ
፴፬ ፱፡ ፲፪፡ ፩፡ ተሰ፡ ፪፡ ፱፤ እነዚህም፡
እጆቼ፡ ለምሸው፡ ነገርና፡ ከእኔ
ም፡ ጋራ፡ ላሉት፡ እንደ፡ አገለገሉ
እናንተ፡ ታውቃላችሁና፤ ም፡ ፲፰፡
፫፡ ፬፤ ቆሮ፡ ፲፪፡ ፩፡ ተሰ፡ ፪፡ ፱፤
፴፭ እንደዚሁም፡ ሠራ፡ መሥራትና
ደካሞችን፡ መርዳት፡ እንዲገባ
ገለጽሁላችሁ፡ ጌታችን፡ ኢየሱ
ስም፡ ከሚቀበል፡ ይልቅ፡ የሚ
ሰጥ፡ ይመሰገናል፡ ያለውን፡ ቃ
፴፮ ሉን፡ አስቡ፤ ይህንም፡ ብሎ፡ ተ

ንበርክኮ፡ከሁሉ፡ጋራ፡ጸለዩ፤
፴፯ ም፡፳፩፡፳፭ ሁሉም፡እጅግ፡ስለ
ቀሱ፡ጳውሎስንም፡አንገቱን፡
አቀፈው፡ሳሙት፥ይልቁንም
እንግዲህ፡ፊቴን፡አታዩኝም፡
ስለ፡አላቸው፡ነገር፡እጅግ፡አዘ
ኑ፡እስከ፡መርከብም፡ድረስ፡ሸ
ኙት።

ምዕራፍ፡፳፩።

ስለ፡አጋቦስ፡በጳውሎስ፡ትንቢ
ት፡መናገር፡ስለ፡ጳውሎስ፡የእሬ
ትን፡ሐጋ፡መሥራቱ፤ከመስጊ
ድ፡አውጥተው፡እንደ፡ደበደቡ
ት፤እንዴ፡ታሠረ፤ከሹሙ፡ፊት
ቀርቦ፡እንደ፡ጠየቀና፡በዕብራ
ይስጥ፡ቋንቋ፡እንደ፡ተናገረ፥

፩ ከእነርሳቸውም፡ከተለየን፡በኋ
ላ፡እኛ፡በመርከብ፡ተሳፈርን፡መን
ገዳችንንም፡አቅንተን፡ወደ፡ቆ
ስ፡መጣን፡በነጋውም፡ወደ፡ሮድ
ስ፡ከዚያም፡ወደ፡ጳጥራ፡ገባን፥
፪ ወደ፡ፊንቂም፡የሚያልፍ፡መር
ከብ፡አግኝተን፡በዚያ፡ላይ፡ተቀ
፫ ምጠን፡ሔድን፥ቆጵሮስንም፡ባ
የናት፡ጊዜ፡በስተግራችን፡ትተ
ናት፡ወደ፡ሶርያ፡ሔድን፡መርከ
ቡም፡ሸክሙን፡በዚያ፡የሚያ
ራግፍ፡ነበረና፡ወደ፡ጢሮስ፡መ
፬ ጣን፥ደቀ፡መዛሙርትንም፡ባ
ገኘን፡ጊዜ፡በእነርሳቸው፡ዘንድ
ሰባት፡ቀን፡ተቀመጥን፡እነርሳ
ቸውም፡ጳውሎስን፡ወደ፡ኢየ
ሩሳሌም፡እንዳይወጣ፡በመ[...]
፭ ፈስ፡ነሉ፡ተቃዋ ፲፩፡፲፪፡ ም፡፳[...]
የተቀመጥንበትንም፡ቀን፡[...]
ጸምን፡ጊዜ፡ለመሔድ፡መጣ[...]፡
እነርሳቸውም፡ሁሉ፡ከሴ[...]ቻ
ቸውና፡ከልጆቻቸው፡ጋራ[...]
ሰከ፡ከተማው፡ውጭ፡ድረ[...]ሸ
ኙን፡በባሕሩም፡ዳር፡በጕል[...]ታ
ችን፡ተንበርክከን፡ጸለይነ[...]ም፡
፮ ፳፡፳፪ አርስ፡በርሳችንም[...]ተ
ሳስመን፡ተሰነባበትን፡ወደ[...]መ
ርክብ፡መጣን፡እነዚያም፡ወ[...]፡
፯ ቤታቸው፡ተመለሱ፥እኛ፡ግ[...]
ከጢሮስ፡ተነሥተን፡ባሕሩን[...]
ጨርሰን፡ወደ፡ጵቶልማይስ፡[...]
ደም፡አኅ፡ገባን፡ወንድሞች[...]
ም፡እንዴት፡ናችሁ፡አልን፡በእ[...]
ርሳቸውም፡ዘንድ፡አንድ፡ቀን[...]
፰ ተቀመጥን፥በነጋውም፡ከዚያ[...]
ወጥተን፡ወደ፡ቂሣርያ፡መጣ[...]
ከሰባቱም፡አንዱ፡በሚሆን፡በ[...]
ወንጌላዊው፡ፊልጶስ፡ቤት፡ገ[...]
ብተን፡ተቀመጥንም፡፮፡፭፥
፱ ለእርሱም፡ትንቢት፡የሚናገሩ[...]
አራት፡ደናግል፡ሴቶች፡ልጆ[...]
፲ ቸ፡ነበሩት፥ም፡፱፡፲፪፥በዚያ[...]
ም፡አያሌ፡ቀን፡በተቀመጥን፡[...]
ጊዜ፡ስሙ፡አጋቦስ፡የሚሉ[...]
ት፡ነቢይ፡ሰው፡ከይሁዳ፡አገር[...]
፲፩ ወረደ፥ም፡፲፩፡፳፰፥ወደ፡እኛ[...]
ም፡መጣና፡የጳውሎስን፡መ[...]

ታጠቂያ፡ወሰደ፡እጁንና፣ እግሩን፡አሠረበት፡እንዲሁም፡መንፈስ፡ቅዱስ፡የዚህን መታጠቂያ፡ጌታ፡አይሁድ፡በ ኢየሩሳሌም፡ያሠሩታል፡ለ ሕዝብም፡አሳልፈው፡ይሰ ጡታል፡ይላል፡አለ። ም፡፳፩፡፲፩ ፲፪ ይህንንም፡በሰማን፡ጊዜ፡እኛ ም፡ያገሩ፡ሰዎች፡ወደ፡ኢየሩ ሳሌም፡እንዳይወጣ፡ለመንነ ው። ም፡፳፩፡፲፪። ፲፫ ጳውሎስም መለሰ፡ለምን፡እንዲህ፡አድር ጋችሁ፡እያለቀሳችሁ፡ልቤን፡ ትሠብሩታላችሁ፡እኔ፡ስለጌ ታዬ፡ስለ፡ኢየሱስ፡ስም፡በኢ የሩሳሌም፡ለመሞትም፡የ ጨከንሁ፡ነኝ፡እንጂ፡ለእሥ ራት፡ብቻ፡የተዘጋጀሁ፡አይደ ፲፬ ለሁም፡አለ፡እምቢ፡ባለንም፡ጊ ዜ፡የእግዚአብሔር፡ፈቃድ፡ይ ፲፭ ሁን፡ብለን፡ዝምም፡አልነ። ከዚ ያም፡ቀን፡በኋላ፡ተዘጋጅተን፡ ፲፮ ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ወጣነ። ከደ ቀ፡መዛሙርትም፡ወገን፡ከቂ ሣርያ፡ከእኛ፡ጋራ፡መጡ፡ከቆ ጵሮስም፡ወገን፡ምናሶን፡ወደ ሚባለው፡ወደ፡ቀደመው፡ደ ቀ፡መዝሙር፡ቤት፡ገብተን፡ ፲፯ እደርን። ወደ፡ኢየሩሳሌም፣ ም፡በደረስን፡ጊዜ፡ወንድሞ ች፡በደስታ፡ተቀበሉን።

፲፰ በነጋውም፡ጳውሎስ፡ከእኛ፡ጋ ራ፡ወደ፡ያዕቆብ፡ገባ፡ሽማግ ሌዎችም፡ሁሉ፡በዚያ፡ነበሩ። ፲፱ ም፡፳፩፡፲፰፡ገላ፡፩፡፲፱። ሰላም ታም፡ከቀረበላቸው፡በኋላ በእርሱ፡ማገልገል፡እግዚአ ብሔር፡በአሕዛብ፡መካከል፣ ያደረገውን፡ሥራ፡በያንዳንዱ ፳ ነገራቸው። እነርሱም፡ይ ህን፡በሰሙ፡ጊዜ፡እግዚአብሔ ርን፡አመሰገኑ፡አሉትም፡ወን ድም፡ሆይ፡ከአይሁድ፡ወገን፡ ያመኑት፡ስንት፡አእላፋት፡እን ደሆኑ፡ታያለህን፡እነርሳቸው ም፡ሁሉ፡ለኦሪት፡የሚቀኑ፡ና ፳፩ ቸው። ም፡፲፭፡፩። አንተም፡በ አሕዛብ፡መካከል፡ያሉትን፡ አይሁድን፡ከሙሴ፡ሥርዓት፡ ይርቁ፡ዘንድና፡ልጆቻቸውን ም፡እንዳይገዝሩ፡በሕጋቸው ም፡እንዳይሔዱ፡እንድታስተ ምር፡ነግረዋቸዋል። ም፡፲፯፡ ፫፡ሮሜ፡፲፡፬።

፳፪ አሁንስ፡ምን፡ይሁን፡ሕዝቡ፡ የአንተን፡መምጣት፡ሰምተ ው፡የግድ፡ሳይሰበሰቡ፡የማ ፳፫ ቀሩ፡ናቸው። ስለዚህም፡ይ ህን፡የምልህን፡አድርግ፡ስለ ት፡ያለባቸው፡አራት፡ሰዎች ፳፬ በእኛ፡ዘንድ፡አሉ። እነዚህን ም፡ይዘህ፡ሒድና፡ከእነርሳቸ

ው፡ጋራ፡ግጹ፡ራሳቸውንም፡እን
ዲሳጮ፡ስለ፡እነርሱ፡ግንዘብ፡
ከፈሏቸው፡እንዲህም፡የሆነ
እንደሆነ፡ስለ፡አንተ፡የሰሙት፡
ወሬ፡ሁሉ፡ሐሰት፡እንደ፡ሆነና፡
አንተም፡ራስህ፡ሕግ፡ጠባቂ፡
እንደ፡ሆንህ፡ያውቃሉም፡፳
፳፭ ፳ቍከአህዛብ፡ወገን፡ለመኑት
ማን፡ለጣዖት፡ከታረደው፡ከደ
ምም፡ከታነቀም፡ከዝሙትም
ሰውነታቸውን፡እንዲጠብቁ፡
አዘናቸዋልቍም፡፲፭፡፩፡፳፱ቍ
፳፮ በዚያም፡ጊዜ፡ጳውሎስ፡ሰዎቹ
ን፡ይዞ፡በማግሥቱ፡ከእነርሳቸ
ው፡ጋራ፡ነጻ፡የመንጻታቸው
ም፡ወራት፡መድረሱን፡ከነገራ
ቸው፡በኋላ፡ሁሉም፡እያንዳን
ዳቸው፡መሥዋዕት፡ያቀርቡ፡
ዘንድ፡ወደ፡መቅደስ፡ይዟቸ
፳፯ ው፡ገባቍዘኁ፡፳፪፡፳ቍሰባቱ፡ቀ
ንም፡ይፈጸም፡ዘንድ፡ሲቀርብ
ከእስያ፡የመጡ፡አይሁድ፡ጳው
ሎስን፡በመቅደስ፡ባዩት፡ጊዜ፡
ሰዎችን፡አስነሥተው፡ይይዙ
ት፡ዘንድ፡እጃቸውን፡ዘረጉበት
፳፰ እየጮሁ፡እንዲህም፡እያሉ፡እ
ናንተ፡የእስራኤል፡ሰዎች፡ር
ዱን፡በየስፍራው፡ሕዝባችን
ን፡ኦሪትንም፡ይህንንም፡ስፍራ
የሚጠላ፡ትምህርት፡ለሰው፡
ሁሉ፡የሚያስተምር፡ይህ፡እነ

ሆ፡ይህ፡ሰው፡ነው፡ደግሞም
ዮናኒውን፡ወደ፡መቅደስ፡አ
ገብቶ፡ይህን፡የተቀደሰ፡ስፍራ
አረከሰውቍም፡፳፩፡፲፩፡ሕዝ
፳፱ ፵፬ቍበፊት፡የኤፌሶኑን፡ጥሮ
ሞን፡ከእርሱ፡ጋራ፡በከተማ
አይተውት፡ነበሩና፡ጳውሎ
ወደ፡መቅደስ፡ያገባው፡መ
ዋቸው፡ነውቍም፡፳፩፡፲፡፲፱፡ጢ
፴ ፲፡፳ቍከተማውም፡ሁሉ፡ታ
ከ፡ሕዝቡም፡ሁሉ፡ተሰበሰበ
ጳውሎስንም፡ይዘው፡ከመ
ደስ፡ጐትተው፡አወጡት፡ያን
ጊዜውንም፡ደጆችን፡ሁሉ፡ዘጉ
፴፩ ሊገድሉትም፡ፈለጉ፡ኢየሩሳ
ሌም፡ፈጽማ፡እንደ፡ታወከች፡
፴፪ ወደ፡ሻለቃው፡ወሬ፡ደረሰቍበዚ
ያ፡ጊዜም፡ጭፍሮቹን፡ከአለቆ
ቻቸው፡ጋራ፡ይዞ፡እየሮጠ፡ደረ
ሰባቸው፡እነርሳቸውም፡የሻ
ለቃውን፡ጭፍሮቹን፡ባዩ፡ጊ
ዜ፡ጳውሎስን፡ከመምታት፡ተ
፴፫ ዉቍበዚያ፡ጊዜም፡የሻለቃ
ው፡ወደ፡እርሱ፡ቀርቦ፡ያዘውና
በሁለት፡ሰንሰለት፡ይታሰር፡
ዘንድ፡አዘዘ፡ማን፡እንደ፡ሆነና፡
ምን፡እንዳደረገም፡ጠየቀ፤
፴፬ ም፡፳፩፡፳፩ቍሕዝቡም፡አኩሌቶ
ቹ፡እንዲህ፡ነው፡አኩሌቶቹ
ም፡እንዲህ፡አይደለም፡እያሉ፡
ይንጫጩ፡ነበሩ፡ስለ፡ጫጫ

ታውም፡ ብዙት፡ እርግጡን፡ ማ
ወቅ፡ ባልተቻለ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ቤተ
ደወስዱት፡ ዘንድ፡ አዘዘ፡ ወደ፡
መውጫውም፡ በደረሰ፡ ጊዜ፡ ስ
ለ፡ ሕዝቡ፡ ጭንቀት፡ ጭፍሮቹ፡
ተሸክመው፡ አወጡት፡ ብዙ፡
ሕዝብም፡ አስወግደው፡ እያሉ
ና፡ እየጮሁ፡ ይከተሉ፡ ነበርና፡
ወደ፡ አደራሹም፡ ሊደርስ፡ ጳው
ሎስ፡ የሻለቃውን፡ አንድ፡ ነገር፡
ብነግርህ፡ ትፈቅድልህን፡ አለው
እርሱም፡ አለው፡ የፅርዕ፡ ቋንቋ
ታውቃለህን፤ እንግዲህ፡ ከዚህ፡ ዘ
መን፡ አስቀድሞ፡ ሁከት፡ ያደረግ
ህና፡ ወደ፡ ምድረ፡ በዳ፡ አራቱን፡
ሺህ፡ ነፍሰ፡ ገዳዮች፡ ሰዎች፡ በተ
ንኮል፡ ያወጣህ፡ የምስር፡ ሰው
፴፱ አይደለህምን፤ ጳውሎስም፡ እ
ኔስ፡ አይሁዳዊ፡ ሰው፡ ነኝ፡ የተወ
ለድሁባትም፡ አገር፡ ጠርሴስ፡ የ
ታወቀች፡ የኪልቅያ፡ ከተማ፡
ናት፡ ለሕዝቡ፡ እነግር፡ ዘንድ፡ እ
ንድትፈቅድልኝ፡ እለምንሃለሁ፡
፵ አሰቀም፡ ፱፡ ፲፪፤ በፈቀደለትም
ጊዜ፡ ጳውሎስ፡ በመውረኩ፡ ሳይ
ቁሞ፡ እጁን፡ ወደ፡ ሕዝቡ፡ ዘረጋ፡
እጅግም፡ ጸጥታ፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ በ
ዕብራይስጥ፡ ቋንቋ፡ ነገራቸው
እንዲህ፡ ሲልም ፲፬፡ ፲፯፡ ፲፫፡ ፲፯፡
፲፱፡ ፴፫፤ ምዕራፍ፡ ፳፪።
ጳውሎስ፡ ተወልደ፡ ስለ፡ አደገበት
አገር፡ በደማስቆ፡ ስለ፡ አየው፡ ራ
እይ፡ ሊገርፉት፡ እንዲ፡ ጐተቱት
ና፡ የሮሜ፡ ሰው፡ ነኝ፡ እንዲ፡ አለ።
፩ እናንተ፡ ሰዎች፡ ወንድሞች፡ አባ
ቶችም፡ አሁን፡ ለእናንተ፡ የም
ናገረውን፡ ስሙቅም፡ ፲፡ ፪፡ ፲፫፡
፪ ፳፯፤ በዕብራይስጥ፡ ቋንቋም
ሲናገር፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ ጸጥታ፡ አ
በዙ፡ እርሱም፡ አለቀም፡ ፳፩፡ ፵፡
፫ እኔ፡ የኪልቅያ፡ አውራጃ፡ በም
ትሆን፡ በጠርሴስ፡ የተወለድሁ
አይሁዳዊ፡ ነኝ፡ በዚያችም፡ ከ
ተማ፡ የአባቶቼን፡ ሕግ፡ ጠንቅ
ቄ፡ እየተማርሁ፡ ከገማልያል፡
እግር፡ በታች፡ አደግሁ፡ እንዲዘ
ሬውም፡ እንዲ፡ እናንተ፡ ሁሉ፡ ለ
እግዚአብሔር፡ ቀናተኛ፡ ሆንሁ
ም፡ ፳፡ ፴፬፡ ም፡ ፱፡ ፩፡ ፳፪፡ ፳፯፡ ፱፡
፬ ፲፰፤ በዚህም፡ መንገድ፡ ወንዶ
ችንም፡ ሴቶችንም፡ እያሠርሁ
እሳልፌ፡ በመስጠት፡ እስከ፡ ሞ
ት፡ ድረስ፡ አሳደድሁቃም፡ ፰፡ ፫፡
፭ ይፈርዱባቸውም፡ ዘንድ፡ ከዚያ
ያሉትን፡ አሥሬ፡ ወደ፡ ኢየሩሳሌ
ም፡ እንዳመጣቸው፡ ከእነርሱ
ቸው፡ መልእክትን፡ ተቀብዬ፡ በ
ደማስቆ፡ ወደ፡ አሉት፡ ወንድሞ
ች፡ እንደ፡ ሔድሁ፡ ሊቀ፡ ካህናቱ
ና፡ ሽማግሌቹም፡ ሁሉ፡ ይመሰ
፮ ክሩልኛልና፡ ስሔድም፡ ወደ፡ ደ
ማስቆ፡ በቀረብሁ፡ ጊዜ፡ ቀትር

ሲሆን፡ድንገት፥ከሰማይ፡ታ
ላቅ፥ብርሃን፡አበራልኝ።ም፡
፯ ፱፡፫፡፲፯፡፩፡ቆሮ፡፲፭፡፰፥በም
ድር፡ላይ፡ወደቅሁ፡ሳውል፡ሳ
ውል፡ስለምን፡ታሳድደኛለ፡የ
ለኝንም፡ድምፅ፡ሰማሁ።ም
፰ ፳፮፡፲፩፡፲፭፥እኔም፡መልሼ፡
አንተ፡ማነህ፡አልሁ፡እርሱም
አንተ፡የምታሳድደኝ፡የናዝሬ
ቱ፡ኢየሱስ፡እኔ፡ነኝ፡አለኝ።
፱ ከእኔ፡ጋራ፡የነበሩትም፡ብርሃ
ኑን፡አዩት፡ውን፡እንጂ፡ፈሩ፡የ
ሚናገረኝን፡ድምፅ፡ግን፡አል
፲ ሰሙም።ም፡፱፡፯።ያንጊዜም
አቤቱ፡ምን፡ላድርግ፡አልሁት
ጌታም፡ተነሥተህ፡ወደ፡ደማ
ስቆ፡ሒድና፡ታደርገው፡ዘን
ድ፡የሚገባህን፡ሁሉ፡በዚያ፡ይ
ነግሩሃል፡አለኝ።ም፡፱፡፮።
፲፩ ከብርሃኑም፡ጸብራቅ፡የተነ
ሣ፡ማየት፡ባይሆንልኝ፡ከእኔ፡
ጋራ፡የነበሩ፡ሰዎች፡እየመሩ
፲፪ ኝ፡ወደ፡ደማስቆ፡ደረስሁ።በደ
ማስቆም፡በሚኖሩ፡በአይሁ
ድ፡ዘንድ፡ሁሉ፡በደግነት፡የተ
መሰገነና፡እንደ፡ሕጉም፡እግ
ዚአብሔርን፡የሚፈራ፡ሰውን
ሐናንያ፡የሚሉት፡አንድ፡ሰው
፲፫ ነበረ።እርሱም፡ወደ፡እኔ፡መጥ
ቶ፡በአጠገቤ፡ቁሞ፡ወንድሜ፡
ሳውል፡ሆይ፡እይ፡አለኝ፡እኔም

ያንጊዜውን፡ወደ፡እርሱ፡አየ
፲፬ እርሱም፡አለኝ፡የአባቶቻችን
አምላክ፡ፈቃዱን፡ታውቅ፡ዘን
ድና፡ጻድቁንም፡ታይ፡ዘንድ፡ከ
አፉም፡ድምፅን፡ትሰማ፡ዘን
አስቀድሞ፡መርጦሃል።ም፡፱
፲፭ ፲፭።ባየኸውና፡በሰማኸው፡
ሥራ፡ሁሉ፡በሰው፡ፊት፡ምስ
፲፮ ር፡ትሆነዋለህና።አሁንስ፡ለ
ን፡ትዘገያለህ፡ተነሣና፡ተጠ
ቅ፡ከኃጢአትህም፡ታጠብ፡
፲፯ ጌታን፡ስም፡ጥራ።ሆነም፡ወ
ኢየሩሳሌም፡በተመለስሁ፡ጊ
ዜ፡በመቅደስ፡ስጸልይ፡በራእይ
፲፰ ተመሰጥሁ።ም፡፱፡፳፮።ስለ፡እ
ኔም፡የምትመሰክረውን፡አይ
ቀበሉህምና፡ከኢየሩሳሌም፡
ፈጥነህ፡ውጣ፡የሚለኝን፡አየሁ
፲፱ ት።እኔም፡አልሁ፡አቤቱ፡በአን
ተ፡የሚያምኑትን፡በመስጊድ፡ሁ
ሉ፡እመታና፡እሥር፡እንደ፡ነበር
ሁ፡እነርሱ፡ያውቃሉ።ም፡፬
፳ የሰማዕትህንም፡የእስጢፋኖ
ስን፡ደም፡ባፈሰሱ፡ጊዜ፡ከእነር
ሳቸው፡አንዱ፡እኔ፡ሁኜ፡ከዚያ፡
ቁሜ፡የገዳዮችን፡ልብስ፡እጠ
ብቅ፡ነበሩ።ም፡፯፡፶፰፡፰፡፩።
፳፩ እርሱም፡በሩቅ፡አገር፡ወደ፡አሉ
ታ፡አሕዛብ፡እኔ፡እልክሃለሁና፡
ሒድ፡አለኝ።ም፡፱፡፲፭፡፲፫፡፪።
፳፪ እስከዚህም፡ቃሉ፡ድረስ፡እርሱ

ን፡ሰሙት፡ከዚህ፡በኋላ፡ተባብ
ረው፡ድምፃቸውን፡ከፍ፡አድ
ርገው፡እንዲህ፡ያለው፡በሕይ
ወት፡ይኖር፡ዘንድ፡አይገባም
ና፡ከምድር፡አስወግደው፡ አ
ሉ፥ም፡፳፩፡፴፪፥ እነርሳቸው
ም፡እየጮሁና፡ልብሳቸውን
ም፡እየወረወሩ፡ትቢያን፡ወደ
ሳይ፡ይበትኑ፡፳፬ መርቆየሻለቃ
ውም፡የጮሁበትን፡ምክንያ
ት፡ያውቅ፡ዘንድ፡ወደ፡አደራሽ
አግብታችሁ፡መርምሩት፡እ
የገረፋችሁ፡ብሉ፡አዘዘ፥
፳፭ ይገርፉትም፡ዘንድ፡ባጋደሙ
ት፡ጊዜ፡ጳውሎስ፡ለማሰገረ
ፍ፡የቆመውትን፡የመቶ፡አለቃ
የሮምን፡ሰው፡ያለ፡ፍርድ፡ትገ
ርፉት፡ዘንድ፡ተፈቀደላችኋ
ልን፡አለውቃም፡፲፮፡፴፯፡፳፫፥
፳፮ ፳፪፥የመቶ፡አለቃውም፡ይህ
ን፡በሰማ፡ጊዜ፡ይህ፡ሰው፡ሮማ
ዊ፡ነውና፡የምታደርገውን፡ዕ
፳፯ ወቅ፡ለሻለቃው፡ነገረው፥የሻ
ለቃውም፡መጥቶ፡አንተ፡ሮማ
ዊ፡እንደሆንህ፡ንገረኝ፡አለው
፳፰ እርሱም፡አዎን፡አለው፥የሻለቃ
ውም፡እኔ፡ይህን፡ሹመት፡ያገኘ
ሁት፡በብዙ፡ገንዘብ፡ነው፡አለ፡
ጳውሎስም፡እኔማ፡እንዳደያ
ው፡የተወለድሁበት፡ነው፡አለ
፳፱ ወዲያውም፡እነዚያ፡ሊመረ
ምሩት፡የመጡ፡ሰዎች፡ከእርሱ
ወገዱ፡የሻለቃውም፡ሮማዊ
መሆኑን፡ባወቀ፡ጊዜ፡ስምን፡አ
ሠርሁት፡ብሎ፡እጅግ፡ፈራ፥
፴ በማግሥቱም፡አይሁድ፡የክ
ሰሱት፡በምን፡ምክንያት፡እን
ደሆነ፡ያውቅ፡ዘንድ፡ሽቶ፡ፈታ
ው፡የካህናት፡አለቆችና፡ጉባ
ዔውም፡ሁሉ፡ይሰበሰቡ፡ዘንድ
አዘዘ፡ጳውሎስንም፡አውርዶ
ከፊታቸው፡አቆመው፥

ምዕራፍ፡፳፫፡፡

ሐናንያ፡ጳውስን፡እንደአስመ
ታው፡ፈሪሳውያንና፡ሰዱቃውያ
ን፡በጳውሎስ፡ስለ፡መጣሉ፤
ጳውሎስን፡ለመግደል፡እንደ፡
ተማማሉ፤ሹሙ፡ወደ፡ቂሣር
ያ፡እንደ፡ሰደደው፤እንደ፡ተመረ
መረ፥

፩ ጳውሎስም፡በአደባባዩ፡ወደ፡አ
ሉት፡ሰዎች፡አትኩሮ፡ተመለከተ
ና፡እናንተ፡ሰዎች፡ወንድሞቼ
እስከዚች፡ቀን፡ድረስ፡በመልካ
ም፡ሕሊና፡ተመህርት፡በእግ
ዚአብሔር፡ፊት፡ኖርሁ፡አለ፡፡
፪ የካህናቱ፡አለቃ፡ሐናንያም፡
ጳውሎስን፡አፉን፡ይመቱት፡
ዘንድ፡ባጠገቡ፡ቆመው፡የነበ
፫ ሩትን፡አዘዘ፥ጳውሎስም፡መ
ልሶ፡አንተ፡የተለሰነ፡ግድግዳ፡
በሐሰት፡ልትፈርድብኝ፡ተቀም

የሐዋርያት፡

ጠህ፡ሰለህ፡ያለ፡ሐሜ፡አመቃ፡ዘ
ኘዴ፡ቃዘለህኘ፡እነሆ፡እግዚአብ
ሔር፡በቍጣው፡መቀሠፍቱ፡ደ
፬ መቃሃል፡ለለው፨ባጠገቡ፡የ
ቆሙትም፡የእግዚአብሔርን
የካህናት፡አለቃ፡እንዴት፡ትሰ
፭ ድባለህ፡አሉት፨ጳውሎስም፡
ወንድሞቼ፡ሆይ፡የካህናት፡
አለቃ፡መሆኑን፡ባላውቅ፡ነው
በሕዝብ፡አለቃ፡ላይ፡ክፉ፡ቃል
አትናገር፡የሚል፡ጽሑፍ፡አ
ለና፡አላቸው፨ዘፀ፡፳፪፡፳፰፡፪፡ጴጥ
፮ ፪፡፲፨ጳውሎስም፡እኩሌቶቹ
ም፡ፈሪሳውያን፡መሆናቸው
ን፡አውቆ፡ሰለ፡ተስፋና፡ስለ፡ሙ
ታን፡መነሣት፡የሚፈርድብኝ
እኔ፡ፈሪሳዊ፡የፈሪሳዊ፡ልጅ
ነኝ፡ብሎ፡በአደባባዩ፡ጮኸ፨
፯ ም፡፳፮፡፭፨ይህንም፡ባለፈ፡
ጊዜ፡ፈሪሳውያንና፡ሰዱቃው
ያን፡ተጣሉና፡ሕዝቡም፡ተከፋ
፰ ፈሉ፨ሰዱቃውያን ተንሣ
ኤ፡ሙታንም፡መልአክም፡መን
ፈስም፡የለም፡የሚሉ፡ናቸው
ና፡ፈሪሳውያን፡ግን፡ይህን፡ሁ
ሉ፡ያምናሉ፨ማቴ፡፳፪፡፳፫፨
፱ ከዚህ፡በኋላ፡ታላቅ፡ፀብ፡ሆነና
ከፈሪሳውያን፡ወገን፡አያሌ፡
ጸሐፎች፡ተነሥተው፡በዚህ፡ሰው
ላይ፡ምንም፡ክፉ፡ነገር፡አላገኘ
ንበትም፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ወይ

ስ፡መልአክ፡ተናግሮት፡እን
ሆነ፡ምን፡ይሁን፡ብለው፡ተጣ
ሉ፨ም፡፳፫፡፳፱፡ም፡፳፭፡፲፱፨
፲ ብዙ፡ፀብም፡በሆነ፡ጊዜ፡የሻ
ቃው፡ጳውሎስን፡እንዳይነጥ
ቁ፡ፈርቶ፡ከመካከላቸው፡
ፈው፡ወደ፡አደራሹ፡ይወስዱ
ዘንድ፡ጭፍሮቹን፡አዘዘ፨
፲፩ በሁለተኛው፡ሌሊት፡ጌታ፡
ቆ፡ቁሞ፡ጳውሎስ፡ሆይ፡በኢ
ሩሳሌም፡ምስክር፡እንደ፡ሆ
ኸኝ፡እንዲሁ፡በሮሜም፡ተ
ሰክርልኝ፡ዘንድ፡ይገባሃልና
አይዞህ፡አለው፨ም፡፲፰፡፱፡ም፡
፲፪ ፲፱፡፳፩፨በጸባም፡ጊዜ፡አይሁ
ድ፡ጳውሎስን፡እስኪገድሉት፡
ድረስ፡እንዳይበሉና፡እንዳይጠ
ጡ፡ተማማሉ፡ተስማምተው
፲፫ ይህንንም፡ለማድረግ፡የተማ
ማሉት፡ሰዎች፡ከአርባ፡ይበዙ
፲፬ ነበር፨እነርሳቸውም፡ወደ፡ካ
ህናት፡አለቆችና፡ወደ፡ሽማግሌ
ቹ፡መጥተው፡አልዋቸው፡እነ
ሆ፡እኛ፡ጳውሎስን፡ሳንገድል፡
ምንም፡እንዳንቀምስ፡ተረገማ
፲፭ መን፡ተማምለናል፨አሁንም፡
እናንተ፡ከሕዝቡ፡ጋራ፡ሁናችሁ
ሁ፡አጥብቃችሁ፡ትመረምሩ
ት፡ዘንድ፡ወደ፡እናንተ፡እንዲያ
መጣው፡ለሻለቃው፡ንገሩትና
እኛም፡ከእናንተ፡ሳይደርስ፡እን

ድንግድ ሰው፡የተዘጋጀን፡ነኝ።
የጳውሎስም፡የአኅቱ፡ልጅ፡
ደባቸውን፡በወቀ፡ጊዜ፡መጥቶ፡
ወደ፡አሥሩ፡ቤት፡ገባና፡ለጳውሎ
ስ፡ነገረው። ጳውሎስም፡ከመቶ
አለቆች፡አንዱን፡ጠርቶ፡ይህ፡ብ
ላቴና፡ለሻለቃው፡የሚነግረው
ነገር፡አለውና፡ወደ፡እርሱ፡አግ
፲ ባልኛ፡አለው። እርሱም፡ወደ፡ሻ
ለቃው፡ወስዶ፡ይህ፡ብላቴና፡የሚ
ነግርህ፡ነገር፡አለውና፡ከአንተ
ጋራ፡አገናኘው፡ዘንድ፡እሥረኛ
ው፡ጳውሎስ፡ጠርቶ፡ለመነኝ፡አ
፱ ለው። የሻለቃውም፡እጁን፡ያዘ
ና፡ለብቻው፡አድርጎ፡በቁይታ፡
የምትነግረኝ፡ነገር፡ምንድር፡
፳ ነው፡አለው። እርሱም፡አለው፡አ
ይሁድ፡አጥብቀህ፡የምትመረ
ምር፡መስለህ፡ጳውሎስን፡ነገ፡
ወደ፡ሸንጎ፡ታወርድላቸው፡ዘን
ድ፡ሊለምኑህ፡ተማክረዋልና።
፳፩ አንተ፡ግን፡በጀ፡አትበላቸው፡ከ
እነርሱ፡ወገን፡እርሱን፡ሳይገ
ድሉ፡እንዳይበሉና፡እንዳይጠ
ጡ፡በራሳቸው፡ምለው፡ያደቡ
በት፡ከአርባ፡ሰዎች፡ይበዛሉና
አሁንም፡እነሆ፡ተዘጋጅተው፡
የአንተን፡ምላሽ፡ይጠብቃሉ።
፳፪ ከዚህ፡በኋላ፡የሻለቃው፡ይህ
ን፡ነገር፡ለእኔ፡መናገርህን፡ለ
ማንም፡እንዳትገልጽ፡ብሎ፡ለ

፳፫ ደደው። ከመቶ፡አለቆቹም፡
ሁለቱን፡ጠርቶ፡ወደ፡ቂሣርያ፡
ይሔዱ፡ዘንድ፡ከሌሊቱ፡በሶስ
ተኛው፡ሰዓት፡ሁለት፡መቶ፡ጭ
ፍሮችን፡ሰብዓ፡ፈረሰኞችን፡
ሁለት፡መቶ፡ባለጦር፡መሣሪ
፳፬ ያዎችን፡አዘጋጁ። አሳቸው። የጋ
ማ፡ከብቶም፡ወስደው፡ጳውሎ
ስን፡አያስቀመጡ፡ከሹሙ፡ከፊ
ልክስ፡ዘንድ፡በደኅና፡እንዲያ
፳፭ ደርሱት፡አዘዛቸው። ደብዳቤ
ም፡ጻፈ፡እንዲህ፡የሚል።
፳፮ ከቀላውዴዎስ፡ሉስዮስ፡ወደ፡
ጠንካራው፡ፊልክስ፡ሰላም፡ለ
፳፯ አንተ፡ይሁን። ይህን፡ሰው፡አይ
ሁድ፡ይዘው፡ሊገድሉት፡ሳለ፡
እኔ፡ሮማዊ፡መሆኑን፡ከአወቅ
ሁ፡በኋላ፡ከጭፍሮች፡ጋራ፡ደር
ሼ፡አዳንሁት። ም፡፳፩፡፴፫፡ም፡
፳፰ ፳፪፡፳፫። የሚከሰስበትንም፡
ምክንያት፡አውቅ፡ዘንድ፡በፈለ
ግሁ፡ጊዜ፡ወደ፡አደባባይ፡አወ
ረድሁትም፡፳፫፡፩፡፴።
፳፱ ያንጊዜውንም፡በሕጋቸው፡ስ
ለ፡መከራከር፡ምክንያት፡እንደ
ከሰሱት፡አገኘሁ፡ስለሞት፡እንኳ
ንስ፡ለሞት፡ለእሥራት፡የሚያ
ደርስ፡ኀጢአት፡ምንም፡አላገ
፴ ኘሁበትም። በዚህም፡ሰው፡አ
ይሁድ፡ክፉ፡ምክር፡እንደ፡መከ
ሩበት፡ባወቅሁት፡ጊዜ፡ያንጊዜ

ውን፡ወደ፡አንቲ፡ሰደድሁት፡ከ
ሰሾቹንም፡በፊትህ፡ይከሱት
ዘንድ፡አዘዝኋቸው፡ደኅና፡ሁ
፴፩ ንቆም፡፲፩፡፫ቆጭፍሮቹም፡
እንደ፡አዘዙት፡ጳውሎስን፡በ
ሌሊት፡ወሰደው፡ወደ፡አንቲጳ
፴፪ ጥሪስ፡አደረሱት፤በነጋውም፡
ከእርሱ፡ይሔዱ፡ዘንድ፡ፈረሰኞ
ቹን፡ትተው፡እነርሱ፡ወደ፡
፴፫ ሰፈር፡ተመለሱ፤እነዚያውም
ወደ፡ቂሣርያ፡በገቡ፡ጊዜ፡ደብ
ዳቤውን፡ለሹሙ፡ሰጡት፡ጳው
፴፬ ሎስንም፡በፊቱ፡አቆሙት፤ደብ
ዳቤውንም፡ካነበበ፡በኋላ፡የወ
ዴት፡አገር፡እንደ፡ሆነ፡ጠየቀው፡
የኪልቅያ፡ሰው፡መሆኑንም፡ዐ
፴፭ ወቀ፡ጊዜቆም፡፲፪፡፫ቆእንግዲ
ከሳሾችህ፡ሲመጡ፡እሰማሃለ
ሁ፡አለው፡በሄሮድስም፡አደራ
ሽ፡አግብተው፡ይጠብቁት፡ዘን
ድ፡አዘዘ። ምዕራፍ፡፳፬።

ጳውሎስ፡በፊልክስ፡ፊት፡እንደ፡
ተከሰሰ፤ፊልክስ፡ከጳውሎስ፡ጉ
ዐ፡እንደ፡ፈለገ፤ፊስጦስ፡በፊል
ክስ፡ፋንታ፡እንደ፡ተሾመ፨

፩ ከአምስት፡ቀንም፡በኋላ፡የካህ
ናቱ፡አለቃ፡ሐናንያ፡ከሽማግሌ
ቾና፡ስሙን፡ጠርጠሉስ፡ከሚ
ሉት፡ከአንድ፡ጠበቃ፡ጋራ፡ወረ
ደ፡ጳውሎስንም፡በሹሙ፡ፊት
፪ ከሰሡት። በተጠራም፡ጊዜ፡ጠ
ርጠሉስ፡ይከሰው፡ዘንድ፡ጀመ
፫ እንዲህ፡እያለ፡ክቡር፡ፊልክ
ሆይ፡በአንተ፡ጊዜ፡ብዙ፡ሰላ
እንዳገኘን፡ለዚህም፡ሕዝብ
በሐሳብ፡መልካም፡መሻሻ
እንደ፡ሆነለት፡በየጊዜው፡በ
ገሩ፡ሁሉ፡እያስተማመን፡እ
፬ መሰግንሃለን፡ነገር፡ግን፡
ጋ፡እንዳላበዛብህ፡በቸርነ
ህ፡ባጭሩ፡ትሰማኝ፡ዘንድ፡
፭ ምንሃለሁ፡እኛ፡ይህን፡ሰወ
የመናፍቃን፡የናዝራውያ
ወገን፡መሪ፡እየሆነ፡በዓለም
ባሉት፡አይሁድ፡ሁሉ፡በሽታና
፮ ሁከት፡ሁኖ፡አገኘነው፤ቤተ፡
መቅደስንም፡ሊያረክስ፡ሲፈ
ልግ፡ያዝነው፡እንደ፡ሕጋችንም
እንፈርድበት፡ዘንድ፡ወደድነ
፯ ም፡፲፩፡፫ቆነገር፡ግን፡የሻለ
ቃው፡ሊስያስ፡መጥቶ፡በግድ
፰ ከእጃችን፡ወሰደው፤ከሳሾቹን
ም፡ወደ፡አንተ፡ይመጡ፡ዘንድ፡አ
ዘዘ፡እርሱንም፡የከሰስነበት
ንም፡ነገር፡ሁሉ፡አንተው፡ራስ
ህ፡እርሱን፡መርምረህ፡ሐታገ
ኘው፡ተቸሳህቆም፡፲፪፡፴ቆ
፱ ከአይሁድም፡በአንድነት፡ሁነ
ው፡እዎን፡ይህ፡ነገር፡እንዲሁ፡
፲ ነው፡አሉቆይናገርም፡ዘንድ፡
ሹሙ፡በጠቀሰው፡ጊዜ፡ጳውሎ
ስ፡መለሰ፡እንዲህ፡ሲል፡ከብዙ

ዘመን፡ ጀምረህ፡ ለዚህ፡ ሕዝብ
አንተ፡ ፈራጅ፡ እንደ ሆንህ፡ እኔ
አውቃለሁና፡ ስለዚህ፡ ልቤን፡ ደ
ስ፡ እያለው፡ በድፍረት፡ እናገራ
ለሁ፦ እሰግድ፡ ዘንድ፡ ወደ፡ ኢ
የሩሳሌም፡ ከወጣሁ፡ ከአሥራ
ሁለት፡ ቀን፡ እንደይበልጥ፡ እን
ተም፡ ልታውቀው፡ ትችላለህ።
ም፡ ፳፩፡ ፯፦ በመቅደስም፡ ከአ
ንድ፡ ሰው፡ ጋ፡ ስነጋገር፡ በመሰጊድ
ም፡ ሆነ፡ በከተማም፡ በሕዝብ፡ ሳ
ይ፡ ሁከት፡ ሳነሣ፡ አላገኙኝም።
፲፫ ዘሬም፡ በከሰሱኝ፡ ነገር፡ ይረቱ
፲፬ ም፡ ዘንድ፡ አይቻሉም፦ ነገር፡
ግን፡ ክህደት፡ ያስተምራል፡
ስለሚሉኝ፡ ነገር፡ አስረዳሃለሁ
እኔ፡ በኦሪት፡ በነቢያትም፡ የተ
ጻፉትን፡ አምኜ፡ የአባቶቼን፡
አምላክ፡ አመልካለሁ፦ ፭፡
፲፭ እነርሱም፡ ለጻድቃንና፡ ለኃጥ
አን፡ የሙታን፡ ትንሣኤ፡ ይሆን
ዘንድ፡ እንዲጠብቁ፥ ለእኔም
እንዲሁ፥ በእግዚአብሔር፡ ዘንድ
ተስፋ፡ አለኝ፦ ዳን፡ ፲፪፡ ፪፡ ዮሐ፡
፲፮ ፭፡ ፳፰፡ ፳፱። ስለዚህም፡ በእግ
ዚአብሔርና፡ በሰው፡ ፊት፡ ሁለ
ጊዜ፡ የማታወላውል፡ ሕሊና፡
ትኖረኝ፡ ዘንድ፡ እጋደላለሁ።
፲፯ ም፡ ፳፫፡ ፩፦ ከብዙ፡ ዓመታትም፡
በኋላ፡ ለወገኖቼ፡ ምጽዋትና
መሥዋዕት፡ አደርግ፡ ዘንድ፡ መ
ጣሁ። ም፡ ፲፩፡ ፳፱፡ ገላ፡ ፪፡ ፲።
፲፰ በዚያም፡ ጊዜ፡ ከእስያ፡ የመጡ
አይሁድ፡ ከሕዝብ፡ ጋራ፡ በመከ
ራከር፡ ወይም፡ በፍጅት፡ ሳይሆ
ን፡ በመቅደስ፡ ስነፃ፡ አገኙኝ።
፲፱ ም፡ ፳፩፡ ፳፯። አሁንም፡ በእኔ፡ ሳይ
ነገር፡ እንዳላቸው፡ በፊትህ፡ መጥ
ተው፡ ይከሱኝ፡ ዘንድ፡ ይገባል፤
፳ ወይም፡ እኔ፡ በሸንጎ፡ ቆሚ፡ ሳለ
ሁ፡ ያገኙብኝ፡ ነገር፡ እንደ፡ አሉ
እነዚህ፡ ራሳቸው፡ ይመስክሩ፤
፳፩ በመካከላቸው፡ ቆሚ፡ ከምና
ገራት፡ ከዚች፡ ከአንዲት፡ ነገር፡
በቀር፡ ዛሬም፡ ስለ፡ ሙታን፡ ትን
ሣኤ፡ በፊታችሁ፡ በእኔ፡ ይፈረድ
፳፪ ብኛል፦ ፊልክስም፡ ይህን፡ በስ
ማ፡ ጊዜ፡ የዚህን፡ ነገር፡ ምክንያ
ት፡ አስተውሎ፡ አውቋልና፡ ለሲ
ላ፡ ቀን፡ ቀጠራቸው፡ የሻለቃው
ም፡ ሊስያስ፡ በመጣ፡ ጊዜ፡ ነገራ
ችሁን፡ በትክክል፡ እመረምራለ
ሁ፡ አላቸው። ም፡ ፳፫፡ ፳፯።
እንጂ። ዮሐ፡ ፲፬፡ ፴፡ ኤፌ፡ ፪፡ ፪።
፲፫ ስለዚህም፡ የእግዚአብሔርን፡
ጋሻ፡ ያዙ፡ ክፉይቱን፡ ቀን፡ መ
ቋወም፡ ይቻላችሁ፡ ዘንድ፡ ድ
ል፡ ተነሱ፡ ዘንድ፡ በሁሉ፡ የተዘ
፲፬ ጋጃችሁ፡ ሁኑ። ወገባችሁን፡ በ
ጽድቅ፡ ዝናር፡ ታጥቃችሁ፡ ቁ
ሙ። የጽድቅንም፡ ጥሩር፡ ልበ
ሱ። ሉቃ፡ ፲፪፡ ፴፭፡ ፩፡ ጴ፡ ፩፡ ፲፫፡ ኢ
፲፭ ሳ፡ ፶፱፡ ፲፯። ፍቅርን፡ የምትናገ
ር፡ የወንጌልን፡ ኃይል፡ ተጫም
፲፮ ታችሁ። ከዚህም፡ ጋራ፡ የሃይ
ማኖትን፡ ጦር፡ መሳርያ፡ በጃች
ሁ፡ ያዙ፡ የጋሳ፡ የክፉውን፡ ፍላጻ
ሁሉ፡ ማጥፋት፡ በሚቻላችሁ
ግንዘብ። ፩፡ ጴ፡ ፭፡ ፱፡ ፩ ዮሐ፡ ፭፡ ፬
፲፯ የሚያድናችሁን፡ ራስ፡ ቍር፡ በ
ራሳችሁ፡ ጫኑ፡ በጃችሁም፡ የመ
ንፈስ፡ ቅዱስን፡ ሰይፍ፡ ያዙ። ይ
ኸውም፡ የእግዚአብሔር፡ ቃል
፲፰ ነው። ፩፡ ተሰ፡ ፭፡ ፰። በጸሎትና
በልመና፡ ሁሉ፡ ስትጸልዩ፡ ሁል
ጊዜ፡ በልቡና፡ ትጉ። ስለ፡ ቅዱ
ሳንም፡ ሁሉ፡ ጸሎትን፡ አዘው
፲፱ ትሩ። ለኔም፡ ምሥጢር፡ ይገለ
ጽልኝ፡ ዘንድ፡ የወንጌልን፡ ም
ሥጢር፡ ገልጬ፡ እንድናገር፡
አፌን፡ ያረታልኝ፡ ዘንድ፡ ቈላ፡ ፬

ሮ፣ ፪፣ ተሰ፣ ፪፣ ፩፣ የሐዋ፣ ፬፣ ፴፬

፳ ማስተማር፡እንደሚገባኝ፡የሱን፡ነገር፡ግልጭ፡አስተምር፡ዘንድ፡ታስሬ፡እሱን፡የምለምነው። ፪፡ቆሮ፡፫፡፲።

፳፩ እናንተም፡ወሬዬን፡ታውቁ፡ዘንድ፡የምንኖርበትን፡የታመነ፡የእግዚአብሔር፡መልክተኛ፡ወንድማችን፡ጢኪቆስ፡የምሠራውን፡ሁሉ፡ያስረዳችኋል። የሐዋ፡፳፬፡፬፡ጢ፡፬፡፲፪።

፳፪ ወሬዬን፡ታውቁ፡ዘንድ፡ልባችሁንም፡ያጽና፡ዘንድ፡ስለዚህ፡ወደናንተ፡የሰደድሁት፡ቈላ፡፬፡፯።

፳፫ ከአባታችን፡ከእግዚአብሔር፡አብ፡ከጌታችን፡ከኢየሱስ፡ክርስቶስም፡ከሃይማኖት፡ጋራ፡ለወንድሞቻችን፡ፍቅርና፡ሰላም፡ይ

፳፬ ሁንላቸው። ጸጋውም፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ባለመለወጥ፡ለሚወዱት፡ሁሉ፡ይደርባቸው፡ያለ፡ሐሰት፡በእውነት። ፪ቆሮ፡፲፫፡፲፫። በሮም፡የተጻፈች፡በቲኪቆስ፡እጅ፡ወደ፡ኤፌሶን፡ሰዎች፡የተላከች፡የጳውሎስ፡መልእክት፡ተፈጸመች።

አስጀምሮ፡ላስጨረሰን፡ለእግዚአብሔር፡ክብር፡ምስጋና፡ይገባዋል።

በሮም፡የተጻፈ፡ወደ፡ፊልጵስዩስ፡ሰዎች፡የተላከች፡መልእክት። ምዕራፍ ፩፡ ክፍል፡ ፩።

ሐዝቡ፡ሳይበቁ፡ዲቁና፡ዲያቆናት፡ሳይበቁ፡ቅስና፡እንሾም፡ሲሳሉና፡ማኅ፡ከማኅ፡ለኖሮ፡ብለው፡ይገጸደው፡ይቀጫውም፡ብለው፡ስለ፡አስተማሩ፡በፊልጵ፡የምክር፡ቃል፡እንደ፡ጻፈላቸው።

፩ ከኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ባሮች፡ከጳውሎስና፡ከጢሞቴዎስ፡የተላከች፡መልእክት፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ለከበሩ፡ለቅዱሳን፡ሁሉ፡ተድረስ፡ከቀሳውስት፡ከዲያቆናት፡ጋራ፡በፊልጵስዩስ፡ሳሉ። ፩፡ቆሮ፡፮፡፬፡ ፩ጢሞ፡፫፡፩፡፰

፪ ከአባታችን፡ከእግዚአብሔር፡አብ፡ከጌታችን፡ከኢየሱስ፡ክርስቶስም፡ሰላምና፡ጸጋ፡ለናንተ፡ይሁን። ሮሜ፡፩፡፯።

፫ እኔን፡በምታስቡበት፡አሳብ፡ሁሉ፡ዘወትር፡ፈጣሪዬን፡አመሰግነዋለሁ። ሮሜ፡፩፡፰፡ ፩፡ቆሮ፡፩፡፬።

፬ ስለናንተም፡ሁልጊዜ፡እጸልያለሁ። የደስታ፡ጸሎትም፡አደርጋለሁ።

፭ ከቀደመችው፡ቀን፡ጀምሮ፡እስከ፡ዛሬ፡ድረስ፡በወንጌል፡ትምርት፡እኔን፡ስለመሰላችሁ።

፮ እሱ፡የጀመረላችሁን፡በጎውን፡ሥራ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እስከ፡ሚመጣበት፡ቀን፡ድረስ፡እሱ፡እንዲፈጽምላችሁ፡አምናለሁና። ምዕ፡፪፡፲፫፡ቆሮ፡፲፬፡፳

፯ ስለ ናንተ፡ ይህን፡ ላስብ፡ ዘንድ የሚገባኝ፡ ስለ ሆነ፡ በእሥራቴ ና፡ በምክራከርበት፡ ወንጌል ንም፡ በማስተምርበት፡ ጊዜ፡ በ ልቡናዬ፡ አሳችሁና፡ በጸጋ፡ ከ ኔ፡ ጋራ፡ ተካፋዮች፡ ስለ ሆናች ሁ። ኤፌ፡፫፡፩፡ና፡፩፡፩። ክርስቶ

፰ ስ፡ ባዘዘው፡ ፍቅር፡ እንዴ፡ እፈ ቅራችሁ፡ እግዚአብሔር፡ ምስ ክሬ፡ ነውና።

፱ በዕውቀትና፡ በል ቡና፡ ጥበብ፡ ሁሉ፡ ፍቅራችሁ እጅግ፡ ይበዛ፡ ዘንድ፡ ስለዚህ፡ እጸልያለሁ። ኤፌ፡፩፡፲፯።

፲ የሚሻለውንና፡ የሚወደደው ን፡ሥራ፡ እንድትመረምሩ። ክር ስቶስ፡ በሚመጣበት፡ ቀን፡ ያለ መነቀፍ፡ ንጹሐን፡ ልትሆኑ። ሮ ሜ፡፲፪፡፪። ፩፡ተሰ፡፫፡፲፫።

፲፩ ለእግዚአብሔር፡ ምስጋናና፡ ክብር፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ የ ጽድቅን፡ ፍሬ፡ የተመላችሁ፡ ሆ ናችሁ። ኤፌ፡፫፡፱።

ክፍል፡፬፤

፲፪ ወንድሞቼ፡ የኔ፡ ወሬ፡ የ ክርስቶ ስ፡ የወንጌሉ፡ ትምህርት፡ በጸረሰ በት፡ ሁሉ፡ እንዲ፡ ደረሰ፡ ታውቁ ዘንድ፡ እወዳለሁ። ፪፡ጢሞ፡፪፡

፲፫ ፱። ስለ፡ ክርስቶስ፡ የሚሆን፡ እ ሥራቴም፡ በፍርድ፡ቤት፡ ሁሉ፡ በቀረውም፡ ስፍራ፡ ሁሉ፡ ፊጽ ሞ፡ እንዲ፡ታወቀ። ምዕ፡፬፡፳፪።

፲፬ በጌታችን፡ ካመኑ፡ ከወንድ ሞቻችንም፡ የሚበዙት፡ በእ ሥራቴ፡ የተቀበልኩትን፡ መከ ራ፡ ታግሠው፡ እንዲ፡ ተቀበሉ፡ ይልቁንም፡ ያለ፡ መፍራት፡ ጨ ክነው፡ የእግዚአብሔርን፡ ነ ገር፡ ሊናገሩ፡ ወደዋልና።

፲፭ ሮ፡፲፫፡፬፡ ቶ ስ፡ ፫፡፫። ከነዚህም ስለ፡ ቅናትና፡ ስለ፡ ምቀኝነት ስለ፡ በጎ፡ ፍቅርም፡ የክርስቶስን ነገር፡ ሊያስተምሩ፡ የወደዱ፡

፲፮ አሉ። ፪ቆሮ፡፲፪፡ ደግሞ፡ መኛ፡ ወንጌልን፡ ለማስተማር፡ እንድ

፲፯ ተሾምኩ፡ ያውቃሉና፡ በመ መካት፡ የክርስቶስ ን፡ ነገር የሚያስተምሩ፡ ግን፡ አምነው አይደለም፡ ይህን፡ አድርገው፡ በእሥራቴ፡ ላይ፡ ኀዘን፡ የሚያ በዙብኝ፡ መስሏቸው፡ ነው፡ እ ንጂ። ዋ ፯፡ አኔ፡ ግን፡ እነሆ፡ በዚ ህ፡ ደስ፡ አለኝ፡ በዚያም፡ ደስ፡ ይ

፲፰ ለኛል። በሐሰትም፡ ቢሆን፡ በ ውነትም፡ ቢሆን፡ በምክንያት ሁሉ፡ የክርስቶስን፡ ነገር፡ ያስተ ምሩ፡ ዘንድ፡ ሰውንም፡ ወደ ሱ፡ ይጠሩ፡ ዘንድ። ም ፬፡ ፲፯፡ ፲፰።

፲፱ እኔም፡ ይህች፡ ሥራ፡ በጸሎታች ሁ፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስም፡ መንፈስ፡ ስጦታ፡ ወደ፡ ሕይወ ት፡ እንድታደርሰኝ፡ አውቃለሁ

፳ ፪ ቆሮ፡፩፡፲፩። በማናቸውም፡ እ

ኝደላፍር፡ ተስፋ፡ እንደደረግ
ሁ፡ መጠን፤ እንግዲህም፡ እንደ
ቀድሞው፡ በልቡና፡ ደስታ፡ እን
ዴኖር፡ ይገለጣል፡ እንጂ፡ ለሁ
ኝም፡ በሕይወትም፡ ቢሆን፡ በ
ሞትም፡ ቢሆን፡ የክርስቶስ፡ ክብ
ሩ፡ በሥጋዬ፡ አሉ፡ ፩፡ ጴ፡ ፬፡ ፲፯፤
፳፩ እኔስ፡ በሕይወትም፡ ብኖር፡ ክ
ርስቶስ ኝ፡ ለማገልገል፡ ነው፡
ብሞትም፡ ለጥቅሜ፡ ነው፤ ገላ
፳፪ ፪፡ ፳፤ በሥጋዬም፡ በሕይወት
ብኖር፡ በሥራዬ፡ ፍሬ፡ አፈራ፡ ዘ
ንድ፡ ነው፤ ሮሜ፡ ፩፡ ፲፫፤ እነሱን
ከሚያስፈልገኝ፡ ከነዚህ፡ ከሁ
ለቱ፡ ለሰውነቴ፡ የምመርጠ
፳፫ ው፡ አጣሁ፤ ነገር፡ ግን፡ ከክርስ
ቶስ፡ ዘንድ፡ ለመኖር፡ ከዚህ፡
ዓለም፡ ተለይቼ፡ ልሔድ፡ እወ
ዳለሁ፤ ፩፡ ነገሥ፡ ፲፱፡ ፬፡ ፪፡ ቆሮ
፭፡ ፰፤ ይልቁንም፡ ይህ፡ ለኔ፡ የ
ሚሻልና፡ የሚሻልና፡ የሚገ
፳፬ ባ፡ ነው። ደግሞም፡ ስለናንተ
በሥጋዬ፡ ሕይወት፡ ልኖር፡ ይገ
፳፭ ባል፤ ይህንንም፡ አውቄ፡ ለደስ
ታችሁና፡ ለሃይማኖታችሁ፡ ክ
ፍታ፡ ከናንተ፡ ዘንድ፡ እንድኖ
ር፡ እምናለሁ፤ ም፡ ፪፡ ፳፬፤
፳፮ ደግሞም፡ ወደናንተ፡ በመ
ጣሁ፡ ጊዜ፡ በኔ፡ ትምሕርት፡ በ
ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ክብራች
ሁ፡ እየተጨመረ፡ ይበዛ ፡ ዘን
፳፯ ድ፤ ሥራችሁም፡ ለክርስቶስት
ምርት፡ ብቻ፡ በሚገባ፡ ይሁን፤
ወደናንተም፡ ብመጣ፡ ይህን፡ አ
ያለሁ፡ ባልመጣም፡ እሰማለሁ
አንድ፡ ልብና፡ አንድ፡ አካል፡ በመ
ሆን፡ ጸንታችሁ፡ እንደሳችሁ፡ የ
ወንጌል፡ ሃይማኖት፡ በመጣው
ድካም፡ እየተጋደላችሁ፤ ቆላ
፩፡ ፲፡ ፩፡ ተሰ፡ ፪፡ ፲፪፡ ፩፡ ጢሞ፡ ፩፡ ፲፰
፳፰ ፲፱፤ የነሱ፡ ጥፋት፡ የናንተ፡ ሕይ
ወት፡ ይታወቅ፡ ዘንድ፡ የሚቃወ
ሙን፡ ሰዎች፡ በማናቸውም፡ አ
ያናውጧችሁ፤ ፩፡ ጴ፡ ፫፡ ፲፬፤
፳፱ ይህንንም፡ ስጦታ፡ እግዚአብ
ሔር፡ ሰጣችሁ፡ ነገር፡ ግን፡ ልታ
ምኑበት፡ ብቻ፡ አይደለም፡ ስለ
ሱም፡ ደግሞ፡ መከራ፡ ትቀበሉ
ዘንድ፡ ነው፡ እንጂ፤ ሮሜ፡ ፭፡ ፫፤
፴ እንደሱም፡ ስለሱ፡ እንድትጋ
ደሉ፡ እኔን፡ እንደ ያችሁ፡ የኔን
ም፡ ነገር፡ ዛሬ፡ እንደ፡ ሰማችሁ፤
የሐዋ፡ ፲፯፡ ፭፡ ፬፤ ቆላ፡ ፳፡ ፱።

ምዕራፍ ፪ ።

ይኸንደደው፡ ይቀጨው፡ ብሉ፡ ውጸሊ፡ ከንቱ፡ ሸ
ቶ፡ ማስተማር፡ እንዳይገባ፡ መታዘዝንና፡ መታበ
ይን፡ ተተ፡ በትሑት፡ ልብ፡ ባልንጀራ፡ ማክበር፡ እ
ንዲገባ፡ እንዲ፡ ጸፈላቸው።

፩ በክርስቶስ፡ የሚገኝ፡ ደስታና፡ በ
ፍቅር፡ የልቡና፡ መጽናናት፡ በመ
ንፈስ፡ ቅዱስና፡ በማዘን፡ በይ-
ቅርታም፡ የሚገኝ፡ አንድነቱ

ዘሬ፡ በእናንተ፡ ዘንድ፡ ካለሁ፡ ሌ
፪ ፊሎ፡ ፬፡ ፩፡ ፫። ደስታዬን፡ ፈጽሙ
ልኝ፡ አሱን፡ ብቻ፡ ታስቡ፡ ዘንድ
አንድ፡ ልብ፡ ሁናችሁ፡ በአንድ፡
ምክር፡ ፀንታችሁ፡ በፍቅር፡ ተ
ኖሩ፡ ዘንድ። ሮሜ፡ ፲፪፡ ፲፮፡ ፩ቆ
፫ ሮ፡ ፩፡ ፲። ውዳሴ፡ ከንቱ፡ ወዳቻ
ሁ፡ ሥራችሁን፡ በፍክክር፡ አት
ሥሩ፡ አትኩሩ፡ ከፍ፡ ከፍም፡
፬ አትበሉ። ከራሳችሁ፡ አብል
ጣችሁ፡ ባልንጀሮቻችሁን፡ ተ
ሐተናን፡ በያዘ፡ ልቡና፡ አክብ
ሩ፡ እንጂ። ገላ፡ ፭፡ ፳፮፡ ሮሜ፡
፭ ፲፪፡ ፲። ለባልንጀሮቻችሁም፡
አስቡ፡ እንጂ፡ ለእናንተ፡ ብቻ
አታስቡ፡ ፩፡ ቆሮ፡ ፲፡ ፳፬፡ ፴፫።
፮ ፍጹማን፡ የሆናችሁ፡ ሁላችሁ
ም፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ለኛ፡ ያደ
ረገልነን፡ ይህነን፡ አስቡ። ዮሐ
፲፫፡ ፲፭። ይኸውም፡ እግዚአብ
ሔርን፡ የሚመስለው፡ ነው፡
ቀምቆ፡ እግዚአብሔር፡ የሆ
ነ፡ አይደለም። ቆላ፡ ፩፡ ፲፭። ዮሐ
፩፡ ፪፡ ፲፬፡ ፳፡ ዘፍ፡ ፫፡ ፳።
፯ ራሱን፡ አዋርዶ፡ የተገዢ፡ መል
ክን፡ ገንዘብ፡ አደረገ፡ እንጂ፡
ሰውን፡ መሰለ። ኢሳ፡ ፶፫፡ ፫፡ ፪
፰ ቆሮ፡ ፰፡ ፱፡ ዕብ፡ ፪፡ ፲፬፡ ፲፯፡ እን
ደ፡ ሰውም፡ ሁኖ፡ ለሞት፡ እስከ
ጀርስ፡ ድረስ፡ ታዘዘ፡ ሞቱም፡
በመስቀል፡ ነው። ዕብ፡ ፲፪፡ ፪፡

፱ ፰፡ ፳። ስለዚህም፡ እግዚአብ
ሔር፡ እጅግ፡ ከፍ፡ አደረገው፡
ከስም፡ የሚበልጥ፡ ስምንም
ሰጠው። የሐዋ፡ ፪፡ ፴፡ ኤፌ፡ ፩
፲ ፳፩፡ ዕብ፡ ፩፡ ፫፡ ፬። በሰማይና
በምድር፡ በባሕርም፡ ከምድ
ር፡ በታችም፡ ያለ፡ ጕልበት፡
ሁሉ፡ ለኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስ
ም፡ ይሰግድ፡ ዘንድ፤ ዮሐ፡ ፭፡
፳፫፡ ራእ፡ ፭፡ ፲፫፡ ኢሳ፡ ፵፭፡ ፳፫

፲፩ አንደበትም፡ ሁሉ። ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ በእግዚአብሔር፡
አብ፡ ክብር፡ ጌታ፡ እንደሆነ፡
ያምን፡ ዘንድ። የሐዋ፡ ፪፡ ፴፮
፲፪ ዮሐ፡ ፭፡ ፳፫። አሁንም፡ ወንድ
ሞቼ፡ ሁሉ፡ ጊዜ፡ እንደ ትሰሙ
ኝ፡ ሳለሁ፡ ብቻ፡ አይደለም፡ ይ
ልቁንም፡ ሳልኖር፡ ነው፡ እንጂ
በመፍራትና፡ በመደንገጥ፡ ለ
ሕይወት፡ የሚሆናችሁን፡ ሥ
ራ፡ ሥሩ። ፩፡ ጴ፡ ፩፡ ፲፯፡ መዝ፡ ፪
፲፫ ፲፩። ለሚወደው፡ ሥራ፡ የሚረ
ዳችሁ፡ እሱ፡ እግዚአብሔር፡
ይቅርታውን፡ ይፈጽምላችሁ
ዮሐ፡ ፲፭፡ ፭፡ ፪ ቆሮ፡ ፫፡ ፭።
፲፬ የምትሠሩትን፡ ሁሉ፡ ያለ፡ ማ
ንጐራጐርና፡ ያለ፡ መለያየት
ተስማምታችሁ፡ በፈቃድ፡ ስ
ሩ፡ ፩፡ ጴጥ፡ ፬፡ ፱።
፲፭ እንደ፡ እግዚአብሔር፡ ልጆች፡

የማትበድሉ፡ የጸሐን፡ ትሆኑ ዘንድ። በማያምኑና፡ በጠማሞች፡ ልጆች፡ መካከል፡ መነቀፍ ሳይኖርባችሁ፡ በዓለምም፡ እንደ፡ ብርሃን፡ ትታያላችሁ። ም ፭፡ ፲፡ ማቴ፡ ፭፡ ፲፬፡ ኤፌ፡ ፭፡ ፰።

፲፮ ክርስቶስ፡ በሚመጣበት፡ ቀን እኔ፡ በምመካባችሁ፡ ግን ዘብ፡ የሕይወትን፡ ትምህርት፡ እያስተማራችሁ፡ የዘራሁና፡ የደከምሁ፡ ለከንቱ፡ እንዳልሆነ፡ ፩ ተሰ፡ ፪፡ ፲፱፡ ኢሳ፡ ፵፱፡ ፬፡ ገላ፡ ፪፡ ፪

፲፯ ቲቶ፡ ፩፡ ፱። ስለ፡ ሃይማኖታችሁም፡ የማገልገል፡ መሥዋዕት እሠዋ ለሁ። እነሆ፡ በናንተ፡ እጅግ፡ ደስ፡ ይለኛል። ፪፡ ጢሞ፡ ፬፡ ፯

፲፰ እናንተም፡ በኔ፡ ደስ፡ ይበላችሁ

፲፱ ም፡ ፫፡ ፩፡ ፬፡ ፩። ጢሞቴዎስን፡ እንድሰድላችሁ፡ በጌታችን፡ በኢየሱስ፡ አምናለሁ፡ እኔም፡ የናንተን፡ ወሬ፡ ሰምቼ፡ ደስ፡ ይለኛ

፳ ዘንድ። እንደኔ፡ ሁኖ፡ በዕውቀት ጕዳያችሁን፡ የሚፈጽም፡ ያለሉ፡ የለኝምና፡ ፩፡ ቆሮ፡ ፲፮፡ ፲።

፳፩ ሁሉ፡ የክርስቶስን፡ ያይደለ፡ የራሱን፡ ጕዳይ፡ የሚያስብ፡ ስለ ሆ

፳፪ ነ። ፪፡ ጢሞ ፬፡ ፲፡ ፲፮። ልጅ፡ ለአባቱ፡ እንዲገዛ፡ በወንጌል፡ ትምርት እንደ፡ ተገዛልኝ፡ የዚህን፡ ሰውነ፡ ማብራን፡ ታውቁታላችሁ። ፩

፳፫ ጢሞ፡ ፩፡ ፪። የሱ፡ መኖር፡ የኔ፡ መኖር፡ እንደሆነ፡ አውቄ፡ እሱን፡ ፈጥኜ፡ እንድሰደው፡ ተስፋ፡ አ

፳፬ ደርጋለሁ። እኔም፡ ፈጥኜ፡ እንድመጣ፡ በጌታችን፡ አምናለሁ

፳፭ ም፡ ፩፡ ፳፪። ይልቁንም፡ ዘሬ፡ በሥራ፡ ከኔ፡ ጋራ፡ እንድ፡ ሁኖ፡ ክርስቶስ ን፡ የሚያገለግል፡ ለናንተ፡ ግን፡ ሐዋርያችሁ፡ የሚሆን፡ ጕደኛን ፡ ለመፈጸም፡ የኔ፡ መልክተኛ፡ የሚሆን፡ ወንድማችን፡ አፍሮዲጡን፡ ወደናንተ፡ እልከው፡ ዘንድ፡ ወደድሁም፡ ፬፡ ፲፰፡ ፪፡ ቆሮ፡ ፰፡ ፳፫።

፳፮ እንደ፡ ታመመ፡ ስለ መሞቱም፡ እንደ፡ ደረሰ፡ ሰምታችሁ፡ እንደዘናችሁ ለቱ፡ አውቆ፡ ሊያችሁ።

፳፯ ይወደልና፤ ነገር፡ ግን፡ እግዚአብሔር፡ ይቅር፡ አለው፤ ይቅር ያለውም፡ እሱን፡ ብቻ፡ አይደለም። እኔንም፡ ይቅር፡ አለኝ፡ እንጂ። በኀዘን፡ ላይ፡ ኀዘን፡ እንዳይጨምርብኝ። ዮሐ፡ ፩፡ ፵፯

፳፰ ኢሳ፡ ፴፰፡ ፩። አይታችሁት፡ ደስ፡ ይላችሁ፡ ዘንድ፡ ፈጥኜ፡ ወደናንተ፡ ሰደድሁት፡ እኔም

፳፱ ደስ፡ ይለኛል፡ ዘንድ። እንግዲህ፡ በብዙ፡ ደስታ፡ በጌታችን፡ መቀበል፡ ተቀበሉት። እንደዚህ፡ ያሉትን፡ ሰዎች፡ አክብራችሁ፡ ተቀበሏቸው። ፩ ቆሮ፡ ፲፮፡ ፲፰

፴ ሮሜ፡ ፲፮፡ ፪። የእግዚአብሐ

ግርኝ፡ሥራ፡ስመሥራት፡እስ
ከ፡ሞት፡ደርሷልና፡ከኔ፡መልእ
ክት፡እናንተ፡ያገኛችሁት
ን፡ይረዱም፡ዘንድ፡ሰውነቱ
ን፡አሳልፎ፡ሰጥቷልና፨፩ቆሮ፡
፲፮፡፲፡፲፯፡ዮሐ፡፳፡፳፬፨

ምዕራፍ፡ክፍል፫።

ቅዱስ፡ጳውሎስ፡ትውልዱ፡ከ፳ኤል፡ወገን
ከብንያም፡ነገድ፡እንደሆነ—ስሕግ፡አሪት፡ቀ
ናተኛ፡በመሆኑ፡በወንጌል፡ያመኑትን፡ያሳድዳቸ
ው፡እንደ፡ነበረና፡በኋላ፡ወደ፡ወንጌል፡እንደ፡ተመለሰ።

፩ አሁንም፡ወንድሞቼ፡በጌታች
ን፡ደስ፡ይበላችሁ፡ይህንም፡ስጽ
ፍላችሁ፡ቸል፡አላልሁም፡ያጸ
ናችኋልና፨ምዕ፡፬፡፲፫፡፬፡፬፨
፪ እናንተም፡ተጠበቁ፡ውሾችን
በሚመስሉ፡ክፉ፡በሠሩ፡ሰዎ
ች፡ዕወቁባቸው፨ሥጋቸውን
ብቻ፡ስመቍረጥ፡ተገዝረናል
በሚሉ፡ሰዎች፡ዕወቁባቸው፨
ራእ፡፳፪፡፲፭፡ኢሳ፡፶፮፡፲፩፡፲፪፨
፫ የተገዘርነስ፡በልቡና፡እግዚአ
ብሔርን፡የምናገለግለውና፡
የምናመልከው፡እኛ፡ነን፡በክር
ስቶስ፡እንመካለን፡እንጂ፡በሥ
ጋችን፡የምንመካ፡አይደለም፡
፬ ሮሜ፡፪፡፳፱፨ግዝረት፡ሳለኝ፡
በግዝረት፡የምመካ፡ከሆነ፡በ
ግዝረቱ፡መመካትን፡የሚያስ
ብ፡ሰውም፡ቢኖር፡ያን፡ሰው፡እ
ኔ፡እበልጠዋለሁ፨፪ቆሮ፡፲፩፡፲፰

፭ ፰ኛ፡በስምንተኛው፡ቀን፡የተ
ገዘርሁ፡ከ፳ኤል፡ወገን፡ከሚሆ
ን፡ከብንያም፡ነገድ፡የተወለድ
ሁ፨ከዕብራውያን፡ወገን፡የ
፮ ምሆን፡ዕብራዊ፨በኦሪት፡ሥ
ራት፡የፀናሁ፡ፈሪሳዊ፡ነኝ፡፡የ
ሐዋ፡፳፮፡፭፨በኦሪት፡ጽድቅ
ያለነውር፡ሁኜ፡ስለ፡ቅናሁ፡
፯ ምእመናንን፡አባረርሁ፨ነገር
ግን፡አጠቀመዋለሁ፡ያልሁት
ን፡ያንን፡ጥቅሚን፡ስለ፡ክርስቶ
ስ፡ላጣው፡ወደድሁ፨ማቴ፡፲፫፡
፰ ፵፬፨የኢየሱስ፡ክርስቶስን፡
ኃይል፡ማወቅ፡ስለ፡በዛልኝ፡
ሁሉን፡እንደምናምንምን፡
ቈጠርሁት፡ሁሉን፡ስለሱ፡የ
ተውሁለት፨እንደ፡ጉድፍም
ያደረግሁለት፡ክርስቶስን፡ጥ
ቅም፡አደርገው፡ዘንድ፨ኢሳ፡
፱ ፷፫፡፲፬፨በእሱም፡እጸና፡ዘንድ
በኦሪት፡እጸድቃለሁ፡ማለት፡
ዛሬ፡ሳይኖረኝ፡ክርስቶስን፡በ
ማመን፡ከእግዚአብሔር፡የሚ
ገኝ፡ጽድቅ፡አለኝ፡እንጂ፨ሮ
፲ ሜ፡፫፡፳፩፡፳፪፡፳፬፨ኢየሱስን
የተገናኘውንም፡ኃይል፡በዚ
ህ፡አውቀዋለሁ፡በመከራው
ም፡በሞቱም፡እመስለዋለሁ
ሮሜ፡፯፡፫፡፭፡ሮሜ፡፰፡፲፯፡ገላ፡
፲፩ ፮፡፲፯፨ሙታን፡በተነሡ፡ጊዜ
በዚህ፡አገኘው፡እንደ፡ሆነ፨

፲፪ ይህንን፡ጨርሼ፡የተቀበል
ሁ፡አይደለሁም፡ኢየሱስ፡ክርስቶ
ስ፡እኔን፡የመረጠበትን፡ክብ
ር፡ባገኘው፡ብዬ፡እከታተለዋለሁ
፩፡ጢሞ፡፮፡፲፪፡የሐዋ፡፱፡፮።
፲፫ ወንድሞቼ፡እኔ፡ግን፡ፍጹሚ
ዬን፡ገና፡ያገኘሁ፡አይመስለኝ
፲፬ ም፤የኋላዬን፡እዘነጋለሁ፡የ
ፊቴን፡ግን፡እከታተላለሁና
እግዚአብሔር፡በኢየሱስ፡ክ
ርስቶስ፡ወደ፡ሰማይ፡ለሚጠ
ራበት፡ክብር፡ጉበኛ፡እንደ፡
መሆኔ፡ዋጋዬን፡እሻለሁ።፩
ጢሞ፡፮፡፲፪፡ዮሐ፡፱፡፮።ፍጹ
፲፭ ማን፡የሆናችሁ፡ሁላችሁም
ይህን፡አስቡ፡ሌላም፡የምታ
ስቡት፡ቢኖር፡እግዚአብሔ
ር፡ያን፡ይገልጽላችሁ።ዕብ፡
፭፡፲፬፡፪፡ቆሮ፡፲፫፡፲፩፡ሮሜ፡፲፬፡
፲፮ ፭፡፫።ነገር፡ግን፡በደረስንበት
ሥራ፡ባንድነት፡እንጽና፡ገላ፡
፲፯ ፮፡፲፮፡፩፡ጴጥ፡፫፡፰።ወንድሞ
ቼ፡እኔን፡ምሰሉ፡እኔን፡እንደ
ምታዩኝ፡በእንዲህ፡ያለ፡አ
ካሄድ፡የሚሔዱትን፡ዕወቁ
፲፰ ባቸው።፩፡ቆሮ፡፲፩፡፩።ሁልጊ
ዜ፡እንደምነግራችሁ፡በሌላ
አካሔድ፡የሚሔዱ፡ብዙ፡ና
ቸውና፡ዛሬም፡የክርስቶስ፡
የመስቀሉ፡ጠላቶች፡እንደ
ሆኑ፡ገልጬ፡እነግራችኋለሁ
፩ቆሮ፡፩፡፳፫፡ገላ፡፮፡፲፬፡ን—
፲፱ ፍጻሜአቸው፡ለጥፋት፡የሚ
ሆን፡ሆዳቸውን፡የሚያመል
ኩ፡ክብራቸውም፡ነውር፡የ
ሚሆንባቸው፡ምድራዊው
ን፡ዓለም፡የሚሹ፡ናቸው፤ሮሜ
፳ ፲፮፡፲፰።እኛ፡ግን፡አገራችን፡በ
ሰማይ፡ነው፡ከዚያም፡ሁነን፡
መድኃኒታችንን፡ኢየሱስ፡ክርስ
ቶስን፡እንጠብቃለን።ኤፌ፡፪፡
፲፱፡ቆላ፡፫፡፩፡ቲቶ፡፪፡፲፫፡ዕብ፡፲፪፡
፳፩ ፳፪።አሮጌውን፡ሥጋችንን፡የ
ሚያድሰው፡የክብሩ፡ሥጋው
ን፡እንዲመስል፡የሚያደርገው
ሁሉ፡የሚገዛበት፡የኃይሉ፡እ
ንግሥነት፡እንደ፡ሚረዳን፡መጠ
ኑ።፩ቆሮ፡፲፭፡፵፫፡፵፱፡፶፫።

ምዕራፍ፡፬፡ክፍል፡፭።

እግዚአብሔር፡እንዳስቻለው፡መወን፡ተ
ድላውንም፡ችጋሩንም፡ረኃቡንና፡ጽጋቡ
ን፡ደስታውንም፡መከራውንም፡ለምጀ
ዋለሁ፡ብሎ፡እንደ፡ተናገረ—

፩ ደስታችንና፡ክብራችን፡የም
ትወዱ፡ወንድሞቻችን፡አሁንም
እንዲህ፡ቁሙ፡በጌታችንም፡ፅ
ኑ።፪፡ቆሮ፡፩፡፲፬፡፩፡ተሰ፡፪፡፲፱፡፳
፪ ኤውድያንና፡ስንጣክንም፡ባን
ድ፡ልብ፡ጌታችንን፡ለማገልገ
ል፡ታስቡ፡ዘንድ፡እማልዳችኋ
ለሁ፡ም፡፪፡፪።

፫ ወንዱሜ፡ አጋዤ፡ ስተረክ፡ እን
ተም፡ ተረዳቸው፡ ዘንድ፡ እማል
ድሃለሁ። ከቀሌምንጦስ፡ ጋ
ራ፡ ወንጌልን፡ በማስተማር፡
እንደኔ፡ ደክመዋልና፡ ስማቸ
ው፡ በሕይወት፡ መጽሐፍ፡ ተ
ጽፏል፡ ሥራቸው፡ ከኛ፡ ጋራ፡ አን
ድ፡ የሚሆን፡ ወንድሞቻችን
ን፡ ሁሉ፡ እርዳቸው። ፊል፡ ፪፡ ሉ፡ ፲፡ ፳፡
ራእ፡ ፲፫፡ ፰። ክፍል፡ ፯።

፬ ቀድሞ፡ በጌታችን፡ በሆነው፡ ነ
ገር፡ ደስ፡ ይበላችሁ። እንግዲ
ህም፡ በሚሆነው፡ ነገር፡ ደስ፡ ይ
በላችሁ፡ እላችኋለሁም፡ ፫፡
፩፡ ፬፡ ቆሮ፡ ፲፫፡ ፲፮፡ ኢሳ፡ ፲፮፡ ፲።

፭ ፍጹምነታችሁም፡ በሰው፡ ሁሉ
ዘንድ፡ ይታወቅ፡ እግዚአብ

፮ ሔር፡ ቅርብ፡ ነው፡ በምንም፡ አ
ታስቡ። ቲቶ፡ ፫፡ ፪፡ ዕብ፡ ፲፡ ፳
፯፡ ፱። በጊዜው፡ ሁሉ፡ በጸሎ
ት፡ ለምኑ፡ እንጂ፡ እያመሰገና
ችሁም፡ ልመናችሁን፡ ወደ፡ እ
ግዚአብሔር፡ አመልክቱ። ማ
ቴ፡ ፯፡ ፳፭፡ ፩፡ ጴጥ፡ ፭፡ ፯፡ መዝ፡ ፻፵

፯ ፶፡ ፲፰። ሁሉ፡ በዕ፡ የሚሆን፡
ከልቡናም፡ ከሐሊናም፡ ሁሉ
በላይ፡ የሚሆነው፡ የእግዚአ
ብሔርም፡ ሰላም፡ ልባችሁ
ና፡ አሳባችሁን፡ በኢየሱስ፡ ክር
ስቶስ፡ ታፅናው። ዮሐ፡ ፲፬፡ ፳፯፡
ቆላ፡ ፫፡ ፲፭፡ ሮሜ፡ ፭፡ ፩።

፰ አሁንም፡ ወንድሞቻችን፡ የ
ቀንነቱንና፡ የንጽሕናውን፡ የ
ዕውቀቱንና፡ የበጎውን፡ የፍ
ቅርንና፡ የመመረቁን፡ ሥራ፡
ሁሉ። የሚገባውንና፡ የሚመ
ሰገነውን፡ እንዲነት፡ ይህን፡
ብቻ፡ አስቡ። ሮሜ፡ ፲፪፡ ፲፯።

፱ ከኔ፡ ዘንድ፡ የተማራችሁትን
የሰማችሁትን፡ ያያችሁትንም
እሱን፡ ብቻ፡ ሥሩ፡ የሰላም፡ አ
ምላክ፡ እግዚአብሔር፡ ከናን
ተ፡ ጋራ፡ ይኑር። ፩፡ ተሰ፡ ፭፡ ፳፫

፲ በጌታችን፡ እጅግ፡ ደስ፡ ስለኛ፡ ከ
ቀድሞ፡ ጀምሮ፡ ሁላችሁም፡ ለ
ቸገረኝ፡ ነገር፡ ተጋታችሁ፡ ታስ
ባላችሁና፡ ዛሬም፡ ቢሰናችሁ
እንግዲህ፡ እንድታስቡልኝ፡ መ

፲፩ ጠንቶ። ፪፡ ቆሮ፡ ፲፩፡ ፱። ይህንም፡
የተናገርሁ፡ ስለ፡ አጣሁ፡ አይ
ደለም። ያለኝ፡ እንዲበቃኝ፡ አ
ውቃለሁና። ፩፡ ጢሞ፡ ፮፡ ፰።

፲፪ እኔ፡ ቸግሬንም፡ ተድሳውንም
እቻላለሁ፡ ሁሉን፡ በሁሉ፡ ለም
ጀለሁ። መራቡንም፡ መጥገቡ
ንም። ጎዘኑንም፡ ደስታውን

፲፫ ም። ፪፡ ቆሮ፡ ፯፡ ፱፡ ፲፮፡ ፳፯። ለሱ
ክርስቶስ፡ ስላስቻለኝ፡ ሁሉን፡
እቻላለሁ። ፩፡ ቆሮ፡ ፲፩፡ ፲፡ ኢሳ፡ ፵

፲፬ ፳፱፡ ፴፩። ነገር፡ ግን፡ በመከራ
ዬ፡ ከኔ፡ ጋራ፡ አንድ፡ በመሆናች
ሁ፡ በጎ፡ አደረጋችሁ።

፲፭ እናንተ፡ የፊልጵስዩስ፡ ሰዎች፡ በመጀመርያ፡ ትምርት፡ ወደ፡ መቄዶንያ፡ በመጣሁ፡ ጊዜ፡ ከምእመናን፡ አንዱስ፡ ስንኳ፡ እሱ፡ በመስጠት፡ እኔ፡ በመቀበል፡ ከኔ፡ ጋራ፡ ኦለዋድ፡ እንደ፡ ልሆነ፡ ታውቃላችሁ፡ እናንተ፡ ብቻ ናችሁ፡ እንጂ፨ ፩፡ ጢሞ፡ ፩፡ ፲፪

፲፮ ቆሮ፡ ፲፩፡ ፱፨ በተሰሎንቄም፡ ዷማም፡ አንድ፡ ጊዜ፡ ሁለት፡ ጊዜ፡ ለችግረኛ፡ ነገር፡ ላካችሁልኝ፡

፲፯ የሐዋ፡ ፲፯፡ ፩፨ ይህንም፡ የምናገር፡ ስጦታችሁን፡ ስሻ፡ አይደለም፡ በናንተ፡ ላይ፡ የጽድቅ፡ ፍሬ፡ ይበዛ፡ ዘንድ፡ ወድጄ፡ ነው፡ እንጂ፨ ፩፡ ቆሮ፡ ፱፡ ፲፩፡ ቲቶ፡ ፫፡ ፲፬፨

፲፰ እነሆ፡ የላካችሁልኝን፡ ሁሉ፡ ተቀበልሁ፡ ለለተ፡ ምግቤ፡ በቃኝ፡ በተረፈውም፡ ጉዳዬን፡ ፈጸምሁ፨ በእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ የተወደደ፡ የተመረጠ፡ በጎ መዓዛ፡ ያለው፡ መሥዋዕት፡ አድርጎ፡ ከናንተ፡ ወገን፡ የሚሆን አፍሮዲጡ፡ ስላመጣልኝ፡ ም ፬፡ ፳፰፡ ኤፌ፡ ፭፡ ፪፡ ዕብ ፲፫፡ ፲፮፨

፲፱ የምትሹትንም፡ ሁሉ፡ አምላኬ፡ ይፈጽምላችሁ፡ እንደ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ክብር፡ ብዛ

፳ ት፨ ፪ ቆሮ፡ ፱፡ ፰፨ እንደ፡ እግዚአብሔርም፡ ክብርነት፡ የዘለዓለም፡ ምስጋና፡ ለሱ፡ የሚሆን፡

፳፩ ቅዱሳንን፡ ሁሉ፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሰላምታ፡ እንዴት፡ ናችሁ ብሉ፡ ከኔ፡ ዘንድ፡ ያሉ፡ ወንድሞቻችን፡ እንዴት፡ ናችሁ፡ ይሏች

፳፪ ኋል፨ ፩፡ ቆሮ፡ ፲፮፡ ፳፡ ቅዱሳኑ፡ ሁሉ፡ ይልቁንም፡ በቄሣር፡ ቤት፡ መንግሥት፡ ያሉ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ እንዴት፡ ናችሁ፡ ይሏችኋል፨ ፪፡ ቆሮ፡ ፲፫፡ ፲፪፨

ወንድሞቻችን፡ የጌታችን፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ጸጋው፡ ከናንተ፡ ጋራ፡ ይሁን፨ ፩፡ ቆሮ፡ ፲፮፡ ፲፫፡ ቆላ፡ ፬፡ ፲፰፨

በሮም፡ የተጻፈች፡ በጢሞቴዎስና፡ በአፍሮዲጡ፡ እጅ፡ ወደ፡ ፊልጵስዩስ፡ ሰዎች፡ የተላከች፡ የጳውሎስ፡ መልእክት፡ ተፈጸመች፨ ፨ ፨

አስጀምሮ፡ ላስጨረሰኝ፡ ለእግዚአብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይግባው፨ ፨ ፨

በሮም፡ የተጻፈ፡ ወደ፡ ቈላስይስ፡ ሰዎች፡ የተላከ፡ መልእክት፡ ይህ፡ ነው። ምዕራፍ፡ ፩። ክፍል፡ ፩።

የቈላስይስ፡ ሰዎች፡ ከኤጳፍራ፡ ስለ ተማሩ፡ ኤጳፍራስ፡ ከጳውሎስ፡ ተምሮ፡ ነበረና የቀጅ፡ ቀጆ፡ ናቸሁ፡ ስላሏቸው፡ እነሱን፡ ጳሉ፡ ሰ ማሰጥ ተ፡ እንዲ፡ ጸፈላቸው።

፩ በእግዚአብሔር፡ ፈቃድ፡ የጌታችን፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሐዋርያው፡ ከሆነ፡ ከጳውሎስና፡ ከወንድማችን፡ ከጢሞቴዎስ፡ የተላከ፡ መልእክት፡ በክርስቶስ፡ አምነው፡ በቈላስይስ፡ ላሉ፡ ከቡራን፡ ወንድሞቻችን፡ ተድረስ። ፪፡ ቆሮ፡ ፩፡ ፪።
፪ የእግዚአብሔር፡ የአባታችን፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ የጌታችን፡ ሰላምና፡ ጸጋ፡ ለናንተ፡ ይ
፫ ሁን። ሮሜ፡ ፩፡ ፯። የጌታችን፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ አባት፡ ስለናንተ፡ ዘወትር፡ እናመሰግ
፬ ነዋለን። በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ እንደመናችሁም፡ ሁሉ፡ እንደ፡ ወደዳችኋቸው፡ ከሰማን፡ ወዲህ፡ እንጸልያለን። ኤፌ፡ ፩፡ ፲፭፡ ፲፮።
፭ በሰማይ፡ ስለ፡ ተዘጋጀላችሁ፡ ተስፋ፡ አስቀድማችሁ፡ በዕውነተኛው፡ ቃል፡ የሰማችሁት፡ የወንጌል፡ ትምርት። ፩፡ ጴጥ
፮ ፩፡ ፫፡ ፬፡ ፭፡ ቆሮ፡ ፯፡ ፯። በዓለሙ፡ ሁሉ፡ እንደ፡ ደረሰ፡ ወደናንተ፡ የደረሰ፡ በናንተ፡ ላይ፡ ብዙ፡ ፍሬ፡ ያፈሩ ላችሁ፡ ዘንድ፡ የእግዚአብሔርን፡ ጸጋ፡ ካያችሁና ከሰማችሁ፡ ወዲህ። ሮሜ፡ ፲
፯ ፲፰። እናንተን፡ ከሚያገለግል፡ በክርስቶስ፡ ያመነ፡ የኛ፡ አገልጋይ፡ ከሚሆን፡ ከወንድማችን፡ ከኤጳፍራስ፡ ዘንድ፡ እንደ፡ ተማራችሁም። ፬፡ ፲፪።
፰ በመንፈሳዊ፡ ፍቅር፡ መፋቀራችሁንም፡ እሱ፡ ነገረን። ፬
፱ ፲። ስለዚህም፡ እኛ፡ የናንተን፡ ወሬ፡ ከሰማን፡ ወዲህ፡ ስለናንተ፡ መጸለይንና፡ መለመንን፡ አላተውንም፡ በብዙ፡ ጥበብና፡ በመንፈሳዊ፡ ማስተዋል፡ እግዚአብሔር፡ የሚወደውን፡ ነገር፡ ማወቅን፡ ትፈጽሙ፡ ዘንድ። ኤፌ፡ ፩፡ ፲፭፡ ፲፮።
፲ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ በሚገባችሁ፡ ትሔዱ፡ ዘንድ፡ የበጎውን፡ ምግባር፡ ፍሬ፡ እያፈራችሁ፡ እግዚአብሔርን፡ የምታውቁበትን፡ ጥበብ፡ እየወደዳችሁ በሁሉ፡ ደስ፡ ታሰኙት፡ ዘንድ። ኤ
፲፩ ፌ፡ ፬፡ ፩። ፊል፡ ፳፯። በጌትነቱ፡ እንደ ኃይሉ፡ ሁሉ፡ ጸናታችሁ፡ ሁሉን፡ በመታገሥና፡ በ

ተስፋ፡በደስታም፡ጸንታችሁ
፲፪ ፩፡ቆሮ፡፩፡፳÷በብርሃን፡ከቅ
ዱሳን፡ጋራ፡ርስት፡ለመካፈል
ዝግጁ፡ያደረገን፡እግዚአብ
ሔር፡አብን፡አመስግኑት÷ኤፌ.
፲፫ ፩፡፲፩÷ለጨለማ፡ከመግዛት፡
አድኖ፡ወደ፡ሚወደው፡/ወደ፡
ልጁ፡መንግሥት፡የመለሰን÷
፲፬ ም፡፪፡፲፫÷መድኃኒታችነኛ፡የ
ኃጢአታችንንም፡ይቅርታ፡ያ
ገኘነበት÷ኤፌ፡፩፡፯÷
፲፭ ይኸውም፡የማይታይ፡እግዚአ
ብሔርን፡የሚመስለው፡ነው
ከፍጥረት፡ሁሉ፡በላይ፡የሚ
ሆን፡የበኵር፡ልጁ፡ነው÷ዕብ፩
፲፮ ፫÷ሁሉን፡ፈጥሮበታልና፡በሰ
ማይም፡በምድርም፡ያለውን፡
የሚታየውንም፡የማይታየ
ውንም፡መናብርትም፡አጋዕ
ዝትም፡ሊቃናትም፡ታላላቆ
ችም፡ቢሆን፡የሆነውን፡ሁሉ፡
በሱ፡እጅ፡ነው። ሁሉም፡በእሱ
ተፈጥሯል÷ዮሐ፡፩፡፫፡፲÷
፲፯ ከሁሉ፡አስቀድሞ፡የነበረ፡ነው።
ሁሉም፡በእሱ፡ጸንቷል። ምዕ
፲፰ ፳፫፡፳፭፡፳፯፡፳፯÷የም አመን
ምን፡ጉባኤ፡እሱ፡ነው÷መጀመ
ሪያ፡ስለሆነ፡ከሙታን፡ሁሉ፡
ቀድሞ፡ተነሣ፡ለሁሉ፡ገዥ፡ይ
ሆን፡ዘንድ÷ራእ፡፩፡፭፡ኤፌ፡፩፡፳፪
፲፱ ዮሐ፡፩፡፲፬፡፲፮÷ሁሉ፡በሱ፡ጸን

ቶ፡ይኖር፡ዘንድ፡ፍጹም፡በሱ፡
ሊሆን፡ወዷልና፡ሁሉንም፡በሱ
ይቅር፡ይለው፡ዘንድም፡፪፡፱
፳ ዮሐ፡፩፡፲፯÷በመስቀሉ፡ባፈሰ
ሰው፡ደሙ፡በሰማይ፡ያሉትንና
በምድር፡ያሉትን፡አስታረቀ፡
ኤፌ፡፩፡፲፡፪፡፲፬፡፲፯÷ዮሐ፡፪፡፪
፳፩ እናንተም፡ቀድሞ፡በልባችሁ፡
አሳብ፡በሥራችሁትም፡ክፋት
ከሱ፡የተለያችሁ፡ጠላቶቹ፡ነ
በራችሁ፡ዛሬ፡ግን፡ይቅር፡ብ
ሏችኋል÷ሮሜ፡፭፡፲፡ኤፌ፡፪፡
፳፪ ፲፪፡፬፡፲፰÷በሥጋው፡በተቀበ
ለው፡መከራውና፡በሞቱ፡ከፊ
ቱ፡ለመቆም፡የተመረጣችሁ
ንጹሐን፡ክቡራን፡ያደርጋችሁ
፳፫ ዘንድ÷ኤፌ፡፭፡፳፯÷ጨክናች
ሁ፡በሃይማኖት፡ብትጸኑ፡ከሰ
ማይ፡በታች፡በዓለሙ፡ሁሉ፡እ
ንደ፡ተነገረ፡ከሰማችሁት፡
ከወንጌል፡ትምርት፡ተስፋ፡ፅ
ኑ÷መሠረታችሁ፡ሳይናወጽ
እኔ፡ጳውሎስ፡ዙሬ፡ለማስተማ
ር፡ሐዋርያነትን፡የተሾምሁ
ለት÷፩ቆሮ፡፲፭፡፶፫፡የሐዋ፡
፳፬ ፱፡፲፭፡ማር፡፲፮፡፲፭÷ዛሬም፡በ
መከራዬ፡ደስ፡ይለኛል፡በሥጋ
ዬም፡ከክርስቶስ፡መከራ፡የቀ
ረኘን፡ስለሥጋው፡አፈጽማለ
ሁ፡እርሷም፡ቤተ፡ክርስቲያን
ናት፡ኤፌ፡፫፡፲፫፡፩፡ጴጥ፡፩፡፲፩።

፳፭ ስለናንተ፡ ባዘዘኝ፡ በእግዚአ
ብሔር፡ ትእዛዝ፡ አገልጋይ፡
ሁኜ፡ የተሾምሁስት፡ የእግዚ
አብሔርን፡ ቃል፡ እፈጽም፡ ዘ
፳፮ ንድ፡ ኤፌ፡ ፫፡ ፬፡ ፯። ከዓለም፡ እ
ስቀድሞ፡ ሰውም፡ ሳይፈጠር
የመከረውን፡ የተሠወረ፡ ም
ሥጢር፡ ሮሜ፡ ፲፮፡ ፳፭።
፳፯ ዛሬ፡ ግን፡ የዚህን፡ ምክር፡ የ
ክብሩን፡ ብዛት፡ በአሕዛብ፡
ላይ፡ ይገልጽባቸው፡ ዘንድ፡
ለወደደ፡ ለቅዱሳን፡ ገልጾላቸ
ው፡ የክብራችን፡ አሰኛቷ፡ በ
ናንተ፡ ሳይ፡ ያደረ፡ ክርስቶስ፡
ነውና። ሮሜ፡ ፰፡ ፲፡ ኤፌ፡ ፫፡ ፲፡
፳፰ ፯፡ ፲፯። እኛ፡ ሰውን፡ ሁሉ፡ መከ
ረን፡ አስተምረን፡ ወደሱ፡ የም
ንጠራስት፡ በጥበብ፡ ሁሉ፡ የ
ሠራውን፡ ሥራ፡ እየተናገርነ
ሰው፡ ሁሉ፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶ
ስ፡ በማመን፡ ፍጹም፡ ሁኖ፡ ይ
ጸና፡ ዘንድ። ዋ፡ ፳፬፡ ኤፌ፡ ፫፡ ፱
፳፱ ፬፡ ፲፫፡ ፳፡ ፳፬። በኃይሉ፡ እንዲ
ረዳኝ፡ ረድኤትነቱ፡ የምጋ
ደልለትና፡ የምደክምለት፡

ምዕራፍ፡ ፪።

ስለ፡ ቆላስይስ፡ ሰዎች፡ ሊጋደልላቸው፡ አ
ኘደ፡ ጠዴና = በነገር፡ ሸኘገላም፡ አኘደ
ዴታ ሰሉ፡ እኘዴ፡ መከራቸው።

፩ ስለናንተም፡ እንድጋደል፡ ልታ
ውቁ፡ እወዳለሁ፡ በሎዶቅያ፡ ስላ
ሉ፡ ሰዎች፡ ፊቴንም፡ በሥጋ፡ ስ
ላላዩኝ፡ ሁሉ። ፊል፡ ፩፡ ፴።
፪ ልባቸውን፡ ደስ፡ ይለው፡ ዘንድ፡
ተምርታቸውም፡ በፍቅር፡ ይ
ጸና፡ ዘንድ፡ በጥበብና፡ በሃይማ
ኖትም፡ ፍጹምነት፡ ባለው፡ ከ
ብር፡ ሁሉ፡ ስለ፡ ክርስቶስ፡ እግ
ዚአብሔር፡ የመከረውን፡ ም
ክር፡ በማወቅ፡ ዮሐ፡ ፲፯፡ ፫።
፫ የጥበብና፡ የዕውቀት፡ መዝ
ገብ፡ ሁሉ፡ የተሠወረበት። ፩
፬ ቆሮ፡ ፩፡ ፳፬፡ ፴። ይህንም፡ የ
ምነግራችሁ፡ በነገር፡ ማታለ
ል፡ የሚያስቱችሁ፡ እንዳይኖ
፭ ር፡ ነው። ሮሜ፡ ፲፮፡ ፲፰። እኔስ
በሥጋዬ፡ ከናንተ፡ ጋራ፡ ባል
ኖር፡ በልቡናዬ፡ ከናንተ፡ ጋራ
ነኝ፡ ማብራችሁንና፡ ሥራች
ሁን፡ በክርስቶስም፡ የሚሆ
ን፡ የሃይማኖታችን፡ ጽናት፡
ስላየሁ፡ እነሆ፡ ደስ፡ ይለኛል
፮ ፩ ቆሮ፡ ፭፡ ፫፡ ፲፬፡ ፵። ጌታችን
ን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ እንደ፡
፯ ተቀበላችሁት፡ በሱ፡ ኑሩ። በ
ሱ፡ መሠረትነት፡ የተሠራች
ሁ፡ ሁኑ፡ በተማራችሁትም፡
ሃይማኖት፡ ጽኑ፡ በዝታችሁ
እሱን፡ ታመሰግኑ፡ ዘንድ። ኤ
ፌ፡ ፫፡ ፲፯፡ ኤፌ፡ ፬፡ ፳፩፡ ፮ ተሰሎ፡ ፲፰

፰ በክርስቶስ፡ሕግ፡ያይደለ፡ሰው በሚያስተምረው፡ሥራት፡ይህን፡ዓለም፡ለማሳት፡በከንቱ የሚሸነግሉ፡ሰዎች፡ነገር፡በማራቀቅ፡እንዳያታልሏችሁ ዕወቁ፡ቍ፡፰፥የመለኮቱ፡ፍጹሜ፡ሥጋ፡በመሆን፡የተዋሃደው ዮሐ፡፩፡፲፬፡፲፯፡፩፡ጢሞ፡፫፡፲፮

፲ እናንተም፡በሱ፡ፍጹማን፡ገዥ፡ለሚሆን፡ለንጉሡ፡ለመስፍኑም፡ገዥ፡እሱ፡ነውና፥ኤፌ፡

፲፩ ፩፡፳፪፡ኃጢአት፡የሚሠራ፡የሰውነት፡ሥጋ፡በመቊረጥ፡የሰው፡እጅ፡ሥራ፡ያይደለ፡ግዝረትን፡በክርስቶስ፡ግዝረት፡የተገዘራችሁ፡በተ፥፩፡ጴ፡፫፡፳፩፡ሮሜ፡፪፡፳፱፥

፲፪ በጥምቀትም፡ከሱ፡ጋራ፡ተቀበራችኋል፡ከሙታን፡ባስነሣው፡በእግዚአብሔር፡አጋዥነት፡በሃይማኖት፡በሱ፡ትንሣኤ፡ከሱ፡ጋራ፡ተነሥታችኋል፥ሮሜ፡፮፡፬፡ኤፌ፡

፲፫ ፩፡፲፱፡፳፥በኃጢአትና፡በልቡናችሁ፡አለመገዘር፡ሙታኖች የነበራችሁ፡እናንተም፡እንደሱ፡ሕያዋን፡አደረጋችሁ፡ኃጢአታችሁንም፡ሁሉ፡ይቅር፡አለችሁ፥ኤፌ፡፪፡፩፡፭፡፲፩፡ሉ፡፯

፲፬ ፵፯፥በሠራው፡ሥራት፡የዕዳችን፡ደብዳቤ፡ከባላጋራችን እጅ፡አጠፋልን፡ከመካከላችን፡አራቀው፥በመስቀሉም፡ቸነከረው፥ኤፌ፡፪፡፲፭፡ኤር፡፲፯፡፩፡ሮሜ፡፲፡፬።

፲፭ ልብሱን፡በመገፈፉ፡ዕራቁቱን፡በመቆሙ፡የቀደሙትን፡ገዥዎች፡አሳፈራቸውም፡፩፡፲፫፡ኤፌ፡፮፡፲፪፡ሉ፡፲፩፡፳

፲፮ ፪፥በመብልና፡በመጠጥም፡ቢሆን፡ልዩ፡ልዩ፡በዓላትንም በማክበር፡የጨረቃንም፡ሠርቅ፡በመቍጠር፡ሰንበታትንም፡በመጠበቅ፡ቢሆን፡የሚነቅፉችሁ፡እንዳይኖር፡ዕወ

፲፯ ቁ፥ሮሜ፡፲፬፡፪፡፫፥ይህ፡ይመጣ፡ዘንድ፡ላለው፡ምሳሌ፡ነውና፡ሰለ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስም፡ሥጋ፡የሚያስንፉችሁ፡አይኑር

፲፰ ዕብ፡፲፡፩፥ባሳወቀው፡ነገር፡ባለቆች፡ሥራት፡ተታዘዙ፡ዘንድ፡በመሸኖግልና፡ራስ፡በማቃለል፡ሊያስቱችሁ፡ወደ፡በሥጋውም፡በመከረው፡ምክር፡ይመካልና፥ቆ፡፰፡፩፡ፊል፡፫፡፲፱፡

፲፱ ሥጋ፡ሁሉ፡በሚጸናበት፡አካልም፡በጅማት፡በሚያያዝበት፡በራስ፡አይጸናም፡በእግዚአብሔርም፡በሚያድግና፡በሚጸና፡በሚፈጸምም፡ግንዘ

፳ ብ፥ኤፌ፡፬፡፲፭፡፲፮፥እንዲህ፡ክርስቶስ፡ከዚህ፡ዓለም፡ኑሮ፡ከተለያችሁ፡እንደገና፡በዓለም፡እ

ንደምትኖሩ፡ሁናችሁ፡ይህን
ሥራ፡ለምን፡ትሠራላችሁ፥ን
፳፩ ሳ፡፲፡፫፡፱፥ ይህን፡አትያዝ፡ይህ
ን፡አትንካ፡ይህን፡አትቅመስ፡
ለምን፡ይሏችኋልና፥ዘሌ፡፲፩፡፪
፳፪ ፩ጢሞ፡፬፡፫፥ ይህ፡ሁሉ፡ለጥፋ
ት፡ነውና፡ጥበብ፡የሚያስመስ
ሉት፡የሰው፡ትእዛዝ፡እንደ፡መ
ሆኑ፥ኢሳ፡፳፱፡፲፫፡ማቴ፡፲፭፡፱፡
፳፫ ልባቸው፡ለሰ፡ተዋረደ፡እግዚ
አብሔርን፡መፍራት፡ለለሌለ
ባቸው፡ለሥጋ፡ማዘን፡ለለሌለ
ቸው፡ምንምን፡ክብር፡የለው
ም፡በሥጋ፡ላይ፡የሚሠራ፡ሥራ
ነው፡እንጂ፡፩፡ጢሞ፡፬፡፫።

ምዕራፍ፡፫ ።

ምድራዊ፡ሐሳብን፡ትተው፡ሰማያዊው
ን፡ሀሳብ፡እንዲያስቡ፡እንደ፡አስተማራቸ
ው፡ጸዊትንና፡የሙሴን፡ምስጋና፡የስሎሞ
ንን፡መኃልዬ፡መጸለይ፡እንዲገባ፡

፩ ከክርስቶስ፡ጋራ፡ከተነሣችሁ፡
በእግዚአብሔር፡ቀኝ፡የተቀመ
ጠ፡ክርስቶስ፡ወደ፡ለበት፡ወደ
ላይኛው፡መሐድን፡ፈልጉ፤ም
፪ ፍ፡፲፪፡ሮሜ፡፯፡፩፥ በምድር፡ያለ
ውን፡ያይደለ፡የላይኛውን፡አስ
ቡ፥ማቴ፡፯፡፫፡ዕብ፡፲፪፡፳፪፡፲፪፡
፫ ፲፬፥ ሙታችኋልና፡ሕይወታችሁ
ም፡ከክርስቶስ፡ጋራ፡በእግዚአብሔር፡ዘንድ
የተሠወረች፡ናት። ሮሜ፡፮፡፪
፬ ፊል፡፩፡፳፩፥ ክርስቶስ፡ግን፡በ
መጣ፡ጊዜ፡ሕይወታችሁ፡ይታ
ወቃል፡ያን፡ጊዜ፡ከሱ፡ጋራ፡በ
ታላቅ፡ክብር፡ትገለጣላችሁ
፭ ፩ዮሐ፡፲፫፡፵፫፥ በምድር፡ላይ
ያለ፡ሰውነታችሁን፡ከዝሙት
ና፡ከርኩሰት፡ከጠብና፡ከክፉ
ፉቃድ፡ከቀሚያም፡ስዩት፡ይ
ህውም፡ጣዖት፡ማምለክ፡ነው
ሮሜ፡፯፡፯፡ምዕ፡፲፫፡ኤፌ፡፭፡፫
፮ ባመፀኞች፡ልጆች፡ላይ፡የእግ
ዚአብሔር፡መቅሠፍት፡የሚ
፯ መጣበት፥ኤፌ፡፭፡፮፥ በዚህ፡ስ
ራ፡በኖራችሁ፡ጊዜ፡እናንተም
ቀድሞ፡የሔዳችሁበት፥ኤፌ
፰ ፬፡፩፡፫፥ እንግዲህ፡ግን፡ብስጭ
ትንና፡ቍጣን፡ከፉትንና፡ስድ
ብን፡የሚያሳፍረውንም፡ነገር
ትውት፡ከንቱ፡ነገርም፡ከፉቻ
ሁ፡አይውጣ፥ኤፌ፡፬፡፳፱፡፴፩
፱ ፭፡፬፥ ባልንጀሮቻችሁን፡አታ
ቋብሉ፡አሮጊውን፡ሰው፡ከሥራ
ው፡ሁሉ፡ጋራ፡ተዉት፡እንጂ፥
፲ ኤፌ፡፬፡፳፪፡፳፭፥ በፈጣሪው
አምሳል፡በዕውቀት፡የሚታደ
ሰውን፡አዲሱን፡ሰው፡ግን፡ም
፲፩ ሰሉት፥ኤፌ፡፬፡፳፬፤ በሱ፡ዘንድ
አይሁዳዊና፡አረማዊ፡የተገዘ
ረና፡ያልተገዘረ፡በሀገር፡ያለ
ና፡በበረሃ፡ያለ፡ቤተ፡ሰብና፡ጌ

ቃ፡ ነው፡ ማስቱ፡ የሌለበቱ፡ ክ
ርስቶስ፡ በሁሉ፡ ነው፡ ብዙ፡ ሁ
ሉን፡ ያስተካክሳል፡ እንጂ፡ ገላ
፲፪ ፫፡ ፳፫፡ ሮሜ፡ ፲፡ ፲፪። እግዚአብ
ሔር፡ እንደ፡ መረጣቸው፡ እንደ
ሚወዳቸው፡ እንደ፡ ቅዱሳን፡ በ
ቸርነትና፡ በይቅርታ፡ በበጎነት
ና፡ በተዋረደ፡ ልብ፡ በቅዋነት
ና፡ በትዕግሥት፡ ምስሉቱ። ኤ
፲፫ ፌ፡ ፬፡ ፪፡ ፴፪። ባልንጀሮቻቸ
ሁን፡ ቻሏቸው፡ እርስ፡ በርሳቸ
ሁም፡ ይቅር፡ ተባባሉ፡ ባልንጀ
ሮቻቸሁን፡ የነቀፋችሁ በተ
ኙ፡ ሥራ፡ ተዉ። ክርስቶስ፡ ይቅ
ር፡ እንደላችሁ፡ እናንተ ምእ
ንደሱ፡ ይቅር፡ በሉ። ማቴ፡ ፮፡ ፲፬
፲፬ ከዚህ ምሁሉ፡ ጋራ፡ ሁለጊዜ
በፍቅር፡ ኑሩ። ያንድነቱ፡ ማሰ
፲፭ ሪያ፡ እሱ፡ ነውና። እንዱ፡ አካል
በመሆን፡ የተጠራችሁለት፡ የ
ክርስቶስ፡ ፍቅር፡ በልባችሁ፡ ይ
ጽና፡ ክርስቶስን፡ በማመስገ
ኛ፡ ኑሩ። ሬሉ፡ ፪፡ ኤፌ ፬፡ ፬።
፲፮ የዳዊትን፡ መዝሙር፡ የሙሴ
ንም፡ ምስጋና። የተለየ፡ የሰሎ
ሞንም፡ ማኅሌይ፡ ድገሙ፡ በ
ጥበቡ፡ ሁሉ፡ ትክብሩ፡ ዘንድ
የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ በናን
ተ፡ ሳይ፡ ይጽና፡ ሰውነታችሁ
ን፡ አስተምሩ፡ ልባችሁንም፡ ገ
ሥፁ፡ በልባችሁም፡ እግዚአ
ብሔርን፡ አመስግኑ። ኤፌ፡ ፭፡
፲፯ ፲፱፡ የምትሠሩትን፡ ሁሉ፡ በጌ
ታችን፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስ
ም፡ ሥሩ፡ ስለሱም፡ እግዚአ
ብሔርን፡ አመስግኑት። ፩ቆሮ
፲፡ ፴፩፡ ኤፌ፡ ፭፡ ፳።

ክፍል፡ ፫ ።

፲፰ ሴቶችም፡ ለእግዚአብሔር፡
የምትገዙ፡ እንደ፡ መሆናችሁ
ለባሎቻችሁ፡ ታዘዙ። ኤፌ፡ ፭፡
፲፱ ፳፪፡ ፳፭። ወንዶችም፡ ሚስቶ
ቻችሁን፡ ሳታዋርዱ፡ ውደዷቸ
፳ ው። ፩፡ ጴጥ፡ ፫፡ ፯። ልጆችም፡ ለና
ት፡ ለባታችሁ፡ በሁሉ፡ ታዘዙ
እንዲህ፡ መታዘዝ፡ ይገባልና፡
እግዚአብሔርም፡ ይወዳልና
፳፩ ኤፌ፡ ፮፡ ፩፡ ፱። አባቶችም፡ ልጆ
ቻችሁን፡ እንዳያዝኑ፡ አታስመ
፳፪ ርሩ። ቤተ፡ ሰቦችም፡ ልበ፡ ሰራ
ሁናችሁ፡ ለጌቶቻችሁ፡ ታዘዙ
በማብዝነት፡ ለሰው፡ ይምሰል
አይሁን፡ እግዚአብሔርን፡ በ
መፍራት፡ ይሁን፡ እንጂ። ኤፌ
፳፫ ፮፡ ፭፡ ፲። ከእግዚአብሔር፡ ዘን
ድ፡ ዋጋ፡ እንድታገኙ፡ ታውቃላ
ችሁና፡ ለክርስቶስ፡ የምትገ
ዙ፡ ስለ፡ ሆነ፡ አልገዛም፡ ያለ፡
ጋን፡ ፍዳውን፡ ይቀበላል፡ እ
ግዚአብሔርም፡ አያዳላለት
ም። ምዕራፍ፡ ፬ ።

ከሃይማኖት፡ ልዩዎች፡ የሆኑ፡ ሰዎች፡ ለ

ምዕራፍ ፬።

ፃቀጽ፡ ለሠጥቁ፡ መጽሐፍ፡ ለልቡ፡ መጠባበቃ፡ እንዲገባ፡ መታሠሩን፡ እንደሚያዘነጉበት፡ እንዴ፡ አሳሰባቸው።

፩ ጌቶችም፡ ለቤቶ፡ ሰባቾቻችሁ፡ የተካከለ፡ ሥራ፡ ሥሩላቸው፡ እውነት፡ ፍርድንም፡ ፍረዱ፡ በሰማይ፡ ጌታ፡ እንዳለባችሁ ታውቃላችሁና። ዘሌ፡ ፳፭፡ ፵፫፡ ፴፫፡ ኤፌ፡ ፮፡ ፱። ፪ በማመስገን፡ ተግታችሁ፡ ጸሎትን፡ አዘውትሩ። ፩፡ ተሰ፡ ፭፡ ፲፯፡ ፊል፡ ፬፡ ፮። ፫ ለኛም፡ እግዚአብሔር፡ የትምህርቱን፡ ደጅ፡ ይከፍትልን፡ ዘንድ፡ በጸሎታችሁ፡ ለምኑልን፡ ስለሱ፡ የታሠርሁለት፡ እግዚአብሔር፡ የመከረውን፡ ምክር፡ እንድናስተምርበት። ሮሜ፡ ፲፭፡ ፴፡ ፪፡ ተሰ፡ ፫፡ ፩፡ ኤፌ፡ ፮፡ ፲፱፡ ፩ቆሮ፡ ፲፮፡ ፱። ፬ እንገልጠው፡ ዘንድ፡ መናገር፡ እንደሚገባኝ። ፭ ከሃይማኖት፡ ወደ፡ ተለዩ፡ ሰዎች፡ በጥበብ፡ ሒዱ። ኤፌ፡ ፭፡ ፲፭፡ ፲፯፡ ፩ ተሰ፡ ፬፡ ፲፪። ፮ ነገራችሁም፡ በእግዚአብሔር፡ ጸጋ፡ እንደ፡ ጨው፡ የጣፈጠ፡ ይሁን፡ እያንዳንዳችሁ፡ የምትመልሱትን፡ ታውቁ፡ ዘንድ። ኤፌ፡ ፬፡ ፳፱፡ ማር፡ ፱፡ ፶። ፯ የኔንም፡ ነገር፡ በእግዚአብሔር፡ ወንድማችሁ፡ የሚሆን፡ በማገልገልም፡ አንድ፡ የምንሆን፡ የታመነ፡ ወንድማችን፡ ጢቂኮስ፡ ይነግራችኋል። ፰ ስለዚህ፡ ነገር፡ ወደ፡ እናንተ የላክሁትም፡ የኔን፡ ነገር፡ ዐውቃችሁ፡ ልባችሁን፡ ደስ፡ ይለው፡ ዘንድ። ኤፌ፡ ፮፡ ፳፪። ፱ ከናንተ፡ ወገን፡ ከሚሆን፡ ከምንወደው፡ ከታመነ፡ ወንድማችን፡ ከአናሲሞስ፡ ጋራ፡ እነሱ፡ የምንሠራውን፡ ያለንበትን፡ ሥራ፡ ያስረዷችኋል። ፊል፡ ፲። ፲ ከኔ፡ ጋራ፡ የተማረከ፡ አርስጥሮኮስ፡ ወደናንተ፡ በመጣ፡ ጊዜ፡ እንድትቀበሉት፡ ያዘዝኋችሁ፡ የበርናባስ፡ የወንድሙ፡ ልጅ፡ ማርቆስ፡ እንዴት፡ ናችሁ ይሏችኋል። ሐዋ፡ ፲፱፡ ፳፱። ፲፩ ከተገዘሩ፡ ሰዎች፡ ወገን፡ የሚሆን፡ ኢዮስጦስ፡ የተባለ፡ ኢያሱም፡ እንዴት፡ ናችሁ፡ ይሏችኋል፡ የእግዚአብሔርን፡ የመንግሥት፡ ሥራ፡ በመሥራት፡ ደስ፡ ያሰኙኝ፡ ረዳቶቼ፡ እነሱ፡ ብቻ፡ ናቸው። ፲፪ የክርስቶስ፡ ባርያ፡ ከናንተ፡ ወገን፡ የሚሆን፡ ኤጳፍራስም፡ እንዴት፡ ናችሁ፡ ይሏችኋል፡ ስለናንተ፡ ሁሉ፡ ጊዜ፡ ይጸልያል፡ እግዚአብሔርም፡ የሚወደውን፡ ሥራ፡ የተመላችሁ፡ ፍጹማን፡ ትሆኑ፡

ዘንድ፡ይለምናል፤ም፡፩፡፲፪፨
፲፫ እጅግ፡እንዲወዳችሁ፡ስለናንተም፡በሎዶቅያና፡በኢያራም
ለሳሉ፡ሰዎች፡እንዲያገዝኝ፡እኔ
፲፬ ምስክር፡ነኝ። የነፍስ፡ባለ፡መድኃኒት፡ወዳጅ፡አቸን፡ሉቃስ፡
እንዴት፡ናችሁ፡ይላችኋል፤ዴማስም፡እንዴት፡ናችሁ፡ይላችኋል። ፪ጢሞ፡፬፡፲፡፲፩፡ፊል፡፳፬
፲፭ በሎዶቅያና፡በንምፋን፡በቤተ
ክርስቲያንም፡ያሉ፡ወንድሞቻችንን፡እንዴት፡ናችሁ፡በሏቸ
፲፮ ው። ይህችንም፡መጽሐፍ፡አንብባችሁ፡በቤተ፡ክርስቲያን፡
ያነቧት፡ዘንድ፡ወደ፡ሎዶቅያ፡
ሰደዷት፡ደግሞም፡እናንተ፡በሎዶቅያ፡የጻፍኋትን፡መልእክት
፲፯ አንብቧት። ለክርጳንም፡ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡የተሾም
ህበትን፡ማገልገል፡እንድትፈ
፲፰ ጽም፡ዕወቅ፡በሉት። እኔ፡ጳውሎስ፡በእጄ፡ጽፌ፡እንዴት፡ናች
ሁ፡እላችኋለሁ፡እሥራ
ቴን፡አስቡ፡ጸጋ፡ከናንተ፡ጋራ፡
ይሁን። ፩ቆሮ፡፲፮፡፳፩፡፪ተሰ፡
፫፡፲፯። በሮም፡የተጻፈ፡በጢኪቆስ፡እጅ፡ወደ፡ቆላስይስ፡ሰዎች፡የ
ተላከ፡መልእክት፡ተፈጸመ። አስ
ጀምሮ፡ላስጨረሰን፡ለእግዚአ
ብሔር፡ክብር፡ምስጋና፡ይግባ
ው። አሜን። ❖ ❖ ❖ ❖

በአቴና፡ሳለ፡የተጻፈ፡ወደ፡ተሰሎንቄ፡ሰዎች፡የተላከ፡መልእክት፡ይህ፡ነው። ምዕራፍ፡፩፡

ክፍል፡፲፯።

የተሰሎንቄ፡ሰዎች፡ቀዱስ፡ጳውሎስን፡በሌሊት፡ወደ፡ቤርያ፡ሸኝተው፡ስለ፡ሰደዱት፡ከሞት፡እንደ፡ዳነ፡ወንጌልንም፡በመቀበል፡ለሌሎች፡አብነት፡እንደሆኑ—

፩ ከጳውሎስና፡ከጢሞቴዎስ፡
ከስልዋኖስም፡የተላኩ፡መልእክት፡ባባታችን፡በእግዚአብሔር፡አብ፡በጌታችንም፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አምነው፡በ
ተሰሎንቄ፡ላሉ፡ምእመናን
ትድረስ፡የእግዚአብሔር፡ያባታችን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስ
ም፡የጌታችን፡ሰላምና፡ጸጋ፡
ለናንተ፡ይሁን። የሐዋ፡፲፯፡፲፱
፲፯፡፩፡፲። ፪ተሰ፡፩፡፩።
፪ ስለናንተ፡ሁልጊዜ፡እግዚአብሔርን፡እናመሰግነዋለን፡በጸ
ሎታችንም፡ሁልጊዜ፡እናመ
ሰግናችዋለን፡እናስባችኋለ
፫ ን። እምናችሁ፡የምትሠሩት
ን፡ሥራ፡የፍቅራችሁንም፡ጽ
ናት፡በጌታችን፡በኢየሱስ፡ክር
ስቶስም፡የሚሆን፡የተስፋች
ሁን፡ትዕግሥት፡በባታችን፡በ
እግዚአብሔር፡ፊት፡እናስባ
ለን። ዮሐ፡፮፡፳፱፡፩ቆሮ፡፲፫፡፲፫፡

የተወደዳችሁ፡ወንድሞቻችን፡እግዚአብሔር፡እንዲመረጣችሁ፡እናውቃለን፨ቆላ፡፫፡፲፪፨በናንተ፡ዘንድ፡ያስተማርነው፡ትምርት፡በነገር፡ብቻ፡አይደለምና፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡በሚደረግ፡ኀይል፡በታመነም፡ልመናም፡ነው፡እንጂ፨ስለናንተም፡በናንተ፡ዘንድ፡የሆነውን፡እናንተ፡ታውቃላችሁ፨፩፡ቆሮ፡፪፡፬፨እነሆ፡እናንተም፡እኛን፡መስላችኋል፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ከሚሆን፡ደስታ፡ጋራ፡በብዙ፡መከራ፡የእግዚአብሔርን፡ቃል፡ተቀብላችኋልና፨፩ቆሮ፡፬፡፲፯፨በመቄዶንያና፡በአካይያ፡ላሉ፡ሰዎች፡ሁሉ፡ምሳሌ፡ሆናችኋቸውም፨፬፡፲፨የእግዚአብሔርን፡ቃል፡ከናንተ፡ዘንድ፡ተምረው፡ተቀብለዋልና፡በመቄዶንያና፡በአካይያ፡ብቻም፡አይደለም፡በእግዚአብሔር፡ማመናችሁ፡በየሀገሩ፡ሁሉ፡ተሰምቷልና፡እንጂ፨የናንተንም፡ነገር፡እንናገር፡ዘንድ፡እኛ፡ምንም፡አንወድም፨ሮሜ፡፩፡፰፨ወደናንተ፡እንዴት፡ገባን፡ጣዖት፡ከማምለክም፡እግዚአብሔርን፡ወደ፡ማምለክ፡እንዴት፡ተመለሳችሁ፡እነሱ፡ቋሉ፡ያውቃሉና፡ሕያው፡ለሆነ፡ለውነተኛው፡ለምሳሌክ፡ትገዙ፡ዘንድ፡፩ቆሮ፡፲፪፡፪፨ከሙታን፡የተነሣ፡ልጁ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ከሰማይ፡እንዲመጣ፡ተስፋ፡አድርጋችሁ፡ከሚመጣውም፡ቍጣ፡እሱ፡ያድነናል፡ብላችሁ፨የሐዋ፡፩፡፲፩፡ፊል፡፫፡፳፡ቲቶ፡፪፡፲፫፨ [illegible]፡፱።

ቀን፡በትምርት፡ሌሊት፡በስራት፡መጽ ከሰው፡እንደ፡ጸፈላቸው፡-ቅዱስ፡ጳውሎስ፡ወደተሰሎንቄ፡ለመምጣት፡ሲያስብ፡እንዴ፡ጊዜና፡ሁለተኛ፡ጊዜ፡መሰናክል፡እንዳገኘው።

፩ ወንድሞቻችን፡እኛ፡ያደረግንላችሁን፡እናንተ፡ቀሉ፡ታውቃላችሁ፡ወደናንተ፡መግባታችን፡በከንቱ፡አይደለምና፨ምዕ፡፩፡፳፨

፪ ፱፨በፊልጵስዩስ፡እንደምታውቁት፡ተሰድብንና፡መከራውንም፡ተቀብለናል፡እንጂ፡ያንጊዜ፡በፈጣሪያችን፡አጋዥነት፡የክርስቶስን፡ትምርት፡በብዙ፡ድካም፡ነገርናችሁ፨የሐዋ፡፲፯፡፩፡፱፡ናሆ፡፲፯፡፪፨

፫ ትምርታችን፡ስሕተትና፡ኀጢአት፡ሽንገላም፡የሆነ፡አይደለ

፬ ምና፨እግዚአብሔር፡በመረመረን፡ወንጌልን፡ለማስተማር፡በሾመን፡ግንዘብ፡እንዲዚያ፡እናስተምራለን፡እንጂ፨ልቡናችንን፡ለመረመረን፡ለእግዚአብሔር፡ነው፡እንጂ፡ሰውን፡ደስ

ዘንድ፡ያለ ምናሌ፥ም፡፩፡፳፥
፲፫ እጅግ፡እንደ ወደዳችሁ፡ለለናገ
ተም፡በሎዶቅያና፡በኢያራም
ስላሉ፡ሰዎች፡እንደ ያዘን፡እኔ
፲፬ ምስክር፡ነኝ፥የነፍስ፡ባለ፡መ
ድኃኒት፡ወዳጃችን፡ሉቃስ፡
እንዴት፡ናችሁ፡ይላችኋል፥ዴ
ማስም፡እንዴት፡ናችሁ፡ይላች
ኋል፥፪፡ጢሞ፡፬፡፲፡፲፩፡ፊል፡፳፬
፲፭ በሎዶቅያና፡በኒምፋን፡በቤተ
ክርስቲያንም፡ያሉ፡ወንድሞ
ቻችንን፡እንዴት፡ናችሁ፡በሏቸ
፲፮ ው፥ይህችንም፡መጽሐፍ፡አን
ብባችሁ፡በቤተ፡ክርስቲያን፡
ያነቧት፡ዘንድ፡ወደ፡ሎዶቅያ፡
ሰደዷት፡ደግሞም፡እናንተ፡በሎ
ዶቅያ፡የጻፍኋትን፡መልእክት
፲፯ አንብቧት፥ለክርጳንም፡ከእ
ግዚአብሔር፡ዘንድ፡የተሾም
ህበትን፡ማገልገል፡እንድትፈ
፲፰ ጽም፡ዕወቅ፡በሉት፥እኔ፡ጳው
ሎስ፡በእጄ፡ጽፌ፡እንዴት፡ናች
ሁ፡እላችኋለሁ፡እሥራ
ቴን፡አስቡ፥ጸጋ፡ከናንተ፡ጋራ፡
ይሁን፥፩ቆሮ፡፲፮፡፳፩፡፪፡ተሰ፡
፫፡፲፯፥በሮም፡የተጻፈ፡በጢቂቆ
ስ፡እጅ፡ወደ፡ቈላስይስ፡ሰዎች፡የ
ተላከ፡መልእክት፡ተፈጸመ፥አስ
ጸምሮ፡ላስጨረሰን፡ለእግዚአ
ብሔር፡ክብር፡ምስጋና፡ይግባ
ው፥አሜን፥ ፥ ፥ ፥

በአቴና፡ሳሉ፡የተጻፈ፡ወደ፡ተሰ
ሎንቄ፡ሰዎች፡የተላከ፡መልእ
ክት፡ይህ፡ነው፥ምዕራፍ፥፩፥

ክፍል፡፲፬፥

የተሰሎንቄ፡ሰዎች፡ቅዱስ፡ጳውሎስ
ን፡በሌሊት፡ወደቤርያ፡ሸኝተው፡ሳሉ፡ሰጻ
ፉት፡ከሞተ፡እንዴ፡ደነ፡ወንጌልንም፡በመ
ቀበል፡ለሌሎች፡አብነት፡እንደሆኑ—

፩ ከጳውሎስና፡ከጢሞቴዎስ፡
ከስልዋኖስም፡የተላከች፡መ
ልእክት፥ባባታችን፡በእግዚአ
ብሔር፡አብ፡በጌታችንም፡በኢ
የሱስ፡ክርስቶስ፡አምነው፡በ
ተሰሎንቄ፡ላሉ፡ምእመናን
ተድረስ፡የእግዚአብሔር፡ያ
ባታችን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስ
ም፡የጌታችን፡ሰላምና፡ጸጋ፡
ለናንተ፡ይሁን፥የሐዋ፡፲፯፡፲፬
፲፯፡፩፡፲፥፪ተሰ፡፩፡፩፥
፪ ስለናንተ፡ሁልጊዜ፡እግዚአብ
ሔርን፡እናመሰግነዋለን፡በጸ
ሎታችንም፡ሁልጊዜ፡እናመ
ሰግናችዋለን፡እናስባችኋለ
፫ ን፥እምናችሁ፡የምትሠሩት
ን፥ሥራ፡የፍቅራችሁንም፡ድ
ናት፡በጌታችን፡በኢየሱስ፡ክር
ስቶስም፥የሚሆን፡የተስፋች
ሁን፡ትዕግሥት፡በባታችን፡በ
እግዚአብሔር፡ፊት፡እናስባ
ለን፥ዮሐ፡፮፡፳፱፡፩ቆሮ፡፲፫፡፲፫፥

፬ የተየወደዳችሁ፡ወንድሞቻ
ችን፡እግዚአብሔር፡እንዲመ
ረጣችሁ፡እናውቃለን፨ቆላ፡፫
፭ ፲፪፨በናንተ፡ዘንድ፡ያስተማር
ነው፡ትምርት፡በነገር፡ብቻ፡አ
ይደለምና፡በመንፈስ፡ቅዱስ
በሚደረግ፡ኃይል፡በታመነም
ልመናም፡ነው፡እንጂ፨ስለናን
ተም፡በናንተ፡ዘንድ፡የሆነውን
እናንተ፡ታውቃላችሁ፨፩፡ቆሮ
፮ ፬፡፫፨እነሆ፡እናንተም፡እኛን፡
መስላችኋል፡በመንፈስ፡ቅዱ
ስ፡ከሚሆን፡ደስታ፡ጋራ፡በብዙ
መከራ፡የእግዚአብሔርን፡ቃል
ተቀብላችኋልና፨፩ቆሮ፡፬፡፲
፯ ፯፨በመቄዶንያና፡በአካይያ፡
ላሉ፡ሰዎች፡ሁሉ፡ምሳሌ፡ሆና
፰ ችኋቸው፨ም፡፬፡፲፨የእግዚአ
ብሔርን፡ቃል፡ከናንተ፡ዘንድ፡
ተምረው፡ተቀብለዋልና፡በመ
ቄዶንያና፡በአካይያ፡ብቻም፡አ
ይደለም፡በእግዚአብሔር፡
ማመናችሁ፡በየሀገሩ፡ሁሉ፡
ተሰምታለች፡እንጂ፨የናንተ
ንም፡ነገር፡እንናገር፡ዘንድ፡አ
ኛ፡ምንም፡አንወድም፨ሮሜ
፱ ፩፡፳፨ወዳናንተ፡እንዴ፡ገባን፡
ጣዖት፡ከማምለክም፡እግዚአ
ብሔርን፡ወደ፡ማምለክ፡እንደ
ተመለሳችሁ፡እነሱ፡ቅሉ፡ያው
ቃሉና፡ሕያው፡ለሆነ፡ለውነተ
ኛው፡አምላክ፡ትገዙ፡ዘንድ
፩ቆሮ፡፲፪፡፪፨ከሙታን፡የተነ
ሣ፡ልጁ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ከሰ
ማይ፡እንዲመጣ፡ተስፋ፡አድ
ርጋችሁ፡ከሚመጣውም፡ቍ
ጣት፡እሱ፡ያድነናል፡ብላችሁ
የሐዋ፡፩፡፲፩፡ፊል፡፫፡፳፡ቲቶ፡፪፡
፲፫፨ምዕራፍ፡፪።

ቀን፡በትምርት፡ሌሌት፡በስራት፡መድከሙን፡
እንደ፡ጻፈላቸው፡፦ቅዱስ፡ጳውሎስ፡ወደተሰሎን
ቄ፡ለመምጣት፡ሲያስብ፡አንድ፡ጊዜና፡ሁለት፡
ጊዜ፡መሰናከል፡እንደ፡አገኘው፡-

፩ ወንድሞቻችን፡እኛ፡ያደረግን
ላችሁን፡እናንተ፡ቀሉ፡ታውቃላ
ችሁ፡ወደናንተ፡መግባታች
ን፡በከንቱ፡አይደለም፨ም፡፩፡፭
፪ ፱፨በፊልጵስዩስ፡እንደምታ
ውቁት፡ተሰድበናል፡መከራ
ውንም፡ተቀብለናል፡እንጂ፡
ያንጊዜ፡በፈጣሪያችን፡አጋዥ
ነት፡የክርስቶስን፡ትምርት፡በ
ብዙ፡ድካም፡ነገርናችሁ፨የሐ
ዋ፡፲፯፡፩፡፬፡ናሆ፡፲፯፡፬።
፫ ትምርታችን፡ስሕተትና፡ኃጢ
አት፡ሽንገላም፡የሆነ፡አይደለ
፬ ምና፨እግዚአብሔር፡በመረመ
ረን፡ወንጌልን፡ለማስተማር፡
በሹመነ፡ግንዘብ፡እንዲዜያ፡እ
ናስተምራለን፡እንጂ፨ልቡና
ችንን፡ለመረመረን፡ለእግዚአ
ብሔር፡ነው፡እንጂ፡ሰውን፡ደስ

እንደሚያስቸ፡ አይደለም፤ ፩፡ ጢሞ፡ ፩፡ ፲፩፤ ገላ፡ ፩፡ ፲፤

፭ ከሆኑ፡ ጀምሮ፡ እናንተ፡ እንደ ምታውቁ፡ በቃል፡ አልሸነገ ልናችሁም፡ በምክንያትም ም፡ አልቀማናችሁም፡ በዚህ እግዚአብሔር፡ ምስክራች

፮ ን፡ ነው፤ የክርስቶስ፡ መላክተ ኞች፡ እንደ፡ መሆናችን፡ ልና ዛችሁ፡ ቢቻለን፡ እናንተም ሌላም፡ ቢሆን፡ በገንዘብ፡ ደ ስ፡ ሲያሰኘን፡ አንወድም፤ ዮ ሐ፡ ፭፡ ፵፩፡ ፵፬፤ የሐ፡ ፳፡ ፴፫፤

፯ በእናንተ፡ መካከል፡ ሕፃናት ን፡ እንደሚያቃልሉ፡ ሆኑ፡ እን ጀራ የምታሳድግ፡ ሞግዚት፡ ልጆቿን፡ እንደምትወድ፡ እንደ ዚህም፡ እኛ፡ እንወዳችኋለን የወንጌልን፡ ትምርት፡ እናስ ተምራችሁ፡ ዘንድ፡ እንተጋ

፰ ላችኋለን፤ የእግዚአብሔ ርን፡ ወንጌል፡ የምናስተም ራችሁ፡ ብቻ፡ አይደለም፡ ሰ ውነታችንንም፡ እንሰጣች ኋለን፡ እንጂ፡ ወዳጆቻችን፡

፱ ሆናችኋልና፤ ወንድሞቻ ችን፡ ድካማችንን፡ መፃራች ንን፡ አስቡ፡ በቀንም፡ በሌ ሊትም፡ የጁ፡ ሥራ፡ እንሠራ ነበርን፡ ከናንተ፡ ወገን፡ አ ንዱን፡ ስንኳ፡ እንዳናስቸ ግር፡ እናንተ፡ ቀሉ፡ ምስክራ ችን፡ ናችሁ። ፩ቆሮ፡ ፬፡ ፲፪።

፲ የእግዚአብሔር፡ የወንጌሉን ትምርት፡ በውነትና፡ በቅንነ ት፡ በንጽሕናም፡ በሚያምኑ ሁሉ፡ ዘንድ፡ እንደ ስተማርኋ ችሁ፡ እግዚአብሔር፡ ምስክ ራችን፡ ነው፡ ፩፡ ጢሞ፡ ፫፡ ፱፤

፲፩ ከናንተ፡ ወገን፡ አያንዳንዳች ሁ፡ እንደምታውቁ፡ አባት፡ ልጁ ን፡ እንደሚልዱ፡ እንመልዳች

፲፪ ኋለን፤ ወደ፡ ጌትነቱ፡ ክብር ወደ፡ ጠራችሁ፡ እግዚአብሔር በሚገባ፡ ትሔዱ፡ ዘንድ፡ እና ደፋባችኋለን፤ ኤፌ፡ ፬፡ ፩፡ ፊ ል፡ ፩፡ ፳፯፤ ክፍል፡ ፪።

፲፫ ስለዚህም፡ እኛ፡ ሁልጊዜ፡ እግዚ አብሔርን፡ እናመሰግነዋለን፡ የ እግዚአብሔርን፡ ተእዘዝ፡ ቃ ል፡ ተቀብላችኋልና፡ የሰው ን፡ የወሬ፡ ቃል፡ አይደለም፡ እ ውነተኛውን፡ የእግዚአብሔ ርን፡ ቃል፡ ነው፡ እንጂ፡ ያመና ችሁ፡ እናንተም፡ ሥራ፡ በመ ሥራት፡ ይረዳችኋልና። ፩ ፭

፲፬ ገሳ፡ ፩፡ ፲፩፤ ወንድሞቻችን፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ አምነው በይሁዳ፡ ያሉ፡ የእግዚአብ ሔርን፡ ማደርያ፡ ምእመናን መስሳችኋቸዋልና፡ እነሱ፡ ጌ ታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ ከ

ግደሉ፡ ከአይሁድ፡ መከራ፡ አ
ኘደ፡ ተቀበሉ፡ እናንተም፡ ከ
ወገኖቻችሁ፡ መከራ፡ ተቀ
፲፭ ብላችኋልና። ከእሳቸው፡ወ
ገን፡ የሚሆኑ፡ ነቢያትንም፡ ለ
ኘር፡ አስጥለው፡ ሰደዋቸው
ነበር፡ እኛንም፡ ያሳድዱናል፤
እግዚአብሔርንም፡ ደስ፡ አ
ያሰኙትም፡ ከሰው፡ ሁሉ፡ ጋራ
ያጣላሉ። የሐዋ፡ ፯፡ ፶፪፡ ና ሆ
፲፮ ፫፡ ፴፫። አሕዛብን፡ በሚድኑ
ገንዘብ፡ እንድናስተምር፡ ይ
ከለክሉናል፡ የአሕዛብ፡ የሁ
ለጊዜ፡ ኃጢአታቸው፡ በነሱ
ይፈጸም ሳቸው፡ ዘንድ፡ የዘ
ላለም፡ መቅሠፍታቸውም
እነሆ፡ ደርሶባቸዋል። ማቴ፡
፲፯ ፳፫፡ ፴፪፡ ፴፫። አኛስ፡ ወንድ
ሞቻችን፡ በዚህ፡ ወራት፡ ከና
ንተ፡ የተነሣ፡ እናት፡ አባቱ፡ እ
ንደሞቀበት፡ ልጅ፡ ሆንን፡ ፊታ
ችሁን፡ ለማየት፡ ነው፡ እንጂ፡ በ
ልባችን፡ ተለይታችሁ፡ አይደ
ለም። ይልቁንም፡ ፊታችሁ
ንም፡ ልናይ፡ ወደናል። ሮሜ
፲፰ ፩፡ ፲፩። እኔ፡ ጳውሎስ፡ አንድ፡
ጊዜ፡ ሁለት፡ ጊዜ፡ ወደናንተ
እመጣ፡ ዘንድ፡ ወዶ፡ ወደድ
ሁ፡ ነገር፡ ግን፡ ሰይጣን፡ አሰና
፲፱ ከለኝ፡ ተስፋችን፡ ደስታች
ንስ፡ የመመኪያችን፡ ዘው
ድ፡ ማነው፡ በመጣ፡ ጊዜ፡ በጌ
ታችን፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡
ፊት፡ መመኪያችን፡ እናንተ
አይደላችሁምን። ፊል፡ ፬፡ ፲፪
ና፡ ፩፡ ፭፤ ክብራችንም፡ ደስ
ታችንም፡ እናንተ፡ ናችሁና

ምዕራፍ ፫።

በእምነት፡ ሳለ፡ ዝም፡ ብሎ፡ ለመቀመጥ፡ በ
ያስቸለው፡ ለማጽናናት፡ ሲል፡ ጢሞቴዎ
ስን፡ እንደ፡ ላከላቸው።

፩ መከራውንም፡ መታገሥ፡ ባ
ይቻለን፡ ብቻችንን፡ አንድ፡ ወገ
ን፡ ሁነን፡ በአቴና፡ መኖርን፡ ወ
፪ ደድን። የሐዋ፡ ፲፯፡ ፲፭፡ ፲፮። እግ
ዚአብሔርን፡ የሚገለግል፡
የክርስቶስን፡ ሐዋ፡ በማስተማ
ር፡ አንጋገር ያቸን፡ የሚሆን፡ወ
ንድማችን፡ ጢሞቴዎስን፡
ላክ፡ ወደናንተ፡ ላከነው፡ ያጸ
ናችሁ፡ ዘንድ፡ ስለ፡ ሃይማኖ
ታችሁም፡ ይማልዳችሁ፡ ዘ
፫ ንድ፡ እንዳትነዋወጡ በዚ
ች፡ መከራችሁም፡ ከናንተ
አንዱስ፡ ስንኳ፡ ተስፋ፡ እንዳ
ይቈርጥ፡ በየሔድንበት፡ ይ
ህ፡ ብቻ፡ እንዲቀየን፡ ታውቃ
ላችሁ። ኤፌ፡ ፫፡ ፲፫፡ ፪፡ ጢሞ፡ ፫
፬ ፲፪። ከናንተም፡ ዘንድ፡ በነበ
ርሁ፡ ጊዜ፡ አስቀድሜ፡ ይህን
ነግሬአችሁ፡ አለሁ፡ መከራ።

እንቀበል፡ዘንድ፡ሥቃይም
ያጸኑብን፡ዘንድ፡እንጸለን፡እ
፰ ንደ፡ነገርናችሁ፡ያው፡ሆነ፡ስ
ለዚህም፡መታገሥ፡ባይቻለ
ኝ፡ሃይማኖታችሁን፡አውቅ፡
ዘንድ፡ጢሞቴዎስን፡ላክሁት
የሚፈታተን፡ሰው፡የፈተና
ችሁት፡ፈተና፡እንደለ፡ሰለናን
ተ፡የደከምነው፡ድካም፡በከ
ንቱ፡ይሆናል፡ብዬ፡ፊል፡፪፡፲፮
፱ ዛሬ፡ግን፡ጢሞቴዎስ፡ከናንተ
ዘንድ፡ደርሶ፡ወደኛ፡ከመጣ፡ወ
ዲህ፡ሃይማኖታችሁን፡ፍቅ
ራችሁንም፡ከነገረን፡ወዲህ
ሁልጊዜም፡በበጎ፡እንድታስ
ቡን፡እኛ፡ልናያችሁ፡እንደ
ንወድ፡እናንተም፡ልታዩን፡
እንድትወዱ፡ከነገረን፡ወዲህ
፲ የሐዋ፡፲፰፡፭፡ወንድሞቻችን
ስለዚህ፡ስለ፡ሃይማኖታችሁ
ስለ፡ተቀበልነው፡መከራ፡ጭ
ንቀት፡ሁሉ፡ደስ፡አለንም፡
፲፩ ፪፡፪ ዘሬ፡እናንተ፡በጌታችን
ባመናችሁት፡ሃይማኖት፡ብ
፲፪ ትጸኑ፡ደስ፡ብሎናልና፡ሰለ
እናንተ፡ደስ፡ስለ፡አለን፡ደስታ
ሁሉ፡ለእግዚአብሔር፡ምን፡
ያህል፡ምስጋና፡ልንሰጠው፡እ
ንችል፡ይሆን፤ቀንና፡ሌሊት፡
በፊጣሪያችን፡ፊት፡እንጸልይ
፲፫ ዘንድ፡ይገባናል፡እንጂ፡ይል
ቁንም፡ፊታችሁን፡ ፡እናይ፡
ዘንድ፡የሃይማኖታችሁን
ም፡ሕፀፅ፡ይፈጽም፡ዘንድ፡የ
ጌታችን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
አባት፡እግዚአብሔር፡አብ፡
ወደናንተ፡መንገዳችንን፡ያቃ
፲፪ ናል፤እኛ፡እናንተን፡እንደ
እምንወዳችሁ፡የናንተም
እስበሳችሁ፡ከየአንደንዱ፡ው
ሉ፡ጋራ፡ፍቅራችሁን፡ያብዛ
፲፫ ላችሁ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክር
ስቶስ፡ከቅዱሳን፡ሁሉ፡ጋራ፡በ
መጣ፡ጊዜ፡ባባታችን፡በእግዚ
አብሔር፡ፊት፡በክብር፡ለመ
ቆም፡ልቡናችሁ፡በንጽሕና፡
ይጽና፤፪፡ተሰ፡፪፡፲፯፡ፊል፡፩፡፲

ምዕራፍ ፬፡ ክፍል ፫።

ፍቅር፡መስፊችው፡እንዲ፡ከንዱ፡ሚስ
ቱ፡የሚሔዱ፡ስለሆኑ፡በዝሙት፡ድልሳ
ትነው፡ብሎ፡እንዲ፡መከራቸው።

— — — —

፩ እሁንም፡ወንድሞቻችን፡እንነ
ግራችኋለን፡በጌታችን፡በኢየሱ
ስ፡ክርስቶስም፡እንማልዳችኋ
ለን፤ከኛ፡ዘንድ፡እንደ፡ታዘዛች
ሁ፡በሚገባ፡ትሔዱ፡ዘንድ፡እግ
ዚአብሔርንም፡ደስ፡ታሰኙት
ዘንድ፤ቀድሞ፡ስትሠሩ፡እንደ
ኖራችሁ፡እንግዲህም፡ይህን፡
አብዝታችሁ፡ትሠሩ፡ዘንድ፡
፪፡ተሰ፡፫፡፲፪፡ኤፌ፡፬፡፩ ።

፪ በጌታችን፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶ
ስ፡ ያዘዝናችሁን፡ ትእዛዝ፡ ታ
፫ ውቃላችሁ። የእግዚአብሔ
ር፡ ትእዛዙ፡ ይህ፡ ነውና፡ ፈቃዱ
ም፡ በንጽሕና፡ መኖራችሁ፡ ከ
ዝሙት፡ ተጠብቃችሁ፡ ርቃ
ችሁም፡ ትኖሩ፡ ዘንድ፡ ነው።
፬ ሁሉም፡ እያንዳንዱ፡ ገንዘቡ
ን ይወቅ፡ በንጽሕናና፡ በክብር፡
፭ ይገዛው። እግዚአብሔርን፡ እ
ንደማያውቁ፡ ይህነንም፡ ሌሎ
ች፡ እንደሚወዱ፡ እንደ፡ አረማ
ውያን፡ ዝሙትን፡ በመውደድ
ድል፡ አትነውሩ። ቆላ፡ ፫፡ ፭።
፮ ባልንጀሮቻችሁን፡ አትቀሙ
ስለዚህ፡ ሁሉ፡ እግዚአብሔር
ይበቀላልና፡ አስቀድሜ፡ እን
ደ፡ ነገርኋችሁ፡ እንደደፐሁበ
፯ ችሁ። እግዚአብሔር፡ ለንጽ
ሕና፡ ነው፡ እንጂ፡ ለኃጢአትሳ
፰ ልጠራችሁምና። አሁንም፡ ይ
ህን፡ የካደ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ የሰ
ጣችሁ፡ እግዚአብሔርን፡ ነው፡
እንጂ፡ ሰውን፡ የካደ፡ አይደ
፱ ለ፡ ይወቀ። ሉቃ፡ ፲፡ ፲፮። ባልን
ጀራችሁን፡ ስለመውደድ፡ ግ
ን፡ እንድጽፍላችሁ፡ ዘንድ፡ የም
ትሹ፡ አይደለም፡ እስበሳችሁ
ትፋቀሩ፡ ዘንድ፡ እናንተ፡ ከእ
ግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ የተማራ
ችሁ፡ ናችሁና። ማር፡ ፲፪፡ ፴፩፡ ፊ
ር፡ ፴፩፡ ፴፫፡ ፴፱።
፲ በመቄዶንያ፡ ካሉ፡ ወንድሞቻ
ችሁ፡ ሁሉ፡ ጋራ፡ ደግሞ፡ እንደ
ዚሁ፡ ታደርጋላችሁ፡ ወንድ
ሞቻችሁን፡ እጅግ፡ ትበዙ፡ ዘ
ንድ፡ እንማልዳችኋለን፨ ሮም፡ ፩
፲፩ ፪፡ ም ፬፡ ፩፨ ቀቀኖች፡ ትሆኑ፡ ዘን
ድ፡ እንደዘዝናችሁም፡ በጃች
ሁ፡ ሥራ፡ እየሠራችሁ፡ ትገዙ፡
ዘንድ፨ ፪፡ ተሰ፡ ከ፡ ፫፡ ፰፡ ፲፪፡ ም፳
፲፪ ፱፨ በአፍአ ያሉ፡ ሰዎች፡ በቀን
ነት፡ ትሔዱ፡ ዘንድ፡ ከማንም፡ ዘ
ንድ፡ ምግብ፡ እንዳትሹ፨ ሮሜ
፲፫፡ ፲፫፨ ክፍል፡ ፬፨
፲፫ ወንድሞቻችን፡ ስለሞቱ፡ ሰዎ
ች፡ ተስፋ፡ እንደሌላቸው፡ እን
ደ፡ አሕዛብ፡ ታለቅሱ፡ ዘንድ፡ እ
ንደይገባ፡ ልታውቁ፡ እንወዳ
ለንና፨ ፩፡ ቆሮ፡ ፲፭፡ ፳፡ ኤፌ፡ ፪፡ ፲፪፡
፲፬ ክርስቶስ፡ ሙቶ፡ እንደ፡ ተነሣ፡
ከመነ፡ እንደዚህም፡ እግዚአ
ብሔር፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ አስ
ነሥቶ፡ ከሱ፡ ጋራ፡ ያመጣቸዋ
ልና፨ ሮሜ፡ ፲፬፡ ፱፡ ፩፡ ቆሮ፡ ፲፭፡ ፳፬
፲፭ ይህንንም፡ በእግዚአብሔር
ቃል፡ እንነግራችኋለን፨ ጌታ
ችን፡ በመጣ፡ ጊዜ፡ ሕያዋን፡ ሁ
ነን፡ የምንቀር፡ እኛ፡ በሞቱቱ፡
አንደርስባቸውም፨ ፩፡ ፲፭፡ ፳፫፡
፲፮ ፶፩፨ በመላእክት፡ አለቃ፡ ቃል፡
በእግዚአብሔር፡ ነጋሪት፡ ድም

ዕ፡ ከሰማይ፡ የሚወርድ፡ ጌታ ችን፡ ያዘልና፡ በክርስቶስ፡ አ ምነው፡ የሞቱ፡ ሰዎች፡ አስቀ ድመው፡ ይነሣሉ፨ ፩ ቆሮ፡ ፲፭፡
፲፯ ፶፩፡ ፶፪፨ ከዚህ፡ በኋላ፡ ሕያዋ ን፡ ሁነን፡ የምቀር፡ እኛ፡ ከነሱ ጋራ፡ አንድነት፡ በደመና፡ እና ርጋለን፡ ጌታችንን፡ በአየር፡ እ ንቀበለው፡ ዘንድ፡ ከዚያ፡ ወዲ ያ፡ ሁለጊዜ፡ ከጌታችን፡ ዘንድ እንኖራለን፨ ራእ፲፬፡ ፲፬፡ ዮሐ፡
፲፰ ፲፪፡ ፳፮፡ ፲፯፡ ፳፬፨ አሁንም፡ ይህ ነን፡ ነገር፡ ለባልንጀሮቻችሁ፡ አስተምሩ፨

ምዕራፍ፡ ፭።

ጌታችን፡ የሚመጣበት፡ ቀን፡ እንደ፡ ሌባ፡ አመ ጣጥ፡ ድንገት፡ እንድትመጣ፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ በ ደኅንነት፡ አለን፡ ሲሉ፡ ድንገት፡ ሞት፡ ጥፋ ት፡ እንዲመጣባቸው፡

፩ ወንድሞቻችን፡ የዘመኑንና፡ የ ጊዜውን፡ የቀኑንም፡ ነገርስ፡ እ ንጽፍላችሁ፡ ዘንድ፡ አትሹም
፪ ማቴ፡ ፳፬፡ ፴፮፨ ጌታችን፡ የሚ መጣበት፡ ቀን፡ በሌሊት፡ እንደ ሌባ፡ አመጣጥ፡ እንድትመጣ፡ አመጣጡም፡ እንዲሁ፡ እን ደሆነ፡ ታውቃላችሁና፤ ማቴ፡ ፳፬፡ ፵፪፡ ፵፬፡ ፪ጴጥ፡ ፫፡ ፲፡ ራእ፡ ፫፡ ፫
፫ ና፡ ፲፮፡ ፲፭፨ እሱን፡ የሚክዱ፡ ሰ ዎች፡ በደኅንነትና፡ በሰላም፡ አ ለን፡ ሲሉ፡ ድንገት፡ ጥፋት፡ ይ መጣባቸዋል፡ የፀነሰች፡ ሴት፡ ም ጥ፡ በመጣባት፡ ጊዜ፡ ማም ለጥ፡ እንዳይቻላት፡ ማምለጥ፡ አይቻላቸውም፤ ኤር፡ ፯፡ ፲፬፡ ና
፬ ፳፡ ፲፮፨ እናንተ፡ ግን፡ ወንድሞቻ ችን፡ በጨለማ፡ የምትኖሩ፡ አ ይደላችሁም፤ ያ ቀን፡ እንደ ሌባ ድንገት፡ ይደርስባችሁ፡ ዘንድ፡
፭ ኤፌ፡ ፭፡ ፰፨ እናንተ፡ ሁላችሁም የብርሃንና፡ የቀን፡ ልጆች፡ ናችሁ ና፡ የሌሊትና፡ የጨለማ፡ ልጆ ች፡ አይደላችሁም፨ ሮሜ፡ ፲፫፡ ፲፪
፮ ኤፌ፡ ፭፡ ፲፬፨ አሁንም፡ እንደነዚያ እናንቀላፋ፡ ነቅተን፡ ተግተን፡ እውቀን፡ እንኑር፡ እንጂ፡ የሚያ ንቀላፉ፡ ሌሊት፡ ያንቀላፋሉና፡
፯ የሚሰክሩም፡ ሌሊት፡ ይሰክራሉ፡ እኛ፡ ግን፡ የቀን፡ ልጆች፡ ከሆነ፡ በአ ሳባችን፡ እንንቃ፡ የሃይማኖ ትንና፡ የፍቅርን፡ ጥሩር፡ እንልበስ
፰ የደኅንነታችንን፡ ተስፋ፡ ራስ፡ ቍ ር፡ እናድርግ፨ ሮሜ፡ ፫፡ ፲፫፡ ኢሳ፡ ፶
፱ ፱፡ ፲፯፡ ኤፌ፡ ፮፡ ፲፬፨ እግዚአብሔ ር፡ ለጥፋት፡ አላደረገምና፡ ለኛ ቢዞ፡ ስለ፡ ሞተ፡ ስለ፡ ጌታችን፡ ኢ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ለሕይወትና፡
፲ ለደኅንነት፡ ነው፡ እንጂ፤ የተኛም የነቃንም፡ ብንሆን፡ ከሱ፡ ጋራ፡ እንድንኖር። ሮሜ፡ ፲፬፡ ፰፡ ፱፡ ም ፬፡ ፲፬።

ክፍል፡ ፪።

፲፩ አሁንም፡ ወንድሞቻችን፡ በዚህ

፤ግር፡ባልንጀሮቻችሁን፡ደስ፡
አሰኙ፡እናንተ፡እንደምትሠሩ
ደግመኛ፡አንዱም፡አንዱም፡ሌ
ሌላውን፡ያጸናው፥ዕብ፡፲፡፳፬፡
፲፪ ወንድሞቻችን፡በናንተ፡ዘንድ
ለሚደክሙ፡ሰዎች፡ድካማቸ
ውን፡ዕወቁላቸው፡ብለን፡እንማ
ልዳችኋለን፤የጌታችንነንም፡ነገ
ር፡ጸንተው፡የሚያስተምሩአች
ሁን፡እጅግ፡አክብሩአቸው፤፩
፲፫ ቆሮ፡፲፮፡፲፰፤ስለምግባራቸው
ም፡ውደዱአቸው፡እጅም፡ንሱ
፲፬ አቸው፤ወንድሞቻችን፡አዘው
ትረው፡ኃጢአት፡የሚሠሩትን፡
ትገሥጹዋቸው፡ዘንድ፡እንማለ
ዳችኋለንየዘኑትንም፡አረጋጉ
ቸው፡የደከሙትንም፡አጽኑአ
ቸው፡ሁሉንም፡ታገሡ፤፪ተሰ
፲፭ ፫፡፲፭፤ክፉ፡ስላደረጉባችሁ፡ክ
ፉ፡እንዳታደርጉ፡ዕወቁ። እስበ
ሳችሁም፡ለሌላውም፡ሁሉ፡ሁ
ልጊዜ፡በጎ፡ሥራ፡ለመሥራት፡ተ
ቀደደሙ፡እንጂ፤ምሳ፡፭፡፳፬፡ሮ
፲፮ ሜ፡፲፪፡፲፯፡፩ጴ፡፫፡፱፤በሁሉ፡ጊዜ
ደስ፡ደስ፡ይበላችሁ፤ሉቃ፡፲፡፳፡
፲፯ ዘወትር፡ጸልዩ፡አጽርጉ፤ሉቃ፡
፲፰፡፩፡ሮሜ፡፲፪፡፲፪፡ቆላ፡፬፡፪፤
፲፰ በሥራው፡ሁሉ፡እግዚአብሔር
ን፡አመስግኑት፡በኢየሱስ፡ክርስ
ቶስ፡በሠራው፡ሥራ፡እግዚአብ
ሔር፡ከናንተ፡ዘንድ፡የሚሻው፡

ይህ፡ነውና። ኤፌ፡፭፡፳፡ቆላ፡፫፡፲፯
፲፱ ና፡፫፡፲፯፤ልባችሁን፡አታባክኑ፤
፳ ፩ቆሮ፡፲፬፡፴፡፴፱፤ትንቢትንም፡አ
፳፩ ትናቁ፤፩፡፲፬፡፩፤ሁሉንም፡መር
ምሩ፡በጎውን፡ሥሩ፡ያዙ፤ሮሜ፡
፳፪ ፳፡፲፯፤የሐ፡፩፡፩፤ከክፉ፡ሥራ፡ሁ
፳፫ ሉ፡ሽሹ፤የሰላም፡አምላክ፡እግ
ዚአብሔር፡በፍጹም፡ክብር፡ያ
ክብራችሁ፤ጌታችን፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡እስኪመጣ፡ድረስ፡ሥ
ጋችሁም፡ልቡናችሁም፡ነፍሳ
ችሁም፡በንጽሕና፡ሕያው፡ሁኖ
ይኑር፤ሮሜ፡፲፭፡፴፫፤
፳፬ የጠራችሁ፡እርሱም፡ይህን፡ያደ
ርግላችሁ፡ዘንድ፡እውነተኛ፡ነ
ውና፤፩ቆሮ፡፩፡፱፡፲፡፲፫፡፲፬፡ተሰ፡፫፫
፳፭ ፬፡ጢሞ፡፬፡፲፫፤ወንድሞቻችን
ጸልዩልን፤ቆላ፡፬፡፫፤
፳፮ በተሰየ፡ሰላምታ፡ወንድሞቻች
ን፡ሁሉ፡እንዴት፡ናችሁ፡በሉ፡እስ
በሳችሁም፡እንዴት፡ናችሁ፡ተ
፳፯ ባባሉ፤ሮሜ፡፲፮፡፲፮፤ይህችን፡መ
ጽሐፍ፡ለምእመናን፡ወንድሞቻ
ችንን፡ሁሉ፡ታሰሙዋት፡ዘንድ፡በ
ጌታችን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስ
፳፰ ም፡አማፅኛችኋለሁ፤የጌታች
ን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጸጋ፡ከ
ናንተ፡ጋራ፡ይሁን፡በውነት፡ያለ
ሐሰት፤ሮሜ፡፲፮፡፳፡፳፩፡ራእ፡፳
፪፤በአቴና፡የተጻፈ፡በጢሞቴ
ዎስና፡በስልዋኖስ፡እጅ፡ወደ፡ተ

ለሰሎንቄ፡ሰዎች፡የተላከ፡መጀመሪያ፡መልእክት፡ተፈጸመ፨
አስጀምሮ፡ላስጨረሰን፡ለእግዚአብሔር፡ክብር፡ምስጋና፡ይገባዋል፨ ፨ ፨ ፨

በሰሎንቄ፡የተጻፈ፡ወደ፡ተሰሎንቄ ሰዎች፡የተላከ፡ሁለተኛ፡መልእክት፡ይህ፡ነው። ምዕራፍ፡፩፡ ክፍል፡፩። እኔ፡ጳውሎስ፡እስከ፡ምጽአት፡ይቆያሉ፡ምጽአት፡በሐዋርያት፡ጊዜ፡ይደረጋል፡ለሚሉ፡የምጽአትን፡ነገር፡መሆኑን፡ለማስረዳት፡ሁለተኛ፡እንደ፡ጻፈላቸው

፩ ከጳውሎስና፡ከስልዋኖስ፡ከጢሞቴዎስም፡የተላከ፡መልእክት በእግዚአብሔር፡አብ፡በጌታችን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስም፡አምነው፡በተሰሎንቄ፡ላሉ፡ምእመናን፡ተደረሰ፨

፪ የአባታችን፡የእግዚአብሔር፡አብ፡የጌታችን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሰላምና፡ጸጋ፡ለእናንተ፡ይሁን፨፩ቆሮ፡፩፡፫ ቆላ፡፩፡፪፨

፫ ወንድሞቻችን፡እንደሚገባው፡ለእናንተ፡እግዚአብሔርን፡ሁልጊዜ፡ልናመሰግን ይገባል፨ሃይማኖታችሁ፡በፍ ታለች፡ከባልንጀሮቻችሁም፡ሁሉ፡ንሩ፡ፍቅራችሁ፡በዝቶአልና፨ምሳ፡፲፡፲፪፡፩ተሰ፡፩፡፲፫፨

፬ ስለ፡ሃይማኖታችሁ፡ታጋሣችሁ፡ታማሣችሁም፡ስለምትቀበሉት፡መከራችሁና፡ጭንቀታችሁ፡በእግዚአብሔር፡ባመኑ፡ምእመናን፡ፊት፡እኛ፡እንመካባችሁ፡ዘንድ፨፪ቆሮ፡፯፡፲፬፨

፭ የእግዚአብሔር፡እውነተኛ፡ፍርዱን፡ተገልጦ፡ዘንድ፡፡ መከራ፡የምትቀበሉት፡መንግሥቱን፡ያወርሳችሁ፡ዘንድ፨ሮሜ፡፩፡፲፫፡ሉቃ፡፳፩፡፲፱

፮ ፨መከራ፡የሚያጸኑባችሁ፡ሰዎችስ፡በእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ብድራቸውን፡ሊቀበሉ፡ይገባልና፨ራእ፡፲፫፡፯፡

፯ ፨መከራ፡ለምትቀበሉ፡ለናንተ፡ግን፡ከኛ፡ጋራ፡ዕረፍት፡ይገባችኋል፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ኃይሉን፡ከሚገልጥባቸው፡መላእክቱ፡ጋራ፡ከሰማይ፡በመጣ፡ጊዜ፨ማቴ፡፲፫፡፴፱፨

፰ እግዚአብሔርን፡የሚያውቁ፡የጌታችን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡የወንጌሉን፡ትምህርት፡የማይሰሙ፡ሰዎች፡ሲያቃጥል፡በሚነድ፡እሳት፡ይበቀላቸው፡

፱ ዘንድ፨ብድራቸውንም፡የጥፋት፡ፍርድ፡ይቀበላሉ፨ከጌታችን፡ፊት፡መራቅና፡በክሃሌ ነቱ፡ከሚያወርሰው፡ክብር፡የዘለዓለም፡መነቀል፡ያገኛቸዋል፨ኢሳ፡

፲ ፪፡፲፡፲፱፨በመላእክትና፡በሚያምኑበት፡በምእመናን፡ቃል፡እየተመሰገነ፡በመጣ፡ጊዜ፡ምስ

፬ ስለ፡ሃይማኖታችሁ፡ታማሣችሁ፡

ክርነቷቸን፡በዚያች፡ቀን፡በና
ኝቱ፡ሳይ፡ይረጸልናልና፦ዋሳ፫
፲፩ ፬፦ስለዚህም፡ስለናንተ፡ሁል
ጊዜ፡እጸልያለሁ፡እግዚአብ
ሔር፡እናንተን፡የጠራለት፡ክብ
ር፡ያድላችሁ፡ዘንድ፡ይቅርታ
ውንም፡ሁሉ፡ከሃሊነቱንም፡እ
ምዋ፡የሚሠራውን፡ሥራ፡ይ
ፈጽምላችሁ፡ዘንድ፦፩ተሰ፩፪
፲፪ የጌታችን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስ
ስም፡በናንተ፡ሳይ፡እንዲመሰግ
ን፦እናንተም፡በሱ፡እንድትመሰ
ገኑ፡እንደ፡ጌታችን፡እንደ፡ኢየሱ
ስ፡ክርስቶስ፡ቸርነት፦እናንተም
ከሱ፡ጋራ፡ትምሩ፡ዘንድ፦

ምዕራፍ፪፡ክፍል፡፪።

ምጽአት፡እንደ፡ደረሰ፡ቢነግሯችሁ፡አትደ
ንግጡ፡ብሎ፡እንደ፡ነገራቸው፦የምጽአት
ምልክቱ፡አስቀድሞ፡የሐሳዊ፡መሲሕ፡
መምጣት፡እንደሆነ።

፩ ወንድሞቻችን፡የጌታችን፡የኢ
የሱስ፡ክርስቶስን፡የመምጣቱን፡
ነገር፡እንነግራችኋለን፡በሱ፡አ
፪ ንድነት፡ያላችሁ፡ናችሁ። ምጽ
አት፡እንደ፡ደረሰ፡አድርገው፡እን
ዳያስደነግጧችሁ፡ዕወቁ፦ከዕ
ውቀትም፡አትነዋወጡ፡በልቡ
ና፡በቃልም፡ቢሆን፡በመጽሐፍ
ም፡ቢሆን፡ጌታችን፡የሚመጣበ
ት፡ቀን፡በኛ፡ጊዜ፡እንደ፡ሆነች፡አ
፫ ታስቡ፦ጥፋት፡የሚገባው፡ኃጢ
ተኛ፡የሚሠራ፡የሚያስክዱ
ሰው፡አስቀድሞ፡ካልተገለጠ፡
በማናቸውም፡የሚያስታች
ሁ፡አይኑር፦፩፡ጢሞ፡፬፡፩፡፩፡ዮ
ሐ፡፪፡፲፰፡፲፡፬፡፫፦እውነትን፡የ
ሚለውጥ፡አሰተኛ፡ራሱን፡የሚ
ያበልጥ፡ለሁሉ፡አምላክ፡የም
ሆን፡እግዚአብሔር፡እኔ፡ነኝ፡ይ
ላል፡በእግዚአብሔር፡ቤት፡ተ
ቀምጦ፡ራሱን፡እንደ፡እግዚአ
ብሔር፡ያደርጋል፦ዳን፡፲፩፡፴፮።
፭ ከናንተ፡ዘንድ፡በነበርሁ፡ጊዜ፡
አስቀድሜ፡ይህን፡እንደ፡ነገር
፮ ኋችሁ፡አታስቡምን፤ዛሬም፡
ከመታየት፡የሚከለክለውን፡ጊ
ዜው፡እስኪደርስ፡እንዲሆን፡ታ
፯ ውቃላችሁ፦የኃጢአት፡ትም
ርት፡ተንኮል፡ፈጽሞ፡በሱ፡ይደ
ረጋልና፡ዛሬ፡ግን፡ከመታየት፡
ተገቷል፡በመካከል፡እስኪገ
ለጥ፡ድረስ፡ዮሐ፡፳፡፳፱፦
፰ የክርስቶስ፡ሥልጣን፡ያጠፋው
ዘንድ፡ያለው፡በዓመፅ፡የተወ
ለደ፡ሐሳዊ፡መሲሕ፡ያንጊዜ፡ይ
ገለጣል፡ክርስቶስ፡መምጫ፡በመ
ገለጡም፡ያስረዋል፦ኢሳ፡፲፩፡፬
፱ ራእ፡፲፱፡፲፭፡፳፦የዚህ፡አመጣጡ
ግን፡ሰይጣን፡በሚያደርገው፡ኃ
ይል፡ሐሰት፡በሚሆን፡ብዙ፡ተአ
ምራትና፡ብዙ፡ምልክት፡ነው።
ማቴ፡፳፬፡፳፬።

፲ ያሳመኑትን፡በሚያቱበት፡በብዙ፡ኃጢአት፡ነው፡በሚድኑ ገንዘብ፡የእውነተኛውን፡የፍቅር፡ተእዛዝ፡አልተቀበሉምና። ፪ቆሮ፡፪፡፲፭፡ና፡፬፡፫።

፲፩ ስለዚህም፡በሐሰት፡ያምኑ፡ዘንድ፡የሚያስተውን፡ተአምራት፡እግዚአብሔር፡ያዝዝ

፲፪ ባቸዋል። ሮሜ፡፩፡፳፬። በእውነት፡የማያምኑ፡በክህደትም የሚተባበሩ፡ሁሉ፡ይፈረድባቸው፡ዘንድ። ሐዝ፡፳፡፳፬።

፲፫ ወንድሞቻችን፡እኛ፡ግን፡እግዚአብሔር፡ስለ፡ወደዳችሁ፡ስለናንተ፡እግዚአብሔርን፡ሁሉጊዜ፡ልናመሰግነው፡ይገባልናል፤የሐይወት፡ባሰቤት፡እግዚአብሔር፡በዕውነተኛው፡ሃይማኖት፡መርጧችኋል፡በመንፈስ፡ቅዱስም፡በሚገኝ፡ቅዱስና፡ይቀር፡ብሏችኋልና።

፲፬ ፩፡፫፡፬፡ኤፌ፡፩፡፬። የጌታችን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ክብር፡ተወርሱ፡ዘንድ፡በወንጌልት

፲፭ ምህርት፡ስለ፡ጠራችሁ። እሁንም፡ወንድሞቻችን፡ጽኑ፡በኛ ቃል፡የወራሳችሁን፡ሥራት፡በኛ፡መጽሐፍም፡ያስተማራችሁን፡ትምርት፡ጠብቁ። ም

፲፮ ፫፡፯። እሱ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡የወደደን፡የዘላለም፡ደስታን፡ዕውነተኛውንም፡ተስፋ፡የሰጠን፡አባታችን፡እ

፲፯ ግዚአብሔርም፤ በጸጋው፡እሱ፡ልባችሁ፡ደስ፡ያሰኛችሁ፤ በበጎ፡ምግባርን፡በበጎ ነገር፡ሁሉ፡ያጽናሳችሁ። ፩ተሰ፡፫፡፲፫ ፨ ምዕራፍ፡፫፨

ክፍል፡፫ ።

የማኅበር፡ጸሎት፡አንዲጠቀም፡ለማስረዳት፡ሲል፡ከክፉ፡ሰዎች፡እንድን፡ዘንድ፡ጸልዩልን፡ብሎ፡እንደ፡ተናገረ—

፩ እሁንም፡ወንድሞቻችን፡የእግዚአብሔር፡ቃል፡ከናንተ፡ዘንድ፡እንደ፡ደረሰ፡ከሁሉ፡ደርሶ፡ይገሰጥ፡ዘንድ፡ስምኑል

፪ ኝ። ቈላ፡፬፡፫። ከክፉዎቹና፡ከመፀኞቹ፡ሰዎች፡እንድን፡ዘንድ፡ሁሉ፡በእግዚአብሔር፡ያመነ

፫ አይደለምና፤ በሃይማኖት፡የሚያጸናችሁ፡ከክፉውም ሥራ፡ሁሉ፡የሚጠብቃችሁ፡እግዚአብሔር፡የታመነ፡እውነተኛ፡ነው። ፩ቆሮ፡፩፡፱፡ና፡፲፡፲፫

፬ ከእግዚአብሔር፡ታዘዝን፡ያዘዝናችሁን፡ትሠሩ፡ዘንድ፡እናምኛለን፡እውቃችሁም፡ሠርታችኋል። ፪ቆሮ፡፯፡፲፮፡ገላ፡፭፡፲። ወደ፡እግዚአብሔር፡ፍቅር፡ወደ፡ክርስቶስም፡ተስፋጌታችን፡ልቡናችሁን፡ያቅናው

፮ ክፍል፡ ፬። ወንድሞቻችን፡ በሠራኛላቸው፡ሥራት፡ያደረ በተንከባለም፡ምንንድ፡የሚ ሒዱትን፡ሰዎች፡ሁሉ፡ተለዩ አቸው፡ብለን፡በጌታችን፡በኢ የሱስ፡ክርስቶስ፡ስም፡እናዝለ ቸኋለን። ማቴ፡፲፰፡፲፯፡ቲቶ፡፫ ፲፡ሮሜ፡፲፮፡፲፯።

፯ እኛን፡ተመስሉን፡ዘንድ፡እንደ ሚገባ፡እናንተ፡ታውቃላችሁ፡ለ ንን ዘባችሁ፡እንደልሳሳን፡መ

፰ ጠንቆሥራ፡ሰንሠራ፡የሌላውን እህል፡አልበላንምና፡እናንተ ን፡እንደናስቸግር፡ሌትና፡ቀን ሥራ፡እየሠራን፡እንደከማለ

፱ ን፡እንጂ። ፩ቆ፡፬፡፲፪ ። ለኛ፡የማ ይገባን፡ሆኖ፡አይደለም፡እና ንተ፡ተመስሉን፡ዘንድ፡ምሳሌ እንድንሆናችሁ፡ነው፡እንጂ።

፲ ማቴ፡፲፡፲፡ ፩፡ቆሮ፡፬፡፲፪። ከናን ቱ ምን፡ዘንድ፡በነበርሁ፡ጊዜ፡ይ ህን፡አዘዝኋችሁ፡ሥራ፡መሥ ራት፡የማይወድ፡እንደይበላት

፲፩ ዘፍ፡፫፡፲፯። ከናንተ፡ወገን፡ሥ ራ፡የሌላቸው፡በስንፍና፡የሚ ኖሩ፡ሰዎች፡እንደሉ፡ሰምተና ል፡ዘዋሪዎች፡ናቸው፡እንጂ

፲፪ እንደዚህ፡ያሉትን፡በጌታችን በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስም፡እና ዝዛቸዋለን፡እየመከራቸዋ ለን፡በቀንነትና፡በጸጥታ፡ሥ ራ፡እየሠሩ፡ምላባቸውን፡ይ መግቡ፡ዘንድ። ፩ተሰ፡፬፡፲፩።

፲፫ እናንተ፡ግን፡ወንድሞቻችን፡ ሁሉጊዜ፡በጎ፡ሥራ፡መሥራትን

፲፬ ቸል፡አትበሉ። ገላ፡፮፡፱። ለቃ ላችሁ፡ለመጽሐፋችሁ፡የማ ይታዘዝ፡ሰው፡ቢኖር፡ያፍር ዘንድ፡ይለይ፡እንጂ፡አትግና ኙ። ማቴ፡፲፰፡፲፯፡፩ቆሮ፡፭፡፱፡፲፩

፲፭ ነገር፡ግን፡እንደ፡ጠላት፡አታድ ርጉት፡ወንድማችሁ፡እንደ፡መ ሆኑ፡ምከሩት፡እንጂ። ማቴ፲፰

፲፮ ፲፭። የሰላም፡አምላክ፡እግዚአ ብሔር፡በሥራው፡ሁሉ፡ሁለጊ ዜ፡ሰላሙን፡ይስጣችሁ፡ጌታች ን፡ምን፡ከሁላችሁ፡ጋራ፡ይኑር። ሮ

፲፯ ሜ፡፲፭፡፴፫፡ና፡፲፯፡፳። ይህን፡ሰ ላምታ፡እኔ፡ጳውሎስ፡በጂ፡ጻፍ ሁ፡በምጽፈው፡መጽሐፍ፡ሁሉ ምልክቱ፡ይህ፡ነው፡እንዲህ፡እ ጽፋለሁ። ፩ቆሮ፡፲፯፡፳፩።

፲፰ የጌታችን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ጸጋ፡ከናንተ፡ጋራ፡ይሁን። ፮፡ጢ

፲፱ ሞ፡፬፡፳፪። በሎዶቅያ፡የተጻፈ በጢኪቆስ፡እጅ፡ወደ፡ተሰሎን ቄ፡ሰዎች፡የተላከ፡ሁለተኛ፡መ ልእክት፡ተፈጸመ። ለስጀምሮ ላስጨረሰኝ፡ለእግዚአብሔር ክብር፡ምስጋና፡ይግባው።

በውነቱ፡ያስሐስቲ

በአቴና፡ የተጻፈ፡ ወደ፡ ጢሞቴ
ዎስ፡ የተላከ፡ መጀመርያ፡ መል
እክት፡ ይህ፡ ነው። ምዕራፍ ፩
ክፍል፡ ፩።

የጢሞቴዎስን፡ ደግነቱን፡ ለይቶ፡ ለግ
ዱ፡ ለሰከተለው፡ በኤፌሶን፡ ኤጲስ፡ ቆጶ
ስነቱን፡ አገደ፡ ሾመው።

፩ በመድኃኒታችን፡ በእግዚአብ
ሔር፡ በተስፋችንም፡ በኢየሱስክ
ርስቶስ፡ ትእዛዝ፡ የኢየሱስ፡ ክ
ርስቶስ፡ ሐዋርያው፡ ከምሆን፡
ከጳውሎስ፡ የተላከ፡ መልእክት
፪ ቆሳ፡ ፩፡ ፳፯። በሃይማኖት፡ ለም
ወደው፡ ልጄ፡ ለጢሞቴዎስ፡ ትድ
ረስ፡ ከአባታችን፡ ከእግዚአብሔ
ር፡ ከጌታችን፡ ከኢየሱስ፡ ክርስቶ
ስም፡ ሰላምና፡ ጸጋ፡ ይቅርታም
፫ ላንተ፡ ይሁን። ቲቶ፡ ፩፡ ፬። ወደመ
ቄዶንያ፡ በሔድሁ፡ ጊዜ፡ በኤፌሶ
ን፡ ተቀምጠህ፡ ዘንድ፡ ማለድሁህ፡ ሌላ
ትምርት፡ እንዳያስጠኑ፡ ትገሥ
ፃቸው፡ ዘንድ። የሐዋ፡ ፳፡ ፩።
፬ ለውን፡ ያስቱ፡ ዘንድ፡ ፈጥረው
የሚነግሩትን፡ ተረትና፡ ጨዋ
ታ፡ እንዳያደምጡ፡ የታመነ፡ የእ
ግዚአብሔርን፡ ሕግ፡ ትተው፡ ክ
ርክርን፡ ያመጣሉና። ም፡ ፬፡ ፯።
፭ የትእዛዝ፡ ፍጻሜ፡ ግን፡ በቅን፡
ልብ፡ መፋቀር፡ ነው፡ በበጎ፡ ሥራ

ጥርጥር፡ በሌለበትም፡ ሃይማ
ኖት፡ መጽናት፡ ነው። ሮሜ፡ ፲፫
፮ ፰፡ ፲። ከዚህ፡ ወጥተው፡ ወደ፡ ከ
ንቱ፡ ነገር፡ የተመለሱ፡ አሉና።
፯ ም፡ ፯፡ ፬፡ ፭። መምሕራንም፡ ሊ
ሆኑ፡ ሲወዱ፡ የሚናገሩትን፡ አ
ያውቁም። ዋሐ፡ ፫፡ ፲፡ ም፡ ፮፡ ፬፡ ፳
፰ ትእዛዙን፡ ለሚፈጽመው፡ ኦሪ
ት፡ በጎ፡ ሕግ፡ እንደሆነ፡ እናውቃ
፱ ለን። ሮሜ፡ ፯፡ ፲፪። ይህንም፡ እ
ናውቃለን፡ ሕግ፡ የሚሠራ፡ ለ
ጻድቃን፡ እንደይደለ፡ ለኃጢአ
ተኞችና፡ ለከዳተኞች። ኃጢ
አት፡ ለሚያዘወትሩና፡ ከጽድ
ቅ፡ ለወጡ፡ ለቡናቸውም፡ ለከ
ፉ፡ እናት፡ አባታቸውንና፡ እያቆ
ቻቸውንም፡ ለማይረዱ፡ ነፍስ
፲ ለሚገድሉ፡ ነው። እንጂ። ለሴሰ
ኞችና፡ ወደሰው፡ ሚስት፡ ለሚ
ሔዱ፡ የሰውን፡ ገንዘብ፡ ለሚ
ሠርቁና፡ ሐሰት፡ ለሚናገሩ፡ በ
ሐሰትም፡ ለሚምሉ፡ ነው፡ ነው
እንጂ። ዘፀ ፳፩፡ ፲፪፡ ም፡ ፯፡ ፲፯፡
፲፩ እኔ፡ ያመንሁበት፡ የክቡር፡ የእ
ግዚአብሔርን፡ ጌትነት፡ በሚ
ናገር፡ በወንጌል፡ የሚገኘውን
የሕይወት፡ ትምህርት፡ በሚቃ
ወሙ፡ ሰዎች። ደማሞ፡ የተሠራ
ሌላ፡ ሕግ፡ አለ። ም፡ ፯፡ ፲፰።
፲፪ የተማመነኝ፡ በጌታችን፡ በኢየ
ሱስ፡ ክርስቶስም፡ ያደናኝ፡ እግዚ

አብሔርኝ፡ አመሰግነዋለሁ፡
ሐጉኝ፡ ለማስተማር፡ የቃመኘሁ
አድርጎኛልና፡ የሐ፡ ፱፡ ፲፭፡ ገላ ፩
፲፫ ፲፭። እኔ፡ ቀድሞ፡ አሱኝ፡ የምሰድ
ብ፡ ሐጉኝም፡ የምነቀፍ፡ ያመኑ
በተኝም፡ የማባርር፡ ስሆኝ፡ ነገ
ር፡ ግን፡ ይቀር፡ አለኝ፡ ሳላምን፡ ባ
፲፬ ለማወቅ፡ አድርጌው፡ ነበርና፡ የ
እግዚአብሔር፡ ጸጋው፡ በኔ፡ ላይ
በዛ፡ የጌታችን፡ የኢየሱስ፡ ክርስ
ቶስም፡ ሃይማኖት፡ ፍቅሩም፡
በኔ፡ ጸና፡ ነገሩ፡ የታመነ፡ ነው።
፲፭ በሁሉም፡ ሊቀበሉት፡ ይገባል፡
ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ እኔ፡ መጀመ
ሪያቸው፡ የምሆን፡ ኃጥአንን፡
ያድናቸው፡ ዘንድ፡ ወደዚህ፡ ዓ
ለም፡ መጥቷልና፡ ማቴ፡ ፲፰፡ ፲፩
፲፮ ነገር፡ ግን፡ ይቀር፡ አለኝ፡ ኢየሱ
ስ፡ ክርስቶስ፡ ቃምራቱኝ፡ የተዐ
ግሥቱንም፡ ብዛት፡ በኔ፡ ላይ፡ ይ
ገልጥ፡ ዘንድ፡ የዘላለምን፡ ሕይ
ወት፡ ለማግኘት፡ ለሚያምኑበ
ት፡ ሰዎች፡ ምሳሌ፡ አሆኞ ቸው
፲፯ ዘንድ፡ የማይሞት፡ የማይታ
ይ፡ የዘለዓለም፡ ንጉሥ፡ አሱ፡ ነው፡
የዘለዓለም፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ግ
ኘዘቡ፡ የሚሆኝ፡ አምላክ፡ አሱ
፲፰ ብቻ፡ ነው፡ በውነት፡ ሎጁ፡ ጢሞ
ቴዎስ፡ ይህን፡ ትእዛዝ፡ አደራ፡ ሰ
ጥቼሃለሁ፡ ባንተ፡ ላይ፡ እንደ፡ ተ
ነገረው፡ ትንቢት፡ በበጎ፡ ገድል፡

ሁሉ፡ ትፀና፡ ዘንድ፥ ም፡ ፪፡ ፲፪።
፲፱ በሃይማኖትና፡ በበጎ፡ ግብር፡ ሁ
ነህ፡ ከሃይማኖት፡ ወጥተው፡ ድ
ል፡ የተነሡ፡ አሉና፡ ም፡ ፫፡ ፱።
፳ እነዚህም፡ ዲማሞ፡ እኝደ ይሰደ
ቡ፡ መከራ፡ ይቀበሉ፡ ዘንድ፡ ለሰ
ይጣን፡ አሳልፌ፡ የሰጠኋቸው
ሔሜኔዎስና፡ አሌ፡ እስክንድሮ
ስ፡ ናቸው። ፪፡ ጢሞ፡ ፪፡ ፲፯፡ ፩ቆሮ
፭፡ ፭። ምዕራፍ ፪። ክፍል፡ ፬
ከሥራ፡ ሁሉ፡ አስቀድሞ፡ መጸለይ፡ እንደ፡ ቃ
ዘዘ፡ ለነገሥታትም፡ መጸለይ፡ እንዲገባ
ለሌቆቹ፡ ጊጣቸው፡ ለምልክት፡ ለግዚአብሔር
ኝም፡ መያዝ፡ ነው፡ አኘጂ፡ ሹርባ፡ መሠራቱ
ብቻ፡ እንዳይደለ . . .
፩ ከሁሉ፡ አስቀድሞ፡ ጸሎትና፡
ልመናን፡ ምስጋናን፡ ቃጸርማ፡ ዘ
ንድ፡ እማልድሃለሁ፤ ፊል፡ ፬፡ ፮፡
፪ ስለዚህም፡ ለሰው፡ ሁሉ፡ ጸልዩ፡ ለ
ነገሥታቱ፡ ለመኳንንቱም፡ ሁሉ
ኑሮአችኝ፡ በጸጥታና፡ በሰላም፡ ይ
ሆን፡ ዘንድ፡ በጽድቅና፡ በንጽሕና
፫ ይሆን፡ ዘንድ፡ በመድኃኒታችን፡
በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ የተወደ
፬ ደ፡ የተመረጠ፡ ይህ፡ ነው፡ ሰዎች
ሁሉ፡ ይድኑ፡ ዘንድ፡ ጽድቅንም፡
ያውቁ፡ ዘንድ፡ እሱ፡ ይወዳል
ና፤ ሕዝ ፲፰፡ ፳፫፡ ፪ጴጥ፡ ፫፡ ፱።
፭ እግዚአብሔር፡ አብ፡ አንድ፡ ነው፡
ሰው፡ ሆኖ፡ በእግዚአብሔር፡ና በ
ሰው፡ መካከል፡ የተመረጠ፡ ኢየሱ

ሉ፡ ክርስቶስም፡ አንድ፡ ነው፤ ኢሳ
ያ ፶፫፡፭-፮፡ ፩ጴጥ ፪፡፳፬፡ ዮሐ፡ ፲፯፡፲፱፡ ዕብ
፲፬ ፲፬፡ ፳፬ቀ ራሱን፡ ለሁሉ፡ ቤዛ፡ አ
ድርጎ፡ የሰጠ፡ በጊዜው፡ ጊዜ፡ም
ስክር፡ የሆነቅንግሉ፡ ፩፡፬፡ና፡ ፬፡፳፡ ቲ
፲፰ ቶ፡ ፬፡፲፬ ቀ እኔ፡ ዞራ፡ ለማስተማ
ር፡ ሐዋርያነት፡ ለተሾምሁ ለት
አውነት፡ እናገራለሁ፡ አስትም
እልናገርም፡ ስአሕዛብ፡ ሃይማ
ኖትንና፡ ጽድቅን፡ ለማስተማ
ር፡ ተሹሜ አለሁቀየ ሐዋ፡ ፱፡፲፭፡
፲፱ ፳ ጢሞ፡ ፩፡፲፩ቀ ስዎች፡ሁሉ፡በየ
በታው፡ ሁሉ፡ ይጸልዩ፡ዘንድ፡ አ
ወዳለሁ፡ ያለ፡ማንጐራጐርና፡
ያለመጠራጠር፡ በንጽሕና፡ እጃ
፲፱ ቸውን፡ እንዲያነሡቀሴቶችም
እንደዚሁ፡ለጸሎት፡ይዘጋጁ፡ እ
ግዚአብሔርን፡ በመፍራትና፡በ
ውኘ፡ በማፈርቀበማስተዋልና
ራሳቸውን፡ከዝሙት፡በመስየት
የወርቅ፡ድሪ፡አልማዝ፡ቀስበት
ም፡ በማጭረግ፡አይደለምቀዋጋ
ው፡ብዙ፡የሚሆን፡ያማረ፡ልብስ
በመልበስ፡ጠጕራቸውን፡ሹሩ
ባ፡በመሠራት፡አይደለምቀ፩ጴጥ
፲ ፫፡፫፡፫ቀ ለሴቶች፡ በሚገባቸው
ሥራት፡ነው፡እንጂቀአስቀድሞ
በእውነተኛው፡ትእምርትና፡በ
በጎ፡ምግባር፡ እግዚአብሔርን፡
ማገልገል፡ነውቀም፡፫፡፲ቀ
፲፩ ሴቶችም፡ በጸጥታ፡ሁና፡ትማር፡በ
ብዙ፡ቀኖችም፡ተቻዝግዞቀኤፌ
፫፡፳፬ቀ ሴት፡ ቃ ስተምር፡ዝንድ
ላን፡ አናዝትም፡ በወንድ፡ ሰይእ
ንደተሠለጥን፡ በጸጥታና፡በቀን
ነት፡ ትኑር፡ እንጂቀ ፩ቆሮ፡፲፬፡ ፴፬
፲፫ ዘፍ፡ ፪፡፲፰ቀ አዳም፡ቀድሞ፡ተፈ
ጥሯልና፡ከሱም፡በኋላ፡ሔዋን
ተፈጥራለች፡፡ ዘፍ፡ ፩፡፳፯ቀ
፲፬ አዳም፡ አልሰተም፡ሔዋን፡ስተቸ
ት አዘዙንም፡ ተላለፈች፡ እንጂ
፲፭ ዘፍ ፫፡፪፡፬ ቀ ሮ፡፲፩፡፲ ፩ቀ ነገርግን
ን፡ ዘሬ፡ ስሉልጆች ዋ፡ ትድናለች
በሃይማኖትና፡በፍቅር፡በዕው
ቀት፡ሁነው፡ራሳቸውን፡በማን
ጻትና፡በቅድስና፡ቢኖሩቀ ቀ

ምዕራፍ፡ ፫፡፡ ክፍል፡ ፫

ቅስና፡ የሚሾም፡ ሰው፡ የማያጻሳና፡ የ
ሐሚትም ክንያት፡ የሌለበት፡ ሊሆን
እንዲገባ፡

፩ ነገሩ፡ እውነት፡ ነው፡ ጳጳስና፡ ሊ
ቀ ሾም፡ የሚወድ፡መልካም፡ሥራ፡
ወደደቀ የሐዋ፡ ፳፡ ፳፰ቀ
፪ ነገር፡ግን፡ ለሰውሬት፡ የማያደ
ላ፡ ጳጳስነት፡ ሊሾም፡ ይገባዋል
የጎጢአት፡ም ክንያት፡ የሌለበ
ት፡ አንዲት፡ሚስት፡ያገባ፡ የሚ
ተጋ፡ ዕውቀትም፡ ያለው፡ አንዳ
ዲ፡ የሚወድ፡ ሰውነቱን፡ የጸሐ
ያደረገ፡ የሚያስተምር፡ የሚ
ገሥጽ፤ዘሌ፡፳፩፡፲፯፡ ቲቶ፡ ፩፡፮፡፯

፫ ወይን፡ አብዝቶ፡ የማይጠጣ፡ ለመማታት፡ እጁን፡ የማያፋጥን፡ መከሮ፡ የሚጠቅም፡ የማይጣላ ገንዘብ፡ የማይወድ ፨ ዘሌ፡ ፲፰፡ ቲቶ፡ ፩፡ ፯ ፨
፬ የቤቱ፡ ሥራት፡ ያማረ፡ በቅንነት፡ ሁነው፡ የሚታዘዙ፡ ልጆች፡ ያሉት ፨ ፩፡ ሳሙ፡ ፪፡ ፲፪ ፨
፭ የቤቱን፡ ሥራት፡ ማከናወን፡ የማይችል፡ ሰው፡ የእግዚአብሔርን፡ ቤተ ማከናወን፡ እንደምን፡ ይቻለዋል
፮ ከአዲስ፡ ተክል፡ ወገን፡ አይሁን፡ እንዳይታበይ፡ በትዕቢት፡ እንዳይሸፈን፡ በሰይጣንም፡ ወጥመድ፡ እንዳይወድቅ ፨
፯ በአፍአ፡ ያሉ፡ ሰዎች፡ የሚያመሰግኑት፡ ሊሆን፡ ይገባል ፨ በመሰደብ፡ እንዳይወረድ፡ በሰይጣንም፡ ወጥመድ፡ እንዳይያዝ ፨ ም፡ ፰፡ ፲፡ ፩ ቆሮ፡ ፰፡ ፲፩፲፫
፰ ዲያቆናትም፡ እንደዚሁ፡ ከኃጢአት፡ የነጹ፡ ይሁኑ፡ የተወሰኑ፡ ቃላቸው፡ አንድ፡ የሆነ፡ መጠጥ፡ የማያበዙ፡ ከንቱውን፡ ትርፍ፡ የማይወዱ፡ ይሁኑ ፨ ፩፡ ፩ የሐዋ፡ ፮፡ ፫ ፨
፱ የሃይማኖታቸውን፡ ምሥጢር፡ በንጹሕ፡ ልቡና፡ የጠበቁ፡ ይሁኑ፡
፲ እሊህንም፡ አስቀድመው፡ ይፍትኑዋቸው ፨ ከዚያ፡ በኋላ፡ ነውር፡ የሌለባቸው፡ ከሆኑ፡ ያገልግሉ ፨
፲፩ ሴቶችም፡ እንደዚሁ፡ ሰውነታቸውን፡ ከኃጢአት፡ ንጹሕ፡ ያደረጉ፡ የቤት፡ ክርስቲያንን፡ ሥራት፡ የተማሩ፡ ሰውን፡ የማያጣሉ ዕውቀትና፡ ቅንነት፡ ያላቸው፡ በሁሉ፡ የታመኑ፡ ቢሆኑ፡ ያገልግሉ ፨ ቲቶ፡ ፪፡ ፫ ፨
፲፪ ዲቁናም፡ የሚሾም፡ አንዲት፡ ሚስት፡ ያግባ፡ ልጆች፡ ያሉት፡ የቤቱ፡ ሥራት፡ ያማረ፡ ይሁን ፨ ፬ ፨
፲፫ በበጎ፡ ማገልገል፡ ለሚያገልግሉ፡ ግን፡ የበለጠውን፡ ሹመት፡ ያድርጉላቸው፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ በማመን፡ ብዙ፡ ክብር፡ አለና ፨ ማቴ፡ ፳፭፡ ፳፩፡ ፩ ዮሐ፡ ፫፡ ፳፩ ፨
፲፬ ይህንም፡ የጻፍሁልህ፡ ፈጥኜ፡ ወደ፡ አንተ፡ እንድመጣ፡ ተስፋ፡ አደርጋለሁ ፨
፲፭ ብዘገይ፡ ግን፡ የሕያው፡ የእግዚአብሔር፡ ማደርያ፡ የምትሆን፡ የቤተ፡ ክርስቲያን፡ ሥራት፡ እንዴት፡ እንዲገባ፡ ታውቅ፡ ዘንድ፡ ነው ፨ የጽድቅ፡ ዓምድ፡ መሠረት፡ የምትሆን ፨ ፪ ጢሞ፡ ፪፡ ፳ ፨
፲፮ የዚህም፡ የጽድቅ ምሥጢሩ፡ ጽኑ፡ እንደ ሆነ፡ እውነት፡ ነው ፨ ይኸውም፡ ሰው፡ ሁኖ በሥጋ፡ የተገለጠው፡ ነው፡፡ በመንፈስ፡ ቅዱስም፡ ተረዳ፡ ለመላእክትም፡ ታያቸው፡ በአሕዛብም፡ ዘንድ፡ አስተማሩት፡ በዓለም ም፡ ታመነ ፨ በክብርም፡ ዓረገ ፨ ዮሐ፡ ፲፯፡ ፲፡ ሮሜ፡ ፩፡ ፬ ፨

ምዕራፍ፡ ፬

ምዕራፍ ፬።

በኋላ፡ዘመን፡ብዙ፡ሰዎች፡ሃይማኖታቸውን፡እንዲለውጡ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ገልጦ፡እንደ፡ተናገረ።—

፩ በኋላ፡ዘመን፡ብዙ፡ሰዎች፡ሃይማኖታቸውን፡እንዲለውጡ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ገልጦ፡ይናገራል፡የሚያስቱ፡ክፉዎችን፡አጋንንትን፡የሚያጠራጥር፡የሰይጣንን፡ትምርት፡እየተከተሉ፡ማቴ፡፳፬፡፳፬፡፪፡ተሰ፡፪፡፫፡፱፡ ፪ጢሞ፡፫፡፩፡፪ጴጥ፡፫፡፫፡፩ዮሐ፡፪፡፲፰፡ጢሞ፡፫፡፩፡ለ

፪ ይሁ፡፲፰። ሐሰት፡የሚናገሩ፡በሰባቸውም፡የሚናደዱ፡ናቸው።

፫ መጋባት፡ርኩስ፡ነው፡ይላሉ፡ጽድቅን፡የማያውቁ፡እያመሰገኑ፡ይበሉ፡ዘንድ፡እግዚአብሔር፡ለምዕመናን፡የፈጠረውን፡መብል፡ይከለክላሉ፨ ዘፍ፡፱፡፫፡፩ቆሮ፡፲፡

፬ ፴፩። እግዚአብሔር፡የፈጠረው፡ሁሉ፡ንጹሕ፡ነውና፡እያመሰገኑ፡ቢቀበሉት፡የሚናቅ፡የሚጣል፡የለምና፨ ዘፍ፡፩፡፴፩፡የሐዋ፡፲፡፲፭፡

፭ በእግዚአብሔር፡ቃልና፡በጸሎት፡የሚቀደስ፡ስለሆነ።

፮ ይህንን፡ለወንድሞችህ፡አስተምራቸው፡የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡የተመረጥህ፡አገልጋይ፡ትሆናለህ፡የሃይማኖትህን፡ነገር፡የተማርከውንም፡በጎ፡ትምህርት፡እየመገ

፯ ብሃቸው፨ ጢሞ፡፩፡፬፡የተወላ፡የባልቴቶችን፡ተረት፡ጣን፡ተወው፡ራስህንም፡ለጽድቅ፡አስገዝቆም፡፩፡፬፡ና፡፯፡፳፡ጢሞ፡፬፡፲፯፡፳፡፪፡፱፡ቲቶ፡፩፡፲፬፨

፰ ለሥጋ፡መገዛት፡ለጥቂት፡ዘመን፡ይጠቅማል፡ጽድቅ፡ግን፡በሁሉ፡ማደጃ፡ተፈጽማለች፡በዚህ፡ዓለም፡በሚመጣውም፡ዓለም፡የሕይወት፡ተስፋ፡አለባትና፡፯

፱ ፯፨ ነገሩ፡እውነት፡ነው፡በሁሉም፡ሊቀበሉት፡ይገባል፨

፲ ስለዚህ፡እንደክማለን፡እንሰደባለን፡ሰውን፡ሁሉ፡የሚያድነን፡ይልቁንም፡ያመኑትን፡በሚያድን፡ሕያው፡በሚሆን፡እግዚአብሔር፡[illegible]፡፬፡፲፡፲፮፡ኤፌ፡፩፡፫፡

፲፩ ፲፮፡፲፱፨ እንዲህም፡ክርስቶስ፡አስተ

፲፪ ምር፨ ሕፃንነትህን፡የሚንቃቁ፡አይኑር፡በፍቅርና፡በሃይማኖት፡በንጽሕና፡ጸንተህ፡በነገርህ፡በሥራህ፡ለምእመናን፡ምሳሌ፡ሁናቸው፨ ቲቶ፡፪፡፯፡

፲፫ እስክመጣ፡ድረስ፡መጽሐፍ፡በማንበብ፡በማስተማርና፡በመምከር፡በጸሎትም፡ተወስነ

፲፬ ህ፡ኑር፨ ዮሐ፡፭፡፴፱፨ ትንቢት፡ከመናገር፡ጋራ፡ሽማግሌዎች፡እጃቸውን፡ጭነው፡ሹመውህ፡ሹመት፡ጋራ፡የተሰጠህን፡ጸጋ፡አታቃልል፨ ፩፡፲፰፡፪ጢሞ፡፩፡፮፡ሐዋ፡፮፡

፲፭ ፮፨ ይህን፡ተመልከት፡በዚህም፡ኑር፡ፍጹምነትህ፡በሁሉ፡ይታ

፲፭ ወቀ፡ዘኘጅ። መጽሐፍ፣ ስለመ
መልከት፡ራስህኘ፡መርምር፡ሁ
ለጊዜም፡በመመልከት፡ኮርቀ
ደህኘ፡ብታደርግ፡ራስህኘም፡
የሚሰማህኘም፡ታስናድለህ፡
ሮሚ፡፲፩፡፲፬ቀ

ምዕራፍ ፫

ሽማግሌዎችኘ፡መደፈርኘ፡ኃይለ፡ቃል
መናገር፡እኘዳይገባ፡-ልጆች፡የሌሳቸ
ውኘ፡ባልቴቶች፡መርዳት፡እኘዴ፡ታዘዙ—
ሸ

፩ ሽማግሌቹኘ፡አታዋርድ፡ሳባ
ቱህ፡እኘዲምትታዘዝ፡ታዘዝ፡እኘ
ጂ፡ለጉበዝዝቱም፡ለወንድሞ
ችህ፡እኘዲምትታዘዝ፡ታዘዝለ
፪ ቸውቀዘሌ፡፲፱፡፴፪ቀለባልቴቶ
ቹም፡ለናትህ፡እኘዲምትታዘዝ
ለቀኘጃጅትም፡ሌቶቹ፡ለእሳ
ቶችህ፡እኘዲምትታዘዝ፡በኘጽ
ሕና፡ሁኘህ፡ታዘዝቀዮሐ፡፲፱፡፳፯
፫ በውነት፡ባልቴቶቹ፡የሆኑትኘ
፬ አክብራቸውቀቆ፭ቀከነሱ፡ወ
ገኘ፡ልጆ፡የልጆ፡ልጆ፡ያሳቱ፡ባ
ልቴት፡ብቶር፡አስቀድመው
ቤታቸውኘ፡ማዘጋጀት፡ይማሩ
እናት፡አባታቸውኘም፡ይርዱ
ይህ፡በእግዚአብሔር፡ዘኘድ፡የ
፭ ተወደደ፡ነውናቀበእውነት፡ድ
ኃ፡የሆነች፡ብቻዋኘ፡የምትኖ
ር፡ባልቴት፡ግኘ፡ተስፋዋ፡እግ
ዚአብሔር፡ብቻ፡ነውቀበቀኘ
ም፡በሌሊትም፡ጸሎቱኘ፡አዘው
ትራ፡ትለምናለችቀና፡፲፰፡፩፡ሉ
፮ ቃ፡፪፡፴፯ቀከጫወታ፡ገራ፡ተ
ጅሳ፡የምታደርግ፡ግኘ፡በሕይ
ወት፡ሳለች፡የሞተች፡ናት፤ሮ
፯ ሚ፡፰፡፲፫ቀእኘዲደደሉ፡ምክኘ
ያቱም፡እኘዲደረጉ፡እኘዲህ
፰ አስተምርቀም፭፡፲፩ቀለቤቱ፡
የማያስብ፡ግኘ፡እናቱ፡አባቱ
ኘም፡የሚጥል፡ይልቁኘም፡ሃ
ይማኖት፡ካላቸው፡ሰዎች፡ወ
ገኘ፡ቢሆኑቀእሱ፡እነሆ፡ሃይማ
ኖቱኘ፡ካደ፡ከማያምነውም፡
ሰው፡ይከፋልቀገላ፡፪፡፲፡፬ ጢ
፱ ሞ፡፪፡፭ቀባልቴቱኘም፡ልትሾ
ም፡ብትመርዋ፡ስሳ፡ዘመኘ፡የ
ሆናትኘ፡አኘድ፡ባል፡አግብታ፡
፲ የኖረችውኘ፡ምረዋቀበበጎው
ሥራ፡ሁሉ፡የሚያመሰግኗት
ልጆቿኘ፡በመልካም፡ብታሳ
ድግ፡እኘግዲም፡ብትቀበል፡የ
ቅዱሳኘኘ፡እግር፡ብታጥብ፡የተ
ራበውኘም፡ብታጠግብቀበጎ
ውኘ፡ሥራ፡ሁሉ፡ብትከተል፡
፲፩ ዕብ፲፫፡፪ቀከባል፡የተለዩቱ፡
ቆነጃጅቶቹኘ፡ግኘ፡ራቃቸው፡
አትሹማቸው፡በክርስቶስ፡ላ
ይ፡ሲሳ፡ተድላ፡እኘዲደርጉ፡
ወደ፡ማግባት፡ሲመለሱ፡ይወ
፲፪ ዳሉናቀየቀደመች፡ሃይማኖ
ታቸውኘም፡ቢክዱ፡ፍርድ፡

፲፫ ይጠብቃቸል፡፡ ደጋግሞም፡ ቤ
ቱ፡ ለቤቱ፡ እየዞሩ፡ ሥራ፡ መፍ
ታትን፡ ሐኬትን፡ ይማራሉ፡
ሥራ፡ መፍታትን፡ ብቻ፡ ይማ
ሩ፡ ዘንድ፡ አይደለም፡ ነገርኛ
ኞቹ፡ ሥራን፡ ደጋግሞ፡ ያበዙ
ዘንድ፡ ነው፡ እንጂ፡ ያልሆነው
ን፡ ነገር፡ ፈጥረው፡ ይናገራሉ
፲፬ ም፡ ፯፡ (፲፭) እንግዲህ፡ ቆነጃጅ
ቶች፡ ሴቶች፡ ባል፡ ሊያገቡ፡ ልጅ
ም፡ ሊወልዱ፡ በሰበቶቻቸውም፡ ሊ
ሆኑ፡ እወዳለሁ፥ ጠላታችው
ሰይጣን፡ በሚዋጋቸው፡ ገንዘ
ብ፡ ለንዱ፡ ስንኳ፡ ምክንያት፡ እ
ንዳያገኝ፡ ራሳቸውን፡ እንዲያ
፲፭ ስነቅፉ፥ ተመልሰው፡ ሰይጣ
ንን፡ የተከተሉ፡ (አሉና፥
፲፮ ም፡ ፩፡ ፪፥ ከምእመናን፡ ወገን
ባልቴቶች፡ እናቶች፡ ያሉቸው፡ ቢኖ
ር፡ ይርዷቸው፡ ቤተ፡ ክርስቲያን
ን፡ እያስቸግር፡ በእውነት፡ ረ
ዳት፡ የሌላቸውን፡ መርዳት፡ ት
፲፯ ችል፡ ዘንድ፥ በመልካም፡ ሥራ
ሳንሰንሉ፡ እጅፍ፡ ክብር፡ ይገባ
ቸዋል፡ ይልቁንም፡ በመምክ
ር፡ በማስተማር፡ ለደከሙ፥
፲፰ ሮሚ፡ (፲፪፡ ፲፫፡ ና (፲፭፡ ፳፯፥ መጽ
ሐፍ፡ እህልህን፡ በምታሔድ፡ ጊ
ዜ፡ የሳመውን፡ አፍ፡ አትሠረው፡
ለሚያገለግልም፡ ዋጋው፡ ይገ
ባዋል፡ ብሏልና፥ዳግ፡ ፳፭፡ ፬፡ ፩ቆሮ

፱፡ ፱፡ ሉ፲፡ ፯፥ በሽማግሌም፡ ላ
ይ፡ ነገረ፡ ሠሪ፡ አትስማበት፡ ሁ
ለት፡ ሶስት፡ ምስክር፡ ሰይመሰ
፳ ክርበት፡ ዮሐ፰፡ (፯፥ ሐጋ፡ ያፈ
ረሱትንም፡ በሁሉ፡ ፊት፡ ገሥፃ
ቸው፡ ሌላው፡ ይፈራ፡ ዘንድ፥ ሌ
፳፩ ፊ (፲፱፡ (፲፫፥ በእግዚአብሔር፡ በጌ
ታችን፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ በተ
መረጡ፡ በመላእክት፡ ፊት፡ አደ
ኛብሃለሁ፡ ሳታደላ፡ ይህን፡ ትእ
ዛዝ፡ ተጠብቅ፡ ዘንድ፡ ከምስክ
ር፡ በፊት፡ ሰውን፡ አውነተኛ፡ ነው
ኣተበለው፡ የምትነቅፍበትን
፳፪ ም፡ ምንግምን፡ አትሥራ፥ ማንኛ
ም፡ ማነን፡ ፈጥነህ፡ አትሹም፡
በዚህ፡ ሌላ፡ በሠራው፡ ኃጢአት
አንድ፡ እንዳትሆን፡ እንግዲህ፡
ራስህን፡ ንጹሕ፡ አድርግ፥የሐ፪
፳፫ ፯፥ብቻ፡ ውኃ፡ አትጠጣ፡ ጥቂ
ት፡ ወይን፡ ጠጅ፡ ምርበት፡ እንጂ
ስለ፡ ሆድህ፡ ሕመም፡ ስለ፡ ዘወ
ትርም፡ ደዌህ፥መዝ፡ ፻፬፡ (፲፭፥
፳፬ ኃጢአቱ፡ የሚታወቅበት፡ ሰ
ው፤ አለ፡ ወደ፡ ፍርድ፡ የሚቀደ
ደመው፡ የሚከታተለውም፡
፳፭ አለ፡፡ በጎ፡ የሚሠራም፡ እንዲህ
ይታወቃል፡ ሥራውም፡ ልዩ፡ የሆ
ኑ፡ ሁሉ፡ ለይሠወርም፤ ገላ፡ ፭፡ ፳፪

ምዕራፍ፡ ፮ ።

ደገኛው፡ሥራችን፡እግዚአብሔርን፡
መፍራት፡እንደሆነ፡በብዙ፡ሲከብሩ
ና፡ሲበለጽጉ፡የሚኖሩ፡ሰዎች፡በመከራ
ላይ፡እንዲወድቁ። ።

፩ ቤተ፡ሰብና፡ተገዢ፡በሥራው፡ሁ
ሉ፡ጌቶቻቸውን፡አክብሩ፡የእግ
ዚአብሔርን፡ስም፡ትምርቱ
ንም፡እንዳይነቀፉ፤ቆሎሴ፡፫፡፳፪
፪ ቲቶ፡፪፡፱፤ያመኑ፡ጌቶች፡ያሏ
ቸው፡ባሮችም፡አይናቋቸው
በሃይማኖት፡ወንድሞቻቸው
ስለሆኑ፡ይልቁንም፡የታመኑ
ወዳጆቻቸው፡ናቸው፡ና፡ይገዙ
ላቸው፡እንጂ፡የጌቶቻቸውን
ትእዛዝ፡ይቀበሉ፡ደስ፡ብሏቸ
ው፡ያገልግሏቸው፡እንዲህ፡ም
ክር፡አስተምር፡ማልዳቸው፡
፫ ም፡፩፡፲፬፤ሌላ፡ትምርት፡የሚ
ያስተምር፡የሕይወትን፡ትም
ርት፡ወደ፡ማስተማር፡ይኸው
ም፡የጌታችን፡የኢየሱስ፡ክር
ስቶስ፡ቃል፡ነው፡የእግዚአብ
ሔርንም፡የውነተኛ፡ሐሳ፡ወ
ደ፡ማስተማር፡የማይመለስ፡
ሰው፡ቢኖር፤፪ጢሞ፡፩፡፲፫፡ገ
፬ ላ፡፩፡፮፡፱፤የሚያውቀው፡ሳይ
ኖር፡የሚታበይ፡እሱ፡ነው፡መ
ቀሠፍቱን፡የክርክርንም፡ነገር
ይሻል፡እንጂ፤ምቀኝነትን፡መ
ቃናት፡ስድብና፡ክፉ፡ምክር፡ሰ
ውን፡መጣላት፡የሚመጣበት

፭ ክፉፉቁ፡ወጥተው፡ፉል፡የተ
ነሡ፡የእግዚአብሔርን፡ሐሳ
መናገድ፡የሚያደርጉ፡አሲያ
፮ ን፡ተስያቸው፤ለኛ፡ስ፡ደገኛው
ሥራችን፡እግዚአብሔርን፡መ
ፍራት፡ነው፤ፊል፡፬፡፲፩፡፲፪፡ም፩
፯ ፳፤ወደዚህ፡ዓለም፡ያመጣነው
ከዚህም፡ዓለም፡ይዘነው፡የም
ንሔድ፡የለምና፤መክ፡፭፡፲፭፤
፰ ምግባችንን፡ልብሳችንን፡ካገ
ኘን፡ይበቃናል፤ዘፍ፡፳፰፡፳፡ም
፱ ሳ፡፴፡፰፤ባለጠጋነትን፡የሚወ
ዱ፡ግን፡ወደ፡ፈተና፡ይወድቃሉ
ሰውን፡የሚጎዳ፡በሞትና፡በጥ
ፋት፡የሚያሰጥም፡ሰንፍና፡የ
ሚሆን፡ፈቃድ፡ባመጣው፡ብዙ
ወጥመድ፡ይያዛሉ፤ምሳ፡፳፰፡
፲ ፳፡ና፳፰፡፳፪፤የክፋት፡ሁሉ
ሥር፡ገንዘብ፡መውደድ፡ነውና፡
ይህን፡በመውደድ፡ከሐማ፡የወጡ
ሃይማኖታቸውንም፡የሰወጡ·
ብዙ፡ናቸው፡ራሳቸውን፡በመ
ጉዳት፡ብዙ፡መቅሠፍት፡ሸተዋ
ሉና፤ሉቃ፡፲፪፡፲፭፡፳፩፡ሉሬ፡፳፡፳
፲፩ አንተ፡ግን፡የእግዚአብሔር፡ሰ
ው፡ከዚህ፡ሁሉ፡ሽሽ፡ጽድቅን፡ማ
ስተማርን፡ሃይማኖትንና፡ፍቅ
ርን፡ተዕግሥትን፡ትሕትናን
ተከተል፤፪ጢሞ፡፪፡፳፪፡ዕብ፡፲
፲፪ ፬፡፲፱፤በሃይማኖት፡በጎ፡ገድል
ተጋደል፡በብዙ፡ምስክር፡ፊት፡

የተጸራቀባት፡ በጎ፡ እምነትም፡ ያመንህለት፡ የዘላለም፡ ሕይወትን፡ ለመውረስ። ፩ቆሮ፡ ፱፡፳፭፡፳፯፡ ፊልጵ፡ ፫፡ ፲፪፡ ፲፬።

፲፫ ሙታንን፡ በሚያነሣ፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ በበጎ፡ ሃይማኖት፡ በጴንጤኑ፡ ሰው፡ በጲላጦስ፡ ፊት፡ ምስክር፡ የሆነ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ፊት፡ እንዲህ፡ እስተምርሃለሁ፡ ዘዳግ፡ ፴፪፡፴፱፡ ዮሐ፡ ፲፰፡፴፯፡ ና ፲፱፡፲፩። ጌታችን፡

፲፬ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ እስኪመጣ፡ ድረስ፡ ሳታደፋ፡ ይህን፡ ትእዛዝ በንጽሕና፡ ትጠብቅ፡ ዘንድ።

፲፭ በጊዜው፡ ጊዜ፡ የሚገለጥ፡ እሱ ብቻ፡ ኃያል፡ የሚሆን፡ የተመሰገነ፡ የነገሥታት፡ ንጉሥ፡ የአማልክት፡ አምላክ፡ የጌቶች፡ ጌታ፡ ም፡ ፩፡፲፮፡ ራእ፡ ፲፯፡፲፬፡ ዘዳግ፡ ፲፡፲፯

፲፮ እሱ፡ ብቻ፡ የማይሞት፡ ዓለም፡ ሳይፈጠር፡ በማይጠፋ፡ ብርሃን፡ የነበረ፡ ያየው፡ ሰው፡ የሌለ፡ እንግዲህም፡ ሊያየው፡ የሚቻል የሌለ፡ ለዘለዓለሙ፡ ክብር፡ ጌትነት፡ ኃይል፡ ያለው፡ አሜን።

፲፯ ዮሐ፡ ፩፡፲፰። የዚህን፡ ዓለም፡ ባለጸጎች፡ እንዳይታበዩ፡ የሚያልፈው፡ ባለጸግነታቸውንም፡ እንዳይታመኑ፡ ምክራቸው፡ ደስ ይለን፡ ዘንድ፡ በለጋስነቱ፡ ብዛት፡ ሁሉን፡ በሰጠን፡ በእግዚአብሔር፡ ይታመኑ፡ እንጂ። መዝ፡ ፷፪፡፲፩። ሉቃ፡ ፲፪፡ ፳።

፲፰ መልካም፡ ይሠራ፡ ይሠሩ፡ ዘንድ፡ ጽድቅንም፡ በመሥራት፡ ይከብሩ፡ ዘንድ፡ ቀናዎች፡ ለጋሶች፡ ለበጎ፡ ሥራ ተባባሪዎች፡ ይሆኑ፡ ዘንድ።

፲፱ የማያልፈውን፡ ሕይወት፡ ለማግኘት፡ ለሚመጣው፡ ዓለም፡ ለራሳቸው፡ በጎ፡ መሠረትን፡ ይመሠርቱ፡ ዘንድ። ማቴ፡ ፮፡፳

፳ ጢሞቴዎስ፡ ሆይ፡ አደራሳን፡ ጠብቅ፡ ከንቱ፡ ነገርን፡ የሚያመጡ፡ እውነትን፡ በሐሰት፡ የሚያርቁ፡ ኃጢአተኞችን፡ ተለያቸው።

፳፩ እንዲህ፡ ያሉ፡ ሰዎች፡ በሃይማኖት፡ ከሚገኘው፡ ተስፋ፡ ወጥተዋልና። ጸጋ፡ ካንተ፡ ይሁን

በአቴና፡ የተጻፈ፡ በቲቶ፡ እጅ፡ ወደ፡ ጢሞቴዎስ፡ የተላከ፡ መጀመርያ፡ መልእክት፡ ተፈጸመ። እስከ፳ምሮ፡ ላስጨረሰን፡ ለእግዚአብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይገባው። በእውነት። አሜን።

በሮም፡ የተጻፈ፡ ወደ፡ ጢሞቴዎስ፡
የተላከ፡ ሁለተኛ፡ መልእክት፡ ይህ፡
ነው።

ምዕራፍ፡ ፩ ። መከራ፡ ስለጸ
ናበትና፡ ምእመናን፡ ጆሮአቸው፡ ፈዘ፡ ል
ባቸው፡ ደኘባዘ፡ ትምርቱን፡ ለልዋበል፡ ሰለለ
ሉት፡ ማስተማሩን፡ ተዉ፡ ተባሕትዎ፡ ይገቡ፡ እዋ
ራለሁ፡ ስላለ፡ በማስተማር፡ ጠንተህ፡ ኑር፡ ብሎ፡ ፪ተኛ፡ እንዲጸፈለ)

፩ በእግዚአብሔር፡ ፈቃድ፡ በኢየሱ
ስ፡ ክርስቶስም፡ በሚሆን፡ የሕይ
ወት፡ አለኝታ፡ የኢየሱስ፡ ክር
ስቶስ፡ ሐዋርያው፡ ከምሆን፡ ከ
ጳውሎስ፡ የተላከች፡ መልእክት
፪ ዮሐ፡ ፩፡ ፱፡ ፩፡ ዮሐ፡ ፳፡ ፲፭፡ ፲፮፡ ለምወ
ድህ፡ ልጄ፡ ለጢሞቴዎስ፡ ትድረ
ስ፡ ከባታችን፡ ከእግዚአብሔር
ከጌታችን፡ ከኢየሱስም፡ ሰላም
ና፡ ጸጋ፡ ይቀርታም፡ ላንተ፡ ይሁ
ን። ፩ጢሞ፡ ፩፡ ፪፡ ቲቶ፡ ፩፡ ፬።
፫ ከባቶቼ፡ ጀምሮ፡ በንጹሕ፡ ልቡ
ና፡ የማመልከው፡ አሱን፡ እግዚ
አብሔርን፡ አመሰግነዋለሁ፡ በ
ቀንም፡ በሌትም፡ በምጸልየው
ጸሎት፡ ዘወትር፡ አስብሃለሁ፡
የሐዋ፡ ፳፫፡ ፩፡ የሐዋ፡ ፳፬፡ ፲፮፡ ሮ
፬ ሜ፡ ፩፡ ፱፡ ዕንባህንም፡ አያስ
፭ ብሁ፡ ሳይህ፡ እወድ፡ ለሁ። በናትህ
በኤውንቄና፡ ባያትህ፡ በሎይድ
ጸንታ፡ ያስች፡ ጥርጥር፡ የሌለበ
ት፡ ሃይማኖትህን፡ አስቤ፡ ደስ፡ ይ
ለኛል፡ ባንተም፡ ሳይ፡ ጸኖታ፡ እን
ድትኖር፡ ተስፋ፡ አደርጌ፡ ደስታ
የን፡ እፈጽማለሁ። የሐዋ፡ ፲፮፡ ፩፡
፮ ስለዚህም፡ እኔ፡ እጄን፡ ባንተ፡ ላ
ይ፡ መጫኔ፡ ያገኘኸው፡ የእግዚ
አብሔር፡ ጸጋ፡ ይታደስልህ፡ ዘ
ንድ፡ አሳስብሃለሁ። ፩ተሰ፡ ፭፡ ፲፱
፯ ፩ጢሞ፡ ፬፡ ፲፬። እግዚአብሔር፡
የመፍራትን፡ ሀብት፡ የሰጠን፡
አይደለምና፡ የኃይልን፡ የን
ጽሕናን፡ የፍቅርን፡ የጥበብ
ን፡ ሀብት፡ ነው፡ እንጂ። ሮሜ፡ ፰፡
፰ ፲፭። እንግዲህ፡ የጌታችን፡ ነገር
ስለ፡ መመስከር፡ አትፈር፡ የታሰ
ርሁለት፡ እኔንም፡ አታሰፍረኝ፡
በእግዚአብሔር፡ አጋዥነት፡ ለ
ማስተማር፡ ድከም፡ እንጂ። ሮ
፱ ሜ፡ ፩፡ ፲፮። መድኃኒታችን፡ የሆ
ነ፡ በልዩ፡ አጠራሩ፡ የጠራን፡ እሱ
ነውና፡ እንደ፡ ሥራችንም፡ አይ
ደለም፡ ዓለም፡ ሳይፈጠር፡ በኢ
የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ለእኛ፡ እንደ፡ ተ
ሰጠ፡ ቸርነቱ፡ ነው፡ እንጂ። ቲቶ
፲ ፫፡ ፭። መድኃኒታችን፡ ጌታችን
ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ በመምጣቱ
ዘሬ፡ ተገለጠ፡ ሞትን፡ ያጠፋ
ው፡ ሕይወትን፡ የገለጣት፡ በወ
ንጌል፡ ባስተማረው፡ ትምርት፡
ጥፋትን፡ ያራቀቀ፡ ሮሜ፡ ፲፮፡ ፳፭፡
ዕብ፡ ፪፡ ፲፬፡ ፩ቆሮ፡ ፲፭፡ ፶፬።
፲፩ እኔ፡ አዋጅ፡ ነጋሪ፡ ሐዋርያም፡ ለ
አሕዛብ፡ መምህር፡ የተሾምሁ
ሁለት። ፩ጢሞ፡ ፪፡ ፯።

፲፪ እለሱም፡ መከራ፡ እቀበላለሁ ከላሁበትም፡ ወጥቼ፡ አላፍርም፡ ያመንሁትን፡ አውቃለሁና፡ እስከዚያ ቀን፡ የሰጠኘን፡ አደራ፡ ሊጠብቅልኝ፡ እንዲቻለው፡ ተስፋ፡ አደርጋለሁ፨ም፡ ፬፳

፲፫ ክርስቶስን፡ በማመንና፡ በመውደድ፡ ከኔ፡ የሰማኸው፡ ደህ፡ የሕይወት፡ ትምርት፡ ምሳሌ፡ ይሁንህ፨ ቲቶ፡ ፪፡ ፩፡ ፩ጢሞ ፮፡ ፫፨

፲፬ እደሮብህ፡ ባለ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ጽኑ፡ አደራህን፡ ጠብቀው፨ ፲፬፡ ፩ጢሞ፡ ፯፡ ፳፨

፲፭ በእስያ፡ ያሉት፡ እነፊሎጎስና፡ እነ፡ ሄርሞጌኔስ፡ እንደ፡ ከዱኝ፡ ታውቃለህ፨

፲፮ እግዚአብሔር፡ ለሔኔሲፎሩ፡ ወገን፡ ይቅርታውን፡ ይስጠው ስለ፡ መታሠሬ፡ ሳያፍር፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ ረድቶኛልና፨ ፈጥኖ፡ ሮም፡ ደርሶ፡ ታሥሬ፡ ቢያገኘኝ፡ ጠይቆኛልና፨ የሐዋ፡ ፳፰፡ ፲፮፨

፲፰ በዚያች፡ ቀን፡ በጌታችን፡ ፊት ይቅርታን፡ ያገኝ፡ ያገኝ፡ ዘንድ እግዚአብሔር፡ በኤፌሶን ምን ያህል፡ እንዳገለገለኝ፡ ሁሉ እንተ፡ ታውቃለህ፨

ምዕራፍ ፪።

እንደ፡ ሥጋዊ፡ አርበኛ፡ ባለሀብት፡ ጽኖ ብሎ፡ እንደ፡ መከረው።

፩ አንተ ግን፡ ልጄ፡ በጌታችን፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ጸጋ፡ ጽና፨

፪ በብዙ፡ ምስክሮች፡ ፊት፡ ከኔ፡ ዘንድ፡ የሰማኸውን፡ ትምርት፡ ያኑ፡ ለሚገባቸው፡ ለታመኑ፡ ሰዎች፡ አስተምራቸው፡ ለሌሎች፡ ያስተምሩ፡ ዘንድ፨ ፩ጢሞ፡ ፫፡ ፪፨

፫ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ እንደሚያገለግል እንደ፡ በጎ፡ አርበኛ፡ መከራ፡ ተቀበል፨

፬ ፬፡ ፭፡ ም፡ ፩፡ ፳፨ ወደ፡ ሰልፍ፡ ሊገባ፡ የዚህን፡ ዓለም፡ ኑሮ፡ የሚያስወ፡ የለምና፡ የ፳መውኝ፡ ደስ፡ ያሰኝ፡ ዘንድ፡ ነው፡ እንጂ፨

፭ ፩ቆሮ ፱፡ ፳፭፨ አርበኛ፡ እንደሚገባው፡ ካልተዋጋ፡ መመስገን፡

፮ አይሆንለትም፨ ም፡ ፬፡ ፲፰፨ በሥራ፡ የሚደክም፡ ገበሬም፡ አስቀድሞ፡ ፍሬውን፡ ያገኛልና፨

፯ የምነግርህን፡ አስተውል፡ እግዚአብሔር፡ በሁሉ፡ ጥበቡን፡ ይሰጥሀልና፨

፰ የዳዊት፡ ዘር፡ የሚሆን፡ ከሙታን፡ ተለይቶ፡ የተነሣ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ አስበው፡ ስሙን፡ ያስተማርሁ ለትል ፩ቆሮ፡ ፲፭፡ ፬፡ ሮሜ፡ ፪፡ ፲፮፨

፱ እኔ፡ እንደ፡ ክፉ፡ አድራጊ፡ የምታሠርሁት፡ መከራም፡ የምቀበልለትም፡ ነገር፡ ግን፡ የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ አይከለከልም፨ ኤፌ፡ ፫፡ ፩፡ ፲፫፡ ፊል፡ ፩፡ ፲፫፡ ፊልጵ ፩፡ ፲፬፨

፲ ስለዚህም፡ ስለ፡ መረጣቸው፡ ሰ

ዎቹ፡ ሁሉን፡ እታግሣለሁ፡ እ
ነሱም፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡
የሚሰጠውን፡ ሕይወትና፡ በ
ሰማይ፡ ያለ፡ የዘለዓለም፡ ክብ
ር፡ ያገኙ፡ ዘንድ◆ ቆላ፡ ፩፡ ፳፬◆
፲፩ ነገሩ፡ እውነት፡ ነው፡ በሞቱ፡
ከተካከልን፡ በሕይወቱም፡ እ
እንተካከላለን◆ ሮሜ፡ ፮፡ ፲፭
፲፪ ፩፡ ጢሞ፡ ፬፡ ፲፫◆ መከራም፡ በመ
ታገሥ፡ ከተካከልን፡ በመንግ
ሥቱም፡ እንተካከላለን፡ ብንክ
ደው፡ ግን፡ እሱም፡ ይክደናል፡
፲፫ ማቴ፡ ፲፡ ፴፫◆ ባናምነውም፡
እሱስ፡ የታመነ፡ ሁኖ፡ ይኖራል
ራሱን፡ መካድ፡ አይቻለውም
ሮሜ፡ ፫፡ ፫፡ ዘኁ፡ ፳፫፡ ፲፱◆

ክፍል፡ ፪

፲፬ እንዲህ፡ እስተምራቸው፡ በእ
ግዚአብሔር፡ ፊት፡ አደኛ፡ ጥቅ
ም፡ በሌለበት፡ ነገር፡ እተጣሉ
የሚሰሙት፡ በሚታወኩ፡ ገ
ንዘብ፡ ፩ ጢሞ፡ ፮፡ ፬፡ ቲቶ፡ ፫፡ ፱
፲፭ ራስህን፡ በእግዚአብሔር፡ ዘን
ድ፡ የተመረጠ፡ ለማድረግ፡ ቸ
ኩል፡ የእግዚአብሔርን፡ ነገር፡
በእውነት፡ አቃንቶ፡ ሲቆርጥ
እንደማያፍር፡ እንጂ፡ ተምር
ቱ፡ ገበሬ◆ ፩ ጢሞ፡ ፬፡ ፮፡ ቲቶ ፪
፲፮ ፯፡ ፰◆ ጥቅም፡ የሌለበት፡ ኃጢ
አተኞቹን፡ ነገር፡ ተወው፡ ኃጢ
አታቸውን፡ ያስፋፉታልና◆ ፩
፲፯ ጢሞ፡ ፬፡ ፯◆ ከንቱ፡ የሚሆን፡
ነገራቸውም፡ በብዙ፡ ሰዎች፡
እየሰፋ፡ እንደሚታይ፡ ቍስለ
ነው፡ እሲህም፡ ከጅጅቅ፡ የወ
ጡ፡ ሔሜኔዎስና፡ ፊልጦስ፡ና
፲፰ ቸው◆ ፩ ጢሞ፡ ፩፡ ፳◆ የሙታን
ም፡ ትንሣኤ፡ ዘሬ፡ ሆኗ፡ ይላሉ፡
የብዙ፡ ሰዎችንም፡ ሃይማኖት
፲፱ ይለውጣሉ◆ በእግዚአብሔ
ር፡ መሠረት፡ የተሠራ፡ ግን፡ ይ
ጸናል፡ ይህ፡ ምልክት፡ አለው፡
እግዚአብሔርም፡ የሱ፡ ወገን
የሆኑትን፡ ይወዳቸዋል፡ የእ
ግዚአብሔርን፡ ስም፡ የሚጠ
ራ፡ ሁሉ፡ ከኃጢአት፡ ይርቃል◆
ማቴ፡ ፯፡ ፳፫፡ ዮሐ፡ ፲፡ ፲፬◆
፳ በትልቅ፡ ቤት፡ የወርቅና፡ የብ
ር፡ ዕቃ፡ ብቻ፡ የሚኖር፡ አይደ
ለም፡ የእንጨትም፡ የሸክላ
ም፡ ዕቃ፡ ይኖራል፡ እንጂ፡ ለመ
ከበርም፡ ለመዋረድም፡ የሚ
፳፩ ሆን፡ እሰ◆ ከዚህ፡ ከክፉ፡ ሥራ
ሁሉ፡ ሰውነቱን፡ ንጹሕ፡ ያደረገ
ሰው፡ የተቀ(ደሰ፡ የክብር፡ ዕቃ
ይሆናል፡ ለበጎ፡ ሥራም፡ ሁሉ
፳፪ የተዘጋጀ፡ ይሆናል◆ የሕፃንነ
ትን፡ ፈቃድ፡ ራቃት፡ ጽድቅንና
ሃይማኖትን፡ ፍቅርንና፡ ሰላም
ን፡ ግን፡ ተከተል፡ በንጹሕ፡ ልቡ
ና፡ የእግዚአብሔርን፡ ስም፡ ከ
ሚጠሩ፡ ሁሉ፡ ጋራ፡ ፩ ጢሞ፡ ፮፡ ፲፩

፳፫ የስንፍናን፡ የመዘባበትን፡ ከንቱ፡ የሚሆን፡ የመራመርን፡ ነገርን፡ ተወው፡ ጥፋትን፡ እንዲያመጣ፡ ታውቃለህና፡ ፩ጢ
፳፬ ፬፡ ፯። የእግዚአብሔር፡ ባርያ የሆነ፡ ሰው፡ ግን፡ አይጣላም፡ ከሁሉ፡ ጋራ፡ እንዲ፡ ሕፃን፡ የዋህ፡ ይሆናል፡ እንጂ። ከክፉ፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ታጋሽ፡ የሚያስተምር፡ ይ
፳፭ ሆናል። ቲቶ፡ ፩፡ ፱። የሚጣሉትን፡ በቅንነት፡ ይገሥፃል፡ እውነትን፡ ለማወቅ፡ እግዚአብሔር ምናልባት፡ ንስሐ፡ ይሰጣቸው እንደ፡ ሆነ። ከሰይጣንም፡ ወጥመድ፡ ሰውነታቸውን፡ ያድኑ፡ ዘንድ፡ ወደ፡ ፈቃዱ፡ ለማስከተል፡ ፈጽሞ፡ ለጥምዱ ቸዋልና።

ምዕራፍ፡ ፫።

በኋላ፡ ዘመን፡ ክፉ፡ ወራቶች፡ እንዲመጡ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ራሱን፡ ብቻ፡ የሚወድ እንዲሆን።

፩ ነገር፡ ግን፡ በኋላ፡ ዘመን፡ ክፉ፡ ወራት፡ እንዲመጣ፡ ይህን፡ ዕወቅ፤
፪ ሰዎች፡ ራሳቸውን፡ ብቻ፡ የሚወዱ፡ ተድላ፡ ደስታን፡ ገንዘብንም፡ የሚወዱ፡ ይሆናሉና። ከፉ፡ የሚናገሩ፡ ከሐዲ፡ የወጡ፡ ትዕቢተኞች፡ የሚሳደቡ፡ ለአባታቸው፡ የማይታዘዙ፡ እግዚአብሔርን፡ የማያመሰግኑ፡ ከእውነት፡ የወጡ፡ ሮሜ፡ ፩፡
፫ ፳፱፡ ፴፩፤ ይቀርታ፡ የሌላቸው፡ ደፋሮች፡ በጎ፡ መሥራትን፡ የሚ
፬ ጠሉ፡ ኃጢአትን፡ የሚያዘወትሩ፡ ሰውን፡ የሚጠሉ፡ እግዚአብሔርን፡ ከመውደድ፡ ይልቅ ተድላ፡ ሥጋን፡ የሚመርጡ፤ ፊ
፭ ል፡ ፫፡ ፲፱። ጻድቃንን፡ የሚመስሉ፡ የጽድቅንም፡ ምሥጢር፡ የሚክዱ፡ ናቸው። ማቴ፡ ፯፡ ፲፭፡
፮ ፳፩፡ ቲቶ፡ ፩፡ ፲፯። እንደነዚህ፡ ያሉትን፡ ተለያቸው፡ ወደ፡ ሰው፡ ቤት፡ ገብተው፡ በኃጢአት፡ የጸኑ፡ ወደ፡ ብዙ፡ ፈቃድም፡ የሚያደርሱ፡ ሴቶችን፡ ነጥቀው፡ ይወስዱ ቸዋልና። ማቴ፡ ፳፫፡ ፲፬፡ ቲቶ፡ ፩፡
፯ ፲፩። ሁልጊዜ፡ ይማራሉ፡ ጽድቅ
፰ ን፡ ከቶ፡ አያውቁትም። ኢያኔስና፡ ኢያንበሬስ፡ ሙሴን፡ እንደ፡ ተቃወሙት፡ እሊህም፡ እንደዚሁ፡ ጽድቅን፡ ይቃወሙታል። አእምሮአቸው፡ የጠፋ፡ ሰዎች፡ ከሃይማኖት፡ የወጡ፡ ናቸው።
፱ ዘፀ፡ ፯፡ ፲፩፡ ፲፪። ነገር፡ ግን፡ ከፍ፡ ወደ፡ አለ፡ ክብር፡ አይሔዱም፡ እንደነዚያ፡ ስንፍና፡ ደግሞ፡ የሌሁ፡ ስንፍና፡ በዝታለች፡ በሁሉም፡
፲ ታውቃለችና። አንተ፡ ግን፡ ትምርቴን፡ ተከተልህ፡ በሥራም፡ እኔን፡ መስለሃል፡ በአስተማርኩህ፡ በሃይማኖትና፡ በፍቅር፡ በትዕግሥትና፡ በዝማታ፡ አገር፡ ዋ

ሉ፡በመሐይምና፡መከራ፡በመፋ
፲፩ በሌ፡ጸንቶሃልና በአንጾኪያና፡
በኢቆንዮን፡በልስጥራንም፡ይ
ህ፡ሁሉ፡እንዲያገኘኝ፡ታውቃለ
ህ፡ካንዱ፡ወደ አንዱ፡በመሰደድ
ሁሉን፡እንደ፡ታገሥሁ፡ከሁሉ
ም፡እግዚአብሔር፡እንደ፡አዳነ
ኝ፡ታውቃለህ። የሐዋ፡፲፫፡፶፡ና፲
፲፪ ፬፡፭፡፲፱፡፳፩። በኢየሱስ፡ክርስቶ
ስ ጽድቅ፡ሊድኑ፡የሚወዱ፡ሁሉ
መከራ፡ይቀበላሉ። ማቴ፲፪፡፳
፲፫ ፬፡የሐዋ፡፲፬፡፳፪። ክፉዎች፡ሰዎ
ች፡ግን፡ከክፉ፡ወደ፡ክፉ፡ይ
ሔዳሉ፡ራሳቸው፡ስተው፡ሌላ
ውንም፡ያስታሉ። ፩ ጢሞ፡፬፡፩፡
፲፬ አንተ፡ግን፡በተማርኸው፡ተም
ሮ፡ባመንኸውም፡እምነት፡
፲፭ ጸንተህ፡ኑር። ምዕ፡፪፡፪። በኢየሱ
ስ፡ክርስቶስ፡በማመንህ፡ለአንተ
ን፡ማዳን፡የሚቻለው፡ክቡር፡
መጽሐፍን፡ከሕፃንነት፡ጀምሮ
ር፡ከማን፡ዘንድ፡እንደ፡ተማር
፲፮ ህ፡ታውቃለህ። ዮሐ፡፭፡፴፱። በእ
ግዚአብሔር፡መንፈስ፡የተጻ
ፈ፡መጽሐፍ፡ሁሉ፡ፍጹም፡ተ
ምርት፡ምክር፡በመሆን፡ልቡና
በማቅናት፡ጥበብ፡በመማሰጥ
ጽድቅን፡በመሥራት፡ይጠቅ
፲፯ ማል። ፪ ጴጥ፡፩፡፲፱፡፳፩። በእግዚ
አብሔር፡ያመነ፡ሰው፡በጎውን፡
ምግባር፡ሁሉ፡ይማር፡ዘንድ፡

፩ ጢሞ ፮፡፲፩፡ ምዕ ፬፡፳፩ ።

ምዕራፍ፡፬ ።

ክርስቶስ፡እስኪመጣ፡ድረስ፡በሐዋርያነቱ፡ጸንቶ፡እንዲኖር፡እንዲ፡መከረው፡እንጥረኛው፡እሉ፡እስክንድሮስ፡በቀዱስ፡ጳውሎስ፡ሥቃይ እንደ፡አደናበት ።

፩ በእግዚአብሔር፡አብ፡ፊት፡በጊ
ቶነት፡በመጣ፡ጊዜ፡ሕያዋንን፡ሙ
ታንን፡ይገዝ፡ዘንድ፡ባለው፡በ
ጌታችን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ
ም፡ፊት፡አዝዝኃለሁ። የሐዋ፡
፲፡፵፪፡፩ ጴጥ፡፬፡፭፡ ሮሜ፡፲፬፡፲፡፲፪
፪ በጸዋታ፡ቁመህ፡ቃሉን፡ታስተ
ምር፡ዘንድ፡በጊዜውም፡ያለጊ
ዜውም፡ሁሉን፡ታግሠሕ፡ስታ
ስተምር፡እያለዘብህ፡እያድናየ
ህ፡ምክር፡ዝለፍ። ሉቃ፡፱፡፳፡፩፡ም
፭፡፳፬፡፫፡፲፱፡ቲቶ ፩፡፱፡፲፫።
፫ ሕይወት፡የሚገኝባትን፡ትምር
ት፡አንቀበልም፡የሚሉበት፡በፊ
ቃዳቸውም፡የሚሔዱበት፡ጊዜ
ይደርሳል፡በጆሮ፡አቸውም፡መ
ቀበዝበዝ፡ለራሳቸው፡መምራን
ያመጣሉ። ፩ ጢሞ፡፩፡፲፫፡ና፡፬፡፩
፬ ጆሮአቸውንም፡ከዕውነት፡ይ
መልሳሉ፡ሌላ፡ትምርትንም፡ያ
መጣሉ፡ወደ፡ተረትም፡ይመለሳ
ሉ። ፩ ጢሞ፡፬፡፯፡፮ ተሰ፡፮፡፲፩።
፭ አንተ፡ግን፡ንቃ፡በሁሉም፡ጥበ
በኛ፡ሁን፡መከራውን፡ተቀበል፡
በመከራው፡ጸንተህ፡ወንጌል፡

ያዘዘውን፣ሥራ፣አገልግሎ
ቱህንም፡ፈጽም፨የሐዋ፡፳፩
፮ ፳፬፨ እኔ፡ግን፡አገልግሎቴን
ፈጽሜ፡ጨርሻለሁ፡የማርፍ
በት፡ዕድሜዬ፡ደርሶ አልቋልና
፯ ፬፡፬፯፨ በጎ፡መጋደልን፡ተጋደ
ልሁ፡ቀድድሜንም፡ፈጸም
ሁ፡ሃይማኖቴንም፡ጠበቅሁ
፩ቆሮ፡፱፡፳፭፡፩ጢ፮፡፲፪ ፊል
፰ ፫፡፲፬፨ እንግዲህ፡ወዲህስ፡በ
ዚያ ቀን፡እውነተኛ፡የሚፈ
ርድ፡እግዚአብሔር፡የሚሰጠ
ኝ፡የጽድቅ፡አክሊል፡ይቆየኛ
ል፡መስጠቱም፡ለኔ፡ብቻ፡አይ
ደለም፡የሱን፡መምጣት፡ለሚ
ወዱ፡ሁሉ፡ነው፡እንጂ፨ም፡፬፳
፭ ጴጥ፡፭፡፬ ያዕ፡፩፡፲፪፡ራእ፡፪፡፲
፱ ፈጥነህ፡ወደኔ፡ትመጣ፡ዘንድ፡
፲ ቸኩል፡ቍ፲፩፨ዴማስ፡ይህን
የዛሬውን፡ዓለም፡ወዶ፡ትቶኝ
ወደ፡ተሰሎንቄ፡ሄዷልና፡ቄሬ
ቂስም፡ወደ፡ገላትያ፡ቲቶም፡
ወደ፡ድልማጥያ፡ሔዷልና፡፬
፲፩ ፲፬፡ም፮፡፲፭፨ሉቃስ፡ብቻ፡ከኔ
ጋራ፡አለ፡ማርቆስን፡ከንተ፡ጋ
ራ፡አምጣው፡ለማገልገል፡ይ
በቍኛልና፨ዋሐ፲፭፡፴፯፨
፲፪ ጢቂኮስንም፡ወደ፡ኤፌሶን፡
ልኬዋለሁ፨ዮሐ፡፳፬ ኤፌ፮፡፳
፲፫ ፩፡ቆላ፡፬፡፯፨በጢሮአስ፡ከአክ
ርጳ፡ዘንድ፡የተውሁትን፡የመ

ጻፉን፡መጠቅለያ፡ጀባውን፡
ይዘህ፡ና፨መጽሐፍቱንና፡ወ
፲፬ ረቀቱን፡ደግሞ፨እንጥረኛ፡እ
ሉ፡እስክንድሮስ፡እጅግ፡መከ
ራ፡አፀናብኝ፡እግዚአብሔ
ር፡እንደ፡ሥራው፡ፍዳውን፡ይ
ሰጠው፨፩ጢሞ፡፩፡፳፡፪ሳሙ፡
፫፡፴፱፡መዝ፡፳፰፡፬፨
፲፭ አንተም፡ልጁ፡ተጠበቀበት፡
ትምርታችንን፡እጅግ፡ተቃወ
፲፮ ሞታልና ፲፩ በመጀመሪያው
ቅምርቴ፡ከኔ፡ጋጋራ፡የተባበ
ረ፡የለም፡ሁሉም፡ተለዩኝ፡
እንጂ፨ነገር፡ግን፡ይህን፡ይቆ
ር፡ይበሳቸው፨ዮሐ፲፪፡፴፬፡፬
፲፯ ጢሞ፡፩፡፲፫፨እግዚአብሔር፡ረ
ድቶኛልና፡በኔም፡ስብከት፡
ያምኑ፡ዘንድ፡አጽንቶኛልና፡
ከአንበሳ፡አፍ፡እንደ፡ዳንሁ፡ለ
ሐዘብ፡ሁሉ፡ይሰሙ፨የሐ፡፳፫
፲፩፡ና፳፪፡፳፫፡የሐዋ፡፲፱፡፲፩፨
፲፰ እንዲህም፡ከክፉ፡ነገር፡ሁ
ሉ፡እግዚአብሔር፡ያድነኛል
በመንግሥቱ፡ሰማያት፡በሕ
ይወት፡ያኖረኛል፡ለርሱም፡
ምስጋና፡ይገባዋል፡ለዘለዓለ
ም፡በእውነት፡ያስሐስቶ፨
ሮሜ፡፲፪፡፳፯፡ገላ፡፩፡፭፡፩ጢሞ
፲፱ ፪፡፲፯፨ጵርስቅላን፡አቂላን፡የ
ሄኔሲፎሩን፡ወገን፡እንዲ
ናቸሁ፡በልልኝ፡የሐ፲፰፡፪፡ሮሜ፡፲፮

፫፡ም፡ ፩፡፲፯።

፳ ኤርስጦስ፡በቆሮንቶስ፡ቀረ፡ጢ ሮፊሞስንም፡መሊጡ፡በሚባ ኑ፡አገር፡ታሞ፡ተውሁት።የሐዋ ፲፱፡፳፪፡የሐዋ፡፳፡፬፡ና ፳፩፡፳፱።

፳፩ ከክረምት፡አስቀድሞ፡ፈጥነህ፡ወ ደኔ፡ና፡ አውብሎስና፡ጱዴስ፡ሊኖ ስና፡ቀላውዲያስ፡ወንድሞቻች

፳፪ ን፡ሁሉ፡እንደ ቲ፡ነህ፡ይሉሃል። ጌ ታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስም፡ከአ ንተ፡ጋራ፡ይኑር፡ጸጋው፡ሰንተ፡ይ ሁን።አሜን።ቲቶ፡፫፡፲፭። በሮም፡ የተጻፈ፡በአንክሮሉስ፡እጅ፡ወደ ጢሞቴዎስ፡የተላከ፡ሁለተኛ፡መ ልእክት፡ተፈጸመ።

አስጀምሮ፡ላስጨረሰን፡ለእግዚ አብሔር፡ክብር፡ምስጋና፡ይግ ባው፡ አሜን።

በናቆጵሊ፡የተጻፈ፡ወደ፡ቲቶ፡የ ተላከ፡መልእክት፡ይህ፡ነው።

ምዕራፍ፡፫። ክፍል፡፫።

ቲቶ፡ጳጳ፡ብላቴና፡ስለሆነ፡ከአረማዊነት መልሶ፡ሳይገዝር፡እንደ፡አስከተ ሰውና፡በቀ ርጤስ፡አውራጃ፡ሹጼዕ፡ቆ ጳስነትን እንዲሾመው።

የእግዚአብሔር፡ተግዥ፡የኢየ ሱስ፡ክርስቶስም፡ሐዋርያ፡ከም ሆነ፡ከጳውሎስ፡የተላከች፡(መልእክት።እግዚአብሔር፡ በመረጣቸው፡ሰዎች፡ሃይማኖ ት፡የእግዚአብሔርንም፡እው ነተኛ፡ሕግን፡በማወቅ።

፪ ሐሰት፡የማይናገር፡እግዚአብ ሔር፡ዓለም፡ከተፈጠረ፡ጀም ሮ፡ያናገረውን፡የዘላለም፡ሕ ይወት፡ተስፋ፡በማድረግ።

፫ እኛ፡የሱን፡ነገር፡በማስተማራ ችን፡በጊዜው፡ጊዜ፡ቃሉን፡የገለ ጠ፡በመድኃኒታችን፡በእግዚአ ብሔር፡ትእዛዝ፡በሕጉ፡ሳይ፡የተ ማመነኝ። ኤፌ፡፩፡፱፡፲፡፩ጢሞ፡፩፡

፬ ፫፡፲፩። በፍቅርና፡በሃይማኖት፡ ለምወደው፡ለልጄ፡ለቲቶ፡ተድረ ስ። ከአባታችን፡ከእግዚአብሔር አብ፡ከመድኃኒታችን፡ከኢየሱስ ክርስቶስም፡ሰላምና፡ጸጋ፡ይቀር ታም፡ለአንተ፡ይሁን። ፩ጢሞ፡፩፪

፭ ከኔ፡የቀረውን፡ታከናውን፡ዘንድ፡ ስለዚህ፡በቀርጤስ፡ተውሁ ህ፡እንደ፡ዘዝኩህ፡በያገሩ፡ቀሳ

፮ ውስትን፡ትሾም፡ዘንድ። እንደ ቶ፡ሚስት፡ያገባውን፡የተመረ ጠውን፡በክፉ፡ነገር፡የማይጠ ቱን፡በኃጢአት፡የማይከሰሰው የታመኑ፡አውታቶች፡ያሉትን፡ ለሁሉ፡የሚታዘዙ፡ልጆች፡ያሉ ትን፡ሹም። ፩ጢሞ፡፫፡፪፡፩፡ጴ፡፫፭

፯ ነውር፡የሌለበት፡የማያዳላም፡ ጳጳስነት፡ሊሾም፡ይገባል።የእግ ዚአብሔር፡ሹም፡እንደ፡መሆኑ፡

ቍጣ፡ያልሆነ፡ዕውቀት፡ያለው፤
ወይን፡አብዝቶ፡የማይጠጣ፤ለመ
ማታት፤እጁን፡የማያፋጥን፡ሰው
ን፡የማይደፍር፤የማይኰራ፡የ
ሚያልፈውን፡ገንዘብ፡የማይወ
ድ፡፩ቆሮ፡፬፡፳፡፬ጢሞ፡፬፡፳፬።
፰ እንግዳ፡መቀበልን፡የሚወድ፡ም
ግባሩ፡ያማረ፡ሰውነቱን፡ከኃጢ
አት፡ንጹሕ፡ያደረገ፤ዕውነተኛ፡
፱ ቸር፡ቀና፤የሚታገሥ፤ይቅር፡የ
ሚል፡የሃይማኖትን፡ነገር፡የተማ
ረ፡ሕይወት፡የሚገኝበትን፡ትም
ርት፡ማስተማር፡የሚቻለው፡የ
ሚከራከሩትንም፡የሚረታ፤፪፡
፲ ተሰ፡፪፡፲፭፤የማይታዘዙ፡ነገራ
ቸውም፡ከንቱ፡የሚሆን፡ሰዎች
ብዙ፡ናቸው፤ልቡናቸው፡ያል
ተገዘረው፡ይልቁንም፡ከአይሁ
ድ፡ወገን፡የተገዘሩትን፡ያስቷቸ
፲፩ ዋል፡አፋቸውን፡ሊዘጉቸው፡የ
ሚገባ፡ናቸው፡የሰውን፡ሁሉ፡
ቤት፡ያጠፋሉና፡ጥቅማቸው፡ኃ
ሣር፡በሚሆንባቸው፡ገንዘብ፡
በማይገባ፡ያስተምራሉ፡ማቴ
፳፫፡፲፬፡፪ጢሞ፡፫፡፯።
፲፪ ከነሱ፡ወገን፡የሚሆን፡እንደ
መምራቸውም፡የነሱን፡ነገር፡
ተናግሯል፤የቀርጤስ፡ሰዎች፡
ሓብዞች፡ሁሉ፡ጊዜ፡ሐሰተኞች፡ክ
ፉ፡አውሬዎች፤የመካን፡ሆዳ፡ና
ቸው፡ብኩል፡ይህም፡በሳቸው፡የ

፲፫ ታመነ፡ምስክር፡ነው፤ስለዚህ
ም፡ሃይማኖትን፡ይረዱ፡ዘንድ፡
ጽኑ፡ዘለፋ፡ዝለፋቸው፤፪፡፲፩
፲፬ ፬፡፯፤ተረትን፡እውነተኛም፡የሚ
ለውጥ፡የሰውን፡ሥራት፡እንዳያ
፲፭ መጡ፤፩ጢሞ፡፩፡፬፤ንጹሓን፡ለ
ሆኑ፡ሁሉ፡ንጹሕ፡ነው፤ለማያ
ምኑ፡ለርኩሳን፡ግን፡ምንም፡
ንጹሕ፡ነው፡የሚሉት፡የላቸው
ም፡ልቡናቸው፡አሳባቸው፡ርኩስ
ነው፤እንጂ፤ማቴ፡፲፭፡፲፩፡ሮሜ፡
፲፮ ፲፬፡፳፤እግዚአብሔርን፡እንደ
ሚያውቁት፡አድርገው፡ያምና
ሉ፤በሥራቸው፡ግን፡ይክዱታል
የተጠሉ፡የማያምኑ፡በመልካ
ም፡ሥራ፡ሁሉ፡የተናቁ፡ናቸው
፩ጢሞ፡፫፡፭። ❖ ❖ ❖

ምዕራፍ፡፪።

ሽማግሌዎች፡ባልቴቶች፡ከዝሙት፡
ንጹሕን፡ሊሆኑ፡እንዲገባቸው፡የሽማግሌ
ና፡የባልቴት፡ሴሰኛና፡ዝሙተኛ፡ምንም
እንዳያምርባቸው—

፩ አንተ፡ግን፡ለሕይወት፡የሚገባ
ውን፡ትምርት፡አስተምር፤፩ጢሞ
፪ ፩፡፫፤፪ጢሞ፡፩፡፲፫፤ሽማግሌዎች
ም፡ከዝሙት፡የነጹ፡ይሁኑ፤የነ
ቁ፡ዕውቀትም፡ያላቸው፡ይሁ
ኑ፤ሃይማኖትም፡አይጠራጠ
ሩ፡ይፋቀሩ፡አውቀውም፡ይታ
፫ ገሡ፡፩ጢሞ፡፫፡፩፤ባልቴቶችም
እንደዚሁ፡የነጹ፡ይሁኑ፡ሥራቸ

ውንም፡ያከናውኑ፡ነገር፡አያዋ
ስዱ፡ለመጠጥም፡አይገዙ፡ሰከረ
ው፡አይውደቁ፥በጎውን፡ተምር
ርት፡ለሴቶቹ፡ሕፃናት፡ይምከሩ
ያስተምሩ፡እንጂ፡ሰውነታቸ
ውን፡ከኃጢአት፡ያነጹት፡ዘንድ
፬ ፩ጢሞ፡፫፡፲፩፥ሕፃናቱም፡ሴቶ
ቹ፡ባሎቻቸውንና፡ልጆቻቸው
፭ ን፡ይወዷቸው፡ሴሰኞችም፡አይሁ
ኑ፥በጎውን፡ሥራ፡ይሥሩ፡እንጂ
ጠባያቸውንም፡ያሰምሩ፥የቤ
ታቸውን፡ሥራት፡ያከናውኑ፡ለ
ባሎቻቸውም፡ይታዘዙ፥በሳቸ
ው፡ምክንያት፡እንዱ፡ሰው፡ስንኳ
የእግዚአብሔርን፡ሕግ፡እንዳይ
፮ ነቅፍ፥ኤፌ፡፭፡፳፪፥ጎበዛዝቱ
ም፡ሰውነታቸውን፡ከኃጢአት
ንጹሕ፡ያደርጉ፡ዘንድ፡ምከራቸ
ው፡አዋቆቹም፡ይሆኑ፡ዘንድ፥
፯ በበጎው፡ሥራ፡ለሁሉም፡ምሳሌ
ሁኗቸው፥ነገርህም፡ትምህር
ትም፡በንጹሕና፡ይሁን፥፩፡ጢሞ
፰ ፬፡፲፪፡፩ጴ፡፫፡፫፥በተከናወነ፡ነገ
ር፡ነውር፡የሌለበት፡እንዲ፡ሰው
ስ፡ስንኳ፡የማይነቀው፡፡ጠላት
በኛ፡የሚናገረው፡ክፉ፡ነገር፡
አዋቆ፡ያፍር፡ዘንድ፡፡፩ጴ፡ ፪
፲፭፥ ክፍል፬፡፡
፱ ቤተ፡ሰበችም፡ለጌቶቻቸው፡ይታ
ዘዙ፡በሁሉም፡ደስ፡ያሰኙዋቸው፡
፩፡ጴ፡፪፡፲፰፡ኤፌ፡፮፡፭፡ጢሞ፮

፲ ፬፥ሌቦች፡አይሁኑ፡በሁሉም፡
አይክራከሩ፡ባለመጠርጠር፡
መታመናቸውን፡ያጽኑ፡እንጂ፥
መድኃኒታችን፡እግዚአብሔር
ያስተማራትን፡ሕግ፡ባራቱ፡ማ
ዕዘን፡ያከብሯት፡ዘንድ፥ም፭
፲፩ ፫፥የእግዚአብሔር፡ጸጋው፡በ
ሰው፡ሁሉ፡ዘንድ፡ታውቋልና፤
፲፪ ፩ዮሐ፡፬፡፱፡ም፫፡፩፥ይህቸው
ም፡ኃጢአትና፡የዓለምን፡ፈቃ
ድ፡እንተዋት፡ዘንድ፡ታስተምረ
ናለች፡በዚህ፡ዓለም፡በእውነት
ና፡በእውነትና፡በንጹሕና፡በፍ
ቅር፡እንኖር፡ዘንድ፥ኤፌ፡፩፡፬፡
፲፫ የተመሰገነውን፡ተስፋ፡የታላ
ቁ፡አምላክ፡የመድኃኒታችን፡
የኢየሱስ፡ክርስቶስንም፡ክብ
ር፡መገለጥ፡እየጠበቅን፥፩ቆ
፲፬ ሮ፡፩፡፯፡ፊል፡፫፡፳፥ለኛ፡ራሱ
ን፡አሳልፎ፡የሰጠ፡ከኃጢአታ
ችን፡ያድነን፡ዘንድ፥ለበጎ፡ሥራ
የምንፈጥን፡የተመረጠ፡ወ
ገን፡ያደርገን፡ዘንድ፥ኤፌ፡፪፡፲
፲፭ ንሳ፡፭፡፬፡፩ጢሞ፡፬፡፪፥እንዲ
ህም፡ከር፡አስተምር፡ገሥጽ፡
ለሁሉ፡ራስህን፡አያዋረድህ፡የ
ሚያስትህ፡አይኑር፡፡፩፡ጢሞ
፬፡፲፪፥ ምዕራፍ ፫ ፲፪

በሰጎ፡ማብር፡ጸንተው፡እንዲያገለግሉ፡ቀሳውስ
ትንና፡ዲያቆናትን፡እንዴ፡መከራቸው፡ተከራካ
ሪን፡ሰው፡እንዴ፡ጊዜን፡ሁለት፡ጊዜ፡ከተረታ፡በኋላ

አልመለስም፡ቢል፡እምቢተኛነቱን፡አስታውቆ፡መተው፡እንዲገባ።

፩ በበጎ፡ሥራ፡ሁሉ፡ይታዘዙ፡ዘንድ፡ለታላቆቹና፡ለተገዥዎች፡አሳስባቸው፡በዚያውም፡የጨከኑ፡ይሆኑ፡ዘንድ። ፩ጴጥ፡፪፡፲፫።

፪ እንዳይቀጡና፡እንዳይጣሉ፡ለሰው፡ሁሉ፡የሚራሩ፡ቅኖች፡ይሁኑ፡እንጂ። ፊል፡፬፡፭።

፫ እኛ፡ቀድሞ፡ያላዐወቅን፡ሰንፈን፡ነበርና፡ክደን፡በድለን፡ልዩ፡ልዩ፡ለሚሆን፡ለኃጢአትና፡ለተድላ፡ተገዝተን፡ክፋትንና፡መቅናትን፡ተከትለን፡ባልንጀሮቻችን፡ጠልተን፡ክፉ፡እንሠራ፡ነበርና። ፩ቆሮ፡፮፡፲፩፡ ኤፌ፡፪፡፪፡ናም

፬ ፬፡፲፯፡፲፰። ሰውን፡የሚወድ፡የመድኃኒታችን፡የእግዚአብሔር፡ቸርነት፡በተገለጠ፡ጊዜ፡ማኘ፡ምዕ፡፲፮።

፭ ጽድቅ፡በመሥራታችን፡አይደለም፡በቸርነቱ፡ነው፡እንጂ። ሁለተኛ፡ልደት፡በሚሆን፡ጥምቀት፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡በመታደስ፡አዳነን። ኤፌ፡፪፡፰፡፱፡ ዮሐ፡፫፡፭፡ ኤፌ፡፭፡፳፮፡፳፯።

፮ ስለ፡መድኃኒታችን፡ስለ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ካሳ፡በልግስና፡በኛ፡ላይ፡ያሳደረው።

፯ በቸርነቱ፡እንጸድቅ፡ዘንድ፡የዘላለምን፡ሕይወት፡እንወርስ፡ዘንድ። ሮሜ፡፭፡፩፡ ሮሜ፡፰፡፲፯።

፰ ነገሩ፡እውነት፡ነው፡እኔም፡ስለዚህ፡ሳጸናህ፡እወዳለሁ። በእግዚአብሔር፡ያመኑ፡ሰዎች፡በበጎው፡ሥራ፡መራዳትን፡ያስቡ፡ዘንድ፡እንድትመክራቸው፡ለሰው፡የሚጠቅመው፡በጎ፡ነገር፡ይህ፡ነውና። ቍ፡፲፬።

፱ የጠብን፡የስንፍናን፡ነገር፡ፈጥረው፡የሚናገሩትን፡ተረቶች፡ዋዘ፡ፈዘዘን፡የሚጫወቱትን፡ሰዎች፡ተለያቸው፡የማይጠቅም፡ከንቱ፡ነውና። ፩ጢሞ፡፩፡፬።

፲ የከዳውን፡አንድ፡ጊዜ፡ሁለት፡ጊዜ፡ከመከርኸው፡በኋላ፡አልመለስም፡ቢል፡ተወው። ፪ዮሐ፡፲፡ ማቴ፡፲፰፡፲፯።

፲፩ ማቴ፡፲፰፡፲፯። እንዲሁ፡ያለውን፡የሚያስትና፡የሚያስክድ፡እንቢተኛ፡እንደሆነ፡አስታውቀ፡በት፡ፍዳውን፡ይቀበላልና። ፩ጢሞ፡፯፡፩።

፲፪ አርጤምን፡ወይም፡ቲኪቆስን፡ወዳንተ፡በሰደድሁት፡ጊዜ፡እኔ፡ወደ፡አለሁበት፡አገር፡ወደ፡ኒቆጵሊ፡ፈጥነህ፡ና፡ከዚያ፡ልከርም፡ወስኜ፡አለሁና።

፲፫ ፪ጢሞ፡፬፡፲፪። አገር፡አሳዳሪ፡ዜማስንና፡አጵሎስን፡በምንም፡በምን፡እንዳይቸገሩ፡ተግተህ፡ርዳቸው። የሐዋ፡፲፰፡፳፬፡ ፩ቆሮ፡፩፡፲፪።

፲፬ የኛ፡ወገኖችም፡በጎውን፡ሥራ፡ይማሩ፡በሚወደደው፡ነገር፡ይ

ጸኑ፡ዘንድ፡ፍሬ፡የሌላቸው፡ እንዳይሆኑ፡ኤፌ ፬፡፳፰፡ማቴ ፯፡፲፱። ፲፭ ከኔ፡ጋራ፡ያሉት፡ሁሉ፡ እንዴት፡ነህ፡ይሉሃል። በሃይ ማኖት፡የሚወዱንን፡ሁሉ፡እን ዴት፡ነህ፡በል፡ጸጋ፡ለሁላችሁ፡ ይሁን፡ያስሐስት፡በእውነት፡ግ ል፡፳፫፡፳፬። ፲፮ በናቁጵልዮን፡የተጻ ፈ፡በዲቂ፡መዝሙሩ፡በአርጣ ማ፡እጅ፡ወደ፡ቲቶ፡የተላከ፡መ ልእክት፡ተፈጸመ።

አስጀምሮ፡ላስጨረሰኝ፡ለእ ግዚአብሔር፡ክብር፡ምስጋና ይገባዋል። አሜን። ። ። በሮም፡ሳለ፡የተጻፈ፡ወደፊልሞ ና፡የተላከ፡መልእክት፡ይህ፡ነው።

ምዕራፍ፡፩።

ባለጸጋው፡ፊልሞና፡ባሪያውን፡አናሲሞስን፡ስለ ተጣላው፡ታረቀልኝ፡ሲል፡ቅዱስ፡ጳውሎስ፡የ መማለጃ፡መልክት፡እንደ፡ላከለት።

፩ የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እሥር፡ከ ምሆን፡ከጳውሎስ፡ከወንድማ ችን፡ከጢሞቴዎስ፡የተላከ መልክት፡ለምንወደው፡በሥ ራም፡ከኛ፡ጋራ፡ለሚተባበር፡ለ ፊልሞና፡ትድረስ። ኤፌ ፫፡፩።

፪ ለእኅታችን፡ለአፍብያም፡ከእ ኛ፡ጋራ፡ሥራ፡ለሚሠራ፡ለአር ክጳም፡ከነሱም፡ጋራ፡በ ቤት፡ክርስቲያን፡ላሉ፡ትድረስ፡

፫ ቆላ፡፩፡፲፪። የእግዚአብሔር፡የ አባታችን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስ ም፡የጌታችን፡ ሰላምና፡ጸጋ፡ለ ናንተ፡ይሁን። ሮሜ፡፩፡፯።

፬ ፈጣሪዬን፡ሁልጊዜ፡አመሰግነ ዋለሁ፡ ሁልጊዜም፡በምጸልየ

፭ ው፡ጸሎት፡አስብሃለሁ። በጌታ ችን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ያመን ከውን፡እምነት፡ለቅዱሳንም፡ ያደረግኸውን፡ፍቅር፡ከሰማ

፮ ሁ፡ወዲህ። በበጎ፡ምግባርና፡በ በጌታችን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ ም፡የሚገኘው፡በጎው፡ነገር ከማወቅ፡ጋራ፡የሃይማኖ ትህ፡አንድነት፡የጸና፡ይሆን፡ዘን

፯ ድ። ፊል ፩፡፱። ፍቅርም፡ስለ፡ አፀናህ፡እጅግ፡ደስ፡አለኝ፡ወን ድሜ፡የቅዱሳን፡ሰውነት፡ካን ተ፡ዘንድ፡ዕረፍት፡አግኝታለች

፰ ና። ፪ቆሮ ፯፡፩። ስለዚህም፡በ ክርስቶስ፡ዘንድ፡ብዙ፡ባለሟል ነት፡አለኝ፡የጽድቅንና፡የፍቅ ርን፡ትእዛዝ፡አዝህ፡ዘንድ።

፱ እኔ፡ጳውሎስ፡አማልድሃለሁ፡እ ንደምታውቅ፡ሽማግሌ፡ነኝና ወዲህም፡ደግሞ፡የክርስቶስ፡

፲ እሥር፡ነኝ። በእስራቴ፡ሳለሁ ስለ፡ወለድሁት፡ልጄ፡አማልድ ሃለሁ፡ይኸውም፡አናሲሞስ፡ ነው። ቆላ ፬፡፱፡ ፩ቆሮ ፬፡፲፭፡ ገ

፲፩ ላ ፬፡፲፱። የቀድሞ፡ሥራው፡አ

ለጠቀመህም፡ነበር፡ዛሬ፡ግን፡
ለኔም፡ላንተም፡እጅግ፡የጠቀ
፲፪ መ፡ሆኗል። እነሆ፡ወደ፡አንተ፡ሰ
ድጄዋለሁና፡ልጄ፡እንደ፡መሆ
፲፫ ኑ፡ተቀበለው። ከኔ፡ጋራ፡ለኖረ
ው፡ወድጄ፡ነበር፡ስለ፡ወንጌል
በመታሠሬ፡በአንተ፡ፈንታ፡ያገ
ለግለኝ፡ዘንድ። ፩ቆሮ፡፲፮፡፲፯
፲፬ ፊሊ፡፪፡፴። ነገር፡ግን፡አንተ፡ሳ
ታውቅ፡ምንም፡ላደርግ፡አል
ወደድሁም፤ በጎነትህ፡በግድ
እንዳይሆን፡በልብህ፡ፈቃድ
፲፭ እንጂ። ፪ቆሮ፡፱፡፯። ወይም፡ስ
ለዚህ፡ጥቂት፡ሰዓት፡ተለይቶ
ህ፡ይሆናል፡የዘለዓለም፡አገ
ልጋይ፡ይሆንህ፡ዘንድ። ዘፍ፡፵፭፡
፲፮ ፭። እንግዲህ፡ወዲህ፡እንደ፡ባ
ርያ፡አይደለም፡ከባርያ፡እንደ
ሚበልጥ፡ልጅ፡ነው፡እንጂ። ለ
ኔስ፡ወንድሜ፡ከሆነ፡ይልቁን፡
ባንተ፡ዘንድማ፡እንዴት፡አይ
በልጥ፡በሥጋውም፡እንደሚ
ገባው፡ይርዳው። በጌታችን
ስለሚሆን፡ሃይማኖትም፡ይ
ጸልይልህ፡ማቴ፳ ሮ፡፳፫፡፩ጢ
፲፯ ሞ፮፡፪። እንግዲህ፡ወንድሜ፡
ከሆንህ፡እንደኔ፡ተቀበለው።
፲፰ የበደለህም፡በደል፡ቢኖር፡የ
ሚከፍልህም፡ገንዘብ፡ቢኖ
፲፱ ር፡በኔ፡ላይ፡አድርገው። እኔ፡ጳ
ውሎስ፡ስለ፡እርሱ፡እከፍላለ
ሁ፡ብዬ፡በጄ፡ጽፌአለሁ፡ወን
ድሜ፡ሰውነትህን፡ስንኳ፡ለተ
ሰጠኸኝ፡ይገባኛል፡እንዳልልህ
፳ እውነት፡ነው። በጌታችን፡ስ
ለ፡ለመንህ፡ባንተ፡ደስ፡ይለኛ
ል። ደግመኛ፡ዕረፍት፡ስጠኝ
ልቡናዬንም፡በክርስቶስ፡ደስ
፳፩ አሰኘው። ፯ቁ መታዘዝህ
ን፡እምኜ፡ጽፌልሃለሁና፡ካዘ
ዝኩህም፡አትርፈህ፡እንድት
ሠራ፡ዐውቄ። ፪ቆሮ፡፯፡፲፮።
፳፪ ከዚህም፡ጋራ፡የማድርበትን፡
ቤት፡አዘጋጅልኝ፡እግዚአብሔ
ር፡በናንተ፡ጸሎት፡ምንግዜ፡
አቀንቶ፡ካንተ፡ጋራ፡እንዲያገ
ናኘኝ፡አምናለሁና። ፊል፡፩፡፳
፳፫ ፭፡፲፱። ከእኔ፡ጋራ፡በኢየሱስ፡ክ
ርስቶስ፡ያመነ፡ኤጳፍራስ፡እንደ
ተ፡ናቸሁ፡ይሳቹኋል። ቆላ፡፩
፳፬ ፡፯፡ና፡፬፡፲፪። በሥራ፡የምንተ
ባበር፡ማርቆስና፡አርስጥርኮ
ስ፡ዴማስና፡ሉቃስም፡እንዲሁ
ናቸሁ፡ይሳቹኋል። ቆላ፡፬፡፲
፳፭ ፬። የጌታችን፡የኢየሱስ፡ክርስቶ
ስ፡ ጸጋ፡ከናንተ፡ጋራ፡ይሁን
ያለሐሰት፡በእውነት።
በሮም፡የተጻፈ፡በአናሲሞስ፡
እጅ፡ወደ፡ፊልሞና፡የተላከ፡መ
ልክት፡ተፈጸመ። ለአስጀምሮ፡ያ
ስጨረሰን፡ለእግዚአብሔር
ክብር፡ምስጋና፡ይግባው።

ዕብራውያን፡ ወደ፡ ተባሉ፡ ሰዎች፡ የተላከ፡ መልክት፡ ይህ፡ ነው፡

ምዕራፍ፡ ፲፪፡ ክፍል፡ ፲፪፡

ክርስቶስን፡ መልአክ፡ እንበለው፡ ወይም፡ ነቢይ፡ እንበለው፡ ስለሱስሉ፡ ከመላእክት፡ መብለጡን፡ በጸጬ፡ እኛ፡ ገኃጢአት፡ ማንፃቱን፡ ለማስረዳት፡ በብዙ፡ ምሳሌ፡ እንደ፡ ጸፈላቸው፡

፩ ከጥንት፡ ጀምሮ፡ እግዚአብሔር፡ ለአባቶቻችን፡ በነቢያት፡ ቃል፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የሆነ፡ ብዙ፡ ነገር፡ ተናገረ። ዘኍ፡ ፲፪፡ ፯፡ ፰፡ ዮሐ፡ ፩፡ ፲፰፡ ቆላ፡ ፪፡ ፲፯።

፪ በኋላ፡ ዘመን፡ ግን፡ ለሁሉ፡ ወራሽ፡ ባደረገው፡ ሁሉንም፡ በፈጠረበት፡ በልጁ፡ ቃል፡ ለእኛ፡ ነገረን። መዝ፡ ፪፡ ፰፡ ዮሐ፡

፫ ፩፡ ፫፡ ቆላ፡ ፩፡ ፲፮። ያኸውም፡ የክብሩ፡ መገለጫ፡ የመልኩ፡ ምሳሌ፡ በቃሉ፡ ኃይል፡ ሁሉን፡ የሚይዝ፡ ነው። በእካሉም፡ ኃጢአታችንን፡ የሚያነፃበትን፡ ሥራ፡ ከሠራ፡ በኋላ፡ በሰማይ፡ በጌትነቱ፡ ቀኝ፡ ተቀመጠ። ፪ቆሮ፡ ፬፡ ፬፡ ቆላ፡ ፩፡ ፲፭፡ ምሳ፡ ፱፡ ፲፱፡ ፳፪፡ ማቴ፡

፬ ፳፪፡ ፵፬። በዚህም፡ ያህል፡ መብለጥ፡ ከመላእክት፡ በላይ፡ ሁኖ፡ ከስማቸው፡ የሚበልጥና፡ የሚከብር፡ ስምን፡ ወረሰ። ፊል፡

፭ ፪፡ ፱። ከሆነ፡ ጀምሮ፡ ከመላእክት፡ ወገን፡ እኔ፡ የወለድሁህ፡ ልጄ፡ አንተ፡ ነህ፡ ያለው፡ ማነው። ዳግመኛም፡ እኔ፡ አባት፡ እሆነዋለሁ፡ እሱም፡ ልጅ፡ ይሆነኛል፡ ያለው፡ ማነው። መዝ፡ ፪፡ ፯፡ ፪

፮ ሳሙ፡ ፯፡ ፲፬። ዳግመኛም፡ ልጁን፡ ወደ፡ ዚህ፡ ዓለም፡ በገባ፡ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር፡ መላእክቶች፡ ሁሉ፡ ይስገዱለት፡ አለ። ሮሜ፡ ፰፡ ፳፱፡ መዝ፡ ፺፯፡ ፯።

፯ ስለ፡ መላእክትም፡ አገልጋዮችን፡ የሚላኩትን፡ የሚነዱ፡ እሳት፡ ነፋስ፡ ያደረጋቸው፡ እሱ፡ ነው። መዝ፡ ፻፬፡ ፬።

፰ ስለ፡ ልጁ፡ ግን፡ አቤቱ፡ ዙፋንህ፡ የዘለዓለም፡ ነው፡ የመንግሥትህ፡ በትርም፡ የቀና፡ በትር፡ ነው። መዝ፡ ፵፭፡

፱ ፮፡ ፯። ጽድቅን፡ ወደድህ፡ ኃጢአትን፡ ጠላህ። ስለዚህም፡ እግዚአብሔር፡ አምላክህ፡ እንደኛ ት፡ ካሉ፡ የሚበልጥ፡ የደስታን፡ ዘይት፡ ቀባህ። ኢሳ፡ ፷፩፡ ፩፡

፲ የሐዋ፡ ፲፡ ፴፰። ዳግመኛም፡ አቤቱ፡ ምድርን፡ አስቀድመህ፡ አንተ፡ ፈጠርካት፡ እሱ፡ ሰማያትም፡ የእጅህ፡ ሥራ፡ ናቸውም፡ መ

፲፩ ዝ፡ ፻፪፡ ፳፭፡ ፳፯። እነሱ፡ ያልፋሉ፡ አንተ፡ ግን፡ ትኖራለህ፡ ሁሉም፡ እንደ፡ ልብስ፡ ያረጃሉ።

፲፪ እንደ፡ መጐናጸፊያም፡ ትጠቀልላቸዋለ፡ ይጠቀለላሉ፡ እነሱ፡ ይለወጣሉ፡ አንተ፡ ግን፡ መቼም፡ መቼ፡ አንተ፡ ነህ፡ ዘመንህም፡ የማይፈጸም፡ ነው። ኢሳ

ሡ፩፡ ፩፡ ራእ. ፯፡ ፲፩፡ ምዕ፡ ፲፫፡ ፳ ፨
፲፫ ከሆነ፡ ጀምሮ፡ ከመላእክት፡ ወ
ግኘ፡ ልጂ፡ በቀኜ፡ ተቀመጥ፡ ያለ
ው፡ ማነው፡ ጠላቶችህን፡ ከእግ
ርህ፡ በታች፡ ከጫማህ፡ እስክዋሳ
፲፬ ቸው፡ ድረስ ፨ መላእክቱማ፡ የ
ዘለዓለም፡ ሕይወትን፡ ሊወርሱ
ዘንድ፡ ስለ፡ ለላቸው፡ የሚላኩ
መንፈስ፡ አይደሉምን ፨ ዘፍ፡ ፲፰
፩፡ ፯፡ መዝ ሡ፩፡ ፳፡ ፯ ፭፡ ፲፮ ፨

ምዕራፍ፡ ፪ ።

የሚመጣውን፡ ዓለም፡ ለመላእክት፡ እንዳላስገ
ዛ፡ የነሣውን፡ ባሕርይ፡ ከአደም፡ ባሕርይ፡ ነሣ፡ እንጂ
ከመላእክት፡ ባሕርይ፡ እንዳልነሣው —

፩ ስለዚህም፡ ይህን፡ የሰማነ፡ እኛ፡
እጅግ፡ ልንጠበቅ፡ ይገባል፡ እንደ
ዳንወድቅም፡ ቸል፡ አንበል፡
፪ የተናገረውም፡ ስለ፡ መላእክት
ቢሆን፡ በጸና፡ በተረዳም፡ ነበር
ሰምቶ፡ የተላለፈውንም፡ ለል
ቃዘዝም፡ ያለውም፡ በሚገባ፡
በተፈረደበት፡ ነበር ፨ የሐዋ፡ ፯
፫ ፶፫፡ ገላ፡ ፫፡ ፲፱ ፨ አስቀድማ፡ በጌ
ታችን፡ ዘንድ፡ የተነገረችውን
ከሱም፡ ቃሉ፡ ከሰሙ፡ ሰዎች፡ በ
ኛ፡ ዘንድ፡ የተረዳችውን፡ ይህን
ያህል፡ ሕይወት፡ ያገኘንበትን
ሐማ፡ ቸል፡ ብለን፡ ብንገኝ፡ እኛ
ከፍርድ፡ እንዴት፡ እናመልጣ
ለን ፨ ም ፲፡ ፳፩፡ ና ፲፬፡ ፳፭፡ ዮሐ ፲፭፡

፬ ፳፮፡ ፳፯ ፨ እግዚአብሔር፡ እየመ
ሰከረላቸው፡ ነገራቸውንም
በእጃቸው፡ ሰይ፡ በሚደረግ፡
ድንቅ፡ ተአምራትና፡ ልዩ፡ ልዩ
በሚሆን፡ ብዙ፡ ኃይል፡ እያደ
ረሳቸው ፨ እሱ፡ ስለወደደ፡ መ
ንፈስ፡ ቅዱስ፡ እንደ፡ አደሳቸው
መጠን ፨ ማር፡ ፲፮፡ ፳፡ ፩ ቆሮ፡ ፲፪፡
፭ ፬፡ ፲፮ ፨ ስለርሱ፡ የምናገረውን
የሚመጣውን፡ ዓለም፡ እግዚ
አብሔር፡ ለመላእክት፡ ያስገዛ
፮ አይደለም ፨ ሰውን፡ ታስበው
ዘንድ፡ የሰውንም፡ ልጅ፡ ትጐ
በኘው፡ ዘንድ፡ ምንድነው፡ ብሎ
መጽሐፍ፡ እንደ፡ ተናገረ ፨ መዝ
፯ ፰፡ ፭ ፨ ከመላእክት፡ ጥቂት፡ አሳ
ነስከው፡ ክብርን፡ ምስጋናን፡ አ
ክሊል፡ አደረግህለት ፨ በእጅህ፡
ም፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ ሾምኸው ፨ ሁሉ
ንም፡ በእግሩ፡ በታች፡ አድርግ
፰ ህ፡ አስገዛህለት ፨ ሁሉንም፡ አ
ስገዛህለት፡ ማለቱ፡ ሳያስገዛ
ለት፡ ለሳልኖረሰው ፨ ዛሬ፡ ግን፡ ሁ
ሉ፡ እንደ፡ ተገዛለት፡ አናውቅ
፱ ም ፨ ጥሳ፡ ፫፡ ፫፡ ፬ ፨ ከመላእክት
ጥቂት፡ ያሳነሰው፡ ስለ፡ ሕማሙ
ና፡ ስለሞቱ፡ ክብርና፡ ምስጋ
ናን፡ አክሊል፡ ያደረገለት፡ እነሆ
ኢየሱስ፡ እንደሆነ፡ እናውቃለ
ን፡ በእግዚአብሔር፡ ጸጋ፡ ስለሁ
ሉ፡ ሞትን፡ ቀምሷልና ፨ ፊል፡ ፪ ፰

፱፡፬ ቆሮ፡፰፡፲፬፡፩፡ዮሐ፡፬፡፬።

፲ ሁሉ፡በእጁ፡ስሆነ፡ሁሉ፡ከሱ፡ለተገኘ፡ብዙ፡ልጆችንም፡ወደ፡ክብር፡ለገባ፡ለርሱ፡ይገባዋልና፡የሕይወታቸውን፡አለቃ፡በሕማም፡ይፈጽመው፡ዘንድ፤ሮሜ፡፲፩፡፴፮፡ሚል፡፬፡፲፫፡ም፰፡፳፡፱

፲፩ እነርሱን፡ያከበራቸው፡እሱና፡የከበሩ፡እነርሱ፡በአንድነት፡ከገድ፡ተገኝተዋልና፡ስለዚህም፡ወንድሞቼ፡ሊላቸው፡አያፍርም፤ዮሐ፡፲፯፡፲፱፡ሉቃ፡፫፡፴፰፡ማር፡፫፡፴፭፡ዮሐ፡፳፡፲፯፤

፲፪ ስምህን፡ለወንድሞቼ፡አነግራቸዋለሁ፡በማኅበር፡መካከል፡እመሰግንሃለሁ፡አለ፤፳፩፡፳፪

፲፫ ደግሞም፡እነሆ፡እኔና፡እግዚአብሔር፡የሰጠኝ፡ልጆች፡አንድ፡ነኝ፡አለ፤ደግመኛም፡እምነበታለሁ፡አለ፤ኢሳ፡፰፡፲፰፡ኢሳ፡፰

፲፬ ፲፰ ልጆቹ፡በሥጋና፡በደም፡ተጋናኝተዋልና፡እሱም፡በዚህ፡ተጋናኛቸው፤እንደ፡ባልንጀራም፡ሆነላቸው፡በሞቱ፡የሞትን፡አለቃ፡ይሽረው፡ዘንድ፤ይኸውም፡ሰይጣን፡ነው፤ሮሜ፡፳፡፫፡፩ጢሞ፡፩፡፲፡ዮሐ፡፲፪፡፲፩፤

፲፭ በሕይወታቸውም፡ዘመናቸው፡ሁሉ፡ሞትን፡በመፍራት፡ለሰይጣን፡ባርነት፡ተገዝተው፡የነበሩትን፡ሁሉ፡ያስርፋቸው፡ዘንድ።ሉቃ፡፩፡፸፩፡ገላ፡፭፡፲፰፤

፲፮ የነሣው፡አካል፡ከአብርሃም፡ዘር፡ነው፡እንጂ፡ከመላእክት፡የነሣው፡አይደለምና፤

፲፯ ስለዚህ፡ወንድሞቹን፡በሁሉ፡ይመስላቸው፡ዘንድ፡ይገባል፡የሕዝቡን፡ኃጢአት፡ለማስተሥረይ፡በእግዚአብሔር፡ዘንድ፡የታመነ፡አዛኝ፡ሊቀ፡ካህናት፡ይሆናቸው፡ዘንድም፡፬፡፲፭፡ፊል፡፪፡፯፤

፲፰ በተፈታተኑት፡መከራም፡ባመጡበት፡ገንዘብ፡በመከራ፡የነበሩትን፡ሊረዳቸው፡ተቻሎታልና።

ምዕራፍ፡፫። ክፍል፡፬

ሊቀ፡ካህናት፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስዋስዋ፡አብነት፡አድርጎት፡እንዲላቸው፡ሙሴ፡፩ልን፡ሥጋዊ፡ምግብ፡በመመገብ፡የታመነ፡እንደሆነ፡ክርስቶስም፡መንፈሳዊውን፡ምግብ፡ለምእመናን፡በመመገብ፡የታመነ፡የባሕርይ፡አምላክ፡እንደሆነ

፩ ዘሬ፡በሰማያዊ፡መጠራት፡የተጠራችሁ፡ቅዱሳን፡ወንድሞቻችን፡እሱን፡ብቻ፡የምታምኑት፡የክህነት፡አለቃ፡ሐዋርያችሁ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ተመልከቱት፤ሮም፡፬፡፲፭፡ም፩፡፲፬፤

፪ ሙሴ፡በቤቱ፡ሁሉ፡ሳይ፡የታመነ፡እንደሆነ፡እርሱም፡ለሾመው፡የታመነ፡እውነተኛ፡ነው፤

፫ ነገር፡ግን፡ክብሩ፡ከሙሴ፡ክ

፬ ብር፡እጅግ፡ይበልጣል፡ከቤቱ፡የባለቤቱ፡ክብር፡እንዲበልጥ፡ቤትን፡ሁሉ፡ይሠራዋልና።

ሁሉን፡ ዓን፡ የሠራ፡ እግዚአብ
፭ ሔር፡ ነው። ሙሴ፡ ሹም፡ እንደ
መሆኑ፡ በቤቱ፡ ሁሉ፡ ሳይ፡ የታ
መነ፡ ነው፡ በሱ፡ ቃል፡ ይነገር፡ ዘ
ንድ፡ ባለው፡ በተናገረው፡ ነገር
ሁሉ፡ ምስክር፡ ይሆነው፡ ዘንድ፡
፮ ክርስቶስ፡ ግን፡ ልጅ፡ እንደ፡ መ
ሆኑ፡ በቤቱ፡ የታመነ፡ ነው፡ ቤቱ
ም፡ ያመነበት፡ እኛ፡ ነን፡ የምና
መካበትን፡ ሃይማኖት፡ ብንጠ
ብቅ፡ ፍጻሜ፡ የሌለው፡ ተስፋ
ችን፡ ይጠብቀናልና። ሊፈ፡ ፬ ፳፬
፯ ም ፯፡ ፲፬። መንፈስ፡ ቅዱስ፡ እንዲ
ህ፡ ብሏልና፡ ዛሬ፡ ቃሉን፡ ብትሰ
ሙ፡ ልባችሁን፡ አታጽኑ። መዝ፡
፰ ፺፬፡ ፯። በገዳም፡ በተፈታተ
፱ ኑበት፡ ቀን፡ እንደ፡ ሳዘኑት፡ የፈ
ተኑኝ፡ አባቶቻችሁ፡ በፈተኑኝ
ጊዜ፡ አርባ፡ ዓመት፡ ሥራዬን፡ እ
፲ ዩ። ዘፀ፡ ፲፯፡ ፯። ስለዚህ፡ እስህ
ን፡ ትውልድ፡ ተቈጣኋቸው፡ ሁ
ለጊዜ፡ ልባቸው፡ ይስታል፡ አልሁ
እነሱ፡ ግን፡ ምንገዴን፡ አላወቁ
፲፩ ም። ወደ፡ ዕረፍቴ፡ እንዳይገቡ
፲፪ ተቈጥቼ፡ እንደ፡ ማልሁ። እናንተ
ይህ፡ ወንድሞቻችን፡ ከናንተ፡
ወገን፡ ባንዱ፡ ሳይ፡ ክፉ፡ አሳብ፡ እ
ንዲገኝ። ሃይማኖት፡ የሌለው
የሚጠራጠር፡ ከሕያው፡ እግዚአ
ብሔር፡ የሚያርቃቸው፡ እን
ደዮር፡ ዕወቁ። ፲፡ ፴፩።

፲፫ በዚህ፡ ግን፡ ዛሬ፡ የሚባል፡ ቀ
ን፡ ሳለ፡ ሁሉ፡ ለጊዜ፡ ራሳችሁን፡ መ
ርምሩ፡ ከናንተ፡ ወገን፡ ማንኛ
ም፡ በኃጢአት፡ ስሕተት፡ እንዳ
ይጸና። ተሰ፡ ፲፮፡ ዘፍ፡ ፫፡ ፲፫።
፫ ሮሜ፡ ፯፡ ፲፩።
፲፬ በዚች፡ ጽድቅ፡ እስከ፡ ፍጻሜ፡
ድረስ፡ የቀደመ፡ ሥራችንን፡ አጽንተ
ን፡ ብንጠብቅ፡ ከክርስቶስ፡ ጋራ
አንድ፡ እንሆናለንና። ፯፡ ፲፬
፲፭ ዛሬ፡ ቃሉን፡ ብትሰሙ፡ እስሱን
ለማሳዘን፡ ልባችሁን፡ አታጽኑ
፲፮ ኑ፡ ብሏልና፡ ሰምተው፡ ያሳ
ዘኑት፡ እነማን፡ ናቸው፡ በሙ
ሴ፡ እጅ፡ ከግብፅ፡ የወጡት፡
፲፯ ሁሉ። አይደሉምን፡ አርባ፡ ዓ
መት፡ የተቈጣኋቸውስ፡ እነ
ማን፡ ናቸው፡ በደለው፡ በምድ
ረ፡ በዳ፡ ሬሳቸው፡ የቀረ፡ አይደ
ለምን። ቈሮ፡ ፲፡ ፲፡ ዘኁ፡ ፲፬፡ ፳፱
፲፰ ወደ፡ ዕረፍቱ፡ እንዳይገቡ፡ በ
ማን፡ ላይ፡ ማለ፡ በማያምኑ፡ ሰ
ዎች፡ ነው፡ እንጂ። መግባት፡ እ
ንደ፡ ልቻሉ፡ ሳቸው፡ እነሆ፡ እናያ
ለን፡ ስለ፡ ማመኑ፡ ምን። ዘኁ፡ ፳፡ ፲፪

ምዕራፍ ፬

ከዋልሰጥሊም፡ ዕረፍተኛ፡ ከሰንበት፡ ዕረፍት፡ የመኖ
ግሥት፡ ለማያት፡ ዕረፍት፡ እንዲበልጥ፡ ሊቀ፡ ካህና
ታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ጸክመን፡ የሠራነውን፡ ኃ
ጢአት፡ ለማስተሠረይ፡ መከራ፡ እንደ፡ ተቀበለ።

፩ እንግዲህ፡ ስንፈራ፡ ትእዛዙን
ም፡ ሳናፍርስ፡ ወደ፡ ዕረፍቱ፡ እ
ንገባ፡ ዘንድ፡ ከናንተ፡ ወገን፡
ልማድ፡ በሚሆን፡ ስሕተት፡ ጸ
፪ ንቶ፡ የሚገኝ፡ ሰው፡ ቢኖር፤ ከ
ናንተ፡ እንዴ፡ ወደ፡ ዕረፍቱ፡ ይገ
ባ፡ ዘንድ፡ የሚተዉት፡ አይምሰ
ለው፤ እነዚያ፡ እንዴ፡ ሰሙ፡ እኛ
ም፡ ሰምተናልና፤ ነገር፡ ግን፡ እ
ነዚያ፡ የሰሙት፡ ቃል፡ አልጠቀ
ማቸውም፡ ከሰሙት፡ ጋራ፡ በ
ሃይማኖት፡ ልባቸው፡ አንድ፡
፫ አልሆነምና፤ እኛስ፡ ወደ፡ ዕረ
ፍቱ፡ እንገባለን፡ አምነናልና
ተቈጥቼ፡ እንዴ፡ ማልሁ፡ ወደ፡
ዕረፍቴ፡ አይገቡም፡ ዘሬ፡ እን
፬ ዴት፡ አስቀድሞ፡ ከተፈጠረ
ጀምሮ፡ የእግዚአብሔር፡ ሥራ
ው፡ ይህ፡ ነው፡ እግዚአብሔር፡ ከ
ሥራው፡ ሁሉ፡ በሰባተኛው፡ ቀ
ን፡ አረፈ፡ ብሎ፡ የሰንበትን፡ ነገ
፭ ር፡ እንዴ፡ ተናገረ፤ ዳግመኛም
ወደ፡ ዕረፍቴ፡ አይገቡም፡ አለ።
፮ ወደዚያ፡ ይገቡ፡ ዘንድ፡ ምንግዱ
ያሳቸው፡ ሰዎች፡ ነበሩና፡ የቀ
ደሙት፡ ግን፡ ሰምተው፡ አልገ
፯ ቡም፡ ከደዋልና፤ የቀደመው
እንደ፡ ተጻፈ፡ ከብዙ፡ ቀን፡ በኋ
ላ፡ በሌላ፡ ቀን፡ ስለማን፡ እንዴህ
አስቀድሞ፡ ዊት፡ ዛሬ፡ ቃሉን፡ ብት
ሰሙ፡ ልባችሁን፡ አታጽኑ፡ ብ

፰ ሏልና፡ ኢየሱስ፡ አሳርፍዋቸ
ው፡ ኖሮ፡ ቢሆን፡ ከዚያ፡ ቀን፡ በ
ኋላ፡ ስለሌላ፡ ባልተናገረም።
፱ ነበር፤ የእግዚአብሔር፡ ወገኖ
ች፡ የሚገቡበት፡ ጸንቶ፡ የሚ
ኖር፡ ዕረፍት፡ እንዳለ፡ ታወቀ።
፲ ወደ፡ ዕረፍቱ፡ የገባው፡ ከሥራ
ው፡ ሁሉ፡ እነሆ፡ አርፍዋልና፡ እ
ግዚአብሔር፡ ከሥራው፡ ሁሉ
እንደ፡ አረፈ፤ ራእ፡ ፲፬፡ ፲፫፡ ፫፤
፲፩ እንግዲህ፡ ወደ፡ ዕረፍቱ፡ እንገ
ባ፡ ዘንድ፡ እንትጉ፡ ያላመኑ፡ እ
ነዚያ፡ እንዴ፡ ወደቁ፡ እንዳንወድ
፲፪ ቅ፤ የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ የጸ
ና፡ ሕያው፡ ነውና፤ ሁለቱ፡
ከሆነ፡ ሰይፍ፡ ይልቅ፡ የተሳለ፡ ነ
ው፡ ነፍስን፡ ከመንፈስ፡ ይለያል
ጅማትንም፡ ከአካል፡ ይለያል
ልቡናም፡ ያሰበውን፡ የወደደ
ውን፡ የመከረውንም፡ ይመረ
፲፫ ምራል፤ በፊቱ፡ የተገለጠ፡ ሳ
ይሆን፡ የተፈጠረ፡ የለም። ሁሉ
በዓይኑ፡ ፊት፡ የተገለጸና፡ የተ
ዘረጋ፡ ነው፡ እንጂ፤ ስለ፡ ሠራነ
ውም፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ ለሱ፡ እንመ
ልሳለን፤ ክፍል፡ ፫ ፲
፲፬ ወደ፡ ሰማይ፡ የወጣ፡ እግዚአብሔ
ር፡ ልጅ፡ ታላቅ፡ የካህናት፡ አለቃ
ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ አለን፡ እንግ
ዲህ፡ በሱ፡ ማመናችን፡ እናጽና፤
፲፭ ሊቀ፡ ካህናታችን፡ ለድካማችን

መከራ፡ መቀበል፡ የማይችል
አይደለምና፡ ከኃጢአት፡ ብ
ቻ፡ በቀር፡ በኛ፡ አምሳል፡ ሁሉ፡
የተፈተነ፡ ነው፡ እንጂ። ም ፳፬
ምዕ ፪፡ ፲፯፡ ፲፰፡ ምዕ ፯፡ ፳፯።

፲፮ እንግዲህ፡ በባለሟልነት፡ ወ
ደ፡ ጸጋው፡ ዙፋን፡ እንቀረብ፡ ይ
ቀርታውን፡ እንቀበል፡ ዘንድ፡
ጸጋውንም፡ እናገኝ፡ ዘንድ፡ በ
መከራችን፡ ጊዜ፡ ረዳት፡ ሲሆነን
ዘፀ፡ ፳፭፡ ፲፯፡ መዝ፡ ፵፪፡ ፳፡ ፯።

ምዕራፍ፡ ፭ ፲

ሊቀ፡ ካህናት፡ ሁሉ፡ ከሰው፡ ወገን፡ እንዲመረጥ፡ ስለ
ሰውም፡ እንዲሾም— እግዚአብሔር፡ የመረጠው፡
ነው፡ እንጂ፡ ራሱን፡ ያመሰገነ፡ ራሱን፡ የመረጠ፡
ሊቀ፡ ካህናት፡ እንዳይሆን—

፩ የካህናት፡ አለቃ፡ ሁሉ፡ ከሰው፡
ወገን፡ ይመረጣል፡ ስለ፡ ሰውም፡
እግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ይሾማ
ል፡ ስለ፡ ኃጢአት፡ የሚያገቡ ት
ን፡ ቍርባንና፡ መሥዋዕት፡ ያቀር

፪ ብ፡ ዘንድ። ም ፰፡ ፫። ጥቂት፡ መ
ከራ፡ ይቀበላል፡ በስንፍናቸው
ከሳቱ፡ ሰዎች፡ ጋራ፡ መከራ፡ ሊ
ቀበል፡ ይችላልና፡ እርሱም፡ የ

፫ ደከመ፡ ስለሆነ። ምዕ ፯፡ ፳፰። ስለ
ዚህም፡ ስለ፡ ሕዝቡ፡ ኃጢአት፡
መሥዋዕት፡ እንደሚያቀርብ፡ ስለ
ራሱም፡ መሥዋዕት፡ ማቅረብ
ይገባዋል። ዘሌ፡ ፱፡ ፯፡ ፲፯።

፬ ለራሱም፡ ክብርን፡ የሚወስድ
የለም፡ እግዚአብሔር፡ ብቻ፡
እንደ፡ አሮን፡ የጠራው፡ ነው፡ እ

፭ ንጂ። ዘፀ፡ ፳፰፡ ፩። ክርስቶስም
እንደዚሁ፡ የካህናት፡ አለቃ፡ ይ
ሆን፡ ዘንድ፡ ራሱን፡ ያመሰገነ፡ አ
ይደለም፡ አንተ፡ ልጄ፡ ነህ፡ እኔም
ዛሬ፡ ወለድሁህ፡ ያለው፡ እሱው
አመሰገነው፡ እንጂ። መዝ፡ ፪፡ ፯

፮ ደግመኛም፡ እንደ፡ መልከ፡ ጼዴ
ቅ፡ ባለ፡ ሹመት፡ ያለም፡ ካህን፡ አ
ንተ፡ ነህ፡ አለው። ዘፍ፡ ፲፬፡ ፲፰።

፯ መዝ፡ ፻፲፡ ፬። በሥጋው፡ ወራት
በነበረ፡ ጊዜ፡ ጸሎትንና፡ ልመና
ን፡ በታላቅ፡ ጩኸትና፡ ዕንባ፡ ከ
ሞት፡ ሊያድነው፡ ወደሚችል፡
አቀረበ፡ እውነተኛ፡ ልመናው
ንም፡ ሰማው። ሉቃ፡ ፳፪፡ ፵፬፡

፰ ልጅ፡ ሆኖ፡ መከራ፡ ስለ ተቀበለ
መታዘዝን፡ ዓወቀ። ፊል፡ ፪፡ ፰፡

፱ መታዘዝን፡ ከፈጸመ፡ በኋላ፡ ለ
ሚታዘዙለት፡ ሁሉ፡ ሕይወት
ን፡ የሚሰጥ፡ የዘላለም፡ መድ
ኃኒት፡ ሆነ። ክፍል፡ ፩።

፲ እግዚአብሔርም፡ እንደ፡ መልከ
ጼዴቅ፡ ሹመት፡ የዘላለም፡ የካ

፲፩ ህናት፡ አለቃ፡ ነው። የዚህም፡
ነገሩ፡ ድንቅ፡ ነው፡ ይተረጕሙ
ት፡ ዘንድ፡ አይቻልም፡ በጆሮአ
ቻሁ፡ ከመስማት፡ ፈዛዛች፡ ሁ

፲፪ ናችኋልና። ካመናችሁ፡ ጀም
ሮ፡ በትምርት፡ ስለዘገያችሁ፡

መምራን፡ ልትሆኑ፡ ሲገባችሁ፡ ግን፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ከመጽሐፍ፡ የሚቀድም፡ የእግዚአብሔርን፡ የነገሩን፡ መጀመሪያ፡ ሊያስተምራችሁ፡ ትወዳላችሁ፡ ወተት ሊጋቷችሁ፡ ትወዳላችሁ፡ የጸናው፡ መብል፡ አይደለም። ፩ቆሮ

፲፫ ፫፡ ፩፡ ፪። ወተት፡ የሚጋት፡ ሁሉ፡ ሕፃን፡ ነውና፡ የእውነትንም፡ ነገር፡ ሊያውቅ፡ አይሻም። ኤፌ፡ ፬

፲፬ ፲፬። የጸና፡ መብልስ፡ መልካሙንና፡ ክፉውን፡ በሚለይ፡ ግንዛብ መመራመርን፡ ለለመዱ፡ ለሽማግሌ፡ ነው።

ምዕራፍ፡ ፮።

ከዚህም፡ ትምርቱ፡ ይለወጥልን፡ ሃይማኖቱ፡ ያው፡ ይሁንልን፡ ስለ ሉ፡ ሌሉ፡ መምር፡ ሌሉ፡ መሠረት፡ ስትፈልጉ፡ ብሎ፡ እንዲ፡ መከራቸው —

፩ ስለዚህም፡ የክርስቶስን፡ የነገሩን፡ መጀመርያ፡ ትተን፡ ወደ፡ ፍጻሜ፡ እንሒድ። እንግዲህ፡ ደግሞ፡ ሌላ፡ መሠረት፡ እንደ ትሹ፡ ዕወቁ፡ ከሞተ፡ ሥራ፡ የእግዚአብሔርን፡ ሐዲስ፡ ሃይማኖት፡ ወደ፡ መማር፡ ተመለሱ፡ ዘንድ። ማቴ

፪ ፬፡ ፲፯። ጥምቀትን፡ እጅ፡ በመጫን፡ መሾምንም፡ የሙታንን፡ ትንሣኤ፡ የዘለዓለምንም፡ ኵነኔ፡ ትማሩ፡ ዘንድ። ሥራ፡ ፲፡ ፰፡ ፳፡ ዘኍ፡ ፰፡ ፲፡ ፲፱።

፫ ይህንም፡ እግዚአብሔር፡ ቢፈቅድ፡ ባደረግነው፡ ነበር፡ የሐዋ፡ ፲፰፥

፬ ፳፩ ፳፩። ነገር፡ ግን፡ ጥምቀትን፡ ከተቀበሉ፡ በኋላ፡ ከሰማይ፡ የሚመጣውንም፡ ጸጋ፡ ከተቀበሉ፡ ከመንፈስም፡ ጋራ፡ አንድ፡ ከሆኑ። ማ

፭ ፲፡ ማ፲ ፪፡ ፩፡ ፪፡ ፪፡ ፫። የእግዚአብሔርንም፡ ትእዛዝ፡ ካወቁ፡ የሚመጣውንም፡ ዓለም፡ ኃይል፡ ካገኙ በኋላ፡ አይቻልም። ማ፡ ፪፡ ፭

፮ ንስሐቸውን፡ ያድሱዋት፡ ዘንድ ዳግመኛ፡ ሊወድቁ፡ አይገባም የእግዚአብሔርን፡ ልጅ፡ ሁለተኛ ይሰቅሉሳቸው፡ ዘንድ፡ ያዋርዱሳቸው፡ ዘንድ፡ አይገባም።

፯ ምድርም፡ በላይ፡ ያወረደውንም፡ ዝናም፡ ብትጠጣ፡ ያንጊዜ፡ ለሰሩ፡ ያረሱባትን፡ መልካሙን፡ ቡቃያ፡ ብቀባለች፡ በረከትንም ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ታገኛለች።

፰ እሾህንና፡ አሜከላን፡ ብታወጣ፡ ግን፡ ለመረገም፡ የቀረበች ናት፡ ፍጻሜዋም፡ ለመቃጠል፡ ይሆናል። ዘፍ፡ ፫፡ ፲፰።

፱ የተመረጣችሁ፡ ወንድሞቻችን እንዲህም፡ ብንናገር፡ ሕይወት ወደለበት፡ ትምርት፡ እንደ፡ ቀረባችሁ፡ እናምናችኋለን።

፲ እግዚአብሔር፡ ሥራችሁን፡ በስሙ፡ የገለጻችሁትን፡ ፍቅራችሁንም፡ ይዘነጋ፡ ዘንድ፡ ዓመፀኛ፡ አይደለም ቅዱሳንን፡ አገልግላችኋቸዋል

ና፡ እንግዲህም፡ ታግሰ ማሳሳች
፲፩ ሁ፡ም፡ ፲፡ ፹፪፡ ፹፩። ነገር፡ ግን፡ ሁ
ላችሁም፡ እስከ፡ ፍጻሜ፡ በዚች፡
ተስፋችሁ፡ ትጋታችሁን፡ ትገል
ጹ፡ ዘንድ፡ እንወዳለን፡ ፊል፡ ፩፡ ፯።
፲፪ እንዳታዝኑ፡ ፌዘዘችም፡ እንዳት
ሆኑ፡ በሃይማኖትና፡ በመታገሥ
ም፡ ተስፋቸውን፡ የወረሱትን፡
ምሰሏቸው። ክፍል፡ ፫፡ ፲፬
፲፫ ለአብርሃምም፡ እግዚአብሔር፥
ተስፋቸውን፡ በነገረው፡ ጊዜ፡ ይም
ልበት፡ ዘንድ፡ ከሱ፡ የሚበልጥ፡
ሌላ፡ ባይኖር፡ በራሱ፡ ማለ፡ ዘፍ፡
፲፬ ፳፪፡ ፲፮፡ ፲፯። መባረክን፡ እባርክ
ኻለሁ፡ ማብዛትንም፡ አበዛሃለ
ሁ፡ አለው። ከዚህም፡ በኋላ፡ ታ
ግሦ፡ ኑሮ፡ ተስፋውን፡ አገኘ።
፲፮ ሰውስ፡ ከሱ፡ በሚበልጥ፡ ይም
ላል፡ የክርክርም፡ መጨረሻ፡
በመሐላ፡ ይረጋል፡ ዘፀ፡ ፳፪፡
፲፯ ፲፩። ስለዚህም፡ እግዚአብሔር
ተስፋውን፡ ለሚወርሱ፡ ሰዎች
ም፡ ከሱ፡ እንዳይለውጥ፡ ይገ
ልጽ፡ ዘንድ፡ ወደደ፡ እንዳይለው
ጥም፡ በመሐላ፡ አጸናው። ዘፍ፡ ፳
፲፯ ፪፡ ፲፮፡ ፲፯። የእግዚአብሔር፡ ቃ
፲፰ ል፡ ሊታበል፡ አይቻልም፤ በሱ፡ ስ
ተማፅነ፡ ተጠብቀን፡ ባለ፡ ተ
ስፋ፡ ማመን፡ ሳፀናን፡ ታላቅ፡ ደ
፲፱ ስቻ፡ አለን። እንደ፡ ነዋወጽ፡ ሰው
ነታችን፡ እንደ፡ ወደብ፡ የምታደ
ናት፡ ዘፀ፡ ፳፪፡ ፹፮፡ ፹፫።
እንደ፡ መልከ፡ ጼዴቅ፡ ሹመት፡ የ
ዘለዓለም፡ የክህነት፡ አለቃ፡ ሁ
ኖ፡ ሐዋርያችን፡ ኢየሱስ፡ ከኛ፡ በ
ፊት፡ ወደ፡ ገባበት፡ መጋረጃ፡ ው
ስጥ፡ የምታገባ። ም፡ ፲፡ ፳፡ ም ፭፡ ፯

ምዕራፍ ፯።

መ ክህነትን፡ ከሌዊ፡ ቤት፡ ለውጦ፡ ለይሁዳ፡ ቤት፡ እንደ ሰጠ፥ ለሚጠየቅ፡ መልከ፡ ጼዴቅን፡ እንደ፡ እነሡ፡ አብርሃም የክህነ ጸጋ ምርኛ፡ ነገሥታት፡ ድል፡ አድርጎ፡ ሲመለስ፡ ሲቀበለው፡ ለመልከ፡ ጼዴቅ፡ ከገንዘቡ፡ ሁሉ፡ ካሥር፡ አንዱ፡ እንደ፡ ሰጠው—

፩ መልከ፡ ጼዴቅ፡ ስ፡ የልዑል፡ የእግ
ዚአብሔር፡ አገልጋይ፡ የሳሌም
ንጉሥ፡ ነው፡ ነገሥታቱን፡ ወጋ
ቸ፡ በተመለሰ፡ ጊዜ፡ አብርሃም፡
ሔዶ ተገናኘው፡ ነው፥ አብርሃም
ም፡ ባረከው፡ ዘፍ፡ ፲፬፡ ፲፰።
፪ አብርሃም፡ ከገንዘቡ፡ ሁሉ፡ ከአ
ሥር፡ አንድ፡ ሰጠው፡ የፊተኛው፡
ስሙ፡ ትርጓሜ፡ የጽድቅ፡ ንጉሥ
ነው፤ ሁለተኛ፡ የሳሌም፡ ንጉሥ፡
ማለት፡ ነው፤ ም ፩፡ ፱፡ መዝ፡ ፸፱፡ ፱
መዝ፡ ፸፪፡ ፪፡ ኢሳ፡ ፱፡ ፯፡ ፯።
፫ አባቱና፡ እናቱን፡ የተናገረለት፡
የለም፡ የዘመኑም፡ ጥንት፡ ፀናዋ
ሩም፡ ፍጻሜ፡ የለውም፡ ከህነቱ
ም፡ በእግዚአብሔር፡ ልጅ፡ አም
ሳል፡ ለዘለዓለም፡ ይኖራል።
፬ ያባቶች፡ አለቃ፡ አብርሃም፡ ከሚ
ሸለው፡ ገንዘብ፡ ሁሉ፡ ካሥር፡ አን
ድ፡ የሰጠውን፡ የሱን፡ ክብሩን፡ ታ

ያላቸውን፡ዘፍ ፲፬፡፳፤

፭ የሌዊስ፡ልጆች፡ከሕዝቡ፡ካሥር አንዱ፡ይቀበሉ፡ዘንድ፡በኦሪት፡የታዘዘ፡ሥራት፡ነበራቸው፡እንደ፡ሕጋቸው፡ሥራት፡ከአብርሃም ወገብ፡ከወጡ፡ከወንድሞቻቸው፡ይቀበሉ፡ነበርና፨ ዘጸ፡፲፬፡፳፯፡፳፰

፮ ዘኍ ፲፰፡፳፩፨ ከወገናቸው፡ሳያደላ፡ለሱ፡ግን፡አብርሃም፡ካሥር አንዱ፡ሰጠው፡እሱም፡ተስፋ፡የተሰጠው፡አብርሃምን፡ባረከው፡ዘፍ ፲፪፡፫፡፯፡፲፬፡፲፱፡፳፨

፯ ነገር፡ግን፡የሚበልጠው፡የሚያንሰውን፡እንዲባርከው፡ያለ፡ጥርጥር፡ይታወቃል፨

፰ በዚህ፡የሚሞቱ፡ሰው፡ካሥር፡አንድ፡ይቀበላሉ፨ በወዲያ፡ግን፡ሕያው፡እንደሆነ፡መጽሐፍ፡የመሰከረለት፡እሱ፡ይቀበላል፨

፱ አብርሃም፡ካሥር፡አንድ፡እንደ፡ሰጠው፡ተነገረ፨ ከአሥር፡አንድ፡የሚቀበል፡ሌዊም፡እሱ፡ስንኳ፡ከአሥር፡አንድ፡ሰጠ፨

፲ መልከ፡ጼዴቅ፡በተገናኘው፡ጊዜ፡ገና፡ባባቱ፡በአብርሃም፡ወገብ፡ነበርና፨

፲፩ እንደ፡ታዘዘ፡ለሕዝቡ፡መሥዋዕት፡በሚያቀርቡ፡በሌዋውያን፡ክህነት፡ፍጸሜ፡ቢሆን፨ ሹመቱ፡እንደ፡መልከ፡ጼዴቅ፡ያለ፡ሌላ፡ካህን፡ይሾም፡ዘንድ፡እንግዲህ፡ለምን፡ይፈለጋል፨ ሹመቱ፡እንደ፡አሮን፡የሆነ፡ባሉነበር፡እንጂ፨ ቍ ፲፰፡፲፱፨

፲፪ ሕጋቸውም፡ክህነታቸውም፡ታልፍ፡ዘንድ፡ነበራቸውና፡ክህነታቸውስ፡ካለፈች፡ሕጋቸውም፡ታልፋለችና፨

፲፫ ሹመቱ፡እንደ፡መልከ፡ጼዴቅ፡ተብሎ፡የተነገረለቱ፡እሱ፡ከወገኑ፡አንድስ፡ስንኳ ምሥዋዕን፡ካልጠበቀ፡ከሌላ፡ወገን፡ተወልዷልና፨

፲፬ ሙሴ፡የክህነትን፡ሹመት፡ስለሱ፡ካልተነገረለት፨ ከይሁዳ፡ወገን፡ጌታችን፨ እንደ፡ተወለደ፡ይህ፡በግልጥ፡ይታወቃል፨

፲፭ ይልቁንም፡ደግሞ፡ይህ፡ያስረዳል፡በመልከ፡ጼዴቅ፡አምሳል፡የተሾመ፡ካህን፡ይነሣል፡ብለዋልና፨

፲፮ የሥጋና፡የደም፡ሥርዓት፡በሚሆን፡ሕግ፡አይደለም፡በማያልቅ፡በሕይወት፡ኃይል፡ነው፡እንጂ፨

፲፯ ሹመቱ፡እንደ፡መልከ፡ጼዴቅ፡ያለ፡ካህን፡አንተ፡ነህ፡ያለው፡ምስክሩ፡ነውና፨

፲፰ ስለ፡ድካምዋ፡በቀደመችው፡ሕግ፡መለዋወዋ፡ነበርና፡ጥቅም፡ስለ፡አልነበራት፨

፲፱ ኦሪት፡ምንምን፡ማደጅ፡አልፈጸመችም፨ ነገር፡ግን፡ስለ፡እርስዋ፡ከርስዋ፡የሚሻል፡ተስፋ፡ገባ፨ በሱም፡እግዚአብሔርን፡እናቀርበዋለን፨

፳ ያለ፡መሐላ፡አልሆነምና፡ያለ፡መሐላ፡የተሾሙ፡ስለነበሩ። በመሐላ፡ለሾመው፡ግን

ተናግሮ፡የማያስቀረው፡እግ
ዚአብሔር፡እንደ፡መልከ፡ጼዴቅ
ሹመት፡ለዘለዓለም፡ካህን፡አንተ፡ነ
፳፪ ህ፡ብሎ፡ማለለት። ኢየሱስ፡ይህ
ን፡ያህል፡በምትሻል፡በምትበ
፳፫ ልጥ፡ሹመት፡ተሾመ፡ብዙ፡የሚ
ሆኑ፡እሊያን፡ካህናትን፡ማን፡ሞ
ት፡ይሽራቸው፡ነበር፡ለዘለዓለ
ም፡ይኖሩ፡ዘንድ፡አያሰናብታ
፳፬ ቸውም፡ነበር። እሱ፡ግን፡ለዘለ
ዓለም፡ይኖራል፡ከህነቱ፡አይ
፳፭ ሽርም፤ በሱ፡በኩል፡ወደ፡እግ
ዚአብሔር፡የሚቀርቡትን፡ሁለ
ጊዜ፡ሊያድናቸው፡ይቻለዋል፡
መቼም፡መች፡ሕያው፡ነውና፡ይ
፳፮ ጸልይላቸዋል። እንደዚህ፡ያለ፡የ
ካህናት፡አለቃ፡ይገባናል፡እውነ
ተኛ፡የዋህ። ከኃጢአትም፡ሁሉ፡
የራቀ፡ንጹሕ፡የሆነ፡ከሰማይ፡በ
፳፯ ላይ፡ያለ። በፊት፡ስለ፡ኃጢአቱ
ኛው፡ኋላ፡ስለ፡ሕዝቡ፡መሥዋ
ዕት፡እንደሚያቀርቡ፡እንደ፡ካ
ህናት፡አለቃ፡ሁለጊዜ፡ሥራ፡የ
ለበትም። እሱ፡ስ፡እንዲህ፡አደረ
ገ፡አንድ፡ጊዜ፡ራሱን፡ሠዋ።
፳፰ ኦሪትስ፡የሚሞተውን፡ሰው፡ለ
ካህናት፡አለቃ፡ትሾም፡ነበር፡ከ
ኦሪት፡በኋላ፡የመጣ፡የመሐላ፡
ቃል፡ግን፡ፍጹም፡ልጅን፡ለዘለ
ዓለም፡ሾመልን። ምዕራፍ፡፰።

የዚህ፡ሁሉ፡ዷግኛ፡ነገሩ፡ሊቀ፡ካህናት፡ኢየሱ
ስ፡ክርስቶስ፡ኃይል፡ባለው፡በአብ፡ቀኝ፡የተ
ቀመጠው፡መቀመጥ፡እንደሆነ፡ሰዎቹንም፡
ሕጉንም፡ነቀፈ፡አዲስ፡ሕግ፡እንደ፡ሠራላቸ
ው —

፩ የዚህ፡ሁሉ፡ዷግኛው፡ነገር፡ሊቀ፡ካ
ህናቶችን፡በሰማይ፡ኃይል፡ባለው
ዙፋን፡ቀኝ፡የተቀመጠው፡ነው
ም፡፬፡፲፬ ቅሉ፡ያይደለ፡እግዚ
አብሔር፡በተከላት፡በጽድቅ፡ድ
ንኳን፡ለቀደሰን፡ሊያገለግላ
፪ ቸው። ኑሮአቸውም፡ሊቀ፡ካህናት
ሁሉ፡መሥዋዕትና፡ቍርባን፡ያ
ቀርብ፡ዘንድ፡ይሾም፡ነበር፡፭፡፩፡
እንዲህ፡ያቀርብ፡ዘንድ፡ሥራው
፫ ነውና። በምድርስ፡የሚኖር፡
ቢሆን፡የካህናት፡አለቃ፡ባልሆነ
ም፡ነበር፡በኦሪት፡ሕግ፡መሥዋ
ዕት፡የሚያቀርቡ፡ካህናት፡በ
፬ ውስጥዋ፡ነበሩና። እነዚያም፡
በሰማይ፡ባለቸው፡ድንኳን፡ለ
ምሳሌ፡የተሠራችውን፡ድንኳ
ን፡የሚያገለግሉ፡ናቸው። ያቸ
ን፡ድንኳን፡እንደ፡ሠራት፡ሰሙ
ሴ፡እንደ፡አሳየው፡ምሳሌዋን
በተራራ፡እንደ፡አየህ፡ሁሉን፡ተ
ሠራ፡ዘንድ፡ዕወቅ፡እንደ፡ሰው፡
ቈሳ፡፬፡፲፯፡ዘፀ፡፳፭፡፵፡ቈ
፭ ዘሬ፡ግን፡የምትሻል፡ማገልገል
ን፡አገኘ። ሰበለጠቸው፡ሥራት፡
ኢየሱስ፡የተመረጠ፡ሆኖ፡የምት
ሻልም፡ስፍራ፡መሠረተ። ምን፡፫፡

፯ ፻፡፹ ፹፡ቁር፡፫፡፯፦የፊተኛ ይ
ቱ ስ፡ነውር፡የሌለባት፡ብትሆ
ን፡ሁለተኛይቱን፡ባልፈለገም
፰ ነበር፨ነገር፡ግን፡እነሱን፡ነቁሮ
ለ፷ል፡ወገኖና፡ለይሁዳ፡ወገን
አዲስ፡ሐጣ፡የምሰራበት፡ዘመ
ን፡ይመጣል፡አለ፡እግዚአብሔ
ር፡ብሎ፦ነቢይ፡ተናገረ፨ኤር፡፴
፱ ፩፡፴፩፡፴፬ ፨ከጣብፅ፡ምድር፡
ባወጣኋቸው፡ጊዜ፡ለአባቶቻ
ቸው፡እንደ፡ሠራሁላቸው፡ሐ
ጣ፡አይደለምቀበኔ፡ኪዳኝ፡እነሱ
አልጸኑምና፡እኔ፡ቸል፡አልኋ
ቸው፡አለ፡እግዚአብሔር፨ዘፀ
፲ ፲፱፡፭፡ሌር፡፲፭፡፩፨ከሌያ፡ወራ
ቶቸ፡በኋላ፡ለ፷ ኤል፡ወገኖቸ፡
የምሠራት፡ሥራት፡ይህቸ፡ና
ት፨ሕጌን፡በልባቸው፡አሰፍ
ረዋለ፡በሐሊናቸውም፡እጽፍ
ዋለሁ፡አለ፡እግዚአብሔር፡እኔ
አምላካቸው፡እሆናለሁ፡እር
ሱም፡ወገኖቼ፡ይሆናሉ፨
፲፩ ፶፩፡፲፫፨እንግዲህ፡እግዚአብ
ሔርን፡ዕወቀ፡ብሎ፡ሰው፡ለወ
ንድሙ፡አያስተምርም፡ትንሹ
ም፡ትልቁም፡ሁሉ፡ያውቁኛል
፲፪ ና፨ኤር፡፱፡፳፬፨ይቀር፡አላቸ
ው፡ኀጢአታቸውንም፡አስተ
ሠርይላቸው፡ዘንድ፡በደላቸ
ውንም፡አላስባቸውም፨
፲፫ እንዲህ፡ብሎ፡መናገሩም፡አዲ
ሱን፡ሐጣ፡ስለ፡ወደደ፡ነው፡የፊ
ተኛይቱ፡አርጅታለችና፡ያረጀ
ው፡ስ፡ዋኝቱን፡ለጥፋት፡የቀረበ
ነው፨ ምዕራፍ፡፱፡ ክፍል፡፳፭

ስለቀደመቸው፡ስለኦሪት፡ድንኳን፡መስዋዕት፡የሚሰዉበት፡መሠርያ
ሁሉ፡እንደ፡ነበራት፡ሊቀ፡ካህናት፡በዓመት፡በዓመት፡የሳምንቱ፡የፍየል
ደም፡አዮዘ፡ይገባ፡እንደ፡ነበረ፦ክርስቶስም፡የራሱን፡ደ
ም፡ይዞ፡ወደ፡መስቀሉ፡ድንኳን፡እንደ፡ገባ—

፩ ለቀደመቸው፡ድንኳን፡የመሠ
፪ ዊያ፡ሥራትና፡መቅደስ፡ነበራት፨ድ
ጅዋ፡የተ ዘጋጀ፡የቀደመቸው
ድንኳን፡መብራት፡የሚበራበት
መቅረዝ፡እንጀራ፡የሚሠራበት
ማዕድም፡ነበራት፨ዘ፬፡፳፭፡፴፫
፴፬፡ዘ፱፡፴፬፡፴፩፨
፫ ቅድስት፡ይልዋት፡ነበር፡ከሁለ
ተኛው፡መጋረጃ፡በኋላ፡ያለቸ
ው፡የውሥጠኛይቱን፡ድንኳ
ን፡ግን፡ቅድስተ፡ቅዱሳን፡ይልዋ
ት፡ነበር፨ዘፀ፡፳፮፡፴፫፨
፬ በውስጥዋም፡የወርቅ፡ማዕጠ
ንት፡ነበራት፡ሁለንተናዋም፡በ
ወርቅ፡የተለበጠ፡ኪዳን፡በው
ስጧ፡ያለባት፡ታቦትም፡ነበረች
የለመለመች፡የአሮን፡በትር
ነበረች፡ኪዳንም፡የተጻፈባ
ቸው፡ጽላቶች፡ነበሩባት፨
ዘፀ፡፴፡፴፬፡፴፯፡ዘፀ፡፲፯፡፵፫፡፱፡
፭ ዘፀ፡፳፭፡፲፡ዘኍ፡፲፯፡፲፨በማሥ
ተስረያውም፡ላይ፡የሚጋርዱ
የክብር፡ኪሩቤል፡ነበሩ፡ነገር

ማን፡ የሠራቱና፡ የጌጡን፡ ነገር፡
እንደምን፡ እንደ፡ ነበረ፡ በየወገኑ
እናገር፡ እናገር፡ ዘንድ፡ ዛሬ፡ ጊዜ
ው፡ አይደለም፨ ዘፀ ፳፭፡ ፲፪፡ ፲፰፡ ና
፮ ፳፪፡ ፴፩ ፨ ወደ፡ ፊተኛይቱ፡ ድንኳ
ን፡ ካህናት፡ ማገልገላቸውን፡ ይ
ፈጽሙ፡ ዘንድ፡ ሁልጊዜ፡ ይገቡ፡ ነ
በር፡ ዘኍ ፲፰፡ ፫፡ ፩፨
፯ ወደ፡ ውስጠኛይቱ፡ ግን፡ ሊቀ፡ ካ
ህናቱ፡ ብቻ፡ ባመት፡ አንድ፡ ጊዜ
ይገባ፡ ነበር፡ ኃጢአታቸውን፡ ለ
ማስተሠረይ፡ ስለ፡ ራሱና፡ ስለ፡
ሕዝቡ፡ የሚያቀርበውን፡ ደም፡
፰ ይዞ፨ ዘፀ፡ ፴፡ ፲፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡
እንዲህ፡ አዝዞ፡ ነበርና፡ በቀደመ
ችው፡ ድንኳን፡ የቅዱሳን፡ ምን
ገድ፡ ገና፡ ስሳልታወቀች፨
፱ ነገር፡ ግን፡ የሚያቀርበውን፡ ፍ
ጹም፡ ማድረግ፡ የማይቻል ሰውን
ቍርባንና፡ መሥዋዕት፡ የሚያ
ቀርቡት፡ ያዘመን፡ ለዚህ፡ ዘመ
፲ ን፡ ምሳሌ፡ ሆነ፨ ከመብላትና፡
ከመጠጣት፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ከሚሆን
ም፡ ጥምቀት፡ በቀር፡ ማደጅ፡ መ
ፈጸም፡ አልተቻላቸውም፨ ያ
ችውም፡ የሥጋ፡ ሕግ፡ ናት፡ የተ
ሠራው፡ ሥራት፡ እስኪቃና፡ ድ
ረስ፨ ዘሌ፡ ፲፩፡ ፲፡ ዘፀ፡ ፳፱፡ ፫ ፩፡ ዜ
ዋ፡ ፫፡ ፳፬፨ ክፍል፡ ፯ ፲
፲፩ ክርስቶስ፡ ግን፡ ለምትመጣው፡
ለበጎይቱ፡ ሥራ፡ የካህናት፡ አለቃ
በሆነ፡ ጊዜ፡ ከቀደመችው፡ ወደ፡
እምትበልጥና፡ ወደ፡ እምትሸ
ለው፡ የሰው፡ እጅ፡ ወደ፡ አልሰ
ራት፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ወደ፡ አለ
ች፡ ድንኳን፡ ገባ፨ ዘሌ፡ ፲፡ ፳፡ ና ፲፡ ፲
፲፪ ፩፡ ም፡ ፳፡ ፳፩ ፨ የላምና፡ የፍየል
ደም፡ ይዞ፡ የገባ፡ አይደለም፡ የ
ራሱን፡ ደም፡ ይዞ፡ የዘለዓለም
ወደምትሆን፡ መቅደስ፡ አንድ
ጊዜ፡ ገባ፡ እንጂ፡ መድኃኒትን
ም፡ አገኘ፨ ዘሌ፡ ፲፮፡ ፫፡ ፲፬፡ የሐ
ዋ፡ ፰፡ ፳፭፡ ኢሳ፡ ፴፪፡ ፲፪ ቀም ፲፫
፲፫ ፳፫፨ የላምና፡ የፍየል፡ ደም፡ የ
ጊደርም፡ ስብ፡ ከኃጢአት፡ የረ
ሚያነፃ፡ የረከሱትንም፡ ሥጋ
ቸውን፡ የሚቀድሳቸው፡ ከሆነ
፲፬ ዘኍ ፲፱፡ ፲፫ ነውር፡ የሌለበት፡ የ
ዘለዓለም፡ መሥዋዕት፡ አድር
ጎ፡ ራሱን፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ለ
እግዚአብሔር፡ የሠዋ፡ የክርስ
ቶስ፡ ደም፡ ማ፡ ይልቁን፡ ሕሊናች
ንን፡ ከሞት፡ ሥራ፡ እንዲቱ፡ ያነ
ፃው፡ ይሆን፡ ሕያው፡ እግዚአብ
ሔርን፡ እናገለግለው፡ ዘንድ፡
ዘሌ፡ ፳፡ ፲፱፡ ፳፡ ፩፡ ጴጥ፡ ፩፡ ፲፱፡ ምዕ ፲፡ ፬
፳፬ ፡ ፩፡ ተሰ ፩፡ ፱፡ ዮሐ፡ ፩፡ ፯፨
፲፭ ስለዚህም፡ ኢየሱስ፡ ለሐዲስ፡
ስርዓት፡ የተመረጠ፡ ሆነ፡ ሞት
ን፡ ቀምሶ፡ በቀደመችው፡ ሥ
ርዓት፡ የሳቱትን፡ ተስፋ፡ ያና
ገረሳቸውን፡ ወደ፡ ዘለዓለም፡

ርስቱም፡የጠራቸው፡ያጸና
ቸው፡ዘንድ፡ነውና ፲፪፡፳፩፡፩ ጢሞ
፬፡፰፡ሮሜ፡፰፡፳፰፡የሐዋ፡፳፯፡፲
፲፯ ፳፫ ሥራት፡ካለ፡ዘንድ፡በሠሪው
ለይ፡ሞት፡ግድ፡ይመጣልና
፲፯ የሚሞት፡ሰው፡ሥራት፡የጸና
ች፡ናትና፤የሠራት፡ሥራት፡በሐ
፲፰ ይወት፡ባለ፡ጊዜ፡አትጠቀምምና፡እንደዚህ
፲፱ ም፡ቀድሞ፡ሥራት፡ያለ፡ደም፡አልነፃችም፡ሙሴ
የኦሪትን፡ትእዛዝ፡ሁሉ፡ለሕዝቡ፡ከነገረ፡በኋላ
የላምና፡የፍየል፡ደም፡ከውሀ፡ጋራ፡ይዞ፡ በ
ዣጕንጕን፡ቀይ፡ሐርና፡በስም
ዕዘ፡ቀጠል፡የኦሪቱን፡መጽሐ
ፍና፡ሕዝቡን፡ሁሉ፡ይረጭ፡ነ
፳ በርና፡እግዚአብሔር፡ያዘዛች
ሁ፡የኪዳን፡ደም፡ይህ፡ነው፡ይላ
፳፩ ቸው፡ነበርና፡ድንኳኑንም፡የ
ሚያገለግሉበትንም፡ዕቃ፡ሁ
ሉ፡ይረጭ፡ነበርና፡ዘሌ፡፰፡፲፡፲፭
፳፪ ፲፱፡እንዲህም፡ደማም፡በቀር
ብ፡ቀን፡ያደርግ፡ነበር፡በኦሪቱ
ሥራት፡ሁሉም፡በደም፡ይነፃ፡
ነበር፡ደም፡ሳይረጭ፡ኃጢ
፳፫ አት፡አይሠረይም፡ነበርና፡በሰ
ማይ፡ድንኳን፡አምሳል፡የተሠ
ራ፡ይህ፡ድንኳን፡በዚህ፡ደም፡የ
ሚነፃ፡ከሆነስ፡ሰማያዊ፡መሥ
ዋዕትማ፡ከዚህ፡የሚሻልና፡የ
ሚበልጥ፡እንዴት፡አይሆንም
፳፬ ኢየሱስ፡የሰው፡እጅ፡ሥራ፡ወደ
ምትሆን፡የጽድቅ፡ምሳሌ፡በመ
ሆን፡ወደ፡ተሠራች፡መቅደስ፡
የገባ፡አይደለም፡ወደ፡ሰማይ
ግባ፡እንጂ፡ስለ፡እኛ፡በእግዚአ
፳፭ ብሔር፡ፊት፡ይታይ፡ዘንድ፤ሁል
ጊዜ፡ራሱን፡የሚሰዋ፡አይደለ
ምና፤የካህናት፡አለቃ፡እንደ፡አ
ሚያደርጋ፡በባዕድ፡ደም፡ባመ
ት፡ባመት፡ወደ፡ቅዱሳንም፡(
፳፮ መቅደስ፡እንደ፡ገባ፤ያስ፡ባይ
ሆን፡ዓለም፡ከተፈጠረ፡ጀምሮ
ብዙ፡ጊዜ፡በሞት፡ነበርና፡በዓለ
ም፡ፍጻሜ፡ዘሬ፡አንድ፡ጊዜ፡ራ
ሱን፡ሠዋ፡እንጂ፡በመሥዋዕት
ነቱ፡ኃጢአትን፡ይሽራት፡ዘንድ
፳፯ ለሰው፡አንድ፡ጊዜ፡ሞት፡እንደ
ተባቀው፡ከዚያ፡በኋላ፡ፍር
፳፰ ድ፡እንደቆየው፡እንደዚሁም፡
ክርስቶስ፡አንድ፡ጊዜ፡ራሱን፡ሠ
ዋ፡የብዙዎችን፡ኃጢአት፡ይቀ
ር፡ይል፡ዘንድ፡ሁለተኛ፡ግን፡ያዳ
ናቸው፡ዘንድ፡ተስፋ፡ለሚያደ
ርጉ፡ያለ፡ኃጢአት፡ይታያቸ
ዋልና፡ምዕ፲፡፲፬፡ኢሳ፡፶፫፡፲፪፡፩ጴጥ
፩፡፲፥ ምዕራፍ፡፲

ኦሪት፡ለወንጌል፡አምሳልና፡መርገፍ፡
እንደሆነች።የላምና፡የፍየል፡ደም።

፩ ኦሪት፡ለምትመጣው፡በጎ፡ሕግ፡
ምሳሌ፡ነበረችና፡ባይነቱ፡ስለ፡
አልሆነች፡ስለዚህም፡ባመት፡በ

መቶ፡ሁለት፡ጊዜ፡ያን፡መሥዕ
ቶ፡ባቀረቡ፡ጊዜ፡እሱ፡ከቶ፡የሚ
ያቀርቡትን፡ይፈጽም፡ዘንድ፡
አይቻለውም፡ነበርና፡ቈላ፡፬፡፲፪
፮ ፲፪። የሚፈጽማቸውስ፡ቢሆ
ን፡ሁለጊዜ፡ከመሥዋዕቱ፡ባረ
ፉ፡ነበርና። ለሚሠዉት፡ሰዎች፡
ኃጢአታቸውን፡ያስተሠርይ
ላቸዋልና፡ባንድ፡ጊዜ፡ያነፃቸ
፯ ው፡ነበርና። በዚያ፡መሥዋዕ፡
ት፡ባመት፡ባመት፡የኃጢአት፡
መታሰቢያ፡የሚያቀርቡት፡ነ
በራቸው፡እንጂ። ዘሌ፡፲፮፡፳፩፡
፰ ሌዋ፡፳፫፡፲፫። የላምና፡የፍየል፡ደ
ም፡ኃጢአት፡ያስተሠርይ፡ዘንድ
አይቻልምና። መዝ፡፵፡፮።
፱ ስለዚህም፡ወደዚህ፡ዓለም፡በ
መጣ፡ጊዜ፡ቍርባንና፡መሥዋ
ዕትን፡አልወደድሁም፡አለ፡ሥ
፲ ጋን፡አለበስከኝ፡እንጂ። ስለ፡ኃ
ጢአት፡የሚቀርበውን፡መሥ
ዕት፡አልወደድሁም። ሚክ፡፮፡
፲፩ ፮። ሁለጊዜ፡እነሆ፡መጣሁ፡አል
ሁ፡የኔ፡ነገር፡በመጽሐፉ፡አርእ
ስቱ፡ተጽፏል፡አምላኬ፡ፈቃ
ድህን፡አደርጋ፡ዘንድ፡መከርሁ
፲፪ በዚህም፡ላይ፡በኦሪቱ፡ሕግ፡ስ
ለኃጢአት፡የሚሠዉትን፡ቍ
ርባንና፡መሥዋዕት፡አልወ
ደድሁም፡ብሎ፡ተናገረ።
፲፫ ከዚህም፡በኋላ፡አምላኬ፡ፈ
ቃድህን፡አደርጋ፡ዘንድ፡እነሆ፡
መጣሁ፡አለ፡ይህ፡ቃል፡የኋለ
ኛውን፡ያፀና፡ዘንድ፡የፊተኛ
፲፬ ውን፡ያፈርስ፡ልቀበሱ፡ፈቃድ
እንድ፡ጊዜ፡በሆነው፡በኢየሱስ
ክርስቶስ፡ሥጋ፡ቍርባንነት፡እኛ
የተቀደስነ፡እንሆን፡ዘንድ።
ም፱፡፲፬፡ቈላ፡፩፡፳፪፡ጲ፡፳፡፲፩
፲፭ የካህናት፡አለቃ፡ሁሉ፡ፈድ
ሞ፡ከኃጢአት፡ማንጻት፡የ
ማይቻላት፡ያችን፡መሥዋዕ
ት፡ይሠዋ፡ዘንድ፡ሁለጊዜ፡ይ
ቆም፡ነበር። ቍ፩፡፲፪፡፲፩።
፲፮ እሱ፡ግን፡ስለኛ፡ኃጢአት፡የሁ
ለጊዜ፡መሥዋዕት፡ራሱን፡እን
ድ፡ጊዜ፡ሠውቶ፡በእግዚአብሔ
ር፡ቀኝ፡ተቀመጠ። ቈ፡፲፡፲፬፡
፲፯ ም፡፩፡፲፫። እንግዲህ፡ጠላ
ቶቹ፡ከእግሩ፡ጫማ፡በታች፡
እስኪወድቁ፡ድረስ፡ይጠብ
፲፰ ቃል፡መዝ፡፻፲፡፩። ለሚቀድ
ሱ፡ሰዎች፡አንዲት፡መሥዋዕ
ት፡ለሁለጊዜ፡አደረገ። ቍ፲
፲፱ ፲፬፡ም፱፡፳፰። ምስክራችንም
መንፈስ፡ቅዱስ፡ነው።
፳ ከዚያ፡ቀን፡በኋላ፡የምሠራላ
ቸው፡ሥራት፡ይህች፡ናት፡ካለ፡
በኋላ፡ሕጌን፡በልቡናቸው፡አሳ
ድረዋለሁ፡በሕሊናቸውም፡
እጽፈዋለሁ፡አለ፡እግዚአብ
ሔር፡ብሎአልና። ኤር፡፴፩፡፴፫።

፲፯ እንግዲህ፡ በደላቸውንና፡ ኃጢ
፲፯ አታቸውን፡ አላስብ፲፰ እንግዲህስ
ኃጢአት፡ የሚሠረይ፡ ከሆነ፡ ኃ
ጢአት፡ ስለ፡ ማስተሥረይ፡ የሚ
ቀርብ፡ ሌላ፡ መሥዋዕት፡ የለም
ኢሳ፡ ፵፫፡ ፳፭፡ ክፍል፡ ፱፲

፲፱ ወንድሞቻችን፡ በኢየሱስ፡ ክር
ስቶስ፡ ደም፡ ወደ፡ ቤተ፡ መቅደስ
ለመግባት፡ ባለሟልነት፡ ስለ
ገኘን፤ ሮ፭፡ ፲፮፡ ኤፌ፡ ፲፰፡ ና ፫፡ ፲፪፤

፳ በሥጋው፡ መጋረጃነት፡ የጽድቅ
ንና፡ የሕይወትን፡ መንገድ፡ አ
ድሶልናልና፤ ፱፡ ፰፡ ዮሐ፡ ፲፬፡

፳፩ ፳፩ ለእግዚአብሔር፡ ቤት፡ ታላ
ቅ፡ አገልጋይ፡ ስላለን፤ ፩፡ ፲፩፡ ፲፪

፳፪ እንግዲህ፡ በውነተኛ፡ ልብና፡ በ
ታመነ፡ ፍጹም፡ ሃይማኖት፡ እን
ቅረብ፡ ልቡናችን፡ ንጹሕ፡ ሁኖ፡
እኛም፡ ከክፉ፡ ሥራ፡ ንጹሕን፡ ሁ
ነን፡ ሥጋችንም፡ በጹሩ፡ ውሀ፡ የ
ታጠበ፡ ሁኖ፤ ሮም ፲፡ ፲፪፡ ሕዝ፡ ፴፮፡
፳፭፡ ቲቶ፡ ፫፡ ፭፤

፳፫ እንግዲህ፡ ያለጥርጥር፡ ሃይማ
ኖታችንን፡ ተስፋችንን፡ እናጽ
ና፡ ተስፋ፡ የሰጠን፡ እሱ፡ የታመነ
ነውና፤ ፬፡ ፲፬፡ ፲፮፡ ፲፬፤

፳፬ በፍቅርና፡ በበጎ፡ ሥራ፡ ከባልንጀ
ራችን፡ ጋራ፡ እንፈካከር፤ ሮም ፲፪፡

፳፭ ፩፡ ዮሐ፡ ፲፫፡ ፴፩፤ እንድነታችንን
ም፡ አንተው፡ ሌሎች፡ እንደ፡ ለመ
ዱ፡ አስ፡ በሳችን፡ እንድናና፡ እንጂ
ያቀኝ፡ እንደ፡ ቀረበ፡ እናውቃለ
ንና፤ ሮ፲፫፡ ፩፡ ተሰ፡ ፭፡ ፮፡ ፲፤

፳፮ ጽድቅን፡ ካወቅናት፡ በሥራ፡ ሆ
ን በድል፡ ኃጢአት፡ ለማስተሥ
ረይ፡ ሁለተኛ፡ መሥዋዕት፡ የለ
ምና፤ ምዕ፡ ፮፡ ፮፡ ዘኁ፡ ፲፭፡ ፴፤

፳፯ የሚያስፈራ፡ ፍርድ፡ የሚከ
ጸትንም፡ የሚያቃጥል፡ የፍር
ድ፡ እሳት፡ ይቈየናል፡ እንጂ፤ ም
፱፡ ፳፯፡ ዘዳ፡ ፴፪፡ ፳፪፡ ሶፎ፡ ፩፡ ፲፰
ሰዉ፡ ፩፡ ፲፰፤

፳፰ የሙሴን፡ ሕግ፡ የተላለፈ፡ ቢኖ
ር፡ ሁለት፡ ወይም፡ ሦስት፡ ሰዎች
ከመሰከሩበት፡ በኋላ፡ ያለ፡ ምሕ
ረት፡ ይሞታል፤ ዘኁ፡ ፲፭፡ ፴፡ ዘ

፳፱ ዳ፡ ፲፯፡ ፲፯፤ ይልቁንም፡ ከእግዚአብሔ
ር፡ ልጅ፡ ጋራ፡ ተጣምሶ
የከበረበትን፡ የኪዳን፡ ደም፡ አ
ንደ፡ ሰው፡ ደም፡ አድርጎ፡ ያ ዋረ
ዱ፡ የስጦታውንም፡ መንፈስ፡ የ
ሰደበ፡ ይፈረድበት፡ ዘንድ፡ እንደ
ምን፡ ይገባው፡ ይመስላችኋል፤ ፩፡ ፮
ዮሐ፡ ፲፫፡ ፲፰፡ ፩፡ ቆሮ፡ ፲፩፡ ፳፱፡ ኦ፡ ፲—

፴ ማቴ፡ ፲፪፡ ፴፩፤ እግዚአብሔር፡ እኔ
እበቀላለሁ፡ ፍዳውንም፡ እከ
ፍላለሁ፡ አለ፡ ያለውን፡ እናውቃ
ለንና፡ ደግሞም፡ እግዚአብሔር
በወገኖቹ፡ ይፈርዳል፡ ብሏልና፤
ዘዳ፡ ፴፪፡ ፴፭፡ ፴፮፡ መዝ፡ ፻፴፭፡ ፲፬።

፴፩ በሕያው፡ እግዚአብሔር፡ እጅ
መውደቅ፡ እጅግ፡ ጭንቅ፡ ነው።

፴፪ ባጠመቋችሁ፡ ጊዜ፡ የነበራችሁበትን፡ የቀደመውን፡ ዘመን፡ አስቡ፡ ብዙ፡ መከራ፡ ታግሣችሁ፡ እንደ፡ ነበረ፥ ፊል፡ ፩፡ ፳፱፡ ፩ተሰ፡ ፪፡
፴፫ ፴፬ቀይ ስድብዋችሁ፡ መከራ፡ ያፀቶባችሁ፡ ይዘብቁባችሁ፡ እንደ፡ ነበረ፥ በዚህም፡ ምኞንዱ፡ ከሐዱት፡ ጋራ፡ እንዱ፡ ሁናችሁ፡ ነበር
፴፬ ከእኔም፡ ጋራ፡ በእሥራቴ፡ ሳለሁ በተቀበልሁት፡ መከራ፡ ደስ፡ ብሏችሁ፡ በተቀበላችሁትም፡ በገንዘባችሁ፡ መዘረፍ፡ እንዱ፡ ሁናችሁ፡ ነበር፥ በሰማይ፡ ለዘለዓለም፡ የሚኖር፡ የበለጠ፡ ገንዘብ፡ እንዳላችሁ፡ ታውቃላችሁና ማቴ ፮፡ ፳፡ ሉቃ፡ ፲፪፡ ፴፫ ፦
፴፭ እንግዲህ፡ ብዙ፡ ዋጋ፡ የምታገኙበትን፡ ሃይማኖታችሁን፡ አትተዉ፥ ም፲፩፡ ፳፮፥
፴፮ ነገር፡ ግን፡ እግዚአብሔር፡ የሚወደውን፡ ሠርታችሁ፡ ተስፋችሁን፡ ታገኙ፡ ዘንድ፡ መታገሥ፡ ያሻችኋል፥ ሉ ፳፩፡ ፲፱፥
፴፯ እንግዲህ፡ ቀኑ፡ ጥቂት፡ ነውና፡ የሚመጣውም፡ ሳይዘገይ፡ ይደርሳል፥ ሐጌ፡ ፪፡ ፮፡ ዕን፡ ፪፡ ፫፡
፴፰ ፬፥ ጻድቅ፡ ሰው፡ ግን፡ በሃይማኖት፡ ይድናል። ወደ ኋላ፡ ቢመለስ፡ ግን፡ ልቡናዬ፡ አይወደውም፥
፴፱ ዕን፡ ፪፡ ፬፥ እኛ፡ ግን፡ ለጥፋት፡ ወደ፡ ኋላ፡ መመለስ፡ አይገባንም፡ የነፍሳችን፡ ሕይወት፡ ወደእምትሆን፡ ሃይማኖት፡ እንሔዳለን፡ እንጂ፥ ኢሳ፡ ፳፰፡ ፲፯፡ ፩ዱ ፩፱፥

ምዕራፍ፡ ፲፩። ክፍል፡ ፲፰

ሃይማኖት፡ ለሚያምንባት፡ ሰው፡ የተረዳች እንደ፡ ሆነች፡ ለማስረዳት፡ ስለአቤል፡ ስለሄኖክ፡ በሃይማኖት፡ የተደረገላቸውን፡ እንዴ፡ ተናገረ —

፩ ሃይማኖትስ፡ ተስፋ፡ ለሚያደርጋት፡ የተረዳች፡ ናት፡ የማይታየውን፡ ገንዘብ፡ ተስፋ፡ አድርገው፡ ያመኑ፡ ነበሩ፥ ም፡ ፲፡ ሮ፫፡ ዮሐ፡ ፳፡ ፳፱
፪ ሮሜ፡ ፩፡ ፲፯፥ ስለዚህም፡ በሃይማኖት፡ የቀደሙት፡ ምስክር፡ ሆኑ፥
፫ ዓለሙም፡ በእግዚአብሔር ቃል፡ እንዲ፡ ተፈጠረ፡ ባለ፡ መኖር ምንም፡ አይታይ፡ የነበረም፡ ወደ መኖር፡ መምጣቱ፡ እንዲ፡ ታየ፡ እናውቃለን፥ ም፡ ፩፡ ፬፡ መዝ፡ ፴፫፡ ፮
፬ ቃየል፡ ለእግዚአብሔር፡ ካቀረበው፡ መሥዋዕት፡ አቤል፡ ያቀረበው፡ መሥዋዕት፡ ተሻለ፥ ጻድቅም፡ እንደሆነ፡ ስለሱ፡ መሰከረለት፥ ምስክሩም፡ መሥዋዕቱን፡ በመቀበሉ፡ እግዚአብሔር ነው፥ ስለዚህም፡ ከሞተ፡ በኋላ፡ ዳግመኛ፡ ተናገረ፥ ዘፍ፡ ፬፡ ፱፡
፭ ፳፡ ፲፡ ም ፲፪፡ ፳፬፥ ሄኖክ፡ ሞትን፡ እንዳያየው፡ በሃይማኖት፡ ከዚህ፡ ዓለም፡ ወጣ፡ ለሞትም፡ አልተገኘም፡ እግዚአብሔር፡ ሠውሮ

ታልና፡ ከዚህ፡ ዓለም፡ ሳያወጣ
ውም፡ እግዚአብሔር፡ እንዲገ
ለገለው፡ መስክረለት፥ ዘፍ፡ ፭፡
፮ ፳፬፡ ዮሐ፡ ፳፡ ፶፩፥ ያለ፡ ሃይማኖ
ት፡ እግዚአብሔርን፡ ሊያገለ
ግሉት፡ አይቻልም፡ ወደ፡ እግዚ
አብሔር፡ የሚቀርብ፡ አስቀድ
ሞ፡ ሊያምን፡ ለሚሹት፡ ሰዎች
ም፡ የሚሰጣቸው፡ ዋጋ፡ እንዳለ
ሊያውቅ፡ ይገባዋልና፨ ኤር፡ ፳፱፡
ሮሜ፡ ፲፬፡ ፳፫፤ አሞ፡ ፭፡ ፬፤ ሚል፡ ፫፡ ፯፡
፯ ፲፯፨ የማይታየውን፡ የተወረ
ውን፡ ነገር፡ በነገሩት፡ ጊዜ፡ ኖኅ
እምነት፡ ፈራ፨ ዓለም፡ በተቀጣ
ጊዜ፡ ወገኖቹን፡ ያድን፡ ዘንድ፡ ክ
ፍል፡ ያለው፡ መርከብ፡ ሠራ፡ በ
ሃይማኖት፡ የሚገኘውንም፥
ጽድቅ፡ ወራሹ፡ ሆነ፨ ዘፍ፡ ፯፡ ፩፥
ሮሜ፡ ፫፡ ፳፪፡ ፳፩፡ ና ፬፡ ፳፩፨
፰ አብርሃም፡ በተጠራ፡ ጊዜ፡ ርስት
አድርጎ፡ ይወርሰው፡ ዘንድ፡ ወደ
ለው፡ አገር፡ ለመሔድ፡ አምኖ፡
ታዘዘ፡ የሚደርስበትንም፡ ሳያ
፱ ውቅ፡ ሔደ፨ ዘፍ፡ ፲፪፡ ፬፨ በሔደበ
ትም፡ አገር፡ የሰጠውን፡ ተስፋ፡
አምኖ፡ ተስፋውን፡ ከሚወርሱ
ከይስሐቅና፡ ከያዕቆብ፡ ጋራ፡
እንደ፡ ስደተኛ፡ በድንኳን፡ ኖረ
፲ ዘፍ፡ ፲፯፡ ፮፡ ና ፲፬፡ ፲፱፨ ብልሃተኛ፡
ሠሪዋ፡ እግዚአብሔር፡ የሚሆ
ን፡ መሠረት፡ ያላትን፡ አገር፡ ደጅ

ይጠኑ፡ ነበርና፨ ምዕ፡ ፲፪፡ ፳፪፡ ኢሳ
፲፩ ፷፭፡ ፲፯፨ ሳራም፡ መካን፡ ስትሆ
ን፡ በእርጅናዋ፡ ጊዜ፡ ልጅ፡ ትወል
ድ፡ ዘንድ፡ በሃይማኖት፡ ኃይል፡
አገኘች፨ ተስፋ፡ የሰጣት፡ እሱ
እውነተኛ፡ እንደሆነ፡ አምነዋ
ለችና፨ ዘፍ፡ ፳፩፡ ፪፨
፲፪ የሁለቱም፡ ሰውነታቸው፡ እን
ደ፡ ሞተ፡ ሁኖ፡ ሳለ፡ ብዛታቸው፡
እንደ፡ ሰማይ፡ ኮከብና፡ እንደ፡ ባ
ህር፡ አሸዋ፡ የማይቈጠር፡ ይሆ
ን፡ ዘንድ፨ ሮሜ፡ ፬፡ ፲፱፡ ዘፍ፡ ፲፭፡ ፭
፲፫ ና ፳፪፡ ፲፯፨ እሊህ፡ ሁሉ፡ አምነው፡
ሞቱ፡ ተስፋቸውን፡ ግን፡ አላገኙ
ም፡፡ ከሩቅ፡ አይተው፡ እጅ፡ ነሡት
እንጂ፨ በምድር፡ ላይ፡ ስደተኞ
ች፡ መጻተኞች፡ እንደሆኑ፡ ዕወቁ
ቀ፨ ዘኍ፡ ፳፬፡ ፲፯፡ ዘፍ፡ ፳፫፡ ፬፡ ፴
፵፯፡ ፱፡ መዝ፡ ፴፱፡ ፲፪፨
፲፬ ስለሳቸውም፡ እንዲህ፡ የሚሉ
ሰዎች፡ አገራቸውን፡ እንዲሹ፥
፲፭ ያስታውቃሉ፨ የወጡባትንስ
አገር፡ ሸተው፡ ቢሆን፡ ወደሷ፡ ይ
መለሱ፡ ዘንድ፡ በተቻላቸው፡ ነ
፲፮ በር፨ እንግዲያስ፡ በሰማይ፡ ያለ
ች፡ የምትበልጠውን፡ አገር፡ ተስ
ፋ፡ ያደርጉ፡ እንደ፡ ነበረ፡ ታወቀ፡
ስለዚህም፡ እግዚአብሔር፡ አም
ላካቸው፡ ይባል፡ ዘንድ፡ አያፍር
ም፡ ተስፋ፡ ያደረጋቸውን፡ አገር
አዘጋጅቶላቸዋልና።

ማቴ፡ ፭፡ ፵፰፡ ፵፭፡ ፵፬፡ ቍ ፲።

ክፍል፡ ፲፩።

፲፯ አብርሃምን፡ እግዚአብሔር፡ በተፈታተነው፡ ጊዜ፡ ልጁን፡ ይስሐቅን፡ ይሠዋው፡ ዘንድ፡ በሃይማኖት፡ ወሰደው። በይስሐቅ፡ ዘር ይጠራሃል፡ ብሎ፡ ተስፋ፡ ያናገረለትን፡ አንድ፡ ልጁን፡ አቀረበው። ዘፍ፡ ፳፪፡ ፪፡ ፲፡ ዘፍ፡ ፳፩፡ ፲፪።

፲፰ እግዚአብሔር፡ ከሙታን፡ ያስነሣለት፡ ዘንድ፡ እንዲቻል፡ አምኖ ስለዚህም፡ መሥዋዕትነት፡ የተሰጠው። ይስሐቅ፡ ለአብርሃም፡ መታሰቢያ፡ ሆነለት። ሮሜ፡ ፬፡ ፲፯

፲፱ ያገኙት፡ ዘንድ፡ ስላላቸው፡ የሚሆነውን፡ አምኖ፡ ይስሐቅ፡ ያዕቆብንና፡ ኤሳውን፡ ባረካቸው። ዘፍ፡

፳ ፳፯፡ ፳፯። ያዕቆብ፡ በሚሞትበት፡ ጊዜ፡ የዮሴፍን፡ ልጆች፡ እያንዳንዳቸውን፡ ባረካቸው። በበትሩ፡ ጫፍም፡ ሰገደ፡ ዘፍ፡ ፵፯፡ ፴፩፡ ዘፍ፡ ፵፰፡

፳፩ ፲፮። ዮሴፍ፡ በሚሞትበት፡ ጊዜ፡ የ፲ል፡ ልጆች፡ ከግብፅ፡ ምድር፡ መውጣታቸውን፡ በሃይማኖት፡ አሰበ፡ አፅሙን፡ ይዘው፡ እንዲወጡ፡ አዘዛቸው። ዘፍ፡ ፶፡ ፳፬፡ ፳፭፡

፳፪ ሙሴ፡ በተወለደ፡ ጊዜ፡ በሃይማኖት፡ በናቱ፡ በአባቱ፡ ቤት፡ ሶስት፡ ወር፡ ሠወሩት፡ መልኩ፡ ያማረ፡ ልጅ፡

፳፫ ሆነ፡ አይተውታልና። የንጉሡን፡ ትእዛዝ፡ አላፈሩም። ዘፀ

፩ ፳፪፡ ፳፪፡ ና ፪፡ ፪። ሙሴ፡ ከደገ፡ በኋላ፡ የፈርዖን፡ የልጅ፡ ልጅ፡

፳፬ ነህ፡ ቢሉት፡ በሃይማኖት፡ አይደለሁም፡ አለ። ዘፀ፡ ፪፡ ፲፡ ፲፩።

፳፭ በኃጢአት፡ ጥቂት፡ ዘመን፡ ደስ፡ ሲለው፡ ይልቅ፡ ከእግዚአብሔር ወገን። ጋራ፡ መከራ፡ ይቀበል፡ ዘ

፳፮ ንድ፡ ወደደ። ከግብፅ፡ ብዙ፡ ገንዘብ፡ ይልቅ፡ የክርስቶስ፡ መከራ፡ እንዲበልጥ፡ አውቆአልና። ም ፲፫፡ ፲፫፡ ዘፀ፡ ፬፡ ፳፱። ም፡ ፲፡ ፵፭፡

፳፯ በሃይማኖት፡ የንጉሡን፡ ቍጣ፡ ሳይፈራ፡ በግብፅ፡ ኖረ፡ ዋጋዩን፡ አገኛለሁ፡ ብሎ፡ ከሚያየው፡ ይልቅ፡ የማይታየውን፡ ሊፈራ፡ ወዱዋልና። ዘፀ ፲፡ ፲፭፡ ፳፰፡ ዘፀ፡ ፫፡ ፳።

፳፰ በሃይማኖት፡ ፋሲካ፡ አደረገ፡ ደምም፡ ረጨ፡ የ፳ልን፡ የበኵር፡ ልጆች፡ ቸነፈር፡ እንዳያጠፋባቸ

፳፱ ው። ፲፪፡ ፲፪፡ ፲፫። በደረቅ፡ ምድር እንደሚያልፉ፡ የኤርትራን፡ ባሕር፡ በሃይማኖት፡ ተሻገርዋት፡ በተሰጠሙ፡ ጊዜ፡ ለግብፃውያን፡ መከራ፡ ሆነባቸው። ዘፀ፡ ፲፬፡

፴ ፳፪። ሰባት፡ ቀን፡ በሃይማኖት፡ በዞርዋት፡ ጊዜ፡ የኢያሪኮ፡ ቅጽሮች፡ ተናዱ። ኢያ፡ ፮፡ ፳።

፴፩ ዘማይቱ፡ ረአብም፡ በሃይማኖት፡ ካላመኑ፡ ሰዎች፡ ጋራ፡ አልጠፋችም። ጉበኞችን፡ በፍቅር፡ ተቀብላ፡ ሠውራቸዋለችና። ኢያ፡ ፪፡

፲፰፡ ፯፡ ፲፯ ፳፫፡ ያዕ፡ ፪፡ ፳፭፨

፴፪ እንግዲህ፡ምን፡እላለሁ፡የጌዴዎንና፡የባራቅን፡የሶምሶንንም፡የዮፍታሔን፡የሳሙኤልንም፡የዳዊትን፡በሃይማኖት፡የተጋደሉ፡የሌሎች፡ነቢያትንም፡ነገር፡እንዳላወራችሁ፡ዘንድ፡ቀን፡አጥሮብኛልና፨ መሳ፡ ፯፡ ፲፩፡ ፴ ፬፡ ፲፰፡ ፲፮፡ ሳሙ፡ ፳፪፡ ፴፡ መሳ፡ ፲፫፡ ፲፪

፴፫ ነገሥታትን፡ድል፡ነሡ፡የሕይወትንም፡ጽድቅ፡አገኙ፡ጽድቅን፡ሠርተው፡ተስፋቸውን፡አገኙ፡የአናብስት፡አፍ፡ዘጉ፨ ፪ ሳሙ፡ ፰፡ ፩

፴፬ ፲፩፡ ዳን፡ ፫፡ ፳፭፨ የእሳትንም፡ኃይል፡አጠፉ፡ከተሳለ፡ጦር፡ዳኑ፡በመከራቸውም፡ፀኑ፨ በመጋደልም፡ጊዜ፡በረቱ፡የጠላቶቻቸውንም፡ጭፍራ፡አሳደዱ።

፴፭ ዳን፡ ፫፡ ፳፪፨ የእናቶችም፡ልጆቻቸውን፡ሙታን፡በትንሣኤ፡ተቀበሉ፡ተፈርዶባቸው፡የሞቱም፡አሉ፨ መዳንን፡አልወደዱምና፡የሚበልጥ፡ትንሣኤን፡ያገኙ፡ዘንድ፨ ፩፡ነገ፡ ፲፯፡ ፳፫፡ ፬ነገ፡ ፬፡ ፴፯

፴፮ የግርፋቸው፡የዘበቱባቸው፡አሥረው፡የያዙዋቸውም፡አሉ፨

፴፯ ኤር፡ ፳፡ ፪፨ በመጋዝ፡የሰነጠቁዋቸው፡በደንጊያ፡የወገሩዋቸው፡በሰይፍ፡መትተው፡የገደሉዋቸው፡ማቅና፡አጽፍ፡የፍየልም፡ሌጦ፡ለብሰው፡የዞሩ፡አሉ፡ተቸግሩ፡ተጨነቁ፨ የሐዋ፡ ፯፡ ፶፰፡ ፩፡ ሳሙ፡ ፳፬፡ ፲፰፨

፴፰ ይህ፡ዓለም፡የማይገባቸው፡እነዚህ፡መከራ፡ተቀበሉ፨ ዱር፡ለዱር፡ተራራ፡ለተራራ፡ዋሻ፡ለዋሻ፡ፈረፈር፡ለፈረፈር፡ዞሩ፨

፴፱ ፩፡ ነገ፡ ፲፰፡ ፬፨ እሊህ፡ሁሉ፡በሃይማኖት፡ለማዕተ፡ሆኑ፡የነገራቸውን፡ተስፋ፡ግን፡አላገኙም፨

፵ የሚበልጠውን፡ክብር፡ያለኛ፡ጨርሰው፡እንዳይወርሱ፡እግዚአብሔር፡አስቀድሞ፡ስለ እኛ፡በይንዋልናም ፲፪፡ ፳፫፨

ምዕራፍ፡ ፲፪። ክፍል፡ ፲፪።

በመስቀል፡ላይ፡የተደረገውን፡መከራ፡ታግሦ፡የተቀበለ፡ክርስቶስን፡አራያ፡ማድረግ፡እንዲገባ፡መከራ፡ለጊዜው፡ደስ፡ባያሰኝ፡በኋላ፡ክብር፡እንዲያስገኝ፨

፩ እንደ፡ደመና፡የሚከቡን፡እነዚህ፡ሁሉ፡ምስክሮች፡ያሉን፡እኛም፡ስለዚህ፡የከበደውን፡ሁሉ፡ሸክም፡የኃጢአትንም፡ተብተብ፡ከላያችን፡ሳይ፡እንጣል፡በመታገሥም፡በሃይማኖት፡ወደ፡ተጠበቀልን፡ተስፋ፡እንገሥግሥ፨ ሮ፡ ፯፡ ፳፩፡ ም ፲፡ ፴፯፡ ፩ቆሮ፡ ፱፡ ፳፬

፪ ወደ፡ፊት፡ስለሚቆየው፡ደስታ፡የሚያሳፍረውን፡መከራ፡ንቆ፡እንደ፡ሆነ፡በመስቀል፡የታገሠ፡በእግዚአብሔርም

ዙፋን፡በቀኝ፡የተቀመጠ፡ፍጹ
ም፡ስለቃችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶ
ስን፥እንከተለው፡ቁም፡፬፡፲፡፲፫፡ፊ
፫ ል፥፪፡፰፡እንደዚህ፡ታግሦ፡ከኃጥ
አን፡የተቀበለውን፡መከራ፡አስ
ቡ፡አስቡት፥እስበሳችሁም፡ተ
ጨዋወቱት፡ነፍሳችሁ፡እንዳት
ደክምና፡እንዳትታክቱ፡፬
፬ ፲፭፡ዮሐ፡፲፫፡፲፯፡፳፩ ደማችሁ
ን፡እስከ፡ማፍሰስ፡ድርሳችሁ፡ገና
አልደናችሁም፡፲፡፴፫፥
፭ እንቢ፡በማለት፡ከኃጢአት፡ጋ
ራ፡ተዋጉ፡ተሰፋችሁን፡የምታ
ገኙባትን፡ትምርት፡ውደዱዋ
ት፥ልጆች፡እንደ፡መሆናችሁ፡ይ
መክራችኋል፡ይወዳችኋልና
ልጄ፡የእግዚአብሔርን፡ምክር
አትሰልቸው፥በገሠፀህም፡ጊዜ
ቢዘልፍህ፡ከሱ፡አትራቁ፡፡ምሳ
፮ ፫፡፲፩፡፲፪፥እግዚአብሔር፡የወደደ
ውን፡ይገሥፃልና፡የሚወዱት
ን፡ልጅ፡ይገርፋታልና፡ራእ፫፡፲
፯ ፱፥የመጣባችሁን፡መከራ፡ታገ
ሡት፥ልጆች፡እንደ፡መሆናችሁ፡
እግዚአብሔር፡ስለ፡ወደዳችሁ
ይመክራችኋልና፡፡አባቱ፡የማ
ይገሥፀው፡ልጅ፡ማነው፥ዘዳ፡
፰፡፭፡፬፡ሰሙ፡፯፡፲፬፥
፰ ካልገሠዋችሁስ፡ባዕዶች፡ና
ችሁ፡ልጆችም፡አይደላችሁም፥
ሳችሁም፡ተካከላችኋል፡መዝ

፱ ፸፫፡፲፫፡፲፭፡፡በሥጋ፡የወለዱን
አባቶቻችን፡የሚገሥፁን
እኛም፡የምናፍራቸው፡ከሆ
ነ፡ይልቁን፡ለመንፈሳዊ፡አባ
ታችን፡ማ፡መገዛትና፡መታዘ
ዝ፡እንዴት፡ይገባን፡ይሆን፡በ
ሕይወት፡እንኖር፡ዘንድ፥ዘኍ
፲ ፲፮፡፳፪፡፳፯፥እነዚያ፡ስለጥ
ቂት፡ቀን፡ያደጋቸውን፡ለመ
ፈጸም፡እንደ፡ወደዱ፡ይገሥፁ
ናል፡እሱ፡ግን፡ለኛ፡እንዲ፡እሚ
ሻለን፡ከብሩን፡እንወርስ፡ዘን
ድ፡ይገሥፀናል፥፩፡ጴጥ፡፩፡፲
፲፩ ፭፡፲፮፥ተግሣፅ፡ሁሉ፡ለጊዜ
ው፡ደስ፡አያሰኝም፡ያሳዝናል
እንጂ፡ኋላ፡ግን፡ታግሠው፡ለ
ተቀበሉት፡የፍቅርን፡ፍሬ፡ያ
ፈራል፡ጽድቅም፡ያሰጣቸዋ
ልና፥ኢሳ፡፴፪፡፲፯፡ያዕ፡፫፡፲፰፥

፲፪ ስለዚህም፡የሰለለውን፡እጃች
ሁን፡ያነከሰውንም፡እግራች
ሁን፡አቅኑ፥ኢሳ፡፴፭፡፫፥
፲፫ ለእግራችሁም፡የቀና፡መንገ
ድ፡አድርጉ፡የላባችሁ፡አንከ
ስና፡ይድን፡ዘንድ፡እንዳትሰነክ
፲፬ ለ፡ከሁሉ፡ጋራ፡አንድ፡ወደ
መሆን፡ግሥግሡ፡ንጽሕናች
ሁንም፡አትተዉ፡ያለዚህ፡እ
ግዚአብሔርን፡የሚያየው፡
የለምና፥መዝ፡፴፬፡፲፬፡ሮሜ፡

፲፬፡፲፯፡ ፬ ጢሞ፡ ፬፡ ፳፬ ።
፲፭ አስተውሉ፡ የእግዚአብሔርን
ጸጋ፡ የሚያቃልል፡ አይኑር፡ መ
ራራ፡ ሥር፡ ሁኖ፡ የሚገኝ፡ አይኑ
ር፡ መከራን፡ የምታስገኝ፡ ብዙ
ሰዎችን፡ የምታስተና፡ የምታ
፲፮ ረክስ። ዘዳ፡ ፳፱፡ ፲፰። ቀብኮርና
ውን፡ ሳንድ፡ መብል፡ እንዲ፡ ሸ
ጠ፡ እንደ፡ ኤሳው፡ ሴሰኛ፡ ርኩ
ስ፡ የሚሆን፡ አይኑር። ኤፌ፡ ፭፡
ራእ፡ ፳፩፡ ፰፡ ዘፍ ፳፭፡ ፴፫ ።
፲፯ ኋላ፡ በረከትን፡ ይወርስ፡ ዘንድ
በወደደ፡ ጊዜ፡ እንደ፡ ሰዱት፡ታ
ውቃላችሁ፡ ንስሐ፡ ጠማባት፡
ተስዋታልናቀንስሐ፡ የሚገባ
በትን፡ምንንድ፡ አላገኘም፡ም
ንም፡ እያለቀሰ፡ ቢሻት። ዘፍ፡
፳፯፡ ፴፬፡ ፴፰ ። ወደ ነደደ፡ የሚታ
ይ፡ እሳት፡ የሚያዝ፡ የመሰለ፡
ጨለማ፡ ጽኑ፡ አውሎ፡ ነፋስ
ም፡ ዐኑ፡ ጨለማ፡ ወደ፡ አሰበት
ዘፀ፡ ፲፱፡ ፲፪፡ ዘዳ፡ ፲፫፡ ፳፬ ።
፲፱ የነጋሪት፡ ድምፅ፡ ፳፩ል፡ ሰም
ተው፡ የተናገራቸውን፡ መስ
ማት፡ ስለ፡ ተሳናቸው፡ ዳግመኛ
ይናገራቸው፡ ዘንድ፡ ያልወደዱ
ት፡ ቃልም፡ ወደ፡ ተሰማበት፡ አ
ልመጣችሁም። ዘፀ፡ ፳፡ ፲፱፡ ፲፱
፳ ወደዚያም፡ ተራራ፡ እንስሳ፡ ቢ
ቀርብ፡ ወግረው፡ ይገድሉት፡ ነ
በር። ዘፀ፡ ፲፱፡ ፲፪፡ ፲፫ ።

፳፩ ይህ፡ ሁሉ፡ ስለ፡ ታያቸው፡ ግሩ
ም፡ ነገር፡ ነውና፡ ሙሴም፡ እኔ፡የ
ፈራሁ፡ የደነገፅሁ፡ ነኝ፡ አለ፡ ዘፀ
፳፪ ፴፪፡ ፲፱ ቀእናንተ ስ፡ በሰማይ፡ ያለ
ች፡ የሕያው፡ እግዚአብሔር፡ አገ
ር፡ የምትሆን፡ ጽዮን፡ ወደ፡ ተ
ባለች፡ ኢየሩሳሌም፡ ደርሳችኋ
ል፡ ደስ፡ ወደ፡ አላቸው፡ ብዙ፡ መላ
እክት ቀ መዝ ፪፡ ፯፡ ፱፡ ፲፡ ፪፡ ራእ ፫
፲፪፡ መዝ፡ ፳፮፡ ፳፮፡ ፲፰፡ ደኝ፡ ፲፡ ራእ፡ ፯፡
፳፫ ፲፡ ፲፩ ቀ ስማቸው፡ በሰማይ፡ ወ
ደ፡ ተጻፈ፡ ወደ፡ በኵሮች፡ ማኅበ
ር፡ ሁሉን፡ ወደ፡ ሚገዛ፡ ወደ፡ እግ
ዚአብሔር፡ ፍጹማን፡ በሚሆ
ኑ፡ ጻድቃን፡ ወደ፡ አደረ፡ መንፈ
ስ፡ ቀዱስቀሉቃ፡ ፲፡ ፳፡ ራእ፡ ፲፱፡ ፲፩
ም ፲፩፡ ፲፪፡ መዝ፡ ፵፫ ፡ ፫፡ ም ፲፩፡ ፵፩
፳፬ በመናገር፡ ከአቤል፡ ደም፡ የሚ
በልጥ፡ ደምን፡ በማፍሰስ፡ ተመ
ርጦ፡ ለሐዲስ፡ ኪዳን፡ መሪ፡ ወደ
ሆነ፡ ወደ፡ ኢየሱስ፡ ቀርባችኋል
፳፭ ዘፍ ፬፡ ፲፡ ም፡ ፬፡ ፲፬ ቀ ከሰማይ፡ወ
ርዶ፡ የተናገራችሁን፡ አይሆን
ም፡ እንዳትሉ፡ ዕወቁ ቀ በተራራ
የነገራቸውን፡ አይሆንም፡ ስለ
አሉ፡ እነዚያ፡ ካልዳኑ፡ ይልቁን
እኛማ፡ ከሰማይ፡ ከመጣ፡ ከሱ፡
ሬታችን፡ ብንመለስ፡ እንዴት
እንድናለን ቀም ፬፡ ፬፡ ፲፡ ና፡ ፳፰፡
፳፮ ፳፱ ቀ ያን ጊዜም፡ ቃሉ፡ ምድርን
፳፯ አነዋወጣት። እንግዲህም፡ ደ

ላመኛ፡ምድርን፡እንድ፡ጊዜ፡ አነዋውጣታለሁ፡ብሎ፡ተናግ ሮዋል፡፡ምድርን፡ብቻ፡አይደለ ም፡ሰማይንም፡ነው፡እንጂ፡፡ሐ

፳፯ ጌ፡፪፡፮። እንድ፡ጊዜ፡ደግሞ፡ማ ለቱ፡የማያልፈውን፡ዓለም፡ እንዲያሳልፈው፡ያስረዳል፡ለ ማለፍ፡የተፈጠሩ፡ናቸውና፡ የማያልፈው፡ጸንቶ፡ይኖር፡ዘ

፳፰ ንድ፡፡ መዝ፡፻፪፡፳፮። ስለዚህ ም፡እኛ፡የማያልፈውን፡መን ግሥት፡እናገኛለን፡ለእግዚአ ብሔር፡መሥዋዕት፡የምናቀ ርብበት፡ጸጋ፡አለን፡በጸሎትና በልመና፡በመፍራትና፡በመ ደንገጥ፡እናገለግለዋለንና፡ደ ን፡፪፡፵፬፡፯፡፲፬፡መዝ፡፪፡፲፩፡ፊ ል፡፪፡፲፪። አምላካችን፡የሚያ ቃጥል፡እሳት፡ነውና። ዘዳ፡፬፡፳፬ ኢሳ፡፴፫፡፲፬ ። ምዕራፍ፲፫፡ክፍል፲፫፣

እንግዳ፡መቀበልን፡እንደግዛነን፡ሲል፡እንግ ዳ፡መቀበልን፡ልማድ፡በማድረግ፡መላእክትን እንግድነት፡እስከ፡መቀበል፡የደረሱ፡ሰዎች መኖራቸውን፡እንደ፡ጻፈልን—

፩ ከባልንጀሮቻችሁ፡ጋራ፡በፍቅር ኑሩ። ሮሜ፡፲፪፡፲፡፪ጴጥ፡፩፡፯።

፪ እንግዳ፡መቀበልንም፡አትርሱ ስለዚህ፡ሳያውቁ፡የመላእክት ን፡እንግዳነት፡ይቀበሉ፡ዘንድ፡ ያደላቸው፡አሉና። ሮሜ፡፲፪፡፲፫ ናሆ፡፲፱፡፬፫፡ዘፍ፡፲፱፡፲፫።

፫ የታሠሩትን፡ከነሱ፡ጋራ፡እንደ ታሠራችሁ፡መከራ፡የፀናባቸ ውንም፡በሥጋችሁ፡ከነሱ፡ጋ ራ፡እንደሳችሁ፡ሁናችሁ፡አስ ቡ። ማቴ፡፳፭፡፴፮።

፬ መጋባት፡በሁሉ፡ዘንድ፡የከበረ ነው፡ለምኝታቸውም፡ርኩስ ት፡የለባትም፡ሥጋቸውን፡በ ሚያረክሱ፡ዘማውያን፡ላይ፡ እግዚአብሔር፡ይፈርድባቸዋ ል፡፡ዘፀ፡፳፲፬፡ኢ.ሬ፡፫፡፫፡፩ቆሮ፯

፭ ፱። እናዋራችሁም፡ገንዘብ፡ሳ ትወዱ፡ይሁን፡ያሳችሁ፡ይበቃ ችኋል፡እንጂ። እግዚአብሔር እሌተውህም፡ችልም፡ብሏልና

፮ ፩ዮሐ፩፡፫። እሁንም፡አምነን፡ እግዚአብሔር፡ይረዳኛል፡ሰው ምን፡ያደርገኛል፡አልፈራም፡ እንበላ። መዝ፡፶፮፡፫፡ናሆ፡፬፡፲

፯ ፫፡፮። የእግዚአብሔርን፡ቃል፡ የነገርዋችሁን፡መምሮቻችሁ ን፡አስቡ፡በሳ፡አካሄዳቸውንም አይታችሁ፡በሃይማኖታቸው ም፡ሰልዋቸው። ፲፮፡፩ቆሮ፡

፰ ፬፡፲፯። ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡የት ናንትና፡የዛሬ፡እስከ፡ዘለዓለ ም፡የሚኖር፡እሱ፡ነውና። ፩ቆሮ

፱ ፫፡፲፩፡ራእ፡፩፡፲፯። ሁለተኛ፡ሌላ ትምርት፡አታምጡ፡የክርስቶስ ጸጋ፡ልባችሁን፡ይስ፡ሊያስናው ይሻልና፡የሚሔዱበትን፡ሰዎ

ቾ፡ በማይጠቅማቸው፡ መብል፡ አይደለም። ኤፌ፡ ፬፡ ፲፬፡ ምሳ፡ ፳፮፡ ፱፡ ሮሜ፡ ፲፬፡ ፲፯።

፲ የኦሪተን፡ ድንኳን፡ የሚያገለግሉ፡ ከሱ፡ ይበሉ፡ ዘንድ፡ የማይገባቸው፡ መሥዋዕት፡ አለን

፲፩ ም፡ ፲፫፡ ፮፡ ፳፯። የሚሠዉት፡ ላም፡ በላ፡ ነበርና። የካህናት፡ አለቃ፡ ኃጢአት፡ ስለ፡ ማስተሥረይ፡ ወደ፡ ቅዱሳን፡ መቅደስ፡ የሙን፡ ያቀርብ፡ ነበርና። ሥጋውንም፡ ከከተማ፡ በውጭ፡ ያቃጥሉት፡ ነበር፡ ዘሌ፡ ፲፮፡ ፳፯፡ ዘፀ

፲፪ ፳፱፡ ፲፬። ስለዚህም፡ ኢየሱስ ሕዝቡን፡ በደሙ፡ ያነፃቸው፡ ዘንድ፡ ከከተማ፡ በውጭ፡ ተሰ

፲፫ ቀለ። ዮሐ፡ ፲፱፡ ፲፯። አሁንም፡ እኛ፡ መስቀሉን፡ ተሸክመን፡ ከከተማ፡ ውጭ፡ ወደነሱ፡ እንሒድ። ም፡ ፲፮፡ ፳፬።

፲፬ በዚህ፡ ያለው፡ አገራችን፡ የሚኖር፡ አይደለም፡ የሚመጣውን፡ መንግሥት፡ እንሻለን፡ እንጂ። ም፡ ፲፩፡ ፲፡ ፲፮፡ ፳፱።

፲፭ በውኑ፡ እንግዲህ፡ የከንፈሮችን፡ ፍሬ፡ የሚሆን፡ የምሥጋና፡ መሥዋዕት፡ ሁልጊዜ፡ ለእግዚአብሔር፡ ማቅረብ፡ አይገባንምን፡ በስሙ፡ እናምን፡ ዘንድ። ፩ጴ፡ ፪፡ ፭፡ ሆሴ ፲፬፡ ፫።

፲፮ ለነዳያን፡ ማዘንን፡ ከእርሳቸው፡ ጋራ፡ አንድ፡ መሆንን፡ አትርሡ። እንደዚህ፡ ያለ፡ መሥዋዕት፡ እግዚአብሔርን፡ ደስ፡ ያሰኘዋልና። ፊል፡ ፬፡ ፲፰።

፲፯ ለመምሮቻችሁም፡ ታዘዙላቸው፡ ተገዙላቸው፡ ስለናንተ፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ ምላሽ፡ የሚሰጡ፡ እንደ፡ መሆናቸው፡ ስለ፡ ነፍሳችሁ፡ ይታገላሉና። ይህነን፡ በደስታ ያደርጉት፡ ዘንድ፡ እንጂ ያዝኑቀ፯፡ ሕዝ፡ ፫፡ ፲፯፡ ና ሆ፡ ፵፫፡ ፬

፲፰ ፳፫፡ ፳፰። ስለኛም፡ ትጸልዩ፡ ዘንድ ይህ፡ ይገባችኋል። ለሁሉም በጎ፡ መሥራትን፡ እንጂ፡ እንድትወዱ፡ እናምናለን። ፪ቆሮ

፲፱ ፩፡ ፲፪። ይልቁንም፡ ይህነን፡ ትሠሩ፡ ዘንድ፡ እማልዳችኋለሁ ፈጥኜ፡ ወደናንተ፡ እንድመጣ

፳ መጠን። የዘለዓለም፡ በሚሆን፡ ሥርዓት፡ ደም፡ ምእመናን የሚጠብቁ፡ የካህናት፡ አለቃ ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስን ከሙታን፡ ያስነሣው፡ የሰላም፡ አምላክ፡ እግዚአብሔር ኢሳ፡ ፵፡ ፲፩፡ ሕዝ፡ ፴፬፡ ፳፫፡ ዮሐ፡ ፲፡ ፲፩።

፳፩ በበጎ፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ የሚወደውን፡ ትሠሩ፡ ዘንድ፡ ያጽናችሁ፡ ለዘላለሙ፡ ምስጋና፡ ባለው፡

በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዲስ፡የ
ሚያስኘውን፡እሱ፡እየሠራ
ሳችሁ፨ አሜን፨
ወንድሞቻችን፡ያስተማርኋ
ችሁን፡ትምርት፡ትቀበሉ፡ዘ
ንዱ፡አማልዷችኋለሁ፨በጥ
ቂቱ፡ለዝዞችኋለሁና፨ከእኛ
ም፡ዘንድ፡ወደናንተ፡የተላከ፡
ወንድማችን፡ጢሞቴዎስ፡እ
ኛደሆነ፡ዕወቁ፨
ፊጥኖም፡ቢመስስ፡እኔ፡መ
ጥቼ፡እያችኋለሁ፨
መምሮቻችሁ፡ምእመናንን
ሁሉ፡እንዴቴ፡ናችሁ፡በሉ፨
ባጣልያም፡ያሉ፡ሁሉ፡እን
ዴት፡ናችሁ፡ይሏችኋል፨
ጸጋው፡ከሁላችሁ፡ጋራ፡ይሁ
ን፨ አሜን፨
ባጣልያ፡የተጻፈ፡በጢሞ፡
ቴዎስ፡እጅ፡ወደ፡ዕብራውያ
ን፡የተላከ፡የጳውሎስ፡መልእ
ክቱ፡ተፈጸመ፨ ለስጃምሮ፡
ሳስጨረሰን፡ለእግዚአብሔ
ር፡ክብር፡ምስጋና፡ይግባው
አሜን፨ ፨ ፨ ፨

አንድ፡ አምሳ ክ፡ በሚሆን፡ በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ስም፡ የጸፉት። የጴጥሮስ፡ መጀመሪያ፡ መልእክት፡ ይህችና ትቃ ምዕራፍ፡ ፩። ክፍል፡ ፩።

በቃሉ፡ ስብከት፡ ሳመኑ፡ በእስጢፋኖስ፡ሞ ት፡ ለተበተኑ፡ በየሀገሩ፡ ሳሉ፡ ምእመናን፡ ቅዱስ፡ ጴጥሮስ፡ የሥጋዊውንና፡ የመንግ ሥተ፡ ሰማያትን፡ ነገር፡ እንዴ፡ ጻፈላቸው

፩ ከጌታችን፡ ከኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሐዋርያ፡ ከጴጥሮስ፡ የተላከች መልእክት፡ ጳንጦስና፡ ገላትያ ቀጶዶቅያና፡ እስያ፡ ቢታንያ፡ ም፡ በተባሉ፡ አገሮች፡ ሳሉ፡ ለተ መረጡም፡ ሰዎች፡ ትድረስ፨ያ

፪ ዕ፡ ፮፡ ፩፨ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ እግዚአብሔር፡ አብ፡ ማወቁን፡ ለቀደሙ፡ ትድረስ። የኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ የደሙን፡ መፍሰስ፡ ይመሰክሩ፡ ዘንድ፡ ሞገስና፡ ሰላም፡ ይብዛላችሁ፨ ሮሜ ፰፡ ፳፱

፫ ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ከሙታን፡ በመነሣቱ፡ ሕይወት፡ በምናገኝበት፡ ተስፋ፡ በቸርነቱ፡ ብዛት፡ የወለደን፡ የጌታችን የኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ አባት፡ እግዚአብሔር፡ ይመስገን፨ ፪ቆ

፬ ሮ፡ ፩፡ ፫። የማይጠፋውን፡ የማይ ለወጥና፡ የማያልፈውን፡ ለኛና፡ ለናንት፡ በሰማይ፡ የተጠበቀ ውን፡ ለመውረስ፨ ቆላ፡ ፩፡ ፲፪።

፭ በኋላ፡ ዘመን፡ ትገለጥ፡ ዘንድ፡ በ ተዘጋጀች፡ መድኃኒት፡ በእግዚአ ብሔር፡ ኃይል፡ በሃይማኖ ት፡ የተጠበቃችሁ፡ ናችሁና፡ ዮ ሐ፡ ፲፡ ፳፰፡ ፲፯፡ ፲፩፨

፮ ለዘላለሙ፡ ደስ፡ ይላችኋል፡ ነ ገር፡ ግን፡ ስለሚመጣባችሁ፡ ል ዩ፡ ልዩ፡ መከራ፡ ዛሬ፡ ጥቂት፡ ታ ዝኑ፡ ዘንድ፡ እላችኋለሁ፨ ሮሜ ፭፡ ፫፡ ፪ ቆሮ፡ ፬፡ ፲፯፡ ያዕ፡ ፭፡ ፲፨

፯ በእሳት፡ ከፈተኑት፡ ከጠራ፡ ወ ርቅ፡ ይልቅ፡ ከሚወደድ፡ ሃይ ማኖታችሁ፡ መፈተኛ፡ ሊሆን፡ ደግሞ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ በተ ገለጠ፡ ጊዜ፡ በምስጋናና፡ በክብ ር፡ በብርሃንም፡ ትገኙ፡ ዘንድ፡ እላችሁ፨ ም ፲፯፡ ፫፡ ሚልክ ፫

፰ ፫፨ ሳታዩት፡ የምትወዱት፡ እ ሱ፡ ነው። እስከ፡ ዛሬ፡ ግና፡ አላያ ችሁትም፡ ታምኑበታላችሁ፡ እንጂ፨ አሁንም፡ ፍጹም፡ በሌ ላት፡ ደስታ፡ ደስ፡ ይላችኋል፡ ዮ ሐ፡ ፳፡ ፳፱፡ ፩ ቆሮ፡ ፪፡ ፱።

፱ በሃይማኖታችሁም፡ ፍጻሜ፡

የነፍሳችሁን፡መድኃኒት፡ታ
ገኛላችሁ። ሮሜ፡፪፡፳፱።
ይህችም፡ስለ፡ክብራችሁ፡ት
ኛቢት፡የተናገሩ፡ነቢያት፡ዞረ
ው፡የፈለጉት፡መድኃኒት፡ና
ት፤ዳን፡፱፡፳፬፡፳፯፡ሉቃ፡፲፡፳፬፡
የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡መንፈስ፡
በሳቸው፡ሳይ፡የተናገረው፡ለ
መቸ፡ዘመን፡ለማናቸውም፡
ቀን፡እንደሆነ፡እየመረመሩ፡ክ
ርስቶስ፡አስቀድሞ፡መከራ፡ይ
ቀበል፡ዘንድ፡ስላለው፡ከዚ
ያም፡በኋላ፡ስለሚገለጥ፡ጌት
ነቱ፡የመሰከረ። መዝ፡፳፪፡፯፡
ኢሳ፡፶፫። ገልጠላቸዋልና፡ይህ
ን፡ዛሬ፡የምነግራችሁን፡በራሳ
ቸው፡ዕውቀት፡የነገራችሁ፡አ
ይደለም። ከሰማይ፡በተላከ፡
መንፈስ፡ቅዱስ፡ነጋረዋቸኋል
እንጂ። ያዩት፡ዘንድ፡መላእክ
ትን፡ካሳመናቸው፡በኋላ። ኤ
ፌ፡፫፡፲። ክፍል፡፬።
አሁንም፡የተረዳ፡የነቃ፡የልቡና
ችሁን፡ወገብ፡ታጠቁ፡በኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡መገለጥ፡የምት
መጣላችሁንም፡ደስታ፡ተስፋ
አድርጉ። ኤፌ፡፫፡፫።
እንደ፡እሚታዘዙ፡ልጆች፡ባለ
ማወቅ፡ወደ፡ወደዳችሁት፡ወ
ደ፡ቀድሞ፡ኃጢአታችሁ፡ሰ
ትመለሱ። ሮሜ፡፲፪፡፪።

የጠራችሁ፡እሱ፡ንጹሕ፡እን
ደሆነ፡እናንተም፡በካሔዳች
ሁ፡ሁሉ፡ንጹሐን፡ሁኑ። ሉቃ፡፩፡
፸፭። እኔ፡ንጹሕ፡እንደሆንሁ
ንጹሐን፡ሁኑ፡የሚል፡ተጽፏ
ልና። ዘሌ፡፲፩፡፵፬፡መዝ፡፳፩፡፩፡
፮። ለየ፡አንዳንዱ፡እንደ፡ሥራው
ሳያደላ፡እውነት፡የሚፈርድ
አብን፡የምትለምኑት፡ከሆነ፥
በሕይወታችሁ፡ዘመን፡ሁሉ፥
እየፈራችሁ፡ባመናችሁ፡ት፥
እምነት፡ኑሩ። ኤፌ፡፩፡፲፯፡ራእ፡
፩፡፲፯፡የሐዋ፡፲፯፡፴፩።
ከአባታችሁ፡ከተቀበላችሁት
ከማይጠቅም፡ሥራችሁ፡ያዳ
ናችሁ፡በሚጠፋ፡ወርቅ፡ብር
እንዳይደለ፡አውቃችሁ። ፩ቆ
ሮ፡፯፡፳፫፡ምዕ፡፲፱። የተወደደ፡ነ
ውር፡የሌለበት፡በግ፡እንደ፡መ
ሆኑ። ክርስቶስ፡ባፈሰሰው፡በ
ክቡር፡ደሙ፡ነው፡እንጂ። ዓለ
ም፡ሳይፈጠር፡የታወቀ፡በኋላ
ም፡ዘመን፡ስለ፡እኛ፡የተገለጠ፤
ሮሜ፡፲፮፡፳፭። ከሙታን፡በስነ
ሣው፡ክብርንም፡በሰጠው፡በ
እግዚአብሔር፡በሱ፡ቃል፡ያመ
ነ። አሁንም፡ሃይማኖታችሁና፡
ተስፋችሁ፡በእግዚአብሔር፡
ይሁን። ዮሐ፡፲፬፡፮። የሐዋርያ፡
በእውነተኛውም፡ትእዛዝ፡በ
ውነታችሁን፡ንጹሕ፡አድርጉ።

በፍጹም፡ ልቡናችሁ፡ ሳትጠራጠሩ፡ ባልንጀሮቻችሁን፡ ትወዱ፡ ዘንድ። ከአንድ፡ አባት፡ እናት፡ እንደ፡ ተወለዱ፡ ልጆች፡ እርስ፡ በርሳችሁ፡ ተፋቀሩ። ከሚጠፋ፡ ዘር፡ አይደለም፡ ከማይጠፋ፡ ዘር፡ ነው። እንጂ፡ ለዘላለሙ፡ ለሚኖር፡ በእግዚአብሔር፡ ትእዛዝ፡ ዮሐ ፩፡ ፲፫፡ ያዕ፡ ፩፡ ፲፰። ሥጋዊ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ እንደ፡ ሣር፡ ነውና፡ ክብሩም፡ ሁሉ፡ እንደ፡ ሣር ፍሬ፡ ነውና። ሣሩ፡ ሲደርቅ፡ ፍሬው፡ እንደረግፍ። ኢሳ፡ ፵፯፡ ፯፡ ያዕ፡ ፩፡ ፲፩። የእግዚአብሔር፡ ቃል ግን፡ ለዘለዓለም፡ ይኖራል፡ የነገርናችሁም፡ ቃል፡ ይህ፡ ነው። ።

ምዕራፍ፡ ፪።

ክፉ፡ ቶኖን፡ ምቀኝነትን፡ አርቁ፡ በወተት፡ እንደሚያድጉ፡ ሕፃናት፡ የቃሉን፡ መሆን፡ እንደገባ ዋ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ እንደ፡ መንገደኛ፡ እንደ፡ መሸበት፡ አደራ፡ እንደደገሙን ←

፩ እንግዲህ፡ ክፋትንም፡ አሰተንም ሁሉ፡ መጠራጠርን፡ መነቃቀፍን፡ መቃናትንም፡ ከናኛት፡ አርቁ። ሮሜ፡ ፮፡ ፬፡ ና፡ ፲፪፡ ፱፡ ፩ቆሮ፡ ፲፬፡ ፳።

፪ ሮ፡ ፲፬፡ ፳። ዕለቱ፡ እንደ፡ ተወለዱ፡ ሕፃናት፡ ሁኑ፡ ቅልቅል፡ የሌለበት፡ የዕውቀትን፡ ወተት፡ ውደዱ፡ ሕይወት፡ ሊሆናችሁ በሱ፡ ታድጉ፡ ዘንድ። ዕብ፡ ፭፡ ፲፪ ፲፫፡ ማቴ፡ ፲፰፡ ፫።

፫ እግዚአብሔርም፡ ቸር፡ እንደሆነ፡ እነሆ፡ አውቃችኋል፡ መመለሳችሁ፡ ወደሱ፡ ነው። መዝ ፴፬፡ ፰።

፬ ያችም፡ ደንጊያ፡ በሰው ዘንድ፡ የተናቀች፡ ናት። በእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ግን፡ የተመረጠች፡ የከበረች፡ ናት። መዝ ፻፲፰፡ ፳፪።

፭ እናንተም፡ እንደ፡ ሕይወት፡ ደንጊያ፡ ፀኑ፡ ነውር፡ የሌለባት፡ ለከበረች፡ ክህነት መንፈስ፡ ቤት፡ ሁኑ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ እጅ፡ እግዚአብሔር የሚቀበላችሁን፡ መንፈሳዊ መሥዋዕት፡ አቅርባችሁ፡ ታሳርጉ፡ ዘንድ። ኤፌ፡ ፪፡ ፳፩፡ ቈ፡ ፱፡

፮ ሮሜ፡ ፲፪፡ ፩። የከበረችና፡ የተመረጠች፡ ደንጊያ፡ በጽዮን፡ አኖራለሁ፡ ያመነባትም፡ አያፍርም፡ የሚል፡ ጽሑፍ፡ አለና። ኢ

፯ ሳ፡ ፳፰፡ ፲፮። ለምታምኑበት፡ ለናንተም፡ ክብር፡ ነው። ሰራተኞች፡ የናቋት፡ ደንጊያ፡ ለሚከዱ፡ ሰዎች፡ ግን፡ ያቺው፡ የማዕዘን፡ ራስ፡ ሆናለች። ማቴ፡

፰ ፳፩፡ ፵፪። በቃሉ፡ ለሚጠራጠሩ፡ የተሰናከሉበትም፡ ለሚከዱ፡ የሚያሰናክል፡ የዕንቅፋት፡ ደንጊያ፡ ነው። ኢሳ፡ ፰፡ ፲፬፡

፱ ሮሜ፡ ፱፡ ፴፫። እናንተስ፡ የተመረጣችሁ፡ ፍጥረት፡ ናችሁ፡ የንጉሥም፡ መቅደስ፡ ናችሁ፡ የተ

ቅዱስ፡ዘርና፡የሚመካ፡ሕዝብ፡ናችሁ፡ከጨለማ፡ወደ፡ድንቅነቱ፡ብርሃን፡የጠራችሁ፡የሱን ሥራ፡ትናገሉ፡ዘንድ። ዘፀ፡፲፱፡

፲ ፮፡ራእ፡፩፡፮። ቀድሞ፡ወገናችሁ፡አልነበራችሁም፡ዛሬ፡ግን፡የእግዚአብሔር፡ወገኖች፡ሁናችኋል። ቀድሞ፡ይቅር፡የተባላችሁ፡አልነበራችሁም፡ዛሬ፡ግን፡ይቅር፡ብሏችኋል። ሆሴ፡፪፡፳፫

፲፩ ሮሜ፡፱፡፳፭። የተወደዳችሁ፡ወንድሞቼ፡እንደ፡ስደተኛ፡እንደ እንግዳ፡እንደ፡ደካማም፡በጀ፡እንድትሉኛ፡አለምናችኋለሁ። ነፍሳችሁን፡የምትወጋ፡የስጋችሁን፡ፈቃድ፡ታርቁ፡ዘንድ መዝ፡፴፱፡፲፪፡ምሳ፡፩፡፴፱፡ሮሜ

፲፪ ፲፪፡፲፫። አካሔዳችሁም፡በአሕዛብ፡መካከል፡የቀና፡ይሁን፡እንደ፡ክፉ፡አድራጊ፡እናንተን፡የሚያሙበት፡ምክንያት፡እንዲያገኙ፡በጐ፡ሥራችሁን፡ም አይተው፡እግዚአብሔርን፡ያመሰግኑ፡ዘንድ፡ወደሱ፡ይመልሳቸው፡ዘንድ። ማቴ፡፭፡፲፮።

፲፫ ስለ፡እግዚአብሔር፡ብላችሁ፡ለሰው፡ሁሉ፡ሥራችሁን፡አዋርዱ ለንጉሥም፡ተገዙ፡ሁሉ፡ሊገዛለት፡ይገባልና። ሮሜ፡፲፫፡፩

፲፬ ፯፡ቲቶ፡፫፡፩። ለመኳንንት(ም፡ታዘዙ፡እሱ፡ይልካቸዋልና ክፉ፡የሚሠሩትን፡ይቀጣቸው ዘንድ፡በጎ፡የሚሠሩትን፡ግን፡ያከብሩዋቸው፡ዘንድ። ሮሜ፡

፲፭ ፲፫፡፩፡፫፡ቲቶ፡፫፡፩። የእግዚአብሔር፡ፈቃዱ፡ይህ፡ነውና፡እግዚአብሔርን፡የማያውቁ፡የሰነፎችን፡ሰዎች፡አፉቸውን፡ለበጎ፡ሥራችሁ፡ትዘጉ፡ዘንድ።

፲፮ ምሮ፡፲፮። ስዑጤአት፡መገዛት እንደ፡   አለባቸው። ሰዎች

፲፯ አትሁኑ፡ገላ፡፭፡፲፫። እናንተስ የእግዚአብሔር፡ባሮች፡እንደ፡መሆናችሁ፡ሁሉን፡አክብሩ፡ባልንጀሮቻችሁንም፡ውደዱ፡እግዚአብሔርን፡ፍሩት፡ንጉሥንም፡አክብሩት፡ሮሜ፡፲፪፡፲፡ማቴ፡፳፪፡፳፩።

፲፰ እናንተም፡ቤተ፡ሰቦች፡በመፍራት፡ሁናችሁ፡ተገዙ፡ቸርነትና፡ይቅርታ፡ላላቸው፡ብቻ፡አይደለም፡ለክፉዎችም ነው፡እንጂ። ኤፌ፡፮፡፭፡ቲቶ፡፪

፲፱ ፱። ሰለ፡በጎ፡ሥራቸው፡በማፍመከራ፡እየተቀበለ፡ኀዘንን፡ለታገሣት፡ሰው፡የእግዚአብሔ

፳ ር፡ጸጋ፡ትሰጣለችና። እየበደላችሁ፡መከራን፡ብትታገሡ መመስገናችሁ፡ምንድን፡ነው። በጎ፡ሥራ፡እየሠራችሁ፡መከራውን፡ብትታገሡ፡በእግዚአብሔር፡ዘንድ፡የምታ

ሰመሰላናቸሁ፡ ይህች፡ ናት እንጂ፨ ም ፫፡ ፲፬፡ ፲፯፡ ፬፡ ፲፬፡ ማቴ፡ ፭፡ ፲፨

፳፩ ስለዚህ፡ ተጠርታችኋልና፡ ክርስቶስም፡ ስለናንተ፡ መከራ፡ ተቀበለ፡ ፍለጋውን እንድትከተሉ፡ ምሳሌውን፡ ይተውላችሁ፡ ዘንድ፨ ማቴ፡ ፲፮፡ ፳፬፨

፳፪ እሱ፡ ኃጢአት፡ እንዳልሰራ፡ በቃሉም፡ ሐሰት፡ እንዳልተገኘ፨ ኢሳ፡ ፶፫፡ ፱፡ ዮሐ፡ ፰፡ ፵፮፡ ፪ ቆሮ፡ ፭፡ ፳፩፨

፳፫ ሲሰድቡትም፡ አልተሳደበም፡ መከራ፡ ሲያመጡበትም፡ አልተቀየመም፡ ፍርድን፡ ዕውነት፡ ለሚፈርድ፡ ሰጠ፡ እንጂ፨

፳፬ ኢሳ፡ ፶፫፡ ፯፨ ስለኛም፡ ኃጢአት፡ በሥጋው፡ በእንጨት፡ ተሰቀለ፡ ከኃጢአት፡ ለውጥተን፡ በጽድቅ፡ ያኖረን፡ ዘንድ፡ በእሱም፡ ቍስል፡ ከቍስላችሁ፡ ድናችኋል፨ እንደ፡ ጠፉ፡ በጎች፡ ሁናችሁ፡ ነበርና፨ ፩ ዮሐ፡ ፫፡ ፭፡ ሮሜ፡ ፮፡ ፲፩፨

፳፭ አሁንም፡ ወደ፡ ነፍሳችሁ፡ ጠባቂ፡ ተመለሳችሁ፨ ኢሳ፡ ፶፫፡ ፮፡ ሕዝ፡ ፴፬፡ ፳፫፡ ዮሐ፡ ፲፡ ፲፩፡ ም ፭፡ ፬፨

ምዕራፍ፡ ፫

በእግዚአብሔር፡ ያመኑ፡ ደጋጎች፡ ሴቶች ለባሎቻቸው፡ መገዛትን፡ ንጽሕ፡ እንዲያደርጉ፡— ወንዶችም፡ ተገዥዎቻችን፡ ናቸው፡ ብለው፡ ሚስቶቻቸውን፡ እንዳይንቁ፡ እንዳያቃልሉ—

፩ እንደዚሁ፡ እናንተም፡ ሴቶች፡ ለባሎቻችሁ፡ ተገዙ፡ በዚህ፡ ነገር የማያምን፡ ሰው፡ ቢኖር፡ ከሴቶች፡ ከበጎ፡ ሥራችሁ፡ የተነሣ፡ ያዩ፡ ዘንድ፡ ያለ፡ ጥርጥርም፡ ሰውነታቸውን፡ ይጠቅምዋቱ፡ ዘንድ፨ ኤፌ፡ ፭፡ ፳፪፨

፪ እየራራችሁም፡ ምግባራችሁ፡ በንጽሕና ያማረ፡ ይሁን፨

፫ ፀጉራችሁን፡ በመሠራት፡ የሰውን፡ ዓይን፡ ደስ፡ በማሰኘት፡ አይደለም፡ ዝርግፍ፡ ወርቅና፡ ብር፡ በማጌጥ፡ አይደለም፨ ዋጋው፡ ብዙ፡ የሚሆን፡ ልብስ፡ በመልበስ፡ አይደለም፨

፬ ለመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ማደሪያ፡ በሆነ፡ በማይጠፋ፡ ጸጥ፡ ባለ፡ ቀናነት፡ የሰውን፡ ውስጣዊ፡ ልቡን፡ ደስ፡ በማሰኘት፡ ነው፡ እንጂ፨ ግናንቱ፡ ብዙ፡ በሆነ፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ ያሉ፨

፭ እንደዚሁም፡ በእግዚአብሔር፡ ያመኑ የነበሩ፡ ሴቶች፡ ቀድሞ፡ ለባሎቻቸው፡ በመገዛት፡ ራሳቸውን ያስጌጡ፡ ነበር፨

፮ ለአብርሃም፡ ትገዛ፡ ጌታዬም፡ ትለው፡ እንደ፡ ነበረች፡ ሳራ፨ እናንተም፡ በበጎ፡ ሥራ፡ ልጆችዋ፡ ሁኑ፡ ከሚያስደነጋጠውም፡ የተነሣ፡ ምንም፡ ምንም፡ ሳትፈሩ፨

፯ እንደዚህም፡ እናንተ፡ ወንዶች፡ ከሚስቶቻችሁ፡ ጋራ ስትኖሩ፡ ባሕርያቸው፡ ደካማ

ስለ፡ሆነ፡ሚስቶቻቸውን፡አ
ታዋርዱ፡ሚስቶቻቸውን፡አክ
ብሩ፡እንጂ። እነሱም፡ከናንተ
ጋራ፡ክብርንና፡ሕይወትን፡ይ
ወርሳሉና፡ጸሎታችሁ፡እንዲ
ትሰነከከል። ቀሌፊ፡፫፡፫፫።
፰ የሁሉ፡ማን፡ፍጸሚው፡ባንድ፡
አሳብ፡አንድ፡ልብ፡ትሆኑ፡ዘንድ
ነው። የባልንጀሮቻችሁን፡ሕ
መም፡ለናንተ፡እንደ ሆነ፡አድ
፬ ርጋችሁ። ልባችሁንም፡ስታ
ኩሩ፡ከፉ፡ለሠራባችሁ፡ክፉ
ሰተመልሱ፡የሰደባችሁንም፡
ባትሰደቡ። ጣላታችሁንም፡
መርቁት፡በረከትን፡ትወርሱ፡ዘ
ንድ፡ስዚህ፡ተጠርታችኋልና፡
፲ ፩፡ተሰ፡፫፡፲፫። ሕይወትን፡የሚ
ወደት፡በጎውን፡ዘመን፡ሊያይ
የሚወድ፡ሰው፡አንደበቱን፡ከፉ
ከመናገር፡ይከልከል፡ከንፈሮ
ቹም፡ሐሰት፡እንዳይናገሩ።
መዝ፡፴፬፡፱፡፩፡፲፯።
፮ ከፉውን፡ትቶ፡በጎውን፡ይሥ
ራ፡ፍቅርንም፡ይሻ፡ይከተሉ
፲፮ ት። የእግዚአብሔር፡ዓይኖቹ
ወደ፡ጻድቃን፡ጆሮቹም፡ወደ ል
መናቸው። ፊቱም፡
ከፉ፡ወደሚሠሩ፡ሰዎች፡ነው።
፲፫ መዝ፡፴፬፡፲፪፡፲፪። እናንተ፡በጎ
ስማድረግ፡ብትቀኑ፡ከፉ፡ሊያ
ደርጋችሁ፡ማነው፡የሚወድ

፱ ጽድቅን፡በመሥራት፡መከራ
ብትቀበሉ፡ግን፡የተመሰገና
ችሁ፡ናችሁ፡የሚገሬም፡ባቸ
ሁን፡አትፍሩ፡አትደንግጡ፡በ
ፍጹም፡ልቡናችሁ፡እግዚአብ
ሔርን፡አመስግኑት፡እንጂ።
፲፭ ም፡፬፡፳፡፳፫። ስለዚች፡ተስፋች
ሁ፡ለጠየቋችሁ፡ሰዎች፡የጠየ
ቁዋችሁን፡ትመልሱላቸው፡ዘ
ንድ፡ሁልጊዜ፡ተዘጋጅታችሁ፡
፲፯ ኑሩ። በቀንነትና፡እግዚአብሔ
ርን፡በመፍራት፡ማብራችሁን
አሳምሩ፡ማብራችሁ፡ከፉ፡እን
ደሆነ፡አድርገው፡የሚነቅፉ
ችሁ፡ሰዎች፡ቢናገሩ፡ስለ፡ክርስ
ቶስ፡ብላችሁ፡ከምትሠሩት፡በ
ጎ፡ሥራ፡ከበጎ፡ማብራችሁ፡የተነ
ሣ፡የሚነቁፉችሁ፡ሰዎች፡ያፍ
፲፯ ሩ፡ዘንድ። ከፉ፡ሥራ፡ከምትሠ
ሩ፡ይልቅ፡እግዚአብሔር፡የሚ
ወደውን፡ሥራ፡እየሠራችሁ፡
መከራ፡ብትቀበሉ፡ይሻላልና፡
፲፰ ቀ፡፲፬። ክርስቶስም፡ስለ፡ሰው
ኃጢአት፡አንድ፡ጊዜ፡ሙቷል
ና፡ኃጢአት፡የሌለበት፡ክርስቶ
ስ፡ ስለ፡ኃጢአት፡ሞተ፡እኛ
ን፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ያቀርበ
ን፡ዘንድ፡በሥጋ፡ሞተ፡በመለኮ
ት፡ግን፡ሕያው፡ነው። ም፡፬፡፳፩፡
፲፱ ነፍሳቸውን፡ትገዛ፡ወደ፡ነበሩ፡
ኃጥአን፡ሔደ። ም፡፩፡፯።

፳ እስቀድመው፡ለካዱት፡የእግ
ዚአብሔርም፡ትዕግሥት፡
ደጅ፡እየጠኑ፡በንስሐ፡ሳነበሩ፡
ነፃነትን፡ሰበከላቸው፨መርከ
ብ፡በሠራ፡ጊዜ፡በኖኅ፡ዘመን፡የ
ነበሩ፡ስምንት፡የሚሆኑ፡ጥቂቶ
ች፡ሰዎች፡ከጥፋት፡ውኃ፡እንደ
፳፩ ዳኑ፡ዘፍ፡፯፡፲፯፨እኛም፡ዛሬ፡በ
ጥላ፡ምሳሌ፡በጥምቀት፡ያድነ
ናል፨ሥጋን፡ከእድፍ፡በማንፃ
ት፡አይደለም፡በጎውን፡ሥራ፡ያ
ስተምረን፡ዘንድ፡ነው፡እንጂ፨
በእግዚአብሔር፡በኢየሱስ፡ክር
ስቶስም፡ትንሣኤ፡በምናምን
፳፪ ግንዘብ፨ኤፌ፡፫፡፯፨ወደ፡ሰማ
ይ፡ያረገ፡በእግዚአብሔርም፡
ቀኝ፡ተቀምጦ፡ያለ፡መላእክት
ሥልጣናትም፡ኃያላንም፡የተ
ገዙለት፨ኤፌ፡፩፡፳፡፳፩፨

ምዕራፍ፡፬።

ክርስቶስ፡በመስቀል፡ላይ፡መከራ፡እንደ፡
ተቀበለ፡እኛም፡መከራ፡በመጣብን፡ጊዜ፡መ
መከት፡እንደ፡ገባን፡የመጣብንን፡መከራ፡ሁ
ሉ፡እንደ፡እንግዳ፡ነገር፡አድርገን፡ሳናደንቅ፡
ክርስቶስን፡በመከራ፡እንድንመስለው፡—

፩ ክርስቶስ፡ስለኛ፡በሥጋው፡ከተ
ሰቀለ፡እናንተም፡በዚች፡አሳብ፡
ተጠበቁ፡በሥጋው፡መከራ፡የ
ተቀበለ፡ሰው፡ከኃጢአት፡ጽኑ
፪ ዋልና፨ዳግመኛ፡በሥጋው፡ፈ
ቃድ፡እንዳይኖር፡በሥጋው፡ከ
ዘመኑ፡የቀረውን፡እግዚአብ
ሔር፡የሚወደውን፡ሥራ፡በመ
፫ ሥራት፡ይፈጽም፡እንጂ፨የአሕ
ዛብን፡ፈቃድ፡የሠራችሁበት
ያለፈው፡ዘመን፡ይበቃችኋል
ና፨ዝሙትንና፡ክፉ፡ፈቃድን፡
ስካርንና፡ወድቆ፡ማደርን፡ያለ
ልክ፡መጠጣትን፡ጣዖት፡ማም
ለክን፡ስትወዱ፡ኤፌ፡፬፡፲፫
፬ ቲቶ፡፫፡፫፨ወደዚህ፡ሥራ፡እን
ደትሐዱ፡ዐወቁ፨ከዚችም፡የ
ገድ፡ልክ፡ከሌላው፡ሥራ፡ልዩ፡ሁ
ኑ፨እነሆ፡ከሱ፡ወገን፡የሚሆኑ
ሰዎች፡ስለናንተ፡ያደንቃሉ፡በ
ዚያ፡በቀደመው፡ሥራ፡ስትመ
ስሏቸው፡ባዩአችሁ፡ጊዜ፡ይስ
፭ ድቡዋችኋል፨በሕያዋኑና፡በ
ሙታኑ፡ይፈርድ፡ዘንድ፡ተዘጋ
ጅቶ፡ባለው፡በሱ፡ፊት፡ስለኃጢ
አታቸው፡መልስ፡ይሰጡ፡ዘን
ድ፡ያላቸው፡አሉ፡ህ፡ናቸው፨፩፡
፮ ጢሞ፡፬፡፩፡፳፮፨ስለዚህም፡በሰው
ሥራት፡በሥጋቸው፡እንደ፡ገዙ፡
በነፍሳቸውም፡በእግዚአብ
ሔር፡ሥርዓት፡እንዲድኑ፡ለሙ
ታን፡ነገራቸው፨ምዕ፡፫፡፲፱፨
፯ የነገሩ፡ሁሉ፡መጨረሻ፡ቀርቧ
ልና፡ልባችሁን፡ንጹሕ፡አድርጉ
ለጸሎትም፡ትጉ፨፩፡ቆሮ፡፲፡፲፩፡፩
፰ ዮሐ፡፮፡፲፰፨ከሁሉም፡በፊት፡በ
ፍጹም፡ልቡናችሁ፡እስ፡በሳች

ሁ፡ ተፋቀሩ፡ ፍቅር፡ ኃጢአትን ሁሉ፡ ፈጽሞ፡ ይሠውራልና። ምሳ፡፲፡፲፪፡ ያዕ፡፭፡፳።

፱ ሳታንጐራጕሩ፡ እንግዳ፡ መቀበልን፡ ውደዱ፤

፲ ዕብ፲፫፡፪፡፪ ቍ ሁላችሁም፡ የእግዚአብሔርን፡ ሀብት፡ እንደ፡ ተቀበላችሁ፡ መጠን፡ እንደ፡ በጎ፡ አገልጋይ፡ እስ፡ በሳችሁ፡ ተረዳዱ፡ ለየአንዳንዱ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ፡ የሚሰጠው፡ ሀብቱ፡ ልዩ

፲፩ ልዩ፡ ነውና፡ የምታስተምሩም የእግዚአብሔርን፡ ቃል፡ አስተምሩ፡ የሚያገለግልም፡ እግዚአብሔር፡ እንደ፡ ሰጠው፡ ኃይል፡ ያገልግል፡ በሁሉ፡ ክርስቶስ በሁሉ፡ እንዲመሰገን፡ ምስጋናና ኃይል፡ ለዘላለሙ፡ ያለው፡ አሜን። ሮሜ፡፲፪፡፯።

፲፪ ወንድሞቻችን፡ የምትመጣባችሁን፡ መከራ፡ እንግዳ፡ ሥራ፡ እንደሚደርስባችሁ፡ አድርጋችሁ፡ አታድንቁት፡ የለመዳችኋት፡ መከራ፡ ናት፡ እንጂ። የምትለምዱትም፡ መከራ፡ ይመጣባችኋል። ምዕ፡፭፡፯፡፯

፲፫ በመከራ፡ ከክርስቶስ፡ ጋራ፡ አንድ፡ ትሆኑ፡ ዘንድ፡ በጌትነት፡ በተገለጠ፡ ጊዜ፡ ክብሩ፤ አማኛታችሁ፡ ደስ፡ ይበላችሁ፡ ዘንድ፡ ዛሬ፡ በመከራው፡ ደስ፡ ይበላችሁ ቍ የሐዋ፡፭፡፵፩፡ ሮሜ፡፰፡፲፯፡ ያዕ፩፡

፲፬ ፪ ቍ ስለ ክርስቶስ፡ ቢሰድቡዋችሁ የተመሰገናችሁ፡ ናችሁ፡ የእግዚአብሔር፡ ክብርና፡ ኃይሉ፡ ሀብቱም፡ በእናንተ፡ ያድራልና፡ ም፡፬፡፩።

፲፭ ከናንተ፡ ወገን፡ ነፍሰ፡ እንደ፡ ገዳይ፡ ወይም፡ እንደ፡ ሌባ፡ ወይም፡ ክፉ፡ እንደሚሠራ፡ ወይም፡ የሌላውን፡ ገንዘብ፡ እንደሚሻ፡ ሰው፡ መከራ፡ የሚቀበል፡ አይኑር ቍ

፲፮ መከራችሁ፡ በክርስቶስ፡ እንደ መነ፡ ሰው፡ ከሆነ፡ አትፍሩ፡ በዚህ፡ ስም፡ እግዚአብሔርን፡ አመስግኑት፡ እንጂ፡ ቍ ፊል፡፩፡፳፱፡

፲፯ እግዚአብሔር፡ ባደረባቸው፡ ሰዎች፡ ፍርድ፡ የሚጀምርበት፡ ጊዜ፡ ደርሷልና፡ ፍርድ፡ መጀመሩ በኛ፡ ዘንድ፡ ከሆነ፡ የእግዚአብሔርን፡ ወንጌል፡ የሚክዱ፡ ሰዎች፡ ፍጻሜያቸው፡ ምን፡ ይሆን። ኤር፡፳፭፡፳፱፡ ሕዝ፡፱፡፮።

፲፰ ጻድቅ፡ ሰው፡ ከጭንቅ፡ የሚድን፡ ከሆነ፡ ኃጢአተኛ፡ ዓመፀኛ፡ በምን፡ ይታይ፡ ዘንድ፡ አለው። ምሳ፡፲፩፡፴፩፡ ሉቃ፡፳፫፡፴፩።

፲፱ እግዚአብሔር፡ የሚወደውን፡ ሥራ፡ ስለ፡ መሥራት፡ መከራ፡ የሚቀበሉ፡ ሰዎች፡ ወደ፡ ታማኙ፡ ፈጣሪ፡ በጎ፡ በመሥራት፡ ሰውነታቸውን፡ ያስጠብቃሉ። መዝ፡፴፩፡፭።

ምዕራፍ፡ ፭።

ከዲያቆናት፡ የሚበልጡ፡ ቀሳውስት፡ ምእመናን፡ ጠብቁ፡ ብሎ፡ እንደ፡ መከራቸው—

ዲያቆናት፡ ለቀሳውስት፡ መገዛትና፡ ትሕ
ትና፡ ማድረግ፡ እንዲገባቸው ።

፩ ከናንተ፡ ወገን፡ የሚሸመግሉ
ትንም፡ ባልንጀራቸው፡ የም
ሆን፡ ሽማግሌ፡ በጌትነቱ፡ ይታ
ይ፡ ዘንድ፡ ያለው፡ የክርስቶስን
ም፡ መከራ፡ የምመሰክር፡ እኔ፡
እማልዳቸዋለሁ፡ እሱን፡ ትመ
ስሉ፡ ዘንድ፡ ከናንተ፡ ዘንድ፡ ያሉ
የእግዚአብሔርን፡ በጎች፡ ጠብ
ቁ፨ ፬፡ ዮሐ፡ ፩፡ ሮሜ፡ ፲፪፨

፪ ስትጠብቋቸውም፡ በግድ፡ አት
ጣሏቸው፡ ስለ፡ እግዚአብሔር፡
በፈቃድ፡ ይሁን፡ እንጂ፡ ትርፍ፡ነ
ገር፡ሽታችሁ፡ በማሰዘን፡ አይሁ
ን፡ በፍጹም፡ልቡናችሁ፡ ደስ፡በ
ማሰኘት፡ነው፡ እንጂ፨ ዮሐ፡ ፳፩፡ ፲
፯፡ የሐዋ፡ ፳፡ ፳፰፡ ፩ ጢሞ፡ ፫ ፬፨

፫ በወገኖች፡ እየተበራታችሁ፡አ
ይሁን፡ በወገኖች፡ በርሳራኄ፡ም
ሳሌ፡ሁኑአቸው፡ እንጂ፨ ፩ ቆሮ፡

፬ ፩፡ ፳፬፡ ቲቶ፡ ፬፡ ፯፨ የጠባቆች፡
ጌታ፡ በተገለጠ፡ ጊዜ፡ የማያልፈ
ውን፡ የክብር፡ አክሊል፡ ትቀበ
ሉ፡ ዘንድ፨ ዕብ፡ ፲፫፡ ፳፡ ፩ ቆሮ፡ ፱፡ ፳
፭፡ ፪ ጢሞ፡ ፬፡ ፰፨

፭ እንደዚህም፡ እናንተ፡ጐበዛዝ
ት፡ ከናንተ፡ ለሚበልጡ፡ ሽማ
ግሌች፡ ተገዙ፡ሁላችሁም፡ ት
ሕትናን፡ ተማሩት፡ እግዚአብ
ሔር፡ ትዕቢተኞችን፡ ያዋርዳል
ራሳቸውን፡ የሚያዋርዱ፡ ግ
ን፡ ያከብራቸዋልና፨ ኢሳ፡ ፶
፯፡ ማቴ፡ ፳፫፡ ፲፪፡ ያዕ፡ ፬፡ ፯፨

፮ እንግዲህ፡ ከፀናች፡ ከእግዚ
አብሔር ፡እጅ፡ በታች፡ ሁ
ናችሁ፡ ራሳችሁን፡ አዋርዱ፡ በ
ጐበኛችሁ፡ ጊዜ፡ ከፍ፡ ከፍ፡ ያደ
ርጋችሁ፡ ዘንድ፨ ሉቃ፡ ፩፡ ፳፬፡ ፳

፯ ፱፡ ያዕ፡ ፩፡ ፲፨ አሳባችሁን፡ ሁሉ
በሱ፡ ላይ፡ ጣሉ፡ ስለ፡ እናንተ፡ አ
ሱ፡ ያስብላችኋልና፨ ማቴ፡ ፮፡

፰ ፳፭፡ ፊል፡ ፬፡ ፮፨ እንግዲህ፡ ወዲ
ህ፡ አዋቆች፡ ሁኑ፡ ልቡናችሁም፡
በዕውቀት፡ አፅኑ፡ ጠላታችሁ፡ ሰ
ይጣን፡ የሚውጠውን፡ ሰው፡ ሽ
ቶ፡ እንደ፡ አንበሳ፡ ይጮሃልና፡
ሉቃ፡ ፳፩፡ ፴፮፡ ፩ ተሰ፡ ፭፡ ፮፨

፱ በሃይማኖታችሁ፡ ጸንታችሁ፡
እሱን፡ ተቃወሙት፡ የዚህ፡ዓለ
ም፡ መከራ፡ ወንድሞቻችሁን፡
ሁሉ፡ እንድትአገኙዋቸው፡ አው
ቃችሁ፡ ፍቅርንም፡ አፅንታችሁ
ያዟት፨ ኤፌ፡ ፮፡ ፲፮፨

፲ የክብር፡ ሁሉ፡ ባለቤት፡ እግዚአ
ብሔር፡ በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ወደ፡ዘ
ለዓለም፡ጌትነቱ፡ ጠርቷችኋል
ና፡ ጥቂት፡ መከራ፡ ተቀብላችሁ
ይፈጽምላችኋል፡ ያፀናችኋል
ዕውቀቱንም፡ ይገልጥላችኋል፨

፲፩ ም፬፡ ፯፨ የዘለዓለም፡ ጌትነት፡
ኃይልም፡ ያለው፡ እሱ፡ ነው፡ ያለ

፲፪ ሐሰት፡ በእውነት። ከታመነ፡ ከ
ወንድማችን፡ ከስልዋኖስ፡ ጋራ፡
እንደ፡ አሰብሁ፡ ጥቂት፡ ጽፌሁ
ላችሁ፡ ለማልደችሁ፡ ይህች፡ እ
ናንተ፡ የቆማችሁባት፡ የእግ
ዚአብሔር፡ ክብር፡ እውነት፡ እ
ንደ ሆነች፡ ለመሰክር፡ ዕብ፡ ፲፫
፲፫ ፳፪። በባቢሎን፡ ውስጥ፡ ያለች
የጓብፅ፡ የተመረጠች፡ ቤተ፡ ክ
ርስቲያን፡ እንደ ተ፡ ናችሁ፡ ት
ላችኋለች። ልጄ፡ ማርቆስም፡
እንዲ ተ፡ ናችሁ፡ ዪ ላችኋልና የ
ሐዋ፡ ፲፪፡ ፲፪፡ ፳፭፡ ፪፡ ጢሞ፡ ፬፡ ፲፩፡
፲፬ ፍቅር፡ ባለው፡ ሰላምታ፡ እስበሳ
ችሁ፡ እንዲ ተ፡ ናችሁ፡ ተባባሉ፡
ክርስቶስን፡ በማመን፡ ያላችሁ
ም፡ ሁሉ፡ በፍቅር፡ እንዲ፡ ሁኑ፡
፲፭ ፩፡ ቆሮ፡ ፲፮፡ ፳። የጴጥሮስ፡ መጀ
መሪያ፡ መልእክት፡ ተፈጸመች
እስጀምሮ፡ ለስጨረሰን፡ ለእግ
ዚአብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይ
ሁባው። አሜን። ። ።

ምዕራፍ ፩፡ ክፍል፡ ፩።

እንድ፡ ጊዜ፡ ካመኑ፡ ከተጠመቁ፡ ምንም
ማባር፡ ያሻል፤ ወራዊ፡ መጋቢ፡ የለም፤ ባለ
ም፡ እያልፍም፤ ሙታንም፡ አይነሡ፤ መን
ግሥተ፡ ሰማያት፡ የለችም፡ ስላሉ፤ ይህ፡ ሁሉ
መናፍቃን፤ ለማስረዳት፡ ሁለተኛ፡ እንደ፡ ጻፈ
ላቸው።

ሁለተኛዩቱ፡ የጴጥሮስ፡ መልእ
ክት፡ ይህች፡ ናት።

፩ የኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ባርያው
ና፡ ሐዋርያው፡ ከሚሆን፡ ኪፋ፡ ከ
ተባለ፡ ስምዖን፡ የተላከች፡ መ
ልእክት፡ ከአምላካችን፡ በመ
ድኃኒታችን፡ በኢየሱስ፡ ክርስ
ቶስ፡ ጽድቅ፡ ባገኙ፡ ሃይማኖት
ክብርን፡ በማግኘት፡ ለምንተ
፪ ባበር፡ ተድረስ። አምላካችንና
ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስን
ባመወቅ፡ ጸጋ ስና፡ ሰላም፡ ይ
፫ ብዛላችሁ። ወደ፡ ሕይወትና፡
ወደ፡ ጽድቅ፡ የሚያደርሰው
ን፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ ሰኛ፡ በሰጠን፡ በ
መለኮቱ፡ ኃይል፡ ወደ፡ ጌትነቱ
ና፡ ወደ፡ ቸርነቱ፡ የጠራን፡ እሱ
፬ ነው። ፩ ጴጥ ፪፡ ፱። በሰጠን፡ ተስ
ፋ፡ ሕይወት፡ በምናገኘና፡ በ
ምንከብር፡ ከፍ፡ በምንል፡ ገን
ዘብ፡ ስለዚህ፡ የጌትነቱ፡ ተካ
ፋዮች፡ ትሆኑ፡ ዘንድ። የዚህን
ዓለም፡ እጥራ፡ ፈቃዱን፡ እየሸ
፭ ሸችሁ። እናንተም፡ በሥራ፡ ሁ
ሉ፡ እየተፋጠናችሁ፡ በሃይማ
ኖት፡ ላይ፡ በጎነትን፡ አስከተሉ
በበጎነትም፡ ላይ፡ ዕውቀትን፡
፮ ገላ፡ ፭፡ ፳፪፡ ፳፫። በዕውቀትም
ላይ፡ ንጽሕናን፡ በንጽሕና፡ ላ
ይ፡ ትዕግሥትን፡ በትዕግሥት
ላይ፡ ለእግዚአብሔር፡ መገ
፯ ዛትን። በመገዛትም፡ ላይ፡ ወ
ንድማማች፡ መሆንን፡ ወንድ

ማማች፡ በመሆን፡ ላይ፡ መፋቀርን፡ ያዙቃግሳ፡ ፯፡ ፲፩፨

፰ ይህ፡ ከናንተ፡ ዘንድ፡ ካለ፡ ሥራፈተ፡ አይደላችሁም፨ የክብር፡ ፍሬም፡ የሌላችሁ፡ አይደላችሁም፡ ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ ወደ፡ ማወቅ፡ ያደርሳችኋል፡ እንጂ፨

፱ በዚህ፡ ሥራ፡ የሌለ፡ ሰው፡ ግን፡ በዳሰሳ፡ የሚሔድ፡ ዕውር፡ ነው፡ ከቀደመው፡ ኃጢአቱ፡ ሰውነቱን፡ ማንጻት፡ የዘነጋ፡ ነው፨ ፩፡ ዮሐ፡ ፪፡ ፱፡ ፲፩፨

፲ እሁንም፡ ወንድሞቻችን፡ በሥራችሁ፡ መጽናት፡ መጠራታችሁ፡ የጸናች፡ ትሆን፡ ዘንድ፡ ቸኩሉ፡፡ የሃይማኖታችሁን፡ ማምግማ፡ ትሰጡ፡ ዘንድ፡ ይህነን፡ ስታደርጉ፡ አትጠራጠሩ፨

፲፩ ወደ፡ ዘለዓለም፡ ሕይወትና፡ ወደ፡ መድኃኒታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ መንግሥት፡ የሚወስድ፡ ሰፊ፡ ምንገድ፡ ይሰጣችኋል።

ክፍል፡ ፪ ፲

፲፪ በሣዘዘው፡ እውነት፡ ሥራ፡ እናንተ፡ ጸንታችሁ፡ ሳለ፡ ይህነን፡ ትእዛዝ፡ አስሰባችሁ፡ ዘንድ፡ ሁልጊዜ፡ ስለ፡ እናንተ፡ እተጋለሁ፡፡ ሮሜ፡ ፲፭፡ ፲፭፡ ፲፬፨

፲፫ በዚህ፡ ሥጋዩ፡ ሳለሁ፡ ይህን፡ በማሳሰብ፡ አነቃችሁ፡ ዘንድ፡ በሚገባ፡ ይመስለኛል፡ ፪፡ ቆሮ፡ ፭፡ ፩፨

፲፬ ከናንተ፡ የምለይበት፡ ቀን፡ የቀረበች፡ እንደሆነች፡ አውቃለሁና፡ ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ እንዳነገረኝ፨ ዮሐ፡ ፳፩፡ ፲፰፡ ፲፱፨

፲፭ ደግሞ፡ ይህቺ፡ ትእዛዝ፡ ከናንተ፡ ዘንድ፡ እንድትኖር፡ ሁልጊዜ፡ እጽራለሁ፡ ከሞቱሁ፡ በኋላ፡ ታስቢት፡ ዘንድ፡ እንድስባችኋትም፡ ተሠሩ፡ ዘንድ፨

፲፮ ተረት፡ የሚሆን፡ ጥበብን፡ የተከተልን፡ አይደለንምና፡ የጌታችን፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ ኃይሉን፡ መምጣቱንም፡ በዚህ፡ ያስታወቅናችሁ፡ አይደለም፡ ክብርንና፡ ምስጋናን፡ ከአግዚአብሔር፡ አብ፡ ዘንድ፡ ገንዘብ፡ ያደረገ፡ የሱን፡ የጌትነቱን፡ አኛ፡ ራሳችን፡ አይተን፡ ነው፡ እንጂ፨ ፩፡ ቆሮ፡ ፩፡ ፲፯፡ ፩፡ ቆሮ፡ ፪፡ ፬፨

፲፯ ከሁሉ፡ በላይ፡ ያለ፡ ክብርን፡ ከተመላ፡ ከአብ፡ ዘንድ፡ የመጣለትም፡ ቃል፡ የመረጥሁት፡ የምወደው፡ ልጄ፡ ይህ፡ ነው፡ አሉ፥ ማቴ፡ ፫፡ ፲፯፡ ና ፲፯፡ ፭፡ ሉ፡ ፱፡ ፴፭፡ ኢሬ፡ ፩፡ ፯፨

፲፰ በተቀደሰ፡ ተራራው፡ ከሱ፡ ጋራ፡ ሳለን፡ ይህ፡ ቃል፡ ከወደ፡ ሰማይ፡ እንደ፡ መጣለት፡ ሰማን፨

፲፱ ደግሞም፡ ከዚህ፡ የሚቀድም፡ ይህን፡ የሚያስታውቅ፡ የነቢያት፡ ቃል፡ አለን፡ እጅግ፡ በጎ፡ ሥራ፡ ብትሠሩ፡ ብትመለከቱትም፡ በጨለማ፡ በታ፡ እንደምታበራ፡ መብ

ራት፡ይሆናሳችኋል። ፀሐይ፡እ
ስኪቃበራላችሁ፡ድረስ፡በልባች
ሁ፡የሚበራ፡የንጋት፡ኮከብም፡
እስኪወጣላችሁ፡ድረስ። መዝ
፻፲፱፡፻፭፡ ፪ቆሮ፡፬፡፮።

፳ በመጽሐፍ፡ያለ፡ትንቢት፡ሁሉ
ትርጓሜው፡በሰዉ፡እንደሌለ፡
ይህን፡አስቀድማችሁ፡ዕወቁ።
ሮሜ፡፲፪፡፮፡ ፪ጢሞ፡፫፡፲፮።

፳፩ ትንቢት፡መናገርን፡በሰው፡ፈ
ቃድ፡እንዳይሆን፡ቀድሞ፡ነቢ
ያት፡ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡
ታዘው፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ተና
ገሩ፡እንጂ።

ምዕራፍ፡ ፪

ሐሰተኞች፡መምህራን፡በየጊዜው፡መነ
ሣታቸው፡ልማድ፡እንደ ሆነ፤ኃጥኣን፡ቍ
ርጥ፡ፍርድ፤እንደ ጠባያቸው፤ጻድቃ
ን፡ግን፡ከመከራ፡እንደ ዳኑ።

፩ ነገር፡ግን፡ሐሰትን፡የሚያስተም
ሩ፥ጥፋት፡ሊሆንባችው፡በሰው፡
ልቡና፡ክህደትን፡የሚያሳድ
ሩ፡የሐሰት፡መምህራን፡በናን
ተ፡ዘንድ፡ዘሬ፡እንደሉ፡ቀድሞ
በሕዝቡ፡መካከል፡ሐሰተኞች
መምሕራን፡ነበሩ። በደሙ፡የ
ገዛቸውን፡ጌታቸውን፡የሚክ
ዱ፡ጥፋትን፡መነቀልን፡በራሳ
ቸው፡ፈጥነው፡የሚያመጡ። ማ
ቴ፡፳፬፡፲፩፡ ጢሞ፡፩፡፬፡፩።

፪ እሊህንም፡ብዙ፡ሰዎች፡በዝሙ
ታቸው፡ይከተሉዋቸዋል፡እ
ውነተኛውን፡ሐሳ፡ይሰድባሉ።

፫ ፪ጢሞ፡፱፡፫፡፩። እነሱ፡ፈጥረ
ው፡በተናገሩት፡ነገር፡ይከራከ
ራሉ፡በሱም፡ይሔዳሉ፡የሌ
ህም፡ፍርዳቸው፡ዓለም፡ከተ
ፈጠረ፡ጀምሮ፡የማያርፍ፡ጥ
ፋታቸውም፡የማያንቀላፋ፡ነ
ው።

፬ እግዚአብሔርስ፡በበደሉ
ት፡ጊዜ፡ለመላእክት፡ስንኳን
አላዘነላቸውም፡ወደ፡ጋሉ፡ወ
ደ፡ፅኑ፡ሥቃይ፡አወረዳቸው፡
እንጂ፡በፅኑ፡ሥቃይ፡ይኖሩ፡ዘ
ንድ፡ለቀጣት፡አሳልፎ፡ሰጣቸ
ው።

፭ ይሁዳ፡ቍ፮። ለቀደሙት
ም፡ሰዎች፡አላዘነላቸውም፡ጽ
ድቀን፡ከጠበቃት፡ከኖኅ፡ጋራ
ስምንት፡ሰው፡አስቀረ፡እንጂ፡
ለሌላው፡ጽድቅን፡የሚያስተ
ምር፡ይሆን፡ዘንድ፡በኃጢአተ
ኞች፡ሰዎች፡ላይ፡የጥፋትን፡ው
ሀ፡አመጣባቸው። ፫፡፳፫፡ ዘፍ፡
፰፡፲፰።

፮ የሰዶምንና፡የገሞራን
አገሮችም፡በእሳት፡አቃጠላቸ
ው፡እንዲህ፡ፈረዳባቸው። በኋ
ላ፡ዘመን፡ለሚነሡ፡ኃጢአተኞ
ች፡ምሳሌ፡አደረጋቸው። ዘፍ
፲፱፡፳፬፡ ዕብ፡፲፩፡፯።

፯ በዝሙታቸው፡ሥራ፡ከሚበድ
ሉ፡ሰዎች፡የተነሣ፡የሚያዝን፡
ጻድቅ፡ሎጥን፡ግን፡አዳነው።

፰ ጻድቅ፡ሎጥ፡ይህን፡እያየና፡እየሰማ፡ከነሱ፡ጋራ፡ሲኖር፡በየቀኑ፡ጻድቅ፡ሰውነቱን፡በክፉ፡ሥራቸው፡አስጨነቃት። መዝ፡፻፲፱፡፻፴፮፡ሕዝ፡፱፡፬፥

፱ እግዚአብሔር፡ጻድቃንን፡ከፈተና፡ሊያድናቸው፡እንዲችል፡እነሆ፡አወቅን፡ኃጢአተኞችንማን፡ልታስጨንቃቸው፡የፍርድ፡ቀን፡ተጠብቃቸዋለች፥ ፩ቆሮ፡፲፡፲፫፡ራእ፡፫፡፲፥

፲ ይልቁንም፡ፈቃዳቸውን፡ተከትለው፡ሰውነታቸውን፡የሚያሳድፉትን፡ፈጣሪያቸውንም፡የሚንቁትን፡እሊህም፡ደፋሮችና፡ተሳዳቦች፡ጌትነቱንም፡ይሰድቡ፡ዘንድ፡የማይደነግጡ፡ናቸው፥

፲፩ በኃይለኛ፡ብርታት፡ከነሱ፡በላይ፡ከሚሆኑ፡ከመላእክት፡በላይ፡ከሚሆን፡የስድባቸውን፡ፍርድ፡ያመጡባቸው፡ዘንድ፡መታገሥ፡የማይቻለው፥

፲፪ እሊህም፡ለጥፋት፡እንደ፡ተፈጠሩ፡አእምሮ፡እንደሌለው፡እንስሳ፡ናቸው፡ጥፋታቸውን፡ለማምጣት፡የማያውቁትን፡ይሰድባሉና፡በጥፋታቸው፡የዓመፅ፡ዋጋ፡ይቀበላሉ፥ ኤር፡፲፪፡፲፫፡ይሁ፡ቍ፲፥

፲፫ በዕለት፡መጠጥና፡ተድላ፡ማድረግን፡አጣፍጠው፡ያዩታል፥ እየሳሱ፡ይበላሉ፡እሊህም፡የማይጠግቡ፡ርኩሳን፡ናቸው፡በፍቅራቸው፡ይሸነግላሉ፥ በጎ፡ሥራ፡እንደ፡ሠሩ፡አድርገው፡ለባልንጀ

፲፬ ሮቻቸው፡ይመክራሉ፥ የሚከለክሉት፡የሌለ፡ኃጢአትና፡ዝሙት፡በዓይናቸው፡የተመላ፡ነው፥ ዕውቀት፡የሌላቸውን፡ሰዎች፡ያሸብራሉ፡ሥራቸውም፡ቀሚያ፡ነው፥ ልጆቻቸው

፲፭ ንም፡ያስረግማሉ፥ እውነትን፡መንገድ፡ትተው፡የበለዓምን፡መንገድ፡ተከተሉ፥ የዓመፅን፡ዋጋ፡የወደደ፡የባሶር፡ልጅ፥

፲፮ ዘኍ፡፳፪፡፯፡ራእ፡፪፡፲፬፥ በለዓምን፡በኃጢአት፡ዘለፈው፡የማይናገር፡አህያ፡በሰው፡ቃል፡ተናግሮ፡የነቢዩን፡ስንፍና፡ከለከለና፥

፲፯ ዘኍ፡፳፪፡፳፰፥ ደረቅ፡ወንዝና፡ነፋስ፡የሚበትነው፡ደመና፡እሊህ፡ናቸው፥ የዘለዓለምም፡የሚሆን፡ጽኑ፡ጨለማ፡የሚጠብቃቸው፥

፲፰ ትልቅ፡ኃጢአት፡ተናግረዋልና፡ለሥጋቸው፡የሚሠሩትን፡ዝሙትን፡በመውደዳቸው፡የሰውን፡ልቡና፡ያስደነግጣሉ፥ ጥቂት፡ቀን፡ከኃጢአት፡ተለይተው፡ወደ፡ኃጢአት፡የተመለሱ

፲፱ ናቸው፥ የነፃነትን፡ሕግ፡የተማሩ፡እነሱም፡ለጥፋት፡የተገዙ፡ናቸው፡፡ ሁሉ፡ለታዘዘለት፡የሚገዛ፡ስለ፡ሆነ። ዮሐ፡፰፡፴፡፴፬

፳ ፈጣሪያችንና፡መድኃኒታችን ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡በማወቅ፡ ከዚህ፡ዓለም፡ኃጢአት፡ከተለዩ በኋላ፡ደግመኛ፡እየተመለሱ፡በ ኃጢአት፡ፀንተው፡ለሉ፡ተግዝተ ዋልና፡ከቀደመው፡በደላቸው ም፡የኋላኛው፡በደላቸው፡የጸና ይሆናልና። ማቴ፡፲፪፡፵፭።

፳፩ ዐውቀዋት፡ከተሰጠቻቸው፡ከ ከበረች፡ትእዛዝ፡ተመልሰው ኬመጡ፡የጽድቅን፡ምንገድ፡ ባላወቋት፡በተሻላቸው፡ነበር ና። ሉ፡፲፪፡፵፯፡፵፰።

፳፪ ውሻ፡ወደ፡ትፋቱ፡ተመለሰ፡እሪ ያም፡ታጥባ፡ወደ፡ጭቃ፡ተመለሰ ች፡ብሎ፡በዕውነት፡የመሰሏት ምሳሌ፡ደረሰችባቸው። ምሳ፡፳፮ ፲፩። ምዕራፍ፡፫። ክፍል፡፫።

ይህ፡አሮጌው፡ዓለም፡የሚያልፍ፡ስለሆነ— የማያልፈውን፡«አዲሱን፡ዓለም፡ተስፋ፡እን ድናደርግ— በማይረባ፡በማይጠቅም፡ተም ርት፡መሳት፡እንደማይገባ።—

፩ ወንድሞቼ፥የጻፍሁላችሁ፡ሁለተ ኛ፡መጽሐፍ፡ይህች፡ናት፡በማሳሰብ አነቃቃችሁ፡ዘንድ፡ጽድቅንም በልባችሁ፡ትጠብቁ፡ዘንድ።

፪ ም፩፡፲፫። የቀደሙ፡ቅዱሳን፡ነቢ ያትም፡የነገሩዋችሁን፡ነገር፡ጌታ ችን፡መድኃኒታችን፡ኢየሱስ፡ክ ርስቶስም፡ለኛ፡ለሐዋርያት፡ያዘ ዘንን፡ትእዛዝ፡ታስቡ፡ዘንድ።

፫ ልባቸው፡በወደደው፡ሥራ፡የሚ ሔዱ፡ሰነፎች፡ሰዎች፡ሰውን፡ለ ማስነፍ፡በኋላ፡ዘመን፡ይመጡ ዘንድ፡እንደ፡አላቸው፡አስቀድ ማችሁ፡ይህን፡ዕወቁ። ይመጣ፡ ዘንድ፡እንደሰው፡የተናገረው፡ ቃሉ፡ወዴት፡ተደረገ። ፩ጢሞ፡

፬ ፬፡፩። እነሆ፡የቀደሙ፡አባቶቻች ን፡ሞቱ፡ወዴት፡ተነሡ፡ፍጥረቱ ሁሉ፡ዓለም፡ከተፈጠረ፡ጀምሮ እንደ፡ሰ፡ይኖራል፡ወዴት፡ያልፋ ል፡ይላሉና። ኢሳ፡፭፡፲፱፡ሕዝ፡፲፪፡፳፪፡

፭ ፳፯፡ ማቴ፡፳፬፡፵፰። ቀድሞ፡ሰማ ያትም፡ምድርም፡ከውሀ፡ጋራ፡በ እግዚአብሔር፡ቃል፡እንደ፡ተፈ ጠሩ፡በውሀም፡ሳይ፡እንደ፡ጸኑ። ማቴ፡፳፬፡፵፰፡ዘፍ፡፩፡፪፡፯፡መዝ

፮ ፴፫፡፮። የቀደመውንም፡ዓለም በውሀ፡እንደ፡አጠፋው፡ይህን፡እ ያውቁም። ዘፍ፡፯፡፳፩፡ዘፍ፡፯፡፳፩

፯ አሁንም፡ሰማያትም፡ምድርም ኃጥአን፡እስከሚጠፉበት፡ፍር ድ፡ቀን፡ድረስ፡በዚያ፡ቃል፡ለሳ ልፈት፡ተቀብለዋልና። ቊ፲።

፰ ነገር፡ግን፡ወንድሞቻችን፡ይህ ን፡አትርሱ፡በእግዚአብሔር፡ዘ ንድ፡አንድ፡ቀን፡በሰው፡ዘንድ፡እ ንደ፡ሺህ፡ዘመን፡በእግዚአብሔ ር፡ዘንድ፡አንድ፡ቀን፡ነውና። መዝ

፱ ፺፡፬። እግዚአብሔር፡የተናገረ ውን፡ነገር፡አያስቀርም፡እንደ

ቀር፡ የሚናገሩ፡ አሉና፡ ነገር፡
ግን፡ ስለነሱ፡ ይታገሣል፡ ማንኛ
ውም፡ ያጠፉ፡ ዘንድ፡ አይወድምና
ንስሐ፡ ይገቡ፡ ዘንድ፡ ለሰው፡ ሁ
ሉ፡ ቀን፡ ይሰጣል፡ እንጂ። ዕን ፬
፫፡ ፩ ጢሞ፡ ፪፡ ፬። ሰማያት፡ የሚ
፲ ያልፉበት፡ እግዚአብሔር፡ የሚ
መጣበት፡ ቀን፡ እንደ፡ ሌባ፡ ድን
ገት፡ ትመጣለች፡ የቀደመው
ም፡ ፍጥረት፡ በእግዚአብሔር፡
ፍርድ፡ ያልፋል፡ ምድርም፡ በ
ሷ፡ ላይ፡ ያለ፡ ፍጥረትም፡ ያልፋ
ል። ፩ተሰ ፭፡ ፪፡ ፫፡ ቆ ፯፡ ማቴ ፳፬፡
፵፫፡ ራእ፡ ፳፡ ፲፩።
፲፩ ይህ፡ ሁሉ፡ የሚያልፍ፡ ከሆነ፡ ሃ
ይማኖት፡ ባለው፡ በበጎ፡ ሥራ፡
፲፪ ትኖሩ፡ ዘንድ፡ ቸኩሉ፤ ሰማያ
ት፡ የሚያልፉበት፡ ፍጥረ ት
ም፡ ሁሉ፡ የሚያልፍበት፡ እግ
ዚአብሔር፡ የሚመጣበት ቀ
፲፫ ን፡ ተስፋ፡ አድርጋችሁ፤ ጽድ
ቅ፡ የሚኖርባቸው፡ አዲሱ፡ ሰ
ማይ፡ አዲሲቱ፡ ምድር፡ ተ
ስፋ፡ እናደርጋለን። ራእ፡ ፳፩፡ ፩
፳፯፡ ኢሳ፡ ፷፭፡ ፲፯፡ ና፡ ፷፮፡ ፳፪።
፲፬ አሁንም፡ ወንድሞቼ፡ ከእርሱ
ጋራ፡ እንድ፡ ሁናችሁ፡ ያለኃጢ
አትና፡ ያለበደል፡ ያገኛችሁ
ዘንድ፡ ይህን፡ ተስፋ፡ አድርጋች
፲፭ ሁ፡ ለበጎ፡ ሥራ፡ ቸኩሉ። የእግ
ዚአብሔር፡ ትዕግሥቱ፡ ለኛ፡ ለ
ናንተ፡ ንስሐ፡ ይሰጣችሁ፡ ዘን
ድ፡ ነው። እግዚአብሔር፡ ጥበቡ
ን፡ ስለ፡ ገለጸለት፡ የምንወደው
ወንድማችን፡ ጳውሎስ፡ እንደ
ጻፈላችሁ። ሮሜ፡ ፪፡ ፬።
፲፮ የዚህን፡ ነገር፡ በተናገረባቸው
በመጻሕፍት፡ ሁሉ፡ እንደ አለ፡
ይህን፡ የተናገሩ፡ ግን፡ አውቀው
የተረዱ፡ ሰዎች፡ ናቸው፡ ተም
ረው፡ ያልተረዱት፡ ግን፡ ብዙ
ዎቹን፡ መጻሕፍት፡ ለማብራቸ
ው፡ ይስማሙ፡ ዘንድ፡ እንደመ
ሰላቸው፡ የመጻሕፍትን፡ ቃል
ለውጠው፡ ሰውን፡ ይጐዳሉ።
፲፯ እናንተ፡ ግን፡ ወንድሞቻችን፡ በ
ማይጠቅም፡ ትምርት፡ ስታች
ሁ፡ ከፅኑ፡ ሃይማኖታችሁ፡ እን
ዳትወድቁ፡ ተጠበቁ። ማር ፲፫፡
፲፰ ፳፱፡ ፴፫። ነገር፡ ግን፡ መንፈስ፡
ቅዱስና፡ መድኃኒታችን፡ ኢየሱ
ስ፡ ክርስቶስን፡ እግዚአብሔር፡ አ
ብንም፡ በማመስገን፡ በዝታች
ሁ፡ ኑሩ፡ በዕውነት፡ ያለ፡ ሐሰት
ዛሬም፡ ለዘለዓለምም፡ ጌትነ
ት፡ ያለው፡ ሁለተኛዪቱ፡ የጴ
ጥሮስ፡ መልእክት፡ ተፈጸመች
አስጀምሮ፡ ላስጨረሰን፡ ለእ
ግዚአብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና
ይግባው። ❖ ❖ ❖ ❖

❖ ❖ ❖ ❖ ❖

የዘብዴዎስ ልጅ፡የሐዋርያው፡ የዮሐንስ፡መጀመሪያ፡መልእክት ምዕራፍ፡፩፡ ክፍል፡፩።

በነቢብ፡በገቢር፡የሠራትን፡እንደ፤በሐልዮ፡የሠራትን፡እያውቅም፤በብርሃን፡የተሠራውን፡እንደ፤በጨለማ፡የተሰራውን፡እያውቅም ሙት፡የተነሣው፡ቀዳማዊ፡እምላክ፡እይደለ ምሰሉ፤ቀዳማዊ ነቅናና፡እዋቂ፡መሆኑን፡እ ንደ፡ደረሳቸው።

፩ ርቀቱም፡የነበረ፡የሱን፡ነገር፡እነግራችኋለሁ፡በጆሮ እችን፡የሰማነው፡በዓይናችን፡ያየነው፡ስለ፡ሕይወት፡ነገር፡በእጃችን ዳሰን፡የተናገርነው፡እሱ፡ነው፤ ዮሐ፡፩፡፩፡፲፬፡ሉቃ፡፳፬፡፴፱።

፪ ሕይወትን፡እይተን፡እውቀናታል ና፡ምስክር፡ሆነ፡ከአብ፡ዘንድ፡ያለ ስቸ፡የዘለዓለም፡ሕይወትን፡እ ኛ፡እንነግራችኋለን፡እኛ፡ታው ቃለቸናል፤ዮሐ፡፩፡፲፰፡ዮሐ፡፩፡፩።

፫ እናንተም፡ከኛ፡ጋራ፡እንድ፡ት ሆኑ፡ዘንድ፡ለናንተ፡እንነግራች ኋለን፡እንድነታችንም፡ከአብ፡ከ ባሕርይ፡ልጁም፡ከኢየሱስ፡ጋራ፡

፬ ነውና፡ደስታችሁም፡በእኛ፡የተ ፈጸመች፡ትሆን፡ዘንድ፡ይህን እንድጽፍላችኋለን፤ዮሐ፡፲፫፡፲፮

፭ ና፡፲፯፡፳፩፤ቀድሞም፡ከሱ፡የ ሰማናት፡ትምርት፡ይህች፡ናት እግዚአብሔርም፡ብርሃን፡እን ደ፡ሆነ፡ምንም፡ጨለማ፡እንደሌ ለበት፡እንነግራችኋለን፡መዝ

፮ ፻፫፡፪፡ዮሐ፡፰፡፲፪፤ከሱ፡ጋራ፡ እንድነት፡እለን፡ብለን፡ሁለን፡ወደ ጨለማ፡ምንም፡ብንሔድ፡ሐሰት፡እ ንናገራለን፤እውነትንና፡ቀን ነትን፡እንሰራትምም፡፩፡፬፤

፯ እሱ፡ብርሃን፡እንደሆነ፡ወደ፡ብ ርሃን፡ብንሔድ፡ግን፡እኛ፡እስ በሳቸን፡እንድ፡ነንና፡የኢየሱስ ክርስቶስም፡ደም፡ከኃጢአታ

፰ ችን፡ሁሉ፡ያድነናልና፤ኃጢአት የለብንም፡ብንል፡ግን፡ራሳች ንን፡እንበድላለን፡እውነትም፡ከ

፱ ኛ፡ዘንድ፡የለምና፤ኃጢአታችን ን፡ግን፡እምነን፡ብንናገር፡ኃጢ አታችንን፡ይቅር፡ይለን፡ዘንድ፡ የታመነ፡ቸር፡ነውና፤ከኃጢአታ ችንም፡ሁሉ፡ያነፃናልና፤ምሳ፡፳

፲ ፲፫፡፩፡ተሰ፡፳፩፡፲፫፤እልበደልን ም፡ብንል፡ግን፡እሱን፡ሐሰተኛ እናደርገዋለን፡ቃሉም፡ከኛ፡ዘ ንድ፡የለም።

ምዕራፍ፡፪።

ኃጢአታችንን፡ለማስተሥረይ፡የታመነ፡የ ባሕርይ፡እምላክ፡እንደሆነ፤ፍቅረ፡ቢጽን፡የ ያዘ፡ሰው፤መሰናክል፡እንደ፡ሌለበት፤ይህንን፡የ ለም፡እጥብቆ፡የሚወድ፡የእግዚአብሔር፡ወ ዳጅ፡እንደ፡ይደለ።

፩ ልጆቼ፡እንዳትበድሉ፡ይህን፡እጽ ፍላችኋለሁ፡የበደለም፡ሰው፡ቢ ኖር፡ከአብ፡ዘንድ፡ጻራቀሊጦስ፡

አለኝ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስም፣ኃ
ጢአታችንን፡ይቅር፡ይለን፡ዘንዱ
እውነተኛ፡ነው፤ሮሜ፡፰፡፴፬፡
፪ ዕብ፡፯፡፳፭፤ስለኛ፡ኃጢአት፡
ብቻ፡አይደለም፡ስለ፡ዓለሙም
ኃጢአት፡ነው፡እንጂ፤ቈላ፡፩፡፳
፫ ስለዚህም፡ትእዛዙን፡ብንጠብ
ቅ፡እንደ፡ወደድነው፡እናውቃለ
፬ ን፤እውቀዋለሁ፡የሚል፡ትእዛ
ዙን፡የማይጠብቅ፡ግን፡ሐሰተኛ
ነው፤የእግዚአብሔር፡እውነተ
ኛ፡ፍቅር፡ከሱ፡ዘንድ፡የለም፤ም
፭ ፩፪፡ና፡፱፡፳፫፤ትእዛዙን፡የሚጠ
ብቅ፡ግን፡በውነት፡የእግዚአብ
ሔር፡ፍቅር፡በሱ፡ላይ፡ለሰ፡በር
ሱ፡እንደለነ፡በዚህ፡እናውቃለን
፮ ዮሐ፡፲፬፡፳፩፡፳፫።በሱ፡እኖራለሁ
የሚል፡እሱ፡እንደ፡ሔደ፡
ሊሄድ፡ይገባዋል፤ዮሐ፡፲፫፡፲፭
፯ ወንድሞቼ፡እንግዳ፡ትእዛዝን
የምጽፍላችሁ፡አይደለም፡ቀ
ድሞ፡በናንተ፡ዘንድ፡የነበረች
ውን፡ትእዛዝ፡ነው፡እንጂ፤ይህ፡
የሰማሁት፡ትእዛዝ፡ቀድሞ፡የ
፰ ነበረ፡ነው፤ደግመኛም፡አዲ
ስ፡ትእዛዝን፡እጽፍላችኋለሁ፣
እሱም፡በናንተ፡የታመነ፡ነው
እናንተም፡በሱ፡ኑሩ፤ጨለማ፡
አልፋለችና፡የእውነት፡ብርሃ
ን፡ፈጽሞ፡ታየ፤ሮሜ፡፲፫፡፲፪፤
፱ በብርሃን፡አለሁ፡የሚል፡ባል

ንጀራውን፡የሚጠላ፡ግን፡አ
ሰተኛ፡ነው፡ገና፡እስከ፡ዛሬ፡በጨ
ለማ፡ይኖራል፤ም፫፡፲፭፡ና፡፬፡፳
፲ ባልንጀራውን፡የሚወድ፡ግን፡
በብርሃን፡ይኖራል፡በሱም፡ዘ
ንድ፡መሰናክል፡የለበትም፤ም
፲፩ ፫፡፲፬፤ባልንጀራውን፡የሚጠ
ላ፡ግን፡እሱ፡ወደ፡ጨለማ፡ይሔ
ዳል፡የሚሔድበትንም፡አያው
ቅም፡ጨለማ፡ዓይኑን፡አሳው
፲፪ ሮታልና፤ልጆቼ፡እጽፍላችኋ
ለሁ፡በስሙ፡ኃጢአታችሁ፡ተ
ሠርዮላችኋልና፤ሉቃ፡፳፬፡፵፯
፲፫ ፯፡ዮሐ፡፩፡፲፪፤አባቶች፡እጽፍ
ላችኋለሁ፡ቀድሞ፡የነበረው
ን፡አውቃችኋታልና፤እናንተም
ጕበዛዝት፡እጽፍላችኋለሁ፡
ክፉውን፡ድል፡ነሥታችሁታል
ና፡ልጆቼ፡ጻፍሁላችሁ፡አብን
፲፬ አውቃችሁታልና፤አባቶች፡
ጻፍሁላችሁ፡ቀድሞ፡የነበረው
ን፡አውቃችሁታልና፤ጕበዛዝ
ት፡ጻፍሁላችሁ፡የጸናችሁ፡ና
ችሁና፡የእግዚአብሔርም፡ቃል
በናንተ፡ዘንድ፡ይኖራል፤ክፉ
ውንም፡ድል፡ነሥታችሁታልና
፲፭ ኤፌ፡፮፡፲፤ይህን፡ዓለም፡በዚ
ህ፡ዓለም፡ያለውን፡አትውደዱ
ት፡ይህን፡ዓለም፡የወደደ፡ግን፡
የእግዚአብሔር፡ፍቅሩ፡ከሱ፡
ዘንድ፡የለም፤ያዕ፡፬፡፬።

፲፮ በዚህ፡ዓለም፡ያለ፡ሁሉ፡የሥ
ጋ፡ፈቃድ፡የዓይን፡አምሮ
ት፡የኑሮ፡ትምክህት፡ነውና፡ይህ
ም፡ከአብ፡አይደለም፡ከዓለም
፲፯ ነው። እንጂ፡ዓለሙ፡ያልፋል
ምኞቱም፡ያልፋል፡የእግዚአ
ብሔርን፡ፈቃድ፡የሚሠራ፡ግ
፲፰ ን፡ለዘለዓለም፡ይኖራል። ልጆ
ች፡ይህች፡ሰዓት፡የኋለኛይቱ፡ሰ
ዓት፡ናት፡ሐሳዊ፡መሲሕ፡እንዲ
መጣ፡እንደ፡ሰማችሁ፡ዛሬም፡ብ
ዙ፡ሐሳውያን፡መሲሖች፡ተነሥተ
ዋልና፡በዚህም፡የኋለኛይቱ፡ሰ
ዓት፡እንደሆነች፡አወቅን። ከኛ፡
ወገን፡ያልሆኑ፡ሰዎች፡ከኛ፡ተለ
ይተዋልና፡ማቴ፡፳፬፡፳፬፡፳፬፡፲፫፡፳፪
፲፱ ከኛስ፡ወገን፡ቢሆኑ፡ከኛ፡ጋር፡በኖ
ሩ፡ነበር፡ነገር፡ግን፡ከኛ፡ወገን፡እ
ንደይደሉ፡ይታወቃሉ። የሐዋ፡
፳፡፴፡፩ቆሮ፡፲፩፡፲፱።
፳ እናንተ፡ግን፡ከመንፈስ፡ቅዱስ
ያገኛችሁት፡ዕውቀት፡አላች
ሁ፡ሁሉንም፡ታውቃላችሁ። ዋ
፳፩ ፩፪ ቆጽዱቅን፡እንደማታውቁ
ት፡አዶርጌ፡አልጸፍሁላችሁም
እንደምታውቋት፡እንጂ፡አሰቲ
ሁሉ፡ከጽድቅ፡ወገን፡አይደለች
፳፪ ምናልሰተኛ፡ማነው፡ኢየሱስ
መሲሕ፡አይደለም፡ብሎ፡ከሚ
ክድ፡በቀር፡ይኸውም፡ሐሳዊ
መሲሕ፡አብን፡ወልድንም፡የሚ

፳፫ ክድ፡ነው። ወልድን፡የሚክድ፡
ሁሉ፡አብን፡በማመን፡የለውም፡
በወልድ፡የሚያምን፡አብንም
በማመን፡አለውም። ፬፡፲፭።
፳፬ እናንተ፡ግን፡ቀድሞ፡የሰማች
ሁትን፡ከናንተ፡ዘንድ፡ይኑር፡ቀ
ድሞ፡የሰማችሁት፡በናንተ፡ዘ
ንድ፡ከኖረ። እናንተም፡አብንና
ወልድን፡በማመን፡ትኖራላች
፳፭ ሁ። የዘለዓለም፡ሕይወትን፡እ
ንድናገኝበት፡እግዚአብሔር፡
የነገረን፡ተስፋ፡ይህች፡ናት።
፳፮ ይህነንም፡ስለሚያስቷችሁ፡
ሰዎች፡እንድጽፍላችኋለሁ።
፳፯ እናንተስ፡ከሱ፡ዘንድ፡ያገኛችኋ
ት፡ዕውቀት፡ከናንተ፡ጸንታ፡ትኖ
ራለች፡ማንም፡ያስተምራችሁ
ዘንድ፡አትሹ፡ሁሉንም፡ነገር፡በ
ሱ፡ያለ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ያስተም
ራችኋል፡እንጂ፡የታመነ፡ነው።
አሰትም፡አይደለምቀ ዮሐ፲፬፡፳፮
፳፰ ፯፡ና፡፲፯፡፲፫። እንደ፡ተማራች
ሁት፡በዚያ፡ኑሩ፡አሁንም፡ልጆ
ች፡በሷ፡ኑሩ፡በተገለጠ፡ጊዜ፡ባለ
ምዋልነትን፡እናገኝ፡ዘንድ፡በ
ሚመጣበትም፡ጊዜ፡እንዳናፍ
፳፱ ርቅም፡፫፡፳፩። እውነተኛ፡እንደ
ሆነ፡አውቃችሁ፡ጽድቅን፡የሚ
ሠራ፡ሰው፡ሁሉ፡ከሱ፡እንደ፡ተ
ወለደ፡ዕወቁ ምዕራፍ ፫።

እግዚአብሔር፡እኛን፡ለመውደዱ፡ምልክት፡

ልጆች፡ እናንደ፡ እዲረገኝ፤ ወንድሙ፡ ተቸጋር፡ እዚ የ፡ ገንዘብ፡ የማይሰጥ፡ ሰው፤ እግዚአብሔርን እወደዋለሁ፡ ማለቱ፤ ሐሰት፡ እንዲሆነ፦

፩ የእግዚአብሔር፡ ልጆች፡ እንሆን ዘንድ፡ አብ፡ የሰጠን፡ ፍቅሩ፡ እንዴት፡ እንደ ሆነ፡ ልጆቹም፡ እንደ ሆነ፡ ዕወቁ፡ ስለዚህ፡ ዓለም፡ አላወቀነም፡ እሱን፡ አላወቀውምና፨ ዮሐ ፩፡ ፲፬፡ ፲፫፡ ዮሐ ፲፯

፪ ፫፨ ወንድሞቻችን፡ ዛሬስ፡ የእግዚአብሔር፡ ልጆች፡ ነን፡ ነገር፡ ግን፡ ምን፡ ምን፡ እንድንሆን፡ አልታወቀንም፡ በታወቀልን፡ ጊዜ፡ ግን፡ እንደሱ፡ እንድንሆን፡ እናውቃለን፡ እሱ፡ እንደ ሆነ፡ እሱን እናየዋለንና፨ ሮሜ፡ ፰፡ ፲፯፡ ቈላ ፫

፫ ፬፨ እሱን፡ ያመነ፡ ሁሉ፡ ሰውነቱን፡ ንጹሕ፡ ያደርጋል፡ እሱ፡ ንጹሕ፡ እንደ ሆነ፨

፬ ኃጢአትን፡ የሚሠራ፡ ሁሉ፡ ሕግ፡ መተላለፍን ያደርጋል፡ ኃጢአት፡ ሕግ፡ መተላለፍ፡ ናትና፨

፭ እሱም፡ ኃጢአትን፡ ያርቃት፡ ዘንድ፡ እንደ፡ ተገለጠ፡ ታውቃላችሁ፡ በሱ፡ ግን፡ ኃጢአት፡ የለም፨ ኢሳ፡ ፶፫፡ ፱፳

፮ ፩ጴ፡ ፪፡ ፳፪፨ በሱ፡ አምኖ፡ የሚኖርም፡ ሁሉ፡ አይበድልም፡ ኃጢአት፡ የሚሠራ፡ ሁሉ፡ አያውቀውም፡ አያየውምና፨ ሮሜ፡ ፯

፯ ፲፬፨ ልጆቼ፡ አያስቱአችሁ፡ ጽድቅን፡ የሚሠራ፡ ሁሉ፡ ጻድቅ፡ ነው፡ እሱ፡ ጻድቅ፡ እንደ ሆነ፨ ምዕ

፰ ፳፱፨ ኃጢአትን፡ የሚሠራ፡ ግን፡ ከጋኔን፡ የተወለደ፡ ነው፡ አስቀድሞ፡ ሰይጣን፡ በድሏልና፡ የሰይጣንን፡ ግብር፡ ያጠፋ፡ ዘንድ፡ ስለዚህ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ ተገለጠ፨ ዮሐ ፰፡ ፵፬፨

፱ ከእግዚአብሔርም፡ የሚወለድ ሁሉ፡ ኃጢአትን፡ አይሠራትም፡ እግዚአብሔር፡ የዘራው ዘር፡ በሱ፡ ይኖራልና፡ መበደልም፡ አይቻለውም፡ ከእግዚአብሔር፡ ተወልዷልና፨ ቀ፡ ፬ ም ፭፡ ፲፰፨

፲ የእግዚአብሔር፡ ልጆችና፡ የሰይጣን፡ ልጆች፡ በዚህ፡ የታወቁ፡ ናቸው፨ ጽድቅን የማይሠራ፡ ሁሉ፡ ባልንጀራውንም፡ የማይወድ፡ ከእግዚአብሔር፡ የተወለደ፡ አይደለም፨

፲፩ ይህች፡ ትእዛዝ፡ ቀድሞ፡ የሰማችኋት፡ ናትና፡ እሰበሳችን፡ እንፋቀር፡ ዘንድ፨ ዮሐ ፲፫፡ ፴፬፨

፲፪ ከክፉ፡ ወገን፡ እንደ ሆነ፡ ወንድሙንም፡ እንደ፡ ገደለ፡ እንደ፡ ቃየል አይደለም፡ ስለምን፡ ገደለው የሱ፡ ሥራ፡ ክፉ፡ የወንድሙ፡ ሥራ፡ ግን፡ ጽድቅ፡ ነውና፨ ዘፍ ፬፡ ፰፨ ማቴ ፳፫፡ ፴፭፨ ይሁ፡ ቍ ፲፩፨

፲፫ ወንድሞቻችን፡ ዓለሙም፡ ቢጠላችሁ፡ አታድንቁ፨ ማቴ ፭፡ ፲፩፡ ዮሐ፡ ፲፭፡ ፲፰፡ ፲፱፨

፲፬ እኛ፡ከሞት፡ወደ፡ሕይወት፡እን
ደ፡ሔድን፡እናውቃለን፡ባልን
ጀሮቻችንን፡እንወዳለንና፡ባል
ንጀራውን፡የማይወድ፡ግን፡በ
ጨለማ፡ይኖራል፡ባልንጀራ
ውን፡የሚጠላ፡ሁሉ፡ነፍሰ፡ገዳ
ይ፡ነውቀዮሐ፡፰፡፵፬፡ም፬፡፲፩ዘ
፲፭ ሌ፡፲፱፡፲፯ቀነፍስ፡ለሚገድል፡ሰ
ው፡በሱ፡ላይ፡የምትኖር፡የዘለ
ዓለም፡ሕይወት፡እንደ፡ሌለው፡
ታውቃላችሁቀማቴ፡፭፡፳፩፡፳፪
፲፮ ፍቅሩንም፡በዚህ፡አወቅነው፡እ
ሱ፡ስለኛ፡ሰውነቱን፡አሳልፎ፡ሰ
ጥቷልና፡እኛም፡ስለ፡ባልንጀ
ራችን፡ሰውነታችንን፡መስጠት
፲፯ ይገባናልቀየዚህ፡ዓለም፡ጥሪት
ያለው፡ሰው፡ባልንጀራውን፡ተ
ቸግሮ፡አይቶ፡ምጽዋቱንም፡
የሚከለክለው፡ሰው፡የእግዚ
አብሔር፡ፍቅር፡በሱ፡ላይ፡እን
ደምን፡ይኖራልቀም፡፬፡፳፡
፲፰ ልጆቼ፡በቃልና፡በንደበት፡አን
ፋቀር፡በውነትና፡በሥራ፡ነው
እንጂቀያዕ፡፩፡፳፪፡ና፡፪፡፲፭ቀ
፲፱ በዚህም፡ከእውነት፡ወገን፡እን
ደሆን፡እናውቃለን፡እኛስ፡በፊ
ቱ፡ልባችንን፡እንመርምረው፤
፳ ከኀጢአታችን፡የተነሣ፡ልባ
ችን፡ቢነቅፈን፡ግን፡እግዚአብ
ሔር፡ልባችንን፡ያከብረዋል፡ሁ
ሉንም፡እንዲያውቅ፡ያደርገዋ

፳፩ ሕ፡ ልቡናችንም፡በኀጢአት፡ባ
ይሰጥም፡ብን፡በእግዚአብሔር፡
ዘንድ፡መወደድ፡አለንቀም፪፡፳
፰፡ና፡፬፡፲፯፡ሮሜ፡፬፡፳፡፭፡፩ዕብ፡፬
፳፪ ፲፮ቀየለመነውንም፡ሁሉ፡ከሱ፡ዘ
ንድ፡እናገኛለን፡ትእዛዙን፡እን
ጠብቃለን፡በፊቱም፡ደስ፡የሚ
ያሰኘውን፡ሥራ፡እንሠራለንና፡
፳፫ ማር፡፲፩፡፳፬፡፡ ትእዛዙም፡በልጁ
በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እናምን፡ዘ
ንድ፡ትእዛዙን፡እንደ፡ሰጠን፡እ
ስበሳችንም፡እንፋቀር፡ዘንድ፡
ይህች፡ናትቀዮሐ፡፲፫፡፴፬፡ማር፡፲
፳፬ ፪፡፴፩ቀትእዛዙን፡የሚጠብቅ
ሰው፡በሱ፡ይኖራል፡እሱም፡በ
ሱ፡ያድራል፡ከሰጠን፡ከመንፈ
ስ፡ቅዱስ፡ግራ፡አድሮብን፡እንደ
ኖር፡በዚህ፡እናውቃለን፡፡ዮሐ
፲፬፡፳፫ቀ ምዕራፍ ፬

መምርያ፡ትምርትን፡ሳይመረምሩ፡ማመን፡
እንደማይገባ፡ወንድሙን፡የማይወድ፡ሰው፡እግ
ዚአብሔርን፡እወዳለሁ፡ማለት፡እንደማይቻ
ለው፡እግዚአብሔር፡ስለ፡ሰው፡ፍቅር፡ልጁን፡
ወደዚህ፡ዓለም፡እንደ፡ሰደደ—

፩ ወዳጆቼ፡መንፈስን፡ሁሉ፥
አትመኑ፡ከእግዚአብሔር፡ዘን
ድ፡እንደሆነ፡መርምሩት፡እ
ንጂ፡ብዙ፡ሐሰተኞች፡ነቢያት
ወደዚህ፡ዓለም፡መጥተዋልና፡
፪ የእግዚአብሔር፡መንፈስና፡የ
ሐሰት፡መንፈስ፡በዚህ፡ታው

ቋቋሳችሁ፡ ኢየሱስ ክርስቶ
ስ፡ በሥጋ፡ እንደ መጣ፡ የምታ
ምን፡ መንፈስ፡ የእግዚአብሔ
ር፡ ወገን፡ ናት❖ ፩ቆሮ፡ ፲፪፡ ፫
ኢየሱስ፡ ክርስቶስ በሥጋ፡ እንዳ
ል መጣ፡ የማታምን፡ መንፈስ
ግን፡ የእግዚአብሔር፡ ወገን፡
አይደለችም። እንዲ መጣ፡ የሰ
ማችሁት፡ ሐሳዊ፡ መሲሕ፡ ይህ
ነው። አሁንም፡ ፈጽሞ፡ መጥ
፬ ቶ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ አለ❖ እናንተ
ግን፡ ልጆች፡ የእግዚአብሔር
ልጆች፡ ናችሁ፡ ክፉውንም፡ ድ
ል፡ ነሥታችኋል፡ በዓለም፡ ካ
ለው፡ ከናንተ፡ ጋራ፡ ያለው፡ ይ
በልጣልና❖ ፬ነገ፡ ፮፡ ፲፮፡ ፩፡ ዜና
፭ ፴፪፡ ፯❖ እነርሱ፡ ከዓለም፡ ወገ
ን፡ ናቸው፡ ስለዚህ፡ የዓለምን
ነገር፡ ይናገራሉ፡ ዓለምም፡ ይ
ሰማቸዋልና❖ ዮሐ፫፡ ፴፩፡ ና፲፭፡
፮ ፲፱❖ እኛ፡ ግን፡ የእግዚአብሔር፡
ወገን፡ ነን፡ እግዚአብሔርን፡ የ
ሚወድ፡ ነገራችንን፡ ይሰማናል
የእግዚአብሔር፡ ወገን፡ ያልሆ
ነ፡ ግን፡ አይሰማንም፡ ስለዚህ
ም፡ የእውነትን፡ መንፈስና፡ የ
ሐሰትን፡ መንፈስ፡ እናውቃለን
፯ ዮሐ፰፡ ፵፯❖ ወንድሞቻችን
እስ፡ በሳችን፡ እንፋቀር፡ ፍቅር
ከእግዚአብሔር፡ የታዘዘች፡ ና
ትና፡ የሚፋቀር፡ ሁሉ፡ ከእግ
ዚአብሔር፡ የተወለደ፡ ነው፡ እ
ግዚአብሔርንም፡ ይወደዋል፡
፰ የማይፋቀር፡ ግን፡ እግዚአብ
ሔርን፡ አይወደውም፡ እግዚአ
፱ ብሔር፡ ፍቅር፡ ነውና❖ እግዚ
አብሔር፡ እኛን፡ መውደዱ፡ በ
ዚህ፡ ታወቀ፡ በሱ፡ እንድን፡ ዘን
ድ፡ አንድ፡ ልጁን፡ ወደ፡ ዓለም፡
ሰዶታልና❖ ዮሐ፫፡ ፲፮፡ ቲቶ፡ ፬
፲ ፲፩❖ የእግዚአብሔርም፡ ፍቅ
ሩ፡ ይህ፡ ነው፡ እግዚአብሔርን
እኛ፡ ስለ፡ ወደድ ነው፡ አይደለ
ም፡ እሱ፡ ስለ፡ ወደደን፡ ነው፡ እን
ጂ፡ ኃጢአታችንን፡ ያስተሠር
ይልን፡ ዘንድ፡ ልጁን፡ ልኮታል
ና❖ ሮሜ፡ ፭፡ ፲፬፡ ቆሮ፡ ፭፡ ፲፱፡ ቆ
፲፩ ላ፡ ፩፡ ፳❖ ወንድሞቻችን፡ እግዚ
አብሔር ስ፡ እንዲህ፡ ከወደደን፡
እኛም፡ እስበሳችን፡ እንፋቀር፡
ዘንድ፡ ይገባናል❖ ማቴ፲፰፡ ፴፫
፲፪ እግዚአብሔርን፡ ከቶ፡ ያየው
የለም፡ እስባሳችን፡ ብንፋቀር
ግን፡ እግዚአብሔር፡ ከኛ፡ ጋራ
ይኖራል፡ በኛ፡ ዘንድ፡ ያለ፡ ፍቅ
ሩም፡ የተፈጸመ፡ ነው❖ ዘፀ ፴፫
፳፡ ዮሐ ፩፡ ፲፰፡ ፩ጢሞ፡ ፮፡ ፲፮❖
፲፫ ከሱ፡ ጋራ፡ እንድንኖር፡ በዚህ፡ እ
ናውቃለን፡ እሱ፡ ከሰጠን፡ ከመ
ንፈስ፡ ቅዱስ፡ ጋራ፡ አድሮብን፡
፲፬ ይኖራልና❖ እኛም፡ አብ፡ ልጁን፡
ለዓለም፡ መድኃኒት፡ አድርጎ፡

እንደ፡ ሰደደው። ሰምተን፡ አይተ
፲፭ ናል፤ ኢየሱስ፡ የእግዚአብሔር
ልጅ፡ እንደ ሆነ፡ የሚያምን፡ ሰ
ው፡ ሁሉ። እግዚአብሔር፡ አዱ
ሮበት፡ ይኖራል፡ እሱም፡ ከእግ
ዚአብሔር፡ ጋራ፡ ይኖራል። ም
፲፮ ፫፡ ፫። እኛ ስ፡ አዱሮብን፡ ያለ፡ የ
እግዚአብሔርን፡ ፍቅር፡ አው
ቀን፡ አምነናል፡ ፍቅርም፡ እግ
ዚአብሔር፡ ነው፡ በፍቅርም፡
የሚኖር፡ ከእግዚአብሔር፡ ጋ
ራ፡ ይኖራል፡ እግዚአብሔር፡
፲፯ ከሱ፡ ጋራ፡ ነው። እግዚአብሔ
ር፡ እኛን፡ መውደዱ፡ በዚህ፡ ተ
ፈጸማለች፡ በፍርድ፡ ቀን፡ በሱ
ፊት፡ መወደድን፡ እናገኛለን፡ ዘንድ
በዚህ፡ ዓለም፡ እሱ፡ እንደ ሆነ፡ እ
ኛም፡ ሆነናልና። ም፡ ፫ ፳ ፩።
፲፰ በፍቅራችንም፡ መፍራት፡ የ
ለም፡ የተፈጸመች፡ ፍቅር፡ መ
ፍራትን፡ ከኛ፡ ወደ፡ ፊት፡ ታወጣ
ለች፡ እንጂ፤ በመፍራት፡ መከራ
አለባትና፡ የሚፈራ፡ በፍቅር
፲፱ ፍጹም፡ አይደለም። እኛም፡ አ
ሰበሳችን፡ እንፋቀር፡ እግዚአ
ብሔርንም፡ እንውደደው፡ እሱ
አስቀድሞ፡ ወደናልና። እግዚ
፳ አብሔርን፡ እወደዋለሁ፡ የሚ
ል፡ ባልንጀራውን፡ ግን፡ የሚጠላ
አሰተኛ፡ ነው፤ የሚያየውን፡ ወ
ንድሙን፡ የማይወድ፡ የማያየው
እግዚአብሔርን፡ ይወደዋልና፡
የማያየው፡ ባልንጀራውን፡ የ
ማይወድ፡ ግን፡ የማያየውን፡ እ
ግዚአብሔርን፡ እንዴት፡ ሊወድ፡
ው፡ ይችላልም፡ ፬፡ ፬፡ ፲፩።
፳፩ ከሱ፡ የተቀበልነው፡ ይህ፡ ትእዛ
ዝ፡ አለን፡ እግዚአብሔርንም፡ ባ
ልንጀራችንንም፡ እንወድ፡ ዘንድ፡
እግዚአብሔርን፡ የሚወድ፡ ባል
ንጀራውን፡ ይወዳልና። ማር፡ ፲፪
፴፩።

ምዕራፍ ፭

ወልድን፡ መውደድ፡ አብን፡ መውደድ፡ እንደ ሆነ፡ የእግዚአብሔርም፡ ትእዛዙ፡ ከባድ፡ እንዳ ይደለ፤ ለሞት፡ የሚያበቃ፡ በደል፤ ለሞት፡ የማያ በቃ፡ በደል፤ ልዩ፡ እንደ ሆነ።

፩ ኢየሱስ፡ መሲሕ፡ እንደ ሆነ፡ የሚ
ያምን፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ከእግዚአብሔ
ር፡ የተወለደ፡ ነው፡ ወላጁንም፡ የ
ሚወድ፡ ሁሉ፡ ከሱ፡ የተወለደው
ን፡ ይወዳልና። ዮሐ፡ ፩፡ ፲፪፡ ፲፫።
፪ እግዚአብሔርን፡ በወደድን፡
ጊዜ፡ የእግዚአብሔርን፡ ልጆ
እንድንወደው፡ ትእዛዙንም፡ እ
ንደ፡ ጠበቅን፡ በዚህ፡ እናውቃለ
፫ ንና፡ ም፡ ፫፡ ፲፬። ትእዛዙን፡ እንጠ
ብቅ፡ ዘንድ፡ የእግዚአብሔር፡
ፍቅሩ፡ ይህ፡ ነው፤ ትእዛዙ
ም፡ የከበደ፡ አይደለም። ዮሐ፡ ፲፬
፲፭፡ ፳፫፡ ፳፬፡ ማቴ፡ ፲፩፡ ፴።
፬ ከእግዚአብሔር፡ የተወለደ፡ ሁ
ሉ፡ ይህን፡ ዓለም፡ ድል፡ ይነሣ

ዋልና፡ ድል፡ መንሣቱም፡ ይህ ች፥ ናት፡ ዓለሙን፡ ድል፡ የነሣ ው፡ እሱን፡ ማመናችሁ፡ ነው። ዮሐ፡ ፩፡ ፲፫፡ ዮሐ ፲፮፡ ፴፫።

፭ ይህን፡ ዓለም፡ ድል፡ የሚነሣው ማነው፡ ኢየሱስ፡ የእግዚአብ ሔር፡ ልጅ፡ እንደ ሆነ፡ የሚያም ን፡ ነው፡ እንጂ። ም፡ ፬፡ ፬፡ ፩ ቆሮ፡

፮ ፲፭፡ ፶፯። በውሀና፡ በደም፡ በመን

፯ ፈስም፡ እንደ መጣ፡ በውሀ፡ ብቻ አይደለም፤ በውሀም፡ በደም ም፡ በመንፈስም፡ ነው፡ እንጂ፡ የእውነት፡ መንፈስ፡ እንደ፡ መሆ ኑ፡ የሚመሰክር፡ ነው። ዮሐ፡ ፲፱፡

፰ ፴፬፡ ፴፭። የሚመሰክሩ፡ መን ፈስና፡ ማይ፡ ደም፡ እሊህ፡ ሦስቱ ናቸው። ሦስቱም፡ አንድ፡ ናቸ

፱ ው። ማቴ፡ ፫፡ ፲፯። የሰውን፡ ም ስክርነት፡ የምንቀበል፡ ከሆነ፡ የ እግዚአብሔር፡ ምስክርነት፡ ይ ልቃል፡ የእግዚአብሔ ርም፡ ምስክርነቱ፡ በልጁ፡ ላይ፡ የ መሰከራት፡ ይህች፡ ናትና። ዮሐ ፰፡

፲ ፲፯። በእግዚአብሔር፡ ልጅ፡ የ ሚያምን፡ የእግዚአብሔርን፡ ምስክርነት፡ በሱ፡ አለ፡ በልጁ ያሳመነ፡ ግን፡ አሰተኛ፡ አደረገ ው፡ እግዚአብሔር፡ ለልጁ፡ የ መሰከራትን፡ ምስክርነት፡ አ ላመነምና። ሮሜ ፰፡ ፲፮፡ ዮሐ ፫

፲፩ ፴፫። የዘለዓለም፡ ሕይወትን፡ የሰጠን፡ የእግዚአብሔር፡ ምስክርነቱ፡ ይህች፡ ናት፡ ይ ህቸውም፡ ሕይወት፡ በልጁ፡ የ ተገኘች፡ ናት። ዮሐ፡ ፩፡ ፬።

፲፪ ወልድ፡ ያደረበት፡ ሰው፡ ሕይ ወት፡ አለው፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ ያላደረበት፡ ግን፡ የዘለ ዓለም፡ ሕይወት፡ የለውም።

፲፫ በእግዚአብሔር፡ ልጅ፡ ስም፡ የ ምታምኑ፡ የዘለዓለም፡ ሕይ ወት፡ እንዳላችሁ፡ ታውቁ፡ ዘ ንድ፡ ይህን፡ ጻፍሁላችሁ።

፲፬ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ያለ ቸን፡ ባለሟልነት፡ ይህች፡ ናት፡ በስሙ፡ ከሱ፡ ዘንድ፡ ያሳመነው ን፡ ያሰምናልናም፡ ፯፡ ፳፲፰፡ ፳፩ ፡ ኤፌ፡ ፫፡ ፲፪።

፲፭ ያሳመነውንም፡ እንደ ሰማን ካወቅን፡ እንግዲህም፡ ከሱ፡ ዘ ንድ፡ የምንለምነው፡ ልመና፡

፲፮ እንዳለን፡ እናውቃለን። ባል ንጀራው፡ ለሞት፡ የማያበ ቃ፡ በደል፡ ሲበድለው፡ ያየው፡ ሰው፡ ቢኖር፡ ለሞት፡ የማያበ ቃ፡ በደል፡ የበደለውን፡ ያድነ ው፡ ዘንድ፡ እግዚአብሔርን፡ ይ ለምንለት፡ ለሞት፡ የማያ በቃ፡ በደል፡ አለና፡ ስለሱ፡ ይለ ምኑለት፡ ዘንድ፡ የምናገር፡ አይደለሁም። ማቴ፡ ፲፪፡ ፴፩።

፲፯ አበሳ፡ ሁሉ፡ ኃጢአት፡ ናትና፡

ለሞትም፡የማያበቃ፡ኃጢአ
፲፰ ት፡አለ ፡ከእግዚአብሔር፡የ
ተወለደ፡ሁሉ፡እንዳይበድል፡
እናውቃለን፡ከእግዚአብሔ
ር፡የተወለደ፡ራሱን፡ይጠብቃ
ል፡እንጂ፡ክፉውም፡አያገኘው
ምቆም፡፫፡፱፡ ፬ተሰ ፫፡፫ቍ
፲፱ እኛም፡ከእግዚአብሔር፡እን
ደሌተወለድን፡እናውቃለን፡ዓ
ለም፡ሁሉ፡በክፋት፡ጸንቶ፡ይኖ
፳ ራልቀገላ፡፩፡፬ቊ በእውነት፡እም
ላክ፡የሆነ፡እግዚአብሔርን፡
እናውቀው፡ዘንድ፡የእግዚአ
ብሔር፡ልጅ፡መጥቶ፡ዕውቀት
ን፡እንደ፡ሰጠን፡እናውቃለን፡
እውነተኛ፡አምላክ፡በሚሆን
በእግዚአብሔር፡ልጅ፡በኢየሱ
ስ፡ክርስቶስ፡በማመን፡እንኖራ
ለን፡የዘለዓለም፡ሕይወት፡ለሰ
ንቆዮሐ፡፲፯፡፫፡ሮሜ፡፱፡፭ ፩፡ጢ፡
፫፡፲፮፡ዕብ፡፩፡፰ቊ
፳፩ ልጆቼ፡ራሳችሁን፡በፊ፡ጣዖት
ከማምለክ፡ተጠበቁቈዘፀ፳፡፫
፩ቆሮ፡፲፡፲፬ቊ
፲፪ የዮሐንስ፡መጀመሪያ፡መል
እክት፡በእግዚአብሔር፡አጋ
ዥነት፡ተፈጸመች።
አስጀምሮ፡ላስጨረሰኝ፡ለእ
ግዚአብሔር፡ክብር፡ምስጋና
ይግባው ✦ ✦ ✦
✦ ✦ ✦ ✦

ሁለተኛይቱ፡የዮሐንስ፡መልእ
ቍ፲፫ ምዕራፍ፡፩ ፲፫

ሮምና፡የምትባል፡ሴት፡ለሳምዋ፡እዋምቁ፡ወደሌ
ላ፡አገር፡ከሔዱ፡በኋላ፡አክብሮ፡የሰላምታ፡መል
እክት፡እንደ፡ጸፈላት፡የሊቀጳጳሳትነት፡መዓርጋ፡ለ
ሰው፡ስለተሐተና፡ከኔ፡ከቄሱ፡የተላከ፡መልክት
ብሎ፡እንደ፡ጻፈ —

፩ ከሊቀ፡ከዮሐንስ፡የተላከች፡መ
ልእክት፡ለተመረጠች፡እመቤት፡በ
ውነት፡እኔ፡ለምወዳት፡ለሷ፡ልጆ
ችም፡ትድረስቆ ስለዚች፡ጽጹቆ
ም፡የምወዳት፡እኔ፡ብቻ፡አይደ
ለሁምቆ ጽድቅን፡የሚያውቁ
ትም፡ሁሉ፡ይወዱዋታል፡እንጂ
፩ጴ፡፭፡፲፫፡ዮሐ፡፩ቊ
፪ ከኛ፡ጋራ፡ስለ፡ነበረች፡ዛሬም
ስለ፡አለች፡ለዘለዓለም፡ስለም
፫ ትኖር፡ስለዚች፡ጽድቅቆሞገ
ስና፡ምሕረት፡ሰላምም፡ከእ
ውነትና፡ከፍቅር፡ጋራ፡ከእግ
ዚአብሔር፡ልጅ፡ከኢየሱስ፡ክ
ርስቶስ፡ከእግዚአብሔር፡አብ
፬ ም፡ለናንተ፡ይሁንቆ ከልጆችስ
በእውነት፡የሚሔዱ፡ስላገኘሁ
አጅግ፡ደስአለኝ፡ትእዛዙን፡ከ
አብ፡እንዲ፡ተቀበልን፡መጠንቆ
፭ እመቤቴ፡ሆይ፡አሁንም፡እለ
ምንሻለሁ፡አዲስ፡ትእዛዝ፡እ
ንደምጽፍልሽ፡አይደለም፡ጥ
ንት፡የነበረውን፡ትእዛዝ፡ነው
እንጂ፡እርስ፡በርሳችን፡እንፋቀር

ዘንድ፡ ፩ዮሐ፡ ፪፡ ፳፬።

፮ መፋቀራችንም፡ ይህቺ፡ ናት፡ በእግዚአብሔር፡ ትእዛዝ፡ እንሔድ፡ ዘንድ፡ ትእዛዙም፡ ይህቺ፡ ናት፡ ጥንት፡ በሰማችሁት

፯ እንሔድ፡ ዘንድ። ክርስቶስ፡ በሥጋ፡ እንደ መጣ፡ የማያምኑ፡ ብዙ፡ አስተኞች፡ ወደ፡ ዓለም፡ መጥተዋልና፡ ሐሰተኞች፡ ሐሰዊ መሢሕ፡ ይህ፡ ነው። ፩ዮሐ፡ ፪፡

፰ ፲፰፡ ና ፬፡ ፩፡ ፫። የሠራችሁትን እንዳታጠፉ፡ ለራሳችሁ፡ ዕወቁ፡ ፍጹም፡ ዋጋ፡ ታገኙ፡ ዘንድ፡ ነው፡ እንጂ። ገላ፡ ፬፡ ፲፩።

፱ የሚጠራጠር፡ በክርስቶስ፡ ትምርትም፡ የማይፀና፡ እግዚአብሔር፡ ከእርሱ፡ ጋራ፡ የለም፡ በክርስቶስ፡ ትምርትም፡ የሚፀና፡ ግን፡ አብን፡ ወልድን፡ በማመን፡ አለው። ፩ዮሐ፡ ፪፡ ፳፪፡ ፳፫።

፲ ከናንተ፡ ዘንድ፡ መጥቶ፡ ይህን፡ ትምርት፡ የሚያስተምር፡ ከቤታችሁ፡ አታግቡት፡ እንዴት ዋልህ፡ ስንኳን፡ አትበሉት፡ ቲቶ

፲፩ ስ፡ ፫፡ ፲። እንዴት፡ ዋልህ፡ የሚለው፡ በክፉ፡ ሥራው፡ ይመስላ

፲፪ ልና። የምጽፍላችሁ፡ ብዙ፡ ነበረኝ፡ ነገር፡ ግን፡ በቀለምና፡ በብራና፡ ልጽፈው፡ አልወደድሁም፡ ወደናንተ፡ መጥቼ፡ ቃል፡ ለቃል፡ እንድንነጋገራችሁ፡ አምናለሁና፡ ደስታችሁ፡ ፍጹም፡ ይሆን፡ ዘንድ። ፫፡ ዮሐ፡ ፲፬።

፲፫ የተመረጠች፡ የእኅትሽ፡ ልጆች፡ እንዴት፡ ነሽ፡ ይሉሻል፡ ከፍቀር፡ ጋራ፡ ባለሟልነት፡ ይደረግላችሁ፡ አሜን። ሁለተኛይቱ የዮሐንስ፡ መልእክት፡ ተፈጸመች፡ ለእግዚአብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይግባው።

፫ተኛይቱ፡ የዮሐንስ፡ መልእክት
ምዕራፍ፡ ፩።

ምእመናን፡ የሚቀበል፡ ጋይዮስ፡ ለሚባል፡ ለፃድ፡ ደግ፡ ሰው፡ የበጎ፡ ሥራውን፡ ምስጋና፡ እያስፋፋ፡ እንደ፡ ጻፈለት፡ በምእመናን፡ ላይ፡ ክፉ፡ ምክር የሚመክር፡ ዲዮጥራጤስ፡ የሚባለውን፡ በክፉ ሥራው፡ እንደ፡ ነቀፈው።

፩ ከሊቀ፡ ከዮሐንስ፡ የተላከች፡ መልእክት፡ እኔ፡ በውነት፡ ለምወደው ለወንድማችን፡ ለጋይዮስ፡ ተጽ

፪ ፈ ራስ፤ ፪ዮሐ፡ ፩። ወንድሜ፡ መንግድህ፡ ትቀናልህ፡ ዘንድ፡ ሰውነትህንም፡ ደስ፡ በሚያሰኝ፡ ት፡ ሕይወት፡ ትኖር፡ ዘንድ፡ ስለሁሉ፡

፫ እኔ፡ እጸልያለሁ። ፍቀርን፡ ይዘህ፡ በእውነት፡ እንድትሔድ፡ ወንድሞቻችን፡ መጥተው፡ በመሰከሩልህ፡ ጊዜ፡ እጅግ፡ ደስ፡ አለኝ

፬ ፪ዮሐ፡ ፬። ልጆቼ፡ የምትበልጥ ደስታ፡ የለችኝም፡ ልጆቼ፡ ወደ፡ እውነት፡ ስራ፡ እንዲሔዱ፡ እሰማ፡

፭ ዘንድ። ወንድሜ፡ ለወንድሞቻ

ቸኝ፡ የሠራኽው፡ ሥራ፡ የታመነ፡ ነው። ፬ በፍቅር፡ ላይ፡ በጎ፡ ሥራ ለኝድት ሠራ፡ በምእመናን፡ ፊት፡ ለሚመሰክሩ፡ ለሌሎችም ሰዎች፡ እንዲህ፡ ሥራ። ይህነንም፡ ለእግዚአብሔር፡ የሚገባ፡ ሥራ፡ አስቀድመህ፡ ሠርተሃል። ቲቶ፡ ፫፡ ፲፫። ፭ ስለ፡ ስሙም፡ ተሰደዋልና፡ ከአሕዛብም፡ የተቀበሉት፡ የለምና። ማቴ፡ ፲፫፡ ፬፡ ቆሮ፡ ፱፡ ፲፬፡ ፲፰። ፮ እኛ፡ ግን፡ ወንድሞቻችን፡ እንዲህ፡ ያሉትን፡ ልንቀበላቸው፡ ይገባናል፡ የጽድቅ ተባባሪዎች፡ እንሆን፡ ዘንድ። ዕብ ፲፫፡ ፪። ፯ ለምእመናን፡ አስቀድሞ ጻፍሁ፡ ነገር፡ ግን፡ በሑ፡ ላይ፡ ለለቃ፡ ሊሆን፡ የሚወድ፡ ዲዮጥራጢስ፡ ነገራችንን፡ አይቀበለንም። ፰ ስለዚህም፡ እኔ፡ በመጣሁ፡ ጊዜ፡ የሚሠራውን፡ ሥራ፡ አሳስባቸኋለሁ፡ በኛ፡ ላይ፡ የሚናገረው ክፉ፡ ነገር፡ አልበቃውምና፡ ወንድሞቻችንን፡ አስከ፡ አለመቀበል፡ ደርሶ፡ ሊቀበሏቸው፡ የሚወዱትንም፡ ይከለክላልና፡ ያማመኛም፡ ከቤተ፡ ክርስቲያን፡ ያስወጣቸዋልና። ፲፩ ወንድሜ፡ ክፉ፡ እንደሚሠራ፡ አትሁን፡ በጎ፡ እንደሚሠራ፡ ሁን፡ እንጂ። በጎ፡ የሚሠራ፡ የእግዚአብሔር፡ ወገን ነውና፡ ክፉ፡ የሚሠራ፡ ግን፡ እግዚአብሔርን፡ አያየውም። ፩ዮሐ ፫፡ ፮፡ ፱። ፲፪ ስለ፡ ድሜጥሮስም፡ ሁሉ፡ መሰከረ፡ ጽድቅም፡ መሰከረችለት፡ እኛም፡ መሰከርንለታል፡ ምስክርነታችንም፡ እውነት፡ እንደ፡ ሆነ፡ ታውቃላችሁ። ዮሐ ፲፱፡ ፴፭፡ ፳፩፡ ፳፬። ፲፫ የምጽፍልህ፡ ብዙ፡ ነበረኝ፡ ነገር፡ ግን፡ በቀለምና፡ በብዕር፡ እጽፍልህ፡ ዘንድ፡ አልወደድሁም። ፲፬ ፪ዮሐ፡ ፲፪። ፈጥኜ፡ እንድ ደይህ ቃል፡ ለቃልም፡ እንድ ነጋገርህ፡ ለምኛለሁ፡ ሰላም፡ ላንተ፡ ይሁን። ወንድሞቻችንም፡ እንዲተነህ፡ ይሉሃል፡ ወንድሞቻችንን ስማቸውን፡ እየጠራህ፡ እንዲቱ፡ ናቸው፡ በልልኝ። ፲፭ ፫ተኛይቱ፡ የዮሐንስ፡ መልእክት፡ ተፈጸመች። ለእግዚአብሔር፡ ምስጋና ይግባው ◆ ◆ ◆ ◆

የጌታችን፡ ወንድም፡ የያዕቆብ፡ መልእክት። ፩ኛ፡ ምዕራፍ፡ ፩ኛ ክፍል።

የጌታ፡ ወንድም፡ ሐዋርያው፡ ያዕቆብ፡ በስደት፡ ለነበሩ፡ ለአሥራ፡ ሁለቱ፡ ነገደ፡ ፲ል፡ የመጣባቸውን፡ መከራ፡ በጸሰታ፡ እንዲቀበሉ፡ የምክር፡ ቃል፡ እንደ፡ ጻፈላቸው —

=

፩ የእግዚአብሔር፡ አብ፡ የጌታችን የኢየሱስ፡ ክርስቶስም፡ ባርያ፡ ከሚሆን፡ ከያዕቆብ፡ የተላከች፡ መልክት፡ ለተበተኑ፡ ለአሥራ፡ ሁ

ለቱ፡ነገድ፡ትድረስ፡ሰላም፡
ላናንተ፡ይሁን። ፩ጴጥ፡፩፡፮።

፪ ወንድሞቼ፡ሆይ፡ልዩ፡ልዩ፡ፈተ
ና፡በመጣባችሁ፡ጊዜ፡በሁሉ፡ደ
ስ፡ይላችሁ፡ሁኑ። ሮሜ፡፭፡፫።

፫ የሃይማኖታችሁ፡ፈተና፡ትዕግ
ሥትን፡እንዲያደርግላችሁ

፬ አውቃችሁ። በትዕግሥት፡ፍ
ጹም፡ሥራ፡አለባት፡ሐይወት
ያላችሁ፡ፍጹማን፡ትሆኑ፡ዘን
ድ፡ምን፡ምን፡የሚጐድላችሁ

፭ ሳይኖር። ከናንተ፡ወገን፡ጥበብ
የሌለው፡ሰው፡ቢኖር፡ለሁሉ፡
አብዝቶ፡ከሚሰጥ፡ከእግዚአ
ብሔር፡ዘንድ፡ይለምን፡ሳይነ
ጸየርና፡ሳይሰድብ፡ለሱ፡ይሰጠ
ዋልና። ምሳ፡፪፡፫፡፬፡ማር፲፩፡፳፬

፮ ሳይጠራጠር፡አምኖ፡ይለምን
የሚጠራጠር፡ሰው፡ነፋስ፡እ
ንደሚመታው፡እንደሚያነሣ
ው፡የባሕር፡ሞገድ፡ይሆናል

፯ ና። ለዚያም፡ሰው፡ከእግዚአብ
ሔር፡ዘንድ፡ምን፡ምን፡የሚ

፰ ያገኝ፡አይምሰለው። ሁለቱ፡ል
ብ፡የሆነ፡ሰው፡በመንገዱ፡ሁሉ
የጸና፡አይደለምና። ም፩፡፳።

፱ ድኻ፡ወንድማችን፡ከፍ፡በማ
ለቱ፡ደስ፡ይበለው። ም፬፡፳።

፲ ባለጸጋም፡በመዋረዱ፡እንደ፡
ሣር፡ፍሬ፡ያልፋልና፡፩ጴ፡፩፡፳፬

፲፩ ፀሐይ፡ከዋዕዩ፡ጋራ፡በወጣ፡ጊ
ዜ፡ሣሩን፡እንዲያደርቀው፡ፍ
ሬው፡እንዲረግፍ፡ለምላሚ
ውም፡እንዲጠፋ፡ባለጸጋውም
በመንገዱ፡ሁሉ፡እንዲሁ፡ይጠ
ፋልና። ኢሳ፡፵፡፮፡፯።

፲፪ መከራን፡የሚታገሣት፡ሰው፡
የተመሰገነ፡ነው፡በመከራ፡ከ
ተፈተነ፡በኋላ፡እግዚአብሔር፡
ለሚወዱት፡ተስፋ፡ያናገረላቸ
ውን፡የሕይወት፡አክሊል፡ይቀ
በላልና። ራእ፡፪፡፲፡፪ጢሞ፡፬

፲፫ ፰። የሚፈተን፡ሰው፡ቢኖር፡እ
ግዚአብሔር፡ፈተነኝ፡አይበል
እግዚአብሔር፡ለክፉ፡አይፈ
ተንምና። እሱስ፡ማንንም፡አ
ይፈትንም። ፩ቆሮ፡፲፡፲፫።

፲፬ እያንዳንዱ፡ወዱ፡በሥራው፡ይ
ፈተናል፡እንጂ፡ወዱ፡ፈተናም፡
በወጣ፡ጊዜ፡ይደነግጣልና፡ሮሜ

፲፭ ፯፡፯፡፰። ልብ፡ፍትወትን፡በፀነ
ሰች፡ጊዜ፡ኃጢአትን፡ትወልዳ
ለችና። ኃጢአትም፡በተፈጸመ
ች፡ጊዜ፡ሞትን፡ታመጣለች፡ሮ

፲፮ ፯፡፳፫። የተወደዳችሁ፡ወንድ

፲፯ ሞቻችን፡አያስቱችሁ። በጎ፡ሀ
ብት፡ሁሉ፡ፍጹም፡እድልም፡
መሰወጥ፡የሌለበት፡ማንም፡
ከሱ፡የሚያመልጥ፡የሌለ፡ከብ
ርሃን፡አባት፡ዘንድ፡ከወደ፡ላይ፡

፲፰ ትሰጣለች። መል፡፫፡፮፡ዮሐ፡፩፡፲፯
እሱ፡በፈቃዱ፡በውነተኛ፡ቃሉ፡

ወልደናልና፡ለፍጥረቱ፡ተቀ
ዳሚዎች፡እንሆን፡ዘንድ፡ዮሐ
፩፡፲፫፡፩ጴጥ፡፩፡፳፫።
፲፱ አሁንም፡ወንድሞቼ፡ተቀዳሚ
ዎች፡ሁኑ፡ሰው፡ሁሉ፡ለመስማ
ት፡የቸኰለ፡ለመናገርና፡ለቍጣ
የዘገየ፡ይሁን። መክ፡፯፡፲።
፳ የሰው፡ቍጣው፡የእግዚአብሔ
ርን፡አያሠራውምና። ኤፌ፡፬፡
፳፩ ፳፪። አሁንም፡ኃጢአትን፡ከፋ
ትንም፡ሁሉ፡ተዋት፡ነፍሳችሁ
ን፡ማዳን፡የሚቻለው፡በልባች
ሁ፡የተዘራውን፡ቃል፡በቀንነት
ተቀበሉት። ሮሜ፡፲፫፡፲፪፡ቆላ፡፫፡፰።
፳፪ ሐሳችሁንም፡የምትፈጽሙ፡ሁኑ፡
በመስማት፡ብቻ፡አይደለም፡እ
ስኪ፡እናንተ፡መርምሩ። ማ
ቴ፡፯፡፳፮፡ሮሜ፡፪፡፲፫። ትምርትን
፳፫ ም፡ሰምቶ፡የማይሠራው፡ሰው
ቢኖር፡ፊቱን፡በመስታዋት፡የ
ሚያይ፡ሰው፡ይመስላልና፡ሉቃ፡
፳፬ ፮፡፵፱። አይቶ፡ከሔደ፡በኋላ፡እን
ደምኖ፡እንደሆነ፡የዘነጋ፡ነውና።
፳፭ ከኃጢአት፡ነፃ፡የሚያደርገው
ን፡ሕግ፡የተመለከተ፡ግን፡መከ
ራውንም፡የታገሠ፡ሕግን፡ይፈ
ጽማል፡እንጂ፡የሰማውን፡የዘ
ነጋ፡ያልሆነ፡ይህ፡በሥራው፡የተ
መሰገነ፡ነው። ም፡፪፡፲፪፡ዮሐ፡፲፫
፳፮ ፲፯። ለእግዚአብሔር፡ብሎ፡ከ
መብላ፡የተከለከለ፡ሰው፡የ
ሚመስለው፡ቢኖር፡እንደበቱ
ን፡የማይገታ፡ልቡናውን፡የሳ
ተ፡እንዲህ፡ያለ፡ሰው፡ከመብል
መከልከሉ፡ከንቱ፡ነው። መዝ፡
፳፯ ፴፬፡፲፫። ነውር፡በሌለበት፡በእ
ግዚአብሔር፡ዘንድ፡የተወደ
ደች፡መከልከልስ፡ይህች፡ናት
እናት፡አባት፡የሌላቸውን፡ል
ጆች፡ባልቴቶቹንም፡በችግ
ራቸው፡ተጐብኙ፡ዘንድ፡ሰው
ነታችሁንም፡ከስስት፡ተጠብ
ቁ፡ዘንድ፡ነው።

ምዕራፍ ፪።

ሃይማኖት፡ለሰው፡ይምሰል፡እንደይደሉ፡በማኅበር፡ውስጥ፡ባለጸጋውን፡አክብሮ፡መቀበል፡ድኃውን፡ንቆ፡ማዋረድ፡ማድላት፡ናትና፡የግብዝነት፡ሥራ፡እንደሆነ።

፩ ወንድሞቼ፡ክብር፡ምስጋና
ይግባው፡ና፡በጌታችን፡በኢየሱ
ስ፡ክርስቶስ፡የምትሆን፡ሃይ
ማኖታችሁ፡ለሰው፡ይምሰል፡
፪ አትሁን። መልካም፡ልብስ፡የለ
በሰ፡የወርቅ፡ቀለበት፡ያደረገ፡
ሰው፡ወደ፡ጉባኤያችሁ፡ቢገፋ
ያደፈ፡ልብስ፡የለበሰም፡ድኃ
፫ ቢገባ። ያማረ፡ልብስ፡የለበሰ
ውን፡አይታችሁ፡አንተ፡በመል
ካም፡ስፍራ፡ተቀመጥ፡ብትሉ
ት፡ድኃውን፡ግን፡አንተ፡ወዲያ
ቁም፡ብትሉት፡ያውም፡ሳይሆ

ከእግራችን፡በታች፡ተቀመ
፬ ጥ፡ብትሉ፥ እንግዲህ፡ለራሳ
ችሁ፡ማድላታችሁ፡አይደለም
ን፡ለክፉ፡አሳብስ፡ዳኞች፡መሆ
፭ ናችሁ፡አይደለምን፧ የተወደ
ዳችሁ፡ወንድሞቻችን፡ስሙ፡
የዚህን፡ዓለም፡ድሆች፡እግዚአ
ብሔር፡የመረጣቸው፡አይደሉ
ምን፡ባለጸጎችም፡እግዚአብ
ሔር፡ለወዳጆቹ፡ያናገረላቸው
ን፡መንግሥት፡በሃይማኖታቸ
ው፡እንዲወርሱ፡ተመርጠዋል
፩ቆሮ፡፩፡፯፡ዘፀ፡፳፯፤
፮ እናንተ፡ግን፡ድሆችን፡አቃለላ
ችኋቸው፡ባለጸጎችማ፡ገንዘ
ባችሁን፡የሚቀሟችሁ፥ ወደ፡
ፍርድ፡አደባባይም፡የሚስድዋ
፯ ችሁ፡አይደሉምን፥ ድሆች፡ግ
ን፡በናንተ፡የተጠራ፡የከበረ፡ስ
፰ ሙን፡ይሰድባሉ፥ መጽሐፍ፡ባ
ልንጀራህን፡ውደድ፡ብሎ፡እን
ደ፡ተናገረ፡ሕጉን፡ከፈጸማችሁ
በጎ፡ተሠራላችሁ፥ ማር፡፲፪፡፴፩
፱ ዘሌ፡፲፱፡፲፰፤ ፊት፡አይታችሁ፡
ግን፡ብታደሉ፡ኀጢአት፡ትሠ
ራላችሁ፡ሕግ፡እንደ፡ተላላፊ
ይዘልፋችኋል፥ ዘዳ፩፡፲፯፡ና
፲ ፲፮፡፲፱፥ በጕውን፡ሁሉ፡ሠርቶ፡
ባንዲቱ፡የሚስት፡በሁሉ፡የበ
፲፩ ደለ፡ሆኖአል፡ማቴ፡፭፡፲፱፥ ወደ፡ሰው
ሚስት፡አትሒድ፡ያለው፡ነፍስ፡

አትግደል፡ብሏልና፡ወደ፡ሰው
ሚስት፡ባትሔድ፡ነፍስ፡ግን፡ብ
ትገድል፡ከሕግ፡የወጣህ፡ሆንህ
፲፪ ዘፀ፡፳፡፲፫፡፲፬፥ እንግዲህ፡ንገሩ፡እ
ንዲህም፡ሥሩ፤ በምታደርግ
ሕግ፡ይፈረድባችሁ፡ዘንድ፡እ
ንዳላችሁ፥ ም፩፡፫፡፳፭፥
፲፫ የምሕረት፡ሥራ፡ያልሠራ፡በ
ፍርድ፡ቀን፡ምሕረት፡የለው
ምና፡ነገር፡ግን፡የምሕረት፡ሥ
ራ፡የሠራ፡ሰው፡በፍርድ፡ቀን፡
ይመካል፥ ማቴ፡፭፡፯፡ና፡፲፰፡፴፫
፴፭፡ና፡፳፭፡፴፭፡፴፯፥
፲፬ ወንድሞቼ፡ሃይማኖት፡አ
ለኝ፡በጎ፡ምግባር፡ግን፡የለኝም
የሚል፡ሰው፡ቢኖር፡ምን፡ይጠ
ቅማል፡በውኑ፡ሃይማኖቱ፡ብ
፲፭ ቻ፡ሊያድነው፡ይቻላልን፧
ማቴ፡፯፡፳፮፥ ወንድሞቻችን፡
ወይም፡ከእኅቶቻችን፡ወገን፡
ልብስ፡የሌላቸው፡የዕለት፡
ምግብ፡ያጡ፡ቢኖሩ፥ ሉ፫፡፲፩
፲፮ በደኅና፡ሒዱ፡እሳት፡ሙቁ፡ጠ
ግባላችሁ፡የሚላቸው፡ሰው
ቢኖር፡ለችግራቸው፡የሚ
ሹትን፡ካልሰጣቸው፡ምን፡
ይጠቅማቸዋል፧ ፩ዮሐ፡፫፡፲፯
፲፯ እንደዚህም፡በጎ፡ምግባር፡የሌ
ለት፡ሃይማኖት፡ሥራ፡አትሠ
፲፰ ራም፥ ነገር፡ግን፡አንተ፡ሃይማ
ኖት፡አለህ፡እኔ፡በጎ፡ምግባር፡

አለኝ፡ ሃይማኖትህን፡ ያለ፡ ም
ግባር፡ አሳየኝ፨ እኔ፡ ግን፡ ሃይ
ማኖቴን፡ ከምግባሬ፡ ጋራ፡ አሳ
፲፱ የሃለሁ፨ ገላ፡ ፩፡ ፪፨ አንተ፡ አ
ምላክ፡ አንድ፡ እንደሆነ፡ ታ
ምናለህ፡ መልካም፡ ታደር
ጋለህ፡ እንደዚህስ፡ አጋንንት
ም፡ ያምናሉ፡ ይንቀጠቀጣሉ፨
፳ አንተ፡ ሰነፍ፡ ሰው፡ ሃይማኖት
ዶለ፡ ምግባር፡ ሥራ፡ እንደተሠ
፳፩ ራ፡ አታውቅምን፨ አባታችን፡
አብርሃም፡ በምግባሩ፡ አብሮ
የስምን፡ ልጁ፡ ይስሐቅን፡ ለመ
ሥዕት፡ ባቀረበው፡ ጊዜ፨ ዘፍ፳፪
፳፪ ፰ ፱፡ ፲፡ ፲፪፨ ሃይማኖት፡ ለምግ
ባር፡ ረዳት፡ እንደሆነች፡ ታያለ
ህን፡ በምግባሩም፡ ሃይማኖቱ፡ ፍ
፳፫ ጹም፡ ሆነ፨ አብርሃም፡ ለእግዚ
አብሔር፡ አመነ፡ ጽድቅም፡ ሁ
ኖ፡ ተቈጠረለት፡ ብሎ፡ መጽ
ሐፍ፡ የተናገረው፡ ተፈጸመ፡ የ
እግዚአብሔር፡ ወዳጅም፡ ተባ
ለ፡፡ ዘፍ፲፭፡ ፮፡ ኢሳ፡ ፵፩፡ ፰፡፡
፳፬ ሰው፡ በሃይማኖት፡ ብቻ፡ ያይደ
ለ፡ በሥራው፡ እንዲከብር፡ ታ
ያላችሁን፡፡ እንደዚሁም፡ ዘማዊ
ቱ፡ ረዓብ፡ በሥራዋ፡ ከበረች
ኮ በሾቹን፡ ተቀብላ፡ በሌላ፡ መ
ንገድ፡ በሰደደቻቸው፡ ጊዜ፡ ዕ
፳፭ ብ፡ ፲፩፡ ፴፩፡፡ ነፍስ፡ የሌለው፡ ሥ
ጋ፡ የሞተ፡ እንደሆነ፡ እንደዚሁ

በኋ፡ ምግባር፡ የሌላት፡ ሃይማ
ኖትም፡ የሞተች፡ ናት፨ ፲፪

ምዕራፍ፡ ፫።

ሳያስተምሩ፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ መምሕራን፡ እንደ
ይሆኑ— እንደበት፡ ከፉ፡ ነገር፡ እየተናገረ
ች፡ ሰውን፡ ሁሉ፡ እንዳታጠፋ፡— መቃናት፡
ከአጋንንት፡ ባሕርይ፡ የተገኘች፡ እንደ፡ ሆነች

፩ ከናንተ፡ ወገን፡ ብዙዎች፡ መምራ
ን፡ አይሁኑ፡ ወንድሞቻችን፡ የበለ
ጠች፡ ፍርድ፡ እንድንቀበል፡ ታ
፪ ውቃላችሁ፨ ሁላችን፡ ብዙ፡ እን
በድላለን፡ በቃሉ፡ የማይበድ
ል፡ ግን፡ ፍጹም፡ ነው፡ ሥጋውን፡
ሁሉ፡ ከበደል፡ ይገታ፡ ዘንድ፡ ይ
፫ ችላል፨ ይታዘዙልን፡ ዘንድ፡ እነ
ሆ፡ በፈረሶች፡ አፍ፡ ልጓም፡
እናገባለን፡ ሥጋቸውንም፡ ሁሉ
በልጓም፡ እንስበዋለን፨ መዝ
፬ ፴፪፡ ፱፨ አካላቸው፡ ይህን፡ ያህ
ል፡ ታላቅ፡ የሚሆን፡ መርከቦች
ን፡ በነፋስ፡ ኃይል፡ ተነድተው፡ በ
ተመለሱ፡ ጊዜ፡ ይህን፡ ያህል፡ ታ
ናሽ፡ በሚሆን፡ ትርከዝ፡ ሰው፡ ይ
መልሳቸዋል፡ ወደ፡ ወደደውም
፭ ወደብ፡ ያገባቸዋል፤ እንደዚህ
ም፡ አንደበት፡ ትንሽ፡ አካል፡ ና
ት፡ ታላላቅም፡ ነገር፡ ትናገራለ
ች፨ እነሆ፡ እሳትም፡ እጅግ፡ ትን
ሽ፡ ናት፡ ምን፡ የሚያህል፡ ሰውን፡ ታ
ላቅ፡ ዘፍ፡ ታቃጥለዋለች፨

፮ ልሳኗም፡የዓለም፡ሁሉ፡ሓፍ
የመሳበቱ፡እሳቱ፡ናቱ፡እነሆ
በሰውነታችን፡ውስጥ፡ተፈጥ
ሯልና፡ሥጋችንን፡ታቃጥለዋ
ለች፡በሥጋችን፡የተሠወረች
ነፍሳችንንም፡ትለበልባለች
ከገሃነም፡ይልቅ፡ታቃጥላለች
ማቴ፡፲፭፡፲፮፡፲፱፡ም፲፪፡፴፮፡፴

፯ ፯ቱ፡የአራዊትና፡የአዕዋፍ፡በ
ባሕርም፡የሚመላለስና፡የእ
ንስሳ፡ባሕርይ፡ሁሉ፡ለሰው፡

፰ ባሕርይ፡ይገዛልና፡የሰውን፡አ
ንደበት፡ማን፡ሊገዛት፡የሚቻ
ለው፡የለም፡ክፉ፡ናት፡ለክፋ
ቷም፡ልክ፡የለውም፡የሚገድ
ል፡መርዝም፡የተመላች፡ናት

፱ መዝ፡፻፡፵፬፡፡ በሷ፡እግዚአብሔ
ር፡አብን፡እናመሰግነዋለን፡በ
እግዚአብሔር፡አምሳል፡የተ
ፈጠረውን፡ሰው፡በሷ፡እንረ
ግመዋለን፡ዘፍ ፩፡፳፯፡

፲ ወንድሞቻችን፡ካንድ፡አፍ፡በ
ረከትና፡መርገም፡ይወጣ፡ዘን
ድ፡ይህ፡ሊሆን፡አይገባም፡

፲፩ ካንድ፡ምንጭ፡ካንድ፡ጕድጓ
ድም፡መራራ፡ውሀና፡የሚጣ
ፍጥ፡ውሀ፡ሊወጣ፡ይቻላልን፡

፲፪ ወንድሞቻችን፡በለስ፡ዘይቶ
ን፡ወይም፡ወይን፡በለስን፡ያፈራ
ዘንድ፡ይቻላልን፡እንደዚህም
መራራ፡ውሀ፡የጣፈጠም፡ውሀ
መራራ፡አይሆንም፡

፲፫ ከበጎ፡አካሔዱ፡የተነሣ፡በቅ
ንነትና፡በጥበብ፡ሥራውን፡ይ
ግለጥ፡ዘንድ፡የተፈተነ፡አዋቂ
ከናንተ፡ወገን፡ማነው፡ቈሎ
፫፡፲፫፡ም፬፡፲፰፡

፲፬ የሚያሳዝን፡መቅናትና፡መ
ከራከርስ፡በልባችሁ፡ካለባ
ችሁ፡አትመኩ፡እውነትንም
አታሳብሉ፡ኤፌ ፬፡፴፩፡

፲፭ ይህችም፡ጥበብ፡ከላይ፡የወረ
ደች፡አይደለችም፡በምድር፡
ከአጋንንት፡ባሕርይ፡የተገኘ
ች፡ናት፡እንጂ፡ም፩፡፳፡፲፯፡

፲፮ መቅናት፡ካለ፡ዘንድ፡ሁከት
ና፡ክርክር፡ክፉም፡ሥራ፡ሁሉ

፲፯ ከዚያ፡አለና፡ከሰማይ፡የወ
ረደች፡የቀደመች፡ጥበብ፡ግ
ን፡ከዚህ፡ሁሉ፡የራቀች፡ናት
የምታስማማ፡ያለመጠን፡እ
ሺ፡በጂ፡የምትል፡ምሕረትን
ም፡የተመላች፡ናት፡ፍሬዋ
ም፡በጎ፡ነው፡ያለ፡ጥርጥር፡

፲፰ የታመነች፡ናት፡ጽድቅ፡የ
ሚሆን፡ፍሬዋም፡ሰላም፡ለ
ሚያደርጉ፡ሰዎች፡በሰላም
ይዘራል፡ኢሳ ፴፪፡፲፯፡

ምዕራፍ፡፬

፩ ብ፡ክርክር፡የሚነሳው፡በቀልጥም፡የሚ
ሞላ፡ዝሙትን፡በመውደድ፡እንደሆነ—
የሰው፡እናዋሩ፡ከጕድጓድ፡እንደሚወጣ፡

ጭስ፡ፈጥኖ፡እንዲጠፋ፤

፩ ጸብ፡ክርክር፡ከወዴት፡መጣባችሁ፤በቀልዋማችሁ፡የሚዋጋ፡ዝሙትን፡ከመውደድ፡የተነሣ፡ከዚህ፡የተገኘ፡አይደለምን፫

፪ ፩ጴ፡፪፡፲፩◆ተመኛችሁ፡የምትሹትን፡አታገኙትም፡እየተቃናችሁ፡ትጋደላላችሁ፡ስለዚህም፡መዳን፡አይቻላችሁም፤እየተጣላችሁ፡ትዋጋላችሁ፡የምትሹትንም፡አታገኙም፤

፫ አትለምኑምና፥ብትለምኑም፡አይሰጧችሁም፡ሰውነታችሁን፡ለዝሙት፡ትሰጡ፡ዘንድ፡ክፉ፡ትለምናላችሁና◆መዝ፡፲፰፡

፬ ሚ፡፳◆ዘማውያን፡ሆይ፡ዘማውያን፡የዚህ፡ዓለም፡ወዳጅ፡የእግዚአብሔር፡ጠላት፡እንደሆኑ፥አታውቁምን፡የዚህን፡ዓለም፡ፍቅር፡የወደደ፡የእግዚአብሔር፡ጠላት፡ይሆናልና፡ሉ፡፲፮፡፲፫፡ሮሜ፡፰፡፯፡፩ዮሐ፡፪፡፲፭◆

፭ ወይስ፡ከናንተ፡አድሮ፡ያለ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡መቃናትን፡እንዲወድ፡መጽሐፍ፡በሐሰት፡የሚናገረ፡ይመስላችኋልን◆ገላ፡፭፡

፮ ፲፯◆ነገር፡ግን፡ፈጣሪያችን፡የበለጠ፡ክብርን፡ይሰጠናል፡ስለዚህም፡እግዚአብሔር፡ትዕቢተኞችን፡ቸል፡ይላቸዋል፡ራሳቸውን፡ለሚያዋርዱ፡ግን፡ክብርን፡ይሰጣቸዋል፡አሶ◆ኢዮ፡፳፪፡፳፱፡ማቴ፡፳፫፡፲፪◆

፯ እግዚአብሔርን፡እሺ፡በጄ፡በሉት፡ጋኔንን፡ግን፡እምቢ፡በሉት፡ከናንተም፡ይሸሻል◆ኤፌ፡፬፡፳፯

፰ እግዚአብሔርን፡ቅረቡት፡እሱም፡ይቀርባችኋል፡ኃጥአን፡እጃችሁን፡ንጹሕ፡አድርጉ፡ልባችሁንም፡ንጹሕ፡አድርጉ፡የምትወራወሩም፡እመኑ◆ዘካ፡፩፡፫፡ኢሳ፡፩፡፲፮◆እዘኑ፡አልቅሱ፡ሳቃችሁን፡ወደ፡ልቅሶ፡ደስታችሁንም፡ወደ፡ኀዘን፡መልሱት◆

፲ ራሳችሁን፡አዋርዱ፡እግዚአብሔር፡ያከብራችኋልና◆፩ጴ፡፭፡

፲፩ ፮◆ወንድሞቻችን፡እስበሳችሁ፡አትነቃቀፉ፡ወንድሙን፡የነቀፈ፡የእግዚአብሔርን፡ሕግ፡ነቀፈልና፡በባልንጀራውም፡የሚፈርድ፡በእግዚአብሔር፡ሕግ፡ይፈርዳልና፡ሕጉንስ፡ከነቀፍህ፡ሕግን፡የምትፈጽም፡አይደለህም፡ሕግ፡አፍራሽ፡ነህ፡እንጂ።መዝ፡፲፭፡፫፡፩ጴ፡፪፡፩◆

፲፪ ሕግን፡የሰጠ፡በሕግ፡አፍራሽም፡የሚፈርድ፡አንድ፡ነውና፡ማዳንም፡መጣልም፡የሚቻለው፡እሱ፡ነው◆አንተ፡ወንድምህን፡የምትነቅፈው፡ምንድነህ◆ማቴ፡፯፡፩◆

፲፫ ዛሬ፡ወይም፡ነገ፡ወደዚ

ያች፡ አገር፡ እንሔዳለን፡ በሷ
ም፡ እንኖራለን፡ ሥራም፡ ሠር
ተን፡ እንጠቀማለን፡ እንደሚ
ሉ፡ ነገ፡ የሚሆነውንም፡ እንደ፡
ማያውቁ፡ ሰዎች፡ አይደላችሁ
፲፬ ምን፨ ምሳ፡ ፳፯፡ ፩ ፨ አናዋራች
ሁ፡ ምንድነው፡ እንዱ፡ ጊዜ፡ ታይ
ቶ፡ ኋላ፡ እንደሚጠፋ፡ ጢስ፡ አ
ይደላችሁምን፡ ሉቃ፡ ፲፪፡ ፳ ፨
፲፭ እግዚአብሔር፡ ቢፈቅድ፡ ብን
ኖርም፡ ይህንን፡ ወይም፡ ያንን፡
እናደርጋለን፡ በማለት፡ ፈንታ
፲፮ የሐዋ፡ ፲፰፡ ፳፩ ፨ ነገር፡ ግን፡ ዛሬ
በሥራችሁ፥ ትመካላችሁ፡ እን
ዲህ፡ ያለች፡ መመካት፡ ሁሉ፡ ክ
፲፯ ፉ፡ ናት ፨ በጎይቱን፡ ሥራ፡ አው
ቆ፡ የማይሠራት፡ ኃጢአት፡ ት
ሆንበታለች ፨ ሉ፡ ፲፪፡ ፵፯፡ ፬ ፨

ምዕራፍ፡ ፭ ።

ስለ፡ ብዕሳቸው፡ መንቀዝና፡ ስለ፡ ወርቃቸውና፡ ስ
ለ፡ ብራቸው፡ መዛግ፡— ስለ ጸያኝም፡ ስለማይ
መጸውቱ፡ እንዲ፡ ዘለፋቸው፡ ፡ የጸድቅ፡ ሰው፡ ጸ
ሎት፡ ሰውን፡ እንዲጠቅም ።

፩ እሁንም፡ ባለጸጎች፡ ተመጣባች
ሁ፡ ዘንድ፡ ባለት፡ መከራ፡ እየተጨ
ነቃችሁ፡ ኑ፡ አልቅሱ ፨ ምሳ፡ ፲፩
፪ ፳፰፡ ሉ፡ ፯፡ ፳፬ ፨ እህላችሁን፡
ነቀዘ፡ ልብሳችሁንም፡ ብል፡ በ
፫ ላቶታል ፨ ማቴ፡ ፮፡ ፲፱ ፨ ወርቃ
ችሁና፡ ብራችሁም፡ ዛገ፡ ዝገቱ
ም፡ ምስክር፡ ይሆንባችኋል፡
ሥጋችሁንም፡ እንደ፡ እሳት፡ ይበ
ሳዋል፡ ለኋላ፡ ዘመን፡ ስለ፡ አከ
፬ ማቻችሁ ፨ ምድራችሁን፡ የ
ሚያርሱ፡ ግባራችሁን፡ ያመወ
ዛችሁን፡ ቀምታችኋል፡ እነሆ
የቀማችኋቸው፡ ግበራርተም
ይጮኻሉ፡ ጮኻታቸውም፡ እ
ቸናሬ፡ ወደሚሆን፡ ወደ፡ እግዚ
አብሔር፡ ጆሮ፡ ደርሶ፡ ተሰምቷ
ል ፨ ዘጸ፡ ፳፬፡ ፲፬፡ ፲፭ ፨
፭ በምድር፡ ላይ፡ ደስ፡ እሳችሁ፡ ስ
ራት፡ አጎደላችሁ፡ ተድላ፡ ደስ
ታ፡ አደረጋችሁ፡ ለሚታረድበ
ት፡ ቀን፡ ሳምን፡ እንደሚያሰባ
ልባችሁን፡ አደነደናችሁ፡ ሐሳ
ትሳስፋችሁ ፨ ሉቃ፡ ፲፮፡ ፲፱፡ ፳፭
፮ ጸድቁንም፡ ሳይጠላችሁ፡ አይሆ
ንም፡ ሳይሉችሁ፡ ገደላችሁት፡
፯ ወንድሞቻችን፡ ጌታችሁ፡ እስ
ከሚመጣበት፡ ቀን፡ ድረስ፡ መ
ከራውን፡ ታገሡ፡ የከበረችው
ን፡ የምድር፡ ፍሬ፡ እስኪቶሸቶ
ና፡ እስክታፈራ፡ እስክትታጨ
ድም፡ ታግሦ፡ ደጅ፡ እንደሚጠ
ና፡ ገበሬ ፨ ሉ፡ ፳፩፡ ፲፱፡ ዕብ፡ ፲፡ ፴፮፡ ፯
፰ እናንተም፡ ታግሡችሁ፡ ልባች
ሁን፡ አፅኑ፡ ጌታችሁ፡ የሚመጣ
ባት፡ ቀን፡ ቀርባለችና፡ ወንድሞ
ቻችን፡ በባልንጀራችሁ፡ አትዘኑ
እንዳይፈረድባችሁ፡ እነሆ፡ ፈራ
ጅ፡ ከደጃችሁ፡ ምድረክ፡ ቁ

ሞ፡ ይጠብቃልናቀማቴ፡ ፳፬ ፴፫
፯ ወንድሞቻችን፡ መከራችሁን
ለመታገሥ፡ ምሳሌ፡ የሚሆናች
ሁ፡ ለእግዚአብሔር፡ ታዘው፡ ት
ንቢት፡ የተናገሩ፡ ነቢያት፡ እሱ
ሳቸሁ፡ መከራውን ― የታገሡ
ትንም፡ እነሆ፡ እናመሰግናቸዋ
፰ ለን። ማቴ፡ ፭፡ ፲፪ ቀየኢዮብንም
ትዕግሥቱን፡ ዕምታችኋል፡እ
ግዚአብሔርም፡ እንደፈጸመለ
ት፡ ለይታችኋል፡ የእግዚአብሔ
ር፡ ቸርነቱ፡ ይቅርታውም፡ ብዙ፡ነ
፱ ው፡ ቀወንድሞቻችን፡ ከሁሉ፡የ
ሚቀድም፡ አትማሉ፡ በሰማይ፡
በምድርም፡ ቢሆን፡ በምንም፡
ቢሆን፡ በሌላ፡ መሐላ፡ ከቶ፡ አት
ማሉ፡ ቃላችሁ፡ እንዱ፡ ይሁን፡ እ
ንጂ፡ እውነት፡ ቢሆን፡ እውነት፡የ
ሌለም፡ ቢሆን፡ የለም፡ ማለት፡
ይሁን፡ ተፈርዶባችሁ፡ ከፍር
ድ፡ በታች፡ እንዳትወድቁ ቀማ
፲ ቴ፡ ፭፡ ፴፬፡ ፩፡ ፵ ፳፯ ቀየሚያዝን፡ሰ
ው፡ ቢኖር፡ ይጸልይ፡ ደስ፡ያለው
ም፡ ቢኖር፡ ያመስግን። መዝ፵
፲፩ ፲፭፡ ቆላ፡ ፫፡ ፲፮ ቀከናንተም፡ ወ
ገን፡ የታመመ፡ ቢኖር፡ በቤተ፡ክ
ርስቲያን፡ ያሉ፡ ቀሳውስትን፡ወ
ርቶ፡ ይጸልዩለትቀበጌታችን፡
በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ስም፡ የጸለ
ዩበትን፡ዘይት፡ ይቀቡት፡ ማር
፲፪ ቆ፡ ፮፡ ፲፫ ቀየሃይማኖትም፡ ጸሎት

ድውዩን፡ ያድነዋል፡ እግዚአ
ብሔርም፡ ያስነሣዋል፡ ኃጢአ
ትም፡ ቢኖርበት፡ ይሠረይለታ
፲፫ ል ቀመዝ፡ ፴፩፡ ፫ ቀእስበሳችሁም
ኃጢአታችሁን፡ ተናዘዙ፡ ለባል
ንጀሮቻችሁም፡ ጸልዩ፡ በሕይ
ወት፡ ትኖሩ፡ ዘንድ፡ የጻድቅም
ጸሎት፡ እጅግ፡ ትረዳለች፡ ግዳ
ጅ፡ መፈጸም፡ ይቻላታልቀመዝ
፲፬ ፬፡ ፴፬፡ ፲፯ ቀኤልያስ፡ እንደኛ፡ያ
ለ፡ ሰው፡ ነው፡ እንዱንታመም፡
ይታመማል፡ ዝናም፡ እንዳይዘ
ንም፡ ጸለየ፡ ሶስት፡ ዓመት፡ ከስድ
ስት፡ ወር፡ በምድር፡ ዝናም፡ አል
ዘነመም ቀሉ፡ ፬፡ ፳፭፡ ፩ነገ፡ ፲፯ ፩
፲፭ ዳግመኛ፡ ይዘንም፡ ዘንድ፡ ጸለየ፡
ሰማይ፡ ዝናሙን፡ ሰጠ፡ ምድር
ም፡ ፍሬዋን፡ አበቀለችቀ፩ነገ፡ ፲፰
፲፮ ፵፪ ቀወንድሞቻችን፡ ከናንተ፡
ወገን፡ ከእውነት፡ መንገድ፡የተ
ሳሳተ፡ ቢኖር፡ ከኃጢአቱም፡ የ
መለሰው፡ ቢኖር ቀገላ፡ ፮፡ ፩ ቀ
፳ ራሱን፡ ከሞት፡ እንደ፡ አዳነ፡ ብዙ፡
ኃጢአቱንም፡ እንዳስተሠረየ፡
ይወቅ። የጌታችን፡ ወንድም፡
የሐዋርያው፡ የያዕቆብ፡ መል
እክት፡ ተፈጸመች ለእግዚአ
ብሔር፡ ምስጋና፡ ይግባውና
የያዕቆብ፡ ወንድም፡ የይሁዳ፡ መ
ልክት ። ምዕራፍ፡ ፩ ።
የያዕቆብ፡ ወንድም፡ ይሁዳ፡ የተንሣኢ፡ ሙ

ቃኘ፡ነገር፡እንደ፡ጸፈሳቸው፡ሕገ እግዚአብሔርን፡
የዘነጉ፡ሰዎች፡ስለ፡ተቀሳቀሱባቸው፡ጥፋትእንደደ
ገኛቸው፡ሲሉ፡የጻብፃው ያገኘ፡ጥፋት፡እያሳሰ
በ፡እንደ፡ጸፈሳቸው……

፩ ከያዕቆብ፡ወንድም፡ከኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ባርያ፡ከይሁዳ፡የተላከች፡መልክት፡እግዚአብሔር አብን፡ለሚወዱ፡በኢየሱስ፡ክርስቶስም፡ስም፡ለተጠሩ፡ሰዎች፡ትድረስ፡ማቴ፡፲፫፡፶፭።

፪ ሰላም፡ለናንተ፡ይሁን፡ፍቅርና፡ይቀርታም፡በመካከላችሁ

፫ ይብዛ። ወንድሞቼ፡ስለ፡ሁላችን፡ሕይወት፡እጽፍላችሁ፡ዘንድ፡እጅግ፡ቸኵልሁ፡ብዙ፡እጽፍላችሁ፡ተግቼ፡ነበርና፡ለቅዱሳን፡ስለ፡ተሰጠች፡ሃይማኖት፡ትጋደሉ፡ዘንድ፡እማልዳችኋለሁ። ፩ጢሞ፡፩፡፲፰።

፬ ቀድሞ፡ለዚህ፡ፍርድ፡የተጻፉ በደለኞች፡ሰዎች፡ተቀሳቅሰውባችኋልና፡የእግዚአብሔርን፡ጸጋ፡በዝሙታቸው፡የለወጡ፡እሱ፡ብቻ፡ንጉሥ፡የሚሆን ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ይክዱታል፡

፭ ቲቶ፡፩፡፲፮። እንድ፡ጊዜ፡ኢየሱስ፡ወገኖቹን፡ከግብፅ፡ሰዎች፡እንደ፡አዳነ፡በሁለተኛው፡ግን ያላመኑትን፡እንዳጠፋቸው፡ታውቃላችሁ። ዘኍ፡፲፬፡፴፯፡፩ቆሮ

፮ ፲፡፭። ባሕርያቸውን፡ያልጠበቁ፡ሥራቸውንም፡የተዉ፡መላእክትንም፡በፍርድ፡በታ፡ለምራቸው፡ራሳቸውን፡ገዥ፡ለሌለ ዱረጉ፡እስከ፡ታላቂቱ፡ቀን፡ድረስ፡ተጋዙ። ሐ፡፰፡፵፬።

፯ ሰዶምና፡ገሞራ፡ከሳቸው፡ጋራ በሳቸውም፡ምስሌ፡የሴሰኑ፡ዝሙትን፡በመውደድ፡የተከሏቸው፡አገሮችንም፡የዘላለም፡እሳት፡ባለበት፡በፍርድ፡በታ፡እኖራቸው፡ቀጣታቸውንም፡ተቀበሉ። ዘፍ፡፲፱፡፳፬።

፰ በሕልማቸው፡ሥጋቸውን፡የሚያረክሱ፡ጌትታቸውንም፡የሚክዱ፡ጌትነቱንም፡የሚነቅፉ፡ሰዎች፡እንደዚሁም፡ናቸው።

፱ የመላእክት፡አለቃ፡ሚካኤል ስለ፡ሙሴ፡ሥጋ፡ሰይጣንን፡በተነጋገረው፡ጊዜ፡የስድብ፡ቃል ይናገር፡ዘንድ፡አልደፈረም፡እግዚአብሔር፡ይጣላህ፡አለው እንጂ። ዳን፡፲፪፡፩ዘካ፡፫፡፪።

፲ የሚሳደቡ፡እኢሁ፡ግን፡የሚያውቁት፡ጌትነቱን፡ይበድላሉ፡የሥጋን፡እሳብ፡ግን፡እንደ፡እንስሳ፡ያውቃሉ፡በዚያውም፡ይ

፲፩ ጠፋሉ። ፩ጴ፡፪፡፲፪። ወዮላቸው፡በቃየል፡ምንገድ፡ሔደዋልና፡በበለዓም፡የስሕተት፡ዋጋ፡ተናደዱ። በቆሬም፡ክሱ፡ጋራ፡በነበሩ፡ሰዎች፡ክህደት፡ተደዘው፡ጠፉ፡ዘፍ፡፬፡፰፡ራእ፡፪፡፲፬

ዘኍ፡ ፲፮፡ ፩፡ ፴፩።

፲፪ እሊህም፡ የሚወድዋችሁ፡ በፍ
ቅር፡ ሊያስቷችሁ፡ ነው፡ ኃጢአ
ት፡ ለመሥራት፡ ደፋሮች፡ ናቸው
በፈቃዳቸውም፡ ይሔዳሉ፡ ራሳ
ቸውንም፡ ያለመፍራት፡ ያሰማ
ራሉ፡ በነፋስ፡ እንደምትበተን፡
ግዛናም፡ እንደሌለባት፡ ደመና፡ ና
ቸው፡ ፍሬ፡ ሳይኖራቸው፡ ደርቀ
ው፡ ተነቃቅለው፡ እንደ፡ ወደቁ።

፲፫ እንጨቶች፡ ናቸው። እንደሚ
ነዋ፡ እንደ፡ ባሕር፡ ሞገድ፡ ኃጢአ
ታቸውን፡ የሚያነሣሡ፡ ናቸው
ብርሃን፡ እንደ፡ ሌላቸው፡ ከዋክ
ብት፡ ናቸው፡ ለዘላለም፡ ለሚሆ
ን፡ ፅኑ፡ ጨለማ፡ ፍርድ፡ ይጠብቃ
ቸዋል። ኢሳ፡ ፶፯፡ ፳። ከአዳም፡

፲፬ ሰባተኛ፡ የሚሆን፡ ሄኖክ፡ በነሱ
ትንቢት፡ እንደ፡ ተናገረ፡ እነሆ፡ እ
ግዚአብሔር፡ ፍርድን፡ ያደርግ፡
ዘንድ፡ ብዙ፡ ከሚሆኑ፡ ቅዱሳን
መላእክት፡ ጋራ፡ ይመጣል፡ ለሁ
ሉም፡ እንደ፡ ሥራው፡ ፍዳውን፡
ይሰጠዋል፡ ብሏል። ዘፍ፡ ፭፡ ፳፩፡

፲፭ የበደሉ፡ ኃጥአንን፡ ሁሉ፡ ስለ፡ ሠ
ሩት፡ ብዙ፡ ኃጢአታቸው፡ በሱ
ም፡ ላይ፡ የማይገባ፡ ነገርን፡ ስለ፡
ተናገሩ፡ ይዘልፋቸዋል፡ ኃጢ
አተኞች፡ ከዲተኞች፡ ናቸውና።

፲፮ ማቴ፡ ፳፭፡ ፴፩። የሚያንጐራጕ
ሩ፡ እሊህ፡ ናቸው፡ ተስፋ፡ ስለሌ
ላቸው፡ ልቡናቸው፡ በወደደ
ው፡ የሚሔዱ፡ ናቸው፡ አፋቸ
ው፡ ትዕቢትን፡ ይናገራል፡ ሰው
ን፡ ያበላልጣሉ፡ ለሰው፡ ፊትም
ያደላሉ፡ ይህ፡ የሚሠሩት፡ ሥ
ራ፡ ሁሉ፡ ጥቅም፡ ያገኙ፡ መስሏ

፲፯ ቸው፡ ነው። ወንድሞቻችን፡ እ
ናንተ፡ ግን፡ የጌታችን፡ የኢየሱስ
ክርስቶስ፡ ሐዋርያት፡ የነገሯች

፲፰ ሁን፡ አስቡ። በኋላ፡ ዘመን፡ ሰ
ውን፡ ለማሳት፡ ልቡናቸው፡ የ
ወደደውን፡ የሚያስተምሩ፡ በ
ኃጢአታቸውም፡ የሚያስቱ
ሰዎች፡ እንዲመጡ፡ ነግረዋቸዋ
ልና። ፩፡ ጢሞ፡ ፬፡ ፩፡ ፪፡ ጴጥ፡ ፫፡ ፫።

፲፱ በስሕተታቸው፡ የሚስቡ፡ ልባቸ
ው፡ በነደደው፡ ነገር፡ የሚያስቱ
እሊህ፡ ናቸው፡ መንፈስ፡ ቅዱ
ስ፡ በሳቸው፡ ላይ፡ የለም። ፩ቆሮ

፳ ፪፡ ፲፬። ወንድሞቻችን፡ እናን
ተ፡ ግን፡ በከበረች፡ ሃይማኖታ
ችሁ፡ ራሳችሁን፡ አፅኑ፡ በመንፈ
ስ፡ ቅዱስም፡ ጸልዩ። ቈላ፡ ፪፡ ፯፡ ፩

፳፩ ተሰ፡ ፭፡ ፲፩። በእግዚአብሔር፡ ፍቅ
ርም፡ ተጠበቁ፡ የዘላለም፡ ሕይ
ወት፡ ያለባት፡ የጌታችን፡ የኢየ
ሱስ፡ ክርስቶስን፡ ምሕረት፡ ተስፋ

፳፪ አድርጉት። ስለ፡ ኃጢአቱ፡ የም
ትዘልፉት፡ የምትመረምሩት

፳፫ ም፡ አለና፡ ከገሃነም፡ እሳት፡ አድ
ናችሁ፡ የምታወጡት፡ ፈርቶን

ለሐ፡ግብቶ፡የሚድኚም፡ለሰ፡
የቀደመውን፡ኃጢአታቸውን፡
ጠላቶው፡የረከሰች፡የዝሙ-
ታቸውን፡ልብስ፡የተዉ፡ለሉ፣
ያዕ፡፭፡፲፱፡፳፡ራእ፡፫፡፬ ።

፳፬ መድኃኒታችን፡እግዚአብሔ
ርም፡ያለ፡ኃጢአት፡ይጠብቃ
ችሁ፡ዘንድ፡ንጹሐን፡ሁናችሁ
ም፡በጌትነቱ፡ፊት፡በደስታ፡ያ
ቆማችሁ፡ዘንድ፡ይቻለዋል፨፩
ተሰ፭፡፳፫፡ፊል፡፩፡፲፨

፳፭ በጌታችን፡በመድኃኒታችን፡በ
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ሥልጣን፡
ለርሱ፡ምስጋና፡ይሁን፨
ጌትነትም፡ኃይልና፡ሥልጣን፥
ም። ዓለም፡ከተፈጠረ፡ጀምሮ፡
ዛሬም፡ዘወትርም፡እስከ፡አሚ
መጣው፡ሁሉ፨ አሜን፨

የያዕቆብ፡ወንድም፡የይሁዳ፡
መልክት፡ተፈጸመች፨ሮሜ
፲፮፡፳፯፡፩ጢሞ፡፩፡፲፯፨ ፨
ለእግዚአብሔር፡ምስጋና፡ይ
ግባው፨ ፨ ፨ ፨ ፨

ራእዩ፡ለዮሐንስ፨

የመዲናይቱ፡የቍስጥንጥንያ፣
ኤጲስ፡ቆጶስ፡ዮሐንስ፡አፈወርቅ
ተሰደ፡የነበረ፡ጊዜ፡ያገኘው ።

ምዕራፍ፡፩ ።

የቍ ስጥንጥንያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዮሐንስ፡
አፈ፡ወርቅ፣ ፍጥሞ፡በምትባለው፡ደሴ
ት፡ተሰዶ፡ሳለ፤ዮሐንስ፡ወንጌላዊ፡ያየው፡
የራዕይ፡መጽሐፍ፡ለማኸቶ፡እንደ፡ጻፈው፤ራ
እዩም፡የተገለጸለት፡እሑድ፡ቀን፡እንደ፡ሆነ–

፩ ዮሐንስ፡ወንጌላዊ፡ያየው፡ራ
እይ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እንደ፡
አየው፡መጠን፡ፈጥኖ፡ይሆን፡ዘ
ንድ፡ያለውን፡ከዚያም፡በኋላ
የሚመጣውን፡ለባሮቹ፡ይገ
ልጥላቸው፡ዘንድ፡እግዚአብ
ሔር፡የገለጠለት፨ቍ፲፱፡ምዕ፳

፪ ፪፡፮፡፮ ፨በመልአኩ፡እጅ፡ወደ
ባርያው፡ወደ፡ዮሐንስ፡የላከው-
ስለ፡እግዚአብሔር፡ቃልና፡ስለ
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ምስክር፡ያ
የው፡ሁሉ፡ላይ፡ምስክር፡የሆ
ነ፡ ቍ፱፡ምዕ፡፮፡፱ ፨

፫ የሚያነበው፡የትንቢቱም
ቃል፡የሚሰማ፡በውስጡ፡የተ
ጻፈውንም፡የሚጠብቅ፡የተ
መሰገነ፡ነው፡ዘመኑ፡ቀርብ፡ነ
ውና፨ምዕ፳፪፡፯፡ምዕ፳፪፡፲፨

፬ ከዮሐንስ፡በእስያ፡ላሉ፡ለሰባቱ
አብያተ፡ክርስቲያናት፡ተጻፈ
ቀድሞ፡ከነበረው፡እንግዲህም

ከሚኖረው፡ ወደዚህ፡ ዓለም፡
ከሚመጣው፡ በኢየሱስ፡ ክርስ
ቶስ፡ በዙፋኑ፡ ፊት፡ ካለው፡
ፍጹም፡ መንፈስም፡ ሞገስና
ሰላም፡ ለናንተ፡ ይሁን፤ ዘፀ፡ ፫፥፲፬
፲፭፡ ዕብ፡ ፲፫፡ ፰፡ ም፡ ፫ ፩፡ ኢሳ፡ ፲፩
፭ ፪፤ የታመነ፡ ምስክር፡ በኵር፡
በመሆኑም፡ ከሙታን፡ ቀድሞ
የተነሣ፡ እሱ፡ ነው፡ የምድር፡ ነ
ገሥታትንም፡ የሚገዛቸው።
እናንተንም፡ የወደዳቸው፡ ከኃ
ጢአታችሁም፡ በደሙ፡ ያነፃች
ሁ፡ እሱ፡ ነው፤ ምሳ፡ ፫፡ ፲፬፡ ዮሐ፡ ፲
፰፡ ፴፯፤ ቆላ፡ ፩ ፲፰፤ ም፡
፲፱፡ ፲፮፤ ም፡ ፪፡ ፲፬፤ ያዕ፡ ፱፡ ፲፬፦
፮ አባቱ፡ እግዚአብሔር በሚመሰ
ገንበት፡ መንግሥት፡ ካህናት
አደረጋቸሁ፡ ምስጋና፡ ኃይ
ል፡ ለዘላለሙ፡ ለርሱ፡ ይሁን፡ አ
ሜን፤ ም፡ ፭፡ ፲፩፡ ፳፡ ፬፡ ፭፡ ፱፡ ዘፀ
፯ ፲፱፡ ፮፡ ፮፦ እነሆ፡ እርሱ፡ በደመና
ከሰማይ፡ ይመጣል፡ ዓይን፡ ሁሉ
ታየዋለች፡ የወጉት፡ እነዚያ
ም፡ ያዩታል፡ የምድር፡ አሕዛ
ብ፡ ሁሉ፡ ስለ፡ እርሱ፡ ያለቅሳሉ
አዎን፡ እውነት፡ ነው፡ ዘካ፡ ፲፪፡
፰ ፲፡ ዮሐ፡ ፲፱፡ ፴፯፦ ወደዚህ፡ ዓለ
ም፡ መጥቶ፡ የነበረ፡ እንግዲህ፣
የሚመጣ፡ ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እ
ግዚአብሔር፡ ቀድሞ፡ የነበርሁ
እንግዲህም፡ የምኖር፡ እኔ፡ ነኝ

ይላቸዋልና፡ ም፡ ፳፪፡ ፲፫፡ ኢሳ
፵፩፡ ፬፡ ፵፬፡ ፮ና ፵፰፡ ፲፪፡ ፲፬፦
፱ ስለ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ መታገ
ሥ፡ በታገሣችሁት፡ መከራ፡ ተ
ካፋያችሁ፡ በመታገሣችሁም
ወንድማችሁ፡ የምሆን፡ እኔ፡ ዮ
ሐንስ፡ የእግዚአብሔርን፡ ቃል
ስለ፡ መናገርና፡ ስለ ኢየሱስ፡ ስለ
መመስከር፡ ፍጥሞ፡ በምትባ
ል፡ ደሴት፡ ሳለሁ፤ ሮሜ፡ ፰፡ ፲፯፦
፲ እሑድ፡ በሚባል፡ ቀን፡ መንፈስ
በላዬ፡ ሳይ፡ ወጣ፡ እንደ፡ ነጋሪት
ድምፅ፡ ያለ፡ ታላቅ፡ ድምፅ፡ ከ
ወደ፡ ኋላዬ፡ ሰማሁ፤ ቍ፡ ፲፭፦
፲፩ እንዲህ፡ የምታየውን፡ የም
ትሰማውንም፡ በመጣፍ፡ ጣፍ
በእስያ፡ ሳሉ፡ ለሰብአቱ፡ አብያ
ተ፡ ክርስቲያናትም፡ ላክ፡ ለኤ
ቺ፡ የኤፌሶንና፡ የሰሚርኔስ፡ የ
ጴርጋሞንና፡ የትያጥሮን፡ የሰ
ርዴስና፡ የፊልድልፍያ፡ የሎ
ዶቅያም፡ ናቸውም፡ ም፡ ፳፪፡ ፲፫፤
፲፪ ያነንም፡ ከኔ፡ ጋራ፡ የሚናገረ
ውን፡ ቃል፡ ለይ፡ ዘንድ፡ ወደ፡ ኋላ
ዬ፡ ተመለስሁ፡ በተመለስሁ፡
ጊዜ፡ ፯ት፡ የወርቅ፡ መቅረዞች
፲፫ አየሁ፤ በ፯ቱም፡ መቅረዞች
መካከል፡ ወልደ፡ እጓለ፡ እመሕ
ያውን፡ የሚመስል፡ ተቀምጧ
ል፡ ጸዴር፡ የሚባል፡ ልብስ፡ ለብ
ሷል፡ በወገቡም፡ የወርቅ፡ መታ

ጠቂያ፡ ታሞቋልና፤ ምዕ፡ ፩፡ ያ
፲፬ ኝ፡ ፯፡ ፲፫፤ ራስ፡ ቀሉ፡ ነጭ፡ ነው፡
ፀጕሩም፡ እንደ፡ ነጭ፡ ሐር፡ ነው፡
ዓይኖቹም፡ እንደ፡ እሳት፡ ነበል
ባል፡ ናቸው፤ ዳን፡ ፯፡ ፱፡ ምዕ፡ ፲፱፡ ፲
፲፭ ፪፤ እግሮቹም፡ በእሳት፡ እንደ
አጋሉት፡ እንደ፡ ሊባኖስ፡ ብረት
ናቸው፡ ድምፁም፡ እንደ፡ ፏፏቴ
ውሀ፡ ድምፅ፡ ነው፤ ምዕ፡ ፬፡ ፲፰፤
፲፮ በቀኝ፡ እጁም፡ ሰባት፡ ኮከብ፡ ይ
ዟል፡ ካፉም፡ ሁለት፡ ልሳን፡ ያለ
ው፡ የተሳለ፡ ሰይፍ፡ ይወጣ፡ ነበ
ር፡ ፊቱም፡ በኃይል፡ ሲያበራ፡ እ
ንደሚታይ፡ ፀሐይ፡ ነው፤ ቍ፡ ፳፡
ምዕ፡ ፪፡ ፩፡ ምዕ፡ ፪፡ ፲፪፡ ፲፮፡ ና፡ ፲፱፡ ፲፭
፲፯ ባየሁትም፡ ጊዜ፡ ከእግሩ፡ በታች
ወደቅሁ፡ እንደ፡ ሞተም፡ ሆንሁ፡
እርሱ፡ ግን፡ በቀኝ፡ እጁ፡ ያዘኝ፡
ሕያው፡ የምሆን፡ ቀድሞ፡ የነበ
ርሁ፡ እንግዲህ፡ የምኖር፡ እ
ኔ፡ ነኝ፡ አትፍራ፡ አለኝ፤ ፵፬፡ ፮
፲፰ እኔ፡ ግን፡ እንዴ፡ ሞተ፡ ሆንሁ፡ እ
ነሆ፡ እኔ፡ ለዘላለም፡ ሕያው፡ ነኝ
የሞትና፡ የሲኦልም፡ መክፈቻ
፲፱ ከኔ፡ ዘንድ፡ አለ፤ ሮሜ፡ ፮፡ ፱። እን
ግዲህ፡ የምታየውን፡ ቀድሞም
የነበረውን፡ ከዚያም፡ በኋላ፡ ይ
ሆን፡ ዘንድ፡ ያለውን፡ ጻፍ፡ ሐ
፳ ለኛቱም፡ ፲፬፡ ፲፫፤ በቀኝ፡ እጄ፡ ያ
የኸቸው፡ የሰባቱ፡ ከዋክብና፡ የሰ
ባቱ፡ ወርቅ፡ መቅረዝ፡ ትርጓሜ
ያቸው፡ ይህ፡ ነው፡ ሰባቱ፡ ከዋክ
ብት፡ በሰባቱ፡ አብያተ፡ ክርስቲ
ያት፡ የተሾሙ፡ አለቆች፡ ናቸው፡
እሊያም፡ ሰባቱ፡ መቅረዞች፡ ሰ
ባቱ፡ አብያተ፡ ክርስቲያን፡ ናቸ
ው፤ ሚልክ፡ ፪፡ ፯።

ምዕራፍ፡ ፪።

የኤፌሶኑ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ አለቃ፡ በሥራ
ድካሙ፡ ንና፡ ትዕግሥቱ፡ አይቶ፡ ካመሰገነው
በኋላ፡ የቀደመ፡ ሥራህን፡ ለምን፡ ተውኸብ
ሎ፡ እንዲ፡ ወቀሰው፡ ጥምቀት፡ በ፫ ዘመን፡ ይገባል
የሚሉ፡ የኒቆላውያንን፡ ትምርት፡ እንዲ፡ ነቀፈው።

፩ ለኤፌሶን፡ ቤተ፡ ክርስያን፡ አ
ለቃ፡ ጻፍለት፡ የሚገዛ፡ ሰባቱን
ም፡ ኮከብ፡ በቀኝ፡ እጁ፡ የያዘ፡
በሰባቱም፡ የወርቅ፡ መቅረዝ
ች፡ መካከል፡ የሚሔድ፡ እሱ፡
እንዲህ፡ አለ፤ ምዕ፡ ፩፡ ፲፫፡ ፲፮
፪ ሥራህንና፡ ድካምህን፡ መታገ
ሥህንም፡ አየሁ፡ ሰይሆኑ፡ በራ
ሳቸው፡ ሐዋርያት፡ ነን፡ የሚሉ
ክፉዎችን፡ ተታግሠቸው፡ ዘንድ
እንዳይቻልህ፡ አወቅሁ፡ ሐሰተ
ኞች፡ ሁነው፡ አገኘተቸዋልና
፫ ፩ዮሐ፡ ፬፡ ፩፤ ከለ፡ ስሜም፡ ስቀ
ሰለኸ፡ መከራውን፡ ታግሠህ፡
ተቀብለሃልና፡ ገላ፡ ፮፡ ፱፡ ዕብ፡ ፲፪፡
፬ ፫፡ ፲፪፡ ፲፭፤ ነገር፡ ግን፡ የምነቅ
ፍብህ፡ አለ፡ የቀደመ፡ ፍቅርህ
ን፡ ትተሃልና፤ ምዕ፡ ፫፡ ፫፡ ፲፱።
፭ እስኪ፡ አስተውል፡ ስለምን፡ ተ

ወዶቃለህ፡እንጫዴህ፡ተመለ
ስ፡ያለዚያ፡ግን፡ንስሐ፡ካልገ
ባሕ፡የቀዴመ፡ሥራህንም፡ካል
ሠራህ፡መጥቼ፡መብራትህን፡
ከመቀረዙ፡አጠፋታለሁ፨
፯ ነገር፡ግን፡ይህ፡አለህ፡እኔ፡እን
ዴ፡ጠላሁ፡የኒቆላውያንን፡
ሥራ፡ጠልተሃልና፡ጆሮ፡ያለ
ው፡ይህን፡ይስማቀ፦፲፫፡መዝ
፺፬፡፱፡፹፭፨መንፈስ፡ቅዱስ፡
ለአብያተ፡ክርስቲያናት፡ም
ን፡አለ፡ድል፡ለነሣ፡በአምላክ፡
ገነት፡ውስጥ፡ካለው፡ከሕይወ
ት፡ዕፀ፡ፍሬ፡ይበላ፡ዘንድ፡እሰ
ጠዋለሁ፨ቀ፦፲፩፡፲፯፡፳፯፡ም፫
፭፲፬፡፳፩፡ም፡፳፬፡፬፡ዘፍ፬፡፱
፰ ለሰሚርስአስ፡ቤተ፡ክርስቲ
ያን፡አለቃ፡ጻፍለት፡ቀዳሞ፡
የነበረ፡ኋላም፡የሚኖር፡ሙቶ
የተነሣ፡እሱ፡እንዲህ፡አለ፨
ም፡፩፡፲፯፡ና፳፬፡፲፫፨
፱ መከራህንና፡መቸገርህን፡አ
ውቃለሁ፡ነገር፡ግን፡አንተ፡ባ
ለጸጋ፡ነህ፡የሰይጣን፡ማኅበር
ናቸው፡እንጂ፡አይሁድ፡ምእ
መናን፡ነን፡የሚሉ፡ሰዎችን፡
መንቀፍህን፡አውቃለሁ፨ያዕ
